# ሀዲስ



ከበአሉ ግርማ

# ሀ ዲ ስ

ከበአሉ ግርማ

መብት በሕግ የተጠበቀ ነው ::
ALL RIGHTS RESERVED

የመጀመሪያ ዕትም 1975 ዓ.ም
እንደገና በ2008 ዓ.ም ታተመ

2010 በማንኩሳ ማተምያ ቤት ታተመ

## ምዕራፍ ፩

# ክፍል ፩

በተማሪዎች ረብሻ ምክንያት አመቱን ሙሉ በባለስልጣኖች ትእዛዝ ሲዘጋና ሲከፈት የቆየው የቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ዩኒቨርሲቲ ለክረምት ወራት ከተዘጋ ቆይቷል ።

ሀዲስ ሳህሌ የባህር ዛፍ ፍሬ አቀጣጥሎ ባጋለው ካውያ ሸክ አድርጎ የተኮሰውን ካኪ ልብሱን ለብሶ የእናቱን ፣ የወይዘሮ እልፍነሽ ትርፌን የቡሄ ዳቦ ከሻይ ጋር ከገመጠ በሁዋላ ለመሄድ ተነሳ ። ተስፋ የጣለበት ቀጠሮ ነበረው ።

«ስሞኑን በማለዳ እየተነሳህ ስራ እንዳለው ሰው የምትሮጠው ወዴት ነው ልጄ? ትምህርት ቤት እንደሁ ተዘግቷል ። አርፈህ ብትቀመጥ ምናለበት?» አሉት ባይናቸው እየሳሱለት ።

«ለክረምት ስራ እየፈለኩ ነው ። ያለ ስራ ተቀምጬ ምን አደርጋለሁ?» ብሎ ዋሻቸው ። ላንድ አመት ወደ ዩኒቨርሲቲ እንደማይመለስ ልቡ ያውቅ ነበር ።

«ለስራ ምን አስቸኩለህ ? ትምህርትህን ስትጨርስ ትደርስበታለህ» አሉት በደከመ ድምፅ ።

እናቱን ትኩር ብሎ ላንዳፍታ ተመለከታቸው ። ሰውነታቸው አልቆአል ። አጥንታቸው ብቻ ነበር የቀረው ። ህይወት አይታይባቸውም ። እርጅናውም ብሶባቸዋል ። እና ፣ ቤቱም ይበርድ ነበር ። ግድግዳዎቹም ፣ የቤት እቃዎቹም ፣ ምድጃውም ጭምር የበሰበሰ የችግር ጥርሳቸውን አግጠው አሳዩት ። ቶሎ ወጥቶ ለመሄድ ፈለገ ።

«ኢስቲ ቆይ» አሉትና ከመቀነታቸው ላይ አንድ ብር ፈተው ሰጡት ።

«ምን ያደርግልኛል እማዬ ፣ ይልቅ ለችግርሽ ይሆንሻል» ብሎ ሊመልስላቸው ሲል ፡-

«ያዘው ። ወንድ ልጅ ባዶ ኪሱን ከቤት አይወጣም» አሉት ።

አይኖቹ እንባ አቀረሩ ። የተጨማደዱትን ጉንጮቻቸውን ስሞ ወጣ ። ባይናቸው ይከተሉት ነበር—በር ላይ ቆመው ። በየመንደሩ ቡሄ ፣ እያሉ ከሚጨፍሩት ልጆች ጋር ልቡ አልጨፈረም ። ይልቅ እንደ ድንጋይ ይከብደው ነበር—ወጣት ልቡ ።

ሰባት ቁጥር አውቶቡስ ሊያመልጠው ሲል በረጅም ቅልጥሙ ሮጥ ሮጥ ብሎ ደረሰበት ። አውቶቡሱ ውስጥ መቀመጫ ቀርቶ መቆሚያ ቦታም አልነበረም ። እንደ እሱ ሮጠው አውቶቡሱ ላይ ለመሳፈር ያል

ቻሉት እርጊቶችና ሽማግሌዎች አሳዘኑት ። የደከሙት አይኖቻቸው ብቻ ነበሩ ከአውቶቡሱ ጋር የሚሮጡት . . . ፒያሳ ላይ ወረደ ። አሪዳ ጭጋግ ለብሳለች ። ከሩቅ የሚታየው የእንጦጦ ጋራ የጥቁር ጉም ክምር መስሎአል ። ከባድ ዝናብ ካሁን አሁን መጣሁ መጣሁ እያለ አዲስ አበባን ያስፈራራል ። ሰውም ዝናቡን ፈርቶ እንደ ማለዳ የመንደር ውሻ ኩስ ኩስ እያለ ቶሎ ቶሎ ይሄዳል ። በሀይል የሚነፍሰው ነፋስ የሴቶችን ቀሚስ እየገለበ ፣ ፀጉራቸውን እየበተነና የአንዳንድ ሰዎችን ባርኔጣ እየወሰደ ያስቸግራል ። አንድ ጠና ያሉ ሰው ባርኔጣቸውን ሲያሳድዱ አሳፌ መኪና ሊበላቸው ነበር ። የመኪናው ጎማዎች አስፋልቱን ነክሰው ሲጮሁ ሀዲስ አይኖቹን ጨፈነ ። ሰውዬው ለትንሽ ተረፉ ። ጥቁር ቆብ መስሎ ሰፋ ካለው ግንባሩ ላይ የሚደፋው ጠጉሩ ቆሞ ነበር—ሀዲስ ። አንዳንድ ሴቶች ካለፉት ,በሁዋላ መለስ ብለው ይመለከቱታል ። ሴቶች ቀና ወይም መለስ ብለው ለምን እንደሚያዩት ይገርመዋል ። እና ፣ የተከዋሉ የሚመስሉትን ትላልቅ አይኖቹን ሰበር ያደርጋል ።

ወደ ሳጋር የሚወስደውን አውቶቡስ ጠብቆ ተሳፈረ ። አንዱ እጁ በአውቶቡሱ መዝጊያ ተይዞ ሲቀር ነበር ። ሰው እንደ ሰርዲን ታጭቆ አል ። መፈናፈኛ ቦታ አልነበረም ። ከፊት ለፊቱ ፀጉርዋ ወርዶ ትከሻዋ ላይ የተኛ አንድ ቀይ ውብ ልጅ ቆማ ነበር ። አውቶቡሱ ፍሬን ሲይዝ እንዳትወድቅ ብላ ወገቡን ያዘችው ። ሰውነቱ ሞቅ አለው ። ላቡ በግንባሩ ላይ ተንቸረፈፈ ። ቀና ብላ ፈገግታ አሳየችው ። አፀፋውን መለሰላት ። የተርከፈከፈችው ሽቶ መአዛ ሳበው ። ከቴሌኮሙኒኬሽን ዋና መስሪያ ቤት አጠገብ ደርሶ ከወረደ በሁዋላ በአይኑ ቢፈልጋት አጣት ። ስንቱ በመንገድ ይተላለፋል እያለ መንገዱን ሊቀጥል ሲል አንድ ጠብደል አፍሮ መጥቶ ፣ «ኢንካ ። ተፀዳዳበት» ብሎት ወይን ጠጅ ቀለም ያለው ሶፍት ሰጠው። በደመ—ነፍሱ የሁዋላ ኪሱን ዳበሰ ። ከቤቱ ይዞት የወጣው የራሱ ሶፍት ነበር ። መለስ ሲል ኪስ አውላቂው ሌባ ውልብ ብሎ ጠፍቶአል ። በራሱ ስቆ መንገዱን ቀጠለ ። ደግነቱ ሌላ ነገር አልጠፋውም። እናቱ የሰጡት ብር ደረት ኪሱ ውስጥ ነበረች ። መጣሁ ፣ ደረስኩ እያለ የሚያስፈራራውን ዝናብ ለመቅደም በረጅም ቅልጥሞቹ መንገዱን አፈስ አፈስ ፣ ያደርገው ጀመር ።

ልክ በቀጠሮው ሰአት በመድረሱ ደስ ብሎት ረጅም ቅልጥሙን አመሰገነ ። በስንት ደጅ ጥናት ያገኘው ቀጠሮ ነበር ።

«ቀጠሮ አለህ?» ብላ ጠየቀችው የቢሮው ፀሀፊ ።

ሽቶዋ ያውዳል ። ጡቶችዋ ጠላት ላይ የተደገኑ ሮኬቶች ይመስላሉ ። «ኮንዶሊቴ» ጥቁር ሹራብ ለብሳለች ። የልብ ቅርፅ ያለው ያንገት ጌጥዋ ከጡቶችዋ መሀል ተሸጉጦ ይታያል ። ቶሎ ብሎ አይኑን ከጡቶችዋ ላይ ነቀለ ። ፈገግ አለች ። ትኩስ የተሸለቀቀ በቆሎ እሸት የሚመስሉትን ጥርሶቹን አሳያትና ፣ «አዎን ፣ ቀጠሮ አለኝ» አላት ።

«ጠብቅ ይመጣሉ» አለችው ፣ የእጅ ቦርሳዋን እየከፈተች ።

ረጃጅም እግሮችዋ በጠረጴዛው ስር ይታያሉ ። ቀይ ቀለም የተቀቡት አውራ ጣቶችዋ የሚያኾቆቡበት መስለው ። እንደገና አይን ለአይን ተጋው።

ረዳጅም እጆቹን የሚያገባበት ቦታ ጠፋው ። ከት ብላ ሳቀች ። ምን እንዳሳቃት አልገባውም ። ጠይም ፊቱ አሸቦ መሰለ ። ወዲያውኑ ቀጠሮ የሰጠው ባለስልጣን መጣ ። ቁመናው አጭር ሆኖ ቦርጫም ነበር ።

«ሌሎች ባለ ጉዳዮች ሳይመጡ ቶሎ ግባ» አለችው ፀሀፊዋ ።

የቢሮውን በር ቀስ ብሎ ከፍቶ ገባ ። ሰውዬው ቀደም ብሎ ከትልቁ ጠረጴዛ ሁዋላ ትልቅ ወንበር ላይ ተኮፍሶአል ። ያ ቅድም ሲገባ ያየው አጭር ሰው አሁን ግዙፍ መስሎ ታየው ።

«ምን ኖሮአል?» — እንደ አንበሳ አጉዋራበት ።

«ባለፈው ሳምንት ለዛሬ ቀጠሮ ሰጥተውኝ ነበር» አለው ፣ እጆቹን ወደ ሁዋላ አድርጎ ፣ ሳምንቱን ሙሉ ተስፋ የጣለበት ቀጠሮ ነበር ።

«እኮ ፣ ጉዳይህ ምንድር ነው?»
«ስራ ፈልጌ ነበር ።»
«ማን ነው የላከህ?»
«ማንም ። እኔው ነኝ የመጣሁት ።»
«የማ ልጅ ነህ?»

የማን ልጅ ነኝ ይበል? መምሬ ሳህሌ—እምላካቸው ነፍሳቸውን ይማረውና—ማንም አልነበሩም። ማንም የማያውቃቸው ተራ ቄስ ነበሩ ። ስራ ሊያስገኝ የሚችል የዘር ሀረግ ከየት አምጥቶ ይምዘዝ ! ኢትዮጵያዊነት ብቻውን አይበቃም ። ስራ ፈላጊ ስራ ለማግኘት ያንድ የታወቀ ሰው ልጅ ወይም ዘር መሆን ያስፈልጋል ። ስራ ለማግኘት ከመረቀት ዲግሪ የተሻለ በመወለድ የሚገኝ የላቀ ዲግሪ ኖሮአል ለካ ! ለዚህም አልታደለም ። ምን ይበል ?

«አገርህ የት ነው?»

ኢትዮጵያዊ አልመሰልም ይሆን ? ወይስ ድሀ ኢትዮጵያዊ አይመስልም? ሀገሬ የት ነው? ወይስ ድሀ ሀገር የለውም? ወይስ ኢትዮጵያ የድሆች አገር አይደለችም ይሆን ?

«የትውልድ አገርህ ማለቴ ነው ።»
«ሸዋ ነኝ ።»
«ምሩቅ ነህ ?»
«አይደለሁም ። ሁለት አመት ይቀረኛል . . .»

«ትምህርቱን ሳልጨረስ ቀርቶ ፣ ወዳጄ ፣ ዛሬ ለምሩቃንም ስራ ማግኘት ችግር ነው ። ፊደል የቆጠረውም ያልቆጠረውም ዛሬ ሁሉም የመንግስት ስራ ፈላጊ ነው ። መንግስት ሁሉንም አስተምሮና ስራ አስይዞ አይችልም ። ለተቀጠሩትም በቂ ስራ የለም ። የመንግስት መስሪያ ቤቶች በስራ ፈቶች ተጣበው ነው የሚታዩት ። አዝናለሁ ። ምሩቅ ብትሆን ኖሮ እንኳ . . .»

«ሀቁስ ። ምሩቅ አይደለሁም ። ርጉም ነኝ......»

ለርጉማን አዲሳባ ቦታ የላትም ፤ ልብ የላትም ። መቆሚያ መቀመጫ የላትም ። ጆሮ የላትም ። ኤሌክትሪክ ብርሃኑም ያፈጣል እንጂ ምንም አያሳይም ። ሰማይ ጠቀስ ፎቆችዋ ወደ ላይ ይንጠራራሉ እንጂ ወደ ታች አይመለከቱም ። የተዘረጉት አስፋልት መንገዶችዋ የትም አያደርሱም ። አዲሳባ ልብ የላትም ። እንዴት ልብ ይኖራታል? ልብዋ በወሲብ ፣ በፍቅረ ንዋይና በስልጣን ተገጥቦ አልቆአል ። ዙፋኑም ጆሮና ልብ የለውም ። ጆሮው እንደ እንጦጦ ተራራ ስምንት ሽህ ጫማ ወደ ላይ ርቆአል ። በሩን ከፍተው ካዳራሹ ሲገቡ የሚችሉት የዘር ሀረግ እየመዘዙ የእገሌ ልጅ ፣ ወይም የልጅ ልጅ ነኝ ለማለት የታደሉት ብቻ ናቸው ።

አዲስ አበባ—የምሩቅ ፃድቃን ምድራዊ ገነት ። የርጉማን ሲኦል፣ የምድራዊ ርጉማን ዋይታ በብሩካን ፍቅረ ንዋይ ፣ የስልጣን ከበሮና ዳንኪራ ፣ ሳቅና እልልታ ፣ ዘፈንና እስክስታ የተዋጣባት ፣ ብዙ የተቆለፉ መዝጊያዎች በውስጡዋ የሚገኙባት የተቆለፈች ከተማ . . .

በእድሉ ክፉኛ እያዘነ ከባለስልጣኑ ቢሮ ወጥቶ ሄደ ። በዱሮ ቄራ መንገድ ሽቅብ ወጥቶ ፤ የተረት ሰፈርን መንገድ በመያዝ ወደ አራት ኪሎ ሲያመራ አንድ ጥቁር ትልቅ ማርቸዲስ ቤንዝ መኪና በጎማው መንገዱ ላይ የተኛውን የዝናብ ውሃ አልብሶት አለፈ ። የባሰውኑ ተናደደ ። ግን መናደድ የት ሊያደርስ ! ንዴቱን ለማብረድ በሀይል ይራመድ ጀመር ።

አንድ ወር ሙሉ ስራ ፍለጋ ሲንከራተት ያልረገጠው የመንግስት መስሪያ ቤትና የግል ድርጅት የለም ። የቢሮውን በር ታቅፎ ይዞ ስንት ሰአት ሙሉ ያልጠበቀው ባለስልጣን ፣ ባይኑ ያልገረፈው ጠብደል የቢሮ ተላላኪ አልነበረም ። ንጉሱ ግቢ ደጅ ለሚጠኑትም ፣ ሰክረው አድረው ቢሮ ላልገቡትም ፣ ገባ ብለው ላጣዳፊ የግል ጉዳይ ተመልሰው ወጣ ላሉትም ፣ ወይም ተሰብስበው ማኪያቶ እየጠጡ የዶሯ ወሬ ለሚያቀልጡትም ፣ ወደ ቦሎቄ እርሻዎቻቸው ሄደው ላልተመለሱትም ባለስልጣኖች ፣ «ስብሰባ ላይ ናቸው» ወይም ፣ «ተጠርተው ወደ ግቢ ሄደዋል» በማለት ከሹራብ ስራዋ ላይ ቀና ብላ ያላመናጨቀችው የቢሮ ፀሀፊ የለችም ። «ወዴት ነው !» ያላለው ያረጀ ዘበኛ አልነበረም ።

— ክፍት የስራ ቦታ የለንም !

— ያለ ስራ መግባት ፍፁም ክልክል ነው !

አቤት ተስፋ ሲያስቆርጡ ! በጋዜጦች የሚያወጡትም የክፍት ስራ ቦታ ማስታወቂያዎችም ያንኑ ያህል ነበር ተስፋ የሚያስቆርጡት ። የሁለተኛ አመት የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ያጠናቀቀና የስድስት አመት የስራ ልምድ ያለው ወይም ቢ. ኤ. ዲግሪ ኖሮት የሶስት አመት የስራ ልምድ ያለው ፣ ወይም ኤም. ኤ. ዲግሪ ኖሮት የሁለት አመት የስራ ልምድ ያለው . . . ወ.ዘ.ተ የሚሉ ናቸው ። ስራ ላይ ላሉ ሰዎች ነው እንጂ ገና ስራ ለሚፈልጉ ስራ አጦች የታቀዱ ማስታወቂያዎች አይደሉም ። ከጊዜ በሁዋላ ነበር ማስታወቂያዎቹ ለግል ሰዎች እንደ ልብስ በልክ ተሰፍተው የሚወጡ መሆናቸውን የተረዳው ። ባንድ አጭር ወር ውስጥ ስድስት መስሪያ ቤቶች ባወጡት የማወዳደሪያ ፈተናዎች ተሳትፎአል ። አንዱንም አላለፈም ። ጎበዝ ተማሪ ከመሆኑም ሌላ ስሙ ከዩኒቨርሲቲው ዲን የክብር መዝገብ ወጥቶ አያውቅም ። የጎ ምህርት ቤት ጎዶኞቹ ባወ

ጡለት ቅፅል ስም ፣ «መፅሀፍ ትራሱ» ወይም «ፕሮፌሰር ሀዲስ» እያሉ የሚጠሩት እንዲያው በዋዛ አልነበረም ። ግን ቀላል ፣ በጣም ቀላል ነው ብሎ ያሰበውን ፈተና ማለፍ ሲያቅተው ምን ይባላል ! ፈተናውን ማለፍ ያለበት ሰው አስቀድሞ የታወቀ ስለሆነ ፣ የሚሰጠው ፈተና እንዲያው ለይስሙላ በውሸት መሆኑ ከገባው ሰንበት ብሎአል ። ጆሊ ባር ገብቶ ማኪያቶና ቀዝቃዛ ውሀ አዞ ፣ ውጭ 'ቴራሱ' ላይ ቁጭ አለ ። መጣሁ ፣ ደረስኩ ፣ እያለ ሲያስፈራራ የነበረው ዝናብ አልፎ ፣ ፀሐይ የደመናውን ብርድልብስ ገልጣ ወጥታለች ። ወፈፍ የሚያደርጋቸው ወጣት አፍሮ 'ለማኞች' ሳንቲምና ሲጃራ አምጡ እያሉ ያስቸግራሉ ። አንድ ጠብደል ለማኝ ደረቱን ገልብጦ ፍራንክ አምጡ እያለ ያስፈራራል ። ስራ የፈቱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አፍ ላፍ ገጥመው እጃቸውን እንደ ጣልያኖች አስሬ እያወናጨፉ ይከራከራሉ ። የሚያብረቀርቁ አዳዲስ ሽንጣም መኪና ዎች በነፃነት ሀውልት ዙሪያ ሽው ሽው ይላሉ ። የቀረበለትን ቀዝቃዛ ውሀ ባንድ ትንፋሽ ጨልጦ ማኪያቶውን ፉት አድርጎ ከጣጣሙ በሁዋላ— ቁጡ ትውልድ መሆናችን ምን ያስገርማል ! አለ የነፃነት ሀውልቱን እየ ተመለከተ ።

ለመጀመሪያ ጊዜ የተማሪዎች ቁጣና ምኞት ልቡ ገባ ።
ተው ስማኝ ሀገሬ
ተው ስማኝ ሀገሬ
መሬት ላራሹ !
ፋና ተሰማራ ! ፋና ተሰማራ
እንደነ ሆቺ ሚን እንደ ቼ ጉቬራ !

—ይህ ቦታ መፈንዳት አለበት ! አለ የእናቱ ስቃይና ችግር ትዝ ብሎት ። ጠዋት ሲወጣ የሰጡትን ያረጀች ብር አውጥቶ ተመለከታት ። የንጉሱ ምስል አፈጠጠበት ። ቀዶ ቢጥለው ንዴቱ በበረደለት ነበር ። እንባ ተናነቀው ። አልቅሶ በወጣለት ! ግን እንባ አይወጣውም ። የእንባው ከረ ጢት እንደ እናቱ ሰውነት እየደረቀ ሄዶአል ።—ሰው ለችግርና ለመከራ ለምን ይወለዳል ! አለ ባንድ እጁ ማኪያቶውን ፣ በሌላው እጁ ቡጢ ጨብጦ ።

ሀዲስ የእናቱን ችግር እያየ ትምህርቱን መቀጠል አልቻለም ። ሁለት አጭር አመት ። ከዚያ በሁዋላ የዲግሪውና ከዲግሪው ጋር የሚመ ጣው ክብር ፣ ደረጃና መብት ባለቤት መሆን—ቢቃ ። ግን የሚወደውን ትምህርት በግድ ማቋረጥ ነበረበት ። ሌላ ምርጫ አልነበረውም ። ድሀ ምን አማራጭ አለው ! እርጅና ከቀን ወደ ቀን እየተጫናቸው የሚሄ ዱት ድሀ እናቱ ብቻቸውን ናቸው። ከእሱ ሌላ ምርኩዝና ተስፋ የላቸውም።

አባቱ መምሬ ሳህሉ እንደሻው ከዚህ አለም በድንገት በሞት የተለዩት በህፃንነቱ ነበር ። ስላባቱ እምብዛም የሚያስታውሰው ነገር የለም ። የሚ ያስታውሰው ነገር ቢኖር ረጅም ፣ ሰይጣን ያወጣው ልታቂት የሚመስለ ውን ፀአዳ ክብላታቸውን ፣ ከትከሻቸው ላይ ዘወትር የማይለይ ጠብደል የማያነሳውን ፍትፍት የመሰለ ጋቢአቸውን ፣ ከቀይ ረጅም ፊታቸው ላይ ተንዠርጎውን የሚወርደውን ሪዛቸውንና ዝንብ ቢኖርም ባይኖርም በባዶ አየር ላይ ዘወትር የሚነሰንሱትን ረጅም ነጭ ጭራ ነበር ። አቤት ! በዚያ ሾጥ ሲያደርጉ እንደ ሳማ ሲቆጠቁጥ አይጣል ! እግዚራቸው ነፍሳ

ቸውን ይማረውና ዘወትር ግልጽው ተነስተው የሚያነበንቡት በቆዳ የተሰገጠ ፣ በግምጃ ጨርቅ የተሸለመ ፣ በብራና የተፃፈ የሙሴን ፅላት የሚያክል ዳዊታቸውን ቢሞትም አይረሳው ። ከሞቀ የናቱ ጉያ ፤ ከጣፈጠ የጠዋት እንቅልፍ በዚያ መከረኛ ጭራ መያዣ እየተጎነተለ ተቀስቅሶ ያንን ዳዊት ተሸክሞ ማውጣቱ ዘወትር ያቃዠው ነበር ። ዳዊቱን ተሳልሞ በቶሎ ወደ ሞቀች መኝታው መመለስ ቢችል ባልከፋው! ከእግራቸው ስር ተቆራምዶ በቆፈን ተይዞ እየተቆራፈደ ጎህ መቅደዱን ፣ ፀሐይ መውጣቷዋን እየናፈቀ ፣ መምሬ ሲያነበንቡ ማዳመጥ ነበረበት—ሰኞ ፣ ከፍካሬ እስከ እኮኑ ፤ ማክሰኞ ፣ ከእኮኑ እስከ ብፁእ ብእሲ ፤ ረቡዕ ፣ ከብፁእ ብእሲ እስከ ሰሎሞን መጨረሻ ድረስ ፤ ከዚያ በሁዋላ እንደገና ድጋም—ሳምንቱን ፣ ወሩን ፣ አመቱን ፣ ዝንተ አለሙን . . . ። የየእለቱን ድጋም ሳይጨርሱ እህል ማን ቀምሶ! በተለይ ሰሎሞን ላይ ሲደርሱ ፣ ምን እንደሚይዛቸው አይታወቅም ፣ ጊዜ ይፈጁ ነበር ። «ዋ ! አቡነ ተክልዬን !» ካሉ ድራሽ ያጠፉሉ ። ድጋሙ ካለቀ ከብሳታቸውን አሳምረው ቆልለው በመነሳንሳቸው ባዶውን አየር እየገረፉ ተነስተው ውልቅ ። አደባባይ ነበር የሚውሉት ። ሀዲስ ነፍስ ማወቅ ከጀመረ ወዲህ ኮሶ ካልጠጡ በስተቀር ባዘቦቱ ቀን ከአደባባይ ተለይተው ቤት የዋሉበትን ቀን አያስታውስም ። ሃያ አንድ አመት የቆየ የመሬት ሙግት ነበረባቸው ።

አባታቸው አለቃ እንደሻው ዘመነ ካህናት ይባል በነበረው በንግስት ዘውዲቱ ጊዜ በአድአ የተተከሉት አንድ ጋሻ መሬት ነበር ። ንግስት ሲሞቱ ፣ «ጰርሃት ቤተ ክርስቲያን» ያሉት እሳቸው ነበሩ ይባላል ።

አዋልደ ነገስት የሆነ አንድ የሸዋ መኳዋንንት ካባታቸው ከወረሱት መሬት ላይ መምሬ ሳህሌን ባልሆነ ምክንያት ነቀላቸው ። ከወረዳ ጀምረው እስከ ጠቅላይ ንጉስ ነገስት ፍርድ ቤት ይገባኝ እያሉ ሃያ አንድ አመት ሙሉ በተስፋ ተሙዋገቱ ። «የንጉሱ ትንፋሽ ፈርዶብኝ ይቅርብኝ ። እንደ አቡነ ተክልዬ ባንድ እግር ቆመው ነውኮ የሚፈርዱት ። ፍትሀ ከዳዊት ፣ ከሰሎሞን ተሰጥታቸዋለች» ይሉ የነበሩት ሰው ፣ ዙፋን ችሎት ቀርበው ተስፋ የጣሉበት የንጉሱ ትንፋሽ ፣ ሃያ አንድ አመት የፈጀውን ክርክር ባምስት አጭር ደቂቃዎች ውስጥ መርምሮ ሲፈርድባቸው ደንዝዘው ፣ የመጨረሻዋ ተስፋ ከልባቸው ውስጥ ተጨምቃ ወጥታ ነበር ቤት የተመለሱት። እንደ መቃዠትም እንደ እብደትም እያደረጋቸው፣ «ልጅ ባባቱ ሀጢአት ይቀጣል ? እሪታውያን ። የፍትወት መቃብር . . . ሰው ያልዘራውን ያጭዳል? በምን ሀጢአቴ ነው? የአርዮስ ግዝት ፣ የይሁዳ ርግመት ። ወይ አስተዋይ ልቡና—መርማሪ ህሊና ! እንዲህም አድርጎ የለ ! እንደ ናቡከደነፆር ልብ አውጥተው . . . አበዱ ብሎ የሚያስራቸው፣ ፊዉመቱ ብሎ የሚያከብራቸው ጠፍቶ! የፍትወት መቃብር—ጰርሃት ኢትዮጵያ» እያሉ ሰንብተው፣ አንድ ቀን ዳዊታቸውን በንዴት ሲያነበንቡ ከቆዩ በሁዋላ ዝም ብለው ቀሩ . . . ያንቀላፉ መስሎት ሀዲስም አሸለበ ። ሞቱ ተባለ ። የሞት ትርጉሙን በምን አውቆ ? ከሄዱበት ሩቅ አገር አንድ ቀን ተመልሰው ዳዊታቸውን የሚደግሙ እየመሰለው እንደ ልማዱ ግለዳ ነቅቶ ይጠብቅ ነበር — ለብዙ ጊዜ ። አልተመለሱም ። እንደ ሄዱ ቀሩ — እንደ ሁለት ወንድሞቹና እህቶቹ ። በዚህ አለም የቀረው ቤተሰብ እናቱ ብቻ ነበሩ ። እሳቸውም መዳከም ጀምረዋል ።

እንደ በፊቱ በየሰው ጫካ ውስጥ ከንብረት ጠባቂ ጋር የነፍስ ግቢ ነፍስ ውጪ አደገኛ ድብብቆሽ እየተጫወቱ ቅጠል ለቅመው በመሸጥ

በሚያገኙዋት ሳንቲም እህል ቆምሰው ማደር ተስናአቸዋል ። ወገባቸው ደርቆአል ። እግርቻቸውም እንደ ልብ አይራመዱም ። ስጋው አልቆ አጥንትና ጅማት ብቻ የቀረው የተለበለበ እንጨት የሚመስለው ክንዳቸው ተዘርግቶ ጭራሮ መስበር አቅቶታል ። በየሰው ቤት እንደ በፊቱ እንጀራ ጋግረው የእለት ጉርስ እንዳያገኙ የሳሳው ልባቸው ከቅርብ ቀርቶ ከሩቅም የእሳት ምላስ አይቅረበኝ ብሎአል ። እንደ በፊቱ ወተት ሸጠው እንዳያድሩ በግጦሽ ስፍራ ማጣትና በመና ውድነት ምክንያት ሀዲስን ያሳደጉትን ላሞች ፣ ቡሬንና ዳለቲን ከሸጡ ቆይተዋል ። እያንዳንዱዋ ከንድ መሬት ታጥራ ላሞቹ የሚግጡበት ቀርቶ የሚቆሙበት ስፍራ አጥተው ነበር ። እምቡዋ እያሉ ነዋፈው ከሚሞቱ በማለት ለሉካንዳ ነጋዴ በርካሽ ዋጋ ፣ «ለሚበላን አፈር ተስገብግቦ መሞት ። አይ ሰው ። ለሰው ሞት አነሰው ። ገድሎ የማይፎከረው እሱ ያውቃል ። ሰዉ ምን ከርስ ለቀቀበት ! አይ ይህ ሆዳም አለም !» ብለው ሲሸጡአቸው ፣ አቤት ሀዲስ ያፈሰሰው እንባ ።

ፀሀይ ወጥታ እስከምትጠልቅበት ጊዜ ድረስ ደከመኝን የማያውቁ ሴት ፣ እየበረደ ከሚሄደው ምድጃቸው ዳር ከቤት መዋል ጀምረዋል ። እረፍት የሚባል ነገር አያውቁም ። «የምን ልግም በገላ ነው ! የዘላለሙ እረፍት ይጠብቀን የለ» ይላሉ አዘውትረው ።

ሰነፍ ሰው አይወዱም ። «ገድሎ የማይፎከረው እሱ ያውቃል ። የመሸታን ንግድ ለእድሌም አላሳየው» ብለው ቤት በመዋል ፤ የፈትል ስራ ከጀመሩ ሰንብተዋል ። ደጋናቸውን ከተሰቀለበት አውርደው ጥጡን ሲነድፉት እንዲያው ስስ የበጋ ጉም አስመስለው ይቆልሉታል ። ከዚያ ቡጭቅ እያደረጉ በቀጭን ረዘም አድርገው በመሳብ እንዝርታቸውን ማሾር ሲጀምሩ ፣ እንቁላል የሚመሳሰሉ ወፍራም ልቃቂቶች ፣ በቆዳ የተለጎመ ጥንታዊ አገልግሎቻቸውን ባንዳፍታ እየሞሉት ይሄዳሉ ። የሚፈትሉትን ጋቢ የሁለት ጉረምሳ ክንድ አይጨምቀውም ። ፈትሉንም ቢሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደ ነገሩ ነበር የያዙት ። ለመኖር የነበራቸው እልክ ያለቀ ይመስላል ። ሆኖም ሀዲስ ትምህርቱን አቋርጦ ስራ በመያዝ እንዲጦራቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ጠይቀውት አያውቁም ።

እንደ ሌሎች ድሀ እናቶች ፣ «ልጄ ፣ ትምህርት ማለቂያ የለው ። ከሞትኩ በሁዋላ ሬሳዬ ላይ እንባ ብታፈስ እንደ አላዛር ከሞት አልነሳ ። እስካሁን የተማርከው ይበቃል ። ስራ ይዘህ ጡረኝ ። የእነ እገሌ ልጅ አባትና እናቱን እንዴት አድርጎ እንደሚጦር አላየህም ? አገር ሁሉ ነው ይባርከው የሚለው ። የኔ እጅ ብቻ አመድ አፋሽ ሆኖ ቀረ» በማለት አማረውት ፤ እሱን የወለዱበትን ማህፀን ረግመው አያውቁም ። ይልቅ ፣ «ሕማዬ ፣ አሁንስ ደከመሽ መሰለኝ ። ላንድ አመት ስራ ልያዝና ትንሽ ልርዳሽ» ባላቸው ቁጥር ፣ «ለዚህ ለዚህ ለምን ለፋሁ ? አይጥ ወልዳ ወልዳ ጅራቷ ሲቀር ሲጥ አለች አሉ ። እኔ ከእንግዲህ ቢደላኝ ፋይዳው ምንድን ነው ? ከጥፍር ሌላ የማበቅለው የለኝ ። ሆድ እንደሁ እየሁ አይል ። ኡዲያ ! ኢከከ የሰጠ ጌታ ጥፍር ላይነሳ ። እዩዩ ሲደላ ብቻ ነው ፣ ልጄ ። ማንኛውም ነገር ሲያልፍ ያልፋል ። ሁን ያለው ላይቀር ። ይልቅ በርታና ተማር ። የድሀ ስቃይ ባመት ሁለት አመት አይለክም ። አብሮ የኖረ ማንኛውም ነገር ይለመዳል ። ምን የሚያስቸኩል ነገር አለ ብለህ ነው ? አታስብ ። አሳብክን ሰብስብ አድርገህ ተማር» ይሉታል ።

ግን ፣ ያንጀታቸውን እየታጠፈ መሄድ ፣ የምድጃቸውን መቀገዘቀገዝና ትክትካቸውን እያየ እንዳሉት እሳቡን ሰብስቦ አድርጎ ለመማር ፈፅሞ አልቻለም ። ለማንበብ ባቀረቀረ ቁጥር ከገለጠው መፅሀፍ ውስጥ እየቀዘቀዘ የሚሄደው የእናቱ ምድጃ ብቅ ብሎ ይታየዋል ። . . . እሳቱ እየተንቀለቀለ ለጎጆዋ ሙቀትና ብርሃን ይሰጥ የነበረው ምድጃ — ገና ሲያዩት የሚያጠግብ ትኩስ እንጎቻ — ቱግ ቱግ እያለ የሚፎክር ያቦል ቡና ጀበና — መአዛው ምራቅ የሚያስውጥ ፣ ደረስኩ ደረስኩ እያለ የሚንተከተክ ድስት — የማይለየው ያ የሞቀ ምድጃ አሁን ቀዝቅዞ ፣ በርዶ ነበር የሚታየው ። እናቱ ከቀዘቀዘው ምድጃው ዳር ተቀምጠው ፣ የቀዘቀዘውን አመድ . . . ወደ መቃብር የሚወርድ ሙታን ድምፅ — አልባ ዋይታ . . . የድሀ ህይወት ···· ረጅም የጉዞ ፍታት ። አእምሮው እረፍት ሊያገኝ አልቻለም ። ሀዲስ ስራ ለመያዝ ቆረጠ ።

«ለወጣት አንድ አመት ምን ትርጉም አላት ? ወጣት ጊዜ አያመልጠውም ። ይደርስበታል እንጂ» አለ ። ገና ሃያ ሁለት አመቱ ነበር ።

አንድ ሳምንት ። ሁለት ! ሶስት ሳምንት ። ወር ። ስራ የለም ። ስራ በቀላሉ የሚገኝ ነገር መስሎት ነበር ።

የቀዘቀዘ ማኪያቶውን እንደ ጨለጠ አንድ አሳብ ብልጭ አለበት ። ስራ ቢጠፋ እስተማሪነት ይታጣል ? በማለት እዳውን ከፍሎ ሲያበቃ ፣ መንገዱን አቋርጦ ወደ ትምህርትና ስነ ጥበብ ሚኒስቴር ሄደ ። መስሪያ ቤቱ መግቢያና መውጫ በሮችና መተላለፊያ ኮሪደሮች ስለሚበዙበት ባለጉዳዮችን ቀርቶ የቆዩ ሰራተኞችንም ያደናግራል ። አቤት የተላላኪዎች ብዛት ! ባለጉዳዮችን ከሩቅ የሚገላምጡ ተላላኪዎች የማይንቃነቁ የብረት ምሰሶ መስለው በያንዳንዱ ቢሮ በር ላይ ተገትረው ይታያሉ ። እንደ ምንም ብሎ የአስተዳደሩን ክፍል ፈልጎ አገኘ ። ከበሩ ላይ 'የአስተዳደር ዋና ዲሬክተር' የሚል ፅሁፍ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በትላልቅ ወርቅ ቀለም ተፅፎ ይታያል ። ከጥቁር ሰሌዳዉ ትንሽ ዝቅ ብሎ ፣ አሁንም በጥቁር ሰሌዳ ላይ በነጭ ቀለም የተፃፈ ስም ይነበባል — ታፈሰ ብሩ ።

«ምን ነበር ! ?» አለው የቢሮው ተላላኪ ።

«አቶ ታፈሰን ነበር የምፈልገው» አለው ፣ ኮስተር ብሎ ። ተላላኪዎች ሲኮሳተሩባቸው ደንግጠው መሽቆጥቆጥ የሚጀምሩ መሆናቸውን በመጠኑም ቢሆን ያገኘው ልምድ አስተምሮታል ።

«ለምን ነበር?»

«ከታፈሰ ጋር የግል ጉዳይ አለኝ» ብሎት ገፍትሮት ገባ ።

ባለስልጣኖችን አንተ ብሎ መዘርጠጥ ተላላኪዎችንም ሆነ የቢሮ ፀሀፊዎችን ሸብረክ የሚያደርግ ስነ ልቡናዊ ተፅእኖ እንደ ሆነ ተረድቶ አል ።

«አቶ ታፈስ አለ?» አላት ፀሀፊዋን ።

«አ—አዎን ። ለምን ኖሮአል?»

«ጉዳይ አለኝ ።»

«ቀጠሮ አለዎት?»

«ከእሱ ጋር ቀጠሮ አያስፈልገኝም» ብሎአት አልፎአት ሄዶ በሩን ከፍቶ ገባ ።

ከራቫቱን አላልቶ በሸሚዝ ብቻ ከትልቅ ጠረጴዛ ሁዋላ የተቀመጠ ፣ ትከሻው ሰፋ ፣ ደረቱ ነፋ ያለ ፣ ፀጉረ ሉጫ ፣ ፊቱን ፈንጣጣ ወጋ ወጋ ያደ.ገው ቀይ ወጣት ታየው ።

ያ የተለመደው ፣ «ምን ነበር?» የሚል የቢሮክራቶች ጥያቄ ቀረበለት።
«ስራ ፈላጊ ነኝ ።»
«ማመልከቻ አስገብተሃል?»
«ሳይነበብ ተቀዶ የሚጣል ማመልከቻ ምን ፋይዳ አለው !»
«ምን ነው ቁጣ ቁጣ ይልሃል ? የተናደድክ ትመስላለህ ።»
«ንዴት ይነስኝ? ቀለቤ ሆኖአል ።»
«እና ፣ አሁን ምን ይሁን ነው የምትለው ?»
«ስራ ስጡኝ ነው የምለው ። ሌላ ምን እላለሁ ?»

«እንደዚሁ እ ! ደግም ነህ ፣ ብሩ ይሙት» አለው ፣ ቅንድቡን ከፍ አድርጎ ።

የታፈሰ ብሩ ድምፅ ለጆሮ ደስ ይላል ። ትናንሽ ዶቃ መሳይ አይኖቹ ቁልጭ ፣ ቁልጭ ይላሉ ። ረጅም አፍንጫው ነገር ከሩቅ የሚያሸት ይመስላል ።

«መቼም ያስተማሪነት ስራ አይጠፋም ብዬ ነው ።»
«ይመስልሃል !» አለ ፣ ታፈሰ ተቆጥቶ ።
«ያስተማሪዎች እጥረት አለ ብዬ ነው ።»

«እና ፣ ባንተ ቤት ማንም ስራ አጥ ከመንገድ መጥቶ አስተማሪ ሊሆን የሚችል ይመስልሃል እ ?» ብሎ ከመቀመጫው ብድግ አለ ። የትም አልሄደም ። ቆሞም አልቀረም ። ወዲያው ተመልሶ ቁጭ አለ ። ጠረጴዛውን በቡጢ ገጨና ፣ «እንዲህ አይነቱን ነገር መስማት ነው የምጠላው ። በእውነት ልቤ ይደማል ። ትምህርት ቤቶች የስራ አጦች መሰብሰቢያ ወይም የቅልደኞች ጊዜ ማሳለፊያ ቦታ አይደሉም ። ለምንደኞች ቦታ የለንም ። ትምህርት ቤቶቻችን መረማመጃ ድንጋዮች አይደሉም ። 'ባጣ ባጣ አስተማሪ ሆኘ እኖራለሁ' ብሎ ነገር ያናድደኛል ። ያሳዝነኛል» አለው ።

«አዝናለሁ ስላናደድክዎት ። ላናድድዎት ወይም ላሳዝንዎት ፈልጌ አይደለም ። ቸግሮኝ ነው . . .»

«ታዲያ ትምህርት ሚኒስቴር የችግረኞች መርጃ ቤት ነው እሉህ !»
«እሺ አይቆጡ ። ወደ ድኩማን መርጃ እሄዳለሁ» ብሎት ሊሄድ ሲል--

«ቆይ ። እናደኸኝ የት ልትሄድ ! ደ'ሞ አንቱታውን ተወኝ ። በእድሜ ብዙም የምንበላለጥ አይመስለኝም» አለው ።

ሀዲስ መለስ አለ ።

«ቁጭ በል ።»

ሀዲስ ቁጭ አለ ።

«ፊፅም ተስፋ የቆረጥክ ትመስላለህ ።»
«ምን ተስፋ አለና !»
«እንዴት ?»
«ወገን የሌለው ድሀ ምን ተስፋ አለው ? ምንስ ምርጫ አለው ? የገዛ ህይወቱ ውጥመዱ ናት።»

«የኛ ትውልድ ጥሎብት ተናዳጅና አመፀኛ ሆነ እንጂ ህይወት ይህን ያህል ክፉ አይደለችም ። ኢትዮጵያችን ገና ድንግል አገር ናት ። የራሳችን ክፉ ጠላትና ባለጋራ እኛው ራሳችን ነን — ሌላ አይደለም» ብሎት አጭር ማንባሩን አሸና ፣ «ለመሆኑ ለምንድን ነው ስራ የምትፈል ገው ? ወጣት ነህ ። ለምን አትማርም?» ብሎ ጠየቀው ።

«ችግር ገጥሞኝ ነው ።»

«ምን አይነት ችግር ?»

«ደካማ አሮጊት እናት አለችኝ ። ያለኔ ምርኩዝና ረዳት የላትም ። ችግርዋን እያየሁ ለመማር አልቻልኩም ። ስለዚህ ባይሆን ሳንድ አመት ሰርቼ ትንሽ ብረዳት ይሻላል ብዬ ነው» በማለት እቅጩን ነገረው ።

«ደህና ። የትምህርት ማስረጃ አለህ ?»

ሀዲስ ማስረጃውን ከደረቱ ኪስ ውስጥ አውጥቶ ሰጠው ። ታፈሰ ማስረጃውን በጥንቃቄ ሲመለከተው ቆየና አፍዋጭቶ ፤ 'ጂኒየስ' አይደ ለህም እንዴ ?» በማለት አደነቀው ።

«ግን ምን ያደርጋል !»

«እንዴት?»

«በብድብት መስሪያ ቤቶች ስድስት ፈተና ወስጄ አንዱንም ለማለፍ አልቻልኩም ። በቢሮክራሲ አካባቢ አንድና አንድ ሁለት እንዳልሆነ የተረዳሁት አሁን በቅርብ ነው» አለው ሳይታወቀው ቡጢ ጨብጦ ።

ታፈሰ በሳቅ ፈነዳ ። ሲስቅ ከሆዱ ነው የሚስቀው ። ጥርሶቹ እንደ ባህር እንቁ ያብለጨልጫሉ ። ጉራማይሌ ተንቀሳአል ። ሳቁን አቆመና ፣ «ልክ ነህ ። ቢሮክራሲ የራሱ የሆነ ሎጂክ አለው» እንዳለው ፣ የቢሮው ፀሀፊ የደለቡ ብዙ ፋይሎች ይዛ ስትረገረግ ገባች ። ሸቶዋ ክፍሉን አወ ደው ። ከሰውነትዋ ጋር ጥብቅ የሚል ቀይ ቀሚስ ለብሳለች ። ፋይሎቹን ሰፊው ባለመስተዋት ጠረጴዛ ላይ አኖረችና ፊትዋ ላይ መጥቶ ዝርግፍ ያለውን ረጅም ፣ ሂና የተቀባ ጠጉርዋን ወደ ላይ መታ አድርጋ ፣ የተከላ ብር የሚመስለውን ትላልቅ አይኖችዋን እያንከባለለችበት ፣ «ብዙ ባለጉዳዮች ውጭ ይጠብቃሉ» አለችው ።

«እነማን ናቸው?»

«እስተማሪዎች ናቸው ።»

«ይጠብቁ ምን የሚያስቸኩል ነገር አለ? እና ፣ ደግሞ ችግር ነው እንጂ መፍትሄ ይዞልኝ የሚጠብቀኝ የለም ። ስለ ሰው ችግር ማሰብ ሰል ችቶኛል» በማለት ተነጫነጨባት ።

ሀዲስን በአይኖችዋ ገርመም አድርጋው እየተረገረገች ስትሄድ በአይኖቹ ተከተላት ።

ሀዲስ እንደ ማፈር ብሎ አንገቱን ደፋ ።

ታፈሰ ማንባሩን እያሸ ሲያስብ ቆይቶ ፣ «ላንድ አመት ብቻ ነው መስ ራት የምትፈልገው አይደለም ያልከኝ ?» ሲል ጠየቀው ።

«አዎን ።»

አንድ ፋይል ከጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ አውጥቶ እያገላበጠ ሲመለከተው ቆየና ፥ «አዝናለሁ ። አዲሳባ ክፍት ቦታ የለንም ። ግን ጠቅላይ ግዛት ለመሄድ የምትፈቅድ ከሆነ ስራ ልሰጥህ እችላለሁ» አለው ።

ሀዲስ ቅር አለው ።

«ምን ነው ከፋህ ?»

«እዚሁ ባገኝ ደስ ይለኝ ነበር ። እንዳልኩት እናቴ ደካማ ናት . . .»

«አታዝላቸው!» ብሎት ፋይሉን ዘግቶ ከራቱ ገፋውና ፥ «አዝኜ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች አሉ» በማለት ከተረተበት በሁዋላ ፥ «ወጣቶች ስንባል ካዲሳባ መውጣት ሞት ይመስለናል ። ያራዳ ሱስ አይለቀንም። አዲሳባ ደግሞ ለሁሉም የሚበቃ ስራ የላትም ። ያሳዝናል ። ሁሉም እዚሁ መሆን ነው የሚፈልገው ። እዚህ የምታየው ፋይል አብዛኛው የሚቀርበው ወደ አዲሳባ አዛውሩን የሚል ጥያቄ ነው ። ገሚሶቹ ደግሞ የተሻለ ደሞዝ ፥ ሌላ መስሪያ ቤት አግኝተናልና ልቀቁን የሚሉ ናቸው ። ትምህርት ሚኒስቴር ለሌሎች መስሪያ ቤቶች የሰራተኛ ማሰልጠኛ ሊሆን ምንም አልቀረውም ።

«በከፍተኛ ወጭ በስንት ድካም ያሰለጠንናቸው አስተማሪዎች ለትንሽ ደመወዝ ጭማሪ ሙያቸውን ለቀው ሲሄዱ ያሳዝናል ። አስተማሪነት ክቡር ሙያ ነው ። ከፍተኛ ተጋድሎንና መስዋእትነትን ይጠይቃል ። ግን ስለ ሙያው ማንም ደንታ የለውም ።

«ይህ ‘ቴክተር ሪቪው’ እየተባለ የሚወራው ነገር ምንድን ነው ?» ብሎ ጠየቀው—ሀዲስ

«እሱ ? ገና እየተጠና ነው ። ምናልባት ለችግራችን መፍትሄ ሊሆን የሚችለው እሱ ሳይሆን አይቀርም ። ለሁሉም የቀለም ትምህርት ስጥቶ አይዘለቅም ። የእጅ ሙያ ማስተማር ያስፈልጋል ። ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት የሚሰራ እጅ ነው» ብሎ ፥ የእጅ ሰአቱን ተመለከተና ፥ «ወደ ዋናው ነገር እንመለስና ፥ መሄድ ትፈልጋለህ ? ወይስ አትፈልግም ?» በማለት ጠየቀው ።

«ለመሆኑ የት ነው የምሄደው ?»

አዲስ አሳብ ብልጭ ስላለለት አይናቹን ቁልጭ ቁልጭ አድርጎ ፥ «እንዲያውም ፥ እንዲያውም ለምን ሱጴ አትሄድም !?» አለው ።

«ሱጴ ! ምንድን ነው ! የት ነው እሱ ?»

ጨረቃ ላይ የሚገኙትን ተራሮችና ሸለቆች ስሞች አጥርቶ ያውቃል ። ሱጴ የሚባል ቦታ መኖሩን ግን ሰምቶ አያውቅም ።

ሱጴ ጅር በኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት ፥ ከጎሬ በስተሰሜን ፤ ከሙቱና ከኖኳ ባሻገር የሶርና የዲዲን ወንዞች ተሻግሮ ከትልቁ ገባ ወንዝ አፋፍ ላይ የምትገኝ በቡና እርሻና ንግድ የደራች ትንሽ ከተማ መሆንዋን ነገረው ። በዚያው ነገሩን አላቆመም ። ገለፃውን በመቀጠል ፥ «ሱጴ ያለም ዳርቻ የሆኑች አገር አትምሰልህ ። በነገራችን ላይ ፥ ከቡና ሌላ እኔንም ያፈራች አገር ናት» አለው ።

«እውነት?»

«እና ልልከህ ያሰብኩት ሀ ሁ እናኤ. ቢ. ሲ. ዲ ቆጥሬ ወደ አደግ ፣ ሁበት ትምህርት ቤት ነው ።»

«እውነት?»

«በጣም የቆየ ትምህርት ቤት ነው ። አባቴ መሬት ላይ ነው የተሰራው ። እልቴ ማርያም ትምህርት ቤት ይባላል ።»

«እሄዳለሁ» አለ ሀዲስ ።

«በጣም ጥሩ ። ደሞዙም ለክፉ አይሰጥም ። ሶስት መቶ አርባ ሰባት ብር ይበቃሃል ። እዚያ እንድትሄድ የፈለኩት በደሞዙ ምክንያት ነው ።»

«አመሰግናለሁ ።»

«ደህና ። ስትሄድ ላንቴ ደብዳቤ ትወስድልኛለህ ። ፊታውራሪ ተካ ኤጀርሶ ይባላሉ ። የሱዳ ባላባት ናቸው ። ደንበኛ የጥንት ፊውዳል ቢሆኑም ጥሩ ሰው ናቸው ። የቀጠር ሰአት የማትጠብቅ ከሆነ ወዮልህ ! ይቅርታ አያደርጉልህም ። ለአይናለምም ትንሽ ስጦታ ትወስድልኛለህ ።»

«የፊታውራሪ ተካ ልጅ ናት ። ከእስዋ በቀር ሌላ ልጅ የላቸውም ። እና ፣ እንደ አይናቸው ብሌን ነው የሚሳሱላት ። ብታያት በጣም ፣ በጣም ውብ ፣ እንዲያው እግዜሩ ጥበቡን የጨረሰባት ልጅ ናት ። እንዲያው ምን ልበልህ ? ለእግዜር አፍንጫና.አይን ደስታ ፣ በገነት ውስጥ በታላቅ ጥንቃቄ ተኮትኩታ የለመለመች ለጋ ፅጌ-ረዳ ትመስላለች . . .» ሲለው—

ሀዲስ በነገሩ መሃል ጣልቃ ገባና ፣ «ባለ ቅኔ ነህ ልበል !» አለው ።

ታፈሰ ተኩራርቶ ደረቱን ነፋና ፣ «ውበትን የሚያደንቅና በውበት የሚደሰት ሁሉ ባለ ቅኔ ነው» ብሎት ፣ በድጋሚ የእጅ ሰአቱን ተመለከተና፤ «መቼ ለመሄድ ታስባለህ?» ሲል ጠየቀው ።

«መቼም ቢሆን ግድ የለኝም ። መጉዋጉዋዣ ካገኘሁ ከነገ ወዲያም ቢሆን ለመሄድ ዝግጁ ነኝ ።»

«ደህና ። ላቶ ይርጋ አለሙም ደብዳቤ ትወስድልኛለህ ። የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ናቸው—ከሰብሰቴ ጊዜ ጀምሮ ። ግን ተጠንቀቃቸው ። የዋዛ ሰው አይደሉም» አለው ።

«እንዴት?»

«ባለ መሬትና የቡና ነጋዴ ሆነዋል ። ሆኖም ፣ በትምህርት ቤቱ ስራ ጉዳይ የሚገባባቸውን ሰው አይወዱም ። ድራሹን ነው የሚያጠፉት ። በተንኮል የሚችላቸው ሰው የለም ።»

«ምን ያደርሰኛል? ባንድ አመት ሊጣሉኝ ቀርቶ ሊያውቁኝም አይችሉም ።»

የውስጥ ስልክ ተደወለ ።

«ማን ነው እሱ ? . . . አውቃለሁ ። ግን ከሚኒስትሩ በቀር ሌላ ሰው የደወለ እንደሆነ አታገናኚኝ ። ስራ ይዣለሁ ። የሚጠብቁኝ ሰዎች አሁንም አሉ ? . . . ምንድን ነው የሚፈልጉት ? . . . ለምን አትጠይቂአቸውም! ለጌጥ ቢሮዬ በር ላይ የተቀመጥሽ መሰለሽ ! ብድር — የደሞዝ ጭማሪ — ዝውውር — ስንብት ሲሉኝ ይሆናል ። ለሁሉም ሰው ችግር መፍትሄ የማሆን የለኝም !» ብሎ ስልኩን ጆሮዋ ላይ ዘጋባት ።

ለሌሎች ባለጉዳዮች ጊዜ አጥቶ ለኔ ይህን ያህል ጊዜ እንዴት ሊሰጠኝ ቻለ ? እያለ ሲያስብ ፥ «የት ነበርን ? አዎን ፣ አቶ ጣሴ ደጉ የሚባሉ አስተማሪ አሉ ። አሁንም እዚያው ናቸው ። እጄን ይዘው ኤ.ቢ.ሲ.ዲ. ያስቆጠሩኝ አስተማሪዬ ናቸው ። በጣም ነው የምወዳቸው ። እንደ እሳቸው ለሙያው ፍቅርና አክብሮት ያለው አስተማሪ አይቼ አላውቅም ። ትምህርታዊ ፍልስፍናና አስተዳደር ያጠናሁት ምናልባት በእሳቸው ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ። ግን ይህን ትምህርት በመውሰዴ ራሴን ስረግም እኖራለሁ ። እርሻ ወይም ንግድ ባጠና ይሻለኝ ነበር» ብሎ በመስኮት ሩቅ ሲመለከት ከቆየ በሁዋላ ፥ «ለማንኛውም ነገር ላቶ ጣሴም ትንሽ ስጦታ ትወስድልኛለህ ። ያ ከእጃቸው የማይለየው ጉማሬ ትዝ ይለኛል ። ምናልባት አሁንም በእጃቸው ሳይኖር አይቀርም ። ስንት ሰው ቀጥቶ ያሳደገ ጉማሬ መሰለህ ! የሱጴ አድባር ነው ተብሎ የሚመለከበት አንድ ትልቅ ወርካ ትምህርት ቤቱ ግቢ አቅራቢያ አለ ። ወርካው ላይ በወጣሁ ቁጥር በዚያ ጉማሬ ይልጡኝ ነበር ። በዚያ ወርካ ምክንያት ብዙ ጊዜ ገርፈውኛል ። አሁን ሳስበው ለምን እንደሆነ እኔ እንጃ ፥ ያ ወርካ ያስጠላኛል ። ለማንኛውም ነገር ሱጴን እንዴት ነሽ ? በልልኝ ። በተለይም አለም ከተፈጠረ ጀምሮ ማንም ያልደፈረው ደን ስላለኝ እሱንም ሄደህ ጎብኝልኝ ። እኔም በቅርቡ እዚያው ሳልመጣ አልቀርም» አለው ።

«እውነት!»

«አዎን ፤ ደህና ሁኝ አራዳ ለማለት እያሰብኩ ነው ።»

«እንደኛውን እዚያው ለመኖር?»

«አዎን ። እዚህ ምን አደርጋለሁ ። የወር ደሞዝ እየጠበቁ መኖር ሰልችቶኛል . . . አባቴ መሬት ላይ ያሉት ጭሰኞች ትንሽ ትንሽ ባይጥሉልኝ ኖሮማ መኖር አልችልም ነበር ።

«አላዩህም በቦሎቄ ሰሞኑን ከትቢያ ተነስተው የማርቸዲስ ጌታ የሆኑትን ? የበሬ ግንባር የምታህል መሬት ያለው ሁሉ ዛሬ የቅዳሜና እሁድ ቦሎቄ ገበሬ ሆኖአል ። ነጭ ወርቅ ሆኖአልኮ ቦሎቄ ። ደህና ሁኝ አራዳ በማለት የከተማ መሬቱንና ቤቱን ሸጦ ወደ አዋሽ ፤ ወደ መቂ ፤ ወደ ሻሸመኔ ፤ ወደ ውልንጪቲ ፤ ወደ አቲያ ፤ ወደ አለም ጤና ፤ ወደ ሰቲት ሁመራ ለመዝመት የማይመኝ የለም ። ስሊጥም ነጭ ወርቅ ነው ።

«ቡና ደሞ የታወቀ ጥቁር ወርቃችን ነው ። ያንን እያፈሰኩ የራሴ ጌታ መሆን እያለ ከበሰበሰ ቢሮክራሲ ውስጥ እስካሁን በስብሼ መቅረቴ ይገርመኛል ። ያራዳ ሱስ ነውኮ እውር አርጎ ያቆየኝ ። ደህና ሁኝ አራዳ ብያለሁ ። ጭሰኞች የሚያላግጡበት ሰፊ ያባቴ መሬት አለ ። እዚያው እንገናኝ ይሆናል ።»

ታፈስ ብሩ ሚኒስትሩ ቢሮ ባይጠራ ኖሮ ለምሳ ቀርቶ ለራትም ነገሩን የሚቆርጥ አልነበረም ። ከመናገር ብዛት ራሱን ለማሳመን ጥረት የሚያደርግ መስሎት ነበር የታየው—ሀዲስ ። ግን ራሱን ከማሳመን ደረጃ ላይ የደረሰ አይመስልም ። ለስንቱ ይህንኑ መልሶ መላልሶ ነግሮ ይሆን ? ከታፈስ አንደበት ሳያቋርጥ የሚናደው የተጠና ንግግር እንጂ ሳይታ ሰብበት በጭውውት መሃል እንዲያው በድንገት የሚሰነዘር አሳብ አል ነበረም ። ሀዲስ ፣ «ሱዲ ላይ እንደምንገናኝ ተስፋ አለኝ» ብሎት በቀጠሮ ተለያዩ ።

በዚያኑ ቀን ከሰአት በሁዋላ በቀጠሮው ሰአት ሀዲስ ሲመጣ ታፈስ ብሩ የጠዋቱ ሳቂታና ተጫዋች ሰው ሆኖ አላገኘውም። አኩርፎ ነበር ። ቢሮውም አብሮት ያኮረፈ ይመስል ቀዝቅዞአል ። አቀርቅሮ ይፅፍ ነበር ። ሀዲስ እንደ ተነገረው የተቀጠረበትን ደብዳቤ ከፔርሶኔል ክፍል ፣ የሁለት ወር ቅድሚያ ደሞዙንና የመጉዋጉዋዣ አበሉን ከሂሳብ ክፍል ወስዶ ሲመለስ ፣ ሁለት ያደራ ደብዳቤዎችና በስጦታ ወረቀት የተጠቀለሉ ሁለት የካርቶን ሳጥኖች ሰጠውና ፣ «እኔም ለመሄድ ወስኛለሁ» አለው ፣ ፊቱን ጨፍግጎ ።

«ከመቼው?»

«ባንድ ወር እዚያ ባታየኝ እኔ ወንድ አይደለሁም» ብሎ ፣ በመስኮት ወደ አራት ኪሎ ሀውልት ተመለከተ ። አገር ሙሉ የቡና እግር ተክል ፣ ሜዳ ሙሉ ጥቁር ወርቅ ። «ነፃነት እያለ! ነፃነትን እንካ ብሎ የሚሰጥ ማንም የለም ። በትግል ነው ነፃነት የምትገኘው ። ትግል ደም ቆራጥነትን ይጠይቃል ። ለመሄድ ቆርጫለሁ.። እውነቱን ነው» አለ ።

«እንዲህ ያጣደፈህ ምን አዲስ ነገር መጣ?»

«የማንም ጅል ሚኒስትር ማላገጫ መሆን ሰለቸኝ ። ገረድ እንኳዋን የተሻለ አክብሮት ይሰጣታል ። እንደ ውሻ ነውኮ የሚያዩን ። ኩቲ ኩቲ ሲሉ ጭራችንን ስንቆላ እያዩን እነሱስ ምን ያድርጉ ! አይፈረድባቸውም ። ስልጣን እውቀት ይመስላቸዋል ። አለ እነሱ አዋቂ የለም ። በነሱ ቤት ሁሉም ደንቆሮ ነው ። እኔ ደንቆሮ አይደለሁም ። ጠጣና ጭሰኛ የሚጫወ ቱበት ያባቴ ድንግል መሬት እያለ በማንም ስሰደብ ፣ ለማንም ስሰግድ አልኖርም ። ለመሄድ ቆርጫለሁ ። በቃ ። ይህ የምታየው የነፃነት ሀው ልት ምስክሬ ነው ። አንተም ታዘበኝ» ብሎ ከመስኮቱ ላይ ዞር ሲል ሀዲስ ለመሄድ ተነሳ ።

ሀዲስ ለመሄድ ልቡ ቆሞአል ። እናቱን ለማየት በጣም ቸኩሎአል ። በግማሽ ልቡ ለእናቱ ምን ይዞ እንደሚሄድ ነበር የሚያስበው ።

«ማታ የት ትገኛለህ?»
«ለምን ፈለከኝ?»
«የወጭ ልልህ ነዋ!»

«ማታ አይመቸኝም ። የማልቀርበት ቀጠሮ አለኝ» አለው አሁንም ለእናቱ የሚወስደውን ነገር እያሰበ ። ቅልጥ ያለ ሎሚ ስጋ ታየው ።

«አይሆንም የሚል መልስ መስማት አልፈልግም ። ባይሆን መሸት ሲል መጥቼ እወስድሃለሁ ። አንድ ጉዋደኛዬ ፓርቲ ያደርጋል ። የኀሬ

ልጅ ነው ። ምን ታስባለህ ። እሺ በል ። ያዲሳባን የምሽት ህይወት ሳታይ ብትሄድ የሱዴ አድባር አትቀበልህም» አለው ።

እምቢ ሲለው አልቻለም ። አድራሻውን ሰጥቶት ሄደ ። እንዲህ በቀላሉ ከታፈሰ ብሩ ጋር መወዳጀቱ ያስገርመው ነበር ። ወዳጅነት በፕላን የሚደረግ ነገር አይደለም ። ወይም እንደ ታናሽ ወንድሙ አይቶት እንደ ልቡ የሚያናግረው ሰው ፈልጎ ይሆናል ። ምንም ይሁን ምን ስራ ስለ ሰጠው በልቡ እያመሰገነው አንዳች የሚያህል የግርሰሪ እቃና ግማሽ ብልት ሙክት ስጋ ይዞ ሜን ሜን እየተነፈሰ ጉለሌ ከእናቱ ደጃፍ ሲደርስ ቤቱ እንደ መቃብር ጭር ብሎ ጠበቀው ።

«እዚህ ቤት!» አለ ደንግጦ ።

መልስ አላገኘም ። ቤቱ ህይወት ያለበት አይመስልም ። ከውስጥ ምንም ብርሃን አይታይም ። እንደ ገሃነም ጨልሞአል — ገሃነም ጨለማ ከሆነ ።

«እማዬ!» አለ ሙክ ብሎ ።

ልቡ በሃይል መምታት ጀምሮአል ። ግን በጆርባው ቀዝቃዛ ላብ ይወርዳል ።

እትዬ በለጡ የሚባሉት የናቱ ጎረቤት ሸከላ መሳይ ፊታቸውን ብቅ አድርገው ፣ «ውይ በሞትኩት አንተ ነህ እንዴ?» አሉት የተሸከመውን እቃ በሞጭሙዋጫ አይናቸው እየቃኙ ።

«እማዬ የት አለች?»
«እሞእቸው ተኝተዋል።»
«ከመቼ ጀምሮ?»

«ከጠዋት ጀምሮ ። ልጄን ፣ ልጄን እያሉ አስጨንቀውኝ ነበር ። አንተም አለወትሮህ ጠፍተህ ነው የዋልከው ። ምን አገኘህ?» እያሉ እቃውን ተቀበሉት ።

እትዬ በለጡ ሀዲስ በሰጣቸው ገንዘብ እንጨትና ላምባ ፣ ክብሪትና የምግብ ዘይት ገዝተው ከተመለሱ ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ፣ ቤቱ ህይወት ዘራ ። ቀዝቅዞ የነበረው ምድጃ ሞቀ ። እሳቱ ተንቀለቀለ—እንጨቱ እየተንጣጣ ። የህ ይወት እሳት ይነድ ጀመር ።

ራት ሲቀርብ እናቱ እጥፍጥፍ ብለው ከተጋደሙበት በግድ ቀና ብለው ፣ «ይህ ሁሉ በረከት ከየት መጣ ልጄ?» አሉት ። የሚነደውን እሳት እይተው ፈገግ እያሉ ።

ላንድ ሕመት ትምህርቱን አቋርጦ ስራ መያዙን ባጭሩ ሲያጫውታቸው የደረቀውን ከንፈራቸውን እየመጠጡ ሲያዳምጡት ከቆዩ በሁዋላ ፣ «ምን ነው ልጄ ምናልኩህ? ላንተ ያለኝ ተስፋ ይህ አልነበረም ። ትምህርትህን እንድትጨርስ ነበር የኔ ምኞት ። እግዜር ሲጣላ ብትር አይቆርጥም ፤ ያደርጋል እንጂ ነገሩ እንዳይጥምም» ብለው የቀረበውን ጥሬ ስጋ በትንሹ ቀምሰው ተመልሰው ገድም ። ቢለመኑ ድርቅ ። ሀኪም ቤት ልው

ሰድሽ ቢላቸው ፣ «እስካሁን በሀኪም አልኖርኩ ። ያኪም ቤት ውስጡንም አይቼ አላውቅም ። ቃልቻ ለራሱ አያውቅም አሉ ። ገድሎ የማይፎክረው እያለ» ብለው ዝም ።

«ሸረ እባክሽ እማዬ . . .» እያለ ቢወተውታቸውም ፤

«ምን ነው ብትተወኝ ልጄ ። መንገዴን እያየሁት ነው ። የኔ ነገር አብቅቶአል ። ይልቅ የመት በለጡን ነገር አደራ ። አፈር ጠፍጥፋ እንዴት ኖር አፈር የተነፈጋት ። አይ የሰው ነገር ። አንድ ቀን ለሚበላን አፈር እንዲህ መስገብገብ» እያሉ ፣ ለብዙ ዘመን ከዳሩ ተቀምጠው ብዙ ጊዜ ከተከዙበት ምድጃ የሚነደውን እሳት እያዩ ትክዝ—ትካዜአቸው እያስ ተከዛቸው ሀዲስና እትዬ በለጡም ዝም ። እየቆዩ ፣ «እህህ» ብለው ፣ «የበለጡን ነገር ብቻ አደራ» ይሉታል ።

እትዬ በለጡ እሳቱን እየቆሰቆሱ እንባቸውን በዝምታ ያፈሳሉ ። እትዬ በለጡ በሸክላ ስራ የሚተዳደሩ ነበሩ ። ፊታቸ፥ ሸክላ ፣ እጃቸው ሸክላ ፣ ሰውነታቸው ሸክላ ይመስላል ። ለሸክላ ስራ የሚጠቀሙበትን ቀይ አፈር ያገኙበት የነበረው መሬት በባላመሬቱ ከታጠረባቸው ቆይቶ አል ። የማንን መሬት ማን ቆፍሮ ይወስዳል ተብለው ፤ ያለባለቤቱ ፈቃድ የቆፈሩትን ቀይ አፈር በማስረጃነት እንደ ተሸከሙ ወደ ፖሊስ ጣቢያ የተወሰዱበትም ጊዜ ነበር ። ደግነቱ የአራት ኪሎ ጋዜጠኞች ወሬውን አልደረሱበትም እንጂ ፣ «የሰው መሬት ጨለማን ተገን አድርጋ የምትቆፍር አመፀኛ ሴባ ተያዘች» የሚል አርእስተ ዜና ባወጡ ነበር ። እና ፣ ያንድ ሰሞን ቡና መጠጫ ወሬ ሆኖ በከረመ ነበር ። በነፃ የሚገኝ ነፃ ቀይ አፈር ስራ የፈታ እጃቸው እየፈለገ ፣ ነፃ ቀይ አፈር በአይናቸው እየዞረ ፣ የቀይ አፈር ሽታ አፍንጫቸው እየናፈቀ ፣ መኖር አይቀርምና ይኖሩታል ፤ ይሰሩት የነበረውን የተቃጠለ ሸክላ መስለው ። የተከለከለ ነፃ ቀይ አፈር . . የማንን መሬት ማን በነፃ ሊቆፍር? «መሬት የሁሉ ናት ባለቤት የላትም» ያለው ማን ነው ! !

ሀዲስ ከእትዬ በለጡ ጋር ፍሙ እየከሰመ ፣ እየበረደ ከሚሄደው ምድጃ ላይ እያፈጠጠ ፣ እናቱ ፣ «ድሀም እገር አለኝ ይላል? መቃብርም የለው እቱ ። በህይወት የተፋችው መሬት ሲሞት ምን መቃብር ትሆነዋለች? እህህ» እያሉ ሲተክዙ አብሮ እየተከዘ እሳቱ ላይ ሲያፈጥ የመኪና ጥሩምባ ሲጮህ ሰማ ።

እናቱን በዚህ ሁኔታ ላይ ጥሎ መሄዱን እየጠላ ፣ ከመርካቶ የገዛውን ‘ነፍስ ይማር’ ሰማያዊ ብሌዘር ኮትና ቡላ ሱሪ ከነጭ ስፖርት ሸሚዝ ጋር ለብሶ የማዱን ተነሳ ።

«በጨለማ የት ልትሄድ ነው?» አሉት ፣ እናቱና እመት በለጡ ተራ በተራ ።

«አንድ ቀጠሮ አለኝ ። ቶሎ እመጣለሁ ። ትንሽ ብቆይም አትስጉ» ብሎ ጠጉሩን አበጣጥሮ ወጣ ።

ታደሰ ብሩ የመኪናውን በር ከፍቶለት በውስጥ መብራት ብርሃን ሀዲስን ከታችው በሁዋላ ፣ «ሸበክ ብለሃል ። ቶንጋ ሰው ሲለብስ ያምራል ፤ ቆንጆ ሰው ሲለብስ ደግሞ መላክ ይመስላል ይባላል» አለው ።

«በነፍስ ይማር ሙሽክ ፣ እንዲህም አ’ርጉን የለ!»

ታፈሰ በሞቅታ ፊቱና አይናቹ ቀልተዋል ። እሱም ነጣ ባለ ልብስ ሽክ ብሎ ነበር ። ከክራቫቱ ጋር የሚሄደው ጥቁርና ነጭ መሀረቡ ከደረቱ ኪስ ላይ እንደ አበባ ፈንድቶ ይታያል ። የተርከፈከፈው 'ኮሎኝ' ጉብ ከሩቅ ይሰባል ። ነጭ ፔዦ 504 መኪናውን አስነስቶ በመብራቶቹ ጨለማ ውን እየሰነጠቀ ፣ በአርበኞች መንገድ ወደ ፒያሳ ፣ ከፒያሳ በራስ መኮንን ድልድይ አድርጎ ወደ አራት ኪሎ ፣ ከአራት ኪሎ ወደ ታላቁ ቤተ መንግ ስት የሚወስደውን መንገድ ይዞ በፊት በር ወደ ካዛ ኢንቼስ በመብረር ፣ ራስ ሙሉጌታ ሰፈር ሲደርስ በመብራቶች ነዶ ከጦፈ አንድ ትልቅ ቪላ ቤት አጠገብ ሲደርስ ፣ ቦታ መርጦ መኪናውን ቀጥ አደረጋት ። ሀዲስ በእፎይታ ተነፈሰ ። ከመኪናዋ ወርደው ተያይዘው ወደ ቤቱ ሲያመሩ ፤

«የምን ፓርቲ ነው?» ብሎ ጠየቀው ።
«ያለማዊ ደስታ ህይወት ።»
«ማለቴ ምክንያቱ ምንድን ነው?»

«ፓርቲ ለማድረግ ምን ምክንያት ያስፈልጋል? ህይወት ነው ምክ ንያቱ ። ካለህ ከወዳጆችህ ጋር መደሰት ነው — በቃ ። ደስታ የተሰጠ ሳይሆን ራስህ የምትፈጥረው ነገር ነው ። አይደለም እንዴ? ያሁኑ የዩኒቨ ርሲቲ ተማሮች 'መሬት ላራሹ!' እያላችሁ ከመጮህ በቀር ሌላ ነገር አታውቁም . . . አይዞህ ግባ» ብሎት በሩን ከፈተለት ።

ቤቱ ውስጥ ያለው ሞቃት አየር በጥፊ መታው ። ከሲጃራ ጢስ ጋር ውሰብስቡ የወጣ የሽቶ አይነት አፍንጫውን ወጋው ። ሙዚቃው ጆሮውን ጠለዘው ። ድብዝዝ ብሎ በሚታየው መብራት ብዙ ወንዶችና ሴቶች ወለሉ ላይ ይደንሳሉ ። ሀዲስ አይኖቹን በሃይል ከፈተ ። መብራቱ አንዳንዴ እንደ ርችት ልዩ ልዩ ቀለማት እየረጨ ብልጭ ድርግም በማለት አይን ላይ ይፈነዳል ። ሴቶችና ወንዶች በሙዚቃ ስልት እየተመሩ ይወዛ ወዛሉ ። አንዳንዶቹ ደግሞ ተቃቅፈው እግሮቻቸውን በማቆላለፍ ጉትናቱ ያስነካሉ ። ሌሎቹ ደግሞ የበረዣ ዛር ከነፈረሱ መጥቶ ላያቸው ላይ የተ ጫነ ይመስል አዶ ከበረ ይወርዳሉ ። ምሱን አጥቶ የተቆጣ ዛር ! ቤቢ . . . ቤቢ ዋው ! መብራቱ ድንገት ቦግ አለ ።

«ታዲያስ የአብድ አለም አይደለም?» አለው ታፈሰ ፤ ምግቡን ለመያዝ እንዳሰፈሰፈ ንስር አይኖቹን ወዲህና ወዲያ እያማተረ ።

«ይመ ስላል» አለ ሀዲስ ሰውነቱ እየተሸማቀቀ ። ከባህር የወጣ አሳ መስሎ ነበር ።

«ካልተግባህበት ጤነኛ አትሆንም ። አይዞህ ፣ ዘና በል ። በግድ ክብረ- ንፅህናህን የሚገስብህ የለም . . .» ሲለው ፣ አንድ በጣም ረጅም የሆነ ‹ ነይም ራሱ በራ ሰው ወደ እነሱ መጣ ።

ከሀዲስ ጋር አስተዋወቃቸው ። ጋባዣቸው ነበር ።

«'መሬት ላራሹ!' ከሚሉት ውስጥ አንዱ ነው ። ታውቅ የለም የዩኒ ቨርሲቲ ተማሪዎችን መንፈስ? — ተናዳጅና አመፀኛ ትውልድ» አለ ታፈሰ ።

«እንዴት እንደምንይዘው ካወቅንበት ጤናማ መንፈስ ነው» ብሎ በንጭ ሙሻረብ በራውን ጠረገና ፣ «ህይወት የማይገራው ነገር የለም ።

በወጣትነቱ ዘመን 'ሪቮሉሽነሪ' ያልሆነ ሰው ጤነኛ አይደለም ። ከአርባ አመት በሁዋላ በዚሁ ከቀጠለ ደግሞ ሞኝ መሆን አለበት ያለው ማን ነበር?» ብሎ ጋባዡ የደራሲውን ስም ለማስታወስ ሲሞክር—

«ሳርትር ነው ። ዣን ፓል ሳርትር» አለ ሀዲስ ።
«ልክ ነህ ። ብዙ ታነባለህ መሰለኝ!»
«'መፃፍ ትራሱ' ነው የቅፅል ስሜ ።»
«አስተማሪ ሆኖ ሱጺ ሲሄድ ነው» — ታፈስ ነበር ።
«እውነት ! ዲግሪህን ተቀብለሃል?»
«ገና ሁለት አመት ይቀረኛል ።»
«ታዲያ ለምን? . . . »
«የፋኖ ተሰማራ ተልእኮውን ሲፈፅም ነው» አለ ታፈስ እየሳቀ ።
«ሲቀልድ ነው» በማለት ሀዲስ ተቃውሞውን አሰማ ።
«ሱጺን ምን አስመረጠህ?» ሲል ጋባዡ ጠየቀው ።

«እኔ ነኝ የመረጥኩለት ። ባይሆን ሱጺ አንድ ጂኒየስ አስተማሪ ይገባታል በማለት . . . »

«መቼ ነው የጎሳ ስሜት የሚለቅህ ?» አለ ጋባዡ ።
«የንጉሱ ነገስቱ መንግስት ያንድ ጎሳ ሞኖፖል መሆኑ ሲቀር ።»
«ይህ ምላስህ ነው'ኮ ጠላትህ !»

«ማን ግድ አለው! ደኔን ሽጨ መኖር አያቅተኝም ። ሂደን እንጠጣ ና» ብሎት ሀዲስን ይዞ መጠጥ ወዳለበት ሄዱ ።

የተደረደረው መጠጥ አይነት አይን ያስከራል ። የጥሬ አይነት በኩንታል ከተከመረበት ክፍል ውስጥ ገብቶ አንድ የወደቀች ፍሬ የምትመለከት አይጥ ይመስል ፣ ሀዲስ ቢራ መርጦ ያዘ ። ታፈስ በበኩሉ ግማሽ ብርጭቆ ደረቅ ውስኪ ለራሱ ከቀዳ በሁዋላ ፣ ጉዋል የሚያካክሉ በረዶዎች ጨምሮበት ብርጭቆውን እጁ ውስጥ እየናጠ ባይኑ ማደን ጀመረ ። ክፍሉ ፣ እንደ በጋ ወራት ከዋክብት በሚያበሩ ጌጣጌጦችና እንደ ምሽት ጀምበር አይን በሚማርኩ ቀሚሶች ነደው ባሸበረቁ ቆንጆ ሴቶች ተሞልቶአል ። እንዲያው የገነት ተክሎች—ምርጥ የገነት በለሶች መስለው ይታያሉ ። ሸንቃጣ ሽንጣቸው ፣ የኩራው ዳሌያቸው ፣ ጉረኛ ጡታቸው ፣ ከሩቅ የሚጣራው አይናቸው ፣ የሚያስጎመጀው ከንፈራቸው ፣ ለህይወት የተራበና የተጠማ ይመስላል ።

«ኤጭ ! ምሽቱ ቀዝቅዞአል ። ህይወት የለውም» አለ ታፈስ ፣ እንዳ መበሳጨት ብሎ ።

«ከዚህ የበለጠ ምን ይሁን ?»

«ምኑን አይተህ ! ገና አልደራም ። እዚህ ቆመህ አታፍጥ ። ሂድና ተደሰት ። እዚህ የምታያቸው ሴቶች ሁሉ ለመቀጠፍ የተዘጋጁ የጎመሩ ፍሬዎች ናቸው» ብሎት ጥሎት ሄደ ።

መጤጥ በያይነቱ እንደ ውሀ ይቀዳል ። ሲጃራው እንደ ጡዋፍ ይቀጣጠላል ፣ ይጤሳል ። የሽቶ መአዛ ያለው አንድ ሲጃራ የሚመስል ነገር የሚያጤሱም ወንዶችና ሴቶች ነበሩ ። ጤነኞች አይመስሉም ። ሸጋ

የሆነ ጣፋጭ ህልም የሚያዩ መስለው ነበር የሚታዩት ። አይን ተከፍቶ ህልም የሚታይበት አለም ! ከሬዲዮ ግራማፎን በሚመነጨው ሙዚቃ ሳይሆን ከውስጣቸው በሚፈልቀው ልዩ ጣእመ ሙዚቃ ነበር የሚደንሱት ። እውነትም ምሽቱ እየገፋ ሲሄድ ፓርቲው እየጋለና እየጦፈ ይመጣ ጀመር ። መብራቱም በይበልጥ እየተሽሩጎረጎረ ይሄድ ነበር — ሙዚቃውም እየናረ — ዳንሱም ጨርሶ ገሀድ ወሲባዊ ንቅናቄ እየሆነ ። በሚደንሱት ሰዎች መሃል አልፎ ሄዶ አንድ ጥግ ይዞ ቆመ ። የሴቶቹ ጠረን አንድ የሆነ ስሜት ቀሰቀሰበት ።

«ና እንደንስ» አለችው ፣ አንድ ረዘም ያለች ሴት ከየት መጣች ሳይባል ፣ ድንገት ከጨለማ ውስጥ ብቅ ብላ ።

«በደስታ» ብሎ ፣ ወደ ዳንሱ ወለል ይዞአት ሄደ ።

ሽቶዋ ያሳብዳል ። ወገብዋ ጭብጥ አይሞላም ። እጅዋ እንደ ሀር እየለሰለሰ ይቀዘቅዛል ። የእሱ እጅ ግን አልቦት ነበር ።

«ከቅድም ጀምሮ ሳይህ ነበር . . . »

«እውነት?» አላት ፣ የራሱን ንቅናቄ ከእስዋ ጋር ለማስተካከል እየሞከረ ።

«ለመታዘብ የመጣህ ትመስላለህ» ብላ ፣ ከዘፋኙ ጋር ለመዘፈን ስትጀምር —

«ህይወትን ከዳር ቆሞ አይታዘቡም ። ይኖሩታል እንጂ» አላት ።

«ከዚህ በፊት አይቼህ አላውቅም ። ከውጭ ነው የመጣኸው?» ብላ ፣ ደረቱ ላይ ተለጠፈችበት ።

«የለም ። ከዚሁ ነኝ» አለ ፣ ሽቶዋን በሀይል እየሳበ ።
«ሎካል ነህ ?!»
«ሎካል ማለት ?»
«አራዳ . . .»
«አይደለሁም ።»
«ባትልም ታስታውቃለህ ።»
«እንዴት ?»
«አራዳ አራዳ አትሸትም» ብላው የባሰውኑ ተለጠፈችበት ።

«አራዳ ምን ምን ይሸታል?» ብሎ ጠየቃት ፣ ጆርባውን ቀኀታዛ ላብ እያስመጠው ።

«የኦ ዶ ኮሎኝ — የብብት ስፕሬ ሽታ ፤ አለ አይደለም ? እሱ እሱን ይሸታል ።»

«እና ፣ እኔስ?!» አላት ሰውነቱ ተሸማቆ ።

«ተፈጥሮአዊ የወንድ ጠረን — ደስ ይላል» ብላው አንገቱ ስር ሽጉጥ አለች ።

መብራቱ ቦግ አለ ። መብራቱን ረገመው ። እንዳጋጣሚ ሆኖ ታፈሰ ከሌላ ሴት ጋር ከጎኑ ይደንስ ኖሮ ፤ «ደህና ይዘሃል ጃል ። አራዳ ኖረሃል ለካ !» አለው በተገማመደ ምላስ ።

«አሳን በማጥመድ ሃዋርያትን ዱሮውንም ማን አክሎ !» አለው መለሰና ።

«በለስ አቅምቢው» አላት አብራው ስትደንስ የነበረችውን ልጅ ። የጠይም ቆንጆ ናት ።

«እንደ አዳም ምኔ ሞኝ» ብሎ ቀለደበት ።

ልጅትዋ መጣሁ ብላው ጥላው ሄደች ። ሶስት አራት ዳንሶች አለፉ ። ተመልሳ አልመጣችም ። ጥጉ ቆሞ ቢራ እየጨለጠ ጠበቃት ። እጁ ላይ የተወችውን የሽቶ መአዛ አሸተተ ። እየዞረ ይፈልጋት ጀመር ። የትም አል ነበረችም ። ፍኛው በሽንት ተወጥሮ ሲፈነዳ ስለ ደረሰ ልጅትዋን ትቶ ሽንት ቤት ፍለጋ ገባ ። አንዱን በር ሞከረ ። ተቆልፎ ነበር ። ሁለተኛውን ከፈት አድርጎ ዘው ብሎ ሲገባ መኝታ ቤት ሆኖ አገኘው ። መብራቱ በርቶ ነበር ። አልጋው ላይ ጋባዡንና የጠፋችበትን ልጅ አየ ። ደንግጦ በሩን ወደ ሁዋላው ወርውሮ ወጣ ። ቀስ ብሎ የመጣበትን መንገድ በመፈ ለግ ወደሚደነስበት ክፍል በመመለስ ታፈሰን ፤ «ቤት መሄድ እፈልጋለሁ» አለው ።

«ለምን ? ኮረዳይቱ ገሰፀችህ !»

«ተነስተህ ትወስደኝ እንደሁ ውሰደኝ ። አለዚያ ራሴ እሄዳለሁ !» ብሎት ወደ በሩ ሲያመራ ታፈሰ እየተንገዳገደ ተከትሎት መጣና ፤ «ምን ሆንሃል ? ምሽቱ ገና ለጋ ነው ። ቆይና አብረን እንሄዳለን» አለው ፤ ሚዛ ኑን ለመጠበቅ እግሮቹን አንፈራጦ ቆሞ ።

«እዚህ ቤት ጣራ ስር የሚካሄደው ብልግና በቅቶኛል ። እንሂድ !» አለ በንዴት ።

ታፈሰ ቀጥ ብሎ ለመቆም እየሞከረ ፣ «ቅድም ካንተ ጋር የነበረችው ልጅ የት አለች?» ብሎ ጠየቀው ።

«ጉዋደኛህ አቶ ሰሎሞን መኝታ ላይ ነች !»
«በዚህ ተናደህ ነው ለመሄድ የፈለከው ?»
«አይደለም ።»
«እህሳ ? ታዲያ ለምን ?»
«ብልግናው በቅቶኛል !»

«የምን ብልግና ! ጅል ! በህይወት መደሰት ባንተ ቤት ብልግና ነው ኤ ? ለማንኛውም ነገር አህያ ማር አይጥማትም ለካ ! እዚህ የምታየው የህይወት ጠብታ -- ጭማቂ ነው ። ገና ጥሬ ነህ ። የህይወት — የመኖር ትርጉሙ ምኑም አልገባህም ። ብልጥና ወኔ ያለው ደፋር ልጅ መስለሽኝ ነበር ያስጠጋሁህና የምስጢሬ ተካፋይ ያደረኩህ ። ግን ፣ ፈረንጆቹ እንደ ሚሉት አንተ የመፅሀፍ ትል ነህ ።

«ምናልባት በልጅትዋ ቀንተህ ይሆናል ። ግን ማወቅ ያለብህ የተኛ ችው ረዳት ሚኒስትርና 'የቦሎቄ ንጉስ' ከሆነ ሰው ጋር ነው ። በመተኛት ላይ ያለችው ከገንዘብና ከስልጣን ጋር ነው ። ነፍስ ይማር ኮትህን አንድት ደርብልህ ተመኝተህ ኖሮአል ! ንፁህ ፍቅር የሚባል ነገር የለም ። ይህ

እውነተኛው አለም ነው ። የዩኒቨርሲቲ 'ካምፐስ' አይደለም — ዳገትና ቁልቁለት የሌለበት ። አንተ ብሎ ታዛቢ ! አንተ ብሎ የምግባር ዳኛ ! አለ ምን እንድታይ ነበር ያመጣሁህ ። በ'ውነቱ ለምን እንዳመጣሁህም አላውቅም ። ለኔ ብለህ እንደሆነ ገደል ግባ !»

ሀዲስን ንዴት ተናነቀው ። ዘሎ ታፈሰን ለማነቅ ዳዳው ። ንዴቱን እንደ ምንም ተቆጣጥሮ ፣ «ይህን ርካሽ ፣ የበሰበሰና የገማ ህይወት ፣ እንደ ጥሩ ነገር ቆጥራችሁት ፣ እንደ ስልጣኔ አይታችሁት ፣ የህይወት ጠብታ -- ጭማቂ በማለት ዋጋ የምትሰጡት ከሆነ በእውነት ያሳዝናል ። በህልም አለም ውስጥ ነው የምትኖሩት ማለት ነው ። አትቸገር ። በእግሬ እሄዳለሁ ። ስላደረክልኝ እርዳታና የልብህንም ገልጠህ ስላጫወትከኝ አመሰግናለሁ» ብሎት ወጣ ።

«ሂድና በምድረ በዳ 'መሬት ሳራሹ' እያልክ ጩህ !» አለው — ታፈሰ።

እኩለ ሌሊት አልፎ ነበር ። በጨለማ እየተደናበረ መንገዱን ቀጠለ ። ጅቦች ይጮሃሉ ። ውሾችም ይጮሃሉ ። ጨረቃም ሆነች ከዋክብት ፈፅሞ የማይታዩበት እልም ፣ ድፍን ያለ ሌሊት ነበር ። እጁን አሽተተ ። ሽተው ገና ከእጁ ላይ አልጠፋም ። አፈር ዘግኖ እጆቹን አሸበትና ጨለማው ላይ በተነው ። ያፈር ሽታ ። ከሁዋላው እየከነፈ የሚመጣው መኪና በመብራት ብርሃን አጥለቀለቀው ። ቶሎ ብሎ የመንገዱን ጠርዝ ያዘ ። መኪናው አጠገቡ ሲደርስ ሲጥጥ ብሎ ቆመ ። በሩ ተከፈተለት ። ታፈሰ ነበር ።

«ግባ ። አስኮናኝ!»

ሀዲስ ዝም ብሎት መንገዱን ቀጠለ ። ታፈሰ በሩን እንደ ከፈተ በመኪናው ተከተለውና ፣ «እሺ ይቅርታ ። ግትር አትሁን ። ግባ» አለው ።

ሀዲስ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አደረገና መኪናው ላይ ተሳፈረ ።

«ትናደህብኛል?»
«ከንዴት ጋር ተላምጃለሁ ። የእለት ቀለቤ ነው ።»

«ደስታ ምን እንደሆነ ማወቅ ያለብህ ይመስለኛል ። ገና ወጣት ነህ ። ንዴት ፤ ህይወትን የምንመለከትበት መነፅር መሆን የለበትም ።»

ከዚያ ብሁዋላ አልተነጋገሩም ። ሁለቱም በየራሳቸው አሳብ ተውጠው ነበር ። ሀዲስ ህልም አልባ የሆነ ሌሊት ነበር ያሳለፈው ። ማታ ካየው የበለጠ ምን ህልም ሊያይ!

እናቱ ወይዘሮ አልፍነሽ ጡዋት ንቁ ሆነው አገኛቸው ። ከባድ የአንቅልፍ ድካም የለቀቃቸው እንጂ ታሞ የከረመ ሰው አይመስሉም ።

«እማዬ የተሻለሽ ትመስያለሽ» አላቸው ፣ ደስ ብሎት ።

«ደህና ነኝ ። አታስብ ። ብሞትም የማሳስብህ ነገር የለኝም ። ራሴን ችዬ ነው የምሄደው ።»

«እንዴት እማዬ ?»

«እንከባክቦ የሚቀብረኝ ጥሩ የድሀ እድር አለኝ ። ካፈ እየነጠኩ የእድር መዋጮዬን ስከፍል የኖርኩት ለምን መሰለህ ? ቀባሪ እንዳላጣ ነው ። ለመቃብር ቦታዬም ማንንም አላሳስብም ። ሰንበቴዬ ማረፊያ ቦታ ይሰጠኛል ። ለንፍሮ የሚሆን እህል ፥ ቡናና ሳጥንም ጭምር እድሬና ሰንበቴዬ ተባብረው ያቀርባሉ ። ከዚህም ሌላ ሰንበቴዬ ሶስት መቶ ብር ለወራሼ ይሰጣል ። ማንንም አላሳስብም ። የሬሳ መኪናም ጭምር የሚያቀርቡት እነሱ ናቸው ። አይዞህ ፥ ድህነትን እንጂ መጥፎ ስምና እዳ አላወርስህም ።»

«ከሞትሽ ደብረ ሊባኖስ ወስደን እንቅበርሽ ብለውኝ ነበር ። ግን ለምን ብዬ ! ለምን ሰው ላስቸግር ? ለምንስ ካባትህ ልለይ ? ምንም አልቀረኝ ። ተዘጋጅቻለሁ ። ሞት እንዴት ሰውን ይቀድማል ? ኸረ ኡዲያ ! ሞትን የሚያክል እንግዳ ተዘጋጅቶ መጠበቅ ነው እንጂ» እያሉ ሲያጫውቱት አዲስ ነገር አልሆነበትም ።

«በሰው ልጅ ላይ ጥላውን እያንዣበበ ዝንተ አለም የሚኖርን ፥ ሞትን የሚያክል ትልቅ እንግዳ ተዘጋጅቶ መጠበቅ እጣ ፈንታችን ነው ልጄ ። ሰው ሞኙ ግን ሞትን የሚያክል እንግዳ አንድ ቀን የሚመጣበት መሆኑን ዘንግቶ ይፈነጥዛል ። ሞት ያለ አይመስለውም ። ጥላ የሌለው ብርሃን ያለ ይመስል ። ወንድም በወንድሙ ላይ መጨከን ። ሲጠግቡ እንደ በቅሎ ይቱ ሰማዩን መርገጥ ። ሰውኮ ሞኝ ነው ። ህይወት ታሞኘዋለች ። ሞት እንዴት ይስቅብን ይሆን ?» ይሉት ነበር ከእድር ልቅሶ ወይም ከሰንበቴ ሰበካ በተመለሱ ወይም ለእድር ወይም ለሰንበቴ የሚከፍሉት ገንዘብ አጥተው በተቸገሩ ቁጥር ። ኑሮአቸውን የሚያማርሩበት ጊዜ ቢኖር ለእድር ወይም ለሰንበቴ የሚከፍሉት ገንዘብ ባጡ ጊዜ ብቻ ነበር ። የሰንበቴ ፅዋ ቤታቸው ገብታ እስክትወጣ ድረስ እንቅልፍ እንደ ልብ አይተኙም ። ባጠቃላይ አይናቸው ከሞት ጥላ ርቆ አያውቅም ። ለርሳቸው ህይወት ማለት ለሞት የሚደረግ የአንድ ረጅም ጉዞ ፍትሃት ዝግጅት ነበር ። ወደ መቃብር የሚያደርጉትን ጉዞ ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን ወደ መንግስተ ሰማያት የሚያስገባቸውንም የይለፍ ወረቀት ሳይዙ የቀሩ አይመስሉም ። ገድሉ የማይፎክረው እሱ ያውቅ የለ ! ምናቸው ሞኝ — ሞት እንዳይስቅባቸው ነዋ !

ጤናቸው አላሰጋውም ። ሀዲስ ደስ ብሎት ተስፋው እያንሰራራ ስለ ጉዞው ነበር ሲያስብ የዋለው ። ምሽት ላይ እጁን ስመው ፥ «የኢጅህን ዋጋ አትጣ» በማለት መርቀውት ደከመኝ ብለው ጋደም - - ትንሽ ቆይተው ዝም ።

ከባድ ዝምታ ቤቱን ዋጠው ። የእናቱን መሞት ማመን አቃተው ። ጭካኔ የተሞላበት ፍች የሌለው የእግዜር እንቆቅልሽ ጨዋታ ከቶ ሊገባው አልቻለም ። አንድ ደቂቃ ህይወት — ተስፋ ። በሚቀጥለው ደቂቃ ሞት— መቃብር ። የህይወት እስትንፋስን ለማቆየት የታሰበ ገንዘብ ለከፈን—ለቃሬዛ ። ቀዝካር የሌለው ሙት አርባ—የድሀ ሞት ። ኑሮው አይሰምር ፥ ሞቱ አያምር — የድሀ ህይወት ፥ የድሀ መቃብር ።

ሞት ለማንም አይቀርም ። ዞሮ ዞሮ ከቤት ፤ ኑሮ ኑሮ ከመሬት ግን ትምህርቱን ጨርሶ ወግ ማእረግ ሳያሳያቸው በመሞታቸው እጅግ በጣም አዘነ ። እሳቸውም እሱ ትምህርቱን ጨርሶ ለማየት በጣም ይጓጉ ነበር—

ከእሱ የሚፈልጉት ነገር ባይኖርም ። እናቴ ከሞተች ለምን ትምህርቴን አቋርጣለሁ ? የሚል አሳብ ቢመጣበትም ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ይህን የማይረሳ ሀዘን ይዤ እንዴት ልማር እችላለሁ ? አሳቤም እሺ ብሎ አይሰበስብልኝም ። ከእናቴ መቃብር ርቄ መሄድ አለብኝ ። ጊዜና ርቀት የማይሽረው ቁስል የለም በማለት ከራሱ ጋር ይሙዋገት ነበር ። ግን ውሳኔ ላይ ሊደርስ አልቻለም ። በቅድሚያ ከተቀበለው የሁለት ወር ደመወዙ ውስጥ ግማሹን ለእናቱ ቀብር ያጠፋው መሆኑ ትዝ ያለው ቆይቶ ነበር ። ሄዶ ያን ያህል እምነት የጣለበትን የታፈሰ ብሩን ፊት እንደገና ለማየት አልፈለገም ። ያጠፋውን ገንዘብ ተክቶ ሄዶ ገቢ ለማድረግ አቅቶት አይደለም ። አንዳንድ የቤት እቃ ቢሸጥ ያጠፋውን ገንዘብ እጥፍ ሊያገኝ ይችል ነበር ። ግን የሙዋች እናቱን እቃ የመሸጥ አሳብ ህሊናውን እንደ ጦር ወጋው ። እትዬ በለጡንስ ምን አደርጋቸዋለሁ? አለ ። ከእናቱ ሌላ ዶጋፊና ረዳት አልነበራቸውም ። በመሄዱ ድንገት ቆረጠ ። ጀርባውን ለአዲስ አበባ ፤ ፊቱን ለሱዱ ሰጥቶ ተነሳ . . .

# ክ ፍ ል ፪

በአይሮፕላን ካዲሳባ ጎሬ ፥ ከጎሬ በበራሪ ሲዮንቺና ሙቱ ፥ ከሙቱ በኪራይ በቅሎ ወደ ሱጴ ተጉዋዘ ። ከበቅሎዋ ጌታ ጋር ፥ ፈልሰስ እያለ በርጋታ የሚወርደውን ከሙቱ ግርጌ ያለውን የሶርን ወንዝ አቋርጦ ፥ አሽዋማውን የኖጳን ከተማ ሰንጥቆ አልፎ ፥ ብርማዋን የዲቢን ጅረት ተሻግሮ ሲያቆለቁል ፥ ታላቁ የገባ ወንዝ ፏዋፏዋቴ እንደ ዶራሽ ነጎድጉዋዳዊ ዝናብ ከሩቅ እያስተጋባና ከዝንተ አለም ጀምሮ የፀሀይን ብርሃን አሻፈረኝ ብሎ የኖረውን ጥቅጥቅ ያለ ደን የምፅአት ቀን ቋዋንቋዋ እያናገረ ልቡን ያሸብረው ጀመር ።

ዙሪያውን በከበበው ጥቁር አረንጉዋዴ ደንና ጥቁር ድንግል መሬት ውበትና ህመልማላዊ ልምላሜ አይኑ ተጭበረበረ ። ቀዝቃዛው ንፁህ አየር ሳምባውን አሳበጠው ። የጥቁር ድንግል መሬት ሽታ — የጥቁር አረንጉዋዴ ድንግል ደን ሽታ — አለም ስትፈጠር የተርከፈከፈ ሽቶ ። ውበቱ አስከረው — ሀዲስን ፤

ከገባ ወንዝ ሲደርስ ድልድዩ ላይ ቆም ብሎ ከሰማይ እምብርት ቁልቁል እየተናደና አረፋ እየደፈቀ የሚወርደውን ፏዋፏዋቴ ባድናቆት ተመለከተ ። ፏዋፏዋቴው አረፋ እየደፈቀ ቁልቁል ሲናድ ፥ ቀስተ ደመና ዎች ሽማኔ እንደ ዘረጋው ድር ከወንዙ ወለል ጥልቀት ውስጥ ወደ ላይ ይወ ረወራሉ ። እና ፥ ድልድዩን ተሻገረ ። የገባን ዳገት ከበቅሎው ጋር ቡዋጦ ወጥቶ አፋፍ ላይ ሲደርስ የገባን ሸለቆ መለስ ብሎ በምሽት ጀምበር ባየ ጊዜ ልቡ በውበት ተመሰጠ ። መሬቱ ባልበገሬነት ወደ ሰማይ ሲንጠራራ ታየው ።

በምሽት ጀምበር·በሰንበተ ጉዳ ሱጴ ደረሰ ። ከመድረሱ ይልቅ በተ ሰፋ መጉዋዝ ይሻል ይሆን ? ሳይሻል አይቀርም አለ ። ድካም ፥ የሚሞ ረሙር ራብና የሚያቃጥል ጥማት ተሰማው ። የደከመ ሰውነቱን ሌሊቱን የት እንደሚያሳርፍም አላወቀም ። የበቅሎዋ ጌታ እንዳመለከተው ወደ ትምህርት ቤቱ በቀጥታ አመራ ። ከትምህርት ቤቱ ደርሶ ከበቅሎዋ ሲወ ርድ ኮርቻ· መቀመጥ ያልለመደው ጭኑ ቆጠቆጠው ።

የትምህርት ቤቱ ምድረ ግቢ ሰው ሊውጥ በሚችል ሙጃና የመስቀል አበባ ተውጦአል ። ዛሞ የሚታየው የትምህርት ቤቱ ህንፃ ጋጣ ቢሆን እንጂ የትምህርት ቤት መልክ ፈፅሞ አይታይበትም ። ካንድ አጠና ላይ እንደ ተሰቀለች የተረሳች የተበጣጠሰች ባንዲራ ንፋስ ያንገላታታል ። ምን ቀለም እንደ ነበራት አይታወቅም ። የሚያውቀው አረንጉዋዴ ፥ ብጫና ቀይ ቀለም በእርግጥ አልነበረም ። ትምህርት ቤቱም ምን ቀለም እንደተ ቀባ አይታወቅም ። የሰው ዘር በአካባቢው አይታይም ። ምድረ ግቢውን እንኩዋን የብዙ ተማሪዎች ቀርቶ ያንድም ተማሪ እግር ሮጦበት የሚያውቅ

አይመስልም ። ላንድ አመት ይቅርና ላንድ ሳምንትም እዚህ የመቆየት አሳቡ ከስሩ ሲናድ ተሰማው ።

ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ተረስቶ የኖረ ትምህርት ቤት ቢሆንስ ? ልቡ ድን ገት ሰመጠ ።

ጀርባው የጎበጠ እንደ ትምህርት ቤቱ ያረጀ አንድ አይና ሰው እህል ውሀ የማያሰኝ ቆመጥ ይዞ እንከስ እንከስ እያለ ካንድ ጨለማ ክፍል ማህፀን ውስጥ ብቅ ሲል ሀዲስ ደነገጠ ። ሰውዬውን የተከተለው ጠብደል ጅራት ጉንድሽ ፣ ጆር ቆራጣ ጥቁር ውሻ እስፈራው ። ወደ ሁዋላው እንደ ማፈግፈግ እያለ ፣ «እዚህ ነው የሚሰሩት?» ይለዋል ፣ አይኖቹን ከውሻው ላይ ሳይነቅል ።

«ዘበኛ ነኝ ።»
«ትምህርት ቤቱ አልተከፈተም እንዴ ?»
«ወንዞች ገና መቼ ጎደሉና !»

ትምህርት ቤት ከመከፈቱ ከመስከረም 18 ቀን 1965 ዓ. ም. በፊት ድረስ ነበር የተባለው ። በናቱ ሞት ምክንያት መድረስ የነበረበትን ቀን በአስር ቀን አሳልፎ ነበር የመጣው ። ልብ ከገዛ በሁዋላ ሀዲስ እየተገረመ ፣ «ታዲያ መቼ ይከፈታል?» ይለዋል—ዘበኛውን ።
«መልካዎች መጉደል ሲጀምሩ ነዋ ።»

በልቡ ፣ ተአምር አያልቅም ብሉ ፣ «ዲሬክተሩን የት ላገኛቸው እችል ይሆን?» ይለዋል ።

«አቶ ይርጋን ?»
«እዎን ፣ አቶ ይርጋ አለሙን ?»
«ወደ መቱ ለስራ ጉዳይ ወጥተዋል ።»

ተአምር አያልቅም ፣ አለ ። ሌሊቱን የት እንደሚያሳልፍ በጣም ይጨ ንቀው ጀመር ። ከትምህርት ቤቱ አንድ ክፍል ውስጥ ወይንም በረንዳ ላይ የማደሩ አሳብ የሚያንቀጠቅጥ ብርድ በሰራ አካላቱ ሰደደበት ። በያ ዘው ያደራ ደብዳቤ አሳቦ ፊታውራሪ ተካ ቤት በዚያን ሰአት መሄድ ፈፅሞ አልታይ አለው ። ቀኑን ሙሉ ተጉዞ ማደርያ ማጣት ። ህይወት አክ እንትፍ ብላ ተፍታ ያወጣችው መሰለው።

«አቶ ጣሴ ደጉ የሚባሉትስ ?»
«አሳቸውም የሉም ። ለኮርስ እንደ ሄዱ አልተመለሱም ።»
«አልቤርጎ ይገኛል?»

«ማዶ ከወይዘሮ ዝናሽ ቡና ቤት ቢጠይቁ ምናልባት ። ሌላ አልቤርጎ የለም ።»

የበቅሎዋ ጌታ መሽቶበት ለመሄድ ቢቸኩልም የወይዘሮ ዝናሽን ቡና ቤት ሊያሳየው ፈቃደኛ ነበር ። የበቅሎዋ ጌታ መርዳሳ ጅሩ በሱጼ የማያውቀው ቦታና የሰው ስም አልነበረም ። በቅሎዋም ብትሆን መሪ አያስፈልጋትም ። መንገድን እየመረጠች የመሄድ ችሎታዋ ሀዲስን ሳያስ ገርመው አልቀረም ። ወደ ዝናሽ ቡና ቤት ሲያመሩ ፣ «አንተስ የት ታድራ ለህ?» ይለዋል ፣ እሱ ራሱ የት እንደሚያድር ገና ሳያውቅ ። እንደ ፡ውነቱ ከሆነ ሊሰማው አልፈለገም ።

«ዘመድ አለኝ ። እዚያ አድሬ ጠዋት ሰው ካገኘሁ ወደ መቱ እመለ ሳለሁ ። በበጋው ወራት በየቀኑ ነው የምመላለሰው ።»

«እውነት ?»

«በሀቀኝነቴ ነው ካባቴ ጋር ከመቱ ሱጴ ፣ ከሱጴ መቱ መመላለስ የጀ መርኩት ። ከሃያ አመት በላይ ሆኖኛል በዚሁ መንገድ ስመላለስ . . .»

«እውነት?» — ተአምር አያልቅም እያለ በልቡ ።
«ይሄው መንገድ ነው እንጀራዬ ።»

መርዳሳ ነጠላውን ከራሱ ላይ ጣል አድርጎ ፣ ከትከሻው ላይ ከተጋደ መው ሽመል ላይ ሁለቱንም እጆቹን ሰቅሎ ከበቅሎዋ እኩል ያለ ምንም ድካም ከጎኑ እንዴት ይራመድ እንደ ነበር ሀዲስ በመገረም እያስታወሰ ፣ «ግብርና አይሻልም ነበር ?» ይለዋል ። ያንን መንገድ ሁሉ አቋርጠው ሲመጡ ፣ መርዳሳ ላንዳፍታ ቆም ይል የነበረው በተወሰኑ ቦታዎች ከም ንጭ ውሀ ለመጎንጨት ብቻ ነበር ። ምናልባት ላለፉት ሃያ አመታት ውሀ በእጁ እያፈሰ ሲጎነጭባቸው የቆዩ ምንጮች ሳይሆኑ አይቀሩም ።

«መሬት ከየት መጥቶ?»
«ይኸ ሁሉ መሬት እያለ !»

«ሁሉም ባለቤት አለው—ጌታው ። አባቴ በጭሰኛነት ለብዙ ዘመን ከኖረበት መሬት በመነቀሉ ነው ለዚህ ስራ ዳርጎኝ የሞተው ። አሁንማ ጭሰኛ የሚፈልግ ባለመሬትም የለ . . .»

«ለምን ?»

«አገሩ እንደሚያዩት የቡና መሬት ነው ። ባለመሬት የተባለ ሁሉ ጭሰኛን እያባረረ ስራ የቡና እርሻ ግልጋት ጀምሮአል ። በዚህ ላይ ደሞ የባለመሬትና ጭሰኛ ግንኙነት አዋጅ ይወጣል የሚል ጭምጭምታ ከተ ሰማ ወዲህ ፣ ጭሰኛን ነቅሎ ያላባረረ ባለ መሬት በውርርድ አይገኝም . . .»

ሀዲስ የታፈሰ ብሩን አላማ እያስታወሰ ፣ «የተነቀሉት ጭሰኞች ምን ይሆናሉ ታዲያ ?» ይለዋል ።

«ምን ይሆናሉ ? እግዜር እንዳደረጋቸው ሆነው ከመኖር ሌላ ። አቤት ቢሉ ማን ሰምቶ ? ፍርድ የለ ። ወደ ኩሊነት መግባት ነዋ ። ሌላ ምን ይሆ ናሉ ? እንዲያው መንከራተት ነው—ከቦታ ቦታ ፣ ካገር አገር ። ተንከራ ተች ያላቹ ነፍስ እስክትወጣ ድረስ ታንከራትታለች—ጌታው ።»

ሀዲስ ሌላ ጥያቄ አላከለም ። ዝም ብሎ ወደ ዝናሽ ቤት ሲያዘግም ፣ የገጠሪቱ ኢትዮጵያን እልፍ አእላፍ ከርታታ ሰራዊት — ቀን የጨለመ በት የሰው መንጋ — ሲንከራተት ውሎ ማደሪያ ያጣ ሰራዊት — የማይሰማ ጩኸት ፣ ዋይታ — የደፈረሰ ምንጭ — ከስሩ የተናጋ ህይወት — ደራሽ ፣ ቅጡ ጅረት በአይነ ህሊናው ይመጣበት ነበር ።

ከዝናሽ ቡና ቤት ሲደርሱ መርዳሳ ቤቱን አሳይቶት ፣ ምንም ጊዜ ሳያጠፋ ተሰናበተውና በቅሎውን በልጉዋምዋ እየሳበ ከጨለማ አብራክ ውስጥ ገብቶ ጠፋ ። ማደርያ ያግኝ አያግኝ ትንሽ ቆይቶ እንኳዋን ለማወቅ ደንታ አጧሳየውም ። «ምን አይነቱ ሰው ነው ? ግን ቢቆይስ ምን አድርጎ

ልኝ ልለው ኖሮአል ?» እያለ ፣ በአለም የነበረችውን ንብረት በሙሉ በት ንሽ ሻንጣው እንዳንጠለጠለ ከዝናሽ ቡና ቤት ሲገባ ቤቱ ውስጥ የነበሩት ሰዎች አይተውት የማያውቁት እንግዳ ሰው ከጨለማ ውስጥ ድንገት ብቅ ሲል በማየታቸው ፣ ምን ጉድ መጣ ? በማለት ሳይሆን አይቀርም ፣ ሁሉም በማሾ ብርሃን አፈጠጡበት ።

ከእግር እስከ ራሱ የሚያማትሩት አይኖች እረፍት እየነሱት ፣ «አል ቤርጎ ነበር የምፈልገው» አለ ።

ሻሽዋን የገርዳሳ አስራ ካንድ የመቶ አለቃ ፖሊስ አጠገብ ቁጭ ብላ ውስኪ በመለኪያ ትጎነጭ የነበረችው ጠይም ሴት ፣ የወርቅ ጥርስዋን ብልጭ አደረገችበትና ፣ «እዚህ አገር አልቤርጎ የት ይገኛል ? እንግዳ ነህ መሰለኝ» አለችውና ከት ብላ ሳቀች ።

ጠርሙስ ውስኪ ካግዳሚ ጠረጴዛ ላይ ከፊታቸው ቆሞአል ።

እንደዚህ ያሳቃት ነገር ባይገባውም ፣ በማላውቀው አገር የጅብ ራት ልሆን ነው ? በማለት እድሉን እየረገመ ፣ «ላገሩ እንግዳ ነኝ ። አሁን ከመሸ ነው ከዚህ የደረስኩት» ይላታል ።

«ከየት ?» ብላ አሁንም ከት ብላ ትስቃለች ።
የሳቅ በሽታ ይዞአታል ይህች ሴት ? እያለ «ካዲሳባ» ይላታል ።

ከባንኮኒው ሁዋላ የቆመችው ቀይ ዳማ ወጣት ብጤ ሴት ትላልቅ አይኖችዋን ትተክልበታለች ። ጠብመንጃ የያዙ ሌሎች ሁለት ፖሊሶች ከመቶ አለቃውና ከሴትዮዋ ራቅ ብለው ካንዱ ጥግ ተቀምጠው እየተጎሾ ካሾኩ ውስኪ ይጠጣሉ ።

«ውይ በሞትኩት ! ካዲሳባ ከፀሀይዋ ከተማ ?»

እንዴት ነሽ ውቢ ?
የልጅነት ልቢ ።
እንዴት ነሽ በረሃ?
ስንቱን ያየንበት የሌትዋ ፍስሃ ።
እንዴት ነሽ በሉልኝ ያቺን ውቢ ሰፈር
የታየንባትን የዳንኪራ መንደር ።

«አንድ ስራ አይገድል ። ምን ነው ፤ ለስራ ?» ብላ እንደገና ከት ብላ ትስቃለች ።

«ላስተማሪነት ነው የመጣሁት ።»
«እዚሁ ሱዱ ?»
«እዎን ፤ ላንድ አመት ።»

ከባንኮኒው ሁዋላ የቆመችው ወጣት ይበልጥ ታተኩርበታለች ።

«ውይ በሞትኩት ! ታዲያ አልቤርጎ የለ ።»
«ምን ይሻለኝ ይሆን ታዲያ ?»

«የማታ እንግዳ ተመለስ አይባል ። ሽታዬ ፣ ለዛሬ ሌሊት እንደ ምንም ተቸግረሽ መኝታሽን ብትሰጭው ።» — ከፍ ካለ ማስካካት ጋር ።

ከሽታዬ ክብ ፊት ላይ ሞቅ ካለ ፈገግታ ሌላ መልስ አልነበረም ። ትላልቅ ውብ አይኖችዋ አሁን በርሱ ላይ ሳይሆን በሱ እግር ስር ደብዳ ከሌለው ከሩቅ ተስፋ ላይ ያረፉ ይመስላሉ ። ከፖሊሱ አጠገብ ተቀምጣ

የነበረችው ሴት ፣ «መግን ውቤ በረሃ ፣ መግን እንቺ ሆዬ» ብላ ተወርውራ ድንገት በመነሳት እንዴ ካስካካች በሁዋላ ፣ ከእህል በረንዳ ያመለጠ ኩንታል የሚመስል ሰውነትዋን እያወዛወዘች ዳንኪራውንም ጭምር በአይነት እያስነካችው—

«በሉ ዳኑብ ዋልትዝ . . . በሉ ታንጐ . . . ሩምባ . . .
ማምቦ . . . ቻቻቻቻ . . . ቡጊውጊ . . . ሳምባ

ሮክ—እን—ሮል . . . ካሊፕሶ . . . ማሪንጌና . . . ኮንጋ
ረግጠንበት ነበር ጀምበሪቱ ጠልቃ ሌቱ እስኪነጋ

ደጃቹ ውቤ ሰፈር እንዴት ነሽ በዝና
የቀን ቀን ሽልቤ የለሊትዋ ፋና
የነዝናሽ መንደር የፍቅር ጎዳና

በሉልኝ በሞቴ ። ውቤ በረሃ መግን እንቺ ሆዬ» ብላ ፣ ላንዳፍታ ቆም በማለት ከንፈርዋን በሀዘን ከመጠጠች በሁዋላ ፣ «እንደ ስራ አይገድል ። ለመሆኑ አሁን እንዴት ናት ?» ትለኛለች ።

«ማን ?»

«ውቤ በረሃ ?» ብላው ፣ ግራ መጋባቱን በማየት ፣ «የውቤ በረሃን ዘመን የደረስክበት አትመስልም ። እንዳንተ ያሉ ሎጋ ወጣቶች ድንግል ናቸውን የሰውበት ፣ ደሞዛቸውን የከሰከሱበት ፣ መሬት ሸጠው ብር የመነ ዘሩበት የሞቀ የፍቅር መንደር ነበር ። ጎረምሳ የጠፋበት ወላጅና ዘመድ የዋተተበት — ፍቅር የያዘው በሬ ፣ ጭድ ካየ ሳምንቱ ዛሬ—አይ ዘመን ። አያልፍ የለም ። እንደ ስራ አይገድል አሉ ። የውቤ በረሃ መድን ያልወጣ ለት ጎረምሳ ምኑን ጎረምሳ ይባል ነበር?

«ታዲያኮ እውነተኛ ፍቅር ነበር በኛ ጊዜ ። ዛሬማ የጉልት ገበያ ሆኖአል ነገሩ ሁሉ ። ሙክት ፣ ሽንጥ ፣ ገረወይና ቅቤ በጉዋዳ እየገባ ወር ሁለት ወር ዶጅ ካልተጠና እንዴት ተደርጎ ? 'ስንት ነው? ነይ !' ማለት! አበስኩ ገበርኩ ። ምን ሲደረግ ! የማንን ቅምጥ ማን ወንድ ደፍሮ ሲነካ—ጉድ ይፈላታል እንጂ ። እሱዋም ብትሆን አዩኝ አላዩኝ ብላ ካልሆነ በቀር የት ልትገባ ። ጌታው በበር ፣ ውሽማ በጉዋዳ ።

«እውነተኛ ፍቅር ነበርኮ — የዛሬውን እያድርገውና ። ደሞ የምን ግፈር ! ፍቅር ያሳፍራል እንዴ ? ውቤ በረሃ በሙሉ የእገሊት የእገሊት ቤት በሚል ነበር የተከፋፈለው ። የዝናሽ ቤት እንዳልተባለ ሁሉ ። አሁን ንፋስ ስልክ እንደሚታየው ቫይኪንግስ ፣ ፍሎሪዳ ፣ እማልፌ ፣ ቤርሙዳ ፣ ሀናይ የሚባል ነገር አልነበረም ። በስማችን ነበር ። የምን ግፈር ? እናፍ ርበትም ነበር ። አይ ጊዜ ። አያልፍ የለም ። እንደ ስራ አይገድል» በማለት የውቤ በረሃ ትዝታዋን ስትደረድርለት ቆይታ ፣ «ሆይ ሆይ ባል አለሽ ወይ ? ሸበላይ ገዳዬ ሚስት አለችህ ወይ ። እንዲህ . . . እንዲያ ያደርገን ነበር የበረሃው ቆሌ . . . የበረሃው ዛር ። ምሱ ፍቅር ነበር» ካለችው በሁዋላ ፣

«ያሁኑ ዳንስ እንዴት ነው?» ትለዋለች ።

«አላውቀውም ።»

«እንደ ባህር ውስጥ ቄጠማ መወዛወዝ ፥ እንዳበደ ሰው ባዶ አየር መቡዋጠጥ ፣ ዛር እንደ ያዘው ሰው አንገት ማሽከርከር ነው አሉ ። እስቲ አሳየኝ በሞቴ ።»

«እውነት አላውቅበትም ።»

«የዘመኑ ልጆች የምታውቁት ፖለቲካ ብቻ ነው—ጡጦ ከጣላችሁበት ቀን ጀምሮ ። አይደለም እንዴ?»

«ሰው እንደ ጊዜው አይደል የሚኖረውና የሚያስበው ?» በማለት ከማጉተምተም ሌላ መልስ አልነበረውም ። የመቶ አለቃው ሲጃራውን እየማገ በጢሱ ውስጥ ተጠራጣሪ ትላልቅ አይኖቹን አሻግሮ ሀዲስን ከማየት ሌላ ትንፋሽ አይወጣውም ነበር ። የዝናሽ ትዝታና ጭፈራም አዲስ ነገር ሆኖ የታየው አይመስልም ። ለሁሉም አዲስ ነገር መስሎ አልታያቸውም ። ዝናሽ እንደ ልማድዋ አንዴ አስካክታ በሚቀጥለው ደቂቃ ዝም ብላ ቀረች ። ትንሽ ቆይታ ስትስቅ እንባዋ ኮለል እያለ ይወርድ ነበር ። የወረደው ውስኪ ገና አልተገባደደም ። ምሽቱ ገና ለጋ ነበር—ምናልባት ለሁሉ ውድቅት ቢሆንም ። ሀዲስ ጎኑን ማሳረፍ በጣም አምሮት ውስጥ ውስጡን ሲቁነጠነጥ ፥ ዝናሽ ፥ «እንደ ሰራ አይገድል» ብላ ፥ መለኪያዋን አንስታ ጨለጠችና ፥ «ውይ በሞትኩት ። ኖር ማለትም እኮ ያባት ነው ። ካዲሳባ የመጣ ወጣት ሳይ የበረሃው ዛር ይቀሰቅስብኛል» አለች ።

«መከረኛው ልብሽ አሳረጅ እያለ ነው» አላት የመቶ አለቃው ።

ቀልዱ አልጣማትም ። እርጅና የሚባለውን ነገር ስትሰማ እንደ እሬት የሚመራት ይመስል ፊትዋን ኮስተር አደረገች ። ሀዲስ ጎኑን ማሳረፍ እንዳማረው ሳይወድ በግድ ወንበር ላይ ቁጭ አለ ። ፖሊሱ ፥ «የመቶ አለቃ እሺን እባባለሁ» ብሎት ከተዋወተው በሁዋላ ሲጃራ አውጥቶ ጋበዘው ።

«አላጨስም።»

ውስኪ ጋበዘው።

«ውስኪ አልጠጣም።»

«ውቤ በረሃ የስንቱን ጀዱ አይነጥላ እንገልጥለት ነበር ። ያዲሳባ ወጣት ትምህርት ቤት ነበርኮ ውቤ በረሃ ። የኛ ቅኝት ያልሆነ ማን ነበር ? አሁን እንዳንተ የማያጨሰውና የማይጠጣው ከጥቂት ሳምንት በኋላ አይ የመለኪያ አያያዝ—አይ የሲጃራ አያያዝ ቄንጥ ። ነበር እንዲህ ቅርብ ? እንደ ሰራ አይገድል» ብላ ሩቅ ስትመለከት አሳቡ አብሮአት ሄደ ።

ስሜትዋ እንደ መስተዋት ጥርት ብሎ ታየው ። አሁን ያለችበት ጊዜ ትርጉም አይሰጣትም ። ወደ ፊት የሚባል ነገር ባሳብዋ ውስጥ ያለ አይመስልም ። ህልውናዋ የትናንቱ—ያለፈው ጊዜ ትውስታ ብቻ ነበር ። የትናንቱን የህይወት እሳት ፍም ከምትሞቅበት ከትውስታዋ ምድጃ ዳር ቁጭ ብላ ታየችው—ያለፈ የትናንቱ ህይወት-የትናንቱ እሳት—የዛሬ ትውስታ ።

የሰው ልጅ ትውስታ—እያንዳንዱ ሰው ከትውስታው ምድጃ ዳር ተቀምጦ የራሱን ህልም ሲያልም—እንደ ዝናሽ ፡፡ አሳዘነችው ፡፡

የመቶ አለቃ አሸኔ ውስኪውን ባንድ ትንፋሽ ጨለጠና ሲጃራውን ማግ ፣ ቡልቅ አድርጎ በጢሱ ውስጥ ሀዲስን በተጠራጣሪ ጎረጥ አይኖቹ እያየው ፣ «የዛሬውን ወጣቶች ባታውቂያቸው ነው ፡፡ ካይን ይቀድማሉ ፡፡ በነገር ወፍ ከሰማይ ያወርዳሉ ፡፡ በኛ ጊዜ ምን ነገር እናውቅ ነበር ? ከሲጃራ አቅም አዩን አሳዩን እያልን ነበር ተደብቀን የምናጤሰው ፡፡

«የዛሬዎቹ ጫት ሲቅሙና ሀሺሽ ሲያጤሱ ነው የሚያድሩት ፡፡ መጠጣቸው ደሞ ምን መሰላችሁ ? ቀንዶ አረቄ ወይም ባሮንስ (ጂን) ከጫት ጭማቂ ፤ ከፈላ ቡናና ቪኖ ጋር በትንሽ ስኲዋር ይደባለቅና ያንን ከባልዲ ውስጥ እየጨለፉ፣ ‘ለውጥ . . . ለውጥ . . . መሬት ላራሹ’ ሲሉ ነው የሚያድሩት ፡፡ የምን ጥናት ? የምን ትምህርት? . . » ከማለቱ ፣ ከሩቅ የሴት ጭኸት ጨለማውን እየሰነጠቀ መሰማት ይጀምራል ፡፡

«እየዩ» አለች ዝናሽ፣ «ያቺ የፈረደባት ያኪም የሺጥላ ሚስት ነች ፡፡ ‘ምን ነው ትደበድባታለህ?’ ብለው ምናለኝ መሰላችሁ? ‘አልፎ አልፎ ክርን ካላቀመስኳዋት የጠላሁዋት እየመሰላት ንትርክ ትጀምራኛለች’ አለኝ ፡፡ እውነትም ከዱላው በሁዋላ ሰምና ጨርቅ ነው የሚሆኑት ፡፡ ገላጋይም ይህን አውቆ ነው መሰለኝ ብቅ አይልላትም ፡፡»

የመቶ አለቃ ጆሮውን አቁሞ ጭኸቱን እያዳመጠ ፣ «እዎን ፣ ሀኪም ለሁሉም ችግር መፍትሄ አያጣም ፡፡ ለንትርክ ክርን ፣ በሽታ ለተባለ ነገር ሁሉ መርፌ ፡፡ አይ ሀኪም የሺጥላ !» ብሎ ራሱን ነቅነቆ ዝም አለ ፡፡

ሀዲስ የሴትዮዋ ጭኸት ጋብ እስከሚልበት ድረስ ጠብቆ ፣ በማን ሚስት ማን ያገባዋል ? የሚል ግምት እየወሰደ ፣ «ወጣቱን እንዲህ የሚያደርገው ነገር ምን ይመስልዎታል ?» ብሎ ሲጠይቀው ፡—

መቶ አለቃ ምንም ሳያመንታ ፣ «ጥጋብ ፡፡ ስድነት ፡፡ ጨርሶ መረን መውጣት ፡፡ ሌላ ምናለ !» ሲለው ፡—

«የተስፋ መቁረጥ ምልክት አይመስልዎትም ?» ይለዋል መልሶ ፡፡

«ይበላሉ ፡፡ ይጠጣሉ ፡፡ ገነት ከሚመስሉ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይምነሸነሻሉ ፡፡ ጥጋብ ነው ፡፡ ምን ያድርጉ ፡፡ የምን ተስፋ መቁረጥ ? ጥጋብ ነው እንጂ . . .»

«አምን ፤ እነሱን የቸገራቸው ነገር ላይኖር ይችላል . . .»
«ታዲያስ ?»
«ለውጥ እንዲመጣ የሚፈልጉት ለራሳቸው አይደለም ማለቴ ነው ፡፡»
«ለማን ነው ታዲያ ?»
«ለህዝቡ ፡፡»

«የት ለሚያውቁት ህዝብ ! በሀሺሽ የሰከረ ናላ ምን ህዝብ ፣ የትኛውን ህዝብ ነው የሚያውቀው ? በሀሺሽ ልቦና ቲዎሪ እያነበነቡ ለውጥ ማለት እብደት ነው እንጂ ሌላ አይደለም ፡፡ የትኛውን የሙጀሌ መንቀያ መርፌ

ሰርተው ያሳዩትን ህዝብ ነው ለውጥ የሚሉት ?» ብሎ ፣ ነገሩን ንዴት በተቀላቀለበት ቁጭት በመቀጠል ፡ «አየህ ወንድም . . . ማን ነበረ ያልከኝ ስምህ ? አዎን ሀዲስ . . . ይቅርታ አቶ ስላላልኩህ ወጣት ነህ ብዬ ነው ። አየህ ፡ የትምህርት ቤት ውጫጮች ትምህርታቸውን ትተው ፖለቲከኞችና ዳኞች የሆኑበትን፣ መግዛት ያለባቸው ባለስልጣኖች የሚፈሩበትን፣ መገዛት ያለባቸው ደግሞ በእብሪት ትከሻቸውን የሚያሳዩበትንና ብሄራዊ ህሊናችን የመንደር አሉባልታ የሆነበትን ሁኔታ ለመቀበል አልችልም ። ዲሲፕሊን ያስፈልጋል ። ህግና ዲስፕሊን ለማስከበር ነው የቆምኩት ። ሙያዬም ነው . . .» ብሎ ነገሩን ሳይጨርስ ፣ ሀዲስ ያቋዋርጠውና ፣ «አዎን ፣ ልክ ኖት ። ካነጋገርዎ እንደ ገባኝ ገገርው መግዛት ፣ ተገዢው መገዛት ካቃታቸው ደረጃ ላይ ደርሰዋል ። ታዲያ ለዚህ መፍትሄው ምን የሚሆን ይመስልዎታል?» ይለዋል ።

«ዲስፕሊን ። ከብረት የጠነከረ ዲስፕሊንና ሞራል ። ባገራቱ ምግባር የሚባል ነገር ጠፍቶአል ። ዲስፕሊን የለም ። እነዚህ ከሌሉ ምን አገር ፣ ምን ህዝብ አለ ለማለት ይቻላል?»

ሀዲስ በመቶ አለቃው አሳብ አልተስማማም ። መፍትሄው ያንድ አምባ - ገነን መነሳት ፣ ወይም የጥቂት ሰማእታት መፈጠር ነው ሊለው አስቦ ያሰበውን አሳብ መልሶ ዋጠው ። ፍየል ከመድረስዋ ቅጠል መበጠስዋ አለ ። ሱጌን ከመርገጡ ዘሎ ከፖለቲካዊ ክርክር ውስጥ መግባት አሁን ምን ይባላል ? ተናግሮ የሚያናግር ሰይጣናዊ ተንኩዋሽ ቢሆንስ ? ‘መላ እክት ዝር ከማይሉበት ስፍራ ሞኞች ዘው ብለው ይገባሉ’ ይባላል ። ያበራሽን ጠባሳ ያየ በእሳት አይጫወትም ይሉ ነበር እናቱ . . . ያውም የኢትዮጵያ ችግር መፍትሄ ዲሲፕሊን ነው ብሎ ከሚያምን ፖሊስ ጋር . . . ባፍ ይጠፉ በለፈለፉ ። ስንቱ እንደ ወጣ ቀረ የገባበት ሳይታወቅ ? በዩኒቨርሲቲ ምድረ ግቢ ዋእሳት ላንቃ የነበረ ፣ ስንቱ ስራ በገባ ማግስት ለጋ ቅቤ እንዳላሉት ህፃን እንደበቴ ለዝቦ ቀረ ? እና ፣ ቢሆንም ፖለቲካ . . . ፖለቲካዊ ክርክር በየደረሱበት . . . መለኪያ አንስተው ባስቀመጡ ቁጥር . . . ፖለቲካዊ ክርክር ከሰላምታ በፊት ። የምንተነፍሰው አየር ፖለቲካ ፤ የምናልመው ህልም ፖለቲካ ። ግን የሚገርመው ነገር ማንም ምንም አያደርግም ። ቁና ሙሉ መፍትሄ—ቅንጣት ያህል ተግባራዊ ርምጃ የለም ። መስዋእት መሆን እንደሚያስፈልግ ሁሉም አፉን ሞልቶ ይናገራል ። ግን ለመስዋእትነት አንገቱን የሚሰጥ የለም ። ምግባር ፣ ተግባር ፣ መስዋእትነት የሚጠበቀው ከራስ ጀምሮ አይደለም ። ከሌላው ነው ። ፈሪ ፣ ወኔ የሌለው ህዝብ ማለት ብቻ ። መፍትሄ የለኝም ። ሶስት ሽህ ዘመን ትርጉዋሜ አሻፈረኝ ብላ ለቆየች አገር መፍትሄ የለኝም—ኢትዮጵያ ታበፅህ እደዊሃ ሀበ እግዚአብሄር። መና ከሰማይ ይወርዳል ! . . .

«ውተት በጨለማ ታበላሻላችሁ ፤ ቀን እንዲህ ይገፋል እኔ ላሳያችሁ።» ብላ ዝናሽ ውስኪዋን ጨለጠች ።

«ጥሩ ዲሲፕሊን ያለህ ትመስላለህ» —መቶ አለቃ አሽኔ ነበር ።
«እንዴት ?»

«አትጠጣም ። አታጨስም ። ጠንቃቃና እንደብተ ቁጥብ ትመስላላህ ፣ እፍሮም አይደለህም» አለው ።

«ሴትም ነክቶ የሚያውቅ አይመስልም» ብላ ዝናሽ አስካካች ።

ሀዲስ እንደ ማፈር ብሎ አይኑን ሰበረ ።

«ውይ ! እዩት ደሞ ሲቅለሰለስ ። የደም ገንቦዬ አይዞህ ። ምን ይደረ ጋል ? ተላለፍናት በመንገድ ! አይ ይች ህይወት ! ! እንደ ሰራ አይገድል» ብላ በሀዘን ከንፈርዋን መጠጠች ።

ሽታዬ ከአይን ሌላ ሰውነት ያላት አትመስልም ። አይን የነፍስ መስተዋት ነው ያለው ማን ነው ? በአይንዋ ላይ የውስጥ ስሜትዋን ማን በብ ይቻል ነበር ። ድንገት ወደ ጉዋዳ ጥልቅ ብላ ጠፋች ።

«ካቶ ይርጋ እለሙ ጋር ሳትስማሙ አትቀሩም» አለ የመቶ አለቃ አሸኔ ። «ወደ መቱ ወጥቶአል ። ምናልባት ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ይመለ ሳል ። ትምህርት ቤቱ ግን በላያችሁ ላይ አንድ ቀን ሳይወድቅ አይቀርም ። በውነት ያሳዝናል ። ነገሩን ሲያዩት ቀልድ ነው የሚመስለው . . .»

«አይ ወጣት ! ሰውነቱ ርጥብ ፣ እጁ ደረቅ ። ስን ??ን እየነው እቴ» ዝናሽ ነበረች ።

«እንዴት ነው የምንስማማው?» አለ ሀዲስ ።

«አቶ ይርጋ ጨመት ያለ ሰው ይወዳል ። በትምህርት ቤቱ ከመጡ በት ግን አይኑ ባንዴ ነው ደም የሚለብሰው . . . »

«ለምን ?»

«እንጃ ። እኔንም ይገርመኛል ።»

ሀዲስ ደከሞኛል በማለት ይቅርታ ጠይቆ ሊነሳ ሲል ሽታዬ እንዲጋ ጣሚ ከጉዋዳ ብቅ ብላ መኝታው የተዘጋጀለት መሆኑን ነገረችውና ወስዳ ክፍሉን አሳየችው ። አንድ ከፍ ያለ የሽቦ አልጋ ፣ አንድ ሌላ ተጣጣፊ የመ ንገድ አልጋ — ሁለት አልጋዎች ነበሩ ። ከፍ ያለውን የሽቦ አልጋ አሳየ ችው ። በኩራዝ ብርሃን ትላልቅ አይኖችዋ ይበልጥ ትላልቅ ሆነው ታዩት ። የሁለቱ ማዞፍ ጥላ ከፊሉ በጋዜጣ ተለብዶ ፣ ከፊል ጎኑ ልስኑ ከሚታየው ግድግዳ ላይ ተላለፉ ።

በጣም ደክሞት ስለ ነበረ ጊዜ አላጠፋም ። ዘሎ ከመኝታው ውስጥ ገባ ። ሽቦ አልጋው ያረገርጋል ። ኩራዝዋን አጥፍቶ አይኑን ከመክደን አንጵልፍ ይዞት ጭልጥ ብሎ የሚሄድ መስሎት ነበር ። እንዳሰበው አልሆ ነም ። የድቤ ድምፅ ድው . . . ድው . . . እያለ ጨለማውን እየሰነጠቀ ከሩቅ ይሰማል ። እጆቹን ተንተርሶ ፊጠው በቀሩት አይኖቹ ጨለማውን ይዳስስ ጀመር ። ካዲሳባ ርቆ መጥቶአል ። ግን ከወይዴትም ርቆ አለመገኘት ፣ እንዲህ አይነቱ ስሜት ነበር ያደረበት ። ብቻውን—አንድ ራሱን ። ተመልሶ የሚገባበት ቤት አልነበረውም ፤ የሚናፍቃቸው ዘመዶች አልነበሩትም ። የናቱን ድሳሳ ጎጆ ለአትዬ በለጡ ሰጥቶአል ። በተወላቸው ገንዘብ ቀይ አፈር ሸምተው ቀይ ሸክላ ፣ ሸክላ በሚመስለው ረጅም አጥንታም እጃ ቸው ሲጠፈጥፉ ታዩት . . . አዲሳባ ምን ቀረው ጭር ካሉ ከሁለት መካነ መቃብሮች ሌላ ? አንድ ራሱን ብቻና ነፃ መሆን—በዚህ ሰፊ ፣ ሰፊ አለም ። ብቸኛው መንፈሱ እንደ ንስር አሞራ ከፍ ብሎ በኢትዮጵያ ምድር ላይ

ተንሳፈፈ—ያፍሪቃ ጣራ የሆኑትን ጥንታዊ ተራሮችና ሸለቆዎችን እያቋ ዋረጠ ። እነዚያ ኩሩ ተራሮች ። እነዚያ የኩሩ ህዝብ የተፈጥሮ ምሽጎች የሆኑት ጥቁር እንቁ ተራሮች —

ያባት አገር ዱሬ
የናት አገር ዱሬ
እገባብሃለሁ የትም ዙሬ ዙሬ ።

እያለ ዱሩንና ተራሮቹን አለኝታ ፣ መከታና ጋሻ አድርጎ ፣

ገለሌ ምሳው ፉጨት ራቱ
መለቃለቂያው ደም ራጨቱ ።

ብሎ በመፎከር አጥንቱ እንደ ተራራ ከፍ ብሎ እስኪታይ ድረስ ዝንተ አለም የተጋደለበት ። የለም—እነዚያ ኩሩ ተራሮች ካፈርና ከድን ጋይ የተፈጠሩ አይደሉም ፤ ለዘመናት ከምድሪቱ ላይ ከወደቁት ጀግኖች ክቡር አጥንት እንጂ ! ነውኮ ። በተራሮቹ ወጣ ገብ ፊት ላይ የኢትዮጵያዊ አትንኩኝ ባይ አይበገሬ መንፈስ ተፅፎ ይነበባል ። እንቅልፍ የባሰውን ሸሸው ። መርዳሳ ከመቱ ሱዳ ዝንተ አለም በዚያው መንገድ ላይ . . . መም ጣትና መሄድ — ዝንተ አለም ። በህይወት መንገድ ላይ መተላለፍ አንዱ ሲሄድ ሌላው ሲመጣ ። ወዴትም የማይወስድ ዝንተ አለማዊ የህይወት ጉዞ ፍተሃት ፤ ከሰው ልብ ውስጥ የማይጠፋ ዘለአለማዊ ተስፋ . . . ግን ፤ ማን ነው ህይወት ከንቱ ናት ያለው ? !

እንቅልፍ ለምን እምቢ እንዳለው ሲያስብ ፣ በህይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሴት መኝታ ውስጥ ገብቼ በመተኛቴ ይሆን ? አለ ። የሴት ምትሃታዊ ጠረን—ከሳማርካንድ ሽቶ የጣፈጠ—ከገሃነም እሳት የገነነ የሽታዬ ሽቶ ሸተተው ። የሚተነፍሰው አየር ሁሉ ሽቶ ሆነበት ። መኝታው ውስጥ እንደ ተገላበጠ በሩ በቀስታ ሲከፈት ሰማ ። ግን ዘይት እይቶ የማያውቀው የበሩ ማጠፊያ ዝም አላለም ። ሽታዬ ነበረች ። ትንፋሹን ውጦ ከመኝታው ውስጥ አደፈጠ ።

በጨለማ ልብስዋንና የጡት መያዣዋን አወላልቃ ባጭር የውስጥ ልብስ ብቻ ከተጣጣፊ የመንገድ አልጋው ላይ ወጥታ ተኛች ። ጡቶችዋ ለጨለማው አምላክ ምህላ ቆመው በሀሳቡ ታዩት ። ትንፋሹን እንደ ዋጠ ቀረ ። እኔ የማስበውን ታስብ ይሆን ? እኔ የሚሰማኝ ይሰማት ይሆን ? አንዱ የሚያስበውን ሌላው እያሰበ ፤ አንዱ የሚሰማውን ሌላው እየተሰማው በመንገድ ላይ የመተላለፍ ጣጣ !

አይኖችዋን ባያይም ከጨለማው ጥልቀት ውስጥ የምታየው ነገር ይታየው ነበር ። የምታስበውን ባያውቅም ፣ ምን እንደምታስብ የሚያስብ መሰለው ። የሳማርካንድ ሽቶ እንዳለ በሙሉ አየሩ ላይ ድንገት ፈነዳ ። የገሃነም እሳት ነደደ ። ልቡ ስልተ—ቢስ ሰይጣናዊ ከበሮ ከአካባቢው ድቤ ጋር ይመታ ጀመር ።— የተከነነች ነፍስ ! ብሎ ሲገላበጥ ፣—

«እንቅልፍ አልወሰደህም እንዴ ?» አለችው ።

ሰውነቱን ላብ እያጠመቀውና የማያውቀው ስሜት እንደ ጉንዳን እየወረረው ፣

«ይሆስደኛል» አላት ።

«እኔስ እንቅልፍ ጥርግ አርጎ የወሰደህ መስሎኝ ነበር ።»
«የምን ድቤ ነው የሚሰማው?»
«ያባ ጨፌ ?»
«ማን ነው እሱ?»
«የሱጺ አዋቂ ናቸው ።»
«ቃልቻ ማለትሽ ነው ?»

«እንደሱ፣ አይባልም» ካለችው በሁዋላ ፤ «እውነት ላንድ አመት ብቻ ነው የመጣሽው ?» ብላ ጠየቀችው ።

«አዎን ።»
«ከዚያ በሁዋላስ ?»
«ወደ ዩኒቨርሲቲ እመለሳለሁ ።»
«ምን ነው ትንፋሽህ ቁርጥ ቁርጥ ይላል ?»

ዝም አለ ። ድቤው ይሁን ወይም የልቡ ትርታ የትኛው ድው ድው እንደሚል ለይቶ ለማወቅ አልቻለም ። ከአባ ጨፌ ድቤ ድምፅ በላይ የእሱ ልብ ትርታ ገንኖ የሚሰማት ስለ መሰለው በመጨነቁ የልቡ ትርታ ይበልጥ ይመታ ጀመር ።

«እውነት ሴት ነክተህ አታውቅም ?» አለች ፤ በተሰባበረ ድምፅ ።
«ምን ማለትሽ ነው ?» አላት በታፈነ ጉሮሮ ።
«እትዬ ዝናሽ ሲሉ ሰምቼ ነው . . .»
«እና ?»

መልስ አልሰጠችውም ። ዝም አለች ። ያቺ የጥቂት ሴኮንዶች ዝምታ እድሜ ልክ ያህል ረዘመችበት ። የልቡ ምት ፈጠነ ።

ያባ ጨፌ ድቤ ድቅድቅ ካለው ጨለማ ጋር ትንቅንቅ ይዞ ሲገን ደረቅ ጨለማ ድንገት እንድቁዋያ እሳት ተቀጣጥሎ ወከክ እያለ ይነድ ጀመር — ፍቅር ጨለማን እንደማያውቅ እየመሰከረ ።

ድንግል መሬት ተገለበጠ . . .

# ክፍል ፫

ሽታዬ ጠዋት በማለዳ ነቅታ ከወፎች ጋር ታንጎራጉር ነበር ። ከወፎቹ ጋር ሚጉሳው አብቦአል ዛሬ እያለች የምትዘፍን መሰለው ። ከሚጉላ ቤት ገና እንዳልወጣች ሙሽራ አይኑን ሰብሮ አይንዋን እየሸሸ በማለዳ ተነስቶ የኪራይ ቤት ፍለጋ ሲወጣ ሽታዬ ፣ በጀርባዋ እንደ ተጋደመች ከትራስዋ ላይ ተንዠርግጎ ከተበተነው ከረጅም ፣ ጥቁር ጠጉርዋ ውስጥ እያንዳንዱን ነዶ እንደ ቀጭን ፈታይ በረጅሙ እየመዘዘች ታንጎራጉር ነበር ።

«ጉሮ ወሸባዬ—እንዲያ እንዲያ ሲል ነው ግዳዬ ።»

የምትል መሰለው ። የምታንጎራጉረው ዜማ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ አልፈለገም ። ደንታ አልነበረውም ። በልቡ ውስጥ አንድ አይነት ፀፀት አድሮበት ነበር ። ቀዝቃዛው የመስከረም አየርም ሆነ ምድረ አለሙን በወርቅ የተሰገጠ አረንጉዋዴ ከፈይ ካባ አስመስሎ የተነጠፈው የመስቀል አበባ ውበት ፣ ያደረበትን ፀፀት ከልቡ ውስጥ ሊያወጣለት አልቻለም ። በሙሉ ግርማ ሞገስዋ ካድማስ ላይ በመንጣለል ፣ የአድማሱ አንድ አካል መስለው የቆሙትን ተራሮች ፣ ወርቅ ድብልቅ የሆነ ሰማያዊና ሀምራዊ ቀለም መቀባት የጀመረችውም የማለዳ ፀሀይ ልቡን አላሞቀችውም ። የሽታዬ ሽቶ ላዩ ላይ እንዳለ ነበር ።

ሱዱ ከእንቅልፍዋ ገና አልነቃችም ። ጥቂት ውሾች እያነፈነፉ ስራ ያለባቸው ይመስል ኩስ ኩስ በማለት ይጣደፋሉ ። ባልና ሚስት አሚና ዎች ካንድ ቤት አጥር ስር ተከናንበው ቁጭ ብለው በመቀባበል ያቅራራሉ። የተቦጫጨቁ ቡቱቶዎች የሚጎትቱ ለማኞች ካንዱ ቤት ወደ ሌላው በመ ሄድ ከውሾች ጋር ምርር ያለ ጥል እየተጣሉ ይለምናሉ ። ካቡዋራማው የመኪና መንገድ ዳር ግራና ቀኙን ይዘው እንብድደው እድሜ የሚለምን ከሚመስሉት አያሌ የሳር ጎጆዎች መካከል በኮባና በሰንሰል አጥር የተሸ ፈኑ የቆርቆሮ ቤቶች አልፎ አልፎ ይታያሉ ። ጠባብ የእግር መንገዶች ከዋናው መንገድ እንደ ቀጭን የደም ስር እየተገነጠሉ ወደ ሩቅ መንደሮች ያመራሉ ። ማታ የመጣበትን የእግር መንገድ በአይኑ ተከትሎ ትምህርት ቤቱን ከሩቅ ተመለከተ ። ከትምህርት ቤቱ ባሻገር ካለው ኮረብታ ላይ የኮራ ጥንታዊ ቤት ተንጣሎ ይታያል ። በቤቱ ትይዩ ከሚገኘው ሌላ ኮረ ብታ ላይ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን አፀድ የፀሀይዋን ጮራ እየተቀበለ መልሶ ያንፀባርቃል ።

በዚች እግዜር በረሳት ትንሽ መንደር ውስጥ አንድ አመት መቆየት እንደ ዘመናት ርቆ ታየው ። ራሱን ፣ መስቀለኛ ከሆነ ከህይወት ትምህርት ቤት እምብርት ላይ ቆሞ እንዳለ አድርጎ አየ ። እርቃኑን የቆመ ጥሬ ህይ ወት ፣ ገሃድ የወጣ የህይወት ትምህርት ቤት ። ህይወትን ፊት ለፊት መጋ ፈጥ—ድፍረትን ምንኛ ይጠይቃል ! በማለት በዚያን ሰአት የቤት ኪራይ ፍለጋ የት እንደሚሄድ ስለ ጠፋው ካደረበት ቤት ተመልሶ ገሰ ።

«ውይ ! የት ጠፋህ ?»

ሽታዬ ባታንጎራጉርም አሁንም የምታንጎራጉር መሰለችው ። የለበሰችው ያገር ልብስ ዳሌዋን አኩርቶታል ፤ ግን ከአይንና ከጠጉር ሌላ ሙልክ አልነበራትም ። ወደ ላይ እንደ መቀለስ የሚለው አሹዋሬ አፍንጫዋ አላስደሰተውም ።

እያንጎራጎረች ቁርስ አቀረበችለት ። ጤና አዳም ያለበት ቀዝቀዝ ያለ እርጎ በትንሽ ሚጥሚጣ ፣ በሽንኩርት የተጠበሰ ፍርፍር እንቁላል በእንጀራ ፣ በቀረፋና በቅርንፉድ ያበደ ትኩስ ሻይ—ሳተ አድርጎ በልቶ ከጠጣ በሁዋላ ፣ «የሚከራይ ቤት ይገኛል ?» ብሎ ጠየቃት ። አይንዋን እየሸሸ ።

በምን አይን እንደምትመለከተው ባያውቅም ፣ ትክ ብላ ትመለከተው ነበር ።

«ምናስቸኮለህ ?» አለችው ።

«መቼም ሁልጊዜ እዚህ አልኖር ። ቤት መፈለግ አለብኝ ። አይደለም ?»

ረጅም አንገትዋን ዘለስ አድርጋ ስታስብ ቆየችና ፣ «እሱስ ነው ። ብቻ . . .» ከማለትዋ ፣

«ብቻ ምን ?» አላት ቸኩሎ ።

«እዚህ የሚከራይ ቤት ማግኘት ችግር ነው ። የሳር ጎጆ ብቻ ነው ያለው—እሱም ቢገኝ ። ምናልባት ፊታውራሪ ተካ የሚከራይ ቤት እንዳላቸው . . .»

«ይኖራቸዋል ?»
«ታውቃቸዋለህ እንዴ ?»

«የለም አላውቃቸውም ። የሚያውቃቸው ሰው ደብዳቤ እንዳደርስላቸው ልኮኛል ።»

«ውብ የሆነች ልጅ አላቸው . . .»
«አይናለም የምትባል ?»
«ታውቃታለህ !»
«የላከኝ ሰው ስለ እስዋ አጫውቶኛል ። ዘመዳቸው ነው ።»
«የመቶ አሊቃ አሸኔን ማታ አይተሽው የለም ?»
«አዎን ። ለመሆኑ ማን ነው እሱ ?»

«የወረዳው ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ ነው ። ትንሽ ዘውድ የጫነ ንጉስ ነው ለማለት ይቻላል ። ታዲያ ይሽውልህ ፣ ያገር ሽማግሌ ይዞ ፊታውራሪን እያስቸገረ ነው» አለችው ።

«አይናለምን እንዲድሩለት ?»

«ታዲያ ሽማግሌ ለምን ይላካል ?» አለች እየሳቀች ። ጥርሶችዋ ዘርዛራ ነበሩ ። ንቅሳቱም ሸጋ ነበር ።

«የመቶ አሊቃ የወይዘሮ ዝናሽ . . . እ . . . መስሎኝ ነበር» አላት ።

«ነው ። እንክት !»

ተአምር አያልቅም ብሎ ፣ «ፊታውራሪ ለኔም አንድ ቤት ቢድሩልኝ ምናለ ታዲያ ?» አላት ፣ ጥቁር ቆብ መስሎ ሰፋ ካለ ግንባሩ ላይ የሚደፋውን ዞማ ጠጉሩን በእጁ እየቆፈረ ።

«ምልቶአቸዋል ። ቡዱ የሚገኙት ቤቶች ግማሾቹ የእሳቸው ናቸው ። ብዙ ደጃፍ ቤት አላቸው ። እኛም የምንኖርበት ይሁ ቤት የእሳቸው ነው ። አብዛኛው የሱጁ መሬትም የእሳቸው ነው ። የቡናና የእህል ምፍጮዎችም በብዛት አሉአቸው ። የቡና ንግድ ፣ የጨው ንግድ ፣ የጣቃ—ምን የማይገቡበት ነገር አለ ብለህ ። ያላቸው የቀንድ ከብት ምኑ ቅጡ—ተቆጥሮ አያልቅም ። ታዲያ ደግ የደግ መጨረሻ ናቸው ። ከጠባይና ከትህትና ጋር ነዋ ለዚያውም ። ደህው 'አባ ብያ' ነው የሚላቸው ። ያገሩ ባላባት አይደሉ ?» አለችውና ፣ እንደ ማንጎራጎር እያላት ፣ «ዛሬ ቀኑ ብራ ሆኖአል ። ደስ ደስ ይለኛል ። በድንገተኛ መውደድ ታምናለህ ? ዛሬ ከሁሉም ነገር ጋር ፍቅር ይዞኛል» ብላ ፣ ከረጅም ጠጉርዋ ውስጥ አንዳንድ ነዶ ወደ ታች እየመዘዘች ታንጎራጉር ጀመር ። ጣቶችዋ አሜጭር ሆነው ደህና ቀን ያላዩ ፣ ስራ ያዶለዶማቸው ይመስላሉ ።

ያስር ብር ኖት አውጥቶ ሊሰጣት ሲል በመጀመሪያ እንደ መደንገጥ ፣ ቀጥሎ እንደ መገረም ከዚያም እንደ መቆጣት አደረጋት ።

«ምን ሆንሽ ?»
«ሂድና ሽርሙጣህን ፈልግ !» አለችው ።

አንቺ ምን ሆንሺና ! ሊላት ፈልጎ ነበር ። ተአምር አያልቅም እያለ የአደራ ደብዳቤውንና ስጦታውን ይዞ ወጣ ። ወጥቶ የትም አልሄደ ። ያ ከትምህርት ቤቱ ባሻገር ከጉብታው ላይ ያለው ጥንታዊ ግቢ የፊታውራሪ ተካ ካልሆነ የማ ሊሆን ይችላል ! በማለት በቀጥታ ወደዚያ አመራ ። የሱጁ አቡዋራማ መንገዶች በሙሉ ከየአቅጣጫው የሚያመሩት ወደዚያ ነበር ።

የቤተኛ አዳሪ ልብ - ስር ብር ነው ሲሉ ሰምቼ ምን ነው ? በማለት ከጆርባው ጎበጥ ጎበጥ እያለ ፣ ረጃጅም እግሮቹን ጎተት ጎተት እያደረገ ሲሄድ ከትምህርት ቤቱ አጠገብ እንደ ደረሰ ሳንዳፍታ ቆም አለ ። ባለፈው ምሽት ልብ ያላደረገው ተራራ የሚያክል ወርካ ከትምህርት ቤቱ በስተጀርባ ራቅ ብሎ ይታያል ። ደረቱን ወደ ሰማይ ገልብጦ ከቆመው ወርካ ጥላ ስር የተሰገጠው የትምህርት ቤቱ ህንፃ ባንፃሩ ኢምንት ሆኖ ይታያል ። ምድረ ግቢው እንደ መቃብር ጭር ብሎአል ። ንፋስ የነቀለው ቆርቆሮ ብቻ ነበር ! የሞት እንጉርጉሮ ድምፅ የሚያሰማው ። ቆርቆሮው በሙሉ ዝጎ ፣ የሶስት ሺህ ዘመን ዝገት የሚያንፀባርቅ ይመስላል ። ምርጊቱ የፈረሰው የቤቱ ግድግዳ እንደ ቆማጣ ቁስል አፍጦ አይን ይወጋል ። ቀለምዋ ጠፍቶ ተበጣጥሳ ልታልቅ የደረሰችው ባንዲራ ከረጅም አጣና ላይ ጣእር ይዞአት በመጨረሻ ትንፋሽዋ የምትውለበለብ መስላ ታየችው ።

የሚያሳዝን ሙዚቃ ከህልውናው ጥልቀት ውስጥ ፈልቆ ሲንቆረቆር ሰማ ። ልቡ በከባድ ሀዘን ተሞላ ። በደመ - ነፍስ ረጃጅም እጆቹን ወደ ላይ አንስቶ ተመለከታቸው ። ረጃጅም እጆቹን የት እንደሚያደርጋቸው ሁል ጊዜ ግራ ይገባዋል ። ለይስሙላ ካልሆነ በቀር ይህ ትምህርት ቤት አይደለም እያለ በመተከዝ አቀበቱን ተያያዘው ። ዳገቱን እየሰገደ ወጣ ። ፊውዳላዊ ባላባቶች መኖሪያ ቤታቸውን ከኮረብታዎች አፋፍ ላይ የሚሰሩት

ሆን ብለው ከሩቅ ለማስገድና ወደ ላይ ለመታየት ሳይሆን አይቀርም በማለት ቁርጥ ቁርጥ በሚለው ትንፋሹ እየተራገመ ካፋፍ ላይ ብቅ ሲል— የፊታውራሪ ተካ ግቢ ጥንታዊ ግርማ ሞገሱን በኵራት ተላብሶ ፊት ለፊት ታየው ።

ከጥርብ ድንጋይና ከጥርብ ሳንቃ የተሰራው ዋናው ባለ አንድ ፎቅ ህንፃ ፡ በሶስት ዙር ጥቁር ድንጋይ ካብ ተከቦአል ። ከፊት ለፊት የሚታየው የህንፃው ጣራ የፒራሚድ ቅርፅ ይዞ ወደ ላይ እንደ መተኮስ ይልና ፡ ግራና ቀኝ ሰፊ ክንፉን ይዘረጋል ። የህንፃው ክፈፍ ከእንጨት በተሰሩ ልዩ ልዩ ቅርፃ ቅርፆች አጊጦ ሲታይ ፡ የምስራቃውያን የእጅ ሙያተኞች ጥበብ በትእግስት የተፈተነበት የኪነት ስራ ይመስላል ።

ፈራ ተባ እያለ ወደ መጀመሪያው የውጭ በር ሲጠጋ ፡ የጎፈሬው ጥላ ከፀሀይ የሚከልል የሚመስል ጠይም ፡ ረዘም ያለ ወጣት ኩታውን እንዳደገደገ መጥቶ ለጥ በማለት እጅ ይነሳዋል ። እንደ ላስቲክ እየተሳበ ጎንበስ ቀና ሲል እንዲያው አጥንት ያለው አይመስልም ።

«ካቶ ታፈስ ዘንድ ለፊታውራሪ ደብዳቤ ይዤ ነበር የመጣሁት ።»
«ከየት ?»
«ካዲሳባ ።»

እንደ ገና ለጥ ብሎ እጅ ነሳውና ሁለቱንም እጆቹን ዘርግቶ እንዲከተለው ከጋበዘው በሁዋላ ፡ የያዘውን ረጅም ዘንግ ከመሬት ላይ ተከል ነቀል እያደረገ ቀደመው ። በመጀመሪያ ፡ በሚቀጥለውና በመጨረሻው አጥር ውስጥ ኩታዎቻቸውን አሸንፍጠው ቆመው የሚተክዙ ፡ ወይም በጣም ዝግ ባለ ድምፅ እርስ በርሳቸው የማያወሩ ጉስቁል ያሉ ሰዎች ተኮልኩለው ይታዩ ነበር ። የምድረ ግቢው ንፅህና እንጀራ ዘርግተው ቢበሉበት የማያፀይፍ ፡ ፀጥታው መርፌ ከመሬት ብትወድቅ የምትሰማበት ይመስላል ። ያካባቢው ግርማ ሞገስ ያስፈራል ፤ ሳይወዱ በግድ እየተጫኑ ያስገዳል ።

ሲረግጡት ስሞታው አይጣል በሆነ የሳንቃ ደረጃ ወደ ፎቅ ወጥተው ከሰገነቱ ላይ ሲደርሱ ፡ ይመራው የነበረው ወጣት አጋፋሪ ወደ ሁዋላ እንዲቆይ በእጁ አመልክቶት ወደ ውስጥ ዘው ብሎ ገባ ። ከሰገነቱ ላይ መላ ሱዱ ከስር አደግድጋ ትታያለች ። ከበስተግራ ፡ ሽታዬ እንደ ነገረችው ጥንታዊት ሱዲንና ሰንበተ ጉዳ የሚባለውን አዲሲቱን ሱዱ ለሁለት ከፍሎ የሚወርደው የእልቄ ወንዝ ሽለቆ ሽለቆውን ይዞ እንደ እባብ እየተጥመለመለ ወደ ገባ ወንዝ ይወርዳል ።

የሀዲስ አይን ፊቱ በተዘረጋው የተፈጥሮ ውበት ፈንቅዞ ሳይጠግብ ወጣቱ አጋፋሪ ተመልሶ መጥቶ እንዲገባ እጆቹን ዘርግቶ ይጋብዘዋል ፡ ትልቅ አዳራሽ ነበር የዋጠው ። ካዳራሹ መጨረሻ ላይ ካለው መስኮት አጠገብ ካለች አንድ ድንክ አልጋ ላይ ብድግ ብለው በትህትና የተቀበሉት ጠጉራቸው ብን ብሎ የሳሳ ፡ ብስል ቀይ አጭር ቀጭን ሽማግሌ ነበሩ ። በአእምሮው እንደ ቀረፃቸው ግዙፍ ፊታውራሪ ሆነው አላገኛቸውም ። አይኑን ማመን እያቃተው ያደራ ደብዳቤውን አውጥቶ ሲሰጣቸው ፡ እንደ ስጋ አይሎን ከሩቅ አነጣጥሮ የሚመታ በሚመስሉት አይኖቹ ትክ ብለው ንመለከቱት ነበር ። ወደ ውስጥ ዘልቆ ከሚመለከተው አይን ፊት ፡ ውስጡ

የጠራ መስታወት ሆኖ ሁሉን ነገር ግልጥልጥ አድርጎ የሚያሳይ ስለ መሰለው ፥ ወኔውን ከፊታውራሪ ሰውሮ የሚደብቅበትን ቦታ አጣ ። ብብቱ ሲረጥብ ተሰማው ።

«ይሄ ደግሞ ለ . . . ለአይናለም የተላከ ነው» አላቸው ።

እንዲቀመጥ ባይጋብዙት ኖሮ ጉልበቱ ሲከዳው ትንሽ ቀርቶት ነበር ። ባደረበት ፍርሃት ፥ ምናባቱ ያስፈራኛል በማለት ራሱን መልሶ ቢታዘብም፣ ፍርሃቱ አልለቅ አለው ። እነዚያ መከረኛ ረጃጅም እጆቹን የሚከትበት ቦታ በማጣቱ ተራገመ ። ወዲያውኑ ክብሳታቸው ስታቴ ድስት መስሎ ከትንሽ ጭንቅላታቸው ጉብ ያለ ፥ ወፍራም አጭር ቄስ እየተድበለበሉ ገቡ ። ቁና ቁና እየተነፈሱ ከደረት ኪስ በቀይ ግምጃ ጨርቅ የተጠቀለለ ወርቅ ቅብ መስቀል አውጥተው አሳለሙ ። ላሳልመው ወይስ ልተው ? እያሉ እንደሚያመነቱ ሀዲስ ቢገባውም አላደፋፈራቸውም ። የቄስ ልጅ ሆኖ የቄስ መስቀል ባየ ቁጥር ድንገት ከውስጥ አንድ ነገር ስለሚመታው ሰውነቱ ይቆጣና ጠጉሩ ይቆማል ። በህፃንነቱ ያባቱን መስቀል እያወጣ ፥ በሱ መጫወት ደስ ይለው ነበር ። ታዲያ መምሩ መስቀሉን ከእጁ ነጥቀው ፥ ያደረበትን መጥፎ ሰይጣን ሊያስለቅቁት በዚያው መስቀል ጭንቅል ጭን ቅላቱን ይሉት እንደ ነበር ፥ መስቀል ባየ ቁጥር ትዝ ይለዋል ። በመስቀል መጫወት ምርቃቱ በመስቀል መገጨት ነበር ።

ፊታውራሪ ደብዳቤውን እየከፈቱ ፥ «ካዲስ አበባ ነው የመጣኸው ?» አሉት ።

ምናልባት እንደዚያ ያለ ወፍራም ድምፅ ሰምቶ፥ እንደዚያ ያሉ ልምጭ መሳይ ረጃጅም ጣቶች አይቶ እንደማያውቅ እየማለ ፥ «አዎን» ይላቸዋል ።

«ከፀሀዩ ንጉስ ፀሀያማ ከተማ?» አሉ መምሩ ፤ መስቀሉን ከደረት ኪሳቸው እየመለሱ ፥ «እንደ ኤደን ገነት ቀን ቀርቶ በመንፈቀ ሌሊት ብር ሃን የማይለያት . . . »

ፊታውራሪ ከሚያነቡት ደብዳቤ ላይ ላንዳፍታ ቀና ብለው ፥ «እኛ በምድረ በርባሮስ ነው የምንኖረው ማለትዎ ነው መምሬ መሀሪ ?» አሉ ዋቸው ።

«በምን ሀጢአታችን ? የኤሌክትሪኩ ብርሃን ትዝ ብሎኝ እንዲያው ለነገሩ አልኩ እንጂ !»

«እንዴት እንደምናበራው ብናውቅበት ብርሃን በያንዳንዳችን ልብ ውስጥ ነው» ብለው እንደ ገና ላንዳፍታ ከደብዳቤው ላይ ቀና በማለት ጉዋዳ ወደሚያስገባው በር አይናቸውን ወርወር አድርገው ንባባቸውን ከመቀጠላቸው ወጣቱ አጋፋሪ ሶስት ብርሌ ጠጅ ይዞ ከተፍ አለ ። በምን ቱጥንቁጥ እንዳዘዙት ምስጢር ሆነበት ።

ጠጁን አልወሰደም ። በእምቢታ እጅ ነስቶ ዝም ማለቱን ፊታውራሪ ነዩ ገ.ዜ ፥ «ጠጣው እንጂ ። ንፁህ የማር ጠጅ ነው ። ደረቅም አይደል ። ?ስኩዋር ጠጅ!መስሎህም እንደሆን አትፍራ» አሉት ።

ሀዲስ ጠጅ ጠጥቶ የማያውቅ መሆኑን ገለጠላቸው ።

«የከተማ ልጅ አረቄ ነው የሚወደው ።»—መምሬ መሀሪ ነበሩ ።

«እሱንም አልጠጣም» አለ ።

ፊታውራሪ እንደ ገና ቀና ብለው ሲመለከቱት እይቶ አይኑን ሰብሮ አንገቱን ወደ መሬት ደፋ ። ውስጡ ተወራጨ ። እንደ ገና ውስጡ ምንም ሳይደብቅ ሁሉን ነገር ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ መስታወት ሆኖ ታየው ።

«ሻሂስ ?»

በእሺታ እጅ ነሳ ።

«የልብ ቃር» አሉ መምሬ ፣ የለፋ ጠይም ቆዳ የሚመስለውን ፊታቸውን ጨፍግገው ። አፋቸው በጢም ተሸፍኖ የት እንዳለ አይታይም ።

ፊታውራሪ ደብዳቤውን እያጣጠፉ ፣ «ከታፈሰ ጋር ትተዋወቃላችሁ?» ብለው ጠየቁት ።

ጢማቸውም እንደ ጠጉራቸው ብን ብሎ የሰሳ ሆኖ ፣ ከአይናቸው ሌላ ከፊታቸው ላይ ጎልቶ የሚታየው ፣ ቀጥ ብሎ ወርዶ ከስር ሰስ ከንፈራቸውን የሚሳለመው ረጅም አፍንጫቸው ነበር ።

«የለም ፣ ብዙም አንተዋወቅም ። ስራ ስፈልግ ነው እንዳጋጣሚ የተገናኘነው ።»

«አዎን ፣ ስለ ስራህ በደብዳቤው ላይ ገልፆልኛል ። የሚቸግር ነገር ካለ ቤቱ ቤትህ ነው ። ለዚያውምኮ ያስተማረ እንግዳ የለውም ። በስጋ ባይወልድም በእውቀት የሚወልድ አባት ነው» ብለው ፣ ደብዳቤውን ከተቀመጡበት ፣ በቀይ ሀር ምንጣፍ ከተንቆጠቆጠች ድንክ አልጋ ላይ ጣል ካደረጉ በሁዋላ ፣ «ታፈሰ አገር ቤት ገብቼ አርሳለሁ ነው የሚለው» አሉ ።

«የማ ታፈስ ? የኛ ?» —መምሩ ነበሩ ።

«አዎን ፣ የኛው ታፈስ ነው ። 'ያገሬ ድንግል መሬት ድምፁን ከፍ አድርጎ ይጠራኛል ። የታረሰ መሬት ሽታ ባይኔ እየሄደ ይናፍቀኛል' ይላል። መሬት ለማያውቃት የማትበገር መሆንዋን ሳያውቅ ። መሬት ሲዘሩባት ዝም ብላ የምታበቅል ይመስል ።

«ገበሬ የዘራውን የሚያጭደው ከተፈጥሮና ከመሬት ጋር አንድ አካል እንድ አምሳል ሆኖ በመኖር ነው ። ታዲያ ከመሬት ርቆ የኖረ የከተማ ልጅ ባላገር ተመልሶ ከመሬት ጋር አንድ አካል ሆኖ ለመኖር እንዴት ይችላል ? "ስር መሰረት ከሌለው ከከተማ ኑሮ ወጥቼ ስሬ ወዳለበት ወደ መሬት እንድመለስ የሚገፋፋኝ ጥሪ ይሰማኛል' ይላል ። ጉድ ነውኮ!» አሉ ፊታውራሪ ፣ እየተገረሙ ።

መምሩ ጠጃቸውን በብርሌ ማንጉቅጉቃቸውን አቁመው ፣ «መሬት ፣ መሬት ብሎ ምንነው ይዋትታል ? ከተማ ሰው ገብቶ እንዴት ይመለሳል ?» ብለው ፣ ሁለት ትርጉም ባለው አባባላቸው ፊታውራሪ እንዳልተደሰቱ በመገንዘብ ሳይሆን አይቀርም ፣ «የለም ፣ ማለቴኮ . . . 'በቅርቡ ከኔ ጋር ሶስት ሰዎች ላንድ ቦታ ለዲሬክተርነት ታጭተናልና በሚያውቁዋቸው ሰዎች በኩል ይርዱኝ' ብሎ የፃፈ መስሎኝ ? 'ተቆናጥጨአለሁ ። በርስዎ ርዳታ እንዲ ዋና ዲሬክተር ከሆንኩኝ የቀረው መንገድ ቀላል ነው ። ከዚያ በሁዋላ ሚኒስትር የምሆንበት ጊዜ ሩቅ አይደለም ። አንድ ቀን የናንተን የዘመዶቼንና የተወለድኩበትን መንደር ስም ሳላስጠራ አልሞትም' ብሎ አልነበረም ወይ ?» አሉ ።

ፊታውራሪ ትክዝ ብለው ሩቅ ፣ ሩቅ እየተመለከቱ ፣ «የዘመኑ ልጆች የሚፈልጉትን አያውቁም ። ምን ይደረግ ?» ሲሉ —

መምሩ ትንፋሽ በግድ እየሳቡ ፣ «እሱ ዱሮም ቢሆን እኮ ቀዥቃዣ ብጤ ነበር ። አንድ ቦታ እርጋ መቀመጥ አይወድም ። እርስዎ አዲሳባ ልከው ባያስተምሩት ኖሮ እዚሁ ሲንቀዠቀዥ ሰው ገድሎ ፣ ወይም ሰው ገድሎት ሞቶ ያርፍ ነበር ። ወይም እንደ ሌሎቹ ካንዱ መሸታ ቤት ወደ ሌላ እያለ መሸተኛ ሆኖ ይቀር ነበር ። ኧረ እዚያው እርጋ እንዲቀመጥ ይምከሩት ። የምን ያፈር ሽታ ፣ የምን የመሬት ናፍቆት ነው እሱ ? እብዶ እንደ ሆን ጠበል ቢሄድ ይሻለዋል» አሉዋቸው ።

ፊታውራሪ እንደ ተከዙ ፣ «ምክንያቱ ምን እንደሆነ እኔ እንጃ — ሰው ሁሉ ስልጣን ፣ መሬት መሬት ማለት ጀምሮአል ። ፍቅርም በሰዎች መካከል የለም» ሲሉ —

መምሩ ፣ «ስምንተኛው ሺ--ስምንተኛው ሺ» ብለው ብርሌአቸውን ባንገትዋ ይዘው እንዳነሱ አንዲት ሎጋ ፣ ለግላጋ ልጃገረድ ሻይ ይዛ ከጉዋዳ ብቅ ስትል ሀዲስ የቤተ መቅደስ ጡዋፍ ያየ ነበር የመሰለው ። ልክ ታፈስ እንዳለው ፣ ለእግዚር አይንና አፍንጫ ደስታ ፣ ከገነት ውስጥ የተተከለች አበባ ምስል አእምሮው ላይ ተቀረፀበት ።

ድንገት ስንጥቅ ብላ የደነገጠችው ልቡ ባፉ ዘላ እንዳትወጣ ትንፋሹን ዋጥ አደረገ ። በፊታውራሪ ወጊ አይን የደነገጠችውን ልቡን ስውሮ የት እንደሚደብቃት ስለ ተጨነቀ እንደ ገና ትንፋሹን መልሶ ዋጥ አደረገ ። በቀይ ጥለት ያጌጠ የቤት ፈትል ረጅም ቀሚስዋን እንዲያው ቦታው ላይ የሌለ ከሚመስለው ቀጭን ወገብዋ ላይ እንደ ቀሚሱ ቀይ ጥለት ባለው መቀነት ሸብ አድርጋዋለች ። ሁለት ሳይ ከፍላው በዘፈቀደ የለቀቀችው ጠጉርዋ ከጥቁር ሀር ነዶ ተጎንጉና እንደ ተሰራ ጎፍላ እየተዘናፈለ ሄዶ ከጀርባዋ ላይ ይንዠረገጋል ። የተነጠረ ብር ጉልላት የሚመስሉት አይኖችዋ ከጉድጉዋዳቸው ውስጥ እንዲያው ዝም ብለው ክብልል ክብልል ይላሉ ። ግን ምንም የሚያዩ ወይም ለማየት የሚፈልጉ አይመስሉም ። ለምንም ነገር ደንታ የላቸውማ ! ለማየት ሳይሆን ለመታየት ብቻ የተፈጠሩ ሆነው ታዩት ። ውበት ለራስዋ እውር አይደለች ? የሻሂውን ሲኒ አንስታ ስትሰጠው ያ የተረገመ መከረኛ እጅ እንዳይንቀጠቀጥበት በልቡ ትንሽ ፀሎት አደረገ ። ሻሂውን ቀድታለት ስታበቃ ወደ መምሬ መሀሪ ዞር ብላ ፣—

«አባቴ ፣ ሀኪም ጠጅ እንዳይጠጡ ብሎ ከልክሎት የለም ?» አለቻቸው ።

የሀዲስ ጆሮዎች ይበልጥ ነቁ ። ምን ድምፅ ነበር የሰማው ? ሰማያዊ ሙዚቃ—ወይስ የሰው ድምፅ ?

«ቶሎሳ ነውኮ የሰጠኝ ።»
«ታዲያ እምቢ አይሉትም ኖሮአል !»

«ጀመርሺኝ እንግዲህ !» ብለው በዝምታ መሸከም ተስኗት ከማጉጫጫው ወንበር ላይ ወፍራም ሰውነታቸውን አመቻቹና ፣ «ምን ላድርግ ብለሽ ነው ? የትኛው ሆዴ እስችሎት የጌታዬን ቤት ጠጅ እምቢ ብሎ ይመልሳል ? ዩዛሬ ሀኪሞች እንደሆኑ ስጋ አትብሉ ፣ ጠጅ አትጠጡ ነው የሚሉናቸው ። ሆድ ደስ ያለውን ካልበሉ ካልጠጡ ምን ኑሮ ሆነ ? ደም የሚከለክሉት ነገር ሁሉ ለትንግርቱ እምጡኝ እምጡኝ እያለ እንዲያው በአይን

ላይ ይዞራል ። [የነመን ውሀ በቁም ሙት ነው የምትይኝ ? እኔስ የሚያም ረኝን እየበላሁ እየጠጣሁ ነው የምሞተው ፤ ለምናባቱ ! ከእንግዲህ ለየት ኛው እድሜ ? ተቆርጦ አይቀጠል ነገር ። የህይወት ጣሙ ካልታወቀ ሞትስ ምን ትርጉም ይኖረዋል ?» አሉዋትና ብርሌአቸውን አንስተው አንዶቀ ዶቁት ።

«እኔ ምን ቸገረኝ ? ሲያሞት ያዙኝ ልቀቁኝ እንዳይሉ ብቻ !» አለቻ ቸው ፈገግ ብላ ።

ፈገግ ስትል ከእልፍኝ ውስጥ ሌላ ገነታዊ የጠዋት ፀሀይ ብቅ ያለች ይመስል መላ ሰውነቱን ሞቅ አለው ።

ፊታውራሪ ፈገግ በማለት ፍንጭታቸውን ብልጭ አደረጉና የታፈሰን ደብዳቤ አንስተው ሰጡዋት ።

«ከማን ነው ?» አለች ።
«ታፈሰ ነው የላከው ። ስጦታም ልኮልሻል ።»

ደብዳቤውን ለማንበብ ቸኩላ ሳይሆን አይቀርም ይዛ ወደ ጉዋዳ ሮጠች ። የሀዲስ ልብ አብሮአት ወደ ጉዋዳ ሮጠ ። እንደ ገና እየሮጠች ተመ ልሳ መጣች ። ታፈሰ የላከላትን ስጦታ ወስዳ አሁንም ወደ ጉዋዳ ሮጠች ። አሁንም ልቡ አብሮአት ሮጠ ።

«መቼ ነው የመጣኸው ?»
«አ . . . አቤት?»
«ካዲሳባ የመጣኸው መቼ ነው ?»

«ትናንት ምሽት» አላቸው ፥ ሁኔታውን ለመደበቅ እየተጨነቀ ። ወገ. አይናቸው አስፈራው ።

«የት አረፍክ ታዲያ ?»

«ለጊዜው ያረፍኩት ካንድ ቡና ቤት ነው» አላቸው የመጣበት ዋና ጉዳይ ትግዝ አለውና የሚከራይ ቤት እፈልጋለሁ ብሎ እንዴት እንደሚነግ ራቸው እየጨነቀው ።

«አዮ . . አጥፍተሃል ። እዚህ አትመጣም ኖሮአል ?» አሉና ከመቅ ፅበት ወደ ጉዋዳው አቅጣጫ ተመልክተው ፊታቸውን መለስ እንዳደረጉ ፤ ወጣ፡ አጋፋሪ ፥ ቶሎሳ ፥ ከተፍ አለ ።

«ስማ ቶሎሳ ፥ ከተማ ባዶ ቤት አለን ?»

ቶሎሳ በአዎንታ ለጥ ብሎ እጅ ነሳ ።

«በል ለሱ ለወንድሜ . . .» ብለው ወደ ሀዲስ ዘወር በማለት ፥ «ሀዲስ ሳህሌ አይደለም ስምህ ? ከታፈሰ ደብዳቤ ላይ አይቼ ነው» አሉና ወደ ቶሎሳ መለስ ብለው «አንድ ጥሩ ክፍል ፈልገህ አዘጋጅለት ። ትርፍ አል ጋና እቃም ካለ አስገባለት ።»

ሀዲ ስ ተነስቶ እጅ ከነሳ በሁዋላ ፥ «አልጋውና እቃው እንኩዋ ግድ የለም ። እገዛለሁ» አሌ ።

እንደ መቆጣት ብለው ፤ «ምናለ ስትገዛ ትመልሳለህ» ብለውት ትኩር ብለው ከተመለከቱት በኋላ ፣ ከንፈራቸውን በሀዘን መጠጡና «እንዲያው ሳይህ አስተማሪዬን መክብብን ትመስለኛለህ ። እንዳንተው ጠይም ፣ ጠጉሩ ከግንባሩ ላይ ግጥም ያለ ፣ ረጃጅም እጆችና ቅልጥሞች ያሉት ሰው ነበር ። ያፍንጫችሁ አወራረድና የዮን አከፋፈታችሁ ሁሉ አንድ ነው» አሉት ።

ቶሎሳ ወደ ፊታውራሪ ጠጋ ብሎ በነጠላው ጫፍ አፉን እየሸፈነ በጆሮአቸው ሹክ ያለውን አዳመጡትና ፣ «አስገባቸው» አሉት ።

ሀዲስ ተሰናብቶ ለመሄድ የተነሳ መሆኑን አይተው ለምሳ እንዲቆይ ነገሩት ። ትእዛዝ ነበር የሰጡት ። ለመሄድ ልቡ እየፈለገ ምርጫ ስላልነበረው ተመልሶ ቁጭ አለ ። አይናለም . . . ትዝ እያለችው ወደ ተሰወረች በት ጉዋዳ ተሰርቆ አይኑን በወረወረ ቁጥር ፊታውራሪ ያደረበትን ስሜት ዘልቀው የሚያዩበት ስለሚመስለው ልቡ እየደነገጠ ይቸገራል ። መቼ መደንገጥ ብቻ—የደነገጠች ልቡን ካይናቸው ለመሰወር እየፈለገ ይጨነቃል ። ጭንቅ ሲለው እጆቹን የሚያገባበት ቦታ ያጣና የባሰውኑ ጭንቀት ውስጥ ይገባል ። ከዚያ ወጥቶ ትኩስ አየር ለመተንፈስ ናፍቆት ነበር ።

ጠጉራቸው የተነደፈ ጥጥ የመሰለ አንድ ጉስቁል ያሉ ሽማግሌ ገብተው ለጥ ብለው እጅ በመንሳት ወለሉን ከሳሙ በኋላ ኩታቸውን እንዳሸነፈጡ ይቆማሉ ። ፊታውራሪ ትክ ብለው ሽማግሌውን እየተመለከቱ ፣ «አባ መርጋ አይደለህም እንዴ ?» አሉ ።

«ነኝ አባ ብያ» ብለው እጅ ይነሳሉ ።
«ምን ነው ድንገት አረጀህ ?»
«ችግር ነው ያስረጀኝ ። ችግር ቀጠሮ ሰጥቶ አይመጣም . . .»
«እንዳንተ ያለ ከእርፉ ላይ የሚሞት ብርቱ ገበሬ እንዴት ይቸግረዋል ?»
«በሰው መሬት ላይ ምን ቢበረቱ አዳሩ ጦም ነው ።»
«እንዴት ! እንዴት !»
«እ . . . ሁሉ መቼ እንደ እርስዎ ሆነና ። ሰውም ጊዜውም ከፍቶአል።»

«እንደ ዱሮ ቢሆን ቅድም የተናገርከው ነገር አርባ ጅራፍ ያስቀጣህ ነበር ። ጊዜው በኛም ላይ ከፍቶአል» አሉትና ፊት ለፊታቸው ካለው ግድግዳ ላይ አይኖቻቸውን አሳረፉ ። ሀዲስ አይናቸውን በአይኑ ተከተለ ። በፊት ገባሮች ሁዋላም ጭሰኞች እጅ ከወርች ታስረው የሚገረፉበት ትልቅ ጥቁር አግረ ሙቅና ቅቤ የጠጣ የሚመስል ረጅም አኮርባጅ ከግድግዳው ላይ ተሰቅለው ይታያሉ ።

ሽማግሌው እጅ ነስተው ዝም አሉ ።

«የወነጨፍከው ድንጋይ እንደ ጥይት ይጮሃል ሲባል ሰምቼ ?» አሉ ።
«ቹግር በወንጭፍ መቼ እሺ ብሎ ይባረርና !»

«ጅራፍህ መልካውን ሲያናግር የሚውል ፣ የሚያዝያ ሲምብር የሀምሌ ወጀብ የማያግድህ ፣ ዲቡንና የምታደባልቅ ፣ በፈር ማረሻ ምድሩን የምታስጨንቅ ፣ የተኩዋረፈ በሬ የምታስታርቅ ፣ የምትቀደውን ፈር መቃብር የምታስመስለው ሰው እንዴት ተቸገርኩ ብለህ ትናገራለህ ?»

«ከሰማይ ዎፍ ከምድረ አውሬ የተረፈ እህል ቢሶው ለባለ መሬት ተሰጥቶ የቀረው ምን ፋይዳ ሊሰራ ! ትርፉ ድካም ነው ፣ አባ ብያ ።»

«እንዴት ! እንዴት ነው የሚናገረው ይህ ደፋር ! ባንተ ብቻ አልመጣም ። ሁሉ ባገር ያለ ነው ።»

«እሱስ ነው አባ ብያ ። ለነገሩ አልኩ እንጂ ። ብሶት ነው የሚያናግረኝ ።»

«ታዲያ ችግርህ ምንድን ነው ?»
«ምን ጉልበቴ ቢዝል እሁንም እርፉን መስበር አሳቃተኝም . . . »
«እኮ ታዲያ ?»

«አባ ብያ—ሁለት ህጣን ልጆቼ በጠና ታመውብኝ ሲሞቱ ሲሉ ፣ ገንዘብ በእጄ ስላልነበረ ፣ ለማሳከሚያ ሁለት መቶ ብር ባራጣ ተበደርኩ ። አሁን ሁለት መቶ ታምሳ ብር ሆኖብኛል ። ሰሞኑን የትም ገብተህ ካላመጣህ በውልህ መሰረት የዘራሽውን እህል ማሳው ላይ እንዳለ ላትራፊ ነጋዴ እንሸጣለን ብለው መግቢያ መውጫ ስላሳጡኝ ነው ወደርስዎ የመጣሁት።»

«ምን እንዳደርግልህ ?»

«ገንዘቡን እንዲያበድሩኝ ነው ። እህል ሲደርስ ሸጬ እከፍላለሁ ። ማሳዬ ያጉዋጉዋል ፣ አባ ብያ ። እንዴት አይኔ እያየ አሳልፌ ልስጠው ?»

. ፊታውራሪ አቀርቅረው ሲተክዙ ቆዩና ቀና ብለው ፣ «እንዳነጋገርህ ከሆነ ብድር ሳይሆን ጅራፍ ይገባህ ነበር ። ጊዜው ነው ያናገረህ ! ይህች ጥሬ ያደረች እንደሆን አትቆረጠምም ይባላል ። እውነት ነው ። መልካም ነው ። ብድር የወሰደ ቢመልስ ቤቱን ፣ ባይመልስ ግን አጥሩን ይሰራል ይባል የለ» ብለው ቶሎሳን ባይናቸው ጠቀሱት ።

ሽማግሌው አስር አስር ጊዜ መሬት እየሳሙ የማይደረድሩት ምድራዊ ምርቃትና ምስጋና አልነበረም ። የግድቃን ከተማ ፣ መንግስተ ሰማያት ቢኖር የተደረደረው ምርቃት የይለፍ ወረቀት ወይም ሸኚ ደብዳቤ ሆኖ ባገለገለ ነበር ።

ሽማግሌው መሬቱን በጉልቻቸው አብሰው እንደ ወጡ ሌላ ሽማግሌ በእግራቸው ተተኩ ። እሳቸውም የተሻለ ሁኔታ አልነበራቸውም ፣ እንደ ተቀናት ምድራዊ ጉስቁል ነበሩ ።

ከትንሽ ትከታ በሁዋላ ፣ «ምንድን ነው ጉዳይህ ወዳጄ ? እባጥሬ አይደለህም እንዴ ? ምንነው በደህና ? . . . ደህና ብትሆንማ አትጠይቀኝም ነበርኮ» አሉዋቸው ።

«አባ ብያ—እውነት ነው ። እግዜርንም ቢሆን ሳይጨንቀው ማን ያስታውሰዋል ? ካልቸገረው ሰማይን ወደ ላይ ቀና ብሎ የሚመለከት የለም ።»

«እግዜርንና ወዳጅን ማስታወስ በተቸገሩ ጊዜ አይደለም ። ያልዘሩት ይበቅላል ወይ ?»

መሬት ስመው ዝም ።

«ወንድምህ ብር የተረፈው ቱጃር ነበር !»

«ፍየል መንታ ወልዳ አንዱ ለመፃፍ አንዱ ለወናፍ ይባል የለ ። እኔም ንግዱን ሞክሬው ነበር ። ለመከራ የጣፈው ቢነግድ አይተርፈው ነገር ሆኖብኝ ነው እንጂ . . . »

«ቡናህን የሸመጠጥክ'ለት ፣ እንግዳ ሲመጣ ገንቦው አይገታ ይባል ልሃል እሱ ። ጥንጫህማ ከንድ ከንድ ያከላል ይባላል ።»

«እዎን አባ ብያ ፣ ከሰው ጋር አብሮ መብላቱንና መጠጣቱንስ እወድ ነበር . . . »

«ታዲያስ?»

«ጠጥቶ በልቶ ዞር ሆን የዘመኑ ፈሊጥ ። ሰው ጨው አይደል ተቀምሶ አይታወቅ ። ሞኝ ሲያመሰግኑት የባሰውኑ ሞኝ ይሆናል ። ሲያመሰግኑኝ ደስ ደስ እያለኝ ብሉ ብሉ ስል እጄ አመድ አፋሽ ሆኖ ከሁብቴም ከወዳጅም ሳልሆን ቀረሁ ።»

«ወዳጅ ማለት ሰው አይደለም ። ጊዜ ነው ። ወዳጅ ማለት ጊዜ ነው ።»

«ጊዜውም ከዳኝ . . . »

«ምንድን ነው ችግርህ ?»

«ግብር የምከፍለው አጣሁ ። ቡናየንም ትል በላው ። እምና ከብቶቼን ሸጬ ከፍዬ ነበር ። ዘንድሮ ምን እንደሚውጠኝ አላቅም ። ልጆቼም እንዳይረዱኝ የሉም ።»

«የት ሄዱ ?»

«አባ ብያ . . . እድሜ ያላደለኝ ሰው ነኝ ። ልጄ ወዳዲሳባ ኮብልሎ ከሄደ ዘመን የለውም ። እዚህ ትንሽ የፈረንጅ ፊደል ቆጥሮ ነበር ። አሁን በህይወት ይኑር አይኑር አላውቅም ። የደረሰች ልጄም እንዲሁ ወዳዲሳባ ኮብልላ ጠፋች ። እሱዋም የት እንዳለች አላውቅም ። በስተርጅና ያለ ጡዋሪ ቀረሁ ።»

ፊታውራሪ ለጥቂት ጊዜ ትክ ብለው ሲያስቡ ቆዩና ፣ «የማያውቋት አገር አይናፍቅም ይባል ነበር ። ዛሬ አዲሳባ ሳትታይ ከሩቅ የምትናፈቅ ከተማ ሆናለች 1 ወርቅ ከመሬት የሚታፈስባት ይመስል ። ግን ወደ ፊት በተቸገርክ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በደህናውም ቀን ጠይቀኝ ። ለአይንና ለወዳጅ ጥቂት ይበቃዋል ። ያልከው ይሁንልህ» አሉዋቸውና ቶሎሳን እንደ ገና ባይናቸው ጠቀሱት ።

«ከእስር ቤት ከዳንኩኝ እንደ ምንም ብዬ እከፍላለሁ ። በፊርማዬም ገዴታ እገባለሁ ።»

«በወዳጆች መካከል ፊርማ አያስፈልግም ። ቃል ይበቃል ። ከቃል የበለጠ ምን ነገር አለ ?»

ሰውዬው ከደስታቸው ብዛት ሲቃ ይዞአቸው መሬት ስመው እየመረቁ ሲወጡ ቶሎሳ እንደገና በጆሮአቸው ሹክ አለ ።

«ስንት ናቸው ?» አሉት
«ኧረ ብዙ ናቸው ።»

«ላንድ ጉዳይ ከሆነ የመጡት ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች ከመካከላቸው መርጠው ያስገቡ ። ስንቱን አዳምጬ እችላለሁ?» ከማለታቸው ፤ አይናለም እንደ ቢራቢሮ ስትበር መጣችና ሀዲስን ፣ «እውነት ጋሼ ታፈሰ ይመጣል ?» ስትለው ፡-

ህልውናው በሙሉ ውብ አይኖችዋ ውስጥ እየቀለጡ ፣ «እመጣለሁ ሲል ነበር እየደጋገመ» አላት ።

«ታድዬ !» አለች ደብዳቤውን ጨብጣ ።

«የምን መታደል ነው የምትይው !» አሉዋት ፊታውራሪ ፣ ቆጣ ብለው ። ሲቆጡ ከግንባራቸው መካከል ያለው የደም ስር እንደ ምሰሶ ትንስቶ ይገተራል ።

«ባይሆን እዚህ ቤት ውስጥ አንድ አጋር ይኖረኛል» አለች ፣ ከጠራረጅም ፊትዋ ላይ ደምዋ እየተተራመሰ ።

«የምን አጋር !» አሉ በዚያ አስፈሪ አይናቸው እየገላመጡዋት ።

እስዋ እንደ ሆነች ፍንክች አላለችም ። የሀዲስ ልብ ተሰቀለ ። ምን እንዳጣላቸው ምኑም አልገባውም ። ምድረ አለም እንደዚያ የሚንቀጠቀጥላቸውን ሰው እንደዚያ አስቆጥታ መልሳ ስታፈጥባቸው ገረመው ። ተአምር ማለቂያ የለውም ፣ አለ በልቡ ። ትክ ብለው ነበር የሚመለከቱዋት ። ግን ከፊታቸው የሚመለከቱት ነገር ምኑም የገባቸው አይመስሉም ። የሰው መስታወት ከፊታቸው አልነበረም ። «ወይ ጊዜ ! ጊዜ አያመጣው የለ ። ጉድና ድንቅ አንድ ሰሞን ነው» ብለው ዝም አሉ ። እስዋም ዝም ብላ ወጣች ። አቤት ስትናደድ ማማርዋ ! የፈነዳ ፅጌረዳ አበባ ትመስላለች ።

«ሰምንተኛው ሽህ—ሰምንተኛው ሽህ ነውኮ» አሉ መምሩ ራሳቸውን እየነቀነቁ ። አይናቸውን ባዶ ብርሌአቸው ላይ ተክለው ።

ፊታውራሪ እየተገረሙ ፣ «አሁን ማ ይሙት ይመጣል ብላ ነው ? እንኳዋን የተማረ ፊደል የቆጠረም ካዲሳባ ወጥቶ ባላገር ሲመለስ አላየንም ። ሰምቹን አስገባ ወንድሜ» አሉ በጎረና ድምፅ ።

«ሰው ከተማ ገብቶ እንዴት ይመለሳል !» መምሩ ነበሩ ።

ሶስት አዛውንቶች ተከታትለው በመግባት እንደ ሌሎቹ ሁሉ መሬት ስመውና እጅ ነስተው እንደ ቆሙ ፣ ፊታውራሪ ግንባር ላይ እንደ ምሰሶ ተገትሮ ቆሞ የነበረው ደም ስር ሙዋሽ ሲጠፋ ይታይ ነበር ። ለጥቂት ጊዜ ተለይተዋቸው የነበረ ደስታ እንደ ተመለሰላቸው ብሩህ እየሆነ ከሚሄደው ፊታቸው ላይ ይነበባል ። የፊታውራሪ ስሜት እንግዳ ነገር ሆነበት ። የደስታቸው ምንጭ ምን እንደሆነ ሊገባው አልቻለም ። ሰዎችን ማነጋገር ልዩ ደስታ የሚሰጣቸው ፣ የሰው ትንፋሽ የሚናፍቃቸው ይመስላሉ ። ሰዎች ገብተው ሲቆሙ ግርማ ሞገሳቸው ይጨምርና ድንገት ግዙፍ እንደ ሆኑ አይነት ስሜት በሰው ላይ ይፈጥራሉ ።

«እንዴ ? እንዴ ? የዳረሙው አባ ዋቆ — የተኮሳት ጥይት ከመሬት ጠብ የማትል ። እንደምነህ ጀግናው ?»

ሶስቱም ጠብ እርግፍ ብለው እጅ ይነሳሉ ። አባ ዋቆ ሸምገል ያለ አንድ አይና ሰው ነው ። «እንጣጥር ለመተኮስ አንድ አይን ይበቃል ፤ ለጥቅሻ ከሆነ የመንደር አውደልዳዮች አይናማዎቹ አሉልን» አለ ይባላል— አባ ዋቆ — እንዴ ። የድኩላና የሚዳቋዋ ቋንጣ ከቤቱ አይጠፋም ። ያባ ዋቆን ክምር ጥይት አይበሳውም ይባል ነበር ።

«ቀኛዝማች ደህና ነው ወይ ?»
«ቀኛዝማችስ ደህና ናቸው ። እኛን ደሀቻቸውን ጤና ነሱን እንጂ . . .»
«እንዴ ? ለምን'ኮ ?»

«ከመሬታቸው ላይ ነቀሉን ። እንዲያው ጎጆአችሁን ነቅላችሁ የምት ሄዱበት ሂዱ አሉን ። እዚህ የመጣነው አርባ ሰባት ሰዎች ነን ። ከቤተ ሰቦቻችን ጋር ከሁለት መቶ በላይ እንሆናለን . . .»

«ምን ሊያደርጉበት ነው?»

«ዘመናዊ እርሻ አስፋፋበታለሁ ነው የሚሉት ። መንዲስ መንዲስ የሚያካክሉ የርሻ መኪናዎች ገዝተውና ሾፌሮች ከዲሳባ ድረስ ቀጥረው አስመጥተው አገር ምድሩን እየገለባበጡት ነው ።»

«ጉድ ነው'ኮ ። እሺ ?»

«መኪናዎቹ የሚገለባብጡት መቼ መሬቱን ብቻ ሆነና ? ያባት የቅመ አያቶቻችንን አጥንት ጭምር ነው ። አባ ብያ — እድሜ ልካችንን ሲሶ ስናፈስና ሁዳድ ስንሆድድ ከኖርንበት መሬት አሁን ተባረን የት እንውደቅ ?

«እንደሚያዩት ጉልበታችን ደክሞአል ። ጎጆ ብርቱ ሰው ታደክማለች ። እድሜ ልክ ከኖርንበት ከምናውቀውና ከሚያውቀን መሬት ድንገት ተነስተን ፣ የትኛው መሬት ሊቀበለን ? የትኛው ጉልበታችንስ ሊያቀናው ይችላል ? ሰውም እግዜሩም ፈረደብን ። አንዳንዴ ሳስበው እግዜሩም የዱሮው እግዜር አይደለም እላለሁ ።»

መምሩ በስመ አብ ብለው አማተቡ ።

«ክስ ሄዳችሁ ነበር እንዴ?» አሉ ፊታውራሪ ።

ሀዲስ ጆሮውን ክፉኛ አንቅቶ ያዳምጥ ነበር ። ሁለመናው ጆሮ ብቻ ሆኖ ነበር—ልቡናው ታፈስ ብሩን እያስታወሰ ።

«ኧረምን አባ ብያ ፣ ያልደረስንበት ፍርድ ቤት የለም ።»
«እና ?»
«በየደረስንበት ትነቀላላችሁ እያሉ ፈጠሙን ።»
«ታዲያ አሁን እኔ ምን እንዳደርግላችሁ ነው የመጣችሁት ?»

«ቢያማልዱን ብለን ነው ። መወሰድ ካለ ማዘን አይገድም ። መቼም እርስዎን ሳይሰሙ አይቀሩም ።»

«ከስ ከመሄዳችሁ በፊት ብትመጡ ነበራ ። ካያያዝ ይቀደዳል ፤ ካነጋገር ይፈረዳል ይባላል ። አባ ዋቆ ዱርውንም ችኩል ነህ ። እንዲያው ከምትተኩሰው ጥይት ትቀድማለህ ። የቸኮለ አፍሶ ለቀመ ይባላል ። የፈሰሰ ውሀ አይታፈስ እንግዲህ ። ለከስ ከሮጣችሁ በሁዋላ አሁን አማልደን ብትሉኝ እንዴት ይሆናል ? ጠላት ግዛ ነው የምትሉኝ ?» ብለው ከተቀመጡበት በመነሳት እጃቻቸውን ወደ ሁዋላ አጣምረው እየተከዙ ሲንጎራደዱ ከቆዩ በሁዋላ ፣ በመስኮት ከአልቄ ወንዝ ባሻገር ካለው ተራራ ማዶ ሩቅ እየተመለከቱ ፣ «ቀኛዝማችም ቢሆን ደግ አልሰራም ። አሁን ከመሸ ይህን ስራ ምን አስመለከተው? ሞልቶ ለተረፈ ሳልጠፉ ሁብት? ወቸ ጉድ—ሰው እንዳስቀመጡት ሳይገኝ ! መሬት ያለ ሰው ብቻውን ምን ረብ ይኖረዋል ብሎ ነው ? አይ አለማወቅ ደንቆሮ ግጥም ! አያጣም አሉ ።

«ሰውን ነቅዬ ብቻዬን ልረስ ማለት . . . ዋ ! . . . ሁዋላ መዘዙ ብዙ ነው ። የሰውን እንጀራ ገመድ መበጠስ በእግዜርም ፊት ያስጠይቃል ። ምን ተይዞ ጉዞ ? የከበሬታው ፣ ታፍሮ በሰላም የመኖሩ ፣ የስልጣኑ ፤ እንዲያው . . . የአገሩ ስርአት ፣ ልማድና ወግ መሰረቱ ምን [illegible] ነው ? መሬት ሰው አይደል ? ሰውን ከመሬት ላይ አንስቶ ማባረር አሁ ን ምን ይባላል ? ምኝ የያዘው ፈሊጥ ካልሆነ በስተቀር ። በገዛ እጃችን ነውኮ በራሳችን ላይ የእግዜሩን መአተ ቁጣ የምንጠራው ። ከመሬት እንዲለይ የተደረገ ሰው ስር የለውም ። ስር ከሌለው ፈሪሃ እግዚአብሄር አያድርበትም ። ጨካኝ አውሬ ነው የሚሆነው ። ካውሬ ከበሬታና ፍቅር ይጠበቃል ወይ ?

«የብር ስልቻዎች ! ጊዜ የፈለፈላቸው የብር ስልቻዎች ናቸው እኮ አገር የሚያጠፉት ! ለስንት ዘመን በሰላም ፀንቶ የኖረውን ስርአት ከስሩ በመናድ የሚያናጉት ። ሳያሽ የበላ ዝንጀሮ ሲስል ያድራል አሉ ።

«እዬ ቀኛዝማች—እሱም የብር ስልቻ መሆን ፈለገ? መወለድ መቼ አነሰው ነበር ፤ ከመወለድ ፣ የበለጠ ምን አዱኛ አለ ?» ብለው ወደ ሰዎቹ ፊታቸውን መለስ አደረጉና—«ክብርና ሞገሱ እናንተና መሬቱ አልነበራችሁም ? ሰው ብቻውን መሬት ቢያርስ ምን ፋይዳ አለው ? ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል ። ሁሉም ተስገበገበ ። ከጅብ ቆዳ እንደ ተሰፋ ከበሮ 'ለኔ ለኔ' ብቻ ሆነ ነገሩ ። በሰዎች መካከል መተሳሰብ— መከባበርና መፋቀር ጠፋ ። አይ ጊዜ—አያመጣው የለ ! ፋሜው ወዴት ሊያደርሰን ይሆን ?» አሉ ።

«ስ ምንተኛው ሺ ነውኮ ። ሌላ ምን መሰሎት ። ጊዜው የሚያሳየንን ምልክት የሚያጤን ልቡና ተሰጥቶናል» አሉ መምሩ ። ትልቅ ዝንብ የሚያንግርብብበትን ባዶ ብርሌአቸውን በጎን አይናቸው እየተመለከቱ ።

ቶሎ ሳ መጥቶ ሌሎች ባለጉዳዮች የሚጠብቁዋቸው መሆኑን ስለነገራቸው ሳይሆን አይቀርም ፣ «በቃኝ ። ለዛሬ ይበቃኛል ። የሕዝብ እንባ ጠባቂ ማን አደረገኝ ። ወረዳው ገዥ ዘንድ ሄደው ለምን አቤት አይሉም ? እሱ ነው የተሾመው» አሉ ፊታውራሪ ተካ ።

ከባለጉዳዮቹ መካከል አንዱ ፣ «እዬ አባ ብያ ፣ ወረዳ ገዥው ጋ ማን አድርሶን? ብንደርስም አቤቱታችንን እንዳመፅ ነው የሚቆጥሩብን» ሲል ፤—

ሌላው ባለጉዳይ ቀጥሎ ፣ «ለዚያውስ የት ይገኙና ። እሳቸው አመቱን ሙሉ መቱ ፣ አዲሳባ እያሉ ነው የሚኖሩት» አለ ።

«ታዲያ እኔን ምን አድርግ ነው የምትሉኝ ? መንግስት የሰጣችሁን አሜን ብሎ መቀበል ነው እንጂ ። ከእንግዲህ ባላባትነት ምን ዋጋ አለው ? ስልጣን የለኝ ። ዛሬ ስልጣኑ የሌሎች ሆኖአል» ብለው ፣ ሰዎቹን ከሸኙ በሁዋላ ፣ «ባንዳዎችና ነጋዴዎች የነገሱበት አገር ! የኛ ዘመን እንደሆነ አከትሞአል ። ምን አድርግ ነው የሚሉኝ ? እኔም ከነሱ የባሰኩ ነኝ ። አያት ፣ ቅመ አያቶቼ የገዙት አገር ማንም ቅማላም ወረዳ ገዥ እየተፈራረቀ ሲሾምበት እያየሁ ተቀምጫ የለ !» በማለት እድላቸውን ሲያማርሩ ቆዩና ፣ «ተጫወት እንጂ ። ምን ነው ዝምታ ታበዛለህ ?» አሉት ሀዲስን ።

«እሺ» አለ ሀዲስ ።

«ጉድ ነው» ብለው ትኩር በማለት ሲመለከቱት ቆዩና ፣ «ከመልካ ችሁ የጠባያችሁ መመሳሰል ። እሱም እንዳንተ በጣም ረጋ ያለ ሰው ነበር ። ሳይህ ልክ መክብብን ትመስለኛለህ» አሉትና እንደገና ትክ ብለው ይመለከቱት ጀመር . . .

# ክ ፍ ል ፬

ሀዲስ ሳህሌን በጣም የገረመው ፈታውራሪ ተካ ካከራዩት ቤት ገብቶ ገና ከመደላደሉ በፊት ፣ መሬትን በሚመለከት ጉዳይ ለጭቃ ሹሞች ፣ ለወረዳ ገዥዎች ፣ ለወረዳ ፣ ላውራጃና ለጠቅላይ ግዛት ፍርድ ቤቶች ማመልከቻ ፣ መልስ ፣ የመልስ መልስ ወይም ያቤቱታ ደብዳቤዎች ፃፍ ልን እያሉ ስሙን ጠርተው ወደ ቤቱ የሚመጡት ሰዎች ቁጥር ብዛት ነበር።

መሬቴን በግፍ ተቀማሁ ። ድንበሬ ተገፋ ። ከሶስት ትውልድ ጀምሮ ከኖርኩበት መሬት ላይ በግፍ ያለ ምንም ካሳ ተነቀልኩ ። በይዞታዬ ስር ያለው መሬት ጋሻ ስለማይሞላ ተለክቶ ልኩ እስኪታወቅልኝ ድረስ የተ ጣለብኝ ግብር ይነሳልኝ ። የዘንድሮ ሰብሌን ውርጭ ስለ መታብኝ የመሬት ግብር ፣ የጤናና የትምህርት ታክስ ይታለፈኝ ። ግብር ከፍዬ አልከፈልክም ተብዬ ስለ ተከሰስኩ ነገሩ ይመርመርልኝ ። ይሄውና የመሬት ግብር ልክ ፍል ብመጣ የጠረጴዛ ክፈል እያሉኝ በመጉላላት ላይ ስላለሁ አቤቱታዬ ታይቶ ግብሩን የሚቀበለኝ ሰው ይታዘዝልኝ . . . ስሞታው ማለቂያ የሌ ውም ።

ትምህርት ቤቱ ገና ስላልተከፈተ ደስ እያለው ነበር የሚፅፍላቸው ። አንዳንዶቹ የድካምህን ዋጋ ካልከፈልንህ ሞተን እንገኛለን በማለት ያስቸ ግሩታል ። ሌሎች ደግሞ አንድ ሁለት ብርሌ ጠጅ ፣ ከፈለክም ሌላ ነገር ወስደን ካልጋበዝንህ በማለት ዱላ ቀረሽ ትንቅንቅ ይገጥሙታል ። ጥቂቶቹ ደግሞ እየመረቁት ይሄዱ ነበር ።

ወሬውና አቤቱታው ስለ መሬት ፣ ጨኸቱ ስለ መሬት ፣ ትንቅንቁና ሙግቱ በመሬት ። የመሬት ነገር እዚህ ፣ የመሬት ነገር እዚያ ፣ የመሬት ነገር በያለበት ። እንደ አዲስ አበባ ማን ምን አይነት አዲስ መኪና ገዛ ? ማን ምን አይነት ቤት በስንት ሺህ ብር ሰራ ? ማን ምን አዲስ ስራ ከፈተ ? ማን ከማን ጋር መውጣት ጀመረ ? ማን ማንን አጨ ? እነ ማን ተጋቡ ? እነ ማን አመት ሳይሞላቸው ተፋቱ ? ማን ለሹመት ታጨ ? እነ ማን ተሾሙ ? እነ ማን ተሻሩ ? አቤት ! አቤት ! ጉድ ነው እኮ ! ሰምታችሁዋል ? ገርማ ዊነታቸው ለዘውድ በአል አዲስ ነገር ሊያውጁ ነው ይባላል ። ምን ሊያደ ርጉ ይሆን ? እንደሚባለውማ ዙፋኑን ለአልጋ ወራሽ ሊሰጡ ነው የሚል ወሬ አይሰማም ። ከመሬት ሌላ ወሬ የለም ። እና ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በህይወቱ ፣ መሬት ፣ በቀጥታ ልቡንና ስሜቱን የሚነካ ነገር ሆኖ ይሰማው ጀመር ። ያየዋል ። ያሸተዋል ። ይሰማዋል ።

እንደ ተለመደው አንድ ቀን ማለዳ በሩ ሲመታ እየተራገመ ሄዶ ከፈተ ። ከጠዋት እንቅልፉ የሚቀሰቅሰውን ሰው እንደ አጥቂ ገዳይ ነበር የሚመለከተው ። ጎረቤቱ የሚኖሩ ፣ እንኳዋን ለሰው ቀርቶ ለምድርም የሚከብዱ አዛውንት ነበሩ ።

«ምን ነው ደህናን?» አላቸው ፤ እኝህ ሰው በጉርብትናቸው ተጠቅመው ልዩ ፀሀፊያቸው ሊያደርጉኝ ነው እንዴ ? በማለት እያሰበ ። ባለፈው ቀን እንዲሁ በማለዳ ቀስቅሰውት አንድ ማመልከቻ ለወረዳው ፖሊስ ጣቢያ ፅፎላቸው ነበር ።

«ከእንቅልፍህ ቀሰቀስኩህ መሰለኝ?»
«ምንም አይደለም» አለ ፤ በልቡ እየተራገመ ።
«ወንድ ልጅ እንቅልፍ ምን ያረግለታል? ማለዳ መታጠቅ ነው'ይ . . .»

ተንጠራርተው አዛጋና አይኖቹን አሽቶ ሲያበቃ ፤ ንጭንጭ ባለ ድምፅ ፤ «ሌላ ማመልከቻ እንድፅፍልዎ ነው የመጡት?» አላቸው ።

«ሌላ እንድትፅፍልኝ አይደለም ። የትናንቱን ትንሽ አሻሽለህ እንድትፅፍልኝ ፈልጌ ነው» አሉት ።

እንቅልፉ ካይኑ እንደ ወፍ በረረች ። የፃፈላቸውን ማመልከቻ ይዘት አስታወሰ ። ፍሬ ነገሩ ፤ ገንዘብ በብድር ወስዶ ያስቀረባቸው አንድ ሰው ፤ ነገ ከነገ ወዲያ እያለ ስላስቸገራቸው በፖሊስ ተገዶ ቀርቦ እንዲጠየቅልኝና ገንዘቡንም እንዲከፍለኝ እንዲደረግልኝ የሚል ነበር ።

«ምኑን ነው የማሻሽለው?» ብሎ ጠየቃቸው ።
«ደረቅ ሆነብኝ»

የባሰውኑ ነቃ ።

«እንዴት?» አለ ።

«መጀመሪያው ላይ ፤ 'እኔ ረዳት የሌለኝ ደካማ ሽማግሌ የሆንኩ አነስተኛ ደሀም' የሚል አሳብ ብትጨምርልኝ ። እንዲሁም መጨረሻው ላይ ፤ 'ፖሊስ እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ' የሚለው ቀርቶ በእሱ ምትክ ፤ ፖሊስ እንዲታዘዝልኝ ከስልጣንም መንበር ስር ወድቄ በታላቅ አክብሮት እለምናለሁ' የሚል አሳብ ብታክልልኝ ደስ ይለኛል ። ወድጄን አይደለም ልጄ ። የመቶ አለቃ አሽኔ አስተዛዝነው ፤ እሱን ከበውና አሞግሰው ካል ገቱለት አይቀበልም አሉ ። እንዲያውም አንዳንድ የገፍክኞቹውን ሰዎች ወረቀት ተቀብሎ ፤ 'ማን ነው እንዲህ ያለ እብሪትና ንቀት የተሞላበትን ማመልከቻ የሚፅፍላችሁ ? ለመሆኑ ለማን እንደምትፅፉ አውቃችሁዋልን ? እንዲህ ያለው ቁጥንቁጥ የትም አያደርሳችሁም!' ሲል ነበር አሉ» ብለው ፤ እንዲፅፍላቸው በአይኖቻቸው ተማፀኑት ።

«እንዲህ አይነቱን ነገር ለመፃፍ ያስቸግራል» በማለት ተነጫነጨባቸው ።

«ምኑ የሚያስቸግርህ ነገር አለ ልጄ? ትንሽ ቃላት ነው'ኮ የምትጨምረው . . .»

«እኔ በድብዳቤ ልመና መፃፍ ደስ አይለኝም . . .»
«ባለ ስልጣኖችን ካልተለማመጡና ካልለመኑ እንዴት ይሆናል ? አይ አለመማር! ብማር'ኮ እኔው እፅፈው ነበር» አሉት እያዘኑ ።

«ቢማሩማ እንዲህ ብለው አይፅፉም ነበር ። መብት ይጠየቃል እንጂ አይለመንም ፤ አባቴ» ብሎአቸው ፤ እየከፋው እንዳሉት ፅፎ ሰጣቸውና መርቀውት ከሄዱ በሁዋላ ፤ እሱም ንፁህ አየር ለመተንፈስ ወጣ አለ ።

የእሁድ ገበያው ፥ ገና ጠዋት ቢሆንም ደርቶአል ። ከኖጺ ፥ ከአልጌ ፥ ከዳሪሙ ፥ ከቡቢ ፥ ከቆላው ፥ ከደጋው ፥ በእግር ፥ በፈረስ ፥ በበቅሎ የመጣው ገበያተኛ ስፍራውን ሞልቶታል ። በየበረንዳው ስር የተደረደሩት ልብስ ሰፊዎች ስራ በዝቶባቸው ይታያሉ ። ነጭ ፥ ጥቁር ፥ ቀይ ፥ ብጫ ፥ አረንግዋዴ ፥ ሰማያዊ ጃንጥላ ። የቀለም አይነት የሚታይበት በአል ይመስላል ። ጎፈሬአቸውን ጥቁር ጉም አስመስለው ያበጠሩ ጎረምሶች ከገበያው አፋፍ ላይ ዘንግ ዘንጋቸውን ተደግፈው ቆመው ጥርሳቸውን እየፋቁ ጢቅ ይላሉ ። የሞቁት እንሰሰሳ ፥ ከሩቅ የሚጣራው ባዱላቸው ገና ያልገጠመ ልጃገረዶች በገበያው መሀል እንደ ቢራቢሮ ውር ውር ይላሉ ።

ጠጅ ቤቱ ሁሉ ከአፍ እስከ ገደፉ ሞልቶ ፥ መሰንቆውን ሲያሙዋሽ የቆየው አዝማሪ ግጥም እስኪያልቅበት ድረስ ማቅራራት ጀምሮአል ። በየጠጅ ቤቱ ደጃፍ እንደ ተለጎሙ የታሰሩት የጋማ ከብቶች ዝንብ ለመከላከል ጭራዎቻቸውን እያወዛወዙ በቁም ያንቀላፋሉ ። ገበያው ሞልቶ አጅግ እንደ ደራ ፊታውራሪ ተካ በሰጋር በቅሎአቸው ሆነው ካጀባቸው ጋር ገበያውን ለሁለት ሰንጥቀው እጅ እያስነሱ ሲያልፉ ተመለከታቸው ። ገበያውን አቋዋርጠው በወርቅ ቅብ መረሻችና እታ ባጌጠች በቅሎአቸው ፈሰስ እያሉ ሲያልፉ ቶሎሳ ካጀቡ ነጠል ብሎ እየሮጠ መጥቶ ፥ «በሰባት ሰአት ለምሳ እንድትመጣ ብለዋል» ብሎት ፥ መልሱን ሳይጠብቅ በመጣበት ፍጥነት ተመልሶ ሮጦ ሄደ ።

ትእዛዝ ነበር የተላለፈለት ። አልከፋውም ። ያችን ውብ ልጅ እንደ ገና ለማየት የሚያስችል እድል ማግኘቱን አልጠላም ። ውበትዋ አይን ያስፈነጥዛል ። የጨነቀው ከሽታዬ ጋር ምሳ አብሮ ለመብላት ያደረገው ቀጠሮ ነበር ። ምን ምክንያት ፈጥሮ ቀጠሮውን ለማፍረስ እንደሚችል ግራ ገባው ። ዝም ብሎ በመጥፋት ቆረጠ ። ሽታዬ በምክንያት የምታምን አይነት ሴት አይደለችም ።

ሰአቱን ተመለከተ ። ፊታውራሪ በቀጠሮ ቀልድ አያውቁም ። ባለፈው ጊዜ ለምሳ ቀርበው ባብዛኛው የጎረሰው የቀረበለትን ፍትፍት ሳይሆን ፊታውራሪ ስለ ጊዜ ያላቸውን ፍልስፍና ነበር ። ከማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ከምእራፍ 25 ቁጥር 1 እስከ 13 ያለውን የብልሆችና የሰነፎች ቆነጃጅት ታሪክ እየጠቀሱ ፥ «በቀጠሮው ሰዓት መቅረዛችንን አብርተን ካልጠበቅን ዘግይተን በር ብናንኩዋኩዋ አይሆንም ። ጊዜና ቀጠር መከበር አለባቸው ፥ ከጊዜና ከቀጠር ውጭ የሚሆን ነገር የለም ። ወቅትና ዘመናት ጊዜና ቀጠሮን ጠብቀው ነው የሚፈራረቁት ። እህል አለጊዜው አይዘራም ፤ አለ ጊዜውም አይታጨድም ። ሰውም ከቀን ቀጠሮው አያልፍም ። ጊዜና ቀጠሮን የማያከብር ሰነፍ ነው ፤ አውሬ ነው እንጂ ሰው አይደለም» ይሉ ነበር ፥— ደጋግመው ።

አዲስ ለቀጠራት ባልቴት ገረድ ፥ ጉዳይ ስለገጠመኝ ሽታዬ ከመጣች እንዳትጠብቀኝ ንገሪአት ብሎ ሲወጣ ሲል አንጉተመተመችበት ። ሶስት ቀን ሳይሞላት ማጉተምተም ጀምራለች ። ስርታ ያቀረበችለትን ጥርግ አድርጎ ካልበላ ጉዋዳ ገብታ ታጉተመትማለች ። ቢርበውም ባይርበውም እየፈራ፦ የቀረበለትን ሁሉ ጥርግ አድርጎ መብላት ጀምሮአል ። ምሳውን ጥርግ አድርጎ መብላቱን ካየች ደግሞ ራቱን ከምሳው ይበልጥ ከምራ ታቀርብለታለች . . .

ተአምር አያልቅም ብሎ ወጣ ። እየፈጠነ ወደ ፊታውራሪ ቤት ሲሄድ አንድ በግ እንጓለለ ሲወጣ በሚችል በዚያ በተለንመ አገልግል የሚቀርበው ምሳ ታየው ። ምሳም ሲቀርብ ከውጭ የመጣ ነው ተብሎ አገልግሉ ፊታቸው ተፈቶ ካሳዩ ፊታውራሪ እህል እንደማይቀምሱ የነገረው ቶሎሳ ነበር ። ታዲያ ከብዙ ዘመን ጀምራ አብራቸው የኖረች ገረድ ቤት የተሰራውን ምግብ ባገልግል አዝላ ስትዞር ትውልና ስአት ሲደርስ ተመልሳ ገብታ አገልግሉን እፊታቸው ትፈታለች ።

አገልግሉን በኩራት አዝላ እሱም አይቶአታል ። ታቦት ያዘለች ይመስል በኩራት ነበር የምትራመደው ። የፊታውራሪ ምሳ ነው በማለት ቆም ብለው ለመሳለም የሚቃጣቸውም ሰዎች ነበሩ ። የፊታውራሪን አገልግል ያላየ በሱጴ ይኖራል ለማለት አያስደፍርም ። እና ፣ አገልግሉን አዝላ ዘወትር ታዘግግለች—የምታልፍባቸውን ዛፎች ጥላ በአይንዋ እየለካች። ከሰአትዋ ዝንፍ የምትልበት ጊዜ አልነበረም ። እንዲያውም በሰዋ አካሄድ ነበር ብዙ ሰዎች ሰአቱ ስንት እንደሆነ የሚገምቱት ። አገልግሉን አዝላ ዳገቶችን ስትወጣ ፣ ቁልቁለቶችን ስትወርድና ወንዞችን ስትሻገር በአይኑ ህሊናው እየታየችው ተአምር አያልቅም . . . ተአምር አያልቅም . . እያለ ዳገቱን ወጥቶ ልክ በሰአቱ ከፊታውራሪ ቤት ከች ሲል ፣ «ጊዜና ቀጠሮን ማክበር እኮ ሌላውን ማክበር ብቻ ሳይሆን ራስንም ማስከበር ነው ። ራሱን የማያከብር ለሌላው ምን አክብሮት ይኖረዋል?» እንዳሉት ፣ መምሬ መሀሪ መስቀላቸውን አውጥተው ሊያሳልሙት አንድ ርምጃ ወደ ፊት ከሄዱ በሁዋላ ቆም ብለው ሲያመነቱ አያቸው ።

«መስቀል ስታይ እንደ መበርገግ ያደረገሃል ልበል?!» አሉት መምሬ፣ እንደ መገረም ብለው ። ቀጥለውም ፣ «ለመሆኑ ተጠምቀሃል?» ሲሉ ጠየቁት ።

«አዎን ።»

«በቀዝቃዛ ውሀ ተጠምቄአለሁ ማለት ብቻውን አይበቃም ። እሁድ ቤተ ክርስቲያን አልመጣህም ። ጥምቀት ብቻ ሳይሆን ተግባር ነው የሚያድነው ።»

ደንገጠ ፣ «ኧረ የቄስ ልጅ ነኝ» አላቸው ።
«የማ?»
«የመምሬ ሳህሌ እንደሻው . . . »
«አለቃ እንደሻው ዝቄ የራጉኤሉ ?»

ለካስ ይህች አለም ትንሽ ኖራለች እያለ በልቡ በአምንታ ሲመልስላቸው ፣ «ኧረ በእልቂይቱ ማርያም ! ለካስ የኛው የልቼ ዘር ኖረሃልና» ብለውት ባርከው ካሳለሙት በሁዋላ ፣ «አባትክን ባላውቃቸውም አለቃ እንደሻው ዝቄ በጣም ትዝ ይሉኛል ። አይ ቁመት ። አይ ድምፅ ! የእሳቸው ድምፅ ማንም ዘንድ አልነበረም ። አንድ ቀን ነው ያየሁዋቸው ። ተቀፀል ፅጌ ላይ ። የራጉኤሎች ተራ ነበር ። እንዲያው በዚያ ቁመታቸው ከወንገዝዳር እንደ በቀለ ሸምበቆ እየተወዛወዙ ያንን ድምፃቸውን ሲለቁት እግዚርን ከነዙፋኑ መሬት የሚያወርዱት ይመስሉ ነበር ። ሴሎቹስ ቢሆኑ — ድምፁስ ድምፅ ነበር ። ልክ እኮ ታቦታቱ እየቀደሱ ቤተስኪያንዋ ራስዋ የምታስከካ ነበር የሚያስመስሉዋት ።

«ታዲያ አለቃ እንደሻው በፊት የልጅ ኢያሱ ሁዋላም የንግስት ሰው ነበሩ ። ንግስት ሲሞቱ 'ጽርሃት ቤተ ክርስቲያን' ያሉት እሳቸው ነበሩ ይባላል ። ሁዋላም መሀል ሰፋሪዎች አድማ መተው ፣ ራስ ተፈሪ ንጉስ ተብለው የኢትዮጵያ መንግስት ባለሙሉ ስልጣን እንዲራሴና አልጋ ወራሽ እንዲሆኑ ከተደረገ በሁዋላ በነገሩ ተቆጭተው እንዴት ነበር? እምን

መሀል ሰፋሪዎች ትናንት ተቀምጣችሁ
የስቀላችሁትን እላይ አውጥታችሁ
ምን ነካችሁና ዛሬ በቁማችሁ
አውርዳችሁ መጣል ከቶ ያቃታችሁ?

ብለው የገጠሙት እሳቸው ነበሩ ይባላል ። ሁዋላ እንኩዋን ተቀምጠን የሰቀልነውን ቆመን ማውረድ አቃተን ብለው የተረቱት ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ ናቸው እየተባለ በሰፈው መወራት ጀምሮ ነበር። ብዙ ዘመን በግዞት ተቀምጠው ነው የሞቱት ። አይ ድምፅ ! የዜማ ሊቅ ነበሩ ። አሁን ሳይህ አይነ ውሀህና ገፅታህ ልክ የእሳቸው ነው ። ይገርማል እኮ የፈጣሪ ስራ ። የወለደ አይሞትም ። ሞቶ ስሙ ሲጠራ የሚኖረው የወለደ ብቻ ነው ። የእሳቸው የልጅ ልጅ ኖረሃል ለካ ?» አሉት ።

«ነበርኩ . . . እ . . . ነኝ» አላቸው ።

አባቱ ከመሞታቸው በፊት እንደ መቃዠት እያደረጋቸው . . . ልጅ ባባቱ ሀጢአት ይቀጣል ? . . . ይሉ የነበረው ድንገት መጥቶ ከጆሮው ውስጥ አስተጋባ ። እገልግሉ ቀረበ ።

ገረድዋ ፣ «ከውጭ አሁን የመጣ ነው» ብላ ከፍትፍቱ በመቅመስ ነጠላዋን አደግድጋ ፊትዋን አዙራ እንደ ቆመች ፣ መምሩ በጠጅ ትንፋሻቸው ፣ «በስመ አብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፣ የአብርሃምን ማእድ የባረከ እምላክ ይባርክልን . . .» ብለው ማእዱን ባረኩ ። ከጥቂት ቃላት በሁዋላ የሚሉት አይሰማም ነበር ።

ፊታውራሪ ፣ «አይናለም የት አለች?» ብለው ጠየቁ ።
ሀዲስ ጆሮውን እንቃ ። ከሆዱ ይልቅ አይኑ ነበር የተራበው ።
ፊትዋን ወደ ግድግዳው አዙራ የቆመችው ገረድ ፣ «እሞኢታል» አለች ።

ቶሎሳ ሰንና ብርት ይዞ ጣት ለማስታጠብ ቆሞ ይጠብቃል ። ፊታው ራሪ ጣታቸውን እየታጠቡ ፣ «ምን ሆና?» አሉዋት ።

«ጥርስዋን ተነቅሳ ነው» አለች ።

ከባህር የተለቀሙ እንቁዎች የሚመስሉት ጥርሶችዋ ከበስተጀርባቸው ሆሞት የሚመስል ንቅሳት ሲጨመርበት ምንኛ ውብ ይሆን ይሆን ፣ እያለ ያስብ ነበር—ሀዲስ ።

«ሲያጌጡ ይመላለጡ አሉ ። ሴት ልጅ እኮ ምን ቆንጆ ብትሆን ውበት በቃኝ አትልም» ሲሉ ፣—

መምሩ ጣታቸውን እየታጠቡ ፣ «ሄዋን አዳምን በምን አሳተችው ብለው—በውበትዋ አይደል?» አሉ ፣ ቶሎሳን በአይናቸው ጠቅሰው ባዶ ብርሌአቸውን እያሳዩት ።

ሀዲስ ተራው ሲደርስ ተነስቶ ቆመ ። ቶሎሳም ካልተቀመጥክ ሞቼ እገኛለሁ እንጂ አላስቀምጥብህም በሚል መንፈስ ሰንና ብርቱን እንደያዘ ቆሞ ቀረ ። ፊታውራሪም ቁጭ በልና ታጠብ ቢሉትም አሻፈረኝ በማለት በግድ ቆሞ ታጠበ ። ፊታውራሪ ፣ አሽከሩን የናቀ ጌታውን እንዴት ሊያከብር ይችላል የተባለውን ፈሊጥ ያውቃሉና በሀዲስ ትህትና ተደስተው ፣ «መምህርነት ከዘርህ የመጣ ነዋ ፣ ልጅ ሀዲስ?» አሉት ።

«አዎን ፣ ግን እኔ አስተማሪ ለመሆን አልፈልግም ።»
«ታዲያ ምን ልትሆን ነው የምትፈልገው?»
«የህግ ትምህርት ለማጥናት ነው የምፈልገው ።»

«የእልቂይቱ ማርያም ! ነገረ ፈጅ ልትሆን ? እንዳባቶችህ ያገራችንን ትምህርት ብትማር ምን ነበረበት ፣ ልጄ?»

«የቱን ትምህርት?» አሉ ፊታውራሪ ፣ ራሳቸው እህል ሳይቀምሱ ምሳ የማያበኝ ጉርሻ ጠቅልለው ቶሎሳን እያጎረሱት ።

«እንዴ? ድጉዋ ፣ ፆመ ድጉዋ ፣ ዜማ ፣ ሰዋሰው ፣ ቅኔ —እረ ስንቱ ተቆጥሮ . . .»

«ምን ፋይዳ ሰራ?»
«ኢትዮጵያን እዚህ ያደረሳት ምን ሆንና ነው?»
«የት ደረሰች?»

ቶሎሳ ሌላ ጠጅ ሲያመጣላቸው ትናንሽ አይኖቻቸውን በደስታ እያቁለጨለጩ «መማር ያገራችንን ትምህርት ነው'ይ ። ተማሩ ተማሩ» ካሉ በሁዋላ ፣ «ከከሳቴ ብርሃን ሰላማ ጀምሮ እስካሁን በክርስትናዋ ፀንታ ፣ ነፃነትዋን ጠብቃ እንድትኖር ያደረጋት ምን መሰሎት ? ያገራችን ትምህርት ነው ። ይሄ የፈረንጅ ትምህርት ከገባ ወዲህ ነው ሃይማኖት ላልቶ ፣ መከባበርና መፋቀር ጠፍቶ ፣ ወግና ስርአታችን ላሽቆ ህልውናችን ፈተና ላይ መውደቅ የጀመረው ። ለሚሲዮኖች ትምህርት በራችንን ከፍተን የለቀቅን'ለት ነው በራሳችን ላይ የፈረድነውና አገራችንን ማንም ከፍቶ የሚገባበት የጋለሞታ ቤት ያደረግናት» ብለው ፣ የብርሌ አቸውን አንገት ጨበጡ ።

የባሰውኑ እየሰለለች ትሄድ የነበረችው ሰላላ ድምፃቸው በንዴት ታንቃ ነበረ ። ፊታውራሪ መመገባቸውን አቁመዋል ። ባሳብ የተመሰጡ ይመስላሉ ። አይናለም ድንገት ከጉዋዳ እንደ ነጭ ጉም እየተንሳፈፈች ብቅ አለች ። ሀዲስ የጎረሰው እንጀራ ጉሮሮው ላይ ቀርቶ ትን ሊለው ነበር ። የተሰራችው ቀሚጭን ሹሩባ ትከሻዋ ላይ ወርዶ ዘፍ ብሎ ይታያል ። ነትከሻዋ ላይ ጣል ባደረገችው ቀጭን ነጠላ አፍዋን ሸፍናለች ። ጀርባዋን ለፊታውራሪና ለመምሩ ሰጥታ ሀዲስን ፊት ለፊት እያየችው «ሻ፣ ትፈላጋለህ?» በምትልበት ጊዜ በእጅዋ ትንሽ ቁራጭ ወረቀት ልታቀብለው ትሞክር ነበር ።

አይኑን ማመን አቃተው ። ትንፋሹ ቆመ ። እጅዋን ቀስ ብላ ዘረጋችለት ። ጀርባውን ቀዝቃዛ ላብ አሰመጠው ። ልቡ ቀጥ አለ ። እየተንቀጠቀጠ ቁራጭ ወረቀቱን ተቀብሎአት ቶሎ ብሎ ወደ ኪሱ ጨመራት ። ለኮንድ ዩማትበልጥ ጊዜ ነበረች ። ግን ለረጅም ጊዜ ሲአል ይሁን ገሃነም ጋዶ የተመለሰ ያህል ነበር የተሰማው ። እፎ ተባስሮ ሻሂውን አፈልጋለሁ

ወይም አልፈልግም አላላትም ። እስዋም መልሱን አልጠበቀችም ። ወደ ፈረደባቸው መምሩ ዞር ብላ ፣ «ስጋ ፣ በርበሬና ቅባት እንዳይበሉ ተብለው አልነበረም?!» አለቻቸው ።

መምሩ ብርሌአቸውን የት እንዳደረጉት አይታወቅም ። አይናቸውን ቁልጭ ቁልጭ እያደረጉ ፣ «ምን ነው ብትተይኝ አንቺ ልጅ ። እንደ ጉሬዛ በቅጠል ኑር ነው የምትይኝ? እኔ እህል በእህል መብላት አይሆንልኝም ብዬሻለሁ ። ዳለቻ ሽሮ ሳይ ወስፋቴ ይዘጋል ። ባዶ ውሀም ጉሮሮዬ እሺ ብሎ አይቀበልም ። ውሀ ሲበዛ መሬት ይሰነጠቅ የለም እንዴ? ኧረ ኤዲያ ! ሞትን ሞቼ አልጠብቀው እየኖርኩ ነው እንጂ» አልዋት ።

እግርዋ ወጣ ሲል ብርሌአቸውን ከደበቁበት ከወንበሩ ስር ወጣ አደረጉና አንዶቀዶቁት ። ፊታውራሪ አሁንም ባሳብ እንደ ተመሰጡ ነበር ። የሀዲስ ልብ ክበሮ መደለቁን አላቆመም ። ልቡ ኪሱ ውስጥ ነበር ። ከቁራጭ ወረቀትዋ ላይ የተፃፈውን ለማንበብ ከመቸኮሉ የተነሳ ልቡ ተሰቅሎ የባሰውን ከበሮ ይደልቃል ። ጊዜው እንደ አመት ይረዝምበት ጀመር ።

«አትበላም እንዴ? ብላ እንጂ» አሉት ፊታውራሪ ።

እጅ ነስቶ በቃኝ አላቸው ። ልቡ ከፉኛ ተሰቅሎ ነበር ።

«ምን ነው አላበሀ? ደህናም አይደለህ?»
«ደህና ነኝ . . . »
«ወይስ ማባያው በርበሬ በዛበት!»
«ኧረ ለስላሳ ነው ። እንዲያው ነው ።»

ማእዱ ከፍ አለ ። ፊታውራሪ ቶሎ ቶሎ ጠቅለል ጠቅለል አድርገው ከጎረሱ ማእድ ላይ መቆየት አይወዱም ። መምሩም ቢሆን ከወደ ውሀው ነበር እንጂ እህል በመድፈር በኩል እጅግም አልነበሩም ። ያ ሁሉ ውፍረት ከየት እንደ መጣ ማወቅ ያስቸግራል ። ፊታውራሪ ጣታቸውን እየታጠቡ ፣ «የዘመኑ ልጆች በርበሬውም ምኑም ቶሎ ያማችሁዋል ብዬ ነው . . . » አሉት ።

የባሰውን ያልበው ጀመር ።

ቀጥለውም ፣ «ምግብ ካልለሰለሰ አትበሉ ። ውሀ ካልፈላ አትጠጡ ። አሾህ ቢወጋችሁ የምትሞቱ ይመስላችሁዋል ። በኛ ጊዜ ወንድ ቀርቶ ሴቶችም ቢሆኑ ጠንካሮች ነበሩ ። ሁሩርና ቁር ማን ለይቶ? ከምንጭ ውሀ እየጠጣን ፣ ምድር ያፈራውን እየበላን ፣ ከምድር ላይ እየተኛን ነበር እዚህ የደረስነው ። እንዴ? ይህች አገር እኮ እንዲሁ በተአምር አልቀናችም ። ነፃነትዋም በንቶ የኖረው በተአምር አይደለም ። ብቻ ምን ያደርጋል ? ነገር ሲቆይ ተረት ይሆናል ። ተረት እንደምናወራ አድርጋችሁ ነው የምታዳምጡን የዘመኑ ልጆች» ብለው ፣ በትካዜ ተዋጡ ።

ሀዲስ ቀስ ብሎ ግራ እጁን ወደ ኪሱ ሰደደ ። ቁራጭዋ ወረቀት የትም አልሄደችም ።

«መምሩ ፣ ትድም የተናገሩት ነገር እስካሁን ይከነክነኛል ።»
«የቱ ?» አሉ መምሩ ፣ ብርሌአቸውን አኑረው ።

ሀዲስ ውስጥ ውስጡን ብሽቅ አለ ።

«ሀገራችን በክርስትናዋ ፀንታና ነፃነትዋን ጠብቃ የኖረችው ባገራ
ችን ትምህርት ነው ያሉት ።»

«ኢህሳ ?»
«አይደለም ።»
«እንዴት ?»
«እንዴት ማለት ያባት ነው ።»
«ነው እንጂ ።»

ሀዲስ ምን ብላ ፅፋ ይሆን ? ሲል ማሰብ ጀመረ ። ምን ልትለው እን
ደምትችል አሰቦ ሊደርስበት ባለመቻሉ ነገሩ ይበልጥ ምስጢራዊ እየሆ
ነበት የባሰውን ይጨነቅ ጀመር። የጭንቀት ጭንቅ ተጨንቆ ፤ መጨነቅ—
ምን ልትለኝ ትችላለች ? . . .

«ቤተስኪያን ነፃነታችን ፀንቶ እንዲቆይ ማድረግ ቀርቶ ለራስዋም
እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ነፃነት አልነበራትም» በማለት ንግግራቸውን
ጀመሩ—ፊታውራሪ ። «የስክንድርያ መንበር አፈ-ቀላጤና ተገዥ ሆና
አይደለም እንዴ የቆየችው ? ታዲያ እነሱ ህዝባችን አይኑን እንዲከፍት
መቼ ይፈልጉ ነበር ?»

መምሩ እንደ መናደድ ብለው የተቀመጡበትን ወንበር ከስር እያን
ሜጡ፤ «ማን አስተማረ? ማን ፊደላችንንና ቅርሳችንን ጠብቆ ቆየ ? ማን
ክርስትናን አስፋፋ ሊሉ ነው ታዲያ ? እንዴ ? ይህ ትምህርት ሚኒስቴር
የሚባለውን መስሪያ ቤት እኮ አሁን የመጣ ነው እንጂ ፤ ትምህርት ሚኒ
ስቴር ሆና ስታገለግል የቆየችው ቤተ ክርስቲያን ናት ። ወቸ ጉድ ! ኧረ
የሰማእታት ፤ የቅዱሳን ጆሮ አይስማዎት» አሉ ።

ፊታውራሪ ከተቀመጡበት ተነስተው ወደ መስኮት በመሄድ ሩቅ
ይመለከቱ ጀመር ።

ሀዲስ እድሌ አሁን ነው በማለት እጁን ወደ ኪሱ ሲሰድ ፊታውራሪ
ዞር ብለው በረጅሙ ተነፈሱና ፤ «ትምህርቱስ ቢሆን መቸ ካውደ ምህረት
አልፎ ያውቅ ነበር ? ክርስትናን በማስፋፋትም ቢሆን እኮ ፤ ጦር ፤ ጋሻና
ጎራዴ ይዘን እየቀደምንና ታቦት አስከትለን እየተከልን ሀገር ያቀናነው
እኛ ነበርን» ብለው ከቶኛ እየተከዙ ፣ «አያልፍ የለም ። አይ ጊዜ ! ጊዜው
ዛሬ የሌሎች ነው ። እኛ እንደሆን የወረዳ ዳኛ ፤ የወረዳ ገዥ ፤ የወረዳ ፖሊስ
አዛዥ መጫወቻ ሆነናል ።»

መምሩ ነገሩን ለመቁረጥ ሳይሆን አይቀርም፤ ክርክሩን ትተው ፤ «ኧረ
የሰይጣን ጆሮ አይስማዎት !» አሉና ብርሌእቸውን ጨበጡ ።

«ቢሰማስ !» አሉ ፊታውራሪ ተቆጥተው ። ከግንባራቸው መሀል ያለው
የደም ስር ቆሞ ይታያል ። «ሀገር እንደ ሆነች የገንዘብ ስልቻዎች ሆና
ለች ። ግን ፤ ምን ይደረግ ? ጳጳሱም ንጉሱም አንድ ሰው የሆነበት አገር ።
ባንዳዎችን ፤ የገንዘብ ስልቻዎችንና ወፍ ዘራሮችን ሰብስቦ አገር እገዛ
ለሁ ማለት የት እንደሚያደርስ እናያለን ! እድሜ ከሰጠን ። ይሁን እስቲ ።
እኛ ፤ ነበርን እንጂ ዛሬ የለንም ። ታሪክ ለጉድ የጎለተን ሰዎች ነን ። የሚ
ቀረን ነገር ቢኖር ትናንት የጠፋው አለም ትውስታ ብቻ ነው ። እሱም

ቢሆን ስናልፍ ከኛ ጋር አብሮ ያልፋል ። እያልፍ የለምና» እንዳሉ ፣ ቶሎሳ መጥቶ በጆሮአቸው አንድ ነገር ሹክ ሲል ፣ «አስገባቸው ። ዱሮውን የለየን ያዬ መንግስት ነው ። ህዝቡ አውራውን መቼ አጣው ?» አሉት ። ፊታቸው ላይ እንደ ጥቁር ደመና ያንዣብብ የነበረው ጥላ እየጠፋ ሲሄድ ይታይ ነበር ።

«ኧረ የሰይጣን ጆሮ አይስማዎት !»

ሀዲስ አሁን አላመነታም ። ለመሄድ ቆርጦ ተነሳ ። ከቁራጭ ወረቀትዋ ላይ የተፃፈውን ነገር ማንበብ ወይም ከጭንቀቱ የተነሳ መፈንዳት ነበረበት ። ፊታውራሪ ድንገት ተነስቶ ለመሄድ በመቸኮሉ ተገርመው ፣ «የዘመኑ ልጆች እኮ አንድ ቦታ አርፋችሁ መቀመጥ አትችሉም ። ምን የሚያስቸኩልህ ነገር መጣ?» ብለው ፣ እንዲቆይ ቢጠይቁትም እሺ አላላቸውም ። ሲወጣ ሩጫ ነበር የቀረው ።

ከግቢው ወጥቶ ቁልቁለቱ ላይ ሲደርስ በሚንቀጠቀጥ እጁ ቁራጭዋን ወረቀት ከኪሱ አወጣና ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ ሲያነብ ፣ በቆንጆ ትባልቅ የእጅ ፅህፈት የተሳለፈለት መልእክት ፣ «የሚነበብ መፅሀፍ ካለህ ላክልኝ ፣ እደራ» የሚል ነበር ። ወረቀትዋን ገልብጦ ጀርባዋን ተመለከተ ። ወረቀትዋ ተጨማሪ መልእክት አላዘለችም ። የወረቀትዋ ነጭ ጀርባ ንፁህ ነጭ ነበር ። በጣቅ ፈነዳ ። ሳቁ በመላ ሰውነቱ የሚሰማ ያህል ነበር ። ቁልቁለቱን ወርዶ ፣ በትምህርት ቤቱ አድርጎ ፣ መብተን የጀመረውን የእሁድ ገበያ አቋርጦ ቤቱ ሲደርስ ሁሉ የኮረኮሩትን ያህል ይስቅ ነበር ።

እርሾ እንደ በዛበት ሊጥ ኩፍ ብላ ከቤት የጠበቀችው ሽታዬ ፣ ሳቁ ደበልጥ አስቆጣት ። ሳቁን ለማቆም አልቻለም ። ሽታዬን ሲያይ እንዲያ ወ ም ባሰበት ። ጥፍሮቹን የዘረጋ ነብር መስላ ታየችው ።

«ከሴት ልጅ ጋር ይሳቃል እንጂ በሴት ላይ አይሳቅም ! እንደ ጉልቻ ተጎልቼ መጠበቄ ነው የሚያስቅህ ?» ብላ ፣ ለምቦጭዋን በመጣል ደም ጎርሳ ደም ለብሳ ስትመጣበት እጅዋን ይዞ ፣ «ባንቺ አይደለም የምስቀው ። እውነት» አላት ።

«ታዲያ ምንድን ነው የሚያስቅህ ?»
«እንዳልሺው በውበት አይሳቅም ።»
«እኮ ?»
«አንዳንዴ የሳቅ በሽታ አለብኝ ። ዝም ብሎ ያስቀኛል ።»
«ሆ ! ጠበል አትሄድም ታዲያ ?»
«ለምን ?»
«ብቻቸውን የሚስቁት እብዶች ብቻ ናቸው ! እኔ እንደማውቀው . . .»
«ቁልጭ ግጥጥ ብሎ ስለሚታዩቸው ይሆናላ ።»
«ምኑ ?»
«የሰው ልጅ ወይም የህይወት አስቂኝ መልክ ።»
«አብድ ነኝ በላ !»
«ነካ የማያደርገው ማን አለ ብለሽ ? ሲያስቡት ያስቃል እኮ ።»
«ምኑ ?»

«የሰው ነገር—ህይወት» ብሎ እየሳቀ ፣ «አለ አይደል ? የሞት ጥላ በላዩ ላይ እያንዣበበበት የሚኖር ፍጡር ሁሉ ጤነኛ መሰለሽ ? እኔን

ከሌላው የበለጠ ይብድ እንጂ ነካ የማያደርገው ሰው የለም ። በሁላችንም ላይ ያለ በሽታ እኮ አንድ ነው—ህይወት የሚሉት በሽታ ። አስቆ ያስለ ቅሳል ። እንዴት ልበልሽ ? አለ አይደል—ሲቀርቡት እንደ ጥላ እየራቀ የሚሄድ ፅላላዊ ሀልውና—አስቆ የሚያስለቅስ ወይም አስለቅሶ የሚያስቅ» ሲላት ፣

«ሆ ! የምትናገረው አማርኛ ሁሉ አይገባኝም እቴ ። እውነትም አብ ደሃል ። የእብድ መድሀኒቱ እኮ እግሮ ብረትና ጠበል ነው» ብላው ፣ ተመ ልሳ ቁጭ ስትል ፣ «እስረኛ በቃ ። ከጠበሉም አጠጪኝ ። ከህይወት በሽታ እፈወሳለሁ ። አልስቅም በቃ ። ዝም እንደ እናቴና አባቴ መቃብር» ብሎ እት ሲያበቃ ፣ «እሱን እንተውውና ምሳሽን በልተሻል ወይ ?» አላት ።

«ብቻዬን እንድበላ ኖርአል የጋበዝከኝ ?»
«አይደለም ። አብረን የገረዴን ወጥ እንድንቀምስ ነበር ።»

ምሳ ቀርቦ ሲበሉ ፣ «እኔ ብቻ ነኝ እንዴ የምበላው ?» አለችው ቆጣ ብላ ።

«እኔኮ በልቼ ነው የመጣሁት ።»

«ከሔይናለም ጋር ነው የበላኸው ? አይንህ ይጥፋና !» አለችው ትላልቅ አይኖችዋን እያጉረጠረጠች ።

«አብረን አልበላንም ።»
«መልኬ በቃኝ ብላ ?» ስትል ጠየቀችው እያሾፈች ።

«ጥርስዋን ተነቅሳ ነው» አላት ፣ ምን መፅሀፍ ልላክላት በማለት እያሰበ ።

«ስቃ አሳየችህ ?!» አለችው ጥፍሮችዋን እንደ አራስ ነብር እያቆመች።

ሁኔታዋ አሳማረውም ። የተቀባችው ቀይ የጥፍር ቀለም ደም መስሎ ታየው ። የአባብ መርዝ ከምላስዋ ስር አውጥታ የምትተፋበት ይመስል አይኖቹን ጭፍን አደረገ ።

«ይህን ጎረጥ አይንህን አንድ ቀን እንደማወጣልህ ታውቃለህ !» አለችው ፣ እንደ እባብ ሲጥጥ በሚል ላንቃ ።

«ምን ባጠፋሁ የኔ እመቤት ?» አላት ፣ ስቆ ሊያሳስቃት እየሞከረ ።

«ካለኔ ሌላ ያይና ዋ ! ብያለሁ» ስትል ፣ አይኖችዋ ውስጥ የሚዋጋ ቀንዳም ሰይጣን ያየ መሰለው ።

«አይን የተፈጠረው ሁሉን ለማየት ነው ፣

አንቺን አይቶ ሌላ—እውይ—አላይ አለ ምን ነው ?» እያለ ዘፈነላት።

ድምፁ መጥፎ አልነበረም ።

«አይንህ ይጥፋ !» ብላ ፣ ስለ ዘፈኑ አሽሙዋጠጠችውና ፣ «አስተማ ሪዎች ለትባሉ እንዲያው በየደረሳችሁበት የምታስተምሩበትን መጥፎ

ሳትገልጡ አይናችሁ የሚንከራተተው የባላባትና የሀብታም ልጅ ፍቢጋ ነው ። አይደለም ? መቼ አጣሁዋችሁና ? አይናለም ሱሚ ናት ። አትገኝም ። ይገባሃል ? ግን አንተ አይገባህም ። እስቲ አለ እኔ ንክች ። እንተያያታለን ። በዚህ ጥፍሬ ነው የምዘለዝልህ ። ይገባሃል ?» አለችው ፣ ንዴትዋ ገንፍሎ እያፈጠጠችበት ።

«አይን የተፈጠረው ሁሉን ለማየት ነው ፣
እንቺን አይቶ ሌላ—አዩዩ—አላይ አለ ምን ነው ?»

ዘፈኑን ደገመላት—ሲያስበው ብዙ ያማርኛ መፅሀፍ ይዞ አልመጣም ።
«ኡኡቴ—እሰይ !»

«ድምፄ ወፍ ከዛፍ ያወርድ የለ ? ያያቴም ድምፅ ግሩም ድምፅ ነበር አሉ ። የዘር ነዋ ። ምን ይደረግ ። መምህርነትም ከዘሬ የመጣ ነው» አላት ።

«ካልክስ አቶ ይርጋ መጥተውልሃል» አለችው ።

«አትይኝም !»

«እንዲያውም ማታ አንድ ወጠጤ አስተማሪ መጥቶልናል ሲሉ ነበር ።»

«እውነት?»

«የመድ አለቃ አሽኔም ፣ ‘ከወጠጤም ወጠጤ፤ ገና ከመድረሱ ለመ ንደር ሰዎች እብሪት የተሞላበት ደብዳቤ እየገፈ እስቸግሮአል’ ሲላቸው ነበር» አለችው ።

«ምን አሉት ታዲያ ?»

«ምን መልስ እንደ ሰጡት አልሰማሁም ።»

«አ ! ሊከፈት ነዋ !» አለ ድምፁን በመለወጥ — ትልቁ የቡዱ ትም ሀርት ቤት ሊከፈት ነው ! አንድ አመት ብዬሽ የለም ? አንድ የተረገመ አመት ። ርግማን ባይኖርብኝ ኖሮ እኮ መጀመሪያውኑ እዚህ አልመጣም ነበር ። ርግማን ሳይኖርብኝ አይቀርም ። እውነቴን ነው ። አንድ አመት ። ከዚያ በጨለማ ተነስቼ እንደ መጣሁ ከዚህም በጨለማ ተነስቼ ጭልጥ ማለት — በመርዳሳ በቅሎ ። ሊያስተምሩበት ቀርቶ ሲያዩትም ይቀፋል — ትምህርት ቤቱ ። የተረገመ ህይወት ። የተረገመ ትምህርት ቤት . . .»

# ክ ፍ ል ፭

ሱዱ የሆን ነገር ሳይሰማ ውሎ አያድርም ። ትንሹ ነገር ወዲያውኑ ጆር ይገባል ። እንዳዲሳባ ፥ በሱዱ ማን ያየኛል ? ማን ይሰማኛል ? ብሎ እንደ ልብ መሆን አይቻልም ። ወሬ እንዴት አድርጎ እንደሚዛመት ሁዲስ ሁልጊዜ ይደንቀዋል ።

የአቶ ይርጋ አለሙን መምጣት ለማሳወቅ ነጋሪት አልተጎሰመም ። ደወል አልተደወለም ። እምቢልታ አልተንካለለም ። ጥሩምባ ተነፍቶ አልተለፈፈም ። ግን አቶ ይርጋ አለሙ ከመቱ ወደ ሱዱ ከተመለሱ ማግስት ጀምሮ ከሶስት ወር በላይ ተዘግቶ የቆየው ትምህርት ቤት በይፋ መከፈቱ ከዳር ዳር ተሰምቶ ተማሪዎች በብዛት እየመጡ መመዝገብ ጀምረዋል ። ሌሎቹም አስተማሪዎች መጥተው ነበር ።

ከአቶ ይርጋ አለሙ ጋር ከመገናኘቱ በፊት አቶ ጣሴ ደጉን ፍለጋ ሄደ ። በሱዱ አቶ ጣሴን የማያውቃቸው ሰው አልነበረም ። ትንሽ ትልቁ ያውቃቸዋል ። ሕና ፥ የሚኖሩበትን ቤት ለማግኘት ችግር አልገጠመውም ። ትንሽ ቤት ውስጥ ነበር የሚኖሩት ። የደጁ አበባ በጣም ደስ ይላል ። አቶ ጣሴን ያገኛቸውም አበባ በመኮትኮት ላይ እንዳሉ ነበር ። ራሱን አስተዋውቆ ታፈሰ ብሩ የላከላቸውን ስጦታ አስረከባቸው ።

የተላከላቸውን ስጦታ ለማየት ቸኩለው ስጦታው የተጠቀለለበትን ወረቀት እየከፈቱ ፥ «ታፈሰ ደህና ነው ? ዋና ዲሬክተር ሆኗል አሉ ። እሰይ ። ሀሁ ያስቆጠሩት ልጅ ለዚህ ወግና ማእረግ ደርሶ ከማየት የበለጠ ደስታ የሚሰጥ ነገር የለም ። አንዱም ተማሪዬ ሰሎሞን ዋለልኝ ረዳት ሚኒስትር ሆኗል ። ታውቀዋለህ ?» አሉት ።

«አዎን ፥ አንድ ቀን ተገናኝተናል» አላቸው ፥ ያንን አስቀያሚ ፓርቲ እያስታወሰ ።

«ምን ነው ከፋህ ?»
ድንገት ብሎ ፥ «ኧረ ምንም አልከፋኝም» አለ ።
«ሰሎሞን የበደለህ ነገር አለ ?»
«ኧረ ምንም የለም» አለ ፤ ስሜቱን ከመቅፅበት ለማንበብ በመቻላቸው ከመገረም አልፎ እየተደነቀ ።

«ደህና » አሉት ፤ ታፈሰ የላከላቸውን ፓርከር ብእር በአድናቆት እየተመለከቱ ቆዩና ፥ «መልካም ማስታወሻ ነው የላከልኝ ። ከብእር የበለጠ መሳሪያ የለም» ብለው ፥ ባሳብ ጎዳና ላንዳፍታ ጭልጥ ብለው ከሄዱ በሁዋላ ፥ «ታፈሰ ለዚህ ቁም ነገር ይበቃል የሚል ግምት አልነበረኝም ። ይገርማል ። ከፈሉ የተጣላ እብድ እንዲያው የሰይጣን ቁራጭ ነበር ። እሁንስ እንዴት ነው — እብደቱን አልተወም ?» አሉት ።

አቶ ጣሴ ቁመናቸው ዘለግ ያለ ጠይም ፣ ራስ በራ ሰው ናቸው ። እድሚአቸው የገፋ ቢሆንም ሽበት አይታይባቸውም ። ወዛቸው እንዳለ ነው ። ሲናገሩ ያፍናቸዋል ። ትርፍ ስጋ የሚባል ነገር በሰውነታቸው ላይ አይታይም ።

«ጨዋ ነው ። እንዲያውም እንደ ነገረኝ ከሆነ ስራውን ለቆ እዚህ ለመምጣት ይፈልጋል ። ገበሬ ለመሆን ይመኛል» አላቸው ።

«አዬ የሱ ነገር ! በልጅነቱም አንድ ነገር ላይ መርጋት አይወድም ነበር ። አሁን ወደ ግብርና ለመመለስ ምን አስመኘው ? እዚያው ቢቆይ ይሻለው ነበር ። ሚኒስትር ለመሆን ትንሽ ሲቀረው ። ምን ታይቶት ይሆን ?» አሉ በነገሩ እየተገረሙ ።

«ግብርና ያዋጣኛል ብሎ አስቦ ይሆናል ። እውነትም ደግሞ ብዙ ወጣቶች ደህና ስራ እየለቀቁ ወደ ግብርና በመግባት ላይ ናቸው ። ብዙዎቹም አመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ከብረዋል» አለ ።

ቤት እንዲገባ ጠየቁት ። ከደጁ ማማር የቤቱ ንፅህና ደግሞ ይበልጥ ደስ ይላል ። ወለሉ እንደ መስተዋት ፊት ሊያሳይ ምንም አይቀረውም ። የቤቱ እቃ ሁሉ በስርአት ተቀምጦ ይታያል ። ቤቱ ውስጥ ሌላ ሰው የለም ።

«ሻሂ ላፍላልህ ?»

«እሺ» አለ ። ፕሪሙዛቸውን ቱግ አድርገው ሻይ አፍልተው ሰጡት ። እንደዚያ ግሩም ጣእም ያለው ሻይ የትም ቀምሶ አያውቅም ።

«ግሩም ሻይ ነው» አለ ።
«ልድገምህ?»
«በቃኝ ። አንዱ ያረካል ።»

«ኋኔው ነኝ ሁልጊዜ የማፈላው ። እንደምታየው ሚስት ፣ ልጅ የለኝም ። ልጆቼ ተማሪዎቼ ናቸው ። አትክልቶቼንና ተማሪዎቼን ከመንከባከብ የበለጠ ደስታ የሚሰጠኝ ነገር የለም» ካሉት በሁዋላ ፣ «ለመሆን እዚህ እንዴት ልትመጣ ቻልክ ?» ብለው ጠየቁት ።

«የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነኝ ። በግል ችግር ምክንያት ስራ ስፈልግ ድንገት እዚህ ስራ አግኝቼ ነው የመጣሁት ። ከታፈሰ ጋር ባንገናኝ ኖሮ እዚህ አልመጣም ነበር ። ለማንኛውም ነገር እዚህ የምቆየው ላንድ አመት ነው» አላቸው ።

ድንገተኛ ሳል ያዛቸው ። ከፉኛ ይስሉ ጀመር ። ታፍነው የሚሞቱ መስሎት ኢብርአቸው ይጨንቅ ጀመር ። ሲጥ ሲጥ የሚል ደረቅ ሳል ነበር የሚስሉት ። አስሉ ፣ አስሉ ፣ አስሉ ሲተዋቸው በእፎይታ ወደ ውጭ በሃይል ተነፈሱና ፣ «ሃይለኛ አስም አለብኝ ። ከፋ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ሳስተምር ነው የያዘኝ ። ቆይቶብኛል ። ገድሎ አይገድለኝ ነገር እንዲሁ ያሰቃየኛል ። በተለይም የዚህ ወራት የአበባ ሽታ ሲሸተኝ ይብሰብኛል ። የጠመኔ ብናኝም አይወድልኝም» አሉት ።

«ታዲያ ለምን አይተዉትም ?»
«ምኑን?»
«አትክልት ቤትክታውንና ማስተማሩን . . .»

«ከሁለቱ ተለይቼ መኖር የምችል አይመስለኝም ። የሚገርመው ነገር ልክ እንዳንተው ሳንድ አመት አስተምሬ ሌላ ስራ እፈልጋለሁ ብዬ ነበር የመምህርነት ስራ የጀመርኩት ። ይሄው ሰላሳ አመት አስፈኝ ። በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች ተዘዋውሬ አስተምሬአለሁ ። የማስተማር ነገር ደምህ ውስጥ ከገባ አይወጣም ። ካንተ የሚበልጡ ሰዎች አፍርቶ ማየት — ትልቅ ቦታ ደርሰው ትልቅ ቁም ነገር ሲሰሩ ማየት ደስ ይላል ። በህይወት ከዚህ የበለጠ ወሮታ ምን አለ ? ትልቅ ቦታ ሳይ የደረሱ የቀድሞ ተማሪዎቼ ሌላ ስራ እንፈልግልህ እያሉ ሁልጊዜ ያስቸግሩኛል ። እኔ ግን አልፈልግም ። ከፍሌ ገብቼ ሳስተምር የሚሰማኝ ደስታ ይሄ ነው አይባልም» አሉት ።

ቀለሙ ተለይቶ የማይታወቅ አንድ አለንጋ ከፅህፈት ጠረጴዛቸው ላይ ተዘርግቶ አየ ። ታፈሰ ስለ አቶ ጣሴ አለንጋ ያጫወተው ትዝ አለው ።

«ታፈሰ ስለዚህ አለንጋ አጫውቶኝ ነበር» አላቸውና አለንጋውን አንስቶ እየተመለከተ ፣ «እሱ ነው ወይስ ሌላ ?» ብሎ ጠየቃቸው ።

ከተጎነጎነ ቆዳ የተሰራ አለንጋ ነበር ።

«እሱው ነው ። ከሰላሳ አመት በላይ እድሜ አለው ። ዛሬ ለብዙ ቁም ነገር የደረሱ ብዙ ሰዎችን ቀጥቶ ያሳደገ አለንጋ ነው ። ከተማሪዎቼ መካከል ጀርባቸው የዚህን አለንጋ ጣእም ያልቀመሰ ጥቂቶች ናቸው ። በዱላ አላምንም ። የፍቅር አለንጋ ነው » አሉት ።

እንደገና ያስላቸው ጀመር ። ነፍሱ ከአቶ ጣሴ ደጉ ጋር አብራ ተጨነቀች ። እሁንም ሳሉ ብሎ ብሎ ሲተዋቸው በእፎይታ ተንፈሱና ፣ «በል እንግዲህ እዚህ መምጣትህ ደህና ነው ። ምናልባት ትምህርት ቤቱ ደስ አይልህ ይሆናል ። በላያችን ላይ ሊፈርስ ደርሶአል ። ታዲያ መንግስት በጀት ካጣ ህዝቡን እንዲረዳን ጠይቀን እናሳድሰው ወይም ሌላ እንስራ ሲሉት አቶ ይርጋ ደስ አይለውም ። እኔንማ እንደ ጠላት ነው የሚያየኝ ። ለመሆኑ ተገናኝታችሁዋል ?» አሉት ።

«ገና አልተገናኘንም» ብሎአቸው ፣ ነገሩ ስለ ከነከነው ፣ «አቶ ይርጋ የሰው ምክር መቀበል ለምን ይጠላሉ ? ለበጎ አላማ መቀደም ከፋ አይደለም ። ለበጎ አላማ መተባበር ጥሩ ነው» አላቸው ።

«ነው ። ነው ልጄ ። ግን እሱ ደስ አይለውም ። ብዬ ብዬ ደክሞኛል ። 'ምን አገባችሁ ? እርፋችሁ አስተምሩ ። የናንተ ግዴታ ማስተማር ነው ። ሌላውን ለኔ ተውልኝ' ይላል ሲናገሩት ። እሱ ደግሞ አይሰራም ። 'ለበላይ አመልክቻለሁ' ነው የሚቀናው ሁልጊዜ ። ትምህርት ቤቱ እስኪወድቅ ድረስ መጠበቅ ምን ያደርጋል ? በዚህ ላይ ፣ ይህም ትምህርት ቤት ሆኖ ተጣቦአል ። በያመቱ ቦታ የለንም እያልን ከበር የምንመልሳቸው ልጆች ቁጥር ይህ ነው አይባልም ። ያሳዝናል» አሉ — እዝነው ።

«በመምህራኑ መካከል መግባባትና ትብብር ካለ እኮ ነገሩ ቀላል ነው ። ግሳደስ ቀርቶ አዲስ ትምህርት ቤት መስራት ይቻላል ። ሰው ከተባበረ የማይሰራው ተአምር የለም ።»

«አዎን ፣ እሱስ ነው ። ግን የሚያጣላ ነው እንጂ የሚያስተባብር ሰው የለም ። እንዳልኩህ ብዙ ትምህርት ቤቶች ዞሬ አስተምሬአለሁ ። ሆኖም እንደ አቶ ይርጋ ያለ ዲሬክተር አጋጥሞኝ አያውቅም ። ምክትል ዲሬክተር አያስቀምጥም ። አሁንም የለንም ። ምክትል ዲሬክተር እንድ ሆን ጠቅላይ ግዛቱ ብዙ ጊዜ ጠይቆኝ ነበር ። እኔ ከማስተማር ሌላ ምንም አልፈልግም ። አቶ ይርጋ ዛሬ አንዱን መምህር 'ምክትሌ' ሳደርግህ ነው ፣ ነገ ደግሞ ሌላውን ፣ እንዲሁ እያለ በማታለል ፣ መምህራኑን እርስ በርሳ ቸው ሆድና ጀርባ ሲያደርጋቸው ይኖራል ። የኛ ነገር ያሳዝናል ። እኔም ከእንግዲህ የትም ልሄድ አልችልም ። አርጅቻለሁ ። ሌላ ቦታ ሄጄ አዲስ ጎጆ ለመቀለስ አቅም ያንሰኛል ። ግን በይበልጥ የሚያሳዝነኝ ፣ ቅን ሆነን ቀናውን መንገድ ለተማሪዎቻችን ለማሳየት አለመቻላችን ነው» አሉት እዝን ፣ ትክዝ ብለው ።

ከአቶ ይርጋ ጋር ለመተዋወቅ ሄደ ።

አቶ ይርጋ ሀዲስን ገና ሲያዩት አልወደዱትም ። ከዩኒቨርሲቲ በመ ምጣቱ የተሰማቸውን ቅሬታ ሳይሸሽጉ ፣ «እንዴ ? ከመምህራን ማሰል ጠኛ ትምህርት ቤቶች የተመረቁ ስንት መምህራን እያሉ አንተን ለምን ላኩህ ? ትምህርትህን ብትጨርስ አይሻልህም ነበር ? ለመሆን የማስተማር ልምድ አለህ ? ወይስ ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ መግደል እንዲሉ ፣ ላንድ አመት እርፈህና ገንዘብ አጠራቅመህ ለመመለስ ነው የመጣኸው ?» እያሉ በጥያቄ ሲያጣድፉት ፣ ከሰፊ ትከሻቸው ላይ ጉች ብላ የምትታየው ትንሽ መላጣ ጭንቅላታቸው እያስጠላችው ሰላላ ድምፃቸው ጆሮውን እየወጋው ፣ ዝም ብሎ ሲያዳምጣቸው ከቆየ በሁዋላ ፣ «የማስተማር ልምድ የለኝም ። ግን የሚቻለኝን እሞክራለሁ ። የመጣሁት ለእረፍት ሳይሆን በችግር ምክንያት ነው» ሲላቸው ፣ ሁልጊዜ የሚያልበውን መላጣቸውን በአዳፋ መሀረብ ጠርገው ፣ «እኮ—ይህንኑ አይደለም ያልኩት ? አስተ ማሪነት የችግር መወጫ አይደለም ። ሙከራ የምናካሂድበት ቦታም አይደ ለም ። የነገውን ትውልድ ኩትኩተን የምናሳድግበት ክቡር ስፍራ ስለሆነ ፣ እዚህ የሚያስፈልጉን በሙያው ጥሩ ልምድ ያላቸውና ለሙያው መስዋ እት የሚሆኑ ዲሲፕሊን ያላቸው አስተማሪዎች ናቸው ። የነገው ትውልድ የማንም መለማመጃ መሆን የለበትም ። ደሞ እኮ የገረመኝ ፣ የደሞዝህ ነገር ነው ። ባስተማሪነት የሰለጠኑም ያንተን ያህል ደሞዝ አያገኙም» አሉት ።

መልስ ልስጣቸው ወይስ ዝም ልበል ? እያለ ሲያስብ ታፈሰ ብሩ ስለ እሳቸው የነገረው ነገር ትዝ ስላለው ካሁኑ ከዚህ ሰው ጋር ምን አጋ ጨኝ በማለት ዝምታውን መረጠ ። አቶ ይርጋ ዝም አላሉትም ። ቀጥለው ፣ «ትምህርት ቤት ለመግባት የሚፈልጉትን ተማሪዎች ከዛሬ ጀምረህ መዝግበህና ፈትነህ ውጤቱን ባስር ቀን ውስጥ እንድታስታውቀኝ ። ካስር ቀን ማለፍ የለበትም» አሉት ።

አሁን ዝም ለማለት አልቻለም ። «ላገሩም ሆነ ለትምህርት ቤቱ እንዲሁም እርስዎ እንዳሉት ለሙያው አዲስ ነኝ ። አሁን ያዘዙኝን ስራ ላንዱ ነባር አስተማሪ ቢሰጡት አይሻልም ?» አላቸው ።

አንዴ አገሱና ከተቀመጡበት ብድግ ብለው ፣ «የሚሻለውን የማው ቀው እኔ ነኝ ! ያዘዝኩህን ትስራ እንደሆን ስራ ። አልሰራም የምትል ከሆንም ንገረኝ» ብለው ፣ በሰላላዋ ድምፃቸው እንዴ ምሁበት ።

«ለስራው አዲስ ነኝ እያልኩዎት ለምን እኔ ብቻ ? . . .»

«የመማሪያ ቦታ አይደለም ብዬሃለሁ ወንድም ! ትሰማኛለህ ? አስተማሪ ነኝ ብለህ ከመጣህ ሂድና ስራ ። እና ፥ ደግሞ ከአንግዲህ መልስ አልፈልግም ! ባስር ቀን ውስጥ ብዬሃለሁ !»

የተሰጠውን ትእዛዝ መፈጸም ነበረበት ። ምርጫ አልነበረውም ። በዚህ አለም ምርጫ ያለው ማነው! በዚያም ላይ ማስተማር ነበረበት ። የተሰጠው እለታዊ ፕሮግራም ቀላል አልነበረም ።

አንደኛ ክፍል ለመግባት ብቻ የተመዘገቡት ተማሪዎች ቁጥር ከሶስት መቶ በላይ ነበር ። ቁጥሩ አላስጨነቀውም ። ይልቅ የጨነቀው ከሶስት መቶ ተመዝጋቢዎች መካከል በተሰጠው ጥብቅ ትእዛዝ መሰረት ስድሳ ብቻ እንዴት አድርጎ እንደሚመርጥ ነበር ። ከስድሳ ሌላ ሳንድም ተጨማሪ ተማሪ ቦታ እንደ ሌለ ተነግሮታል ። ከባድ ፈተና ከማዘጋጀት ሌላ ምርጫ አላገኘም ። ፈተናውን ሲያወጣ ህሊናውም ጭምር ነበር አብሮ የተፈተነው ። አብዛኛዎቹን ተፈታኞች ለመጣል ሆን ተብሎ ታስቦበት የሚዘጋጅ ፈተና የትምህርትን መሰረት አላማ ውድቅ ከማድረግ አልፎ ፈታኙን ራሱን መልሶ ከባድ የህሊና ፈተና ላይ የሚጥል ከባድ ወንጀል ሆኖበት ሌሊት ሲቃዥ ያድራል ። ቀንድና ጅራት ያወጡ ህፃናት የገሃነምን እሳት አስር እጥፍ የሚሆን አንድደው ፥ ዙሪያውን በመዞር እየጨፈሩ እርቃኑን ጎትተው ከእሳቱ ላንቃ ውስጥ ሲጥሉት ሆዳቸው የተነፋ ፥ እግራቸው የቀጠነ ፥ ጭንቅላታቸው የከበደ ህፃናት እንደ ቢላዎ የተሳለ ጥርሳቸውን እንደ ተናደደ ሰይጣን እያፋጩበት ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ካለው ትልቅ ወርካ ላይ አውጥተው ሆ እያሉ ሲሰቅሉት — በሺህ የሚቆጠር የህፃናት ሬሳ ከመቃብር እንደ ትል ተፈልፍሎ ወጥቶ ሲወረው— ከጠራ ሰማይ ድንገት መብረቅ ተንተርክኮ ሲወድቅበት በህልሙ ይመጣበታል ። ከትምህርት ቤቱ ግድግዳ ላይ እርቃኑን እንደ ቆመ አስደግፈው በጥይት እሩምታ ይደበድቡታል ። ግን አይሞትም ። ይጮሃል ። የሚያስጥለው የለም ። ሮጦ ለማምለጥ ይፈልጋል ። እግሩ አይንቃነቅም ። ሲመለከተው ከቆመበት ቦታ ላይ እግሩ ስር አብቅሎአል ። ያበቀለውን ስር ከእግሩ መንቀል ያቅተዋል ። ሊንቃነቅ አይችልም ። ሌላ የጥይት እሩምታ ። ላብ በላብ ሆኖ እየጮኸ ይነቃል ።

በሩ በሃይል ይንኳኳኳዋ ነበር ። ሰአቱን ሲመለከት ከጠዋቱ አስራ ሁለት ተኩል ይላል ። ተነስቶ በሩን ከፈተ ። ማመልከቻ ፃፍልን ለማለት የመጡ ሰዎች ይሆናሉ ብሎ አስቦ ነበር ። ቶሎሳ ነበር በሩ ላይ የቆመው ።

ሀዲስ እንቅልፍ ያልጠገቡትን አይኖቹን እያሸ ፥ «ለካ አንተ ኖረሃል የጥይት እሩምታ የምትለቅብኝ» አለው ።

«የምን ጥይት ?»

«ተወው ። መጥፎ ቅዠት ውስጥ ነበርኩ» ብሎት ፥ ተንጠራርቶ አዛጋና ፥ «ምን ነው ደህና ?» ሲል ጠየቀው ።

«በቀደም ለት የወሰድኩዋቸውን መፃፎች ልመልስ ነው» ብሎት እራቱንም መፃህፍት ይሰጠዋል ።

'አርአያ' ፣ 'እንደ ወጣች ቀረች' ፣ 'ፍቅር እስከ መቃብርና' 'አደፍርስ' ነበሩ—መፃሀፍቱ ።

ተገርሞ መፃሀፍቱን እያየ ፣ «ከመቼው አነበበቻቸው?» አለው ።

«ሁሉንም በፊት አንብቤአቸዋለሁ ብላሃለች» አለው ።

እንግዲህ ካባቱ ዳዊት ሌላ የምልክላት መፅሀፍ የለኝ ፣ እያለ በሆዱ ፣ «ማንበብ ታዘወትራለች መሰለኝ ?» አለው ።

«ከመፃፍ ተለይታ ውላ አታውቅም ። በጀርባዋ ተጋድማ እሱኑ ስታነበንብ ነው የምትውለው ። ከራዲዮም ስር አትለይም ። ጠዋት ፣ ቀንና ማታ ራዲዮ እስኪዘጋ ድረስ ከስሩ አትጠፋም ። ወደ መቱ የወጣ ሰው ጋዜጣ ይዞ ካልመጣ መግቢያ የለውም» ብሎ አጫወተው ።

«ሃይለኛ ናት በለኛ ።»

«አራስ ነብር እንጂ ። ሌላውን ቀርቶ ጌቶቹንም ሲ... ታንቀጠቅጣቸዋለች ። ታዲያ እንዲህም ሆና ከትእዛዛቸው ውጭ ፍንክች የለችም ።»

ሀዲስ ተጣድፎ ፣ «በጋብቻም ቢሆን ?» አለው ። ቶሎሳ ጥያቄው ስላልገባው ፣ «እንዴት ማለት ?» ብሎ መልሶ ጠየቀው ።

«ማለቴ ፣ የማትፈቅደውን ሰው አግቢ ቢሉዋት እሺ ብላ ትቀበላለች?»

ቶሎሳ በነገሩ በመገረም የኮረኮሩትን ያህል ስቆ ፣ «ቤት ልጅ ምን ምርጫ አላት ? የሚፈቃቀዱት ቤተሰቦች ናቸው እንጂ ጋብቻ በሴት ፈቃድ መቼ ሆነ? ምን ነው የጋለሞታዎች ነገር አደረከው ጃል? ወቾ ጉድ !» አለና ፣ በሀዲስ ሞኝነት እንደገና ከት ብሎ ስቆ ለሌላ ጥያቄ እድል ሳይሰጠው ተቻኩሎ ሄደ ።

ቶሎሳ ሲስቅ ከሆዱ ስለሆነ ሳቁ እንደ ክረምት ሰማይ ያጉረመርማል ። እንደዚያ ከሆዱ ውስጥ እያጉረመረመ ሲስቅ ሳቁ በመላ ሱሪ ቦር የሚያስተጋባ ይመስላል ። የሱ የሆነ አንድ ነገር በእስዋ እጅ እንዲቆይ የመፈለጉን ያህል የሚልክላት ሌላ መፅሀፍ በማጣቱ እያዘነ — አዝና እየተበሳጨ — ተበሳጭቶ እየተነጫነጨ — የፈተናውን ውጤት ወስዶ ልክ በተባለው ቀን ለአቶ ይርጋ አስረከባቸው ። ሊያመሰግኑት ቀርቶ ቀና ብለው እንኳ ዋን አላዩትም ። እሱም ሲከነክነው ለስንበቱው ወንጀሉ ምስጋና አልፈለገም ። ወደደም ጠላም የታዘዘውን መፈፀም ነበረበት ። ምርጫ አልነበረውም ። ህይወት ለሰው ልጅ የምታቀርበው ምርጫ የላትም በማለት ፣ ፈተናውን ለማለፍ ያልቻሉትን ከሁለት መቶ አርባ በላይ የሚሆኑትን ተማሪዎች አይቶ እንዳላየ አይኑን ጨፍኖ ሊወጣ ሲል ፣ «እኮ ሩጫው ምንድን ነው !» አሉት አቶ ይርጋ ። ሰላላዋ ድምፃቸው ጆሮውን ወጋቸው ። መለሱ ሲል ፣ አንዱ አገሉበትና አሻሸለው የሰሩትን የሚያስተምርበትን መርሀ ግብር ሰጡት ። የተሰጠውን መርሀ ግብር ሽምጠጥ አድርጎ ሲመለከተው ፣ ከሌሎች አስተማሪዎች የስራ ድርሻ ጋር ሲነፃፀር የሱ ከበድ ያለ ሆና ቢያገኘውም ተቃውሞ ለማሰማት አልፈለገም ። ወረቀቱን ኪሱ ወ ምር ሊወጣ ሲል ፣ አሁንም ፣ «የሚያርጥህ ነገር እኮ አልገባኝም» አሉት ።

እንደገና ተመልሶ ቆመ ። አቶ ይርጋ ከቢሮአቸው ውስጥ ትርፍ ወንበር አያኖሩም ። ወንበር ጠፍቶ አይደለም ። እንዲቀመጥ የሚፈልጉት እንግዳ ከመጣ ወንበር ያስገቡለታል ። አስተማሪዎች ግን እሳቸውን ቆመው ለማነጋገር ይገደዳሉ ።

አሁንም አገሉበትና ፣ «ከታፈሰ ብሩ ጋር ዝምድና አላችሁ ?» ብለው ጠየቁት ።

ከታፈሰ ዘንድ ይዞላቸው የመጣውን ደብዳቤ እያስታወሰ ምንም ዝምድና እንደ ሌላቸው ነገራቸው ። ደብዳቤውን ከሳምንት በፊት ሲሰጣቸው ከየት እንደ ተላከ ሊጠይቁት ቀርቶ ቀና ብለው እንኳዋን አላዩትም ነበር ። ከፊታውራሪስ ጋር ? ብለው ይጠይቁኛል ብሎ ጠብቆ ነበር ።

«እብሪት ደግ አይደለም» አሉት ።
«የምን እብሪት ?»

«ሳያሰናብቱህ መርጥ እብሪት ነው ። እብሪታችሁን እዚያው ዩኒቨርሲቲአችሁ ብታሳዩ ይበቃል ። ለመንደር ነገረተኞች እብሪት የተሞላበት ማመልከቻ መፃፍ ጀምረሃል አሉ ። እንደ ሳውል ከአይናችሁ እኮ የሚወድቅ ቅርፊት የለም ። በትእቢትና በእብሪት አይናችሁ ተጋርዶአልና ምንም አይታያችሁም ። አሁን ያለህበት የስራ አለም መሆኑን አትርሳ ። የቲዎሪ አለም ውስጥ አይደለም ያለኸው ። አሁን ልትሄድ ትችላለህ» ሲሉት ፣ ዘሎ ሊያንቃቸው ፈልጎ ነበር ። ንዴቱ ከጉሮሮው ላይ ተወትፎ እፍን አደረገው ። ንዴቱን እንደ ምንም ውጦ ወጣ ። እንደዚያን ቀን ተናዶ አያውቅም ። ሀዲስ በተፈጥሮው ተናዳጅ ሰው አይደለም ። ያን ቀን ግን አቶ ይርጋን አንቆ ቢገድላቸው ፣ ወይም ቢያንስ ከመላጣቸው ላይ ደህና ኩርኩም ቢያቀምሳቸው ደስ ባለው ነበር ። ንዴቱ ገንፍሎ በትንሳ ቁጥር መላጣቸው ይታየዋል — የማሾፍ ሳቅ ያሰኘዋል ። መደበኛ ትምህርት ገና ያልተጀመረ ቢሆንም ፣ ክፍል ገብቶ ተማሮቹ ላይ ፣ ቀጥሎም ጣራው ላይ ፣ ሲለው ደግሞ ጥቁር ሰሌዳው ላይ ለመጮህ ቢሞክርም ንዴቱን ሊወጣ አልቻለም ። በቀጥታ ወደ ወይዘሮ ዝናሽ ቡና ቤት ሄዶ ሜታ ቢራ አዘዘ ።

ሸታዬ ጆሮዋን አላመነችም ።

«አይንሽን ጎልጉዬብኝ አላልኩም ። ሜታ ቢራ ነው ያልኩሽ» አላት ጠጉሩን በጣቱ እየቆፈረ ።

«ከመቼ ወዲህ ?» አለችው አፍዋን ከፍታ ።

«ከዛሬ ጀምሮ ። ያስተማሪዎች ጉሮሮ ፈሳሽ ነገር ያስፈልገዋል ። ሲደርቅና ሲዳረቅ ነው የሚውለው ። አስተማሪዎች በቀን ስንት ሰዓት እንደሚለፈልፉ ታውቂያለሽ ? ሰባት ሰአት ። በሀልማቸውም ሳይለፈልፉ አይቀሩም ። ማስረዳት አለባቸው ። ማስረዳት — ማስረዳት ። ጉሮሮአቸው ይደርቃል ። ምራቃቸው ይደርቃል ። ምራቃቸው ደርቆ እንደ ሬት እስኪመራቸው ድረስ ነው የሚለፈልፉት ። እና ፣ ፈተና ሲያርሙ ደም ልባቸው ይደማል ። ለማስረዳት የሞከሩትን ሁሉ ያልተረዱ ብዙ ሆነው ይገኛሉ ። ያ ሁሉ ጩኸትና ማስረዳት ዋጋ ቢስ ይሆንባቸዋል ። እና ፣ ጉሮሮአቸው ይደርቃል ። ልባቸው ይደማል ። ሀሊናቸው ቆስሎ ይመግላል ። በፈተና መጣል ገሃነም መስደድ ማለት ነዋ ። የፈረደበትን ልጅ እድል ለዘለአለም መዝጋት ነው ። ሂድ ፣ የሀይወትን ጠመዝማዛ መንገድ ጥረህ

ግረህ ውጣት ማለት ነው ። እግዜርስ አዳምን ይህን አይደለም ያለው ? ላዳም ፈተና ሰጠው ። አዳም ከተከለከለችው ፍሬ በመብላቱ ፈተናውን ወደቀ ። በግንባርህ ወዝ ለፍተህ ብላ ብሎት ከገነት አባረረው ። ልክ አይደ ለም ? እምን ፤ እግዜር ላዳም ፈተና መስጠት አልነበረበትም ። አዳም ፈተናውን እንደሚወድቅ አስቀድሞ ያውቅ ነበራ ! ሰውን እያወቀ በፈተና የሚጥል ጨካኝ አምላክ ነው ። መንግስተ ሰማያት ተመልሰን ለመግባት ፀሎት ፤ ጦም ፤ ጂኒ ቁልቁዋል የምንልበት ምክንያት አይገባኝም ። መልስ ያባርረናላ ! ጨካኝ የሆነ የፍጥረት—አለም ጨዋታ ! ጉሮሮዬ ደርቆአል ። ቢራ ነው የምልሽ !» አላት ፤ አሁንም ጠጉሩን እየቆፈረ ።

ሽታዬ በመገረም አፍዋን ከፍታ ዘርዛራ ጥርሶችዋን እያሳየች ስታዳ ምጠው ከቆየች በሁዋላ ፤ «እግርና እጅ የሌለው ጉድ ነው የምትናገረው እቴ ። እውነትም የማያስለፈልፍ ሰይጣን ይዞሃል» አለችው ።

«እሷም ይህንኑ ነውኮ የምልሽ ። ምሱ ቢራ ነው ብዬሻለሁ» አላት ።

ጠርሙሱ አቡዋራ የጠጣ ለብ ያለ ሜታ ቢራ ከፍታ ሰጠችው ። ከጠ ርሙሱ አንገት ላይ አቡዋራ ጠርጎ የጠርሙሱን ከንፈር ቀና ብሎ እንደ ሳመ፣ወይዘሮ ዝናሽ ኩብለል ኩብለል እያለች መጣችና ሽታዬን ገና ሲታ ያት ፤ እንደ ቄብ ዶሮ ማስካካት ጀመረች ። የተጎነጨው ቢራ ትን ሊለው ነበር ።

ማስካካቱዋን አቆመችና ወደ ሽታዬ እየተመለከተች ፤

ፍቅር ያዘኝ ብለሽ አትበይ ደንበር ገተር
እኛም እንድ ሰሞን እንዲህ አርጎን ነበር ።
. . . ውድቀት ስትሻ ስታበዛ ሩጫ
ሄዳ ታሽታለች የፍቅር አፍንጫ ።

ብላ ደግሞ እንዴ አስካካችና ፤ «ወንድን ያመነ ፤ ጉምን የዘገነ አንድ ነው ፍቅርዬ ። ወንድ ሲቀርቡት የሚርቅ ፤ ሲርቁት ደሞ አልቅቦ ልቅረብ የሚል ከሀዲና አደገኛ ፍጡር ነው ። ወንድ እኮ ልክ እንደ ንብ ነው ። ከዚ ህም ከዚያም አበባ—ካየው አበባ ሁሉ ማር መቅሰም ይፈልጋል ። ለዚያ ውም በነፃ ። ሴት ደሞ ሁሉንም አይነት አበባ ልትሆን አትችልም ። ሴት ልጅ ማርዋን ደብቃ መያዝ አለባት ። ትንሽ ማላስ ፤ ደሞ ያዝ ማድረግ ። ወንድ እንዲህ ነው መያዝ ያለበት ። ጨርቅን ጥሎ አብሮ በማበድ አይደ ለም ። እንደ ስራ አይገድል» አለችና ሄዳ ከወንበር ላይ የተነደፈ የጥጥ ክምር መስላ ተቀመጠች ። ያገር ልብስ ታዘወትራለች ።

ህዲስ በንግግሩዋ ተናዶ ፤ «ሴቶችም ያው ናቸው ። ከዚህም ከዚ ያም መቅሰም የህይወት ህግ ነው ። ይህ መራራ ህይወት አንዳንዴ መጣ ፈጥ አለበት» አለና ፤ መራራ ቢራውን ጨልጦ ሌላ አዘዘ ።

«እውነትም ጉሮሮህ ደርቆአል » አለችና ሌላ አቡዋራም ጠርሙስ ከፈተችለት ።

«ምን ነው ጉሮሮው አይደርቅ ። ከማንም ደንቆሮ ጋር ሲዳረቅ አይደ ለም የሚውለው ?» አለች ዝናሽ ነጠላዋን እየቋዋጨች ።

ሀዲስ ጠጉሩን እየቆፈረ ፣ «ከሀይወት የተገኘ ልምድ ድምፅ ይሉ ሻል ይሄ ነው !» ብሎ ፣ ቢራውን ተጎነጨ ።

ዝናሽ ፣ «እንጉደ ስራ አይገድልሽ» ብላ ፣ ከንፈርዋን መጠጠችና ሀዲስን በእውን ሳይሆን በህልም እንደምታየው ሆና ፣ «ዋ እናቴ ። እኔን አፈር ይብላኝ ። ትዝ ይሉኛል እነዚያ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ወጣቶች ። ነጭ ሱፍ ልብሳቸውን ለብሰው ማታ ላይ ደጃች ውቤ በረሃ እንደ ጨረቃ ብቅ ሲሉ ። አይ እናቴዋ ። ከሰው የተፈጠሩ አይመስሉም ነበር ። እነሱንም አፈር ጨክና ትበላ ይሆን ?» አለች ።

ሀዲስ ነጣ ያለ ኮትና ሱሪ ነበር የለበሰው ። በንዴት ጠጉሩን ቆፈረና ፣ «አፈር በልቶአቸው ይሆናል ። ኖሮ ኖሮ ካፈር የሚቀር ማን አለ ? ይህች አለም ቤታችን ናት ያለውስ ማን ነው ? ቤታችን አይደለችም ። ቤት እኮ ወጥተው የሚመለሱበት ቦታ ነው ። ካለም ከወጣን አንመለስባትም ። እያለቀስን መጥተን ዝም ብለን ጥለናት ነው የምንሄደው —በዝምታ ።

«አፈር ነው ቤታችን ። ሌላ የዘላለም ቤት የለንም ። ቀና ብለን ብናየው ሰማዩ ባዶ ነው ። እንዳልኩት አፈር በልቶአቸው ይሆናል ወይም ጥርሳቸው አልቆ ድዳቸው ብቻ ቀርቶ የኢድሜ ቁራኛ ሆነው ጎብጠው ይሆናል ። አለ አይደለም ፣ ሀይወት ሳታስጎበድድና ባራት እግር አስኪዳ ሳታስግድ አትለቅም ። ሀይወት እኮ በመጨረሻ ልትስቅብን ፣ ልታሾፍብን ነው የምትፈልገው ። አይደለም ? ወይም በያሉበት እየበሰበሱ ይሆናል ፣ ወይም ካገር ተሰደው ሳህን እያጠቡ የፈረንጅ ዲቃላዎቻቸውን ያሳድጉ ይሆናል ። ምናልባት አንዳንዶቹ ስለ ውቤ በረሃ ያላቸውን ትዝታ ይፅፉ ይሆናል ። አላውቅም ። በዚህ አለም ማን የት እንዳለ ማን ያውቃል ? ሁሉም ብቸኛ ነው» አለና ቢራውን ባንድ ትንፋሽ ጨለጠ ።

«ምን ነው ቂጣ ቂጣ ይልሃል ? እንጉደ ስራ አይገድልሽ» አለች ዝናሽ ፣ ነጠላዋን ቶሎ ቶሎ እየቋዋጨች ።

«ቂጣ ቂጣ ፣ አለ አይደለም ፣ ንዴት ንዴት የማይለው በዚህ አለም ማን አለ ?» ብሎ ፣ ፊቱን ሞዠሮቆ ፣ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አድርጎ ሲያበቃ ፣ የቢራውን ጠርሙስ እያሽከረከረ ፣ «ይህች አለም በንዴታም ሰዎች የተሞላች ነች ። አይደለም እንዴ ? ነው እኮ ። አስተማሪዎች ፣ መልካቸውንና ስማቸውን ለይተው በማያውቁዋቸው ተማሪዎች ይናደዳሉ ። ተማሪዎችም አስተማሪው የሚናገረው ስለማይገባቸው ይናደዳሉ ። ወላጆች ልጆቻቸው እሺ ብለው ስለማይታዘዙ ይናደዳሉ ። ልጆች ወላጆቻቸው ስለማይሰሙአቸው ይናደዳሉ ። ባል በሚስቱ ፣ ሚስት በባልዋ ይናደዳሉ ።

«እናቲቱ የሞተችበት ይናደዳል ። ፍቅረኛው የከዳችው ፣ ወይም ፍቅረኛዋ የከዳት ይናደዳሉ ። ሞትና መለያየት ሁልጊዜ አብረውን የሚኖሩ ስለሆኑ ሁልጊዜ እንናደዳለን ። ወጣትነት እየከዳን ሲሄድ ፣ እንጆ ትጩሏ እየጠወለገና እየረገፈ የሚሄደውን መልካችንን እያየን እንናደዳለን ። ለማግኘት የምንፈልገውን ነገር ሳናገኝ ስንቀር እንናደዳለን ።ለማድረግ የምንፈልገውን ነገር ከፍርሃት የተነሳ ሳናደርግ ስንቀር እንናደዳለን ። ፍርሃታችን ያናድደናል ። ሽንፈታችን ያናድደናል ። በላያችን ላይ እንደ ጥላ የሚያንዣብበው ሞት ያናድደናል ። አለም በንዴታም ሰዎች የተሞላች ነች ። እና ፣ ንዴታችንን እርስ በርሳችን ላይ እንደ ጅራፍ እናጮሃለን ።

«ታዲያ ፣ ይህ ሁሉ ንዴት ለምን ይመስሎታል ? አለ አይደለም ፤ ማንም አሁን ያለበትን ህይወት አሚን ፣ በቃኝ ብሎ አይቀበልም ። ያለውም የሌለውም ፣ ሁላችንም ፣ አለ አይደል ፤ አለማችንን ለመለወጥ እንፈልጋለን ። ሰው እኮ የሚፈልገው አለምን እንዳለች ለመቀበል ሳይሆን ለመለወጥ ነው ። እና ፣ እንናደዳለን ። አለ አይደለም ፣ ህይወት ሁልጊዜ አይመስሌ ናት ።

«እና ፣ እኔም አሁን ተናድጃለሁ ። ለምን ቢሉኝ ? ይህ ቢራ እንደ ፈለኩት ጭንቅላቴ ላይ ሳይሆን የወጣው ወርዶ ፊኛዬን ነው የወጠረው ። እና ፣ ያናድዳል» አለና ሂሳቡን ከፍሎ ወጣ ።

የተናደዱ ሰዎች ። የተናደደች አለም ። እስከ እግዜሩ ሰማይ ድረስ ዘልቆ የሚጮህ የንዴት ጅራፍ ። ከዝንተ አለም ጀምሮ በንዴት የቀላ ደም ። የደም እንጀራ ። ግን ይመሻል ይነጋል ። የአቶ ይርጋ መላጣ ቀንድ አብቅሎ ሊወጋው ሲያባርረው ፣ እሱም መሮጥ ተስኖት ሲንደፋ ደፍ ፣ ተማ ሪዎች እንደ ማስጣል ቆመው ሲስቁበት — ሲቃዥ አድሮ ተናዶ ነበር የነቃው ።

ከትምህርት ቤቱ ሲደርስ የፈተናቸው ልጆች ከዋናው ቢሮ ውጭ ተኮልኩለው አገኛቸው ። አንድ አይናው ዘበኛ ያቺን አንድ አይኑን አፍ ጥጦባቸዋል ። ጆሮ ቆራጣው ጠብደል ጥቁር ውሻ እንደ ጉቶ ድልዱም ሆና የቀረችውን ቆራጣ ጭራውን እያወዛወዘ ተማሪዎቹ ላይ ይጮሃል ። ሀዲስ መምጣቱን ሲያዩ ተማሪዎቹ ዙሪያውን ከበውት በጥያቄ ያዋክቡት ጀመር ።

ሀዲስ በንዴቱ ላይ ንዴት ጨምሮ ድምፁን ከፍ በማድረግ ፣ «አንድ ጊዜ ዝም በሉ ! እንዴ ? ሁላችሁንም ባንድ ጊዜ ለመስማት አልችልም ። ያለኝ ሁለት ጆሮ ብቻ ነው ። የፈተናችሁን ውጤት እንደሆነ የምትፈልጉት ዲሬክተሩን ጠይቁዋቸው . . . »

«ዘበኛው አላስገባም አለን» ብለው ጮሁበት ።

ወደ ዘበኛው ሂዶ ውሻውን በአይኑ እየጠበቀ ፣ «ለምን አያስገቡአ ቸውም ?» አለው ።

«በማን ሃላፊነት ?» የሚል ጥያቄ አቀረበለት ።

ሀዲስ ወደ ልጆቹ ተመልሶ ፣ «አንዴ አድምጡኝ ልጆች ። ውጤታችሁ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ካልተለጠፈ መቼ እንደሚገለፅ ጠይቄ እኔ እነግራ ችሁዋለሁ ። እሺ ?» ብሎ በፈተናው ለወደቁት በልቡ እያዘነና እየተናደደ ሁሉም እኩል የሚጉዋጉበት አለም የሚል አሳብ በአእምሮው ውስጥ እየተጉላላ ወደ አቶ ይርጋ ቢሮ በቀጥታ አመራ ። አቶ ይርጋ ጠዋት በማ ለዳ ከሁሉም ቀድመው ነበር ቢሮ የሚገቡት ። ቀና ብለው አላዩትም ። መላጣቸው አፈጠጠበት ። መላጣቸው በይበልጥ ተመልጦ ታየው ።

«ምን ኖርአል ?» አሉት ።

የመጣበትን ጉዳይ ባጭሩ ነገራቸው ።

«ፈተናውን አርመህ ጨርሰህ ሰጥተኸኝ የለም ?»
«አዎን።»
«የቀረው ስራ የኔ ድርሻ ነው» አሉት ።

ወባ እንደ ያዘው ሰው መላ ሰውነቱ በንዴት ተንቀጠቀጠ ። የቆመ በት መሬት ጭምር አብሮት የሚንቀጠቀጥ ነበር የመሰለው ። ከንዴቱ የተነሳ ጉሮሮው ተዘግቶ ትንፋሽ ስላጠረው እንደ ምንም ብሎ በትንፋሹ ጉሮሮውን ጠረገ ።

«ሌላ ጉዳይ አለህ?» አሉት ።
ከንፈሮቹን በግድ አላቆ ፣ «እስኪያሰናብቱኝ ብዬ ነው» አላቸው ።

የበለዙ ጥርሶችና የቀሉ አይኖች አሳዩት ።

እኔን ለማናደድ ካልሆነ በቀር ያለቀለት ጉዳይ ለምን እንደማይገለፅ አይገባኝም ። ግን ምን አደረኩት ? እያለ ሄዶ የሚጠብቁትን ልጆች በማዕ ናናት ከሸኘ በሁዋላ ለማስተማር ክፍል ገባ ።

ክፍሉ ብርሃን እንደ ልብ አይገባውም ። ይጨልማል ። ምርጊቱ የፈረሰ ግድግዳ ያገጣል ። ከስር እግር ላይ እየዘለሉ የሚፈተፍቱት ቁንጫ ዎች ያዘልላሉ ። የክፍሉ ሽታ እስከ ሰማይ ድረስ ይቀረናል ። ከመቶ ሃያ በላይ የሚሆኑ አይኖች ይቁለጨለጫሉ ። ስማቸውንና መልካቸውን ለይቶ እያስታውሰም ። የያንዳንዱን ተማሪ አቅም አውቆ ሊረዳቸው አይችልም ። ዝም ብለው አይናቸውን ያቁለጨልጭብታል ። ምና ልባት እሱም ዝም ብሎ እንደ ዮሀንስ መጥምቁ በምድረ በዳ የሚጮህ ይሆናል ። እፍግ ፣ ትፍግፍግ ያለ ጨለማ—እና ፣ እዚህ ውስጥ ለመግባት እድል የሚጠብቁ ብዙ ልጆች—አስር እጥፍ ድርብ ልጆች ከውጭ ይጠብ ቃሉ ። ኤጭ ! ማስተማር አይበለው ! ብሎ ሲደወል ወጣ ።

የፈተናው ውጤት አልወጣም ። አቶ ይርጋን የገጠማቸው ችግር ሊገ ባው አልቻለም ። በበነገታው እንዲሁ ውጤቱ ሳይገለፅ ዋለ ። በሶስተኛው ቀን ላይ ነበር የፈተናው ውጤት የተገለፀው ።

ሀዲስ ለማስተማር ሌላ ክፍል ከመግባቱ በፊት ከበረንዳ ላይ ቆሞ ያስተውላል ። ፈተናውን ያለፉ መሆናቸውን ያወቁ አንዳንድ ልጆች እየ ሳቁ ሙቤ መርገጥ ይቃጣቸዋል ። አንዳንዶቹም ሙቤ ይረግጡ ነበር ። ስማቸውን ከወጣው ዝርዝር ውስጥ ያጡት ጥቂት ልጆች እንባ ያፈሳሉ ። የእሱም አይን እንባ አቅርአል ። አብዛኛዎቹ በእድላቸው አዝነው አቀርቅ ረው ይሄዳሉ ። ሳቅ . . . እንባ . . . ህይወት . . . የት ነው የሚሄዱት ? . . . ትምህርት ቤት ለመግባት እድል ያላገኙት ሁሉ የት ነው ያሉት ? . . . ምን ይሆናሉ ? . . . ቤታ ወደ ገሃነም እንዲሄዱ ፈረድኩባቸው ማለት ነው . . . ብሞት አስተማሪ አልሆንም . . . ከዚህ የሀሊና ገሃነመ እሳት ውስጥ መው ጣት አለብኝ . . . እያለ በአሳብ ጭልጥ ብሎ ሄዶ ስለ ነበረ ሲደወል አል ሰማም ።

አስቆምር ከክፍል ሲወጣ ስሜቱ ትንሽ ለወጥ ብሎ ነበር ። እንዲ ያውም ፣ በክፍሉ ጣራ ላይ ፣ በመስኮትና በጥቁር ሰሌዳው ላይ ሽር እያሉ የሚያልፉ ወፍራም አይጦችና እንሽላሊቶች ባይኖሩ ኖሮ ደስ ብሎት በወጣ

ነበር ። ሀዲስ በሆዳቸው የሚሳቡ አውሬዎች ፈፅሞ አይወድም ። ይቀፋታል ። በተለይም እባብ ፈፅሞ አይወድም ። እባብን ማን ይወዳል ?! ዶሮ እባብ ስለምትበላ ዶሮም አይወድም ። የሱዳ ዶሮዎች ደግሞ ከየስንሰሉ ስር እባብ አያጡም ። የሞተ እባብ አንጠልጥለው ሲሮጡ ባያቸው ቁጥር ከሩቅ ይሸሻቸዋል ። የሞተ እባብም አያምንም ። ከአዳምና ከሄዋን ጀምሮ በሰውና በእባብ መካከል ለዘለአለም ፀንቶ እንዲኖር የወረደው ርግማን ይሆናል በአእምሮው ውስጥ ተቀርፆ የቀረው—እባብ የሰው እግር እንድትነክስ ፣ ሰውም ጭንቅላትዋን እንዲቀጠቅጥ ። በሆዱ የሚሳብ አውሬ ባየ ቁጥር ያዘልለዋል ።

አይጥ ወይም እንሽላሊት ባየ ቁጥር ስለሚዘል ያራተኛ ክፍል ተማሪዎች ሁልጊዜ ይስቁበታል ። በተለይም ፋጡማ መሀመድ ማስቲካ ቀጭ ቀጭ እያደረገች ሁልጊዜ ትስቅበታለች ። ባይዘልም ትስቃለች ። ሁልጊዜ ትስቃለች ። ቁንጫዎች በልተውት ሲያክም ትስቅበታለች ። ባይሆን የእስዋን ስም አውቆአል ። የምትቀባው ዝባድና የምትታጠነው ከርቤ ይሁን ስንደል ከፍንጫው አይጠፋም ።

ትላልቅ አይኖችዋ እንደ ቤተ መቅደስ ጡዋፍ ያበራሉ ። ሲያስቡት ነቢዩ መሀመድ በእውነቱ ብልጥ ነበር ። ሰዎችን ወዳለመው ጀና መሳብ የሚቻልበትን ዘዴ ያውቃል ። ወደ እስላሞች ጀና የሚገቡት ልጆች ሁሉ እንደ ወንዝ ዘለአለም ከሚፈስና ምንም ራስ ምታት ከማይሰጥ ወይን ጠጅ እየጠጡ ፣ ልባቸው ከሚመኘው የፍሬና የስጋ አይነት እየበሉ ፣ የወርቅ ፅዋቸውን ይዘው በሚከተሉዋቸው ፣ አይኖቻቸው እንደ ጡዋፍ በሚያበሩ ኮረዳዎች ተከበው ዘለአለም ደስታ ከማይለየው የገነት አትክልት ውስጥ ይኖራሉ ። ሀዲስ ለሃይማኖት ቁብ ቢኖረው የእስልምና ሃይማኖትን በመረጠ ነበር ። በህይወት ሳሉ ብዙ ሚስቶች የሚፈቅድ ፤ ከአይናማ ኮረዳዎች የማይለይ ሃይማኖት ምን ይጠላል ?

ስለ ሃይማኖት ባሰበ ቁጥር ፤ ንዳዱ እንደ እሳት በሚያቃጥል አሸዋማ ምድረ በዳ ውስጥ ከቴምር ወይም ከዘምባባ ዛፍ ጥላ ስር ቁጭ ብለው አትክልት በሌለበት ስፍራ ተበልቶ የማያልቅ የጎመራ ፍሬ—እንዲት ጠብታ ውሀ በሌለበት በተጠማ ምድር ላይ ዘላለም የሚፈስ ቀዝቃዛ ጣፋጭ ውሀ— ቁጥቁዋጦ ለአመል በማያበቅል አሸዋማ ምድር ላይ ለማየትም ሆነ ለመብላት የሚያጉዋጉ ዛፎችና አበባዎች አፍንጫ በሚወጋ ደረቅ አየር ምትክ የሽቱ መአዛ የያዘ ህይወት አዳሽና ፈዋሽ የሆነ ቀዝቃዛ አየር ባሸዋው ባህር ምትክ ዘላለም የሚፈስ ወተትና ማር—የሚያልሙ ጢማም ሽማግሌዎች በአይኑ ህሊናው ይመጣሉ ። እና ፣ ታላላቅ ሃይማኖቶች በምድረ በዳ ማበባቸው አያስደንቅም ። ምክንያቱም ንዳድ የበዛበት የምድረ በዳ አሸዋ በሰው ላይ ፅላላዊ ህልውናን ያሳድራል ። እና ፤ ሃይማኖት ከምድረ በዳ የፈለቀ ተረት ነው እያለች ፣ ፋጡማ መሀመድ የምትስቅበት ሳቅ እየታየው ፣ የፈተናቸው ልጆች ውጤት ከተለጠፈበት ስሌዳ አጠገብ ሲደርስ ለማየት ያህል ቆም አለ ። ዝርዝሩን እንዲ አንብቦ ወጣና ሲሄድ ሲል አንድ ነገር ስለ ከነከነው ተመልሶ የስሞቹን ዝርዝር አንድ በአንድ ቀስ ብሎ አነበበ ። እሱ የሚያስታውሳቸው አንዳንድ ስሞች ነበሩ ። ያስቀረውን ኮፒ ከያዘው ፋይል ውስጥ አውጥቶ በጥንቃቄ ማመሳከር ጀመረ ። እውነትም እሱ ፈትኖ ያሳለፋቸው የአስራ አምስት ልጆች ስም ተሰርዞ ፈተናውን ያላለፉ ልጆች ስም በምትኩ ገብቶአል ።

ነገሩ በነጭ ወረቀት ላይ በጥቁር ቀለም ተፅፎ እያየ ማመን አቃተው ። መረዳትም ተሳነው ። ልቡ ሰይጣናዊ ከበሮ ይደልቅ ጀመር ። ንዴት ይሁን እ፣..ት ፤ ሳቅ ይሁን እንባ— የትኛው እንደ ያዘው ለይቶ ለማወቅ አል ቻለም . . .

ፈተናውን ሳያልፉ እንዲገቡ የተደረጉትን ተማሪዎች ስም ዝርዝር ለቀመና ንዴት እየተናነቀው አቶ ጣሴ ደጉን ፍለጋ ሄደ ። አቶ ጣሴ ካንድ ክፍል ውስጥ ሆነው የሚያስተምሩትን ትምህርት ሲያዘጋጁ አገኛቸው ። በያዙት ስራ ተመስጠው ስለ ነበሩ የህዲስን ሁኔታ አላጤኑም ።

«የማስተምርበትን ‘ኖት’ እያዘጋጀሁ ነው ። ይህን ሁሉ ዘመን ሳስ ተምር ባሮጌ ‘ኖት’ ተጠቅሜ አላውቅም ። አስተማሪ ዘላለም አዲስ ተማሪ መሆን አለበት» አሉት ።

«አቶ ጣሴ» አለ ህዲስ ።
«ወዬ . . . »
«አዲስ ነገር ገጥሞኛል ።»
«ምንድር ነው ልጄ ?»

«መንፈሴ በጣም ታውኮአል» በማለት የመጣበትን ጉዳይ ከስር ጀምሮ ያጫውታቸው ጀመር ።

ፈተናውን ለወደቁት ልጆች አዝና የሚናገር መስሎአቸው ፣ «መቼስ ምን ይደረጋል !» አሉት ።

«እንዴት !» አለ ።

«አይዞህ ፣ ምንም አይደለም ። አትዘን ፣ እንዳየኸው ያለን ቦታ በጣም የተወሰነ ነው ። ልንቀበል የምንችለው በጣም ከፍተኛ ውጤት ያመጡትን ብቻ ነው ። መቼስ ምን ማድረግ ይቻላል ?» አሉት ።

«ያሳዘነኝ ቦታ ያጡት ልጆች ጉዳይ ብቻ አይደለም ። ፈተናውን ያለ ፉት አንዳንድ ልጆች ተሰርዘው ያላለፉት እንዲገቡ መደረጋቸው ነው ፣ በጣም አድርጎ ያሳዘነኝ ፣ እንዴት እንዲህ ይደረጋል !» በማለት ወረቀቱን ሰጣቸው ።

የተማሪዎቹን ስም በጥንቃቄ ሲመለከቱ ከቆዩ በሁዋላ ፣ ራሳቸውን በሀዘን ነቅነቁና ፣ «ሆይ ! ጉድ ነው’ኮ ። በ’ውነት ይገርማል ። ብዙ ዘመን ሳስተምር እንዲህ አይነቱ ግልፅ አድልዎና በደል ተፈፅሞ አይቼ አላው ቅም ። እሄሄ ! የባላባቶች ፣ የቱጃሮችና የባለስልጣኖች ልጆች ብቻ ነው’ኮ መርጦ ያስገባው ። ላገሩ እንግዳ ለስራው አዲስ መሆንክን በማየት ሞኝ ያገኙ መስሎት ይሆናል እንዲህ ያደረገው ። እይ ይርጋ !» አሉ አዝ ነው ።

ህዲስ የባሰውኑ ተናዶ ፣ «እኔ ነገሩን እንዲህ አላልፈውም ። እንዴት እንዲህ ይደረጋል ! ፈተናውን ያለፉት የድሀ ልጆች ተባረው ፈተናውን ያላለፉት የሀብታም ልጆች እንዲገቡ ሲደረግ ቆሜ ማየት አልችልም ! አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ !» አላቸው ።

«እስቲ ረጋ በል ። እኔ ቀስ ብዬ ስለ ሁኔታው አነጋግረዋለሁ ።»

«አይሆንም ። እርስዎ በነገሩ አይግቡበት ። ምን ያደርጉኛል ! ግፋ ቢል ከዚህ ይሂድልኝ ነው የሚሉት ። ሞት የለብኝም ። በእውነቱ አዲስ ትምህርት ቤትም መስራት አለበት። የስንቱ ልጅ እድል እንዲህ ሲቀጭ ዝም ብለን ማየት የለብንም» አለ በምሬት ።

«አዩ አንተ ልጅ ! ሳይህ የጉርምስናዬን ዘመን ታስታውሰኛለህ ። እኔም ማስተማር እንደ ጀመርኩ ልክ እንዳንተ ነገሩ ሁሉ በጣም እያሳዘነኝ ያስቆጣኝ ነበር ። በፈተና አሰጣጥና በትምህርት ክፍሎች መጥበብ ከብዙ ዲሬክተሮች ጋር በጊዜዬ ተጣልቻለሁ ። በዚህም ምክንያት ነው ካንዱ ጠቅላይ ግዛት ወደ ሌላው ስንከራተት እድሜዬን የጨረስኩት . . .» ብለው ነገራቸውን ሳይጨርሱ ፥

«እኔ ላንድ አመትም ቢሆን በዚህ አሰቃቂ ሁኔታ አልኖርም ። አንድ ነገር መደረግ አለበት !» ብሎ ተነስቶ ወደ ቤቱ ሄደ ።

# ክ ፍ ል ፳

ሱጴ ቦር በጨለማ ተውጣለች ። ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ—እንደ መቃብር ፀጥ—ረጭ—እረጭ—ዝም ያለ ጨለማ ።

ከብቶች ገብተው ከታለቡ በሁዋላ የሱጴ ነዋሪዎች የትም አይሄዱም ። ሽማግሌዎች ቀፎ ቆራጭ መስለው ከጉብታዎች ላይ በመሰየም ጨለማው ላይ ያፈጣሉ ። የጠላ ቤት ጡዋፍ ይንቀለቀላል ። የጠጅ ቤት ኩራዝ ይንበለበላል ያረቄ ቤት ፋናስ ወይም ማሾ ይንቦገቦጋል ። የምድጃ እሳት ይዳፈናል ። ድፍን ፣ ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ።

አልፎ አልፎ የእጅ ባትሪ ብርሃን ጨለማውን እየሰነጠቀ ሲጉዋዝ ይታያል ። የጨለማ አይን ። የባለባትሪው ሁኔታ ብርሃን ከሚሄድበት አቅጣጫ ይታወቃል ። የሰከረው ኢያሳስትም ። የባትሪው ብርሃን አንዴ ወደ ሰማይ ፣ አንዴ ወደ ምድር ፣ አንዴ ወደ ቀኝ ፣ አንዴ ወደ ግራ ያበራል ። አንዳንዴም ድርግም ብሎ ይጠፋል ። ወይም በጨለማው ባህር ላይ ነጭ የብርሃን ኩሬ ፈጥሮ ዝም ብሎ ይቀራል ።

ሀዲስ ከቤቱ ሰብሳብ ላይ ምሰሶ ተደግፎ ቆሞአል ። ፍንትው ብላ ወጥታ ስቃ የምታሳስቅ ሙሉ ጨረቃ አትታይም ። ሆጭ ብለው ፈሰው ጠቅሰው የሚያጠቃቅሱ ምድረ ከዋክብት ከጥቁሩ ሰማይ ላይ አልተኩዋሉም ። ጭው ያለ ጥቁር ሰማይ ፣ ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ።

ያባ ጨፌ ድቤ ድው ፣ ድው ! ኢያለ ከሱጴ አድባር ጋር አድሞ ፣ የሱጴን ዛር ከተኛበት በመቀስቀስ የገባ በረሃን ኢጋንንት ጠርቶ የውድቅት ዳንኪራ ማስረገጥ ገና አልጀመረም ።

ሀዲስ የወጣውን የፈተና ውጤት ካየ ወዲህ ብቻውን ሲያዝን ፣ ሲስቅ ፣ ሲተክዝና ሲበሳጭ ነበረ የዋለው ። እንባ እንባ ፣ ሳቅ ሳቅ ይለዋል—ከመሬት እየተነሳ ። አንዳንዴ እንደ እብደትም ይቃጣዋል ።

ከቤቱ ባሻገር ፣ ከእልቂ ወንዝ ማዶ ካለው ትራራ ላይ የሚኖረው ዋሸንት ተጫዋች ጣእመ ዜማውን ጭው ብሎ ከተዘረጋው ጨለማ ላይ ማንቆርቆር ጀምሮአል ። ሀዲስ ጆሮውን ያነቃል ።

ዋሸንቱ ጨለማውን እየጣሰ ፣ በቀዝቃዛው አየር ላይ እየተንሳፈፈ ፣ አንዳንዴም የጠፋችውን ጨረቃና የተደበቁትን ከዋክብት ፍለጋ ወደ ጥቁሩ ህዋ ቀና እያለ ፣ ሲለው ደግሞ ከእልቂ ወንዝ ጋር እየተገማሸረ ወደ ገባ ወንዝ ሸለቆ በማሽቆልቆል ጭልጥ ብሎ ይወርዳል—እልል ፣ ኩልልል ፣ ጭልልል እያለ የሀዲስ ሀሳብ ከዋሸንቱ ጋር ከገባ ወንዝ ጋር ወድቆ እየተነሳ ወደ ባሮ ፣ ከባሮ ወንዝ ጋር ኢየሰመሰመ ወደ ጥቁር አባይ ፣ ከጥቁር

አባይ ጋር እየተናደ የኢትዮጵያን ገላ አጥቦ ሲያበቃ ድንገል ጠረንጥን ይዞ በምድረ ሱዳንና በምድረ ግብፅ በረሃዎች ሲንከራተት ይቆይና ወደ ሜዲቴራንያን ባህር ይንቀረቀራል ። እና ፣ እንደ ገና ተመልሶ ወደ ህዋው ይመጥቃል— ጨረቃዋንና ከዋክብቱን ፍለጋ ። እየተናደደም ፣ እያዘነም ፣ እያቃሰተም ፣ እየሳቀም ወደ አለማት አብራክ ዘልቆ ይገባል ። ከዚያ ያጉረመርምና ወደ ምድሪቱ ይመለሳል ።

ከዝቋዋላ፣ ከኤረር ፣ ከራስ ዳሽን ተራሮች ላይ ይነጥራል። ከአሞ፣ ከዋቢ፣ ከገናሌ ፣ ከአዋሽ ፣ ከተከዜ ወንዞች ላይ ይንሳፈፋል ። ከኢትዮጵያ አምባዎች ላይ እየወጣ ፣ የኢትዮጵያ ቀዬዎችን ፣ ጎጦችን ፣ ማማዎችን ፣ የሳር ጐጆዎችን እየዳሰሰ የሶስት ሽህ ዘመን የትካዜ ፣ የሀዘንና የተስፋ ታሪክ ይተርካል ።

ሀዲስ የባለዋሽንቱን ጨዋታ ባዳመጠ ቁጥር አሳቡ ከዋሽንቱ ጋር አብሮ ይመጥቃል ፣ ይንሳፈፋል ፣ ይነሆልላል ፣ መድረሻ ከሌለው ጥልቀት ውስጥ ይገባል ፣ ጭልጥ ብሎ ይሄዳል ፣ ይበራል ።

«ማን ነው የሰው ልጅ ኢምንት ነው ያለው ?» አለ ። «የሰው ልጅ ጭንቅላት ከአለማት ይበልጥ ግዙፍ ነው ። ሰው ራሱ አለም ነው ። ከሚመለከታቸው ከዋክብት ይበልጣል ። በሁለት እግሩ ቀጥ ብሎ ቆሞ የሚሄድ ያለ ሰው ሌላ ማን አለ ? ግን የሰው ህይወት እንዴት ያናድዳል ? እንዴት ያሳዝናል ? ንዴትና ሀዘን ። ንዴት ፣ ሀዘን ፣ ብሩህ ተስፋ ። ህይወት ያልፋል ። ህይወት ይቀጥላል ። ዋሽንቱ የሚለው ይህን አይደለምን ?»

እዝን አለ ። ሀዲስ ሲያዝን እናቱ ባሳቡ ይመጡበታል ።

— ተንልቶ ሕበሳ ከመቁጠር አንደኛውን ሞቶ ማረፍ ይሻላል ። ግን ሞቶ ስሙ ሲጠራ የሚኖር ማን እንደሆነ ታውቃለህ ?

— ማን ነው እሱ እማዬ ?

— የወለደ ። የወለደ ነው ልጄ ። . . . የእጅህን ዋጋ አትጣ ። እጅህ ይባረክ . . . እህ . . .

የመጨረሻ ትንፋሽ— ለመኖር የሚደረግ የመጨረሻ ትግል- -የማይበገር የሰው ልጅ መንፈስ—ማን ነው እንደ ሞት መቅረት የሚፈልገው ? ዘለአለም የመኖር ተስፋ የሰው ልጅ ረሃብና ጥማት አይደለምን ? ተስፋ ቆርጦ እጅ ከመስጠት መታገል ይሻላል—በዚህ አለም የሰው ልጅ ፈፅሞ ተስፋ መቁረጥ የለበትም—በህይወት የመጀመሪያ ግዴታ መጠናከርና ለመኖር መታገል—ትግል የሰው ልጅ እጣ ፈንታ ነው—እንኖራለን—የሰው ልጅ ይኖራል . . .

ዋሽንቱ አሁን ድምፁን ዝቅ እያደረገ እንደ ማዘንም መናደድም እያለ መቆጣት ጀምሮአል ። ከዋክብቱንና ጨረቃዋን ከተደበቁበት ፈልጎ ሊያገኝ አልቻለም ። ተስፋ ወደ መቁረጥ ይቃረብና ደግሞ ይነሳል ፣ ያንሰራራል ፣ ይበራል ።

ያባ ጨፌም ድቤ ድው ፣ ድው ማለት ጀምሮአል ። የጨለማውን ልብ ትርታ ያስተጋባል ። በምድር ከርስ ውስጥ ፣ ከጥቁሩ ህዋው አብራክ ውስጥ የተደበቁትን ፣ በጨለማ ክንፍ ላይ የሚበርሩትን ርኩሳን መናፍስት ይጠራል ። የገሃነም ዋይታ ፣ የሲኦል ጩኸት ፤ የዲያብሎስ ፉጨት እያስማ በሰው ልብ ውስጥ ፍርሃት ያሳድራል ። ፍርሃቱ ድል ፣ ድል ፣ ድል አድርጉ አይልም ። ፈፅሞ ። ገብሩ ፣ ገብሩ ፣ ስገዱ ፣ ስገዱ ይላል ፣ ጨርሶ በማይ ለወጥ ስልት እያስተጋባ ።

እንቅልፍ የሚሉት ነገር በአይኑ አልዞረም ። ካቶ ይርጋ ጋር እንዴት አድርጎ አይን ለአይን እንደሚተያዩ ነበር የሚያስበው . . . የትምህርት ቤቱ ጣራ ድንገት ተደርምሶ ሲወድቅበት . . . አቶ ይርጋ ድቤ እየመቱ ከመላጣቸው ላይ ቀንዶች አብቅለው ሲወጉት ከክፍል ክፍል ሲያራውጡት እንደ ንስር አሞራ ከፍ ብሎ አየር እየራቀን እየሰነጠቀ ሲበር አድሮ ወፎች ሲንጫጩ ነቃ ።

ያን ቀን ጠዋት ምንም አይነት ፍርሃት በልቡ አላደረም ። ነፃ ሰው ፍርሃት አይሰማውም ። ስለማይፈራም ነፃነቱን አክብሮ ያስከብራል ። ነፃ ሰው ከጭቆናና ከግፍ ሌላ የሚጠላው ነገር አይኖረውም ። የሚጠላውን ነገር ለማስወገድ ደግሞ አይፈራም ። በዚህ አለም ካንድ ጊዜ ሌላ ማን ይኖራል ? እና ፣ ያለ ነፃነት ደግሞ ህይወት ምንድን ናት? ባዶ ቅል ፣ የሚ ጮህ ባዶ ናስ !

ከት ብሎ ሳቀ—በራሱ ላይ ። ከትናንት ጀምሮ መፈላሰፍ በማብዛቱ ሳቀ ። አሳቦቹ ሁሉ እንደ ባዶ ናስ መልሰው ከጆሮው ውስጥ ሙሁበት ። . . . አሳብ የሚሉት ነገር ርግማን ነው አለ ። እንደ ባዶ ቅል በሚንኳኳኩት አሳቦቼ ውስጥ የታየኝ ነገር ቢኖር ፈሪነቴ ብቻ ነው ። ፍርሃት ። አቤት ስንፈራ ! ፍርሃት ነው እኮ የህይወት ክብር የሚነሳን . . . እንደ ገና ሳቀ ። በሳቁ ውስጥ ፈሪ ስለ ፈራ ብቻ ከምንም ነገር ሊድን እንደማይችል ታየው ። በፈሪና በጀግና መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው ? ብሎ ራሱን ሲጠይቅ ለጊዜው የመጣለት መልስ ፈሪ ሲሸሽ ፣ ጀግና ሲታገል የመሞታቸው ጉዳይ ብቻ ሆኖ ታየው . . . ሞት ለማን ይቀራል ? ፈሪም ይሞታል ። የሞት ሞት ። ታሪክ ማለት ሞታችንን ከማሳመር ሌላ ምን ይሆናል ? ሰው የማይቀር ሞቱን በማሳመር ክብርና ሞገስ ሊሰጠው ይገባል ። ሸሽቶ የት ሊደርስ ? ከመቃብር የሚያልፍ የለ ! የህይወትን ጣጣ አይሸሹም ፣ ይጋፈጡዋል እንጂ ። የጀግና ክብሩ የሞቱ ማማር ነው . . . እያለ ወደ ስብሰባ አዳራሽ ገባ ።

ያን ጠዋት አቶ ይርጋ የአስተማሪዎች ስብሰባ ጠርተው ነበር ። ከጋሼ ቀውሌ ጎን ሄዶ ቁጭ አለ ። ለመምህሩ ተማሪዎች ያወጡለት የቅ ፅል ስም ነበር ። ሀዲስ እውነተኛ ስሙን አያውቅም ። የሰውን ስም ማስታ ወስ አይችልም ። ጋሼ ቀውሌ ረጅም ቅልጥሞቹን በረጅሙ ዘርግቶአል ። እንደ ከስሕት በላይ ጥላ ረጅም ነበር ። ጤነኛ ግንባር ኖሮት አይቶት አያ ውቅም ። ከግንባሩ ላይ ቁስል አይጠፋም ። በገባበት ክፍል ሁሉ አንበሩ ይገጨዋል ። ሁልጊዜ ይገጨዋል ። ታዲያ ፣ ድንቅ ነው ይላል ። «ድንቅ ነው» የሚል ቃል ከአፉ አይጠፋም ። ለማንኛውም ነገር የሚሰ ጠው መልስ ፣ «ድንቅ ነው» የሚል ነበር ። አንበሩ ሲፈነክተው ፣ «ድንቅ ነው» ይላል ። እናትህ ሞተች ቢሉትም እንኩዋን «ድንቅ ነው» ሳይል አይቀርም ።

«ለምንድን ነው ሁልጊዜ ድንቅ ነው የምትለው ?» አለው ሀዲስ ።
«ሁሉ ነገር ድንቅ ነዋ ።»
«ተማሪዎች ጋሼ ቀውሴ ይሉሃል ።»
«ድንቅ ነው ። የድንኮች ነገር ድንቅ ነው ።»
«መቼ ነው 'ድንቅ ነው' ማለትክን የምትተው ?»

«ድንቅ ነው ። ስሞት ። ሞትም ድንቅ ነው ። አዲሳባ በሬሳ ሳጥን ሻጮች ደጅ ሳልፍ ነጋዴዎች እኮ ትክ ብለው ሁልጊዜ ያዩኛል ። 'ምን አይነት ሳጥን ነው የሚበቃው ይሆን' የሚሉ ይመስላል ። ድንቅ ነው ።»

«ስለ ሞት ብዙ ጊዜ ታስባለህ ?»

«እንዲያውም ። የማይቀር ነገር ምን ያሳስባል ? እኔ የማስበው ስለ ህይወት ነው ። ህይወት ድንቅ ናት ። አንተስ ?»

«እኔ ስለ ሞት አስቤ አላውቅም ነበር ። ግን እናቴ ከሞተች ወዲህ ሁልጊዜ ስለ ሞት አስባለሁ ።»

«ስለ ህይወት ማስብ ጀምር ። ህይወት ድንቅ ናት ።»
«ተአምር አያልቅም» ብሎ ዝም አለ—ሀዲስ ።

ከሀዲስ በስተቀኝ የተቀመጠው ሌላው አስተማሪ ደግሞ ፣ «ጋሼ ማይዘር» ይባላል ። ተማሪዎች ለአስተማሪዎች መቼም የማያወጡት ስም የለም ። ጦጦች አይደሉ ? ጋሼ ማይዘር የተባለበት ምክንያት ማርክ ለመ ስጠት በጣም ስለሚቆናቆን ነበር ። አንዴ ጨክኖ ከሰጠው ማርክ ነቅንቅ አይልም ። ያንኑ ማርክ ነበር ደጋግሞ የሚሰጠው ። በኑሮውም ቢሆን እንዲሁ ጭቅ ነው ይባላል ። ቢሞት ከኪሱ ሳንቲም አውጥቶ ሰው አይጋ ብዝም ። ግብዣም ፈፅሞ አይቀበልም ።

«ማርክ መስጠት ላይ ጭቅ ነህ ይባላል ?» አለው ሀዲስ ።

«ማርክ ምፅዋት አይደለም ። ምፅዋት የሚፈልግ ካለ ልመና መሄድ አለበት ።»

«አንድ አይነት ማርክ ነው እሉ ደግሞ የምትሰጠው ?»
«የመጀመሪያ አስተያየቴ የመጨረሻም ነው ።»

ከጋሼ ማይዘር ጎን.የተቀመጠው ሌላው አስተማሪ ደግሞ ፣ «አባ መስጠት» ይባላል ። ደህና ማርክ ስለሚሰጥ ብቻ አይደለም አባ መስጠት የተባለው ። ዱላውም ያንኑ ያህል ነበር። ጠመኔ ከወረወረ አይስትም። ክፍል ገብቶ ብዙ ጠመኔዎች ሳይወረውር አይወጣም ። ማርክ ላይ ግን ሊጋስ የሊጋስ መጨረሻ ነው ይባላል ። «አስተማሪ ማርክ በመስጠት ምን የሚ ያጣው ነገር አለ ? የትምህርት ቤቶች አይነተኛ ተግባር ተማሪዎችን መር ዳት ነው ። ህይወት ራስዋ ሁዋላ ምርቱን ከግርዱ ትለይ የለ? በትምህርቱ ጎበዝ የሆነ ተማሪ በስራ አለምም እንደዚያው ይጎብዛል ማለት አይደለም ። ቸርቺልና አይንሽታይን ትምህርት ቤት ሳሉ ደደቦች ነበሩ ይባላል ። ማርክ የችሎታ መለኪያ አይደለም» ይላል ።

«ታዲያ የችሎታ መለኪያ ምንድን ነው ?»

«ህይወት ። የህይወት መንገድ ። ጥቂቱ ወደ ፊት ይሄዳል ። ጥቂቱ ወደ ሁዋላ ይቀራል ። ህይወት ናት ደንበኛ የችሎታ መለኪያ ትምህርት ቤት ።»

«ተአምር አያልቅም ።»

«አዎን ፣ ተአምር አያልቅም ። ግን ከተአምራት ሁሉ ይበልጥ ተአምር ራሱ ሰው ነው ።»

«ይህን አባባል ከዚህ ቀደም ሰምቻለሁ ወይም አንድ ቦታ አንብቤ አለሁ . . .»

«ከማክሲም ጎርኪ የተወሰደ ጥቅስ ነው ።»
«አዎን ፥ እሁን ትዝ አለኝ ።»
«መፃህፍት ማንበብ ትወዳለህ ?»
«አዎን ፣ መፃህፍት ህይወቴ ናቸው ።»
«እንግዲያውስ የማውስህ መፃህፍት አሉኝ» አለው ።

ከአባ መስጠት ሁዋላ የተቀመጠው ሌላ አስተማሪ ደግሞ ፣ «ጋሼ ታዲያስ ?» ይባላል ። ሁልጊዜ እንደ ሳቀና እንደ ቸኮለ ነው ። ሁልጊዜ ከፊቱ ላይ ፈገግታ አይጠፋም ። ምናልባት በአለም ላይ መሳቁ ይሆናል — አለም ታስቅ እንደሆን ። ደግሞ ሁልጊዜ እንደ ቸኮለ ነው ። የት ለመድረስ እንደሚጣደፍ አይታወቅም ። ታዲያ ክፍል በገባ ቁጥር እንደምን አደራችሁ ? እንደምን ዋላችሁ ? ማለትን አያውቅም ። ሁልጊዜ ፣ «ታዲያስ ልጆች ?» ይላል ።

«አለናን» ይሉታል ።

በመንገድ ላይ ያገኘውን ሁሉ ፣ «ታዲያስ ?» ሳይል አያልፍም ። አለምን በሙሉ እጅ የሚነሳበት መንገድ ከታዲያስ ሌላ የተሻለ ዘዴ አልኖ በረውም ። «አለናን» ካሉት ሌላ ጥያቄ አይጠይቅም ። እየሳቀ ተጣድፎ ያልፋል ። ምናልባት ስለ ምንም ነገር ለማወቅ ስለማይፈልግ ይሆናል ። ማን ነው ስለ አለም ለማወቅ የሚፈልገው ? ይልቅ የሚያስፈልገው ከተቻለ አለምን መለወጥ ነው ። . . . በማለት ሲያስብ አቶ ይርጋ መጡ ።

አቶ ይርጋ አስተማሪዎች ከሚሰበሰቡበት ቦታ ቀድመው አይገኙም ። ወደ ሁዋላ ቀረት ብለው መምጣትን ያዘወትራሉ ። ወደ ስብሰባው አዳራሽ ሲገቡ አስተማሪዎች ሁሉ ተነሱላቸው ። ከጋሼ ቀውሌ ፣ ከጋሼ ማይዘር ፣ ከጋሼ አባ መስጠትና ከጋሼ ታዲያስ ሌላ፣ ሌሎች አራት አስተማሪዎች አዳራሹ ውስጥ ነበሩ ። እምብዛም ትዝ አይሉትም ። እንደ መናፍስት ሹልክ ብለው የሚጠፉ አይነት አስተማሪዎች ነበሩ ። ምናልባት አለም በእንደዚህ ያሉ አስተማሪዎች አይነት የተጣበበች ትሆናለች—የተለየ ስብእና በሌላቸው ሰዎች—ዝም ብለው መጥተው ምንም አይነት ዱካ ሳይተው ዝም ብለው በሚሄዱ ሰዎች ። የተለየ መልክ ፣ የተለየ ስም ፣ የተለየ ጠባይ የሌላቸው የአለም መናፍስት ።

ከአራቱ አንዱ ለየት ያለ ነበር—«ዱቤ ።» እንደ ዱቤ ያለ ወፍራም ጂምናስቲክ አስተማሪ ሀዲስ በህይወቱ አጋጥሞት አያውቅም ። ግን የሚገርመው ነገር ዱቤ ሰውነቱ አይከብደውም። ተማሪዎችን ላባቸው ጠብ

እስኪል ድረስ ሜዳ ለሜዳ ፥ ወንዝ ለወንዝ ሲያስሮጥ ፥ ሲያዘልል ፥ ኳዋስ ሲያጫውት እሱም አብሮ ሲሮጥ ፥ ሲዘል ሲጫወት ይውላል ። ሰውነቱን ማንቃንቅ ይወዳል ። ታዲያ ይርበዋል ። ሁልጊዜ ይርበዋል ። ከኪሱ ውስጥ የሚበላ ነገር አይጠፋም ። ቢያጣ ቢያጣ እንጀራ በሚጥሚጣ ይዞ ይመጣል ። ሁልጊዜ እንደ በላ ነበር ። ለቁርስ ፍርፍር ፥ ዳቦ ፥ እንቁላል ፥ ወተት ፥ ለምሳው ቢያንስ ሶስት እንጀራ ፥ ለራቱም እንደዚሁ ይበላል ። ይበላል ። ሁልጊዜ ፥ «ከሆድ የበለጠ የሰው ጠላት የለም ። ዘለአለም በቃኝን አያውቅም ። ሰው እክ ሆድን የሚያክል ጠላት ተሸክሞ ነው የሚኖረው» ይላል ።

አቶ ይርጋ የሚያነሱት የተለየ ነጥብ አልነበራቸውም ። ለሃያ ደቂቃዎች ያህል ስለ ዲስፕሊን አስፈላጊነት ነበር አጥብቀው ሲናገሩ የቆዩት ። በዲስፕሊን ያልታነፁ መምህራን በዲስፕሊን የታነፁ የነገውን ትውልድ ለማፍራት አይችሉም ፤ አገራችን ባሁኑ ጊዜ በጣም የሚያስፈልጋት ነገር ቢኖር ዲስፕሊን ነው ። ልጅ አባቱን ፥ ታናሽ ታላቁን ፥ ጭፍራ አለቃውን ፥ ወጣት አዛውንቱን ማክበርና መታዘዝ ከጥንት ጀምሮ ባህላችን ከመሆኑም በላይ ፥ ኢትዮጵያ አገራችንን አሁን ካለችበት የስልጣኔ ደረጃ ሲያደርሳት የቻለውና ታፍራና ተከብራ እንድትኖር ያደረጋት ዲስፕሊን ነው ። ሌላ ነገር አይደለም ። ይህንን በመገንዘብ እኛ መምህራን ስለ ዲስፕሊን አጥብቀን ማስተማር አለብን ። የቀለም ትምህርት ማስተማር ብቻውን ረብ የለውም ። ዋናው ቁም ነገር ዲስፕሊን ነው ። ምግባሩ የላላና የላሸቀ ትውልድም ለራሱም ሆነ ላገሩ አይበጅም ። ላገራችን ችግር አይነተኛው መፍትሄ ዲስፕሊን ነው ፤ መታዘዝን የማያውቅ ለማዘዝ አይችልም ። ለሰው አክብሮት የሌለው ሊከበር አይችልም ። ጨው ለራስህ ስትል ብትጣፍጥ ጣፍጥ ፥ አለበለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል ፤ እንደሚባለው ነው ። ነገር ከስሩ ፥ ውሃ ከጥሩ እንደሚባለው ዲስፕሊን ከትምህርት ቤት መጀመር አለበት ። የአስተማሪዎች ሀላፊነት ብቃትና ጥራት የሚለካው የነገው ትውልድ በሚከተለው ዲስፕሊን ነው . . . ወ.ዘ.ተ. እያሉ እንደ አባ ጨፌ ድቤ ስልቱን በማይለውጥ ሰላላ ድምፅ ዲስፕሊን . . . ዲስፕሊን . . . ዲስፕሊን ሲሉ እውነትም የኢትዮጵያ ችግሮች ሁሉ መፍትሄ ዲስፕሊን መሆኑን ለማሳመን ምንም አይቀራቸውም ።

ከአስተማሪዎቹ ጥያቄም ሆነ አስተያየት አልቀረበም ። የመልካም ዲስፕሊን ምልክት ይሆን ? ሀዲስም ዝም አለ ። ስለ ዲስፕሊን ለቀሪው ሀይወቱ የሚበቃውን ያህል ሰምቶአል ። ጋሼ ማይዘር ከተቀመጠበት ሲነሳ ስለ ዲስፕሊን ይጠይቅ ይሆን ? በማለት በልቡ አሰበ ።

«ሁላችሁም እንደምታውቁት በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ ያለን መምህራን ብዙ የተለያዩ ችግሮች ያጋጥሙናል ። እኔ የሚገርመኝ እንደ ዛሬው በምንሰበሰብበት ጊዜ የሚያጋጥመን ችግር የሚቃለልበትን መንገድ የሚያሳየን ቀርቶ አቅጣጫውን እንኳን የሚያመለክተንን ሀሳብ የሚሰጠን የለም ። ዛሬም በቃን እስከንል ድረስ የሰማነው ስለ ዲሲፕሊን ነው ። በሉ እንግዲህ የሰማነውን በልባችን ያሳድርልን ።» ብሎ ቁጭ ሲል ፥ ፀጥ ብሎ የነበረው ክፍል በጭብጨባ አስተጋባ ።

አቶ ይርጋ የሚያልበውን መላጣቸውን አስር አስሬ ይጠርጉት ነበር ።

ጋሼ ቀውሴ ረጅም ቁመናውን እንደ ሽመል መዞ ተነሳ ። «ድንቅ ነው እዚያውን ፈርቶ ዳውላውን መደብደብ» ብሎ እንዲ አናፋና ፥ «አቶ

ይርጋ ላይ ከመዘባነን አስተያየትህን በጋዜጣ አታወጣውም ኖሮአል ? ነገሩ በሁላችንም ልብ ውስጥ ያለ ቢሆንም እዚህ እንደ ዮሀንስ መጥምቁ በምድረ በዳ ብትጮህ ምን ይጠቅማል ? ድንቅ ነው በምድረ በዳ መጮህ» አለው ።

አቶ ይርጋ ፈገግ አሉ ።

«በማን ላይ ቆመሽ ንጉሡን ታሚያለሽ አሉ ። በማን ጋዜጣ ማን ሲፅፍ! በጋዜጣ ስለ ችግርና ብሶት ሲፃፍ አላየንም። ኢትዮጵያ ምን ችግር አለባት ? የጥጋብ አገር ናት ። እድሜ ለንጉሥ ነገስታችን» አለ ጋሼ ማይዘር ።

«እንግዲያውስ ባፍ ይጠፉ በለፈለፉ ብለህ—ዝም፤ዝምታ ድንቅ ነው ። ከአፍ የወጣ አፋፍ ይባላል ። አቶ ይርጋ የመንግስት ደንብና ስርአት ሲያ ስለውጡልህ አይችሉም ። ስርአት የሚለወጠው በስርአት ነው» ብሎት ቁጭ አለ ።

አቶ ይርጋ የተባለውን ነገር ሁሉ በመጣደፍ ይፅፉሉ ። ሁዲስ ለማስ ፈራራት የሚያደርጉት ሙከራ መሰለው ። ጋሼ ዱቤ ወፍራም ሰውነቱን በቀላሉ ተሸክሞ ተነሳና ፥ «የኔ ጥያቄ ከሌሎቹ ለየት ያለ ነው» ብሎ መና ገር ጀመረ ፤ «እኔ እንኩዋን ሚዳ ሚዳውን ስሮጥ ስለምውል ችግሩ ይህን ያህልም ላይሰማኝ ይችላል ። ግን ያሉን ክፍሎች በጣም ተጣበዋል ። በዚያም ላይ ትምህርት ቤቱ በላያችን ላይ ሊፈርስ ነው።ይህን ጥያቄ አም ናም አንስቼ ነበር ። ለዘንድሮ ምን ሊደረግ እንደ ታሰበ ለማወቅ እፈልጋ ለሁ ። ሁለተኛው ነገር ፤ መቼም የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣልና ደሞዛችን በየወሩ ሳይዘገይ እንዲደርስን ምን እንዳደረጉልን ለማወቅ እፈልጋለሁ ። ለወር ተኩል ፥ ለሁለት ወር ደሞዛችን ሳይከፈል እየቆየ እንዴት ይሆናል ? ሆድ ቀጠሮ አይሰጥም ። ባዶ ሆድም ዲስፕሊን እሺ ብሎ አያከብርም» ብሎ ቁጭ ሲል ሁሉም ሳቁ ።

አቶ ይርጋ አልሳቁም ። ጥያቄ በቀረበላቸው ቁጥር መሳጣቸውን ያል ባቸዋል ። ኮስተር እንዳሉ ፥ «ሙከት ሲሰባ ሾተል ይልሳል» ብለው ተረ ቱና ፥ «ለማንኛውም ነገር ስለ ትምህርት ቤቱም ሆነ ስለ ደሞዛችሁ አከ ፋፈል ለጠቅላይ ግዛቱ ፅህፈት ቤት በቃልም ሆነ በፅሁፍ አሳስቤአለሁ ። በዚህ አመት ደሞዛችሁ በወቅቱ እንደሚከፈል ተስፋ አደርጋለሁ ። ስለ ትምህርት ቤቱ አድሳትም ሆነ መስፋፋት ጉዳይ ግን እንደ አምናው ዘንድሮም የተሰጠኝ መልስ ፥ 'በጀት የለም' ነው ። 'በጀት የለም' ። ሁልጊዜ የሚሰጠው መልስ ይኸው ነው ። እኔ በጀት አልሆንም እንግዲህ ። ከማሳሰብ ሌላ ምን አድርግ ትሉኛላችሁ ?» አሉ እየተማረሩ ።

ጲላጦስ ከደሙ ንፁህ ነኝ ብሎ እጁን ባደባባይ ታጥቦ ክርስቶስን አሳልፎ ሲሰጥ በአቶ ይርጋ ተመስሎ ሁዲስን ታየው ። እሱም በተራው ተነሳና ፥ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አድርጎ ሲያበቃ ፥ «መቼም ትምህርት ቤቱ በላያችን ላይ ሊወድቅ የተቃረበ መሆኑ ግልፅ ነው ። ታዲያ በጀት የለም ስለ ተባለ ዝም ብለን ማየት የለብንም ። ይቅርታ ይደረግልኝና ፥ በማሳሰብ ብቻ ሀላፊነትን ከራሳችን ማውረድ አንችልም . . . » ሲል—

አቶ ይርጋ ቱግ ብለው ፥ «ታዲያ ምን ይሁን ነው የምትለው ! እናቱ የሞተችበትና ገበያም የሄደችበት እኩል ያለቅሳል ይባላል ። ፍየል ከመድ ረስዋ ቅጠል መበጠስዋ አሉ ። ዝም በል ። እንቶን አያገባህም» አሉት ።

«ይናገር እንጂ ! ለምን ዝም ይላል ። ሁላችንም ሀሳፊነት አለብን» — አቶ ጣሴ ደጉ ነበሩ ።

«ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድም ብዬ ነው» አለ ሀዲስ ።
«ሙሾ ካማረሀ ንካዋ ። ማን ከለከለህ !» አሉት አቶ ይርጋ ።

ንዴት እየተናነቀው ፥ «ነገርዎ አሳዝኖኛል» ከማለቱ ፥ ይባስ ብለው ፥ «ከል መልበስ ፣ ያዘነ ከል ይለብሳል» አሉት ።

ሀዲስ ንዴቱን እንደ ምንም ውጦ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አደረገና ፥ «አዎን—የትምህርት ቤቱ ሁኔታ ከል ቀርቶ ማቅም ያስደርባል ። በጆት የለም ስለ ተባለ ምን አገባን በማለት እንደ ጲላጦስ እጃችንን ታጥበን መቀመጥ የለብንም ። የህዝቡ ችግር ይመለከተኛል ፤ ምክንያቱም የኔም ችግር ነውና ። ህዝቡንም ይመለከተዋል ፤ ምክንያቱም የራሱም ችግር ነውና ።

«አዩ ፥ አቶ ይርጋ ፥ ለበጎ አላማ የማይተባበር ፥ የራሱን ችግር በራሱ ጥረት የማይፈታ ህዝብ የለም ። በተአምር መና ከሰማይ ይወርዳል ፥ ውሀ ወደ ወይን ጠጅ ይለወጣል ብለን መጠበቅ የለብንም ። ህዝቡ ለጋራ ችግሩ የጋራ መፍትሄ እንዲፈልግለት ካስተባበርነው ይህችን ትምህርት ቤት መስራት ቀርቶ ተራራውን ሜዳ ሊያደርገው ይችላል ። እኛ ከልብ ካመንበት ህዝቡን ማሳመን አያቅተንም ። በፊት እንዳልኩት ለበጎ አላማ የማይተባበር ህዝብ የለም ። ባጭር ጊዜ ውስጥ አዲስ ትምህርት ቤት ለመስራት እንደምንችል አልጠራጠርም» አለና በረጅሙ ተነፈሰ ።

«ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው» ብለው አቶ ይርጋ ተረቱበትና ቀጥለውም ፥ «አዎን ፥ ማገር እያግዝ ቤት አስፋ ይላል አሉ ። አንተ አሁን የምትለውን ሳናስብበት ቀርተን አይደለም ። አዲስ አሳብ ያመጣህ መስሎህ ከሆነ ተሳስተሃል ።» ወደ ጋሼ ዱቤ እየተመለከቱ ፥ «አይደለም እንዴ ?» ካሉ በሁዋላ ወደ ጀመሩት ነጥብ ተመልሰው ፥ «በመፅሀፍ የምናነበውና በውጭው አለም የምናየው ነገር ሁሉ አንድ አይምሰልህ ። ህዝቡን ማስተባበር አንተ እንደምታስበው ቀላል ነገር አይደለም ።

«በዚህ ላይ ደግሞ ፥ በሁዋላ የመጣ አይን አወጣ ሆነና ነው እንጂ ፥ ህዝቡ ፥ ወዳጄ ፥ ጉልበቱንና ገንዘቡን አስተባብሮ መስራት ተሰኖታል ። ጉልበቱም ገንዘቡም የለውም ። ካልክስ በመረዳጃ ስራ እምነት አጥቶአል ። ለምን ? ብትለኝ ፥ ዛሬ ጭቃ ሹሙም ፥ ወረዳ ገዥውም ፥ የመጣው ባለስልጣን ሁሉ ኑ መንገድ ስሩ ፥ ኑ ገንዘብ አዋጡ ፥ መንገድ ልንሰራላችሁ ነው ፥ ክሊኒክ ልንከፍትላችሁ ነው የማይል የለም ።

«የተሰራ መንገድ የለም ። ህዝቡ ስር ከመማስና ቅጠል ከመበጠስ አላለፈም ። በግድም ሆነ በውድ የተሰበሰበው ገንዘብ ሁሉ እንደ ቅቤ የትም ቀልጦ ቀርቶአል ። ቅድም እንደ ሰማኸው የኑሮ ውድነት ሁሉንም ቀስፎ የያዘበት ጊዜ ነው ።

«አይምሰልህ ወዳጄ ፥ ወጣቶች ስትባሉ መቼም ሁሉም ነገር ሜዳ ሆኖ ነው የሚታያችሁ ። በናንተ ቤት ዳገት ፥ ቁልቁለት ፥ ገደል የሚባል ነገር የለም ። ሁሉም ሜዳ ነው ። ኢትዮጵያ ተራሮች የበዙባት አገር አይደ

ለችም — ለናንተ ። ትምህርት ቤቶችና ክሊኒኮች ቢሰሩ ህንፃዎች ብቻቸውን ትምህርት ቤት ወይም ክሊኒክ ሊሆኑ የሚችሉ መሰለህ ? አስተማሪዎች ፥ የህክምና ባለሙያዎች ያስፈልጋሉ ። እነዚህ ደሞ እንደ ሸቀጥ በፋብሪካ የሚሰሩ አይምሰልህ ። የእነ ቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ ይሉሃል ይኸው ነው ። የመጣኸው ላንድ አመት መሆኑ ነው መሰለኝ እንዲህ የሚ ያደርግህ !»

ሀዲስ ብልጭ አለበት ።

«እርስዎ እንደሚሉት እንዲሁ ከመሬት ተነስቼ አይደለም የምናገረው» ብሎ ጀመረ— «በዚህ አመት አንደኛ ክፍል ለመግባት ከተመዘገቡት ከሶስት መቶ በላይ ከሚሆኑ ልጆች ውስጥ ቦታ አለን የተባለው ለስድሳ ብቻ ነው ። ከበር የመለስናቸው ልጆች የት ይግቡ ነው የምንለው ? የከብት ጭራ እየተከተላችሁ ቅሩ ብለን እንፍረድባቸው ? ዘላለማችሁን ውሀ ቀጂ ፥ እንጨት ሰባሪ ሆናችሁ ቅሩ ነው የምንላቸው ? ልጆቻቸው ትምህርት ቤት ያጡባቸው ወላጆች ይህ አይነቱን ፍርድ የሚሰጡ አይመስለኝም ። የምን ሰጠው ፍርድ ይህ ከሆነ ምናለ ! ታሪክን እንተወው ፥ ህሊናችን አይፈርድ ብንም ? ወይስ ህሊና የለንም ?

«አሁንም ቢሆን እኔ በበኩሌ ህሊናዬ እንደ እሾህ እየወጋኝ ነው ። የሚያሳዝነኝ ፥ ከሁለት መቶ ስድሳ በላይ የሆኑ ልጆችን ቦታ የለንም ብለን እያለቀሱ ከበር እንዲመለሱ ማድረጋችን ብቻ አይደለም» ሲል እንባ ይተና ነቀው ጀመር ። እንባውን እንደ ምንም ብሎ በመዋጥ ቀጠለና ፥ «ህሊናዬን በይበልጥ የሚቆጠቁጠው ነገር የተሰጣቸውን ፈተና ካለፉት ስድሳ ልጆች ውስጥ አስራ አምስቱ ተሰርዘው ፥ ሌሎች ፈተናውን ያላለፉ አስራ አምስት ልጆች እንዲገቡ መደረጋቸው ነው ። ማስረጃው በእጄ ይገኛል ።»

አቶ ዶርጋ ከተቀመጡበት ተስፈንጥረው በመነሳት ፥ «እዚህ ውስጥ የሚያገባህ ጉዳይ የለም !» አሉት ፥ ሌባ ጣታቸውን ቀስረውበት ።

«ለምን አያገባኝም ?»

«የፖሊሲ ጉዳይ አንተን አይመለከትም ! አመፅ ነው እኮ ። ሌላ አይ ደለም ። ይህን አመፅክን እዚያው የለመድክበት ብትሞክረው ይሻላል ። እዚህ ያመፅ ቦታ አይደለም !» ብለው ጮሁበት ።

ሀዲስ ጠጉሩን ቆፈረና ፥ «ፈተና ያለፉትን የድሀ ልጆች ጥላችሁ የባላ ባት ፥ የነጋዴ ፥ የመንግስት ባለስልጣን ልጆች አስገቡ የሚል ፖሊሲ አላየሁም ። ካለ እርስዎ ይንገሩን ። ከሌለ ግን የተሰረዙት ልጆች እንዲመ ለሱ አጥብቄ እጠይቃለሁ ። ትክክለኛ ስራ እንስራ ማለት ደሞ አመፅ አይ ደለም !» ሲል—

«ወንበሬን ውሰዳ ! ይኸው ነው የቀረህ ! ነገሩ ደሞ አንተ እንዳልከው አይደለም ። እኔ ዶርጋ ይህ የህብታም ፥ ያ የድሀ ልጅ ብዬ ለትምህርት በደረሱ ቡቃያዎች መካከል ልዩነት አድርጌ አላውቅም ። በስነ ስርአት ብቻ ሳይሆን በህግ ፊት ያስጠይቅሃል ። ስሞች ካንዱ ወረቀት ወደ ሌላው ሲገለበጡ ምናልባት ስህተት ደርሶ ይሆናል ። የተጭበረበረ ነገር እንደ

ተስራ አስመስለህ እፍክን ሞልተህ መናገርህ አጉል ድፍረት ነው ። አየህ! ሃያ አምስት አመት ሙሉ ሳስተምር እንዲህ አይነቱ ውርደት ደርሶብኝ አያውቅም ። መልካም ስሜ ደሞ በከንቱ ጠፍቶ የሚቀር አይምሰልህ» ብለው አሁንም ምሁቡት ።

ሀዲስ በጭኸታቸው ፍንክች አላለም ።

«እኔ የጠየኩት የተሰረዙት ልጆች እንዲመለሱ ነው» አላቸው ኮስተር ብሎ ።

«ባይመለሱ ምን ትሆናለህ !?»

«የልጆቹ ወላጆች እንዲያውቁት አደርጋለሁ ። ከዚያም አልፎ ለበ ላይ አመለክታለሁ ። አለዚያ ሀሊናዬ ሊያርፍ አይችልም ። መጥፎ ህሊና ይዤ ከምኖር ሞቴን እመርጣለሁ» አላቸው ድርቅ ብሎ ።

አቶ ይርጋ መላጣቸውን እየጠረጉ ትኩር ብለው ይመለከቱት ጀመር ። ምናልባት በሰው የተመሰለ ሰይጣን ነበር የሚመለከቱት ። በቀላሉ የሚያ ስፈራሩት አውሬ መስሎ አልታያቸውም ። ሌሎቹ አስተማሪዎች አንገታ ቸውን ደፍተዋል ። የህሊና ፀሎት የሚያደርሱ ይመስላሉ ። ክፍሉ ፀጥ ብሎ ነበር ። ሀዲስ ሲተናነቀው የቆየውን እንባ መያዝ አቃተው ። የተወለደበ ትን ቀን ፣ እግሩ ሱዱ ቦሮን የረገጠበትን ቀን በልቡ ረገመ ። አቶ ይርጋ በእንባው ውስጥ ብዥ ብለው ታዩት ። አይናቸው የጥላቻ ጦር ይወረውር በታል ። የጥላቻ ጦር መልሶ አልወረወረባቸውም ። ጥልቅ ሀዘን አጥንቱ ድረስ ዘልቆ ተሰማው ።

«ስለ ትምህርት ቤቱ ስራ ምን ቀረጥን ታዲያ ?» ጋሼ ዱቤ ነበር ።

አቶ ጣሴ ደጉ ተነስተው ፣ «እኔ የመምህር ሀዲስን ሀሳብ እደግፋለሁ ። ሌላው ቢቀር ሁለት መቶ ስድሳ ወላጆች ይተባበሩናል ። ጎበዝ ፣ መምከር አለብን ። ጥቂት ሰዎች ተፍጨርጭረው መዳህ ካልጀመሩ ሌሎች በሁለት እግሮቻቸው ሊቆሙ አይችሉም» ብለው ቁጭ ሲሉ ፣ የተቀሩትም አስተ ማሪዎች ባንድነት እጃቸውን በማሳየት ተባባሪነታቸውን ገለጡ ።

ያቶ ይርጋ ግልምጫ ሰው ለመግደል የሚችል ቢሆን ኖሮ አቶ ጣሴ አይተርፉም ነበር ። ሀዲስ ትንሽ የተስፋ ጭላንጭል ታይቶት ፈገግ አለ ።

# ክፍል ፯

የአስተማሪዎች ስብሰባ በተደረገ በሶስተኛው ቀን ፣ የፈተናው ውጤት መግለጫ ተነስቶ በምትኩ ፣ «የወጣው መግለጫ አንዳንድ ስህተቶች ስላሉ በት ሁኔታው ተጣርቶ ትክክለኛው መግለጫ በቅርቡ ይሰጣል . . . » የሚል ማስታወቂያ በተለጠፈ በሁለተኛው ቀን ፣ ፈተናውን ያለፉ ልጆች ስም ዝርዝር ወጣ ። የፈለገው ይህን ነበር ።

ተንኮል ካልተጨመረበት በቀር መጀመሪያውኑ ስህተቱ እንዴት ሊደርስ እንደ ቻለ አሁንም አልገባውም ። ለማንኛውም ነገር ስህተቱ ታርሞአል ። አላማው የደረሰው ስህተት እንዲታረም ማድረግ ነበር ። ሀዲስ በቂም በቀል ስለማያምን ይቅርታ ብላቸውስ ምናለበት ? በማለት ወደ ቢሮአቸው ሲገባ ቀና ብለው ሳያዩት ፣ «ወንድም ፣ ስራ ይዤአለሁ ። ቢሮ ማንም በፈለገው ጊዜ ዘው ብሎ የሚገባበት የጋለሞታ ቤት አይደለም ። ጉዳይ ካለህ ቀጠሮ ጠይቀህ ና» አሉት ።

መላጣቸው የሚያይ አይን ያለው መሰለው ። ቀንዱዋን እንደ ተመታች ከብት ቶሎ ምልስ በማለት የሻፍረት ማቁን ተከናንቦ ሊወጣ ሲል ፣ «እላሰናበትኩህም» አሉት ።

ጀርባውን እንደ ሰጣቸው ቀጥ ብሎ ቆመ ። ወጥቶ በመሄድና በመቆየት መካከል ነፍሱ ላንዳፍታ ተሙዋገተች ።

«ምን ኖሮአል ?» አሉት ።

ይቅርታ የሚሉት ቃል ከአፉ ሊወጣ አልቻለም ። ፊቱን መለስ አድርጎ ፣ «ሌላ ጊዜ ቀጠሮ ጠይቄ እመጣለሁ ። የሚያስቸኩል ጉዳይ የለኝም» አላቸው ።

«አዎን ፣ ምናለ ፣ አብረት ነው» ብለው ፣ መላጣቸውን ከፊቱ ዞር በማድረግ ፊት ለፊት እያዩት ፣ «አየህ ፣ ሀዲስ ፣ ባያድለኝ ነው እንጂ አንተን ሶስት አራት ጊዜ በእድሜ የሚበልጡ ልጆች አደርስ ነበር ። ካንተ ውርደት ሳይሆን አክብሮት ነበር የምጠብቀው ። አየህ ፣ መልካም ስም ከሽቶ ይሸታል ይባላል ። መልካም ስሜን አጉል ጥርጣሬ ላይ በመጣልህ በጣም አዝናለሁ ።

«የሰው ሀዘን በከንቱ የሚቀር አይምሰልህ ። ሰው ከሚያዝንብህ በጨቤ ቢወጋህ ይሻላል ። ቢሮዬ መጥተህ ስህተቱን ብታስታውቀኝ ወዲያውኑ ይታረም ነበር ። ወይም ተመካክረንበት አንድ ዘዴ እንፈልግለት ነበር ። ይርጋ ተንኮል ሰርቶአል ብለህ በመገመት በቅን ልቦና የተሰራውን ስህተት በልብህ ይዘህ ባደባባይ ስትወነጅለኝ እኔ ለራሴ አላዘንኩም ።

ነገሩ እትስረቅ አትፍራ ነው ። የሚሰራ ሰው ይሳሳታል ። ይልቅ ያዘንኩት ለወጣቱ ትውልድ ነው ።

«ለውንጀላም ሆነ ለማንኛውም ነገር ትጣደፋላችሁ ። መሸቶ የሚነጋ አይመስላችሁም ። ማስተዋል የለም ። አክብሮት ፣ ዲስፕሊን የሚባል ነገር በናንተ ቤት የለም ። ሌላው ቢቀር ሽበት አይከበርም ? ሃያ አምስት አመት ሙሉ በንጠር እየተንከራተትኩ ሳስተምር የኖርኩት የድሀውን ልጅ ነው ። አይምሰልህ ። ይርጋ ለባለጠጋ ልጆች አያደላም ። ይህን ትምህርት ቤት ደግሞ እንደ ልጄ አድርጌ ነው የምመለከተው ። ልጅ አልሰጠኝም ! ሌላ ልጅ የለኝም ። ትምህርት ቤቱን የሚጎዳ ነገር ማየት አልፈልግም ። የሚጠቅም ነገርም ካለ ደግሞ እኔ እንድስማማበት ያስፈልጋል ። ገባህ ? . . . ለማንኛውም ነገር ያለፈ አለፈ ―ሳለፈ ከረምት ቤት አይሰራም ይባላል ። አሁን የምፈልገው ያስቀረሽውን ኮፒ እንድትሰጠኝ ነው ። ዱሮውንም ቢሆን ያለኔ ፈቃድ ኮፒ ማስቀረት አልነበረብህም» አሉትና በረጅሙ ተነፈሱ ።

«ቀድጀ ጥዬዋለሁ» ብሎ ዋሸ ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ቀዶ ሊጥለው አስቦ ነበር ። አሁን ግን አሳቡን ለወጠ ።

«ቅዳሀን ሲያዩት ምኝ ትመስላለሀ ?»
«ቀድጀ ጥዬዋለሁ ።»
«ለምን ቀደድከው?»

«ስህተቱ ከታረመ ምን ያደርግልኛል ? ዱሮውኑ ኮፒ ያስቀረሁት ለጥንቃቄ ብዬ ነው እንጂ ለተንኮል አልነበረም ። እኔ ተንኮል አላውቅም ። ፊት ለፊት መናገር ተንኮል አይደለም ። ጤናማ ምልክት ነው» ሲላቸው ፣ የውሸት ሳቅ የሚስቀው አይናቸው ሰይጣናዊ ተንኮል ይፈነጥቅ ነበር ። በሀዲስ ላይ አሉባልታው ተጋግሞ መወራት የጀመረውም ከዚያ በሁዋላ ነበር ።

ነገሩ ባሉባልታ ተወስኖ አልቀረም ። የታጠቁ ፖሊሶች ከማያስተምር በት ክፍል ድረስ መጥተው ለጥያቄ እንደሚፈለግ ነገሩት ፡

«የምን ጥያቄ ?»
«በሁዋላ ይደርሱበታል ። አሁን እንሂድ !»
«ደህና ። ለዲሬክተሩ ልንገራቸው ።»
«ሰምተዋል ።»
«እና ?»
«እና ፣ እኔ ምንም አያገባኝም ብለዋል ።»

ተማሪዎቹ በረንዳ ላይ ተደርድረው ወሬ ያዳምጡ ነበር ። ፋጡማ መሀመድን ጠራትና አቶ ጣሴን ፈልጋ ለጥያቄ ወደ ፖሊስ ጣቢያ መወሰዱን እንድትነግራቸው አደራ ብሎአት እንደ በግ እየተነዳ ሄደ ። ሁለተኛ እመለሳለሁ የሚል ግምት አላደረበትም ። ለጥያቄ ትፈለጋለህ ተብሎ ሄዶ ከሀይለ ስላሴ እስር ቤት በጤና የሚመለስ ሰው ቁጥር ብዙ እንዳልሆነ ያውቃል ። እንደ እውነቱ ከሆነ ስምንና አድራሻን ከማመለከት ሌላ ጥያቄ የማያቀርብም አልነበረም ። የሰውዬው ሀጢአት ከተነበበለት በሁዋላ

በቃ—ፍፁም ጨለማ ። አለምን ረስቶና በአለም ተረስቶ በጨለማ ተውጦ ቀርቶ የግፍን ፅዋ እስኪያቅር ድረስ መጨለጥ ። የምን ሰብአዊ መብት ? ድሀ መብት አለው ያለውስ የማን ቂል ይሆን ? ድሀ መብት አልነበረውም ። ቅርሱ ግዴታ ብቻ ነበር—ለእግዜሩና ለንጉሱ ። ሀገ መንግስት ? የምን ሀገ መንግስት ? መብት አይሰጥ ወይም አይነፍግ ። የኢትዮጵያ ሀገ መንግስት አባት በህግና በህዝብ ላይ በአደባባይ የተቀኙት ቅኔ ፣ ይበል ፣ የሚያሰኝ መልካም ሰምና ወርቅ ፣ ምስጢሩ ተፈቶ የማያልቅ ። እንዳያማህ ጥራው ፣ እንዳይበላ ግፋው ነበር ነገሩ ። አይ ጥበብ ፣ አይ ዘዴ ! ሰዩመ እግዚአብሄር ፣ ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ። የቤተ ዳዊትን ፣ የቤተ ሰሎሞንን፣ የቤተ ይሁዳን ጥበብ እንዳለ የማን ቤት ወረሰና ! ተአምር አያልቅም ።

የወፍ መንጋ ወደ ገባ በረሃ ሲበር ተመለከተና ነፃነት ደህና ሁኚ ብሎ እንደ ታጀበ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሲዘልቅ ከመቶ አለቃ አሸኔ ትከሻ ላይ ያለው ኮከብ ብልጭ አለበት ። ፖሊስ ባየ ቁጥር የሀዲስ ልብ ይሸበራል ። የአራት ኪሎ ጋዜጠኞች ፣ «በየአመቱ የሚያገረሽ በሽታ» ወይም «የድን ቁርና ትእይንት» የሚሉት የአራት ኪሎ ግርግርና ሽብር ይመጣበታል ። በሚያስለቅስ የመርዝ ጢስ የደም እንባ ሲያስለቅሰውና ባልተወለደ አንጀት በቆመጥ እንደ እህያ ሲነርተው ይታየዋል ። ተው ስማኝ ሀገሬ . . . . ተው ስማኝ ሀገሬ . . ፣ የማን ጆሮ ቢሰማ ! ተማሪ በባዶ ጉልበቱ ጠዋት በማለዳ ጠጠር ላይ እንዲሄድ ሲደረግ ማን ዞር ብሎ ሊያይ ! . . . የጥጋበኞች ዋይታ ፣ ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ እንዲሉ ። የገደል ማሚቶ በልቶት የሚቀር ጩኸት ። እና ፣ መፍትሄው ፣ ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ እንዲሉ ። ተማሪዎች አጥፍተዋል ፣ ወላጆች ይካሱ ማለት ነበር ።

—ንጉስ መሀሪ ነው ። ማሩልን ። አባት መሀሪ ነው ። ማሩልን ።

እንግዲህ ምህረቱ ከዙፋን ይወርዳል ። አባት መሀሪ አይደል ? አባቱን ክዶ በሀይለ ስላሴ የማይምል ማን ነበርና ! አፉን የፈታው በሀይለ ስላሴ፣ ፊደል ሀ ብሎ የጀመረው በሀይለ ስላሴ ፣ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ የተማረባቸው ትምህርት ቤቶች የሀይለ ስላሴ ፣ ተወልዶ ያደገበት ጎዳና የሀይለ ስላሴ ፣ የሚዳኝበት ህግ በሀይለ ስላሴ ፣ ቴያትር ቤቱ የሀይለ ስላሴ ፣ በትረ መንግስቱ የሀይለ ስላሴ ፣ ተወልዶ የሚኖርበት አገር የሀይለ ስላሴ—የሀይለ ስላሴ ፣ ለሀይለ ስላሴ ፣ በሀይለ ስላሴ—ማን በሌላ ሊምል !

«ቤት ለእምቦሳ» አለው የመቶ አለቃ አሸኔ ፣ በሲጃራ የበለዙትን ጥርሶቹንና በመጠጥ የቦዘዙትን አይኖቹን እያሳየው ።

ሀዲስ ወንበር ስቦ ቁጭ አለ ። ከመናገር መስማት ይሻላል ብሎ ዝም ።

«አንድ ቀን እዚህ እንደምንገናኝ ይታየኝ ነበር» አለው ።
«እንዴት ?»
«የመጣህበት አላማ ምን እንደ ሆነ መቼ አጣሁትና ።»
«ምንድን ነው የመጣሁበት አላማ ?»
«አንተው ንገረኝ» አለው ጥርሱን ነክሶበት ።
«እዚህ የመጣሁበት አላማ ፣ አላማ ከሆነ ፣ ለማስተማር ነው . . .»

የመቶ አለቃ ጠረጴዛውን በጡጫ አንዴ ነርቶ ሁልጊዜ ደም ለበሰው በሚታዩት ጎረጥ አይናቹ እየገረመመው ፣ «አዎን ፣ ከድሀ ልጅ ሌላ የጌታ

ልጅ ትምህርት ቤቱ ገብቶ እንዳይማር ለማስተማር ነው የመጣኸው አይ ደለም ? መቼ አጣሁት ። አንተ ባትነግረኝም እኔ አውቀዋለሁ ። ‘ፋና ተስ ማራ ፥ ፋና ተስማራ ፥ እንደነ ሆቺ ሚኒ ፥ እንደ ቼ ጉቫራ’ ብላችሁ የለም ? ድሃ ጌታ እያላችሁ በሰላም ተከባብሮ የሚኖረውን ህዝብ ለማበጣበጥና ፀንቶ የቆየውን የኢትዮጵያን አንድነት ለማናጋት ። ሰይጣናዊ አላማ ችሁን መቼ አጣሁት ?

«የኢትዮጵያ ጠላቶች መሳሪያ በመሆን የወላጅ እናታችሁን ጡት የምትነክሱበቺ ፥ እንደ ይሁዳ አሳልፋችሁ የምትሰጡበት ምክንያት . . . አይ ፥ ኢትዮጵያ የወላድ መሀን መሆንዋ ነው የሚያሳዝነኝ ። በእውነቱ ያሳዝናል ። ገንዘብ ያለው በገንዘቡ ጉልበት ያለው በጉልበቱ እየተረዳዳ በሰላምና በፍቅር የሚኖረውን ህዝብ ባታበጣብጡት ምን አለበት!» አለው ።

ሀዲስ በትእግስት ሲያዳምጠው ከቆየ በሁዋላ ፥ «ጌታዬ ይቅርታ አድ ርግልኝና በእውነት የምትለው ነገር አይገባኝም» አለው ።

«የሌባ አይነ — ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ እንደሚባለው ፥ ስንተዋወቅ ምን ነው ባንተናነቅ ። የሰራኸው ወንጀል ቀላል መስሎህ እንደሆነ የምት ቀልደው ካሁኑ ጀምሮ ቀልድህን ብታቆም ይሻላል ። ቀልድና ቅዘን ቤት ያጠፋል አሉ» ብሎት ፥ ጠረጴዛውን እንደገና በጡጫ ደበደበና ከመቀመ ጫው ተስፈንጥሮ ተነስቶ ላዩ ላይ እያንዣበበበት ፥ «የባላባት ፥ የቱጃር ነጋዴ ፥ የባለስልጣን ልጆች ትምህርት ቤት ገብተው እንዳይማሩ ብለህ አሁን ማ ይሙት አድማ አልተነኮስከውም ነው የምትለኝ ? ህዝቡን ማንሳሳት አለብን አላልከውም ነው የምትለው ? አገሪትዋ የማ መሰለችህ እ ? መንግ ስትስ በማን ትከሻ ላይ የቆመ ይመስልሃል ? ከባድ የፖለቲካ ወንጀል ነው የተናገርከው ። ድሀ ፥ ጌታ በማለት ወገን ከወገን ጋር እንዲጋጭና ህዝብ እንድትከፋፈል ከማድረግ የበለጠ ወንጀል የለም ።

«ግን ነገሩን ሳታውቀው አድርገኸው ይሆናል ። በነገሩ ተፀፅተህ የእምነት ቃልክን ከሰጠህ ጉዳዩ ቀለል ይልልሃል ። ከአያያዝ ይቀደዳል ካነጋገር ይፈረዳል ይባል የለ ። ወጣት ነህ ። ነገሩ እንዲከብድብህ አልፈል ግም ። ምኞትም የለኝም ። አይ ካልክ ግን ፥ ምናለ ፥ በቅሎ ማሰሪያዋን በጠሰች ቢሉ ፥ ለራስዋ አሳጠረች እንደሚባለው ይሆናል ። አስብበት» አለው ፥ ሌባ ጣቱን አፍንጫው ላይ ቀስሮበት ።

ሀዲስ አይኑ እንዳይንሸዋረር አይኑ ስር ያለውን የሙቶ አለቃ ሌባ ጣት እየሸሸ ፥ «የሙቶ አለቃዬ ! እንዲያው ሲበሉዋት የፈለጉዋትን እምራ ጅግራ ናት ይሉዋታል እንደ ሚባለው ሆኖ ነው እንጂ ፥ እኔ አንተ እንደምትለው የፖለቲካ ተልእኮ የለኝም ። የፖለቲካ ጣጣ ውስጥም አልገባሁም . . .»

የሙቶ አለቃ የሀዲስን ንግግር አቋርጦ ጠረጴዛውን እንደገና በጡጫ ደብድቦ ሲያበቃ ፥ ሲጃራ አውጥቶ ለኩሶና በቦንኑው ጢስ ውስጥ እያየው ፥ «ቀልድህን ተወኝ ብያለሁ ! ስማ ወንድም ፥ ተራ ነገር ቀርቶ የዝንብ ጠን ጋራም አታመልጠኝም ። ተማሪዎች ስትባሉ ያለ ፖለቲካ ሌላ ምን ስራ አላችሁ እ ? ትምህርቱን እንደሆነ እርግፍ አድርጋችሁ ትታችሁዋል ። ፈተና በደረሰ ቁጥር ውሀ ቀጠነ ብላችሁ ሰላማዊ ሰልፍ የምታደርጉበት ፥

መስኮት የምትሰባብሩበት ፣ ህግን ለማስከበር በተሰማሩት ፖሊሶች ላይ ድንጋይ የምትወረውሩበት ምክንያት ምን እንደሆነ ለማንም ስውር አይደለም ። ያለ ፈተና ከክፍል ክፍል እየቀለዳችሁ ለማለፍ ነው ።

«ግን የምትቀልዱት በራሳችሁ ላይ ነው ፣ በማንም ላይ አይደለም ። የምታጠፉት ንብረትና ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ ንብረትና ጊዜ መሆናቸውን አዙራችሁ አትመለከቱም ። ግዴታችሁ ምን እንደሆነ አታውቁም ። የተማሪ ግዴታ መማር ነው ። የአስተማሪዎች ግዴታ ማስተማር ነው ። ፖለቲካ የናንተ ስራ አይደለም ። ተምራችሁ ነገ የምትደርሱበት ጉዳይ ነው ። ግን በጥባጭ ካለ ንፁህ አይጠጣም እንደሚባለው ፣ ከሁዋላ ሆኖ የሚጎትቱታችሁ የውጭ እጅ እንዳለ እናውቃለን ። የማናውቀው ነገር የለም ።

«ግን ምን ይደረጋል ? ሁልጊዜ የምለው ነገር ነው እኮ ። መግዛት ያለባቸው አይገዙም ። መማር ያለባቸው አይማሩም ። መታዘዝ ያለባቸው አይታዘዙም ። አሉባልታ ብሄራዊ ሙያችን ሆኖአል ። የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል አሉ ። ይህች ታፍራና ተከብራ የኖረች አገር ይኸው ነው የቀራት በናንተ ምክንያት ። እንዳልኩህ ሀቁን ብትነግረኝ ይሻልሃል ። ልረዳህ እችላለሁ» ብሎት ፣ የሲጃራውን ቁራጭ ካንድ አርጌ መኮስተሪያ ውስጥ አወደመ ።

ሀዲስ ብስጭት ብሎ ፣ «ሀቁን ልነግርህ ጀምሬ ነበር እኮ» አለው ። «እኮ ንገረኝ !»

ሀዲስ አእምሮውን ሰብሰብ አድርጎ የነገሩን አመጣጥ ከስር ጀምሮ ሲያስረዳው ከቆየ በሁዋላ ፣ «እምን ፣ ነገሩ እንደዚህ ነው ። እኔ ለምን የሀብታም ልጆች ይማራሉ ? አላልኩም ። ፈተናውን ያለፉት ልጆች ተሰርዘው ፈተናውን ያላለፉት አንዳንድ የባላባቶችና የነጋዴ ልጆች ለምን እንዲገቡ ተደረገ ? ነው ያልኩት» ብሎት ፣ በረጂሙ ተነፈሰና ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አደረገ ።

«አሁን ያልከው ለመደረጉ ምን ማስረጃ አለህ ? የሰው ስም በከንቱ ማጥፋት ራሱ ወንጀል ነው ። አሁን ማ ይሙት አቶ ይርጋ ይህን አደረጉ ብለህ ልታሳምነኝ ነው ? አሉባልታ የትም አያደርስህም» አለው ።

ሀዲስ የያዘውን ማስረጃ ይዞት ከመጣው ፋይል ውስጥ መዞ ጠረጴዛው ላይ ቁጭ አደረገለት ። የመቶ አለቃ አሸኔ ድንግጥ ሲል አየው ። ነገሩ አሁን በይበልጥ ገባው ። ማስረጃውን ይዞ በማቆየቱ ደስ አለው — መቶ አለቃው ሀዲስ ያልጠበቀው ዱብ እዳ ነበር ። ማስረጃውን እያፈጠነ ያነብ ጀመር ።

አንብቦ ከጨረሰ በሁዋላ ፣ «ይህ ማስረጃ ብቻውን በቂ አይደለም» አለው ፣ በቦነነው የሲጃራ ጢስ ውስጥ እያየው ። ረጂም ፣ ጠይም ፣ አጥንታም ፊቱ ሁልጊዜ በሲጃራ ጢስ ጉም ውስጥ ነው ።

«ሌላ ምን ይፈለጋል ?»
«ብዙ ነገር አለ ።»
«እንደምን ያለ ?»

«አንተ አሁን ማስረጃ ነው ብለህ ያቀረብከው ወረቀት ፣ አንዳንድ ስህተት መድረሱን ነው እንጂ ወንጀል ወይም አድልዎ የተፈፀመ መሆኑን

አያመለክትም ። ይሁንና ክስ የቀረበብህ ስም በማጥፋት ሳይሆን ደቅርታ የሌለው ፖለቲካዊ ውዝግብ በትምህርት ቤቱ በመፍጠርህ ነው ። የምስክር ቃላቸውን የሰጡ አንዳንድ አስተማሪዎች ይህንኑ አረጋግጠውብሃል ። በተጨማሪም በአካባቢው የተገኘው መረጃ ይህንኑ የፖለቲካ ዝንባሌህን ያስረዳል» አለው ።

«ለምሳሌ ?» አለው ቅንድቡን ከፍ አድርጎ ።
«ለምሳሌ ላንዳንድ የመንደር ነገረተኞች የምትፅፈው ማመልከቻ ።»
«እና ?»

«እና ፣ የሰው ማንነቱ የሚታወቀው በሚያስፍራቸው ቃላት ነው ። በእብሪት የታጠረ ነው ። የወረዳ ገዥው አቶ ጥላሁን ሸዋረጋ ይህንኑ እንዳጣራ ጠይቀውኛል ።»

«ፍሬ ነገሮችን ብቻ ማስፈር እብሪት ነው ከተባለ ምናለ ? ጥሩ ነው ። ነገር እንደ ተረጎሙት ነው ። ግን ፣ እውነት ተሸፍና አትቀርም ።»

ሲጃራውን ፀንጼት ከስተረና ፣ «ለማንኛውም ነገር ንፅህናህን የሚያስረዳ ነገር አልነገርከኝም ። እንዳልኩህ የተከሰስከው በቀላል ነገር አይደለም» አለው ።

«ለመሆኑ ማን ነው ከሳሼ ?»

«ማን ብልህ ትወዳለህ ? የከሰሱህ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎች ናቸው . . . »

«እሺ አሁን ታዲያ ምን ላድርግ ?»
«ዋስ ጥራና ሂድ ።»
«የምን ዋስ ?»
«ስትፈለግ የሚያቀርብህ ።»
«ዋስ ከየት አመጣለሁ ። ሳገሩ እንግዳ ነኝ ።»

«ታዲያ ምናለ ። ጥሩ ማረፊያ ቤት አለን» አለውና ፣ የዛጉትን ጥርሶቹን አሳየው ።

ሀዲስ ብልጭ አለበትና ፣ «ስማ ወንድም ! ማንም በተንኮል ተነሳስቶ በውሸት ስለ ከሰሰኝ መታሰርም ሆነ ዋስ መጥራት የለብኝም ። የራሴ ቀርቶ የማንንም መብት ያለ ምክንያት ሲደፈር ማየት አልወድም ። ምትን እመርጣለሁ ። እና ፣ አሁንም ብትፈልግ ግደለኝ እንጂ እዚህ ቆይቼ አይቀለደብኝም !» ብሎት ቆርጦ ሊወጣ ሲነሳ ፣ አቶ ጣሴ ደጉና ታፈሰ ብሩ ተያይዘው ገቡ ።

ታፈሰና ሀዲስ የጋለ ሰላምታ ተለዋወጡ ። ቀጥሎ ፣ ታፈሰ ራሱን ከመቶ አለቃ አሸኔ ጋር አስተዋወቀ ።

«የፊታውራሪ ወንድም ልጅ ኖት ?»

«አንተ በለኝ» ብሎት ፣ ወደ ሀዲስ ዞር አለና ፣ «ገና እዚህ ከመድረሴ የምሰማው ነገር ምንድን ነው ?» ብሎ ጠየቀው ።

«ምኑም አልገባኝም ። ፖለቲካዊ ወንጀል ፈፅመሃል ይሉኛል ። መላ ቅጡ የጠፋ ነገር ነው» አለው ።

ታፈሰ ወደ ፖሊሱ መለስ ብሎ ፣ «የምን ፖለቲካዊ ወንጀል ነው ?« አለው ።

«አሁን ግድ የለም ። ዋስ ጠርቶ ሊሄድ ይችላል» አለ ።
«እኔ ዋስ እሆነዋለሁ» አሉ አቶ ጣሴ ።

«እርስዎ ደግሞ ምን አገባዎትና ! ከእሱ ጋር ከሚዶልቱት ሰዎች ውስጥ አንዱ እርስዎ ኖት ይባላል ። ለምን አርፈው አይቀመጡም!» አላቸው እየገላመጣቸው ።

«ምን ነው አያገባኝ ! ያገባኛል እንጂ ። ሰው በጎ ሲያስብ ተከታትሎ ማጥፋት ደግ አይደለም ። ሲሆን ማበረታታት ያስፈልግ ነበር ። እኔም በጊዜዬ ተባባሪ ባገኝ ኖሮ ይህ ትምህርት ቤት እስካሁን በጥሩ ሁኔታ በተሰራ ነበር ። ቢያቅተኝ ደሞ ለመተባበር ልስነፍ ?» አሉት ፤ ሳል እፍን እያደረጋቸው ።

«በማያውቁት ነገር ገብተው አሁን ባይናገሩ ምናለበት !»

«ነገሩን አሳምሬ አውቀዋለሁ ። ተንኮል ነው ። ሌላ አይደለም ። አንስራ ወይም አናስራ ፤ ተንኮል ብቻ ። አንተስ ብትሆን ነገሩን መቼ አጣ ኸው ?»

«የተንኮል ተባባሪ ነህ ሊሉኝ ይሆን ?»
«ምን ቆርጦኝ ። ቤታችንን ታውቀዋለህ ማለቴ ነው እንጂ . . .»
«ጡረታዎን በጤና ቢጠባበቁ ምናለበት !»

«የመምህር ጡረተኛ የለውም ። ሳስተምር ክፍል ውስጥ ነው የምሞ ተው ። ስለ ዋስትናው ልፈርምና እንሂድበት» አሉት ።

«ግድ የለም ። እኔ ዋስ እሆነዋለሁ» አለ ታፈሰ ።
«ጌታዬ አንተ ዋስ ከሆንከው በደስታ» አለ የመቶ አለቃ ።

ከአስር ደቂቃ በሁዋላ ሶስቱም ተያይዘው ከመቶ አለቃ አሸኔ ቢሮ ወጡ ።

ከፖሊስ ጣቢያው ቅጥር ግቢ እንደ ወጡ ፣ «ተንኮል ነው እኮ» አቶ ጣሴ ፣ «ለማስፈራራት የተደረገ ተንኮል ነው ። የሚያሳዝነው ደግሞ አሸኔ የይርጋ መሳሪያ መሆኑ ነው ።»

«የተሳሰረ የጥቅም ግንኙነት እንዳላቸው ?» አለ ታፈሰ ።

«አብረው ቡና ሲነግዱ ፣ ሲጠጡና ሲበሉ ነው የሚውሉት ። የወረዳ ገዥውም ቢሆን የእነሱ ግብረ አበር ነው ። ባያውቀው ነው እንጂ ይርጋ ለእሱም አይተኛ ። ተንኮል ብቻ ! አብሮ ከመብላት ፣ ከመጠጣትና ሰው ከማማት ሌላ አብሮ መስራትን ፣ ላንድ አላማ መሰለፍን አያውቅም ። ከነፈሰው ጋር አብሮ መንፈስ ። ከበሮ መደለቅ ። ሽርጉድ ሲል ምሳሩን ማብዛት ። ተንኮታኩቶ እስኪወድቅ ድረስ እየተከታተሉ መጥለፍ ፣ ግብ

አቶ መሬቱን ማጣደፍና ቃሬዛውን ባስር ሳንቲም ምስማር ቸንክሮ በውሸት ሀዘን ከንፈር መምጠጥ ። ያሳዝናል ስነ ልቦናችን ። ጠባያችን ሁሉ እንደ ስነ ግጥማችን ሰምና ወርቅ ነው» አሉ ። ቀጠሉና በችግር እየተነፈሱ፣ «አሁንም ቢሆን ይርጋ አይተኛልህም ። ካሁኑ መምህራኑን በተንኮል መከፋፈል ጀምሮአል ። ያው የተለመደ ዘዴውን በመጠቀም ላይ ነው» አሉ ።

«አንተ ግን በምንም ነገር አትደናገጥ ተስፋም አትቁረጥ ። እንደም ገምተው ከሆነ ፣ የዚህ ትምህርት ቤት ተስፋ አንተ ነህ ። ግድ የለም ፣ እኔም እሰሁልሀ ። ሌሎችም አሉ ። እኔን የሚቆጨኝ ነገር ቢኖር እንዳንተ አፍላ ጉልበት በነበረኝ ጊዜ ተስፋ መቁረጤ ነው ። አንተንም ሁዋላ እንዳይቆጭህ» አሉ አቶ ጣሴ ። ቀጥለውም ፣ «በሉ እናንተ ተጫወቱ ። እኔም ወደ ቤቴ ልግባ» ብለው ሄዱ ።

ከአድማስ ስር ያቆለቆለችው ፀሀይ እንደ ባህር ቀዝቅዞና ጠለቅ ብሎ ከተንጣለለው ሰማይ ላይ የቀለጠ ወርቅ የምታፈስ ትመስላለች ። የወፍ መንጋዎች ለመስፈር ወደ ገባ በረሃ ይበራሉ ። የነፃነት ፀአዳ ሸማ ፣ ሰላም ላንቺ ትሁን እለና በልቡ ፣ ወደ ላይ አሻቅቦ ወፎቹን በአይኑ ሳንዳፍታ ተከተላቸው ። አንድ ደቂቃ የጨለማ ተስፋ ቢስ ህይወት ። በሌላ ደቂቃ ልብ ሙሉ የፈካ ተስፋ ። ህይወት ክንፍዋን ዘርግታ ትበራለች ።

«ጊዜ እኮ ቆሞ ማንንም አትጠብቅም ። ምን እናድርግ ታዲያ ?» አለው ታፈሰ ።

ጠብመንጃ ያነገቱ ሁለት ሰዎች በብር መረሻት የተንቆጠቆጠች በቅሎ ይዘው ይጠብቁት ነበር ።

«የገቢ እልሃለሁ» አለው ቀዝቃዛ አየር እየተነፈሰ ።

«የት እንሂድ ታዲያ ?» ብሎት ካንዱ አጃቢ ሽጉጥ ወስዶ ከጎኑ ሻጠና አሽከሮቹን ሸኛቸው ።

«ዝናሽ ቡና ቤት — የሱጴ ሂልተን ። ሌላ የት ይኬዳል ? ሱጴ አዲሳባ መሰለችህ ? ሱጴ መሸት ካለ ወይ መኝታ ወይም ወደ ዝናሽ ቤት» አለው ።

«አዲሳባ ያለሁ እየመሰለኝ ነው ። ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ በቀላሉ ይለቃል ብለህ ነው ?» ብሎ መለሰለት ።

ታፈሰ ቢራመድ ይፈጥናል ። ረጋ ብሎ መሄድ ፣ ረጋ ብሎ መናገር አይሆንለትም ። አሳቡም ይፈጥናል ። ከምላሱ የሚቀድሙትን አሳቦች ለመግለፅ እንዳንዴ ይቸገራል ።

«ትምህርት ቤታችሁ አንተን ፍለጋ ሄጄ ነበር ። ትናንት ከመሸ በሁዋላ ነው የመጣሁት ። መንገድ ላይ ሁሉ ሳስብህ ነበር ። ትምህርት ቤታችሁ አቶ ይርጋ ቢሮ ገብቼ ስጠይቅ ፣ ‘ፖሊሶች አሁን መጥተው ወሰዱት’ አሉኝ ። ‘በምን ምክንያት ይሆን ?’ ብላቸው ፣ መጀመሪያ መልስ ሊሰጡኝ አልፈለጉም ። አጥብቄ ስጎተጉታቸው ጊዜ ፣ ‘ምን ይታወቃል ? የዘመኑ ልጆች እጃቸውን የሚያስገቡበት ቀዳዳ አይታወቅም’ አሉኝ ። ‘አይ እንግዲያውስ ፖሊስ ጣቢያ ሄጄ ልጠይቅ’ ብዬ ስነሳ ፣ ‘የተፈለገበትን ምክንያት

ሳታውቅ ለምን ትሄዳለህ ? ሳይቸግር ጤፍ ብድር ! በከባድ ፖለቲካ ወንጀል ተፈልጎ እንደሆንስ ? ዶሮ መሞትዋ ሳይቀር ስትንደፋደፍ ሰው ትበክላለች አሉ ። እርፈህ ተቀመጥ ወንድሜ ። በገዛ እጅህ መዘዝ አታምጣ' እያሉ ያከላክሉኝ ጀመር . . . 'ጭፍራም ሲያዝ እንዴት ዝም ይላሉ ? ባይሆን የተያዘበትን ምክንያት አውቆ ዝም ማለት ያባት ነው' ብላቸው ፣ 'ምናገባኝ ወንድሜ ። እሱም እርፎ የሚቀመጥ ሰው አይምሰልህ ። ተንኮለኛ ነው ። የቄስ ልጅ አይደል ? አንተም የሚያገባህ ጉዳይ የለም ። እርፈህ ተቀመጥ ። አሳ ጎርጉዋሪ ዘንዶ ያወጣል ይባላል ። የተፈለገበት ጉዳይ ከባድ ቢሆን ነው እንጂ ሰው በግ አይደል ዝም ብሎ ወደ ፖሊስ ጣቢያ የሚጎተት' ሲሉኝ ካነጋገራቸው ነገር ሸተተኝና ስመጣ መንገድ ላይ አቶ ጣሴን አገኘሁ ። አቶ ጣሴ በጣም ይወዱሃል ። ሳየው ፣ የወጣትን ቱን ዘመን ያስታውሰኛል አሉኝ ። እድለኛ ነህ ። ዝነኛም ሆነሃል» አለው ።

«እንዴት ?»

«ስምህን የማያውቅ የለም ። አሽከሮቼ ቅድም ስላንተ ያጫውቱኝ ነበር . . . »

ሀዲስ ከታፈሰ ጋር እኩል ለመራመድ እየተቸገረ ፣ «ምን ብለው ?» ሲል ጠየቀው ።

«ሊቱቸገረ ሰው ሁሉ ማመልከቻ ስትፅፍ ነው አሉ የምትውለው ። ተማሪዎችህም አውን ገና ጥሩ አስተማሪ አገኘን እያሉ ያወራሉ አሉ ። ማን እያሉ ነው የሚጠሩህ አሉ ? . . . አዎን 'ጋሼ ተአምር እያልቅ' ። ሲያና ድዱህም፣ ጥያቄ ሲጠይቁህም 'ተአምርእያልቅ' ትላለህ አሉ ። ወላጆችም ባንተ መያዝ ማጉረምረም ጀምረዋል አሉኝ . . . »

ሀዲስ ቁና ቁና እየተነፈሰ ፣ «ለምን ?» አለው ።
ታፈሰ እንደ መበሳጨት እያረገው ፣ «ጥያቄ ታበዛለህ !» አለ ።
ሀዲስ ፣ «እዝናለሁ» ብሎት ዝም አለ ።

«የድሀ ልጆችን ለመርዳት የተነሳውን ሰው ምን አድርግ ሲሉት ነው ? እያሉ ነው የሚያጉረመርሙት» ብሎት ወደ ፊት እየገሰገሰ ፣ «አንተ ያለብህ የመጀመሪያ ግዴታ ራስክን መርዳት ነው ። የራስህ ጌታ መሆን ። ጌትነት ማለት ያለ አሳብና ያለ ጭንቀት መኖር ማለት ነው ። ያለ አሳብና ያለ ጭንቀት መኖር ደግሞ የሚቻለው ብር ሲኖር ነው ። የራስህ ጌታ ስትሆን ያኔ ሌላውንም ልትረዳ ትችላለህ ። ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ ።

«ያለ ገንዘብ ሰው ሰው አለመሆኑን እይቻለሁ ። በኢትዮጵያ ውስጥ ባሁኑ ጊዜ ሰው ማለት ብር ያለው ነው ። ስልጣንም ቢሆን ያለ ብር ዋጋ የለውም። የህይለ ስላሴ ባለስልጣኖች በብር ሲሸጡና ሲለወጡ ነው የሚውሉት ። ህይወት ያለ ገንዘብ ምን ዋጋ አላት ? እየህ ፣ አለም ብዙ የሚያጉዋጉ ቆንጆ ቆንጆ ፣ ውብ ነገሮች ፊትህ ላይ ስታስደንስ ትውላለች ። ታዲያ ያለ ገንዘብ አይገኙም ። ያለ ገንዘብ የህይወት ውብ ነገሮች አይገኙም ። ጉሩም ሻሂ ፣ ያለው ይጠጣል ፣ የሌለው ያፈጣል እንደ ሚባለው ነው ። ያለ ገንዘብ ከጥሩ የህይወት ምንጭ ፣ ከህይወት ሻሂ ፉት ማለት አይቻልም» እያለ ብር ፣ ብር ፣ ብር ፣ ሲል ከዝናሽ ቤት ደርሰው ሲገቡ የሚጨሰው እጣን ቡልቅ ቡልቅ እያለ ተቀበላቸው ።

ዝናሽ ከቡና ሲኒዋ ላይ ቀና ብላ የወርቅ ጥርስዋን ብልጭ አደረገች ።

«ቀሃ ጀባ ፡ አቦል ጀባ ፡ የሱጺዋ አድባር ትቀበለን አቦ» ብሎ ከዝናሽ ጎን ሄዶ ሻጥ አለ ታፈሰ ።

«ውይ በሞትኩት ! በስማብ እቴ» ብላ አማተበች ።

«ምን ታየሽ ? ዲያብሎስ ? ወይስ መላኩ ገብርኤል ?» አላት እየሳቀ ፤ ነጭ ጥርሱ በጠፍ ጨረቃ ካፎቱ የተመዘዘ ስለት ይመስል ያንፀባርቃል ።

ዝናሽ አይን አይኑን እያየች ፡ «ቁርጥ እኮ ነው» አለች ።

«ቁርጥ ማንን ? ዝኑ ዝናሽ ። ካዲሳባ ድረስ ዝናሽን ስምተን መጣን ። ውስኪ ጀባ» አላትና ፡ ሲጃራ አቀጣጥሎ የጢስ ቀለበት እያከታተለ ይለቅ ጀመር ።

ታፈሰ እያከታተለ የሚለቀው የጢስ ቀለበት እየሰፋ ሄዶ በንኖ እስኪጠፋ ድረስ በአይኖችዋ እየተከተለችው ፡ «ቁርጥ ልኡልዬን ። የውቤ በረሃ ልኡል የምንለው ልጅ ነበር ። እንዳንተ ቀይ ፡ ፀጉረ ሉጫ ፡ መልከ ቀና ልጅ ነበር ። አይ ጨዋታ ! አይ ዳንስ ። ታንጎውን ሆነ ቫልሱን ፡ ሩምባውን ሆነ ማምቦውን ፡ ቻቻውን ሆነ ሜሬንጌውን ፡ ኮንጋውን ሆነ ሳምባውን ፡ ቡጊ ውጊውን ሆነ ሮኩን ሲረገረገው ፤ አይ እናቴ ! እንዲያው ከሙዚቃውና ከምቱ ጋር አብሮ የተፈጠረ ይመስል ነበር ። ዋ እና ቴዋ ! በተለይ ዳንስ ፡ በሴሪና ዳንስ የምትል ሙዚቃ በጣም ይወድ ነበር ። በዚያ ነጭ ልብሱ በቀይ መብራት እንደ እንዝርት ሲሾር ፡ ሲሽከረከር ልብን እያንሳፈፈ ይዞ ጭልጥ ይል ነበር . . . » ስትል—

«ወዴት ?» አላት ።

«ወደ ፍቅር አለም ነዋ ። ወደ ሴሲት ውበት» ብላ እንዲ አስከካችና ፡ «ከልኡልዬ ጋር ደንሶ ከሴላ ጋር መደነስ ኧረ ኤዲያ ! እንደ መራገጥ ነበር ። በዚያ ዳንሱ የሰው ልብ ይዞ ጭልጥ እያለ ‹እምቢ ብትይኝ አላሳዝንሽም ? በፍቅርሽ ጥም አርሬ ለምን ልሙትብሽ በዚህ በረሃ ? እፀ በለስ ነሽ ። ልቅመስሽና ልኩነን በቃ›ሲል የውቤ ልጆች ልብ ፀሀይ እንደ ነካው ቅቤ ቅልጥ» አለች ፡ ከፊትዋ ቆሞ የምታየው ይመስል ባዶው አየር ላይ አፍጥጣ ።

«አንቺስ ?» አላት ።
«በእቅፉ ውስጥ ሙትት ። ሰርሳሪ ሌባ ነበር ።»
«የምን ሌባ ?» አላት ።
«የሴት ልብ ሌባ ነዋ» አለችው ።

«ታዲያ እኔ ሌባ እመስላለሁ ?» ብሎ ታፈሰ በክንዱ ያረጀ ጎንዋን ወጋ አደረጋት ።

አንድ አይነት ስሜት ሳይቀሰቀስባት አልቀረም ። እንደ ገና አስካካችና ወፍራም ሰውነትዋን በቀላሉ ተሸከማ ተነስታ ፡—

ምሽቱ ሲጀነን ያገር ልጅ ጅንኑ ተጀንነህ ናልኝ
በፍቅርህ ካልቀደስኩ ሌቱም አይነጋልኝ
ጅንኑ ያገር ልጅ ናልኝ አይናማው ጅንኔ በዝና

ጆንኑ ካራዳ ፣ ጆንን ካራት ኪሎ ፣ ጆንን ከጉለሌ ፣ ጆንን ከቀበና
ጆንኔ በምሽት ተጀንነህ ናልኝ
በፍቅርህ ካልቀረብኩ ሌቱም አይነጋልኝ

ጆንኑ ያገር ልጅ ፍቅር ይቀሰሳል ከጊዮርጊስ በላይ
ጆንን ሲል ሌቱ በጨረቃ ብርሃን ከውድቅቱ ላይ
ጆንን ተጀንነህ ና እንቁረብ በፍቅር
ውቤ በረሃ ላይ በጊዮርጊስ ጥላ ስር
ጆንኑ ያገር ልጅ ልደታም ባትደርስ ተጀንነህ ናልኝ
ካንተ ጋር ካልቀረብኩ ሌቱም አይነጋልኝ ።

በትዝታ ቅኝት እየተወዛወዘች ከዘፈነች በሁዋላ ፣ «ሆይ ሆይ ቻቻቻ ፣ የኛ መደሰቻ» ብላ ዳንሱን ጭምር ስትለው ታፈሰ ተነስቶ . . . ቻቻ . . . ቻቻቻቻ እያሉ አብረው ዳንሱን ያቀልጡት ጀመር . . . ቻ . . . ቻ . . . ቻቻ . . . ቻቻ . . . ቻቻ . . .

ሁዳንሱ በሁዋላ ፣ «እንደ ሰራ አይገድል» አለች እንባዋ ግጥም ብሎ ።

«ለመሆኑ ከውቤ በረሃ ሱጴ ድረስ ምን አመጣሽ ?» አላት ታፈሰ ።

«ከውቤ በረሃ የወጣሁበት ታሪኩ ብዙ ነው ። ሱጴ ግን አንድ የታመመ ዘመድ ለመጠየቅ መጣሁ ። የታመመውም አልዳነ—እኔም እዚሁ ቀረሁ እልሃለሁ ።»

«ጨካኝ አይደለ ?» አላት ።
«ማን ?» ስትለው ፣—

«እግዜሩ ነዋ ። እንደ ሰራ የማይገድለው ፣ ወጣትነትንና ሀብትን ሰጥቶ የሚነሳው» ብሎ እየሳቀ መለሰላት ።

በውቤ በረሃ ከአራዳው ጊዮርጊስ ጥላ ስር እንደ ጥላ ኮብልሎ ያለፈውን የጆንኖችን ዘመን በታፈሰ ላይ እያየች ተቁዋጥሮ የቆየው እንባዋ ኮለል ብሎ ወረደ ። እንደ ታፈሰ አንጀቱ እጥፍ ያለ ጆንን ወጣት ባየች ቁጥር የጥንቱ ትዝ እያላት ሳይሆን አይቀርም እዝን ትላለች ። «በሀይወት መንገድ ላይ ተላለፍናት» ያለችው ትዝ አለው—ሀዲስ ። የሀይወት ዋንጫ ሙሉ ትዝታ ። ግን ለምን በሀይወት እናዝናለን ? እስካሉ ድረስ በሀይወት መኖሩ ራሱ ይበቃ የለም ? አለ ።

ዝናሽ እንባዋን በነጠላዋ ጫፍ አድርቃ ለሀዲስ ቢራ ለታፈሰ ውስኪ ቀድታ ሰጠቻቸውና ፣ ሀዲስን ፣ «ሽታዬ አንተን ፍለጋ እንደ ሄደች አልተመለሰችም» ብላ በጆሮው ሹክ አለች ፦

«ለምን ?» አላት ።

«ምናውቃለሁ ልጄ ። ድንጋይ እንደ ወረወሩባት ወፍ ድንገት ብር ብላ ነው የወጣችው» ስትለው ታፈሰ የተቀዳለትን ውስኪ ሳይቀምስለት ወደ ውጭ እረጨው ።

«ውይ በሞትኩት ! ምናገኘህበት ?» አለችው ዝናሽ ደንግጣ ።

«ላድባርዋ ነው» ብሎ ሌላ እንዲቀዳለት እጁን ዘረጋ ። ድጋሚ ቀዳ

ችለት ። እስዋንም ጋበዛት ። ለራስዋም ቀዳች ። ሀዲስ የተደፋው ውስኪ እያስቆጨው ሀብታም ነኝ ለማለት ነው ? ጉረኛ ! አለ በልቡ ።

«ለውቤ በረሃ ጅንኖች ዘመን» ብሎ መለኪያውን አነሳ ።
«ያራዳው ጊዮርጊስ ቁጣ በታትኖን ቀረ ልጄ» አለችና ቁና ተነፈሰች።

«አንዱን ጅንን እንኩዋን ሳታስቀሪ እንዲያው ያሳዝናል» አላት አይኑን ከተንጠለጠለው ቦርጩዋ ላይ ተክሎ ።

«ክቡራ ክቡራ የንጉሱ አሽከር ባለ ጎፈሩ» ብላ ዝም አለች ። ከአገጭዋ ስር የተንጠለጠለው ስጋ ሁለተኛ አገጭ ያላት ያስመስላታል ።

አንድ የክብር ዘበኛ ሻምበል ወዳጅ ነበራት ። ስለ እሱ ሀዲስን አጫውታዋለች ። ትዝ ሲላት ስለ ሻምበል አበበ ማውራት ትወዳለች ። ደጃች ውቤ ሰፈር ቆንጆ ሴት መጣች ወይም ቤት ከፈተች ከተባለ ይሞታታል እንጂ የግድ እስዋን ማግኘት ነበረበት ። የታወቀ ጠባኛ ስለነበረ በጊዜ መጥቶ በር ያዘጋል ። ጡንቸኛ አልነበረም ። እንዲ‸ው ሰውነቱ እንደ ጅማት የከረረ ሰው ነበር ። ታዲያ ሴትዮዋን በጣም ወደ‸ . ቢባል ከሳምንት በላይ ከቤትዎ አይቆይም ። ደግሞ ሌላ ቤት ሄዶ በር ያዘጋል ። ሳንድ ሳምንት ይሞሽራታል ። ሴትዮዋ ከሻምበል አበበ ጫጉላ ቤት ጉብታለች ይባላል ። የዝናሽ ስም በውቤ በረሃ ተጋኖ መወራት እንደ ጀመረ ሄዶ በርዋን አዘጋት። ሳምንት መጣ፥ ሄደ። ወር ተተካ።ወራት አለፉ። ከዝናሽ ቤት ተኝቶ፥ «ያቀመሺኝ ቅጠል ምንድን ነው ማርከሻው ? ሌላ ሰው አስጠላኝ እስከ መጨረሻው» እያለ ይዘፍን ጀመር ይባላል ። የኮርያ ጦርነት ሲያያቸው ። እሱም አልተመለሰ ፥ እስዋም አልሆነላት ። በርዋ መከፈት ሲጀምር በውቤ በረሃ አዳዲስ የምሽት ልእልቶች ተፈጥረው ቆዩዋት ። እንዳንዶቹ የዱሮ አሻሻጮችዋ ነበሩ ። በደጅዋ እያለፈ የሚሄድ እንጂ ጎራ የሚል ጅንን አል ነበረም ። ከደጃች ውቤ ሰፈር ስትርቅ ስትርቅ ይሽውና ሱዱ ደርሳለች ። ከሱዱ በሁዋላስ ? የትም የምትሄድ አትመስልም ። ከህይወት ጋር የምትሽረት ትግል የምታደርግበት የመጨረሻ ምሽግ ! ተጉዘው ተጉዘው ከዝግ መንገድ ላይ ሲደርሱ ወዴት ይኬዳል ? በትዝታ ጎዳና ወደ ሁዋላ . . . ወደ ሁዋላ . . . አፈር እስኪነክሱ ድረስ . . .

«ምን ነው ዝም አልክ ? ዝምታ ታብዛለህ ። የዝምተኞች ቦታ ቤተ ስኪያን ጉዋሮ ነው» አለው ታፈስ ነጭ ጥርሱን ካፎቱ እየመዘዘ ።

ሲሄድ ይፈጥናል ። ሲናገር ይፈጥናል ። ሲያስብ ይፈጥናል ። ስስ ከንፈሮቹን አሹሎ የሲጃራ ጢስ ቀለበት አከታትሎ ከለቀቀ በሁዋላ አንዱ የጢስ ቀለበት በሌላው ውስጥ ገብቶ ሲጠፋ እያየ ፥ «ህይወት ጤዛ ናት ። ሳትረግፍ በፊት መደሰት ነው ። የዘለአለም ዝምታ ሲመጣ ይመጣል ። ድምፃችንን ስንሰማ ነው እኮ መኖራችንን የምናውቀው» አለው ።

«ውስኪ እየረጩ መደሰትና መምህ ነዋ !» አለው ሀዲስ በቀልድ ።

«አዎን፥ ውስኪ መርጨት የሚያስደስተኝ ከሆነ ለምን አልረጨውም?» ብሎ የውስኪ መለኪያዋን እያሽከረከረ ተመቻችቶ ተቀመጠና ፥ «ግን ውስኪ ለመርጨት ገንዘብ እንዲኖርህ ያስፈልጋል ። ገንዘብ ደግሞ ደስ በሚለን ነገር ላይ ካላጠፋነው የገንዘብ ጥቅሙ ፥ የህይወት ጣእሙ ምን ላይ ነው ? በዚህ አለም ላይ የምንኖረው አንድ ጊዜ ብቻ ነው ። ሁለ

ተኛ እድል የለንም ። ገንዘብ ኖሮን ደስ የሚለንን ነገር ካላደረግን ደግሞ ኖሮን ማለት መራራ ቀልድ ነው» ካለ በሁዋላ ሲያስብ ቆየና ፥ «ያለ ገንዘብ ደስታ አለ ቢሉህ አትመን ። የዋሾዎች ወይም የደካሞች ወሬ ነው ። ያለ ገንዘብ የሚገኝ ነገር የለም ። ሰው በመሰረቱ አላቂ እቃ ላይ የሚያተኩር እንስሳ መሆኑን አትርሳ ። የተራቡ ሰዎች ስለ እግዜርና ስለ አስርቱ ቃላት ቁጭ ብለው የሚያስቡና የሚፈላሰፉ አይመስልህ ። የተራበ ወስፋት ለዚህ ጊዜ የለውማ ። የሚያስቡት ወስፋታቸውን እንዴት ሊያስታግሱት እንደሚችሉ ነው ። ግን ስላሰቡት ብቻ ምግብ አይገኝም ። ይገኛል ወይ ? ሙሴ የለማ ጣፋጭ መና ከሰማይ የሚያወርድ ። ዛሬ ገንዘብ ነው እግዜር ። ሀይል ነዋ ። ገንዘብ ሀይል ነው ። በሞትና በሽረት መካከል ያለውን ጥያቄ የሚወስነው ገንዘብ ነው ። ገንዘብ ካለህ በምድር ላይ የማትገባበት ገነት የለም» አለው ።

ሀዲስ ፥ «ለጥቁር ወርቅ» ብሎት የቢራ ጠርሙሱን አነሳ ።

እሱም ፥ «ለጥቁር ወርቅ» አለና ውስኪውን ባንድ ትንፋሽ ጨልጦ ሌላ ሲጃራ አቀጣጠለ ።

ሀዲስ ታፈሰ ከአፉ ቡልቅ ቡልቅ እያደረገ በማከታተል የሚለቃቸውን የጢስ ቀለበቶች በአይኑ እየሸኘ ፥ «ጨክነህ የምትመጣ አልመሰለኝም ነበር» ሲለው ፦—

«ለምን ?» ብሎ ጠየቀው ።

«አለ አይደለም ? አንድ ነገር አደርጋለሁ ብለው ብዙ ሲናገሩ ሳያደ ርጉት ይችላሉ ። ያኔ ሳይህ የምትናገረው ራስክን ለማሳመን ያህል እንጂ በእውነት እምነት አድሮብህ የምትናገር አልመሰልከኝም ነበር» ብሎ መለ ሰለት ።

ታፈሰ ከተቀዳለት ውስኪ ላይ ፉት አለና ፥ «ልክ ነህ ። ለመቁረጥ ተቸግሬ ነበር ። ጨክኖ ከሀይለ ስላሴ ቢሮክራሲ መውጣት ለቆየበት ያስ ቸግራል ።»

«ለምን ?»

«ስላልነበርክበት ምናልባት የምልህ ነገር ላይገባህ ይችላል» ብሎ ንግግሩን በመቀጠል ፥ «አየህ ፥ በሀይለ ስላሴ ቢሮክራሲ ውስጥ ነፃነት ተነፍ ገህ ትኖራለህ ። ሁሉንም እሺ ጌታዬ ትላለህ ። በጭፍን ስልጣን ታምና ለህ ። ለጭፍን ስልጣን ትንበረከካለህ ። ከጭፍን ቢሮክራሲያዊ መመሪያዎ ችና ልምዶች ሌላ እውቀት አይኖርህም ። ከጭፍን የአሰራር ዘዴ ዝንፍ ማለት አይቻልማ ። በመጨረሻ በራስህ ላይ እምነት ታጣለህ ። ያኔ ኤክ ስፐርት ትባላለህ ። የራስህ አስተሳሰብ የሌለህ እቃ ሆነሃላ» ካለ በሁዋላ ፥ አሳቡ ከምላሱ ስለሚፈጥን ሁለቱን ለማስተባበር ያህል ንግግሩን ቆም አድርጎ አቀማመጡንም አመቻችና ፥ «ሲቃ ስልህ ውሸት ፥ ሰብቅ ፥ ቅጥ ፈትና አሉባልታ የተካነ እቃ ማለቴ ነው ። ሀሊና የሚባል ነገር የለም ። ቢኖርም የዋዋሆች ልቅሶ ነው ይባላል ። ብልጦቹ ከፍ ያለ ዋጋ ለሚከፍል ለማንኛውም ባለስልጣን ይሸጡታል ። እንዱ በሌላው ይቀናል ፥ ይመቀ ኛል ፥ እና ፥ በሰብቅ ፥ በውሸትና በአሉባልታ ሊያጠፋው ይነሳል ። በዚህ አደገኛ ጨዋታ ውስጥ ከላይ ለመድረስ የሚችሉት ጠንካሮች ወይም ጠን

ካራ ዶጆን ወይም ወገን ያላቸው ብቻ ናቸው ። የዳርዊን ቴዎሪ በተግባር ሲውል ማየት የሚፈልግ ሰው ካለ የሀይለ ስላሴን ቢሮክራሲ መመልከት ይበቃዋል» ብሎ እንደገና ቆም ከማለቱም ሌላ ፣ አቀማመጡንም በመለ ወጥ ንግግሩን ቀጠለና ፣ «ቤት ማቃጠርም አለ ። ብልጥ ብልጡ እየቀመሰ ወደ ላይ ያሳልፋል ። በእቁባቶች ቤት እየተሰበሰቡ ማታ ማታ አብሮ ካርታ መደብደብ ፣ ክራር እየመቱ ወይም እያስመቱ ጉብልዩን መዝፈን ፣ ውስኪ መጨለጥና ጮማ መቁረጥ መሾም ለሚፈልግ ሰው ሁሉ ግዴታው ነው ።

«ሁሉም መሾም ይፈልጋል ። አበሻ ሹመት ይወድ የለ? ሁሉም ለሹ መት ይሞታል ። ሹመት የሚታየው ከሚያስከትለው ሀላፊነት አንፃር ሳይሆን በሚያመጣው ክብርና ገንዘብ አኩዋያ ነው ። ሹመትህ ከፍ ሲል ነዋ መኪና ፣ ቪላና መሬት የሚመጣው ። ጠዋት ጠዋት ግቢ እጅ እየነሱ ያዩትን ቪላ ፣ የከተማና የገጠር መሬት መለመን ነው በቃ ። ስልጣን ካለ በሰማይ መንገድ አለ ። ሊቅነትም የሚመጣው ከስልጣን ጋር ነው ። በስ ልጣን ሊቅነት ይህም አለ ለካ ብላችሁ የለ ? 'ጠይቁ ታገኛላችሁ' ብሎ የለ መፅሀፉ ። ለእግዜር ምን ይሳነዋል ? እጅ ካልነሱና ካልለመኑም እኮ ችግር ነው ። ጌቶቹ ፣ 'ይህ መናጢ የድሀ ልጅ ኮርቶ ነው እጅ የማይነሳንና ችግሩን የማይገልፅልን ? ምን አግኝቶ ነው እንዲህ የጠገበው ? እኛ አይደ ለንም ከትቢያ ያነሳነው ?' ካሉ መልሰው ትቢያ ያደርጉታል ። ነገሩ እኮ እግዜር ይሰጣል ፤ እግዜር ይነሳል ነው ።

«ሁሉም ሹመት ስለሚፈልግ ሲለምን ፣ ደጅ ሲጠና ፣ እርስ በእርሱ እንደ ቁራ ውሻ ሲናከስ ነው የሚውለው ። እንደዚህ ያሉትን ሰዎች ደግሞ ከፋፍሎ መግዛት ቀላል ነው ። ሽሚ ምኑ ሞኝ መሰለህ ? ሙዳ ስጋ ፣ ጣፊያ ፣ ልፋጭ ከላይ ሲወረውር — በቃ — እዚያ ላይ እንደ ቁራ ውሻ ጭራ እየቆሉና ክራንቻ እያሳዩ መቦጨጫጨቅ ነው» አለና ፣ መነሻ ነገሩ ስለ ጠፋው ፣ «ምን ለማለት ነበር ይህን ሁሉ ያመጣሁት?» ብሎ ጠየቀው።

«ከሀይለ ስላሴ ቢሮክራሲ መውጣት ያስቸግራል በማለት ነው ።»
«አዎ ፣ አስቸጋሪ ነው ።»

«ገፅታው እንዲህ አስቀያሚ ከሆነ ለምን ያስቸግራል ?» አለው ሀዲስ ፣ የታፈሰን አሳብ መስመር ለመከተል እየተቸገረ ።

«አንገትህ ድረስ ተዘፍቀህበት ከኖርክበት በሁዋላ ጥሎ መውጣቱ ያስቸግራል ። በራስህ ላይ እምነት አጥተሃላ ። የቢሮክራሲያዊ ህይወት ሁለተኛ ተፈጥሮህ ሆኖአላ» ብሎት አሁንም አቀማመጡን አመቻቸና መለኪያውን እጁ ውስጥ እንደ እንዝርት እያሽከረከረ ፣ «የሚያሳዝነው የተማረው ወጣት ሁሉ የመንግስት ስራ ፈላጊ መሆኑ ነው ። ሌላ አይታየ ንም ። ሹመት ነዋ ጭንቅላታችን ውስጥ ያለው ። የተማርነው ለመሾም ለመሸለም ይመስለናል ። በሁለት እግራችን ቆመን የራሳችን ጌታ ለመሆን እንፈልግም ወይም አንችልም ። ዘለአለም ሞግዚት ያስፈልገናል ። በራ ሳችን ላይ እምነት የለንማ ። በዚያ ላይ ካራዳ ህይወት ርቆ መኖር ሞት ይመስለናል ። ወኔ የለንም ። ድፍረት የለንም ። ኮስታራ ወኔና ድፍረት የሌለው ትውልድ ራሱንም ሆነ አገሩን ሊጠቅም አይችልም ። ያውሮፓና ያሚሪካ ስልጣኔና ሀብት የተገነባው በማን መሰለህ ? በተአምር አይደለም ። ወኔ ፣ ድፍረትና አርቆ ማስተዋል ባላቸው ሰዎች ነው» አለው ።

«ለደፋርነትህ ፅዋዑን እንሳለሁ» ብሎ የቢራ ጠርሙሱን አነሳ ።

ታፈስ አፀፋውን አልመለሰለትም ። ከት ብሎ ይስቅ ጀመር ። እንባ እስኪወርደውና ሆዱን እስኪያመው ድረስ ሆዱን ይዞ ሲስቅ ቆየና «ማምቦ !» ብሎ ተነስቶ ማምቦ እየደነሰ ወደ ዝናሽ ሄደ ።

ሀዲስ ታፈስን ያሳቀው ነገር ምን እንደሆነ አልገባውም ። ሊገባውም አልቻለም ። ነገሩ ተምታታበት ።

«ቡም ቡም . . . ቡቡቡምቡም . . . ሁለት ወደ ግራ ሁለት ወደ ቀኝ . . .»

የራስ አለም ፈጥሮ መደሰት ። ደስታ እንዳደረጉት ነው ። ያለፈውን አለም አሁን እንዳለ አድርጎ ማየት ። ማን ነው በእውነታ አለም ውስጥ የሚኖረው ? ያለፈውን ህይወት በማስታወስ ወይም መጭውን ጊዜ በመመኘት አሁን ያለውን እውነታ ለማምለጥ የሚደረግ ከንቱ ሙከራ—እያለ በአይኑ ዳንሰኞቹን ሲከተል ሽታዬ መምጣትዋን አላየም ነበር ። እስዋም በታፈስና በዝናሽ ዳንስ እየሳቀች ፣ «ፖሊሶች ወስዱት ሲሉ ሰምቼ ደንግጬ ነበር» አለችው ።

«ዋስ ጠርቼ መጣሁ ። ዋስ የሚሆን ዘመድ እያሳጣ ማለት ነው» አላት «ለምን ኖርማል ለመሆኑ ?»

«ምንም አይደለም ። አንዳንድ ተንኮለኞች የሚፈጥሩት ችግር ነው ። ም ቀኝነት መሰረታዊ ፍልስፍናችን አይደለም ወይ ? ምንም አይደለም ?» አላት ።

«አንተን ፍለጋ የመጡ ሌሎች መእት ሰዎች ነበሩ» አለችው ።
«እነማን ልጂ ?» አላት ።

«አላታቸውም ። ወሳጆች ሳይሆኑ አይቀሩም ። ተማሪዎችህም በብዛት ነበሩ ። እስከዚህ ድረስ የሰው ፍቅር አፍርተሃል ለካ !» አለችው እየሳቀች ።

የዝናሽ ዳንስ ሳይሆን አይቀርም የሚያስቃት ። ዝናሽ ስትደንስ እንደ በሬ ሻኛ ትገላበጣለች ።

«ያንቺን ልብ በምን የማረኩት መሰለሽ ታዲያ ?» ብሎ ቀለደና ፣ «እነሱ ለኔ ያላቸውን ፍቅር ትንጣት ያህል ፍቅር በልቤ ቢኖረኝ ምንኛ በታደልኩ ነበር ። ግን ፍቅር የለኝም ። ልቤ ባዶ ነው ። ውስጤ ጠጠር ነው . . .» ሲል ታፈስ ተመልሶ መጣ ።

አይኑ ከሽታዬ ላይ አርፎ ነበር ። ሀዲስ አስተዋወቃቸው ።

«ውብ ፀጉር አለሽ ። ቆንጆ ፀጉር ያላቸው ሴቶች ደስ ይሉኛል ። ቆንጆ የሴት ፀጉር ላይ ውስጡ ገብተህ ጥፉ ጥፉ ይለኛል» አላት ።

ሽታዬ እንደ ልጃገረድ ተሽኮረመመችና ወደ ዝናሽ ሄደች ። በአይኑ ተከተላት ። ሽታዬ የሚስብ አካሄድ ነበራት ።

«ውስኪ ጀባ !» አለ ።

ሀዲስ እንደ ልማዱ በጣቶቹ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አደረገና ፥ «ቅድም እንደዚያ ያሳቀህ ነገር አልገባኝም» አለው ።

«ድፍረት የሚባለው ቃል ያስቀኛል» ብሎ እንደ ገና ከት ብሎ ሳቀ ።
«ለምን ?»

«ለምን? ለምን ? ጥያቄ ታበዛለህ ። ድፍረት ብሎ ነገር! ባዶ ቃል ነው ። ማን ነው ድፍረት ያለው ? እርሳው» ብሎት አቀማመጡን አመቻቸና ፥ «ይልቅ ማስተማሩን ትተህ ከኔ ጋር ብትሰራ ምን ይመስልሃል ? ብዙ መሬት አለኝ ። ብዙ ድንግል መሬት ። ለኔና ላንተ ቀርቶ ለብዙ ይበቃል ። አብረን ሚሊዮኔሮች የማንሆንበት ምንም ምክንያት የለም» አለው ።

«እኔን ምን አስመረጠህ ?» አለው ሀዲስ ፥ በነገሩ እየተገረመ ።

«ጠባያችን የሚስማማ ስለ መሰለኝ ነው» ብሎት ሲጃራውን አቦነነና፥ «እኔ እንደምታየኝ ፈጣን ነኝ ። አንተ ደግሞ ረጋ ያልክ ነህ ። በጣም ስፈጥን ልጉዋም ትሆነኛለህ ። አንተ ደግሞ በጣም ስታዘግም እኔ ወደ ፊት እስብ ሃለሁ ። ከዚህ የበለጠ ምክንያት ምን ያስፈልጋል ?» አለና ውስኪውን ጨልጦ ሌላ ሲጃራ አቀጣጠለ ።

ሀዲስ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አድርጎ ፥ «እኔ የራሴ እቅድ አለኝ» አለው።

«ትምህርትህን ለመቀጠል ?» ብሎት አቀማመጡን እንደ ልማዱ ድንገት ለወጠና ፥ «እሱን እርሳው ። የሀይለ ስላሴ ቢሮክራሲ ከአፍ እስከ ገደፉ በተማሩ ሰዎች ጢም ብሎ ሞልቶአል ። መቀመጫ የለም ። ብታገ ኝም በስብሰህ ነው የምትቀረው ። ለሹመትና ለእድገት 'ሀሎ' የሚልልህ ደህና ወገን ያስፈልግሃል ። ቅድም ያልኩት ነገር ነው እኮ ። ከመንስሥት ስራ ሌላ አይታየንም» አለ እንደ መበሳጨት ብሎ ።

«እሱን ማለቴ አይደለም ።»
«ታዲያ ሌላ ምን እቅድ አለህ ?»

«አዲስ ትምህርት ቤት ለመስራት አቅጃለሁ ። እቅዱን የሚ የቀናብር አንድ ኮሚቴም ተቁዋቁሞአል ። አዲስ ትምህርት ቤት ያስፈልጋል ። አሮጌው ሊፈርስ ነው» ሲል ፥ ታፈሰ በሳቅ ፈነዳ ።

«ምን የሚያስቅ ነገር አገኘህ?» ብሎ ጠየቀው ሀዲስ እንደ ልማዱ ረጋ ብሎ ። እርጋታ መቼም የታወቀ ጠባዩ ነበር ። ዝናሽና ሽታዬ እየተሳ ሳቁ ተያይዘው ወጡ ።

«በጣም ነው እንጂ የሚያስቀው» ብሎት ፥ እንደ ገና የኮረኮሩትን ያህል ከት ብሎ ሳቀ ።

«አብረን እንድንስቅ ቀልዱን ለኔም አጫውተኝ» አለው ፥ ኮስተር በማለት ።

ታፈሰ ሳቁን አቆመና በቁም ነገር ፥ «ስማ ሀዲስ ፥ አልነገርኩህም እንጂ የትምህርት ኤክስፐርት ነኝ ። ዲግሪዬን ከኦሀዮ ዩኒቨርሲቲ ያገኘሁት በትምህርት ፍልስፍናና አስተዳደር ነው ።»

«እና ?» አለ ሀዲስ ፣ ግንባሩን አጨማዶ ።

«እና ፣ አንድ ከጭቃ የተሰራ ትምህርት ቤት በመስራት አይደለም ለኢትዮጵያ ችግር መፍትሄ የምታገኘው . . . » ከማለቱ ፤—

ሀዲስ አቋዋረጠውና ፣ «ኢድሜአቸው ለትምህርት የደረሰ ልጆች የከብት ጭራ እየተከተሉ ሲቀሩ ዝም ብሎ በማየት ነው ታዲያ ?» አለው ።

ታፈስ ተቆጥቶ ፣ «ስናገር አታቋዋርጠኝ ። ሲያቋዋርጡኝ አልወድም» ብሎት ተንጫንጩና ፣ «ልብ በል እስቲ ። እየው ፣ መንግስት በሺህ የሚቆጠሩ የጭቃ ትምህርት ቤቶች በየቦታው መስራት የሚያቅተው አይምሰልህ ። ይቻላል ። ግን ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት የኢኮኖሚ ሁኔታ የትምህርት አላማ መሆን ያለበት ትምህርትን የማዳረስ ጉዳይ አይደለም ። ትምህርትን የማዳረስ ጉዳይ በሁለተኛ ደረጃ የሚታሰብበት ነው ። እሱ ቀስ ተብሎ ይደረስበታል» አለና ፣ ሲጃራውን በፍጥነት ስቦ ባፍንጫው ጢሱን እያተነነ ፣ «አሁን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ነገ ያገራቱን ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ህይወት ሊመሩ የሚችሉ ምርጥ ምሁራን በጥንቃቄ ኮትኩቶ ማፍራት ነው ። ይሄ ነው ዋናው ቁም ነገር ። በባእዳን ኤክስፐርቶች ስንመራ መኖር የለብንም ። የትምህርት አሰጣጥ ፕሮግራማችን እዚህ ላይ ማተኮር አለበት ። ባሁኑ ጊዜ ትምህርትን ማዳረስ በሚለው አላማ ላይ ማተኮር ፣ አንደኛ ፣ ትምህርትን በአይነት ዝቅ ማድረግ ይሆናል ። ሁለተኛ ፣ እና ፣ በጣም አደገኛው ደግሞ ፣ እንዱስትሪ ሳይስፋፋ ፣ ፍላጎታቸውን ልታረካላቸው የማትችለውን ብስል ከጥሬ የሆኑ የስራ አጦች ሰራዊት መፈልፈል ይሆናል ። እንዳል ኩት ይህ ዝንባሌ ፣ ፖለቲካዊ አደጋና የማኅበራዊ ኑሮ ቀውስ በገዛ እጅ መጋበዝ ነው ። ቢሮክራሲ የተማረውን ሁሉ ሊውጥ አይችልም» ካለው በሁዋላ ነገሩን በማያያዝ ፣ «ለዚህም ነው መንግስት ሴክተር ሪቪው ወይም የትምህርት አጠቃላይ ጥናት የጀመረው ። ጥናቱ ተጠናቆ ለው ሳኔ ቀርቦአል ። እኔም በጥናቱ ላይ ነበርኩበት ። ግሩም ጥናት ነው ። አሁን ኢትዮጵያ ላገጠማት የትምህርት ችግር መሰረታዊና ዘላቂ መፍትሄ የሚሰጥ ጥናት ነው ። የዚህ ጥናት አላማ ምንድን ነው ? ብትለኝ ፣ ባጭሩ ፣ ብሩህ አእምሮ ያላቸው ተማሪዎች በፈለጉት የትምህርት መስክ ወደ ፊት እንዲገፉ ፣ የተቀሩት ደግሞ የእጅ ሙያ እውቀት አግኝተው ባሉበት አካባቢ እጥቅም ላይ እንዲውሉ ፣ ራሳቸውንም ሆነ ህብረተሰቡን እን ዲረዱ የሚያደርግ ጥናት ነው ። መፍትሄ ይሉሃል ይሄ ነው ። ጭቃ ቤት መስራት አይደለም መፍትሄው» አለና በአሳቡ የረካ ይመስል በረ ጅሙ ተንፍሶ የሞቀ ፈገግታ አሳየው ።

ሀዲስ በነገሩ ሲያስብበት ቆየና ፣ «አንድ ጥያቄ አለኝ» ከማለቱ ታፈስ አቋዋረጠውና ፣ «አንድ ጥያቄ ካለህ ላዲስ ዘመን ጋዜጣ ላከው» አለና ቀለደበት ።

«እውነቴን ነው !»
«እሺ ፣ ምንድን ነው ጥያቄህ ?»
«ትምህርት በሰፊው ቢዳረስ ለማን ነው አደጋው ?»

«ምን አይነት የጅል ጥያቄ ነው ? ላገሪቱዋ ነዋ !» አለው በእጁም ጥምር እየተናገረ ።

«አይደለም ። ራስክን አታታለው ። አደጋው ለገዢው ወገን ነው ። ለገዛ አገሩ አደገኛ የሚሆን ህዝብ የለም» አለው ፍርጥም ብሎ ።

ታፈሰ ከመቀመጫው ዘሎ ለመነሳት እየቃጣው ፤ «ኤዲያልኝ የኛ ሬቮሉሽነሪ ! ጭቃ ለጠፍ ለጠፍ ። ተምረናል የሚሉ ማይማን በብዛት መፈልፈል ። ባንተ ቤት እንግዲህ ይሄው ነው መፍትሄው ?» አለ እያላ ገጠበት ።

ሀዲስ መልስ አልሰጠውም ። ዝም አለ ።

«ምን ዝም ያሰኝሃል ? ሬቮሉሽነሪ ከመሆንህ የተነሳማ ትምህርት ቤት ለመስራት ብቻህን ታጥቀህ ተነስተሃል ፤ ኤ ?»

«ብቻዬን አይደለሁም ።»
«ታዲያስ ?»
«ህዝቡ ይረዳኛል ።»

«አትቃዥ አቦ !» ብሎት አቀማመጡን ከመቅፅበት ለወጠና ፤ «ህዝቡ እንኳን መርዳት ቀርቶ ራሱንም መርዳት አልቻለም ። እሱን እርሳው። ፍፁም ቅዠት ነው። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ቅዠት ብትረሳው ይሻላል ። ይህ ህዝብ ምን እንደሆነ ታውቀዋለህ ?»

«አንተው ንገረኝ» አለው ፊቱን አጨማዶ ።

እንደ ልማዱ አቀማመጡን ለወጠና ፤ «ገና በመካከለኛው ጭለማ ዘመን የሚኖር ህዝብ ነው» አለው ።

«እንዴት ?»

«ሃይማኖቱ ከጅማት የከረረ ፤ ሰሎሞናዊ ሀረግ በሚል ተረት የሚያምን ፤ ያርባ ቀን እድሌ የተፃፈው ገና ስወለድ ነው ፤ ሰው ያስባል ፣ እግዜር ይፈፅማል ፤ ምን አለፋኝ ? እሱ ያለው ሳይቀር ፤ ለሁሉም ጊዜ አለው ፤ ያለጊዜው አይዘራም ፣ ያለጊዜው አይታጨድም ፤ ማንም ከተቆረጠለት ቀን ሳያልፍ ፤ ለዚች ጠፊ አለም ፣ እግረ መንገዳችንን ሳጭር ጊዜ ለምንኖርባት ጊዜያዊ ኪራይ ቤት ማሰብ ከንቱነት ነው ፤ እያለ በመካከለኛው ጭለማ ዘመን የሚኖረውን ህዝብ እለውጠዋለሁ ማለት ቅዠት ነው» ብሎት ፣ አሳቡ ራሱ ስላሳቀው እየሳቀ ፣ «ከቅዠትም ቅዠት ። አንድ የጭቃ ትምህርት ቤት በመስራት ህዝቡን እረዳለሁ ወይም እለውጣለሁ ማለት ደግሞ የባሰ ቅዠት ነው» ብሎት ሲጃራውን ማግ አድርጎ የጢስ ቀለበት እያከታተለ ከለቀቀ በሁዋላ ፣ «ጊዜህን በከንቱ አታጥፋ ፤ ይህ ህዝብ ያመሰግነኛል ብለህም አታስብ ። አበሻ አቃቂር ማውጣት እንጂ ማመስገን አያውቅም ። ያስታውሰኛል ብለህም አታስብ ። የህዝብ የማስታወስ ችሎታ እድሜ አጭር ነው ። ለዚያውም ደግሞ ፣ እንደ ገባኝ ከሆነ እንደ አቶ ይርጋ ያሉ ምቀኞች ተነስተውብሃል ። ያጠፉሃል ። ለምን ብለህ ነው ጣጣ ውስጥ የምትገባው ? ቂል አትሁን ። ይልቅ ቅዠቱን ተወውና ከኔ ጋር እንስራ ። እንዳንተ ያለ የተማረ ወጣት ከጎኔ ያስፈልገኛል ። የሚያነጋግረኝ ሰው እፈልጋለሁ ። ከድንቁርና ባህር ውስጥ ከምጨማ ብቻዬን መኖር አልፈልግም» አለው ።

ሁዲስ ጠጉሩን ቆፈረና ፥ «ሁሉም ነገር አንተ እንደምትለው አይመስለኝም ። አንተ የምታወራው ስለ ፊውዳሎች ነው ። ህዝቡ ግን ለውጥ ፈላጊ ነው ። እውነቱን ነው ። ቅዠት አይደለም ። እዚህ ከመጣሁ ጊዜ ጀምር እንኩዋን አይኔ ብዙ አይቶአል ፥ ጆሮዬ ብዙ ሰምቶአል ። አንድ ትርታ ይሰማኛል ። የለውጥ ትርታ ነው ። ይታየኛል» አለው ።

«ምን አይነት ለውጥ ?»

«አላውቅም ። ግን ከትከሻው ላይ ተጭኖት ያጎበጠውን ሸክም ለማውረድ እንደሚፈልግ አውቃለሁ ።»

ታፈሰ እየቀለደበት ፥ «ሶሻሊስታዊ ለውጥ ለምን አትለኝም ? ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ይህንኑ አይደለም ስታቦኩ የምትውሉት ? የኤርትራ አርነት ንቅናቄ የሚባለውም እዚያው ነው አሉ የተፈጠረው ። እና ፥ ደግሞ ትደግፉታላችሁ አይደለም ?» አለው ።

«የሀይለ ስላሴን ፊውዳላዊ ስርአት የሚገረስስ ከሆነ ለምን አይደገፍም ?» በማለት ጥያቄውን በጥያቄ ኮስተር ብሎ መለሰለት ።

ታፈሰ በመገረም ራሱን ከቱኛ ነቀነቀና ፥ «እሺ እሱስ ይገርሰስ ። እኔም እንዳንተ ለውጥ ፈላጊ ነኝ ። ለውጥ የማልፈልግ አይምሰልህ ። የድንጋይ ዳቦ ዘመን በምትሉት ጊዜ እኔም ለውጥ ፥ ለውጥ ከሚሉት ተማሪዎች ውስጥ አንዱ ነበርኩ» ብሎት አቀማመጡን እንደ ልማዱ ከመቅዕበት ለወጠና ፥ «በነገራችን ላይ ፥ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተማሪዎች ተወከዬ የኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነት ማህበር የተባለውን ድርጅት በሀንፃ ኮሌጅ ውስጥ ከመሰረቱት ተማሪዎች ውስጥ ነበርኩ ። በመንግስቱ ንዋይ የታህሳስ ግርግር ጊዜ 'መሬት ላራሹ' ብለው ሰላማዊ ሰልፍ ካደረጉት ቀንደኛ ተማሪዎች መካከል አንዱ ነበርኩ ።

«አይናችንን የከፈቱልን በሀይለ ስላሴ ስኮላርሺፕ የመጡት ያፍሪቃ ተማሪዎች ነበሩ ። ጊዜው ተለወጠ ። እኛም ተለወጥን ። ከህይወት የምታገኘው ልምድ ብዙ ነገር ያስተምርሃል ።»

«እንደምን ያለ?» ብሎ ጠየቀው ሁዲስ ።

«መጀመሪያ ነገር ህዝብ ፥ ህዝብ ማለትን ታቆማለህ ። ምክንያቱም ህዝብ ሲባል የግለሰቦች ጥርቃም እንደ መሆኑ መጠን ሁሉም በፊናው ለራሱ ጥቅም የሚሩዋሩዋጥ መሆኑን ትገነዘባለህ ። እና ፥ የሰው ልጅ በመሰረቱ በጎ አሳቢ እንዳልሆነ ታያለህ ። ህይወት ብዙ ነገር አስተምሮኛል ። ለውጥ ፥ ለውጥ እያሉ መጮህ ቀላል ነገር አይምሰልህ ። የሰውን ተፈጥሮ ሊመለወጥ አትችልም ።»

ሁዲስ ጠጉሩን ቆፈረና ፥ «ሰው ከንብረት ጋር ተፈጠረ አሉህ ? ከንብረት ጋር ይቀበራል አሉህ ? አንተ ከህይወት አገኘሁ የምትለው ልምድ የካፒታሊስቶች ስርአት ያመጣውን ባህርይ ነው ። እውነቱን ነው . . . ስማኝ እንጂ . . . ይህች አለም የጋራ ንብረታችን ናት ። በጋራ ልንጠቀምባት ይገባል . . . ስማኝ እንጂ . . . አስጨርሰኝ . . . ይህች አጭር የሰው ልጅ ህይወት በተቻለ መጠን ለሁሉም ጣፋጭ እንድትሆን ከማድረግ

የበለጠ ክቡር አላማ የለም ። ይህች አለም ለጥቂቶቹ የሳቅ አለም ፣ ላብዛኞዎቹ የእንባ አለም ፣ ለብዙዎቹ ሲኦል ለጥቂቶቹ ገነት ብትሆን ምን ደስታ ይገኛል ? ያላቸውም ሊደሰቱ አይችሉም ። የሰው ልጅ የተሟላ ደስታ ሊኖረው የሚችለው የጋራ ደስታ ሲኖረው ነው ። የሰው መድሀኒቱ ሰው ነው ። ሰው ለተሻለ የጋራ ህይወት ፣ ለጋራ ደስታ ራሱን ሊሰውጥ የሚችል ይመስለኛል» አለው ።

«አቤት ! አቤት ! እንዲህ አርጎም የለ» ብሎት አፈዘበትና ፣ «ፕሮዳክሽን ሪሌሽንን ምንድን ነው የምትሉት በዩኒቨርሲቲ ቋዋንቋዋችሁ ?» አለው ራሱን እያከከ ።

«የምርት ግንኙነት» ብሎ ነገረው ።

«አዎን ፣ ባንተ ቤት እንግዲህ የምርት ግንኙነት ሲለወጥ የሰው ተፈጥሮም አብሮ ይለወጣል ! አይ እናቴ ! እንዲህ አይነቱን ቀልድ ተወኝ አቦ ። ህልም ነው» አለ ታፈሰ ።

«ግን ጥሩ ህልም ነው ። የቆየ የሰው ልጅ ህልም ነው ። አንድ ቀን እውን ይሆናል ።»

«አታልም ያለህ የለም ። እድሜህን ሙሉ ልታልም ትችላለህ ። ግን ሶሻሊስታዊ ለውጥ በኢትዮጵያ ይመጣል ብሎ ማሰብ እብደት ነው» ብሎት አቀማመጡን ለወጠ ።

«ለምን ?»
«አፉ ! እንደ ህፃን ለምን ? ለምን ? ማለት ባታበዛ ምናለበት !»
«ኢሺ ።»

«የሀይለ ስላሴ ፊውዳላዊ አገዛዝ እንዳልከው ይገርሰስ እንበል ። ምንድን ነው በእሱ ቦታ የምትተካው ? ሶሻሊስታዊ ስርአት ልትለኝ ነው ? እብድ አትሁን ። አሁን ያለው ስርአት ቢገረሰስ አገሪትዋ ምን ላይ ልትወድቅ እንደምትችል አስበህበታል ?» ብሎት ውስኪውን አንስቶ ከጨለጠ በሁዋላ ፣ «አንተም ሆንክ ሌሎች ያሰባችሁበት አይመስለኝም ። በጣም በጥንቃቄ የሚያዝ ፖለቲካዊ ሚዛን የሚያስፈልጋት አገር ነች ። የእምቡዋይ ካብ ስትሆን ለማየት የሚፈልጉ ብዙ ጠላቶች ዙሪያዋን ከበዋታል ። የብዙ ጎሳዎችና ሃይማኖቶች አገር መሆንዋን አትርሳ ። ይህ ሁሉ የፖለቲካ ጥበብና ሚዛን ያሻዋል ። ለውጥ ፣ ለውጥ ማለት ቀላል ነው» አለው ፣ ምላሱን ያዝ እያደረገው ።

«እንደ አባባልህ ከሆነ በቃ ኢትዮጵያ ምንም ለውጥ አያስፈልጋትም ማለት ነው ። ህልም ፈርተን ሳንተኛ እንደር . . . ሶስት ሺህ ዘመን አንቀላፍተናልና ለሚቀጥለውም ሶስት ሺህ ዘመን ዝም ብለን እንተኛ ነው የምትለኝ ፣ አይደለም ?» አለው ፣ ጠጉሩን እየቆፈረ ።

ታፈሰ ብስጭት ብሎ ቋንጥር ቋንጥር እያለ ፣ «ለውጥ ፈፅሞ አያስፈልግም ማሌቴ አይደለም» አለው ።

«ታዲያስ ?»
«ለውጥ ያስፈልገናል ።»
«ምን አይነት ለውጥ ?»

«የመፃፍና የንግግር ነፃነት ። የመሬት ይዞታ መስተካከል ። በህግ ተርጉዋሚና በህግ አስፈፃሚ ተቋዋሞች መካከል የስልጣን መከፋፈል ። በህግ ስር የሚተዳደር ዘውዳዊ አገዛዝ ። እና ፣ ይህን ሁሉ ያቀፈ የማያሻማ ህገ መንግስት» ብሎት መለኪያውን አንስቶ በንዴት ከውስኪው ተጎነ ጨና ፣ «አሁን የሚያስፈልጉን ለውጦች እነዚህ ናቸው ። ግን ሮማ ባንድ ቀን አልተገነባችም ። ጊዜ ይወስዳል ። ለውጥ ስንል ደግሞ በታሪካችን ፣ በባህ ላችንና በልማዳችን ላይ የተገነባ ለውጥ መሆን አለበት ። ኢትዮጵያ ረጅም ታሪክና ሰፊ ባህል ያላት አገር ናት ። ይህንን ፀጋ እንዳሮጌ ቁና አውጥተን መጣል የለብንም ። በራሳችን ላይ እምነት እንዲኖረን ያስፈልጋል ። መሰ ረት እንዲኖረን ያስፈልጋል ። መሰረት የሌለው ለውጥ ድቡሽት ላይ እንደ ተሰራ ህንፃ ከፍ እያለ በሄደ ቁጥር አወዳደቁም እንደዚያው ፍፁም ይሆ ናል» አለው ።

ሀዲስ ተራውን ሳቀበትና ፣ «ባንተ ግምት ህዝቡን የራበው የመፃፍ ነፃነት ነው ፣ እ ? የጠማው የንግግር መብት ነው ፣ እ ? ብዙሃኑን የኑሮ ሸክም የሆነበት የስልጣን አለመከፋፈል ነው ፣ እ ? ባንተ ቤት ዘጠና እም ስት በመቶ ማይም የሆነው ህዝብ ችግርና ብሶት የመናገርና የመፃፍ መብት ወይም በወረቀት ላይ የተፃፈ ህገ መንግስት ነው ፣ እ? ታስቃለህ ። በእው ነት ታስቃለህ» አለውና የፌዝ ሳቅ ፊቱ ላይ ሳቀበት ።

ታፈሰ ጥርሱን ነክሶበት ፣ «ባንተ ቤትስ ?» አለው ።

«ህዝቡ የሚፈልገው ከብዝበዛና ከጭቆና ራሱን ነፃ አድርጎ ከማይ ምነት ፣ ከእጦትና ከበሽታ መላቀቅ ነው ። የተበዘበዘና የተጨቆነ ህዝብ ምን ጊዜም ቢሆን መሰረታዊ ፍላጎቱ ነፃነት ፣ እኩልነትና ፍትህ ነው ። እነዚህ ደግሞ ያለ ስር ነቀል ለውጥ አይገኙም ። ህዝቡ ለቅንጦት ነፃነት ደንታም ሆነ ጊዜ የለውም !» አለው ድምፁን ሳይወድ በግድ ከፍ አድርጎ ።

«ለሶሻሊዝም ነዋ ደንታ ያለው !» አለው ፣ የምፀት ፈገግታ ከፊቱ ላይ ለጥፎ ።

«ለድሪቶ አሳብና ለተደረተ ለውጥ አይደለም» አለው ሀዲስ ፣ አሁንም ሳይወድ ድምፁ ከፈለገው በላይ ከፍ እያለበት ።

«ቂል ሆንክብኝ» ብሎ ምርር በማለት ታፈሰ ንግግሩን ጀመረ ፣ «ሶሻሊዝም ሲባል ትርጉሙ የገባህ አይመስለኝም ። እኔ ሶሻሊዝም የምለው ሰው ስርቶ የሚያድርበትን ስራ መፍጠር ነው ። ግን ስራ መፍጠር እትች ሉማ ። በየትኛው እውቀት ? ቁጭ ብላችሁ ስር ነቀል ለውጥ እያላችሁ መጮህ ይቀላችሁዋል ። የፀረ—ስራ ሶሻሊስቶች ጩኸት ሰልችቶኛል ።

«በነገራችን ላይ ፣'ወደ ሁዋላ ቀረን ፣ የስልጣኔ ጭራ ሆን ፣ ትናንት ነፃነታቸውን የተጎናፀፉት ያፍሪቃ አገሮች እንኳዋን ቀድመውን ሄዱ ፣ ስለዚህ ስር ነቀል ለውጥ ያስፈልገናል' አይደለም ወይ የምትሉት ? ግን ለውጥ ስለ መጣ የግድ እድገት የሚከተል አይምሰልህ ። የእድገት ችግሩ ምርት አይደለማ ። ችግሩ ህዝቡ ያለው የማምረት ችሎታ ነው ። ሁዋላ ቀርነት ምን ማለት እንደሆነ ይገባሃል ? የሁዋላ ቀርነት ትርጉም በመሰረቱ የአእምሮ ሁዋላ ቀርነት ማለት ነው ። እና ፣ ሶሻሊዝም ስታመጣለት ህዝቡ ምን የሚጋራ መሰለህ ? እልም ያለ ድህነት ። ሌላ ምን ሊጋራ ይችላል ?

ዝም ብላችሁ በምድረ በዳ ባትሞሁ አሁን ምናለበት ! ባዶ ህልማችሁን ፣ የቂሎች ጎነታችሁን እዚያው ዩኒርቨሲቲ ባዶ አየር ላይ ብትፈልጉ ካቡ ። ህዝቡን ግን ተውት» ብሎ መለኪያውን አንስቶ ውስኪውን በንዴት ትን ፋሽ ጨለጠና ሲጃራ አቀጣጥሎ እያከታተለ የሚለቃቸውን የጭስ ቀለበ ቶች በቀሉ አይኖቹ ይመለከት ጀመር ።

ሀዲስ ጠጉሩን መቆፈር ሳይሆን ቡጭር ቡጭር አደረገና ፣ «የቡርዥዋ ህልምና ዲሞክራሲ ያስቀኛል ። አፍንጫ እየቆጠሩ በቁጥር መጫወት ያስቃል ። ለብዙሃኑ ህዝብ—በተለይ በአእምሮ ወደ ሁዋላ ቀርቶአል ለም ትለው ህዝብ—የስልጣን መከፋፈል ፣ የንግግርና የመፃፍ መብት ፣ ህገ መንግስት የምትለው ባዶ ኩዋኩዋታ ሁሉ ምኑም አይደለም ። እሱ የቡርዥዋ ካፒታሊስቶች ህልም ነው ። የብዙሃኑ ህዝብ ህልም አይደለም ።

«የብዙሃኑ ህልም እውነተኛ ነፃነትና እኩልነት ነው ። አዎን ፣ እንዳ ልከው ድህነቱን ለተወሰነ ጊዜ ይጋራ ይሆናል ። ያንዳንድ ጥጋበኞችን ግሳት ከመስማት አብሮ መደህየት ይሻላል ። አብሮ የተሰቃየ ህዝብ አብሮ መደሰቱና መበልፀጉ አይቀርም ።

«ካፒታሊዝም ብዙሃኑን ህዝብ ከማይምነት ፣ ከእጦትና ከበሽታ ነፃ ሲያወጣ በታሪክ አላየንም ። የታሪክ ቀስት የሚያመለክተው ወደ ሶሻሊ ዝም ነው ። የታሪክን ጎማ ወደ ሁዋላ ለማሽከርከር ማንም አይችልም !»አለ።

«እና ፣ ሶሻሊዝም አገራችን ይመጣል ነው የምትለው !» ብሎ ታፈሰ በሳቅ እንደገና ፈነዳ ። ሆዱን ይዞ የኮረኮሩትን ያህል ከት ብሎ ሳቀ ። ሳቁ አላባራ ስላለው ሳቀ ። ሀዲስም የታፈሰ ሳቅ ስላሳቀው አብሮት ይስቅ ጀመር ። ታፈሰ ስቆ ስቆ ሲያበቃ :-

ደህና ሁኚ አራዳ
የኔ ፅጌ ረዳ
ተለያየን ቢቃ ደህና ሁኚ አራዳ
ጥቁሩ ወርቅ ጠርቶኝ ወጣሁ በማለዳ
ደህና ሁኚ አራዳ
የኔ ፅጌ ረዳ

ዳ ዳ ዳዳዳዳ . . . እያለ ሲንገዳገድ ተነስቶ ፣ እየተንገዳገደ ብቻውን ቻቻ ዳንስ ይደንስ ጀመር ። ዝናሽና ሽታዬ አልነበሩም ። የሁለቱም ውስኪ እንደ ተቀዳ ቀርቶአል ።

«ዳ ዳ . . . ዳዳዳዳ . . . ጥቁር ወርቅ ሲፈነዳ . . . ቻቻቻቻ . . . ብር በስልቻ . . .» እያለ ሲደንስ ከቆየ በሁዋላ ፣ ሽጉጡን መዞ ሲንገዳገድ መጣና በተከላተፈ ምላስ ፣ «ከኔ ጋር ሚሊየኔር መሆን አትፈልግም ፣ ኢ?» አለው ሽጉጡን ሀዲስ ግንባር ላይ ደግኖበት ።

የሽጉጡ አፈ-ሙዝ ቀዳዳ ከመጠን በላይ ሰፍቶ ታየው ።

«ካፒታሊዝም፣ባንተ ቤት ሙዋች ነው ፣ ኢ ?»

ሀዲስ ቀስ ብሎ ከሽጉጡ አፈ-ሙዝ ላይ ራሱን ዞር አደረገ ። ቀዝ ቃዛ ላብ ጀርባውን አሰመጠው ።

«እና ፣ ባንተ ቤት የታሪክ ቀስት የሚያመለክተው ወደ ሶሻሊዝም ነው ፣ ኤ ? እና ፣ ባንተ ቤት እኔ ከዚህ የመጣሁት ህዝቡን ልዘርፍ ነው ፣ ኤ ? አንተ ደሞ የቆምከው ለህዝቡ ነው ፣ ኤ ? አንድ ጭቃ ቤት በመስራት ። አንተ ለህዝብ የቆምክ ፣ ለህዝብ የምታስብ ጀግና ነህ ። እኔ ደሞ ባንተ ቤት ለህዝብ ምንም የማላስብ ፣ ራሴን ብቻ የምወድ ፡ ግብግብ ነኝ ። ባንተ ቤት እኔ ወኔ የሌለኝ ፈሪ ነኝ ፣ ኤ ?»

ሀዲስ ከግንባሩ ላይ መንጠፍጠፍ የጀመረውን ተገዘቃዛ ላብ በእጁ ቀስ ብሎ ጠረገና ፣ «እንዲህ ያለ ነገር አልወጣኝም» አለው ።

«አሁን የምንጫወተውን ጨዋታ ታውቀዋለህ ?»
«አላውቀውም ። ግን ጥሩ ጨዋታ አይደለም ።»
«የሞት ጨዋታ ይባላል ።»
«ደስ አይልም ።»
«ሞትን ትፈራለህ ?»

«ለምን አልፈራም ? ህይወት ምን እንደ ሆነች የማያውቅ ብቻ ነው ሞትን የማይፈራው . . . »

«ምንድን ነች ህይወት ?»

ሀዲስ አቀርቅሮ ዝም አለ ። የሽጉጡን አፈ-ሙዝ ቀዳዳ ባየ ቁጥር አፉ እየሰፋበት ይሄድ ነበር ። ጭለማው ቀዳዳ የምፀአት ቀን ቁዋንቁዋ የሚናገር ይመስላል ። በቀዳዳው ውስጥ ወደ ዘለአለማዊነት የሚያስገባ ጭለማ በር ተከፍቶ ታየው ።

«ንገረኝ እኮ ። ምንድን ነች ህይወት ?»
«ህይወት ላንዱ ሚሊዮን ብር ፣ ለሌላው ጭቃ ቤት ናት ። ጥቁር ወርቅ ጭቃ ቤት ። እንደ ሁኔታው ነው» አለው ።
«ጅል ! እንደሱ እንድትለኝ አልነበረም የፈለኩት ።»
«ምን እንድልህ ኖሮአል የፈለከው ?»
«ህይወት ርግማን ናት እንድትለኝ ነበር ።»
«ለኔ የተባረከች ናት ።»
«እና ፣ መኖር ትፈልጋለህ ?»
«አዎን ፣ መቶ አመት ። ቢቻል ከዚያም በላይ . . . »
«ለምን ?»

«ሞት ካረጀ አጥንትና ከተጨማደደ ቆዳ ሌላ የሚዘርፈኝ ነገር እንዳ ይኖረው ነዋ ።»

«ሞትንም ልትረታው ትፈልጋለህ ፣ ኤ ?»

«ቢቻለኝ ለምን አልፈልግም ? ሞትን ድል የማድረግ ፍላጎት በሁሉም ልብ ውስጥ ያለ ነገር ነው ። ማን ሞትን ይሻል ? ሰው ለህይወት ነው የሚታገለው . . . »

ታፈሰ እንደ ገና በሳቅ ፈነዳና የሽጉጡን አፈ-ሙዝ ወደ ጣራው ቀና አድርጎ ሁለት ጥይት አከታትሎ ተኮሰ ። «በቃ ገደልኩት ሞቶአል» አለው።

«ማን ነው የሞተው ?»

«ሞት ። ሞትን ገደልኩልህ» ሲል ዝናሽና ሽታዬ ተከታትለው እየ ሮጡ ገቡ ።

«ምንድን ነው እሱ ? በሞትኩት ምንድን ነው ?» ትል ነበር ዝናሽ ። ሁለቱንም እንደ ትንግርት እያየች ። የወደቀ ሬሳ አልነበረም ። ወከክ ብሎ የሚነደውም ማሾ የሚያሳየው ጉድ አልነበረም ።

ታፈሰ በሳቅ እየተንከተከተ ፥ «እሱን ነበር የምንጫወተው» አላት ። «ምኑን ?» አለች ፥ በአይንዋ ይጫወቱት የነበረውን ነገር እየፈለገች ።

የሽታዬ አይን ተጎልጉሎ ሊወጣ ደርሶአል ። የተተኮሰባት ሚዳቋዋ ይመስል ደንግጣለች ። ለመጮህም ይቃጣት ነበር ። አንዴ ወደ ሀዲስ ፥ ደግሞ ወደ ታፈሰ ትመለከታለች ። የፈሰሰ ደም አልነበረም ። የባሩድ ሽታ ብቻ ነበር ።

«የሞት ጨዋታ ። የሞት ጨዋታ ተጫውተሽ ታውቂያለሽ ?» ሲል ፥ ታፈሰ በፊት የሸኛቸው ሁለት አሽከሮች ከየት እንደ መጡ ሳይታወቅ ገብተው ሽጉጡን ከእጁ ቀሙት ።

«ህይወት ጨዋታ ነች ። የሞት ጨዋታ ። ከሞት ጋር የድብብቆሽ ጨዋታ ። ኩኩሉ አልነጋም ። ጭቃ ቤት ፥ ኤ ? ሀሀሀ ሆሆሆ . . . »

ሰዎቹ ግራና ቀኝ ደግፈውት በግድ ይዘውት ሲወጡ ፡—

ደህና ሁኚ አራዳ
የኔ ፅጌ ረዳ
ሽው ሽው ባራዳ
ቀረ በማለዳ
ዱዳዳዳ
ጥቁር ወርቅ ሲፈነዳ
ቻቻቻቻ

ብር በስልቻ... እያለ ሲጮህ ፡—

ድምፁ እየራቀ ፥ እየራቀ ከጭለማው ጥልቀት ውስጥ ይሰማ ነበር ...

# ክ ፍ ል ፳

ጡዋት ፲፡ ፲ሰዓ ሽታዬ ሀዲስን ከጣፈጠ እንቅልፉ ቀሰቀሰችው ።
«ስንት ሰአት ነው ?» አላት እየተነጫነጨ ።
«አስራ ሁለት ሰአት ተኩል ነው» አለችው ።

የጡዋት እንቅልፉን በጣም ስለሚወድ ማለዳ ሲቀሰቀስ ይነጫነጫል። የማለዳን ጭጋግም ፣ ጭፍግግ ግራጫ መልክ ማየት አይወድም ። ያባቱ ዳዊት ባሳቡ ይመጣበታል ። የሚያዛጋ ቆፈናም ግራጫ አለም ይታየዋል ። ግራጫ ወርቅ የደረበች ፣ አንገትዋን በሀዘን የዘለሰችና በገዛ እንባዋ የራሰች ተፈጥሮ በአይኑ ሀሊናው ትመጣለች ። ጤዛ እኮ ተፈጥሮ ማለዳ የምታነባው የሀዘን እንባ ሳይሆን አይቀርም ይላል ። የማለዳ ውበት ከምኑ ላይ እንደሆነ አይገባውም ። የሚያዛጋ ግራጫ ፣ ቀዝቃዛ አለም ። ወፎች ማለዳ ዝማሬ የሚያቀልጡበት ምክንያት ምስጢር ይሆንበታል ። ማለዳ ፣ ለወፎች ፣ ለመንገደኞች ፣ ለለማኞችና ለመርዶ ነጋሪዎች ነው ይላል ።

ጭንቅላቱ የከበደው ይመስል በሁለት እጆቹ ደግፎት ቁጭ ብሎ ቀረ ። ማለዳ ባዶ ጭንቅላቱ እንደ ድንጋይ ይከብደዋል ። እንደ አንዳንድ ሰዎች ቶሎ ነቅቶ እንደ ወፍ ብር ብሎ መሄድ አይሆንለትም ። ፍዝዝ ብሎ ይቀራል ። እስሬ ያዛጋል ። ሰው እለቱን የሚጀምረውና የሚጨርሰው በማዛጋት መሆኑ ይገርመዋል ። እሱ እያዛጋ እንደ ቀንድ አውጣ ሲጎተት ጊዜው ደግሞ እንደ ወፍ ክንፍ አውጥቶ ይበርበታል ። እና ፣ የሚይዘውና የሚለቀው ነገር እየጠፋው ተጨንቆ ይበሳጫል ።

ሀዲስ አዛጋና ሽታዬን ቀና ብሎ በቀሉት አይኖቹ ተመለከታት ። ትክዝ ብላ ቆማለች ። በዚያ ጭጋጋም ሰአት ከእንባ አገር ተልካ የመጣች መሰለችው ።

ጠጉሩን እንደ ልማዱ ቆፈረና ፣ «የማንን መርዶ ልትነግሪኝ ነው በለሊት የመጣሽው ?» ብሎ ጠየቃት ፣ እየተነጫነጨ ።

«ቃሬስ አንተ ከሄድክ በሁዋላ ተመልሶ አልመጣ መሰለህ ?» አለችው ፣ ለምቦጭዋን ጥላ ። አመድዋ ወጥቶአል ። ተኝታ ያደረች አትመስልም ።

«ምን ሊያረግ ?» አላት ።

«ምን ለማረግ ይመስለሃል አንተ ስታስበው ?» አለችው ፣ ጥያቄው አስቆጥቶአት ።

«ምናውቃለሁ ? አንቺው ንገሪኝ» አላት ጫማውን እያጠለቀ ። ሱሪውን ከማጥለቁ በፊት ጫማውን ማጥለቅ ይቀናዋል ። እና ፣ ሁልጊዜ የሱሪውን እግር እጥፋት በጫማው ተረክዞ ይተረትራል ።

«እኔን ፍለጋ ነዋ ! ሌላ ለምን ይመስልሃል?» አለችው እየተነጫነ
ጨች ።

«እንቺን ፍለጋ ? ለምን ?» አላት በነገሩ ሳያስብበት ። ማለዳ ሲነሳ
ነገር ቶሎ አይገባውም ።

ከስር እጥፋቱ የተተረተረው ሱሪ የጫማውን ተረከዝ ይዞበት ሲኒ
ጫንጭ በትዝብት እያየችው ፣ «በሩን ካልከፈታችሁ ብሎ ሊሰብረው ሲል
ከተከፈተለት በሁዋላ 'ካንቺ ጋር ለማደር ነው ይህን ጨለማ በስካር ልብ
ስንጥቄ የመጣሁት ። መንገድ ስደርስ ጠጉርሽ ትዝ አለኝ' እያለ ያስቸግ
ረኝ ጀመር» አለችው ፣ ጣቶችዋን በንዴት እያንቋዋቋዋች ።

«እናና?» አላት ።

«አይሆንም ። እኔ የምወደው ሰው አለኝ ። ያም ሰው ጉዋደኛህ ነው
ብለው ሊለቀኝ መሰለህ ! ጠጉሬን ጭምድድ አድርጎ ይዞ 'እኔም ወንድ ነኝ።
ከማን የማንስ መሰለሽ ? ወይስ የኔ ብር ዋጋ የለውም አሉሽ ?» ብሎ ያን
መከረኛ ሽጉጡን ሲመዝ ጊዜ እትዬ ዝናሽ ፈርተው ጥለውኝ ውልቅ
አሉ ። እኔም ለህይወቴ ፈርቼ ፣ ይኸውልህ ከሱ ጋር ለማደር ተገደድኩ ።
ዋ ሴት መሆን!» ብላ ጣትዋን ቋዋ አደረገች ።

«በውነት ባለጌ ነው» ብሎ ነትቶ ልብሱን እንደ ነገሩ ቶሎ ለባበሰና ፣
«አሁን የት ነው ያለው ?» አላት ።

«አይ ! እኔኮ እንድትጣሉ አይደለም ። ሱጲ መቼም እንኩዋን የሆነው
ያልሆነውም ነገር ይወራልና ከሌላ ሰው ከመስማትህ በፊት እኔው ልንገ
ርህ ብዬ ነው እንጂ ፣ የሞት ጨዋታ እንጫወት ከሚል እብድ ሰው ጋር
እንድትጣላ አይደለም ።»

«የሞት ጨዋታ የሚለው ለጉራ ነው እባክሽ ። ህይወት ምን እንደ
ሆነች ሳያውቁ ስለ ሞት ትርጉም ማውራት ጅልነት ነው» ብሎአት ፣
ሊወጣ ሲል ታፈሰ ብሩ በሩን ከፍቶ ሰተት ብሎ ገባ ።

ሽታዬ «በሞትኩት !» ብላ ሮጣ ወደ ጉዋዳ ጥልቅ አለች ።

ታፈሰ ቃል አልወጣውም ። እንደ መጣ ሄዶ ከሀዲስ ፊት ተንበረከከና፣
«እግዜር ካደረጋቸው ስህተቶች ውስጥ አንዱ እኔን መፍጠሩ ነው ። መጥፎ
ነኝ ። ይቅርታ አድርግልኝ ። መጀመሪያ በነገር አስቀየምኩህ ። መጥፎ
ቀልድ ነበር ። ይኸው ሳያንስህ ደግሞ ሴትክን ቀማሁህ ። ከዚህ የበለጠ
በደል ምናለ? ግን አናደኸኝ ነበር ። እና ፣ ያደረብኝን ቂጭት ለመወጣት
ሴትክን ልቀማህ ፈለኩ ። አሁን ግን ነገሩ አሳዝኖኛል ። ይቅርታ ካላደረክ
ልኝ አልነሳም» አለው ።

ሀዲስ መቼም ልቡ ምልስ ስለሆነ ይቅርታ አድርጎለት ታፈሰ ከተንበረ
ከከበት እንዲነሳ ትከሻውን ይዞ እየጎተተው ፣ «ምን አድርጌ አናደድኩህ?»
ብሎ ጠየቀው ።

የታፈሰ ፊት ነብዞአል ። ከንፈሮቹ ኩበት መስለዋል ። የአይናቹ
ቀለም ቀይ ሆኖ ነበር ።

«በጣም ነው እንጂ ያናደድከኝ» ብሎ ከተንበረከከበት ተነሳ ።

«እኮ ምን አድርጌ ?»

«ችኮ ሆንክብኝ ። ደቅርታ አድርግልኝና እኔ ካንተ በእድሜም ሆነ በልምድ እና በትምህርትም ቢሆን እበልጥሃለሁ ። ግን ፣ ይህ ሁሉ ላንተ ዋጋ ያለው መስሎ አልታየህም ። ዝም ብለህ ቴዎሪ ነው የምታነበንበው ። እና ፣ በዚህ ላይ ደግሞ የመንግስት ስራዬን ጥዬ እዚህ የመጣሁበትን አላማ ስታራክስብኝ በጣም ነው ያናደድከኝ ።»

ነገሩን ቀበል አደረገና ፣ «አንተ ባላማህ ካመንክበት እኔ ምንስ ብልህ ምን ቸገረህ ?» አለው ።

«እሱስ እውነትክን ነው ።»
«ታዲያስ ?»
«ግን ፣ ያልገባህ ነገር አለ ።»
«ምን?»

ታፈስ በሀዲስ ጥያቄ እንደ መበሳጨት ብሎ የቀረችውን አንድ ሲጃራ አቀጣጥሎ ሲያቦቃ የሲጃራውን ፓኮ አጨማዶ ጣለና በሚለቀው የጢስ ቀለበት ውስጥ በቀይ አይኖቹ እየተመለከተው ፣ «በዚህ እድሜዬ መጥፎውን ከደግ ለይቼ የማላውቅ ህፃን ይመስል ፣ አንተ ሶሻሊዝም ምና ምን እያልክ ሊሌብነት ፣ ለዝርፊያና ለቅሚያ የመጣሁ አድርገህ ታወራለህ ። ፊታውራሪ ደግሞ ‘አውሬ ፣ ጨካኝና ነፍሱን ለብር የሸጠ የብር ስልቻ እያደ ረጉኝ ፣ አባትህ መሬት ላይ ያሉትን ጭሰኞች ብትነቅል ገዝቼሃለሁ’ ይሉ ኛል!።

«‘የባላባቶች ክብርና ግርማ ሞገስ፣ ያገራችን ወግና ስነ ስርአት መሰረት መሬት ብቻ እይምሰልህ ። ጭሰኞቹም ናቸው ። የአያት የቅመ አያቶቻቸው አጥንት ከተቀበረበት መሬት ተነቅለው ሲያመልኩትና ሲሰግዱለት ከኖ ሩበት አድባር ርቀው ጭሰኞች የትም እንዲሰደዱ ማድረግ መዘዙ ሁዋላ ደግ አይደለም ። አውራ ያጣ ንብ ምን ረብ አለው ? ከኖረበት መሬት ተነ ቅሎ የትም የሚባክን ህዝብ እየበዛ ሲሄድ ሁዋላ እንዴት ? በማን ? በምንስ ህግ ይዳኛል ? ስር የሌለው ህዝብ የትኛውን ህግ ይፈራል ? የየትኛውን ወንዝ ወይም ቀዬ አድባር ያከብራል ? የየትኛውን ሽማግሌስ ምክር ይቀበ ላል ? ለየትኛው ባላባት እሺ ብሎ ይገዛል ? እንግዲህ አገር ፣ ወገን ፣ ስነ ስርአት ጠፉ ማለት አይደለ? እኛስ ምን አለን ብለን እንኖራለን ? የባላባት ስልጣን እንደሆን ተወስዶአል ። ጭሰኞችን ነቅለን ካበረርን ምን ሊቀረን ነው ? ምንስ ልንሆን ? የብር ስልቻ ! በስመ አብ ። በዘራችን ፣ በቤታችን ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅ ። የኛ ክብር ፣ ፀጋና ሀብት ፣ ጥንትም ሆነ አሁን ፣ እንዲሁም ለወደፊት ፣ መሬት ፣ ሰውና ጀግናነት ነው ። ምን አባ ህና ነው ገበሬ ካልሆንኩ የምትለው ?’ እያሉ ገና ከመምጣቴ አላስቆም አላስቀምጥ ብለውኛል ።

«አንተ እጉል ጀብደኛ ፣ ፊዎዱሽነሪ ነኝ ባይ ነህ ። ፊታውራሪ ደግሞ እልም ያሉ ፊውዳል ናቸው ። አንተ ከጊዜው በጣም ቀድመሃል ። እሳቸው ከጊዜው በጣም ወደ ሁዋላ ቀርተዋል ። ሁለታችሁም ብትሆኑ የማታው ቁትና ያልገባችሁ ነገር ቢኖር በኢትዮጵያ እያቆጠቆጠ የመጣው ካፒታሊ

ዝም መሆኑን ነው ።'የኢንተርፕረነሮች' ዘመን ነው ። አንተ እንደምትለው ጊዜው የወዛደሮች አይደለም ።

«ለመሆኑ 'ከኢንተርፕረነሮችና' ከወዛደሮች ማን ቀድሞ የተገኘ መሰለህ ? 'ኢንተርፕረነሮች' ናቸው ። ኢንዱስትሪያል ሬቮሉሽንን ያመጡት 'ኢንተርፕረነሮች' መሆናቸውን አትርሳ ። ከኢንዱስትሪያል ሬቮሉሽን የምንግግረው፣ ቁም ነገር ቢኖር ፣ የስልጣኔ ታሪክ ጎማ በመጀመሪያ ድጠ የሚያልፈው ድሀውን ገበሬ ነው ። በመጀመሪያ የሚፈርሰው ቤት የድሀው ገበሬ ቤት ነው ። ስልጣኔ የተገነባው በድሀ ገበሬዎች ጥፋት ላይ ነው ።

«እና ፣ ማንም ይሁን ሂደት ሊለውጠው አይችልም ። መሬት ወደ ካፒታል መለወጥ አለበት ። ያያት ፣ የቅመ አያት አጥንት ፣ አድባር ምና ምን—እኔ ለዚሀ ሁሉ ደንታ የለኝም ። መሬት ለጥቅም መዋል አለበት ። የጭሰኞች ጭንቅላት በመቁጠር ተኮፍሰን የምንኖርበት ጊዜ አክትሞ አል ። እንዳልኩህ ጊዜው 'የኢንተርፕረነሮች' ጊዜ ነው ። ግን ግራና ቀኝ እያላችሁ ጥርጣሬ ታሳድሩብኛላችሁ» ብሎት የ፦፦ውን የሲጃራ ጢስ ሀዲስ ፊት ላይ አቦነነበት ።

«ቆርጠህ ከመጣህ ለምን ትጠራጠራለህ ?»

«የቆረጥኩ አልመሰለህም አይደለም ?» አለው ።

«ካልክስ በነገሩ የቆረጥክበት አትመስለኝም ። ልብህ አሁንም ያለው አዲሳባ ይመስለኛል» ብሎ ቁርጡን ነገረው ።

«ለምን የቆረጥኩ አልመስልህም ?» ብሎ ጠየቀው ።

«እንጃ ። ብቻ አለ አይደል ፣ ብዙ በመናገር ራስክን ለማሳመን የምትጥር ትመስለኛለህ ።ሕይዞህ ፣ በርታ ብሎ የሚያደፋፍርህ ሰው የምትፈልግ ነው የሚመስለኝ» ብሎ መለሰለት ።

ታፈሰ የሲጃራውን ቁራጭ በጣቱ ወደ ውጭ አስፈንጥሮ ጥሎ የግገውን አንድ እገር ጢስ በሀይል ወደ ውጭ እየተነፈሰ አቡኖ ሲጨርስ ፣ «ልክ ነህ» ብሎ ነገሩን በመቀጠል ፣ «እንደ እውነቱ ከሆነ የፈለኩትን ሹመት ባገኝኦ ኖሮ አልመጣም ነበር ። የሀይለ ስላሴ መንግስት ለሚሸራምጡ ላት ሰዎች ብቻ ነው ሹመት የሚሰጠው ። እኔ ግን ሸርሙጣ አልምስልህ ፣ የልብ ኩራት አለኝ ። የባላባት ልጅ ስለሆንኩ ፣ ወይም መሬት ስላለኝ አይደለም ። እድሜ ላባቴ መሬት ፣ አርሼ እበላለሁ ብለው እንደሚኩራሩት አንዳንድ ሰዎች አይደለሁም ።

«ነፃነት ይሰማኛል ። የሀይለ ስላሴ መንግስት ደግሞ ነፃነት የሚሰማቸውን ሰዎች አይወድም ። እና ፣ ጉዋደኞቼ ሚኒስትሮች ፣ ምክትል ሚኒስትሮች ፣ ረዳት ሚኒስትሮች ሲሆኑ እኔን አልሾመኝም ።

«ከጉዋደኞችህ በታች ሆነህ መኖር ምን አይነት መጥፎ ስሜት እንደሚያሳድርብህ ታውቃለህ ? ከነሱ በጭንቅላት የምትበልጥ መሆንክን እያወክ በራስህ ላይ እምነት ማጣት ትጀምራለህ ። ግን ራስክን አታማርርም ፣ አለምን ታማርራለህ ። መናደድ ፣ መጠጣት ፣ መናገር ትጀምራለህ ፣

ራስክን በገዛ እጅህ እያጠፋህ ስትሄድ ጉዋደኞችህም እየሸሹህ ይሄዳሉ ። ከዚያ እንግዲህ የሚቀርህ ውርደትና ቅሌት ነው ። ይህ ከሚደርስብኝ ብዬ ነው ሸሸቼ የመጣሁት ።

«ግን ችሎታ ያለኝ መሆኔን ማሳየት አለብኝ ። እራዳ ተፍታኝ ወድቄ አልቀርም ። ታያለህ» ብሎት ወለሉን በንዴት ረግጦ ወጥቶ ለመሄድ ወደ በሩ ሲንደረደር፣—

«ቁርስ ለምን አትበላም ?» አለው ።
«በጠዋት እህል አይዋጥልኝም ።»
«የት ነው የምትሄደው ?»
«ወደ መሬቴ . . . »

«ቆየኝ አብረን እንወጣለን ። እኔም የትምህርት ቤቱ ኮሚቴ ስብሰባ አለብኝ ።»

«መንገዳችን የተለያየ ነው» ብሎት እንደ ልማዱ እየተቻኮለ ወደ በሩ ሲሄድ ወይዘሮ ዝናሽና ሸታዬ ወደ ውስጥ ገፍትረውት ተከታትለው ገቡ ።

የሁለቱም ሻሽ ተፈቶአል ። ነጠላዎቻቸውም ከትከሻዎቻቸው ላይ ወርደው መሬት ለመሬት ይጎተታሉ ። ሁለቱም ቁና ቁና ይተነፍሱ ነበር ።

ዝናሽ ሻሽዋን ንያስተካከለች ሀዲስና ታፈስን በአይኖችዋ ከቃኘች በሁዋላ፣ «ደህና ናችሁ ?» አለች በመገረም ።

ሀዲስ ተገርሞ፣ «ምን ነው ? ምን መጣ ?» አሳት ።

«እኛስ ተጋደላችሁ ብለን ደንግጠን ነበር ስንሮጥ የመጣነው» ብላ ሸታዬን በአይኖችዋ ገረፍ አደረገች ።

ሀዲስ ነገሩ ገባውና እየሳቀ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አድርጎ፣ «ለምን እንጋደላለን ?» አላት ።

ታፈስ ሸንጡን ይዞ ከበር ላይ ቁሞ የሚሉትን ያዳምጣል ። ሸታዬ እየሰረቀች በጎን ሁለቱንም ትመለከታለች ። ከሁለቱም ጋር አይን ለአይን ስትጋጭ አንገትዋን ትደፋለች ። ዝናሽ እንደ ልማድዋ አንዴ አስካካች ።

«ምን አሳቀሽ ?» አላት ታፈስ ።

እንደ ገና አስካካችና፣ «ወንድነት የሚባል ነገር መቅረቱ ነው የሚያስቀኝ ። ኤጭ !» ብላ፣ በንቀት እንትፍ አለች ።

ሀዲስ ነገርዋን ቀበል አደረገና፣ «እንዴት ?» አላት ።

«አበስኩ ገበርኩ፣ እቴ ። እንደ ሰራ አይገድል፣ አሉ ። ዱሮ የማንን ሴት ማን ደፍሮ - ምድር ቀውጢ ትሆን ነበር እንጂ ። የሰላ ጩቤ በጠፍ ጫሪታ ጎኳጭ ብሎ ደም ጎርሶ ሲጨልም፣ ጀግና ወድቆ ውሀ ውሀ ሲል፣

ዋ ! እናቴዋ ። አይ ዘመን ! አያልፍ የለምና አለፈ ። አበስኩ ፥ እቴ ። ያ የጀግኖች ዘመን በወንድ አልጫዎች ዘመን መተካቱ ነው የሚያስቀኝ» ብላ አሁንም አስካካች ።

«እንዴተ ?» አላተ ሀዲስ ።

«ወንዱ ምን ደካማ ቢሆን የልብ ኩራት ነበረው ፤ ለሴትም ክብር ይሰጥ ነበር ። የማንን ወንድ ውሽማ ማን ነክቶ ። ኧረ ኤዲ‚የ!» አለች ።

«በሴት ላይ መፋለጥ ከውቤ በረሃ ጋር ሞቶአል» ብሎአት ስአቱን ተመለከተና ትቶአቸው ውልቅ ሲል በር ድረስ ተከትላው ፥ «ሚስቶቻችሁንም ቢወስዱባችሁ እንዲሁ ሳትሉ አትቀሩም !» ብላ አሁንም እንትፍ አለችበት ። ታፈሰ ሲስቅባት ይሰማ ነበር ።

ሀዲስ ሲስቅ አይታው ፥ «አንተን ብሆን አልስቅም ነበር» አለችው ።
«ታዲያ ምን ያደርጋሉ ?» አላት ።
«ታንቄ እሞታለሁ . . .»

«ምን በወጣኝ ። ልንሞትላቸው የሚገባ በህይወት ሌሎች ብዙ ቁም ነገሮች አሉ ። ለሴት ብሎ እንዴት ሰው ይሞታል ?» አላት እየቀለደ ።

«ኤጭ !» ብላ ወደ ሽታዬ ዞረችና ፥ «እኔ አንቺን ብሆን እነዚህን ውሾች ሁለተኛ ዞር ብዩ አላይም ። ዛሬ እንዲህ የሰሩሽ ነገ ቀን ተራ ሳያስገቡሽ አይቀሩም ። አበስኩ ገበርኩ ፥ እቴ ። ይህ እድሜ የሚሉት ጣጣ የማያሳየን ጉድ የለም» ብላው ነጠላዋን መሬት ለመሬት እየጎተተች ስትወጣ ፥ ሽታዬን ያዝ አድርጎ ወደ ሁዋላ አስቀራትና ፥ «አንቺ ላይ ካልተጋደልን ወንድ ላንባል ነዋ !» አላት እየቀለደ — ሀዲስ ።

መልስ አልሰጠችውም ። በንቀት አይን እየተመለከተችው ዝም ብላ ቀረች ።

«ሲያዩሽ የከፋሽ አትመስይም» አላት ።

«እንዴት ማለት?»

«ታፈሰን በማግኘትሽ ።»

አሁንም ዝም ብላ ቀረች ።

«ንገሪኝ እንጂ !» አላት ።

«ሸጋ ነው ። የልብ ያደርሳል» ስትለው ፥ ሳይታወቀው ትከሻዋን ጭምድድ አድርጎ ያዛት ።

«ምን ልትሆን !» አለችው ።

ቅርብ ለቅርብ ሆነው አይን ለአይን ተያዩ ። በእሰዋ አይን ውስጥ ንቀት ፥ በእሱ አይን ውስጥ ንዴት ይታይ ነበር ። ለምን ድንገት እንደ ተናደደ ባይገባውም እዚያው አንቀህ አንደፋድፋት የሚል ስሜት አድሮበት ነበር ።

«እኔ የልብ አላደርስም ?» አላት ።

እጁን ምንጭቅ አድርጋው ወጣች ። ሰድብዋ እንደ ጩቤ ልቡን
ሰንጥቅ አደረገው ። ወይስ ቅናት ነበር ? ውስጡ ባለው በማያውቀው ሌላ
ሰው ላይ ከት ብሎ ሳቀ . . .

የጠዋት ፀሀይ የሳቁን አፀፋ መለሰችለት ። ተንጣሎ የሚታየው
ጥልቅ ሰማያዊ ሰማይ ቢንጠራሩ የሚደረስበት ይመስላል ። ታላቅ ሰአሊ
ለጌጥ ያህል ነካ አድርጎ ያለፋቸው ቅቦች የሚመስሉ ስስ ደመናዎች ከት
ልቁ ሰማያዊ ሰማይ ላይ አልፎ አልፎ ይታያሉ ። ይነፍስ የነበረው ቀዝቃዛ
አየር ዛፎችን ቀና ጎንበስ ፣ እጥፍ ዘርጋ እያደረገ በስልት ያስደንሳል ፤ ሜካ
ውን እያተራመሰ በሹክሹክታ ያናግራል ። በወፎች ዝማሬ ፣ በእንቁራሪ
ቶች ቁርርታ ፣ በጅረቶች ሹዋሹዋቴ መልካው ከሩቅ እንዲያው ያስካካል ፣
እልልታ ያቀልጣል ። ንቦች ከአበባ ወደ አበባ እያመሙ ይበራሉ ። ቢራቢ
ሮዎች ውር ውር ይላሉ ። ተፈጥሮ ሞገሳዊ ውበትዋን ተጎናፅፋ እንዲያ ስራ
በዝቶባት ሲታሽበርቅ በየማሳው የተሰማራው ገበሬ ግን ባንፃሩ የደስታ
መልክ አይታይበትም ፤ ግርና ወተት ይፈስባታል በሚሉዋት አገር ሀዘን
ቤት የተቀመጠ ይመስላል ። ሁሉም የህይወት ጣጣ ትከሻው መሸከም
ያቃተው ይመስል አፍንጫውን ከመሬት ላይ ተክሎ ያዘግማል የታመቀ
ብጭት እየተነፈሰ ። ምድራቱም ጭምር እንዳትከዳው ከመሬት ጋር ተጣ
ቂቆ የሚጎትተው እግሩ አቡዋራ ያቦናል እሱም አቡዋራ መስሎ አቡዋራ
ለብሶ . . .

ገበሬው ሞፈርና ቀንበር እንደሚጎትቱት ከሲታ በሬዎቹ እርፉን
ይዞ በጫእር ይጎተታል ። የቀደደው ፈር መቃብር ሆኖ እዚያው ይውጠው
ይመስል ምድራቱን ትኩር ብሎ እያየ ፣ አፈር ጨብጦ ፣ አፈር መስሎ ፣
አፈር ነክሶ ።

በዚች ምድራዊ ገነት በሆነች አገር ውስጥ ትካዜና ሀዘን አሁን ምን
ይባላል ? ወይስ በገሃነም ነፃነት ይሻል ይሆን ? የተሰበረ ቅስም ፣ የፈሰሰ
ወኔ ፣ የታጠፈ አንጀት ፣ የጎበጠ ጀርባ ፣ አፈርና ላብ ፣ ዋይታና ለቅሶ በዚች
ውብ ፣ ድንግል አገር !

ከል ፣ ማቅ ፣ ቡቱቶ ። እናት አለም አዝናለች ። ልጆችዋ በልባቸው
ደስታ የላቸውም ። እህ—አንቺ የኩሩዎች ፣ የደጎችና የጀግኖች ውብ እናት
አገር ፣ የወላድ መካን የሆንሽ ይመስል ዝምታሽና ሀዘንሽ ለምንድን ነው ?

ሁዲስ እንዲህ ባሳብ ተመስጦ ሲጉዋዝ መንገዱ አልታወቀውም ።
ኮሚቴው ከሚሰበሰብበት ክፍል ሲደርስ ግን አንድም ሰው አልነበረም ።
ሰአቱን ተመለከተ ። ከቀጠሮው ሰአት አስር ደቂቃዎች ያህል ቀደም ብሎ
መድረሱን በመገንዘቡ ቁጭ ብሎ የማስታወሻ ደብተሩን እያገላበጠ ያስብ
ጀመር ። ደቂቃዎች ድንጋይ እንደ ተወረወረባቸው ወፎች ብር ብለው
ሄዱ ። የመጣ ሰው ግን አልነበረም ።

እንደ ገና የእጅ ሰአቱን ተመለከተ ። የሰአት እጆች ቀጭ ቀጭ እያሉ
ሲዞሩ ፣ ሰአት አልፎ ሰአት ሲተካ ፣ ቀን ቀንን ሲወልድ ፣ ወር በወር ሲተካ ፣
ዘመን በዘመን ሲለወጥ . . . ሲሄድ ሰአቱ ቀጭ ቀጭ እያለ . . . ምን ይነግ
ሩን ይሆን ? ምን አቀድክ ? ምን ሰራህ ? የትናንቱን ቀን እንዴት አሳለፍ
ከው ? ዛሬስ እንዴት ይዘሽዋል ? ነገንስ ለራስህና ለሰው ልጅ ምን ታደ
ርገባታለህ ?

ሰው እንደ መሆንህ ፡ በዚህ አለም ታሪካዊ ድርሻህን እየፈፀምክ ነው ፤
ከሆነ አንተ ደስተኛ ነህ ። ማለፊያ ህይወት ኖረሃል ። ሞት ምንህም አይደ
ለም—በስራህ ከሞት በላይ ነህ . . . ።

«ምን ነው ተክዘሃል ?» — ቀውሌ ነበር ።

ሀዲስ ባሳብ ጎዳና ጭልጥ ብሎ ሄዶ ኖሮ «ቀውሌ» ሰላምታ ሲያቀርብ
ለት አልሰማም ነበር ። እንደ መባነን ብሎ ፡ «የቀጠሮ አለማክበር ልማ
ዳችን እያሳሰበኝ ነው» አለው ።

«አዎን ፡ መጥፎ ልማድ ነው» አለውና ረጃጅም ቅልጥሞቹን ዘርግቶ
ቁጭ አለ ።

«ግን መጥፎ ልማድ መሆኑን እያወቅን አናርመውም ። በከንቱ የጠፋ
ጊዜ ብልህ እያደርገንም ፡ እደህይቶን ነው የሚሄደው ። በጊዜው መጠቀም
ያልቻለ ሰው የት ሊደርስ እንደሚችል እኔ እንጃ !» አለ ሀዲስ ሰአቱን
እየተመለከተ ።

«የት ይደርሳል ብለህ ነው ? — ግን ከመቃብር ያልፋል» አለው ።

ሀዲስ ራሱን ነቀነቀና ፡ «አይምሰልህ ። ጊዜ ከኛ ውጭ የሆነ ነገር
አይደለም ። በሚገባ ልንጠቀምበት ከቻልን ከመቃብር በላይ ለመሆን እን
ችላለን ። የሰው ፍፃሜው መቃብር አይደለም» አለው ።

«እንዴት ቢባል ?»

«በስራችን ። የሰው ልጅ በስራው ይኖራል ። ስራን የሚወስነው ደግሞ
ጊዜ ነው ። የሰው ልጅ የጊዜ እስረኛ አይደለም ። የጊዜ ጌታ ነው» አለው ።

ቀውሌ ረጃጅም ቅልጥሞቹን ዘርግቶ ሲያዳምጠው ቆየና ፡ «ካስተማ
ሪነት ይልቅ ደራሲ ብትሆን ይሻልህ ነበር» አለው ።

ሀዲስ መልስ ለመስጠት አላመነታም ፡ «ምን አውቄ ? ምንስ ለማለት?»
ብሎ ንግግሩን ቀጠለና ፡ «የባዶ ቃላት ክምር መፅሀፍ አይሆንም ። ስለ
ህይወት የማውቀው ብዙ ነገር የለኝም ፤ ስለ ድርጊትስ ምን አውቃለሁ ?
እውቀት አለ ድርጊት ካለማወቅ ይቆጠራል ። እና ፡ ስለ ህይወት ሀቅ ምን
አዲስ ነገር ልፅፍ እችላለሁ ብለህ ነው ? ሀቀኛ ደራስያን መፃፍ እያቃታ
ቸው እጅግ የሚጨነቁ ናቸው ይባላል ። ሀቅ ታስጨንቃለች ። ሲፈልጉዋት
ቶሎ አትገኝም ። ከሰው ልብ ጥልቀት ውስጥ ነዋ የምትኖረው ። እና ፡ ስለ
ሰው ምን አውቃለሁ ? ልቤ በቂ ፍቅር የለውም ። ፍቅርንና ተስፋን በሰው
ልብ ውስጥ የሚያሳድሩ ቃላት የሉኝም ። ለራሴ የመንፈስ ጥንካሬ ስለ ሌለኝ
የሰውን ልብ ለማጠናከር አልችልም ። የመንፈስ ድሀ የሆነ ሰው የሚያወ
ርሰው ያንን ድህነቱን ነው ። ደራሲ መሆን አልችልም ። ይልቅ ማስተማሩ
እየጣመኝ ሄዶአል» አለውና ፤ ተማሪዎቹ ከፊቱ ያሉ ይመስል አይናቸን
ከክፍሉ አንዱ ማእዘን ወደ ሌላው እንዳፍታ አንከራተተ ።

«እንዴት ?» አለው ቀውሌ ቅልጥሙን እየሰበሰበ ።
«ተማሪዎችን ከፊቴ ላይ አለምርቄ ይነቃል ።»
«ለምን ?» ብሎ ጠየቀው ።

«ለጋ ህፃናት ከፊቴ ተኮልኩለው ሳይ ፥ እንዴት ልበልህ ? — በውስጣቸው የነገው ብሩህ አለም ይታየኛል ። እና ፥ ከለም መሬት ላይ ፍሬ ስዘራ እያለሁ ። የተዘሩት ፍሬዎች ስር ይዘው ሲያብቡ ፥ በአይኔ ይመጣሉ የአለም አበቦች ። ክፍል በገባሁ ቁጥር ያበባ አትክልቶቹ መሀል የቆምኩ ነው የሚመስለኝ ። ታዲያ የሚገርምህ ነገር ፥ ባሳቤ የሚመጣውና በአይኔ የማየው ነገር እልጣጣም ሲለኝ እናደዳለሁ ። ንድድ እያለኝ እበሳጫለሁ ።»

ቀውሉ ነገሩን አቋዋረጠውና ቅንድቡን ከፍ ዝቅ እያደረገ ፥ «ምን ነው የሚያናድድህ ?» አለው ።

ሀዲስ ጠጉሩን ቆፈር አድርጎ ፥ «የህፃናቱ ጠውልጎ መታየት ነው የሚያናድደኝ ። ሆዳቸው ይጮሃል ። ወስፋታቸው ይንጫጫል ። የረባ ምግብ አያገኙማ ። አብዛኛዎቹ የሚሞቅ ጨርቅ ከጀርባቸው ላይ የላቸውም ። ብርድና ረሃብ ያንቀጠቅጣቸዋል ። ልባቸው እርፎ የሚማሩ አይመስሉኝም ። እና ፥ እጨነቃለሁ ።

«አብዛኛዎቹ በችግር መንገድ ላይ ሲቀሩም ይታየኛል ። እና ፥ ከንቱ ልፋቱ ያበሳጨኛል ። በዚያ ላይ ደግሞ የምናስተምራቸውን ነገር ሳስበው አንዳንዴ ፊቴም ተስፋ እቆርጣለሁ ። ምንድን ነው የምናስተምራቸው ? ያረጀ ፥ ያፈጀ ፥ የሻገተ ግብረገብ ። እንዲህ አይነቱን ጊዜ ያለፈበትን ትምህርት ቀስመው የሚያድጉ ልጆች የህብረተሰቡ ሀቀኛ ዜጋዎች ሲሆኑ እንዴት ይችላሉ ? አለምን እንዳለ አሜን ብለው እንዲቀበሉት ነውኮ የምናስተምራቸው ። ግን የትምህርት አላማ ይህ አይደለም ። ትምህርት ፥ አለምን ለተሻለ ህይወት የምንለውጥበት አይነተኛ መሳሪያ ሲሆን ይገባል። የእውቀት ጥቅሙ ከምን ላይ ነው አለምን እንድንለውጥ የሚያስችለን መሳሪያ ካልሆነ ? በእውነቱ ባስተማሪዎች ላይ ያለውን ሀላፊነት ሲመለከቱት በጣም ከባድ ነው ። የነገውን ትውልድ ፥ የነገውን አለም የመኮትኮት ፥ የማነፅ ሀላፊነት ነው ። እና ፥ ስንቶቻችን ይህን ከባድ ሀላፊነት ለመሸከም የህሊና ዝግጅት አድርገናል ? እኔ በጣም ነው የሚከብደኝ» አለውና ፥ በረጅሙ ተነፈሰ ።

«ግን እድለኛ ነህ ።»
«ለምን?»
«ጭንቀትህ ላንድ አመት ብቻ በመሆኑ ።»

ሀዲስ ቅትክዝ ብሎ ፥ «ማን ያውቃል ?» አለና በአቱን ሲመለከት የሰዎችን መምጣት የሰማ ስለ መሰለው ጆሮዎቹን አቆመ ። እውነትም ሲጠበቁ የነበሩት አስተማሪዎች ነበሩ—ጋሼ ዱቤና የተቀሩት ። ዘግይተው መድረሳቸው ምንም አይነት ስሜት አላሳደረባቸውም ። ያሰቡበትም አይመስሉም ። ነውሩ ከምኑ ላይ ነው ? ዘግይቶ መድረስ የተለመደ አይደል ! ጨዋ ፥ የጨዋ ልጅ ፀሀይ ሞቅ ካለች በሁዋላ አይደል ቀስ ብሎ ወደ አደባባይ ብቅ የሚለው ?

ሁሉም ቭፍራ ስፍራቸውን ከያዙ በሁዋላ ፥ «ዛሬ እንድንሰበሰብ የጠራሁዋችሁ ስለ ኮሚቴአችን ስራ ለመነጋገር ነው ።»

ጋሼ ዱቤ ነገሩን አቋዋረጠውና ፥ «ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ ?» ብሎ ጠየቀው ።

«ባለፉት ጥቂት ቀናት ውስጥ ያልጠበኩት አንዳንድ ነገር በመፈጠሩ ነው» በማለት ንግግሩን ጀመረ ። «ነገሩ ስላሳሰበኝ ነው ። የዚህ ኮሚቴ ስብሳቢ አድርጋችሁ የመረጣችሁኝ እናንተው ናችሁ ። ነገር ግን ለስብሰባ ስትጠሩ አብዛኞዎቻችሁ አትመጡም ። በተለይም ፣ ባለፉት ጥቂት ቀናት ያልሆነ ምክንያት እየፈጠራችሁ መቅረት ጀምራችሁዋል ። በዚህ ሁኔታ የትም ልንደርስ አንችልም ። ማንም ሳያስገድደን ወደን የጀመርነውን ነገር ከግቡ ማድረስ አለብን ። በተግባር ላይ የማናውለው አላማ ፣ አላማ ነው ለማለት አይቻልም ። ችግር ካለ እንወያይበት ። ከሌለም ተባብረን እንስራ። በእውነቱ ፣ እናንተ እንዴት እንደምታዩት አላውቅም እንጂ እያንዳንዳችን ታሪካዊ ሀላፊነት አለብን ። ይህ ትምህርት ቤት ከያንዳንዳችን መስዋእትነትን ይጠይቃል» አለ ።

ክፍሉ ላይ ከባድ ፀጥታ ወደቀ ።

«የማይገባህ ነገር አለ» — ጋሼ ማይዘር ነበር ።

«ምን ?» አለ ሀዲስ ቀና ብሎ ።

« የፖለቲካ ጉድጉዋድ እየተቆፈረልን ነው ያለው » ብሎ ጀመረ — «እስር ቤት ውስጡ ምን እንደሚመስል አይተህ ታውቃለህ ? አታውቅም ። ቁንጫና ቁሀን ፈትፍተውህ አያውቁም ። ሰው በሰው ላይ ተደራርቦ በሚተኛበት ክፍል ውስጥ ጎንህን የምታሳርፍበት አጥተህ በቁምህ እንቅልፍ እያንገላጀጀህ ምትክን የተመኘህበት ጊዜ አላጋጠመህም ። ገለባው ጉሮሮ የሚያደማ የፉርሽካ ዳቦ ፣ ባረረ ዶኬ ፣ እየተናነቀህ ፣ ለመኖር ያህል በልተህ አታውቅም ። ከሰዎች ጋር በሰንሰለት ተቆራኝተህ ስገራ ወጥተህ ታውቃለህ ? አታውቅም» አለና ፣ ኮቱንና ሸሚዙን ከመቅፅበት አውልቆ ወደ ሀዲስ በመዞር ፣ ነብር በንዴት የቡዋጨረው የሚመስለውን ዥንጉርጉር ጠባሳ ጀርባውን እያሳየው ፣ «እንደዚህ ጀርባህ እስኪተላ ድረስስ ተገርፈህ ታውቃለህ ?» ብሎ ጠየቀውና ኮቱንና ሸሚዙን ከመቅፅበት እንዳወለቀ ሁሉ ከመቅፅበት ለብሶ ሲያበቃ ፣ «ከዚች አጭር ህይወት ውስጥ ፣ ደጁ እየናፈቀህ ፣ ላንዲት ደቂቃ ብቻህን ሆነህ የራስክን አሳብ ለማሰብ እየተመኘህ ፣ ብቻህን ስገራ የምትወጣበት ጊዜ እየናፈቀህ ፣ ጥሩ መኝታና ምግብ በአይንህ እየዞረ ፣ ሶስት አመት በእስር ቤት ማሳለፍ ቀልድ አይደለም ። ይህ ጣጣ ሁሉ የደረሰብኝ ለምን ይመስልሃል ? አንድ ቀን በስካር ልብ ፣ 'የሰለሞን ዘር የሚባለው ነገር ተረት ነው' ስላልኩ ብቻ ነው ። ኧረ ስክሬ ነው ብል ማን ሰምቶኝ ! 'ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል ተብዬ' ፍዳዬን ቀመስኩ ። ባንድ ፊት ምትክን እየተመኘህ በሌላ ደግሞ ትንፋሽህ እንዳትወጣ ህይወትን የሙጥኝ ስትላት አበሳው አይጣል ነው ። ያንን ፍዳ እንደ ገና ለመቅመስ አልፈልግም» ብሎ ዝም አለ ።

«የፉርሽካ ቂጣ ! ጎመን በጤና አሉ ። ረሃብን የሚታገስ ሆድ ፣ ጅራፍ የሚችል ጀርባ የለኝም ፣ አቦ» አለ ጋሼ ዱቤ ።

ሀዲስ አንገቱን ደፍቶ ሲያዳምጥ ከቆየ በሁዋላ ቀና በማለት ፣ «ፖለቲካ ፣ ጅኒ የምትሉት ነገር አልገባኝም ። እኛ የተነሳነው አዲስ ትምህርት ቤት ለመስራት ነው ። እዎን ፣ ሀዲስ የሀብታም ልጆች እዚህ ትምህርት ቤት ገብተው እንዳይማሩ እያለ አድማ ያስመታል በመባል ተከስሼ ፖሊስ ጣቢያ ለጥያቄ ተጠርቼ ነበር ። እኔ የሰራሁት የፖለቲካ ወንጀል የለም ፣

እኔ ያልኩት ነገር ቢኖር ፥ 'በፈተና ያለፉ ልጆች ተሰርዘው ፥ የወደቁት አንዳንድ የሀብታም ልጆች ለምን እንዲገቡ ተደረገ?' ነው ያልኩት ። ደግሞም ማንንም ለማሳደም የሞከረ ሰው የለም ።

«ይህ ኮሚቴ የተመሰረተው ለአድማ ሳይሆን ለበጎ አላማ ነው ። የትምህርት እድል ተነፍገው ለሚኖሩ ልጆች ትንሽ የተስፋ በር ለመክፈት ነው» ካለ በሁዋላ ፥ ስሜቱ በሃይል ስለ ገነፈለበት ፥ የተቀመጠበትን ወንበር በቡጢ መታና ፥ «አንዳንድ ምቀኞች በሚያውጠነጥኑት ሴራ መሸበር የለብንም ። የተነሳሳነው ለበጎ አላማ እስከ ሆነ ድረስ ቁርጠን መስራት አለብን ። አላማ ያለው ሰው እስራት ፥ ግርፋት ፥ ረሃብ ፥ ስቃይ ወይም ሞት ምንም አይደሉም ። ከመሞታችን በፊት አስሬ መሞት የለብንም ። ኤጭ ! ምንድን ነው የሚያስፈራን ! ድንቢጥ እንኩዋ ካቅምዋ ልብ አላት ። ሀተታ አላበዛም ። ስራችንን እዚሁ ላይ እናቁም ? ወይስ እንቀጥል ? ውሳኔው የናንተ ነው !» አለና ጠጉሩን ቆፈረ ።

«እንዴ ! የምን ወደ ሁዋላ ማለት ነው !» አሉ አቶ ጣሴ ፥ «ሁላችንም ስንመኘው የነበረ ነገር አይደለም እንዴ ! ምኞት ብቻውን እስከ ዛሬ የትም እንዳላደረሰን አይተናል ። መምህር ሀዲስ እንዳለው ምኞታችንን በእውነት ከልብ የምናምንበት ከሆነ ፥ ወደ ተግባር መለወጥ አለብን ። እስካሁን እርስ በእርሳችን ሆድና ጀርባ ሆነን እንድንኖር የተደረግነው አይበቃንም ወይ ? ጎበዝ ! ለተንኮለኞች በር አንክፈት ። ለበጎ አላማ እንተባበር ። ተንኮለኛው ማን እንደ ሆነ ሁላችንም እናውቃለን ። እኔ በበኩሌ ፥ ከዚህ ልጅ ጋር ተሰልፌን ስራውን እንቀጥል ነው የምለው ።»

እንደ ገና ቤቱ ላይ ታላቅ ፀጥታ ወደቀ ።
«ታዲያስ ጎበዝ !» አለ ጋሼ ታዲያስ ።
«ታዲያ ምን ?» አለው ሀዲስ ።
«እንበተን ወይስ እንቆይ ?»

«ውሳኔው የናንተው ነው ብያለሁ» ብሎት ፥ ሳይወድ በግድ ድምፁን ከፍ አድርጎ ፥ «ለመሄድ የምትፈልጉ ካላችሁ በሩ ክፍት ነው ። ግዴታ የለባችሁም ። በይሉኝታና በፍርሃት ምንም ማድረግ አይቻልም ። ውዴታ ካለ ግን አንዲት ትንሽ ትምህርት ቤት መስራት ቀርቶ ታላቅ ተራራ መፈንቀል ይቻላል» አለ ።

ጋሼ ማይዘር ተነስቶ ወጣ ። ሌሎች ሁለት መምህራን ተከትለውት ወጡ ። 'አለም ምን ጊዜም የቁራጦች ናት !' የሚል አሳብ መጣበት ።

«ታዲያስ ጃል ?» አለ ጋሼ ታዲያስ ።
«ታዲያስ ስራችንን እንቀጥላ!» አለ ሀዲስ ።

አቶ ጣሴ ደጉ ፍዝዝ ብለው ይመለከቱት ነበር ...

ምእራፍ ፯

## ክፍል ፱

ሀምሌ ግም ሲል ፣ ሰማዩ ፊቱን አጥቁሮ ሲያጉረመርም ፣ ደመናው ዝናብ ቁዋጥሮ ሲያንዣብብ ፣ የምድር ማህፀን ሲርስ ፍሬ ተቀብሎ ፍሬ ሊሰጥ፣ በዶፍ ውስጥ ቀና ጎንበስ ይላል - የቡና ገበሬ የቡና ችግኝ ሊያፈላ - ሊተክል ፣ ሊኮተኩት ።

ችግኞቹ ስር ሰደው ስር በመያዝ ቀና ማለት ሲጀምሩ የጎመራ ቀይ የቡና ፍሬ በአይኑ-ህሊናው ከሩቅ እየታየው ተስፋው ያንሰራራል ። እና ፣ ፍሬ የከለከሉትን አሮጌ የቡና ዛፎች እየገነደሰ ይጥላል - እድባርዋ ታውቃለች እያለ - ችግኞቹ አድገው ከሚሰጡት የመጀመሪያ ፍሬ ሸምጥጦ ላድባርዋ ቡን-ቀላ ሊያቀርብ በልቡ ቃል እየገባ ።

የተተከሉት የቡና ችግኞች ስር ይይዛሉ።ህይወት በክረምት ብርድ ተቆራምዳ እያሸለበች ታዘግማለች ። የክረምት ጭጋግና ደመና ለመስከረም ወርቅማ ጮራ ቦታውን ይለቃል ። መሬቱ ጠፍ ብሎ ፣ ሰማዩ ኩል መስሎ ሲንጣለል ፣ ወንዞች እንደ መስተዋት ጠርተው ልጃገረዶች ውበታቸውን ሲያዩባቸው ፣ የቡና ምንጣሮ በደቦ ይጀመራል ። ወንዙ ፣ ሜዳውና ሸንተረሩ በስራ ዘፈኖች ያስተጋባሉ ። ስራው ይፋጠናል ። ስታሸልብ የከረመችው ህይወትም ፍጥነት ትጀምራለች ።

ታህሳስና ጥር ላይ ሱዷ እንጆሪ መስሎ ያሸተ ቡና ጫካ ትሆናለች ። ፍሬአቸው የከበዳቸው የቡና ዛፎች ጡትዋ እንዳጋተ ላም ወይም ቀንዋ እንደ ደረሰ ነፍሰ ጡር ከብደው ይንዠረገጋሉ ። እንጆሪ መስሎ ያሸተው የቡና ፍሬ ያስጎመጃል ። ወፎችና ልጆች ጎምጅተውም አይቀሩ ፤ ከእሸቱ በልተው ፍሬውን ይጥላሉ ። የተጣለውም የቡና ፍሬ ለከርሞ ችግኝ ሆና በየዱሩ ያቆጠቁጣል ። ህይወት ትቀጥላለች ።

ጥር ላይ ከቡና እሸት ጋር የሱዷ ስልተ-ህይወት ይለወጣል ። ቡና ለመሸምጠጥ ፣ ለመልቀም ፣ ለማድረቅ ፣ ለመፈልፈል ፣ ለማጠብና ለመጫን የደቦ ስራ አይበቃም ። በሽህ የሚቆጠሩ ሰራተኞች ያስፈልጋሉ ። ይህንን የሚያውቁ ቦዘኔዎች ከሰባት ቤት ጉራጌ ፣ ከወሎና ከትግራይ በቡድን መጥተው ጊዜያዊ ሰፈር በማበጀት ስራ መጫረት ይጀምራሉ ። ቃላቸው ህግ ስለሚሆን በዋጋ የሚከራከራቸው የለም ። ያሉትን ዋጋ አሜን ብሎ ከመቀበል ሌላ አያዋጣም ። ቡና በጊዜ ተለቅሞ ፣ በጊዜ ገብቶ ፣ በጊዜ መሸጥ አለበት ። የጥር ቡና ገበያ ቆሞ ማንንም አይጠብቅም ።

ዘላን ኮማሪዎችና ሴተኛ አዳሪዎችም የቦዘኔዎቹን እግር ተከትለው መጥተው የሻማ ፣ የኩራዝና የፋኖስ ሰፈር ያበጃሉ ። ያምቡላና ያተላ ሽታ

ሱቋን ማወድ ይጀምራል ። 'እዚህ ቤት ጠላ አለ' በማለት የሚያመለክቱ በእንጨት ላይ የተሰኩ የተጨረማመቱ ጣሳዎች በየደጃፉ ስልፍ ይቆማሉ ። ጠጅ ቤቶችና ጠላ ቤቶች ካፍ እስከ ገደፋቸው በሰው ጢም ብለው ይሞላሉ ። ቡና የሸጠው የፍንጥር ይገዛል ። ቡና የገዛው የፍንጥር ይገዛል ። የከሰረው ተናዶ ይጠጣል ። ያተረፈው ተደስቶ ይጠጣል ። ሁሉም ይጠጣል- ቡና ጀባ፥ ቀሀ ጀባ ፥ የቡናው ሼሀ ዘንግ አደራ እያለ ። ከዘንድሮ የቡና ሰብል መጠንና ዋጋ ሌላ ወሬ አይሰማም ። ሁሉም ስለ ቡና ያወራል ፥ ሁሉም ስለ ቡና ይጠጣል ።

ጉሮሮአቸው የሸረሪት ድር አድርቶ ዝጎ ለደግ ቀን የመስንቆዎቻቸውን ጭራዎች በባህር እጣን ሲያሙዋሹ የከረሙት አዝማሪዎች ፥ ጉሮሮአቸው በጠጅ ርሶ ፥ ግንባራቸው በአረንጉዋዴና በቀይ ብር አጊጦ እንዲያው ማቅራራት ፥ ማስካካት ይጀምራሉ . . .

አበጀሽ ! አበጀሽ! አበጀሽ!

ያገዳ ጥንቅሽ መጠው ያደጉ ቅልብ የሀረር ሰንጋዎች የሚመስሉ የቡና መሬት ባለርስቶች ፥ በቡና ንግድ የከበሩና የወፈሩ ቱጃሮች ፥ ቱባ ቱባ ብር ተሸክመው ገንዘብ የቸገረውን ሰው ከፉቅ የሚያሾቁ አራጣ አበዳሪዎች ፥ ቅልብልብ ደላላዎችና ትእግስት የሌላቸው የጭነት መኪና ባለቤቶች ከዝናሽ ቡና ቤት ይሰበሰባሉ ...

ሆይ ሆይ!
እንደ ሰራ አይገድል!

ከጠዋት እስከ ማታ ጠርሙስ ዊስኪ እያወረዱ መለኪያዎቻቸውን እንስተው ባስቀመጡ ቁጥር የቡናን ዋጋ ከፍና ዝቅ ለማድረግ ይችሉ የነበሩት የቡና ንጉሶች ዘንድሮ የልባቸውን ያደረሱ አይመስሉም ። ካንድ ቦታ ላይ ችግር የፈጠረባቸው አንድ ነገር ያለ ይመስላል ።

አነስተኛ የቡና ገበሬዎች እንደ ዱሮ ከደጃቸውና ከጉዋሮአቸው የሸመጠጡትን ጀንፈል ቡና በስልቻ ይዘው ወደ ገበያ ሲመጡ አይታዩም። እነዚህ አነስተኛ ገበሬዎች በግል ወደ ገበያ ይዘውት የሚያመጡት ቡና ነበር እንደ ምንጭ ከዚህም ከዚያም ተጠረቃቅሞ የቡና ገበያ ባህር ይፈጥር የነበረው ። አሁን ግን ምንጮቹን ምን ነካቸው?

አልፎ አልፎ የታፈሰ ብሩ ስም ከጆሮ ይገባል ። የታፈሰ ስም በተነሳ ቁጥር የፊታውራሪ ተካም ስም አብሮ ይነሳል ።

«ፊታውራሪ በወንድማቸው ልጅ ስም የቡና ንግድ ጀመሩ እንዴ?» እየተባለ ይወራል ።

የታፈሰ ስም ሲነሳ በየቦታው ይሰማ እንጂ እሱ የትም አይታይም ። የቡና ቱጃሮች በእግር በፈረስ ይፈልጉታል ። ደላላዎች ያሳድዱታል ። የማያሳድደው ቱጃር ቡና ነጋዴ አልነበረም ። በእሱ ምክንያት ያንድ ፈረሱላ ቡና ዋጋ በየቀኑ እየጨመረ ከመሄዱም ሌላ በቱጃሮች ላይ ያልታሰበ የመደናገጥ ሁኔታ ፈጥሮ ነበር ። ግን ታፈሰ የትም አልነበረም ። ሀዲስም ፈልጎ ሊያገኘው አልቻለም ።

በቡና ገበያ ትርምስ ውስጥ ማ ማንን ፈልጎ ሊያገኝ ይችላል? ሁሉም ቡና ለመግዛትና ለመሸጥ ይሮጣል ፥ ይጣደፋል ። ለሰላምታ እንኳዋን ጊዜ የለም ። ታዲያ ከዶራ ቡና ገበያ ጋር በብዙ ሰዎች ላይ የሚደርሰው ምሬትና ሀዘንም ያንኑ ያህል ነበር ። ያተረፈው የሚደሰተውን ያህል ያጣውም ያዝናል ።

በክረምቱ ወራት የቤተሰቡን ህይወት ለማዳን ሲል የቡና ዛፎቹን እግር ቆጥሮ የሸጠው ድሀ ገበሬ ፥ ቡና ደርሶ በአበዳሪው በገፍ ተሸምጥጦ ሲወሰድ እየተመለከተ ከዳር ቆሞ ባዶ እጁን በማጨብጨብ የደም እንባ ያለቅሳል ። ያምናው ክረምት ጨለማ ነበር ። የከርሞውም ክረምት ጭላንጭል አያሳየውም ። ለመኖር እንደ ገና መበደር እንዳለበት እያሰበ ከገበያ አፋፍ ላይ ቆሞ የተወለደበትን ቀን ይረግማል ።

አንዳንዶቹም ቡና ሸጠው ያገኙትን ብር ለአራጣ አበዳሪዎች በውድም ሆነ በግድ ያስረክቡና ከእሳት ዳር ተቀምጠው የተራቡና የተራቆቱ ልጆቻቸውን እንባ ባቀረዘዙ አይኖች እየተመለከቱ ጥሬ እንዳጣ ፈረስ እህህ ይላሉ ፡

እምናና ካቻምና የቡና ዛፎችዋን ተስፋ አድርጋ የቆየች ሚስት ዘንድሮ ም እንዳለፈው የመከራ ጊዜ ሁሉ እጅዋ አመድ አፋሽ ሆኖ ሲቀር እያየች የደረቀውን ቡሃቃ ሳትከድን ቤትዋን ጥላ ትጠፋለች ። ውብ ገላዋን የምትሸፍንበት ብጣሽ ጨርቅ ያጣች የደረሰች ልጃገረድ አሁን ካለሁበት መራራ ህይወት የባሰ ምን ሊመጣ? በማለት እድልዋን ለመሞከር ከቡና ጋር ተጭና ትኮበልላለች ። ለፍቶ መና የቀረው የቡና ገበሬ የቤተሰቡን ችግር ዳግመኛ ላለማየት ርጥብ ሳር በጥሶ መንገዱን ርጥብ አድርጊልኝ በማለት አድባርዋን እየተማፀነ ከልጆቹ ጋር በአይኑ ስጋ በደህና አገናኝኝ እያለ የገባን ወንዝ ተሻግሮ ይጠፋል ። ጥር ወር ላይ የቤተሰብ ኑሮ ይላላል ፥ ይናጋል ፥ ይፈርሳል ። ይህ ሁሉ የቡና ማከተሚያ ወግ ይሆናል ። ህይወት ትቀጥላለች ። ስቃይ ይደርሳል ፥ ያልፋል ፥ አዱኛ ይመጣል ፥ ይሄዳል ፤ ደስታ ይገኛል ፥ ይጠፋል ። የከሰረውም ከሰረ ፥ ያተረፈውም አተረፈ ፥ የጠፋውም ጠፋ ። ግን በሰው ልብ ተስፋ አይሞትም ። የከርሞ ሰው ያድርገን ይባላል ። እምናና ካቻምና በክረምት ወራቶች የተተከሉት የቡና ችግኞች ደርሰው ለከርሞ ፍሬ ይሰጡ ይሆናል ። ህይወት ምን ጊዜም ቢሆን አታልፍም—ትቀጥላለች ።

የቡና ቅሽር ብናኝ ሰከን ብሎ የቡና ንግዱም ጋብ ሲል የሱዱ ህዝብ እንግዲህ ከቡና ባሻገር ሌላ ወግ ይሻል ። እንደ መሻቱም ወግ አያጣም— እንደ አዲሱ ትምህርት ቤት ስራና እንደ ፊታውራሪ ተካ ልጅ ሰርግ አይነቱን ይጥልለታል ።

ሀዲስ ሳህሌ እንደ ተመቸው ሰው ወዙ ፍልቅ ብሎ አምሮበታል ። ቀን ከሌት እንቅልፍ አጥቶ ያላንዳች እረፍት ሲሰራ የከረመ ሰው አይመስልም ።

ለአዲሱ ትምህርት ቤት ስራ የሚያስፈልገውን የገንዘብና የማቴሪያል ርዳታ ለመሰብሰብ የተማሪዎች ቀን በአል ፥ የወላጆች ቀን በአል ማዘጋጀት ፥ ተማሪዎችን አስተባብሮ በቡና ለቀማ ስራ ማሰማራት ፤ በሚቻላቸው አቅም ገንዘብ እንዲሰበስቡ ማድረግ ፥ በየቤቱ ፥ በየቀዬውና በየማሳው

እየሄደ አላማውን ማስረዳት ፣ ገበያ በዋለበት ቦታ ሁሉ በመገኘት ርዳታ መለመን ፣ ከድሀ ገበሬዎች በገንዘብ ምትክ ያገኘውን ጆንፈል ቡና ሰብስቦ ገበያ በሚውልበት ቦታ ሁሉ እየሄደ ጉሮሮው እስኪደርቅ ድረስ በመከራ ከር መሸጥ ፣ እንደ ሂሳብ ሹምም ሆኖ ቀን ሲሰራባቸው የዋሉትን የደረሰኝ ካርኒዎች ውድቅት ድረስ ቁጭ እያለ መመርመር ቢኖርበትም፤ ድካም የሚሉት ነገር አይሰማውም ነበር ።

ካርኒውን በተመለከተ ቍጥር አቶ ይርጋ ሲፈጥሩበት የሞከሩት ችግር ትዝ ይለዋል ። ህጋዊ ካርኒ በመንግስት ተፈቅዶ ካልታተመ በስተቀር በት ምህርት ቤቱ ስም ማንም ሰው ከመሬት ተነስቶ የርዳታ ገንዘብ ሊሰበስብ አይችልም ፤ ሁዋላ በሀላፊነት ማን ይጠየቃል? ይህ ካልሆነ በትምህርት ቤቱ ውስጥ የወላጆችም ሆነ የተማሪዎች ቀን በእል ተደርጎ ቀዳዳ ሳንቲም በርዳታ መልክ ቢጠየቅ ውርድ ከራሴ ብለው እሻፈረኝ በማለታቸው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትም ፈርተው ፤ «ነገሩ፤እዚህ ላይ አበቃ» ሲሉት ፦

«ግን ለምን!» አለ ።

«የገንዘብ መሰብሰቢያ ካርኒ ማሳተም ቀላል ነገር አይደለም ። ለመን ገድ ፣ ለክሊኒክ ፣ ለትምህርት ቤት ስራ እያሉ ካርኒ በማሳተም ህዝቡን ዘር ፈው የውሀ ሽታ ሆነው የሚቀሩ ሌቦች እየበዙ ስለ ሄዱ ፈቃድ በቀላሉ አይገኝም ። አቶ ይርጋ የነገሩን አስቸጋሪነት እያወቀ ነው ካርኒ ካልታተመ ሞቼ እገኛለሁ ያለው ። የዋዛ ሰው አይምሰልህ ። የሚሄድበት መንገድ አይ ታወቅም ። አስፈቅዶ ካርኒ ለማሳተም አንድ አመት ይፈጃል ። ካመት በሁዋላ ደሞ አንተ የለህም ። ነገሩ አበቃ ማለት ነው» አሉት አቶ ጣሴ እየ ተቆጩ ።

«ሁዋላ የሚመጣብንን መዘዝ አታውቀውም ። ሳንቲም ሳናነል ትም ህርት ቤቱን ብንሰራም ዘርፈው በልተዋል ተብለን መወንጀላችን አይቀ ርም ። የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል እንዲሉ ፣ ከተወነጀልን በሁዋላ የሚመሰከርብን ይበዛል ። የተዘረጋልን ወጥመድም ይኸው ነው ። እያየን እወጥመድ ለምን እንግባ?» ስላሉት ደረሰኝ ከማሳተም በቀር ሌላ ምርጫ እንዳልነበረው በማወቅ ወደ መቱ ለመሄድ ተነሳ ።

በበራሪ መኪና የገባን ቁልቁለትና ዳገት በጣር ቡዋጦ ወርዶና ወጥቶ ፣ ኖጳን አልፎ ፣ የሶርን ወንዝ ተሻግሮ መቱ እንደ ደረሰ የተንቂዋቂትን አጥን ቶቹን ለመዘርጋት ገና ሲንጠራራ ፣ ታፈሰ ብሩ በብዙ ሰዎች ታጅቦ እየተ ጣደፈ መንገድ ሲያቋዋርጥ ከሩቅ አይቶት ሮጦ ያዘውና ፣ «የት ጠፍተህ ከረምክ ጃል?» ብሎ ጠየቀው ፣ ከጠጉሩና ከቅንድቦቹ ላይ አቡዋራ እያራ ገፈ ።

«አልጠፋሁም ። ስራ በዝቶብኝ ነው ። ከትናንት ወዲያ ነው እዚህ የመጣሁት» ሲለው ፣ እያንዳንድዋ ደቂቃ የምታመልጠው ይመስል ሰአ ቱን እስራ ይመለከት ነበር ።

«ሱዷ አንተን የማይፈልግ የቡና ነጋዴ የለም ።»

«አውቃለሁ ። አፋቸውን ከፍተው ይጠብቁኝ ። እኔ በምፈልገው ጊዜ ፣ ቦታና ሁኔታ ያገኙኛል» ብሎት ሀዲስ በለበሰው አቡዋራ በመገ ረም ፣ «አንተስ እዚህ ምን አመጣህ?»

ሀዲስ አሁንም አቡዋራውን ከላዩ ላይ እያራገፈ መቱ የመጣበትን ጉዳይ ባጭሩ እንዳጫወተው ፣ ታፈሰ እንባ እስኪወርደው ድረስ ሆዱን ይዞ ሲስቅበት ፣ ያጀቡትም ሰዎች ምንም እንኳዋን የተባለውን ነገር ባይሰሙም አብረውት ይስቁ ነበር ።

«እንዲህ የሚያስቅ ነገር ምን አገኘህ?» አለው ፣ አቡዋራም ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር እያደረገ ።

«ታስቃለህ ። ሀይለ ስላሴ ይሙት በጣም ነው የምታስቀው» ብሎት እንደ ገና ሆዱን ይዞ ሲስቅበት ከቆየ በሁዋላ እንባውን እየጠረገ ፣ «ሳይህ ምን ምስል በአይኔ ይመጣል መሰለህ?»

«ምንድን ነው የሚመጣብህ?»

«የጥራጥሬ ክምር በሞላበት ክፍል ውስጥ አንዲት የወደቀች ጥሬ የምትፈልግ አይጥ ምስል እየታየኝ ነው የምስቀው ። አታስቅህም?» ብሎት እንደ ገና ከት ብሎ ሲስቅበት ፣ ትቶት ሊሄድ ሲል ታፈሰ ትከሻውን ይዞ እያቆመው ሰአቱን ተመልክቶ ሲያበቃ ፣ «ስራዬ ብለህ ለያዝከው የእብድ ወይም የሞኝ ፈሊጥ ጊዜ ባይኖረኝም እረዳሃለሁ ። ግን እንደ እውነቱ ከሆነ እንዳንተ ያለ ጭንቅላት ያለው ሰው በእንደዚህ ያለው የቂል ስራ ላይ ጊዜውን በከንቱ ለምን እንደሚያጠፋ አይገባኝም ። የትምህርት ቤቱ ነገር እንደ ውቃቢ በላይህ ላይ ሰፍሮ በሽታ ሆኖብሃል ። ደረስኝ ለማሳተም ፈቃድ አይደለም የምትፈልገው? እሺ ፣ በል ተከተለኝ » ብሎት አጃቢዎቹን ሸኝቶ እየተጣደፈ ሲቀድመው ፣ ከእሱ እኩል ለመራመድ እየሞከረ :-

«በምስራው የማታምን ከሆነ ለምን ትረዳኛለህ?» አለው ።

ታፈሰ በፍጥነት ወደ ፊት እየተምዘገዘገ ፣ «አንተን ለመርዳት ብዬ አይምሰልህ ።»

«ለምን ብለህ ነው ታዲያ?» ብሎ ቆም ሲል ፣

«ገንዘብ ያለውን ሃይል ላሳይህ ብዬ ነው» በማለት ፣ ዞር ብሎ ፣ «ፈቃዱን አግኝተህ ተአምራዊ ትምህርት ቤትክን ለመስራት ትፈልጋለህ አትፈልግም?!» ብሎት ፣ ከጠቅላይ ግዛቱ ትምህርት ቤት ስራ አስኪያጅና ከበጅሮንድ ጽህፈት ቤቶች በመግባት ፣ ግማሽ ሰአት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ተመልሶ ወጥቶ ፣ «አቶ ይርጋ የፃፋብህን ሪፖርት ብትሰማ ፣ የኔ ወንድም ፣ ትምህርት ቤት ማሰራት ቀርቶ አገር ጥለህ ትጠፋ ነበር» ብሎት ፈቃዱን ሰጠው ።

ሀዲስ ፈቃዱን በቀላሉ በማግኘቱ ደስ እያለው ፣ «ምን አሉኝ አባክህ?» ብሎ ጠየቀው ።

«ምን ያላሉህ ነገር አለ!» ብሎት በቀረበበት ክስ ፍንክች ባለማለቱ እየተገረመ ፣ «ዲስፕሊን የጎደለው ፣ ለተማሪዎች አርአያ ሊሆን የማይችል ፣ ላድማ የማይመለስ አደገኛ የፖለቲካ ሰው ነው ፣ የሚል ከባድ ሪፖርት ነው ያቀረቡብህ ።»

የተሰጠውን ፈቃድ በደስታ አገላብጦ እያነበበ ፣ «እንደየእቅማችን ለህዝብ ያሰብነን ግዴታ ለመፈጸም መሞከር አደገኛ የፖለቲካ ወንጀለኛ የሚያሰኝ ከሆነ ምናለ—አይከፋኝም ። ግድም የለኝም ። ይልቅ የሚከፋኝ ባለችኝ ትንሽ አቅም ለዚህ ደግ ህዝብ ምንም ሳላደርግ ብቀር ነው ። ወን ጀል ማለትም እሱ ነው» ብሎት ወረቀቱን በጥንቃቄ አጣጥፎ ኪሱ እየከ ተተ ፣ «ያቶ ይርጋን ክስ እርሳውና ይልቅ ደረሰኙን የት እንደማሳትመው ንገረኝ ።»

«አዲሳባ ነዋ ። እዚህ ማተሚያ ቤት የት አለ? ለዚያውም ገና ሳንሱር ማስደረግ አለብህ»

«አትለኝም!»
«ሌላ ምርጫ የለህም ።»

«ታዲያ ምን ይሻላል?» ብሎ ግራ ሲገባው በማየቱ ታፈሰ «እፋ!» ብሎ ወረቀቱን ተቀብሎት ፣ ዛሬ ወደ አዲሳባ የሚሄድ ሰው አለ ። እሱ አሳትሞ ያመጣልሃል ። ስለ ማተሚያ ዋጋም አትጨነቅ ። የኔ መዋጮ ይሆ ናል ። ለማይረባ ነገር መዋጮ አድርጌ አላውቅም ። ግን ፣ ታሳዝነኛለህ» ብሎት ጥሎት ሲሄድ ሲል ከተል ብሎት ፣ «ምን ስትሰራ እንደ ከረምክ አልነገርከኝም።»

«ጊዜ ሲገኝ ። አሁን ጊዜ የለኝም» ብሎት የመቱን መንገድ አቡዋራ በጫማው እንስቶ እያቦነነ ጥሎት ሄደ ።

ሀዲስ የቀረውን ጊዜ በመቱ ያሳለፈው የሚነበብ ያማርኛ መፅሀፍ በመ ፈለግ ነበር ። መፃህፍት ቤት የሚባል ነገር በከተማው አልነበረም ። ከአ እምሮ ድህነት የከፋ ነገር የለም ። 'በቋዋንቋዋችን የምናነበው ነገር እየፈ ለግን ስናጣ ያሳዝናል ። የሚያሳፍርም ነገር ነው—የሶስት ሺህ ዘመን ታሪክ ተሸክመን ፣ ከማንም በፊት የፊደል ባለቤት ሆነን ፣ የስን ፅሁፍ መናጢ ድሆች ሆነን ስንገኝ!' እያለ ፣ በሚያፈጡበት ብዙ ወጣት ሴተኛ አዳሪዎች እንደ ተከበበ ካንድ ቡና ቤት ተቀምጦ ሲበሳጭ ነበር ፣ አንድ ሱቅ በደረቴ መጥቶ «መፅሀፍ ይገዛሉ?» ብሎ የጠየቀው ።

ሱቅ በደረቴው ከያዛቸው መፃህፍት ውስጥ 'አንድ ለናቱ'፣ 'ቀሪን ገረ መው'፣'የታሪክ ማስታወሻ' የተባሉትን መፃህፍት መርጦ ፣ በዋጋቸው ላይ ክርክር ሳያበዛ ፣ «እነዚህንም እንዳላነበበች ተሰፋ አድርጋለሁ» በማለት የገዛቸው ።

በማግስቱ የመርዳሳ ጅሩን በቅሎ ተከራይቶ ፣ መርዳሳን ፣ «ታዲያ መን ገዱ እንዴት ይዞሃል?» ሲለው :-

እሱም ፣ «ካለሱ ምን ህይወት አለኝ? ህይወት ነው ጌታው» ብሎ ሲመ ልስለት :-

መልሶ ፣ «አይደክምህም ወይ በየቀኑ በዚህ መንገድ ስትመላለስ?»

«ጌታው ፣ ህይወት ራሰዋ አድካሚ ነች ። ከማንከራተት ሌላ ምን አላት ። ተንከራተቺ ያላት ነፍስ ስትንከራተት ትኖራለች» እያለ ከበቅሎ ይቱ እኩል በመሮጥ ይመልስለታል ።

ሀዲስ ድካሙን አይቶ ዋ! ከበቅሎ እኩል ሮጦ ማደር! ብሎ መርዳሳ ከለመዳት ጥላ ስር ላንዳፍታ አረፍ በማለት ከሚያውቃት ምንጭ ቀዝቃዛ ውሀ ሲጎንጭና ከማጅራቱና ከግንባሩ ላይ ውሀ ሲያፈስ እያየው ፣ «እርስህ ብትበላ እኮ ይህ ሁሉ ድካም አይኖርብህም ነበር ።»

መርዳሳ በሀዲስ ሞኝነት እየሳቀ ፣ «በማን እድሌ ጌታው? ድሀ የሚያ ርሰው ቀርቶ ለመቃብሩም ቦታ አጥቶአል ። ቢያርስስ ምን ሊተርፈው፣ ደክሞ ለቀን ጅብ» በማለት እያጫወተው ነበር ጀምበር ሳትጠልቅ ሱዱ የደረሱት ።

ሀዲስ ወደ ቤቱ አልሄደም ። በቀጥታ ያመራው ወደ ፊታውራሪ ቤት ነበር—እንዳላነበበቻቸው ተስፋ አደርጋለሁ እያለ።ትምህርት ቤቱ አጠገብ ሲደርስ ሳያስበው ቆም አለ ። እና ፣ እጆቹን ተመልክቶ መንገዱን ቀጠለ ። ወደ ፊታውራሪ ቤት የሚያወጣውን ዳገት ሲያያዝ ፣ አሁን ምን ሳደርግ ነው የመጣሁት ልል ነው? ምን ምክንያት ይኖረኛል? በማለት ልቡ ቢያመ ንታም እግሩ ይራመድ ነበር ። እንዲሁ እያመነታ ሄዶ ሲደርስ ግቢው ጭር ብሎ አገኘው ። ወደ ሁዋላ የመመለስ ፍላጎቱ ቢበረታም አላስቻለውም ። የመጣው ይምጣ በማለት ቆርጦ ዘው ብሎ ገባ ።

ቀና ሲል አይናለም ከሰገነቱ ላይ ቆማ በምሽት ጀንበር ብርሃን ጋዜጣ ስታነብ አያት ። ልቡ ካለችበት ዘላ ከጉሮሮው ላይ የተወተፈች ይመስል ትንፋሹ ታነቀ ። ጀንበሪቱ ሳትጠልቅ ትንሽ እንድትቆይ ሊማለዱዋት የሚፈልጉ ይመስል ፣ ርግቦች ከጣራው ላይ እየተነሱ ወደ ጀንበርዋ አቅ ጣጫ ይበሩ ነበር ። አይናለምም ነጭ ጉም በመሰለው የሀገር ልብስዋ ነጠላ ዋን ከንፍ አድርጋ እያውለበለበች የምትበር መስላ ትታየው ነበር—ነፋስ የበተነው ጠጉርዋ የምሽት ጀንበርዋን ብርሃን እየጋረደ ። በድኑ ነበር ያንን ስሞተኛ የእንጨት ደረጃ የወጣው ። ደረጃው ሳይሆን ልቡ የሚያቃስት ነበር የሚመስለው ።

«ፊታውራሪ አሉ?»

«የሉም ።»

የት እንደ ሄዱ ለመጠየቅ አልፈለገም ። ፊትዋ ላይ የሚተረማመሰው ፣ የምሽት ጀንቦር ብርሃን የሚመስለው ደም ልቡን አተረማመሰበት ። በሚንቀጠቀጡት ከንፈሮቹ ፣ «ምንድን ነው የምታነቢው?» አላት ፣ አሮጌ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ቅጂ መሆኑን እያወቀ ።

«አሮጌ ጋዜጣ ።»

ኡለም ሁሉ ወደ ሙዚቃ ተለውጦ የእልቂ ወንዝ እየዘፈነ የሚወርድ ፣ ዛፎች እየዘፈኑ ዳንኪራ የሚረግጡ ይመስለው ነበር ።

«አዲስ ጋዜጦች አምጥቼልሻለሁ . . . እ . . . ጥቂት መፃህፍትም ይዤ ልሽ መጥቼ ነበር» ብሎአት ፣ ጋዜጦቹንና መፃህፍቱን ሊሰጣት እሱ ሁለት እጆቹን ሲዘረጋ ፣ እስዋም ለመቀበል እጆችዋን ስትዘረጋለት ፣ ድንገት እጆቻቸው ተያያዙ ።

ኮሬንቲ የያዘው ይመስል መላ ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ ። መፃህፍቱያ ሆኑ ጋዜጦቹ ግራና ቀኝ ከመሬት ሲወድቁ እጆቻቸው እንደ ተቆላለፉ ቀሩ ። ላንዳፍታ አይን ለአይን ተጋጩ ። የንዳድ በሽታ የያዘው ይመስል ሰውነቱ ነደደ ። እጆቹን አልቦት ነበር ። ቀስ ብሎ እጆችዋን ለቀቀ ።

ርግቦቹ ለምሽቱ ጀንበር መልእክታቸውን አድርሰው እየተመለሱ ከጣራው ላይ ይሰፍሩ ነበር ። ጀንበራቱ ግን እያሽቆለቆለች ሄዳለች ። የወደቁትን መፃህፍትና ጋዜጦች አንስቶ ቀና ሲል የጀንበራቱ መልክና አይናለም ፊት ላይ ይተራመስ የነበረው ቀለም አንድም ፣ ሁለትም ሆኖ ተማታበት ። የሚነፍሰው ቀዝቃዛ አየር ጠጉርዋ ውስጥ ገብቶ ይጫወት ነበር ።

መፃህፍቱንና ጋዜጦቹን ሰብስቦ እየሰጣት ፣ «መፃህፍት ማንበብ ደስ ይልሻል?» አላት ።

«አዎን ፣ ከመፃህፍት ሌላ ምን መስኮት አለኝ?» አለችው የመፃህፍቱን አርእስቶች አገላብጣ እያየች ።

«እንዴት?» አላት ።
«መሄጃ የለኝማ ። ምን መሄጃ አለኝ?»
«እንዳላነበብሻቸው ተስፋ አለኝ ።»
«እነዚህንስ አላነበብኩም ። ለመሆኑ ስለ ምንድን ነው የሚናገሩት?»

ደስ እያለውና የሚያልቡትን እጆቹን ሱሪው ላይ እየጠረገ ፣ «ሁለቱ ፣ በቀጥታ የታሪክ መፃህፍት ሲሆኑ አንደኛው ፣‘አንድ ለናቱ’ የተባለው መፅሀፍ ፣ ታሪክም ነው ፣ ልብወለድም ነው» አላት ።

ነፋስ የበትነውን ጠጉርዋን ከፊትዋ ገለል አድርጋ ፣ «እኔ ደስ የሚለኝ ልብወለድ መፅሀፍ ነው ። በተለይ ስለ ፍቅር የሚተርከ ልብወለድ መፅሀፍ በጣም ደስ ይለኛል» ብላው እንደ መተከዝ ካለች በሁዋላ ፣ «ለመሆኑ መቼ ነው የምትመለሰው?» አለችው ።

«ወዴት?»
«ወደ አዲሳባ ።»

«ከሰባት ወር በሁዋላ ነው» ሲላት ፊትዋ ከቃላቱ ጋር ሲጨልም ታየው ።

«ምን ሆንሽ?»

«ምንም ። ጀንበር ልትጠልቅ ስትል ልቤ ያዝናል» አለችው ፣ ፈገግ ለማለት እየሞከረች ። ግን አልሆንላትም ።

«ነገ ተመልሳ ትወጣ የለ?»

«አዎን ። ብቻ ልቤ ማዘኑ አይቀርም» ብላው ርግቦች ሲበሩ በማየትዋ ፣ «እነዚያን ርግቦች ባደረገኝ» አለች ።

በምሽት ጀንበር እንደ ቤተ መቅደስ ጡዋፍ የሚያበሩት ትላልቅ አይኖችዋ ከርግቦቹ ጋር አብረው ይበሩ ነበር ።

«ለምን?» አላት ። በአይኑ አይኖችዋን እየተከተለ ።

«ነፃነት አላቸዋ ። ወደ ፈለጉበት ቦታ ይበራሉ» አለቻው ። አይኖችዋ እንባ ቋጥጥረው ነበር ። እንባዋን እንደ ምንም ውጣ ፤ «እሁድ እሁድ ቤተ ክርስቲያን ለምን አትመጣም?» ብላ ያላሰበውን ጥያቄ ጣለችበት ።

«ምን ላደረግ?»
«ም' ነው ክርስቲያን አይደለህም?»
«ምን እንደሆንኩ አላውቅም።»
«እንዴት?»

«እኔ የማምነው ህይወት ፥ ነፃነትና ደስታን መሻት በሚሉት ሃይማኖት ነው—ሃይማኖት ሊባል የሚችል ከሆነ» አላት ።

«ጥሩ ነው።»
«ምኑ?»

«የምትከተለው ሃይማኖት» ብላው ፥ ተጋልጦ እ... ፅርሀ አርያም ያበራ የነበረውን ደረትዋን በነጠላዋ እየሸፈነች ፥ «ህይወት ሰጥቶ ነፃነት የሚነፍግ እግዜር ደስ አይልም ። ያናድዳል» ስትለው በንግርዋ ተደንቆ ፈዞ ቀረ ።

ከዚያ ቀን ምሽት በሁዋላ እሁድ በደረሰ በማለት ቀኑ መሽቶ አልነጋ፥ ወይም ነግቶ አልመሽ እያለው ሲጨነቅ ነበር የከረመው ። እይደርስ የለ ምና እሁድ እያዘገመ ደረሰ ። ከመቅደሱ ወዲህና ወዲያ ማዶ ሆነው አይና ችዋ እንደ ጥዋፍ እያንቦገቦጉበት ከሩቅ እየተሰረቁ ከመተያየት ሌላ ተገና ኝተው ለመነጋገር እድል አልነበራቸውም ። ልትነግረው የፈለገችውን ነገር ለማወቅ ያደረበት ፍላጎት ስለ ትምህርት ቤቱ ከሚያውጠነጥነው አሳብ ጋር ተደምሮ እረፍት አሳጥቶት ነበር ...

መቱ ሄዶ ከተመለስ ሁለት ሳምንት አልፎታል ። ግን ይጠባበቀው የነበረው ደረሰኝ ታትሞ አልመጣለትም ። ስለሆነም የርዳታ መሰብሰቡን ስራ ለመጀመር አልቻለም ። እና ፥ የአይናለምን አሳብ የማወቅ ጉጉቱ ተወ ማሪ ስቀቀን ሆኖበት ነበር ።

በሶስተኛው ሳምንት መጨረሻ ላይ ደረሰኞቹ ታትመው ሲደርሱት ከደስታው ብዛት ድንጋይ እንደ ተወረወረባት ወፍ ነበር በሮ አቶ ይርጋ ቢሮ የደረሰው ።

አቶ ይርጋ ከቡና ሽያጭ ያገኙትን ብር በር ዘግተው ይቆጥሩ ስለ ነበረ ያለ ቀጠሮ በመምጣቱ ደስ አላላቸውም ።

«ያለ ቀጠሮ አትምጣብኝ ብዬህ አልነበረም! መቼም የዘመኑ ልጆች ካለ እብሪት ሌላ አታውቁም ። የሚነግሩዋችሁን አትሰሙም ። በእብሪት የተሞላው ልባችሁ እያስተውልም ፥ አይሰማም ፤ እያ ይምን ይሉታል ፥ ከፊ ታቸው ተከምሮ የነበረውን ብር ሰብስበው ከጠረጴዛቸው መሳቢያ ውስጥ እየከተቱ ።

ደረሰኞቹን ፊታቸው ቁጭ ሲያደርግ አይናቸውን ለማመን እያቃታ ቸው ፥ «እንዴት በቀላሉ ሊሳካልህ ቻለ ፥ ወዳጄ?» አሉት ብስጭት ብለው፥

«አሁን የርዳታ መሰብሰቡን ስራ ልንጀምር እንችላለን?»
«ርዳታ የሚሰጥህ ካለ ምናለ» ብለው ዝም አሉ ።
«አዎ ። ስራውን የምንጀምር መሆናችንን እንዲያውቁት ነው ።»
ጥርሳቸውን ነክሰው ፣ «ከሆነልህ ምናለ!» አሉት ።

ደረሰኞቹ እጁ ከገቡ ወዲህ የሚያሳስበው ነገር አልነበረውም ። በትም ህርት ቤቱ ስራ እየተጠመደ በሄደ ቁጥር የአይናለም ነገር ካሳቡ እየራቀ ይሄድ ነበር—ተቆርሳ የማትበላ የህልም እንጀራ ፣ እያለ።ታዲያ የሚገርመው ነገር ወዞ ፍልቅ ብሎ ሰውነቱ እንደ ባህር ዳር ቄጤማ እየለመለመ ሲሄድ ይታይ ነበር ።

«ምን አግኝተህ ነው እንዲህ ያማረብህ ፣ ጃል?» አሉት አቶ ጣሴ ፣ በመ ውደድ አይን እያዩት ።

«ተስፋ ፣ ተስፋ ያለመልማል ። የምንጠወልገው ተስፋ ስናጣ ብቻ ነው» አላቸው ።

«አዎን ፣ ተስፋ የህይወት ምግብ ነው» አሉት ።
እየሳቀ ፣ «የሚወዱትም ስራ ከምግብ ይቆጠራል» አላቸው ።

«አዎን ፣ እውነትክን ነው ። እኔም የማላረጀው በዚሁ ምክንያት ነው ። ከማስተማር ይበልጥ ደስ የሚለኝ ነገር የለም» አሉት ።

ታዲያ መንገዱ ሁሉ ቀና ሆኖለት አልነበረም እንዲህ የሚለው ። ርዳታ ለመጠየቅ ሲሄድ ውሾች የሚለቁበት ፣ ወይም የመጣበትን ጉዳይ ካዳመጡ በሁዋላ፣«ሴባ ሁሉ!ምላሳችሁ የመላእክት—ልባችሁ የሰይጣናት። ሌሎች በብጣሽ ካርኒ ሲዘርፉን የከረሙት እነሰንና ነው? ሄደህ ሞኝህን ፈልግ ። ሰው እንዴ ሁለቴ ይታለላል ፣ ምነው ጃል? ለሶስተኛ ጊዜ አይ ታለልም ። የሌባ አይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ» ብለው እየገፈተሩ ከቤ ታቸው የሚያስወጡትም ነበሩ ። ሆኖም እልፍ ሲል ፣ «ለግብር ካልሆነ በቀር መቼም እኛን ዞር ብሎ የሚያየን የለም ። ራሳችንን ካልረዳን ማን ይረዳናል? ያንዳንድ ሰዎች ሌብነት ተስፋ ሊያስቆርጠን አይገባም» ብለው ፣ ቍዋጠ ሮአቸውን ፈተው የተጨማደደች ብር ወይም ነጭ ሽልንግ በእምነትና በተስፋ የሚሰጡት ደግ ሰዎች ሲያጋጥሙት የእሱም እምነት ይጠነክርና ተስፋው ይታደሳል ።

ርዳታ መሰብሰብ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስካጋጠ ሙት ችግሮች አንድ ቀን የደረሰበት ችግርና ያገኘው ልምድ ከሁሉም ይበልጥ ትዝ ይለዋል ።

እለቱ እርብ ነበር ። እኩለ ቀን ሆኖአል ። ከጠራው ሰማይ እንብርት ላይ የተንጠለጠለችው የቀትር ፀሀይ እናት ትወጋለች ። የሚወብቅና እቡዋ ራማ ቀን ነበር ።

ቍጥራቸው ከመቶ የማያንስ ተማሪዎች ከአንድ የቡና ተክል ማሳ ውስጥ ገብተው ፣ ዘፈን እየተቀባበሉ ፣ እየተሳሳቁና እየተንጫጩ እንጆሪ መስሎ የተንዠረገገ ቡና ይሸመጥጣሉ ፣ ይለቅማሉ ፣ ይሸክማሉ ፣ ይገለብ ጣሉ ። እንዲያው ወበቁም ወበቅ ሳይመስላቸው ስራውን ባፍላ ጉልበታ ቸው እንዳንበጣ ይወርዱበታል ። ሀዲስም ከተማሪዎቹ እኩል እየተሩዋሩ ዋጠ ቡና ይለቅማል ፣ ይሸከማል ፣ ያወርዳል ፣ የጠማውን ውሀ ያጠጣል . . . ስራው ላይ የተሰማሩት ጎሀ ገና እንደ ቀደደ ቢሆንም በእንዳቸውም ላይ የድካም መልክ ፈፅሞ አይታይም ።

ሀዲስ በልቡ ወደው የሚሰሩት ምን ቢያደክም ፣ ምን ስቃይ ቢኖርበት ደስ ይላል ፣ ምክንያቱም ፣ ድካሙ ፣ ስቃዩ ፣ ትግሉ ሳይሆን የሚታየው በጉጉት የሚጠብቀው ጣፋጭ ውጤት በመሆኑ ነው ፣ እያለ ሸክሙን አውርዶ ቀና ሲል ፣ ቆንጨራ የያዙ የቀን ሰራተኞች ከጫካ ውስጥ ከየአቅጣጫው ብቅ ፣ ብቅ ፣ እያሉ ሲከቡዋቸው ይመለከታል ። ቀደም ብለው ሁኔታውን የተረዱ አንዳንድ ተማሪዎች ከከበባው አምልጠው እየጮሁ ወደ ከተማ ይሮጣሉ ። ጩኸት የሰሙ ተማሪዎች እየተደናገጡ ከቡና ጫካ ውስጥ ተንጋግተው በመውጣት የተለቀመ ቡና ከሚከምሩበት ገላጣ ስፍራ ላይ ሲሰበሰቡ ፣ የቀን ሰራተኞቹም ቆንጨራቸውን መዘው እየከበቡ ቀስ ብለው እየተጠጉዋቸው ይመጣሉ ።

ቀዝቃዛ ላብ ጀርባውን ሲያስምጠው ይሰማዋል ። የተማሪዎቹ ፣ በተለይም የልጃገረዶቹ፣ ጩኸት እየበረከተ በሄደ ቍጥር ጉልበቱ ጭምር ሲከዳው ይከጅላል ። በኩሊዎቹ አይን ውስጥ ይታይ የነበረው ጥላቻ በልቡ የባሰ ሽብርና ፍርሃት ይለቅበታል ። ለምን እንደሆነ ሳያውቀው ፣ ላንዳፍታ ከመትረየስ ላንቃ ፊት ፀጥ ብሎ የቆመ ያቡን ጴጥሮስ ምስል ይመጣበታል ። ድንገት ድምፁን ከፍ በማድረግ ፣ «ምን ሆናችሁዋል ! እስቲ አንዴ ፀጥ በሉ!» በማለት ተማሪዎቹን ዝም ያሰኛል ።

በቀትር አየር ላይ ከባድ ፀጥታ ይወድቃል ። ድው ድው የሚለው ያባጨፌ ድቤ ሳይሆን ህይወትን የሚማፀን የሰው ልብ መሆኑን ይገነዘባል ።

ሀዲስ ከተማሪዎቹ መካከል ወጣ ብሎ የደረቀውን ጉሮሮውን በትንፋሹ ጠርጎ እየከፈተ ፣ «ወንድሞቼ ፣ ምንድር ነው ከኛ የምትፈልጉት?» በማለት የከበቡዋቸውን ኩሊዎች ይጠይቃል ።

ራሱ ላይ አዳፋ ጨርቅ የጠመጠመ ፣ እጅጉርድ ዝንጉርጉር ሹራብ ያጠለቀ አንድ ጠብደል ሰው ቆንጨራውን ይዞ እንደ ሀዲስ ከኩሊዎቹ መካከል ብቅ በማለት ፣ «እናንተስ እዚህ ምን ታረጋላችሁ!» ብሎ እንደ ነጎድጉዋድ ያጉረመርምበታል ።

ጎልያድ እንደዚህ አይነት አስፈሪ ድምፅ ቢኖረው ኖሮ ፣ ዳዊት ከፊቱ እግሬ አውጪኝ ብሎ በፈረጠጠ ነበር ፣ ይላል ሀዲስ በተሸበረ ልቡ ።

«ቡና ነው የምንለቅመው ። ሌላ ምን እናረጋለን?» ብሎ ይመልስለታል ፣ አይኑን ከቆንጨራው ላይ ሳያነሳ ።

«ዋጋ እየተጫረታችሁ በእንጀራችን መግባት የጀመራችሁት ከመቼ ወዲህ ነው!» ብሎ ቆንጨራውን እያወዛወዘ እንዴ ገና ያንባርቅበታል።

«እነማን?»

«እናንተ ተማሪዎች!»

«እኛ ዋጋ ለመጫረትም በእንጀራችሁ ለመግባትም አይደለም . . .»

«ታዲያስ?!»

«ቡና ለቅመን በምናገኘው ገንዘብ ትምህርት ቤታችንን ለማስፋፋት ነው ። ሌላ አላማ የለንም» ይለዋል ጠጉሩን እየቆፈረ ።

«እኛ የተነገረን ይህ አይደለም!» ብሎ ወደ ሀዲስ ጠጋ ሲል ፣ ሌሎቹም እሱን አይተው የከበባ ቀለበታቸውን ማጥበብ ይጀምራሉ ።

«ምንድን ነው የተነገራችሁ?»

«ዋጋ እየሰበራችሁ ስራችንን ልትቀሙን ተነስታችሁዋል ተብሎ ነው የተነገረን ። እኛ ዋጋ አነስን ብለን የተውነውን ስራ ዋጋ ሰብሮ ማን ወንድ ሊሰራት—አ? ደም ይፈሳል እንጂ!!»

«ማን ነው እንዲህ ያላችሁ?»
«ማን ቢሆን ማ እሱ ምን ያረግልሃል?»

ሀዲስ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር ያደርግና፡ «የሰም ወንድሞቼ፣ የተነገራችሁ ነገር ውሸት ነው ። ቅድም እንዳልኩት የኛ አላማ ትምህርት ቤታችንን ማስራት ነው ። ትምህርት ቤታችንን ለማስራት ያለንን ቁርጠኛነትና በጎ ፈቃድ ለመግለፅ ከህዝቡ መዋጮ መሰብሰብ ብቻ በቂ ሆኖ አላገኘነውም ። እኛም ራሳችን በጉልበታችን ሰርተን ገቢ ለማግኘት በማሰብ ነው ቡና ለቀማ ስራ ላይ የተሰማራነው ። እንድታውቁልን የምንፈልገው ፣ የግል ጥቅም ለመሻት ወይም በእንጀራችሁ ለመግባት አይደለም ይህንን ስራ የጀመርነው ። እናንተ በዋጋ ተጣልታችሁ የተዋችሁት ስራ መሆኑን አስቀድሜ ባውቅ ኖሮ እነዚህን ንፁሃን ወጣቶች እዚህ ጣጣ ውስጥ ባላስገባሁም ነበር ። ጥፋተኛው እኔ ነኝ ። እኔን የፈለጋችሁትን ነገር ልታረጉኝ ትችላላችሁ ። ምንም በደል ያልሰሩትን እነዚህን ንፁሃን ተማሪዎች ግን ተውዋቸው—ይሂዱ» ብሎ ዝም ይላል ።

«ለመሆኑ በስንት ብር ነው የተኮናተራችሁት?»
«ባንድ ሽህ ብር ።»
«እኛ በሶስት ሽህ ብር እምቢ ያልነውን?»

«እንዳልኩዋችሁ እኛ ስራውን የፈለግነው ለጥቅም ብለን አይደለም ።»

አይናቸው ደም ጎርሶ ደም ለብሶ ያፈጡባቸው የነበሩት ኩሊዎች እርስ በእርሳቸው መተያየት ይጀምራሉ ። በቃል የሚለዋወጡት ሀሳብ አልነበረም ። ነገር ግን አንዱ የሌላውን ሀሳብ የሚያነብ ይመስላሉ ። አየሩ ላይ ወድቆ የነበረው ከባድ ፀጥታ የባሰውኑ እየከበደ ይሄዳል ። ነፋሱም ጭምር ፀጥ ብሎአል ። ዛፎች አይንቀሳቀሱም። የቀትርዋ ፀሀይ አትሞቅም—ትበርዳለች ። ሰማዩ ቀጥሎ የሚመጣውን ነገር ለማየት ያልፈለገ ይመስል ጥቁር ዳመና መጥቶ ፀሀይቱን ይጋርዳታል ።

ምን አስበው ይሆን? ልባቸውን ዘልቆ ለማወቅ ያቅተዋል ። ልብ የላቸውም ፣ የህይወት ችግር ልብ ነስቶአቸዋል ፣ ከጭካኔ ሌላ ልብ የላቸውም ፣ እያለ ሲያስብ ፣ አንዱ ከመካከላቸው ወጣ ብሎ እግሩ ስር አስር ብር ይጥላል ። 'ጎሊያድም' ለጥቆ አስር ብር ይጥላል ። የተቀሩት ሁሉ ወደ ፊት እየመጡ አረንጉዋዴ፣ ብጫ ፣ ቀይ ብር እግሩ ስር በሚጥሉበት ጊዜ ፣ ክፋት ካሰበበት ቦታ ደግነት ፈንቅሎ በመምጣቱ ልቡ ክፉኛ ተነክቶ ስለ ሰው ልጅ ያለን አስተሳሰብ ምንኛ ስህተት ነው? እያለ ፈዞ ቆሞ ትኩስ ጣፋጭ እንባ ማንባት ይጀምራል ። በእንባው ውስጥ ከፊቱ ቆመው የሚታዩት የበፊቱ አስፈሪና ጨካኝ የምድር ጎስቋዋሎች ሳይሆኑ የአለም ውብ ሰዎች ይሆናሉ ። የሰው ልብ ከመናኛ ጥቅም በላይ ሲውል የሚጎናፀፈው ግርማ ሞገስና ውበት በእንባው ተፅኖ ይነበብለታል . . . በምስኪኖች ልብና ጎጆዎች ውስጥ የሚኑደው ዘለአለማዊ የደግነት እሳት ላንቃ ከፊቱ እየነደደ ሰማይ

ድረስ ዘልቆ ይንቦገቦጋል . . . ከዋክብትና የምድር አበቦች ወደ ሰው ልጅ ልብ ተለውጠው ሰማይና ምድርን አጊጠው ይታዩታል . . .

«ምንድር ነው! የምን አመፅ ነው ! ምንድር ነው እዚህ በመካሄድ ላይ ያለው!» የሚል ድምፅ ሰምቶ ሀዲስ ከጣፋጭ የቀን ህልሙ ባንኖ ይነቃል ።

የመቶ አለቃ አሽኔ ድምፅ ነበር ። ደመናው ገፎ የቀትርዋ ፀሀይ ብቅ ብላለች ። መቶ አለቃ ሽጉጡን መዞ ይዞ እየተንጎራደደ አይኑን አንዴ ሀዲስ እግር ስር በተቆለለው ብር ላይ ፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ በኩሊዎቹና በተማሪዎቹ ላይ በመወርወር ፣ «ምንድር ነውኮ! ማን ነው የሚያስረዳኝ» ይላል እየደጋገመ ።

ጠብመንጃዎቻቸውን አቀባብለው የደገኑ አራት ፖሊሶች ግራና ቀኝ እያማተሩ አብረውት ይንጎራደዳሉ ። ተማሪዎቹን የቀጠረው የቡናው ባለቤት የእብድ ነጋሪት የሚያከለውን ቦርጩን አንገፍጥጦ የሚያልበውን የተደራረበ ማጅር ግንዱን በዠንጉርጉር መሀረብ እየጠረገ ፖሊሶቹን ተገን በማድረግ ቀጭን እግሮቹን አንፈራኮ ቆሞ ያለከልካል ።

የተማሪዎቹ ወላጆችና ዘመድ አዝማድ ፣ እንዲሁም የደረሰውን ጉድ ለማየት እንዳለ ተገልብጦ የመጣው የሱጴ ህዝብ ትክሻ ለትክሻ ገጥሞ አቡዋራውን ሰማይ ድረስ በማስነሳት እንደ ደራሽ ጎርፍ ወደ ፊት እየተናደ ተማሪዎቹ ወዳሉበት ሲገሰግስ ከሩቅ ይታያል ።

የመቶ አለቃ ቀያይ አይኖቹን ሀዲስ ላይ እያጉረጠረጠበት ፣ «የዚህ ሁሉ ሁከት ምክንያት አንተ ሳትሆን አትቀርምና ብታስረዳኝ!» ይለዋል፣ ከትእዛዝ ጭምር ።

«ምንድን ነው የማስረዳው?»
«ምንድር ነው እዚህ በመካሄድ ላይ ያለው?!»

«እንደምታየው መዋጮ እየሰበሰብን ነው» ይለዋል ሀዲስ ፣ እግሩ ስር የተከመረውን ብር ተመልክቶ እያመለከተው ።

አንዳንድ ኩሊዎች አሁንም መዘዝ ብለው በመውጣት ወደ ፊት እየመጡ በሀዲስ እግር ስር ከተቆለለው የብር መአት ላይ ተጨማሪ ብር ይጥላሉ ።

መቶ አለቃ በገጠመው ነገር ግራ እየገባውና እየተገረመ ፣ «የምን መዋጮ ነው እሱ?» ይለዋል ድምፁን ለስለስ አድርጎ ።

«ለአዲሱ ትምህርት ቤት ማሰሪያ የሚሆን ገንዘብ ነው የምንሰበስበው . . .»

«ከማን?»

ከከተማ ተገልብጦ የመጣው ህዝብ ደርሶ በመገጥገጥ ምድሪቱን አውኗት ይታያል ። ህዝቡ ከነጠመንጃው ፣ ከነጦሩ ፣ ከነሽመሉ ፣ ከነዱላው ፣ ከነአንካሴው ባንድነት ሲታይ ለደመራ ሆ ብሎ የወጣ ይመስላል ። ራሳቸውን ይዘው ፣ «ልጄን! ልጄን!» እያሉ እዩዩአቸውን የሚያቀልጡ ብዙ ሴቶችም ነበሩ ። የተነሳው አቡዋራ ረግቶ ሲመለከቱ ፣ በቆንጨራ ተዘንጥሎ

የተዘረገፈ አንጀት ፡ ወይም ተቀንጥሶ የወደቀ ጭንቅላት ፡ ወይም በተጠማ ምድር ላይ በራሱ የደም ኩሬ ውስጥ የተጋደመ ትኩስ ሬሳ—ምንም አልነበረም ። ዋይታው ወደ ሹክሹክታ ፡ ሹክሹክታው ወደ ዝምታ ፡ ዝምታው ወደ ከባድ ፀጥታ እየተለወጠ ሲሄድ ፡ ሀዲስ ወደ መቶ አለቃ አሸኔ ዞር ብሎ ፡ «ሊያየህ ከማን ብለህ ለምን ትጠይቀኛለህ?» እንዳለው አቶ ይርጋ ፡ ቾርችም ብሎ የቆመውን ህዝብ ጥሰው ገብተው ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ በሚል ትንፋሽ ፡ «አላልኩህም! ምን ብዬህ ነበር!» ይሉታል መቶ አለቃውን ። ላባቸው በማጅር ግንዳቸው ይንቆረቆራል ።

«ምን ብለኸኝ ነበር?» ይላል የመቶ አለቃ አሸኔ ተቆጥቶ ።
«ይህ እንደሚደርስ አስቀድሜ ነግሬህ አልነበረም?»
«ምን ደረሰ?»
«ይህ . . . ያልኩህ . . . ይሄ ነዋ . . .»
«ኧኮ ምን?»

አቶ ይርጋ ግራ ይጋባሉ ። የባሰውኑ ያልባቸዋል ። ከሀዲስ እግር ስር ከተቆለለ ብር ሌላ ምንም አይታያቸውም ።

መቶ አለቃ የአቶ ይርጋን መርበትበትና ግራ መጋባት ተመልክቶ ይስቅና ፡ «ይልቅ አንተም አዋጣ» ብሎ አስር ብር ከኪሱ በመምዘዝ ከሀዲስ እግር ስር ይወረውራል ።

«ምን?»
«ለትምህርት ቤትህ ማሰሪያ ነዋ ።»

እያላባቸው ቀስ ብለው አስር ብር ከኪሳቸው አውጥተው ይጥላሉ ።

ለተማሪዎቹ ስራ የሰጠው ባለርስትም ለመለገስ ከኪሱ ገንዘብ መዘዝ ሲያደርግ የመቶ ብር ቅጠል ይወጣል ፡ ደንግጦ መልሶ ብሩን ይከታል ። አሁንም ሲመዝ የሃምሳ ብር ቅጠል ብቅ ይልበታል ። አሁንም ይደነግጥና መልሶ ብሩን ይከታል ። ለሶስተኛው ጊዜ አስር ብር ሲወጣለት የሻገተ ጥርሱን እያሳየ ከሀዲስ እግር ስር ይጥላል ። ከዚያ በሁዋላ ትእይንቱ ሁሉ ወደ አንድ ትልቅ የመዋጮ በአል ይለወጣል . . .

በዚያን እለት የደረሰውን ታሪክ የሰሙ ሌሎች የቀን ስራተኞች ቡድኖች ሀዲስን ፍለጋ ትምህርት ቤቱ ድረስ እየመጡ የእርዳታ እጃቸውን በደስታ ይዘረጉለት ነበር ።

ችሮታቸው ቀላል አልነበረም ። ለገንዘብ አይሳሱም ። ቡና ይለቅማሉ ፡ ገንዘብ እንዳፈር ይዝቃሉ ፡ ይበላሉ ፡ ይጠጣሉ ። ከቡና ዛፍ ስር ተጋድመው ጠርሙስ ውስኪ የሚጨልጡ ከሩቅ አገር ስንት ወንዝ አቋርጠው የመጡ የቀን ስራተኞች ቍጥር ጥቂት አልነበረም ። ለየትኛው ነገር ብለው? ህይወትም እንደ ጥር ወር አጭር ናት ። ላብዛኛዎቹ ነገ የሚባል ትስፋ የለም። ነገ የራሱ ጉዳይ ነው ። ሲቻል መኖር—ጥር ሲያከትም 'የከርሞ ሰው ያርገን አቦ' እያሉ በየአቅጣጫው ወደየመጡበት የየአገራቸውን ዘፈን እየዘፈኑ ሲሄዱ ፡ ምናልባትም ወደ ባህር እንደሚፈሱ ጅረቶች ዳግመኛ ተመልሰው አይመጡም ይሆናል! ባህር ምን ጊዜም አይሞላም ፡ የታወቀ ስም ፡ ተለይቶ የሚታወስ መልክ የሌላቸው ህይወትን መግበው የሚያልፉ የህይወት ጀግኖች ፡ እያለ ሀዲስ በሀዘን ተሞልቶ ወንዞችን እያቋዋረጠ ፡ ተራ

ሮችን እየወጣና እየወረደ አብሮአቸው ሲጉዋዝ ይቆይና ፣ አደራ ጥለውበት የሄዱ ይመስል ወደ ትምህርት ቤቱ አሳብና ስራ በተጠናከረ መንፈስ ይመለስ ነበር ።

በሚቀጥለው አመት ፣ ጥር ወር ላይ ፣ አንዳንዶቹ የከርሞ ሰው ሆነው ለተለመደው ስራ ፣ በተለመደው መንገድ ፣ የተለመደውን ዘፈን እየዘፈኑ ተመልሰው በሚመጡበት ወቅት ያዲሱ ትምህርት ቤት ስራ ተጠናቆ አገልግሎት ላይ ውሎ ሲመለከቱ ምንኛ ደስ ይላቸው ይሆን? «የዚህ ትምህርት ቤት ስራ ሲጀመር እዚህ ነበርኩ ። ርዳታም ሰጥቻለሁ ። እንዴት መሰለህ ርዳታ ልንሰጥ የቻልነው? ታሪክ ነው እኮ . . .» እያሉ ስለ ትምህርት ቤቱ ሲጨዋወቱ ለምን አይደሰቱም? እነሰም በዛም ባንድ ታሪካዊ ተግባር ውስጥ ታሪካዊ ድርሻቸውን ለግሰዋል ፣ በማለት የቤቱን ፕላን እየተመለከተ አንዳንዴ ያስባቸዋል ።

ግን አሳቡ እዚያው ላይ ተገትቶ አይቆምም ። ያዲሱን ትምህርት ቤት ፕላን በተመለከተ ቍጥር አሳቡ እንደ ንስር አሞራ መጥቆ መብረር ይጀምራል ። አዲሱ ደወል ሲደወል ይሰማል ። ትምህርት ቤት አጥተው በእረኝነት ይኖሩ የነበሩት ህፃናት ደወሉን ሰምተው እየተንጫጩ ተንጋግተው ወደ ክፍል ሲገቡ . . . በጣውላ የተነጠፈው ክፍል በወርቅማ የፀሀይ ብርሃን ተሞልቶ ፣ የተማሪዎቹ ፊትና በክፍሉ ውስጥ የተደረደሩት አዳዲስ ጠረጴዛዎች ፣ ክፍሉን ያጥለቀለቀውን የብርሃን ጎርፍ መልሰው ሲያንፀባርቁ፣ ደስ የሚል ቤት ለደስተኛ ተማሪዎች . . . በአይኑ ይመጣበታል ። እና ፣ ወደ እውነታ ተመልሶ ፣ ፕላኑን ስራ ላይ ለማዋል ያጋጠመውን ያልታሰበ አዲስ ችግር ሲያስብ ይበሳጫል ፣ አንዳንዴም ነገሩ እየገረመው ብቻውን እንደ እብድ ይስቃል ።

ፕላኑ እንከን ኖሮት ወይም ካቅም በላይ ሆኖ ተገኝቶ አልነበረም ። ፕላኑ ችግር አልፈጠረም ። ከብዙ ዘመን በፊት በመሀንዲሶች ተንድፎ ያቶ ይርጋ ቢሮ ግድግዳ ጌጥ ሆኖ የቆየ ግሩም ፕላን ነበር ። የሚሻሻል ነገር ቢኖር ፣ ፕላኑን ለማስፈጸም የሚያስፈልገው ወጪ ከብዙ ዘመን በፊት የተተመነ እንደ መሆኑ መጠን ከጊዜው የዋጋ ሁኔታ ጋር አስተያይቶ የማስተካከሉ ጉዳይ ነበር ። እሱም ቢሆን ተስተካክሎአል ። ከአስራ ሁለት አመት በፊት አርባ ሽህ ብር ይፈጃል ተብሎ የተገመተው ቤት አምስት እጅ ጨምሮ መገኘቱ ሀዲስን ሳያስደንቀው አልቀረም ። ገንዘቡም ችግር አልፈጠረም ። በቂ ገንዘብ ነበር ።

ችግር የፈጠረው ያዲሱ ትምህርት ቤት መሰረት ከየትኛው ቦታ ላይ ይጣል? የሚለው ጥያቄ ነበር ። ከባድ የሆነ የመጨረሻ መሰናክል ።

ያዲሱን ትምህርት ቤት መሰረት ለመጣል የታሰበው ያሁኑ ትምህርት ቤት አቅራቢያ ያለው ትልቁ ወርካ ካለበት ቦታ ላይ ነበር ። በዚህ አሳብ ላይ ለመስማማት የተቻለው ያለ ምክንያት አልነበረም ። አሮጌው ትምህርት ቤት በሚፈርስበት ጊዜ ሰፊ የመጫወቻ ሜዳ ለመስራት የሚያስችል ጥሩ እድል የሚያስገኝ በመሆኑ ነው ። ቦታው የተመረጠው በዚህ ግምትም ብቻ አልነበረም ። አንደኛ ፣ ለተወሰነ ጊዜ ትምህርት መስጠት እንዳይቋረጥ ካልተደረገ በስተቀር ፣ አሮጌውን ትምህርት ቤት አፍርሶ አዲሱን መስራት የሚያዋጣ አማራጭ ሆኖ አልተገኘም ። ለዚያውም ፣ አሮጌው ትምህርት ቤት ዱሮውኑም ቢሆን ጥሩ ቦታ ላይ የቆመ

አልነበረም ። ሁለተኛ ፣ እዚያው አካባቢ ሌላ ቦታ እንዳይመረጥ በቂ ቦታ አልነበረም ። ሶስተኛ ፣ ከዱሮው ትምህርት ቤት ራቅ ብሎ ሌላ ቦታ መፈለግ የማይታሰብ ነገር ሆኖ በመገኘቱ ነበር ። ለትምህርት ቤት የሚሆን ስፊ ቦታ አይኑ እያየ የሚሰጥ ሰው ባሁኑ ጊዜ የት ይገኛል? በቀላሉ ለመ ግዛት ይቻላል ብሎ ማሰብ—ያውም የቡና አገር—ፈፅሞ የሚያዋጣ ነገር አልነበረም ። የህዝብ ገንዘብ ካልሆነ ቦታ ላይ ወስዶ ለማፍሰስ ካልሆነ በስ ተቀር ። ዞር ዞር ወርካው ካለበት ስፍራ ሌላ አማራጭ ቦታ መፈለግ እን ዲያው ቀልድ ነበር ። ግን እንዴት ተደርጎ!

ከብዙም ዘመን ጀምሮ እንደ እግዜር ሲመለክበትና ሲሰገድበት ፣ በየ አመቱ ፣ በተለይም በህዳርና በግንቦት ወራት ፣ ያልተቀጠቀጡ ኮርማዎች ሲጣሉለት ፣ ንፍሮ ፣ ቆሎ ፣ ቡና ጠላና ቂጣ ሲቀርብለት የኖረውን ፣ ደም መረጩትና ቅቤ መቀባት የለመደውን ወርካ ማን አባቱ ደፍሮ ንክች አድ ርጎት!እሱ ምሱን አግኝቶ ካልታረቀ ከገባ በረሃ ዛር ማን ሊያስጥል? የሙ ታንን መናፍስት ማን ሊያስታግስ? ወይም የውቃቢን ቁጣ ማን ሊያበርድ? ወይስ ቆሌዋን ማን ሊያስደስት? ደም ካጣ ፣ ካልሸተተው እጣንና ከርቤ— አቦል ቡና—ማእት—ቁጣው ይወርዳል፣ ወርዶም አያባራ ። ዝናብ ይጠፋል፣ ወንዞች ይደርቃሉ ፣ ከብቶች ያልቃሉ፣ በሽታ ባገር ገብቶ ቀባሪ ይጠፋል— እና ፣ የሴጼ ምድር በሚያቃስቱ የሙታን መናፍስት ትሞላለች ። ያኔ ከወ ርካው ጫፍ ላይ ተጠምጥሞ የሚኖረው ታላቅ ዘንዶ ሲወራጭ ምድሪቱ ትሰነጠቃለች ፣ የአለም ፍፃሜም ይሆናል ! እየተባለ ፣ ወርካው የሰው ልጅ ሳያርፍበት ፣ ደም የለመደውን ግንዱን አወፍሮ ፣ ቅርንጫፎቹን በየአቅ ጣጫው እየዘረጋ ደረቱን ለፀሀይ ገልብጦ ሰጥቶ ዝንተ አለም ይኖራል ። ጊዜው በመለወጡ ነበር እንጂ ጥንትማኮ ካለ ልጃገረድ ደም እርቅ አያወር ድም ነበር ይባላል ። በጣልያን ወረራ ጊዜም ቢሆን የሰው ደም እየጠጣ መኖሩ ይነገራል ።

«ይሂውና! እናንተን ከዘመነ ጨለማ ወደ ስልጣኔ ብርሃን ለማሸጋ ገር የመጣውን ደጉን የሮማን መንግስት አሜን ብላችሁ ባለመቀበላችሁ አድባሩ ተቆጥቶአል ። ሽፍቶችን ይዛችሁ ካላመጣችሁ አይታረቃችሁም ፣ አይን ያለው ይመልከት ፣ ጆሮ ያለው ይስማ ፣ ልብ ያለው ያስተውል ። ጥላ ችሁ ካድባሩ ጋር ነው» እያሉ ፣ ገበያ በዋለበት ቀን ሁሉ የወርካው ሊቀ ጳጳስ ፣ አባ ጨፌ በመስበክ ፣ የተማረኩትን አርበኞች ፣ ወይም ከአርበኞች ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የተጠረጠሩትን ሰዎች ፣ ወርካውን አስደግ ፈው በጥይት አረንዛ ይረሽኑ ፣ ወይም ከወርካው ላይ አውጥተው ይሰቅሉ ነበር—ወርካው ህዝቡን እንዲታረቅ ።

ወርካው ምን ያላየው ታሪክ ይኖር ይሆን? ጊዜን አሻፈረኝ ብሎ ይኖ ራል—ይህ የድንቁርና ዛፍ!

«ምን!ይበጀናል ታዲያ?» አለ ህዲስ ለተሰበሰበው ኮሚቴ ።

መጀመሪያ የተናገሩት አቶ ጣሴ ደጉ ነበር ።

«ቦታው መቼም ላዲሱ ትምህርት ቤት የሰጠ ነበር ።ነገር ግን፣ወርካውን ልንቆርጠው አንችልም ። ቃልቻው ሁሉ ይነሳብናል ። ህዝቡም ቢሆን ደስ አይለውም ። ከሁሉም ነገር ይበልጥ መጠንቀቅ ያለብን ደግሞ ነገሩ ከሰው ጆሮ እንዳይገባ ነው ። ወርካውን መንካት ቀርቶ ፣ እንዲህ ልማድረግ አስበው ነበር ብንባል ፣ ነገሩ ሌላ ትርጉምና መልክ ይሰጠዋል» አሉ ።

«አዎ» አለ ዱቤ ፥ «በሰው አምልኮ መግባት ሁዋላ መዘዙ ብዙ ነው ። በእሳት ባንጫወት ይሻላል ። አቶ ጣሴ እንዳሉት ሴላው ቀርቶ ነገሩን ማን ሳታችን እንኳዋን በኛ መሀል መቅረት አለበት ።»

«እንማማል ነው የምትለው?» በማለት አባ መስጠት ሁሉንም አንጿ አሳቁ ።

«እሺ ፥ ምን እናድርግ አሁን?» አለ ሀዲስ ።

«ከዚህ በፊት እንደ ተነጋገርነው ትምህርት መስጠት ካልቆመ በስ ትቀር አሮጌው ትምህርት ቤት በቆመበት ቦታ ላይ ለመስራት አንችልም ። ሌላ ስፊ ቦታ የሚሰጠን ሰው ደግሞ የለም ። ለማድረግ የምንችለው መንግ ስትን መሬት መለመን ብቻ ነው» አሉ ።

«ጊዜ ይፈጃል!» አለ ሀዲስ ።

«ለምን ፊታውራሪ ተካን መሬት አንለምንም ። ሞልቶአቸዋል» አለ አባ መስጠት ።

«እዚህ ከተማ ላይ ስፊ ቦታ የላቸውም ። ያላቸውንም ሱቆችና ወፍጮ ቤቶች ሰርተውባቸዋል» በማለት አቶ ጣሴ ደጉ መልስ ሰጡት ።

«ታፈሰን ብንለምነውስ?» አለ ሀዲስ ።
«ጠይቄው ነበር» አሉ አቶ ጣሴ ።
«እና?»

«'ድሮ የሰጠሁት መቼ አነሰ' አለኝ ። ችግሩን ባጫውተው ፥ 'ለምን ወርካውን ቆርጣችሁ አትጥሉትም! እኔ እንደ ካራሚሌ የማድለው መሬት የለኝም' ብሎኝ ሄደ» አሉና አጫወቱት ።

«የሰይጣን ጆሮ አይስማው!» አለ ዱቤ ።
«የቱን?» አለ ጋሼ ቀውሌ ።
«ቆርጦ የመጣሉን ነገር!» ብሎ መለሰለት ።

«ይህ ሁሉ ስፊ መሬት እያለ እንዴት እንቸገር!» አለ ሀዲስ ጠጉሩን በንዴት እየቆፈረ ።

«ያለን አማራጭ እንዳልኩት መንግስትን መሬት መለመን ነው ። ለምሳሌ ገበያው የሚቆምበት ቦታ ጥሩ ነው ። ለገበያ ሌላ ቦታ አይጠፋም» አሉ አቶ ጣሴ ።

ኮሚቴው በዚሁ አሳብ ተስማምቶ ተበተነ ። ሀዲስ ግን ፥'ለምን አላፊ ነዳውም!'የሚል አሳብ አድሮበት ነበር ። ውሎ አድሮ ባሰበበት ቁጥር ወር ካውን እንዳለ ከማፈንዳት የተሻለ ዘዴ አላገኘም ። ግን እንዴት? ነገሩ እያ ደረ እንቅልፍ ይነሳው ጀመር ። አንድ ቀን ጠዋት ከቤቱ ሊወጣ ሲል ከታ ፈሰ ብሩ ጋር በሩ ላይ ተገናኙ ።

«የት ጠፍተህ ከረምክ?» አለው ሀዲስ ።

«ስራ ይዞኝ ነው» ካለው በሁዋላ ፣ «ምን ነው የደከምክ ትመስላለህ?» አለው ።

«ኢንቅልፍ አጥቼ ነው . . .»
«ስለ ትምህርት ቤቱ ስታስብ ይሆናላ!»
«መሬት ብትሰጠኝ ኖሮ አላስብም ነበር . . . ።

«ኢንደ ካራሚላ የማድለው መሬት የለኝም ብዬ ላቶ ጣሴ መልስ ሰጥ ቻለሁ ። እዚህ የመጣሁት መሬት ለማደል ሳይሆን ለማልማት ነው ። መሬት ካፒታል ነው ወንድም ። እንዴ የሆነ ሆነና ነው እንጂ አሁን ትም ሀርት ቤቱ ያለበት ቦታም ለስራ ያስፈልገኝ ነበር ። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ያ መሬት ግማሽ ሚሊዮን ብር ያወጣል ። መሬት ጨው እየሆነ በመሄድ ላይ ነው ። የምለው ነገር የሚገባህ ከሆነ» ብሎት ተያይዘው ወደ ቤት እን ደገቡ ፣ «ለማንኛውም ነገር ችግሩ ወርካው ከሆነ ለምን ቆርጠህ አትጥለ ውም» አለው ።

«ኢያሰብኩበት ነው።»

«ምን ማሰብ ያስፈልጋል? ማድረግ ነው ። ድርጊት! ድርጊት ። እኔም ድርጊት ላይ ነበርኩ ። እየሆነልኝ ነው» አለ ።

«ምኑ?»
«በቅርብ ጊዜ ሚሊዮኔር ሳልሆን አልቀርም ። ታያለህ!»
«ኢንዴት ተሳካልህ እባክህ?»

«ድርጊት! ድርጊት! ብዬሃለሁ» ብሎት ፣ ምን ሲያደርግ እንደ ከረመ ያጫውተው ጀመር ።

ታፈሰ ብሩ አዲስ አበባን ለቆ ሲመጣ ከሃያ ሽህ ብር የሚበልጥ ገንዘብ አልነበረውም ። ይህንንም ያገኘው መኪናውንና የቤት እቃውን በመሸጥ ነበር ። አላማው በያዘው ገንዘብ የቡና ችግኝ ገዝቶ ለመትከል ነበር ። ሲያ ስበው ፣ ጊዜ የሚፈጅ ነገር ሆኖ ታየው ። ሚሊዮኔር ለመሆን አምስት ወይም አስር አመት መጠበቅ የሚያዋጣ ነገር መስሎ አልታየውም ። የተ ከላቸው የቡና ችግኞች ገና አድገው ፣ አፍርተው ፣ ተለቅመው—እንዲህ ያለ ትእግስት የለውም ። ስለዚህ አቋራጭ መንገድ መፈለግ ጀመረ ። ጥሩ ዘዴ መጣለት ። የባላባት ልጅ ነው ። ስም አለው ። የታጠቁ ተከታዮች አሉት ። ቢገርፍ ፣ ቢያስር ፣ ወይም ቢገድል ማን ይነካዋል? ማን አባቱ ደፍሮ ከእሱ ፈቃድ ውጭ ሊሆን ይችላል? ከባላባት የመወለድ እድሉንና ሃይሉን መሰረትና መከታ በማድረግ ፣ የታጠቁ አሽከሮቹን አስከትሎ በሱዚ እየዞረ ፣ አነስተኛ የቡና ገበሬዎችን ሲቻለው በማግባባት ፣ ሳይቻ ለው በማስፈራራትና በማስገደድ ሰብላቸውን እሱ በቆረጠው ዋጋ ፣ ያውም በዱቤ በገፍ ይሰበስብ ጀመር ። በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ያብዛኛዎቹን አነስተኛ ቡና ገበሬዎች ሰብል በውድም ሆነ በግድ እጁ ለማስገባት በቃ ። እምቢ በማለት ሲጋፈጡት የሞከሩት አንድ ሁለት አነስተኛ ቡና ገበሬዎች ባልታወቀ ምክንያት በየቦታው ተደፍተው ቀሩ ።

በዚህ ሁኔታ የሰበሰበውን የቡና ሰብል ወዲያውኑ ለቱጃር ቡና ነጋዴ ዎች አሳልፎ አልሸጠም ። ቡና ከገበያ በመጥፋቱ ዋጋው እየተወደደ ሄደ ። የቡና እጥረት ለምን እንደ ተፈጠረ ነገሩን ተከታትለው የደረሱበት ታላላቅ

ነጋዴዎች ታፈስን በእግር በፈረስ ይፈልጉት ጀመር ። በእሱ ምክንያት ኪሳራ የደረሰባቸው አንዳንድ ታላላቅ ነጋዴዎች ሲያጠፉትም ፈልገው አልሆነላቸውም ። ታፈስ የሚያስከትላቸው የታጠቁ አሽከሮቹ ቁጥር ቀላል አልነበረም ። በተለይም ዋና ጣላቶቹ የቡና ደላላዎችና አራጣ አበዳሪዎች ነበሩ ። አንዳንዶቹ የተወለዱበትን ቀን እስኪረግሙ ድረስ ተደብድበው ፣ እንዲሁም አንድ ሁለት የሚሆኑት ደማቸው ደመ ከልብ ሆኖ ስለ ቀረ የሚቁዋቁዋመው ሰው ጠፋ ።

በሱቁ ቡና ንግድ ብቸኛ ሃይል መሆኑን ካረጋገጠ በሁዋላ ፣ ያንድ ፈረሱላ ቡና ዋጋ ስንት መሆን እንዳለበት በስልጣኑ ይደነግግ ጀመር ። ቱጃሮች ፣ እሱ ባለው ዋጋ እጁን ስመው ቡናውን ከመግዛት ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም ።

«እንዳልኩህ ፣ ሀብታም ለመሆን ሁልጊዜ ካፒታል አያስፈልግም» አለው ፣ ነጭ ጥርሱን እያሳየው ።

«ሃይል መጠቀም ነው ዘዴው?»

«አዎ ፣ ኩቲ ኩቲን የምትበላበት አለም ነው ። ይህን መርሳት የለብህም ። በትክክል የሚሰራው ህግ ይኸው ብቻ ነው . . .»

«በዱቤ ቡና የወሰድኩባቸውን ሰዎች ከፍለሃቸዋል ብዬ ተስፋ አደር ጋለሁ . . .»

«እየከፈልኩዋቸው ነው ። በዚህስ አልጠረጠርም ። እጥፍ ድርብ ዋጋ እግኝቼበታለሁ ። አይዞህ ፣ ልብህ አይድማ ። እኔም ባልኖር ፣ አራጣ አበዳ ሪዎችና ደላላዎች ይሜወቱባቸው ነበር ። አታልቅስብኝ ። ልቅሶ የሚያ በዙ ሰዎች አልወድም ። ልቅሶ የደካሞችና የየዋሆች ስራ ነው» አለው ፣

ሀዲስ በጥሞና ነገሩን ሲያዳምጥ ነበረና እንደ ልማዱ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አድርጎ በልቡ ተአምር አያልቅም እያለ ፣ «እንደኛውኑ 'የማፊያ' ስራ ስሰራ ነው የከረምኩት በለኛ!» አለው ።

ታፈስ ኮስተር ብሎ ምንም ሳያመነታ ፣ «ታዲያ ንግድ ምን መስሎህ ኖሮአል? ሀቀኛ ነጋዴ አለ ቢሉህ አትመን ። አልም ያለ ቅጥፈት ነው» ብሎት እንደ ልማዱ በድንገት አቀማመጡን ለውጦ የምፀት ፈገግታ እያሳ የው ፣ «ስማ ሀዲስ ፣ እነዚህን ሞራልና ሃይማኖት የሚባሉትን ነገሮች ለደ ካሞች ተዋቸው ። አለም ምን ጊዜም ቢሆን የሙሴዎችና የጠንካሮች ናት ፣ ሰው መሞቱ ላይቀር ሀሊናና ሀላፊነት በሚባሉት ጣጣዎች ለምን ራሱን ያስጨንቃል? አለም ከንግድ ሌላ ፣ ሌላ ነገር አታውቅም ። እመነኝ ። በድል አድራጊነት ተመልሼ አራዳን ስረግጣት ይታየኛል ። እነዚያን ውሾች ማን እንደ ሆንኩ አሳያቸዋለሁ ። እመነኝ ።

«ስራውን ገና ጀመርኩ ነው ። ለሚመጣው አመት በተሻለ ሁኔታ ስለምደራጅ የበለጠ ትርፍ እንደማገኝ ጥርጥር የለውም ። እንዳልኩህ ይህች አገር ለብልጦችና ለጠንካሮች ብዙ የብር አምባሮች የሚሰበሩባት ድንግል አገር ናት» አለው ።

«የቡና ተከላውን ስራ ተውከው ማለት ነው?»

«ሁሉንም በቅርቡ እጀምራለሁ ። ጭሰኞቹ እንዲለቁ ተነግሮአቸዋል ። ፊታውራሪ ተካ በጣም አዝነዋል ። አይኔን ለማየት አይፈልጉም ። እሳቸው መቼም ያለ ጭሰኛ ትንፋሽ ሊኖሩ የሚችሉ አይመስላቸውም ። አሁንም የሰው ክብሩ ሰው ነው ማለታቸውን አልተውም ። እኔ ደሞ ለጭሰኛ ግድ የለኝም ። መሬቱ ያስፈልገኛል ። ለኔ የሰው ክብሩ ገንዘቡ ነው ፤ ጭሰኛ አይደለም» ካለው በሁዋላ ፣ ሌላ ነገር ትዝ ብሎት ፣ «መሬቱን እየዞርኩ ስጎበኝ ምናገኝሁ መሰለህ? አለም ከተፈጠረች ጀምሮ ያልተነካ ድንግል ደን ። ወይራ ፣ ወርካ ፣ ዝግባና ጥድ ብቻ ነው ። ሰዎች አምጥቼ አስገምቼው ነበር ። ቢሸጥ በጊዜው ዋጋ ስንት ያወጣል አሉኝ መሰለህ? አምስት መቶ ሺ ህ ብር ። ግን አሁን አልሸጠውም ። ካራት አምስት አመት በሁዋላ ፣ ምናልባት ባለኝ ፣ ከሚሊዮን ብር በላይ ያወጣል ። ምን ትፈልጋለህ እንግዲህ? ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ ነዋ! አዲሳባ ላይ የምሰራው ቪላ እና ፣ የማደርገው ፓርቲ ይታየኛል» ብሎት የሀዲስን ፊት በጭሉሌ አይኖቹ ባንዳፍታ አጠናና ፣ «ምን ነካህ?» በማለት ጠየቀው ።

«ሳስብ ነበር ።»
«ምን?»
«በጣም ትልቅ ምኞት ነው ያለህ» በማለት አሾፈበት ።

«ውሻ አትሁን። ገንዘብ፣ ስልጣን ፣ ቤት—ከዚህ የበለጠ በአለም ምን ትፈልጋለህ!» ብሎት ሳቀበትና ፣ «ዳሩ ግን አንተ የምትኖረው በምኞት አለም ውስጥ ነው» በማለት እንደ ገና ሳቀበት ።

«ምናልባት ይሆን ይሆናል ።»
«ለመሆኑ ያ መከረኛ ትምህርት ቤትህ ከምን ደረሰ?»
«ወደ መቆሙ ደርሶአል» አለው ተከዞ ።
«በወርካው ምክንያት?»
«አዎን ።»

ታፈሰ ሩቅ እየተመለከተ ፣ «ታውቃለህ? ስለ እሱ ወርካ የቆየ ትዝታ አለኝ» አለው ።

«የምን ትዝታ?»

ታፈሰ ብሩ ህፃን ሆኖ እልቴ ቅድስት ማርያም ትምህርት ቤት ሲማር ፣ ደፋር መሆኑን ለጉዋደኞቹ ለማሳየት ሲል ፣ ወርካው ላይ የወጡ ልጆች ባጭር ያቀጫሉ ፣ ወይም ወርካው ላይ የሚኖረው ዘንዶ ይውጣቸዋል እየተባለ የሚነገረውን የማስፈራሪያ ቃል ከምንም ሳይቆጥር ፣ ከወርካው ላይ ተንጠላጥሎ ያየው አላፊ አግዳሚ ሁሉ ፣ 'አይንክን ላፈር ያርገው! የሉጲ አድባር እንዳሌች ባጭሩ ትቅጭህ!' እያለ እንዴት ይረግመው እንደነበርና፣ እናቱ ይህን በሰሙ ቁጥር የረገሙትን ሁሉ አስጠርተው ፣ 'ማሩልኝ' በማለት እንትፍትፍ ሲያሰኙበትና ሰዎቹ ከሄዱ በሁዋላ ቅቤ በጠጣ ጉማሬ ፣ 'ሁለተኛ ይለምድሃል?' እያሉ ልቡ እስኪጠፋ ድረስ እንዴት ይገርፉት እንደ ነበረ ካጫወተው በሁዋላ፣ «አባ ሰይጣን የሚለው የቅፅል ስም የወጣልኝ በዚሁ ምክንያት ነው።» በእውነትም የሰይጣን ቁራጭ ነበርኩ ። መቼ ይህ ብቻ መሰለህ? ገበያ በቆመ ቀን ከገበያተኞች ጥንቅሽ እገዳና ሸንኮራ አገዳ እየመዘዝኩባቸው እሮጥ ነበር ። አሁን ሳስበው ይገርመኛል ።

«ግን ቤተሰቦቼን ስለሚፈሩ የሚነካኝ አልነበረም ። ሆኖም ፣ ርግማን የሚደርስ ቢሆን ኖሮ እስካሁን አልተርፍም ነበር ። ይኸውልህ ፣ ጊዜ ይሮጣል ። እና፣ እያንዳንዷዋ ደቂቃ ባለፈች ቁጥር መቃብራችንን እያቀረበች ትሄዳለች ። ሰው የሚቸግረው ነገር ቢኖር ጊዜ ብቻ ነው ። ወርካው ግን ይኖራል ። እኛ ካለፍን በሁዋላ ሁሉ ይኖራል፣ ከኛ በፊት እንደ ነበረ ሁሉ ። እሱን ባደረገኝ» አለ ።

«እኔ ግን ባፈንዳሁትና ከዚህ አለም ባጠፋሁት ነው የምለው» አለ ሀዲስ ፣ ጠጉሩን እየቆፈረና ጥርሱን በንዴት እየነከሰ ።

«ችግር ውስጥ ትገባለህ ። »
«አውቃለሁ።»
«ታዲያ ምን ልታደርግ ነው?»

ሀዲስ በአልክ ትከሻውን ነቀነቀና ፣ «ምናደርጋለሁ? በገዛ እጁ ተገርስሶ እንዲወድቅ ሂጂ እስግድለታለሁ ። ወይፈን እሰዋለታለሁ» ብሎ ቡጢ ጨብጦ እየሩ ላይ ከወረወረ በሁዋላ ፣ «ይገርማል ፣ አንድ የድንቁርና ዛፍ የሰውን ፍላጎት ሲገታ» በማለት ለራሱ አልጎመጎመ ።

ታ ፈሰ የቡት ጫማውን ጫፍ ሲመለከት ቆየና ፣ «አንድ ዛፍ መጣል አቅቶህ ነው እንዲህ የምትጨነቀው?» አለው ።

«ተራ ዛፍ ባለ መሆኑ ነው ።»
«አውቃለሁ ። ግን እንዳልከው ለምን አታፈንዳውም ወኔ ካለህ?»
«ወኔ የማጣት ነገር አይደለም ። »
«ታዲያ ምንድር ነው?»
«ጀብደኛነት የትም አያደርስም ብዬ ነው . . . »

«ቱ! እንግዲያውስ እንዳልከው ሂድና ስገድለት ፤ በገዛ እጁ ይወድቅልሃል ። ግን እኔ አንተን ብሆን የምፈልገውን አደርግ ነበር» አለውና ከተቀመጠበት ድንገት ተስፈንጥሮ ተነስቶ ቆመ ።

«እንዴት? እስቲ ንገረኝ።»
«በእውነት ችግርህ ይኸው ነው?»
«አዎን ። »

ታፈሰ ፀጥ ብሎ ሲያስብ ቆየና ፣ «ስለ ወርካው የልጅነት ትዝታ ብቻ ሳይሆን ቂምም አለኝ ።»

«የቀመስከው ዱላ?»
«እሱም አንዱ ነው ።»
«ሌላው ደሞ ምንድን ነው?»

«ፋሺስቶች አባቴን ሰቅለው የገደሉት ከእሱ ወርካ ላይ ነው» ብሎት ዝም አለ ።

ዝምታ ውጦአቸው አይን ለአይን ተጋጩ . . .

«እናፈንዳዋለን!» ካለ በሁዋላ ፣ ታፈሰ ስይጣናዊ ሳቅ ሳቀና ፣ «ግን አንተን ለመርዳት ወይም ጀል አላማህን ልመደገፍ አይደለም» አለው ።

«ያባትህን በቀል ለመወጣት ይሆናል . . .»
«ለእሱም አይደለም ።»
«ታዲያ ለምንድን ነው?»

«አንድ ነገር ማድረግ ። ራሱ በቂ ምክንያት ነው ። እና ፣ ደግሞ ምንም ፍንጭ ሳይተው ማምለጥ ። ደስ ይላል ። ግን እንዲህ አይነቱ ነገር አንተን አይገባህም ። አሁን እንዲያው በሞቴ ይህ ትምህርት ቤት ምን ጥቅም ይሰጣል ብለህ ነው ጊዜህን በከንቱ የምታጠፋው?» አለው ።

«አንድ ታሪክ ላጫውትህ?»
«እንዲያው ለጫወታ ያህል አጫውተኝ ።»

«አንድ ወጣት መንገደኛ አንድ ቀን አንድ በጣም ያረጀ ሽማግሌ የዛፍ ችግኝ ሲተክሉ ያገኛቸውና 'የምን ችግኝ ነው የሚተክሉት ፣ አባቴ?' ብሎ ይጠይቃቸዋል ። 'ጣፋጭ ፍሬ የሚያፈራ ዛፍ ነው' ይሉታል ። 'ከስንት አመት በሁዋላ' በማለት ሲጠ ይቃቸው ፣ 'ተሰባ አመት በሁዋላ' ሲሉት ወጣቱ በጣም ይገረምና ፣ «ከፍሬው ሳይቀምሱ ምን ያደርግልዎታል? እንዲያው በከንቱ ነው የሚለፉት' ይላቸዋል ። ሽማግሌውም በወጣቱ ነገር ተገርመው ፣ 'አይ ልጄ ፣ እንዳልከው እኔ አልደርስበትም ። ግን ወደዚህ አለም ስመጣ አለም ባዶ አልነበረችም ። እኔም ከሄድኩ በሁዋላ ባዶ አትሆንም ። እኔ ስበላው የኖርኩት ፍሬ አባቶቼ ከተከሉት ዛፍ ነው ። እኔም በተራዬ ለልጆቼ በመትከል ላይ ነኝ' አሉት ይባላል» አለው ።

«ምን ለማለት ነው?»

«ሁላችንም ለግላችን ብቻ ሳይሆን ለህብረተሰቡም ደህንነት ግዴታ አለብን ለማለት ነው . . .»

«የቀሳውስት ስብከት!»

«ደላል አባ ሰይጣን!» አለ ሀዲስ ።

# ክ ፍ ል ፲

ድፍን ሱዴ ቦሮ ከኖጸና ከሱዴ ባላባት ቤተሰቦች ጋብቻ ሌላ ወሬ አል ነበረውም ። ጃኖ ከላያቸው ላይ ጣል የተደረገባቸው የደለቡ ስንጋዎችና የሰቡ ሙክቶች ወደ ፊታውራሪ ተካ ግቢ ሲሳቡ ያየ ሁሉ ፣ ከፊሉ ፣ «አጅሬ መቼም ሁሉን ነገር በጊዜ ነው ። የቀጠሮ ነገር አይሆንላቸውም ። ጠጁ መጣል ከጀመረ መንፈቅ አልፎታል አሉ» ሲል ፣ ሌላው ደግሞ ፣ «እዬ ፣ በድግስስ ፊታውራሪ እያናን የሚያስንቅ በድፍን ኢሉባቦር አይገኝም ። በያመቱ ለህዳር ሚካኤል የሚያደርጉት ድግስ ኧረ ኤዲያ! ሁለተኛ ጮማ ባይኔ አልይ ያሰኛል ። ጠጁስ ቢሆን ፣ እንደ ገባ ወንዝ አይደለም እንዴ ሞልቶ የሚፈሰው ። ልጃቸውን ሲድሩማ ምኑ ቅጡ ፣ አለም ሳያልፍ አይ ቀርም . . .

«ደሞስ የእሳቸው ድግስ በበአል ቀን ብቻ መቼ ሆነና? ቤታቸው ዘወ ትር ሰርግና ምላሽ ነው ። ታዲያ ምን ያደርጋል? ያብሉ ያጠጡ እንጂ ሳን ቲም የምትባል ነገር እንስተው መስጠት አይወዱም ። የገንዘብ ነገር ሲነ ሳባቸው እንደ እግር ውስጥ እሳት ያንገበግባቸዋል» እያሉ በሁለቱ ባላባት ቤቶች ስለሚደረገው የሰርግ ድግስ ዝግጅት ያወራሉ ።

ውስጠ አዋቂዎች ነን የሚሉ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ፣ «ፊታውራሪ እያና ዘወትር የሚያበሉት እኮ ወደው አይደለም ። እህል ስለማይበላላቸው ነው ። ሰው ሲበላ በማየት ነው የሚደሰቱት ። ይህን አታውቁም ኖሮአል? ‘በል እኮ ይህን ጮማ ጨርሰው ። ዱሮውኑ ላትበላ ለምን መጣህ? ይህን ሳትጨርስ ከዚህ ውልፍት ማለት የለም!’ እያሉ ቁ!ቁ! ካላስኙ አይለቁም ። ታዲያ ለራሳቸው ፣ ቁራሽ እንጀራ በወጥ ጥራጊ በድስት ተጠብሶ ካልሆነ በቀር ሌላ ነገር አይበሉም ።

«ስለ ገንዘብ ሲያስቡና ሲጨነቁ ነው የሚውሉት ። አቤት ሰው ሲጠ ራጠሩ! ቤታቸው የሄደው ሁሉ ገንዘብ ሊለምናቸው የመጣ ነው የሚመስላ ቸው ። እና ፣ አስቀድመው ስለ ችግር ማውራት ይጀምራሉ ። ላልጠፉ ሀብት እንዲህ አድርጎ መጨነቅ! የቡና መሬቱ ፣ ሁዳዱ ፣ የእህል ወፍጮ ፣ ሱቅ ፣ የሉካንዳ ቤቱ ሳይቀር የእሳቸው ነው ።

«ሀብታም ባይሰስት ምናለበት?» ብቻ ባይሰስት ኖሮ እንዴት ሀብታም ይሆን ነበር? ነው ጥያቄው ። የገንዘብ ነገር አይሆንላቸውም ። መናጢ ድሀ ይመስል ስለ ችግር ሲያወሩ ነው የሚኖሩት ። ‘ገንዘብ የልብ ስር ነው’ ስለ ሚሉ በር ዘግተው ሲቆጥሩ ነው የሚውሉት ።

«ከልጃቸው ከዳኛቸውም ጋር ሆድና ጀርባ ሆነው የሚኖሩት በዚሁ ምክንያት ነው ። ሲነሳሡት ሽጉጥና ጦር ይመዘብቻቸዋል ። አንዳንዴም

በግድ ይዞ ነው እሉ ሳጥን የሚያስከፍታቸው ። ሰይጣን ነው ። ግን ምን ያድርግ? አላስተማሩት ፣ ስራ የለው ።

«እሱ ግን እንደ እሳቸው አይደለም ። ካባቱ የነጠቀውን ገንዘብ የትም ለማንም እንዳፈር ሲበትነው ነው የሚውለው ። ነጋ ጠባ መጠጣት ፣ መስ ከር ፣ አዝማሪ አቁሞ ማዛፈን ፣ ከበር መልስ መጋበዝ ነው ልማዱ ። ለሰው በጣም የሚያዝን ቦርቡዋሬ ከመሆኑ የተነሳ ፣ ተቸገርኩ ካሉት ሄዶ አባቱን ያንቃል ።

«ካገባ እሱም ምናልባት ይለወጥ ይሆናል ። ጎጂ የስንቱን ጸተኛ ልብ ትሰብር የለ ። እሳቸውም ቢሆኑ ትዳር ከወጣ በሁዋላ በቂ መተዳደሪያ ሳይሰጡት አይቀሩም» በማለት ጉድ ያወራሉ ።

በእድሜ የገፉ ሽማግሌዎች ግን ስለ ሁለቱ ባላባት ቤተሰቦች ጋብቻ አንስተው በሚጫወቱበት ወቅት ደጋግመው የሚጠቅሱት የሁለቱን ቤተ ሰቦች ታሪካዊ ጠላትነት ነበር ። «ያም ሲቃቡ የቆዩት ቤተሰቦች አሁን በጋብቻ ለመተሳሰር የፈለጉት ለምን ይሆን? ጊዜ መቼም የማይሽረው ቁስል የለ ። እድሜ መስተዋት ነው ፣ ብዙ ነገር ያሳያል ። የገባን ወንዝ ልጆች ሲያፋጁ እንዳልኖሩ ሁሉ!» በማለት እየተገረሙ ያለፈውን ታሪክ ያስታውሳሉ ።

ጥንት የፊታውራሪ ተካ አያት ሱዲ ቦሮንና ኖጳን እያስገበሩ በሚገዙ በት ዘመን ፣ የፊታውራሪ አያና አያት ታማኝ ሎሌአቸው ነበር ይባላል ። ተኩሶ የማይስት ክር ከሩቅ የሚበጥስ ጀግና—የጀግኖች መስፈሪያ ቋና ነበር ። ታዲያ ፣ የፊታውራሪ ተካ አያት ጎበዝ ይወዱ ነበርና ከገባ ማዶ ያለ ውን አገር ኖጳን ይሾሙታል ። ጀግንነቱንና ለጋስነቱን በማየት የኖጳ ህዝ ብም አሜን ብሎ በደስታ ይቀበለዋል ። ምክንያቱም የፊታውራሪ ተካ አያት—ሁዳዴን አረስልኝ ፣ የምኖርበት ቤት ስራልኝ ፣ በቤቱ ዙሪያ አጥር አጠርልኝ ፣ ዘመቻ መሄዴ ነውና ከግብርህ በላይ ትርፍ ስጠኝ ፣ ድግስ አለብኝና እርዳኝ፣ እንግዶች መጥተውብኛልና ተቀብለህ አስተናግድልኝ— በማለት የሰው ትከሻ ቀርቶ ምድሪቱ ልትሸከመው የማትችለውን የግፍ ቀንበር ከላዩ ላይ በመጫን ከፉኛ አስመርረውት ነበርና'ነው ። የህዝቡን ምሬት በመመልከትና የራሱንም የስልጣን ጥላንት ለማርካት ግራዝማች ጆቴ ራሱን ፊታውራሪ ይልና ለተድሞ ጌታው አልገብርም ብሎ አሻፈረኝ ይላል ። የሱዲው ባላባትም በዚህን ጊዜ ተናደው ሽፍታ ተነስቶብኛል በማለት ጦራቸውን ከተት ብለው የገባን ወንዝ ይሻገራሉ ። ሁለት ስአት ባልፈጀ ውጊያ እየርከረ የገባን ወንዝ የተሻገረው ጦር ድል ይሆናል ።

ፊታውራሪ ቦሮ ከጥቂት ተከታዮቻቸው ጋር ያመልጣሉ ። ልጆቻቸ ውን ፣ «የኖጳን ነገር እንዳትረሱ» በማለት እንደ ወተወቱ ነበር የሞቱት ይባላል ።

የፊታውራሪ ተካና የፊታውራሪ አያና አባቶችም ፣ ይህንኑ ቂም በቀል በመውረስ ፣ በየጊዜው አንዱ የሌላውን አገር እየወረረ የድህውን ደም በከ ንቱ ሲያፋስሱ ከቆዩ በሁዋላ ነበር በራስ ናደው ዘመን በያዙዋቸው ግዛቶች ክልል ውስጥ በመወሰን ከጦርነት መቆጠብ የጀመሩትና ህዝቡም ሰላም ያገኘው ።

በፊታውራሪ ተካና በፊታውራሪ አያና ዘመን የማእከላዊው መንግስት ስልጣን በይበልጥ እየተጠናከረና እየተስፋፋ በመሄድ፣ ሁለቱም ህዝቡን ለጦርነት መጋበዝ ቀርቶ እንደ ለመዱት ግብር ለመሰብሰብም እድል አልነበራቸውም ። በፋሽስቶች ወረራ ጊዜ ፊታውራሪ ተካ ከራስ እምሩ ሀይለ ስላሴ ጦርና ከጥቁር አንበሳ ጦር ጋር በመቀላቀል አርበኝነት ስለ ገቡና በሌላ በኩል ደግሞ ፊታውራሪ አያና ለወራሪው ጦር ስላደሩ፣ የወራሪው ጦር የበላይ አዛዥ ጄኔራል ጋዜራ የዋሉለትን ውለታ በመቁጠርና ፍላጎታቸውንም በመገንዘብ ሱጲንም ጭምር እንዲገዙ ሾሞአቸው ነበር ። አዝማሪዎች እየቆሙ—

ገባን ተሻግሮ ሱጲን ለማስገበር
ሲናፈቅ የኖረ የቆየ ህልም ነበር
ፍች አጥቶም አልቀረ፣ የማታ የማታ
በዳግማዊ ዮሴፍ ባያና ተፈታ

በማሰኘት መሲንቆ ሲያስመቱ ነበር፣ አምስቱን የወረራ ዘመን ያሳለፉት ...

ባንዲራ ከተመለሰ በሁዋላ ፊታውራሪ ተካም በበኩላቸው ብድር ለመመለስ አዲስ አበባ ድረስ እየተመላለሱ፣ «አያና ለጣልያን ጦር አድሮ ጀግኖችን ሲወጋ የኖረ ባንዳ ነበር» በማለት ክስ ቢያቀርቡም የሚያዳምጣቸው ሰው አልነበረም ። ክሳቸውን የሚያቀርቡት ለቀድሞ ባንዳዎች መሆኑ የገባቸው ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ነበር ። እንዲያውም ይግረምዎት ተብሎ ሳይሆን አይቀርም ከጥቂት ወራት በሁዋላ ፊታውራሪ አያና የውስጥ አርበኛ ነበሩ ተብለው፣ ማእረጋቸው እንዲፀናላቸው ተደርጎ ካባም ጭምር ተሸለሙ ። ያኔ ነበር ፊታውራሪ ተካ፣ «ኢትዮጵያ አገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ፣ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ... ስደትም ለወሬ ያመቻል አሉ» ብለው ዝም ማለትን የመረጡት ። ፊታውራሪ አያናም የገንዘብን ጥቅም በይበልጥ የተረዱት ያኔ ነበር ይባላል ።

ታዲያ ይህ ሁሉ በመካከላቸው እያለ አሁን ከመሸ ጋብቻ ለመሆን የፈለጉት ለምን ይሆን? የሚለውን ጥያቄ እያነሳ ነበር ሁሉም ቡና የሚያንቃርረው ። እርገጠኛው መልስ ይህ ነው ብሎ የሚናገር አልነበረም ። የባላባቶችን ምስጢር ማን ያውቃል? ምናልባት እነሱ የዘመናቸው የመጨረሻዎቹ ትውልድ መሆናቸውን በመገንዘብ በመካከላቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ የቆየውን የጥላቻ ታሪክ አጥፍተው በፍቅር ለመተካት ይሆናል—ከዘመናቸው ጋር ከሞት አፋፍ ላይ የቆሙ ሰዎች የመጨረሻ ኑዛዜ !

ሀዲስ ስለ ሰርጉ በሄደበት ቦታ ሁሉ ይሰማ ነበር ። በደረሰበት ቦታ ሁሉ ከእይናስም ሰርግ ሌላ ከጆሮው የሚገባ ወሬ አልነበረም ። ንፁህ አየር ለመተንፈስ ወደ መስክ ወጣ በሚልበትም ጊዜ እረኞች በየአፋፉ ላይ ቆመው —

እዚህም ተደገሰ እዚያም ተደገሰ
የቆየው ጥላቻ በፍቅር ፈረሰ
የተጣለውም ዳስ እየሰፋ ሄደ
የሚጠራኝ አጣሁ ሆዴ እየወደደ
ሽ_ እየታረደ ባይናለም ስናይ
የድሀ ልጅ ጮማ ቆርጦ ያቃል ወይ?

አሸከርስ በቅቤ በልቶ ያቃል ወይ?
አሆ ጉማ ፣ የደም ጉማ ፣ አሆ ጉማ ፣ አሆ ጉማ!

እያሉ በመዝፈን መልካውን እያናገሩ ያሽሹታል ። እንሶስሳ ሞቀው ፥ ሳዱላቸውን አሳምረው ፣ አሸንክታባቸውን አጥልቀውና የክት ልብሳቸውን ለብሰው ከፊታውራሪ ግቢ ዘወትር ምሽት ላይ በመሰብሰብ ድቤ እየመቱ፡ ቀደም በማለት የሰርግ ዘፈን መዝፈን የጀመሩት የሱጴ ልጃገረዶች ውድቅት ድረስ አያስተኙትም ። እንቅልፋን እያባረሩበት በግድ ስለ አይናለም እንዲያስብ ያደርጉታል ። ከቤተ መቅደስ ውስጥ ቆማ ድርገት ከመውረዱ በፊት ቅዳሴው እጅግ በሚደምቅበት ወቅት ፣ አይኖችዋን እንደሚንቦገቦገው የቤተ መቅደስ ጡዋፍ እያንቦገቦገች ጉም መስሎ በሚንሳፈፈው የእጣን ጢስ ውስጥ ስትመለከተው በአይኑ ትመጣለች ። ብጫ ፣ ሰማያዊና ቀይ ቀለሞች በተቀባው የቤተ መቅደስ መስኮት ውስጥ ተሰርቃ የገባችው የጡዋት ጮራ ፊትዋ ላይ ባረፈች ጊዜ ከድንግል ማርያም ስእል ጋር መልክዋ ሲማታበት ትዝ እያለው እንቅልፍ አጥቶ ከደረቅ አልጋው ላይ ይገላበጣል ። አንድ ነገር ልታዋየው እንደ ፈለገች ልቡ ያውቃል ። ምን ይሆን? በማለት በደረቅ ሌሊት እንቅልፍ አጥቶ ይጨነቃል ። የልጃገረዶቹ ዘፈን ከሩቅ ሲሰማ ተስፋ ይቆርጥና በትምህርት ቤቱ ስራ መፅናናት ሲጀምር የወርካው ጥላ መጥቶ ጥቁር ግርዶሹን ይጥልበታል ። ታፈስ ብሩን ምን እንደ ዋጠው አይታወቅም ። እንደ ልማዱ ጠፍቶአል ። እና ፣ ወርካው አሁንም ግርማ ሞገሱ የሆነውን ደረቱን ወደ ሰማይ ገልብጦ ፀሀይ በመሞቅ ላይ ይገኛል ። እና ፣ ሀዲስ ስራ በመፍታቱ ያዝናል ። ጊዜ ይበራል ። ጊዜ እሱን ጥሎት ለመብረር የተነሳ ነበር የሚመስለው ።

በዛሬው ምሽት እንደ ሌሎቹ ምሽቶች እምብዛም አልተጨነቀም ። ዘንድሮ ቦና ሊሆን ነው ሲባል ድንገት የመጣው የበልግ ዝናብ በሃይል ይወርድ ስለ ነበረ የልጃገረዶቹ ዘፈን አይሰማም ። ያባ ጩሬም ድቤ ያለ ወትሮው ፀጥ ብሎ ነበር ። ዋሽንት ተጫዋቹም ድምፁን ካጠፋ ሰንብቶአል ። የሚወርደው ዶፍ የቤቱን ቆርቆሮ ሲያናግር ብቻ ነበር የሚሰማው ። ዝናብ ከሀዘን ጋር የተቀላቀለ አንድ አይነት ልዩ ስሜት ይሰጠዋል ። ዝናብ ሲወርድ በሚሰማበት ጊዜ አንድ አይነት የሀዘን ሙዚቃ ከልቡ ውስጥ ፈልቆ መንቆርቆር ይጀምራል ። ባጭር የተቀጨ ፍቅር እንባ ወይም ሞልቶ የፈሰሰ የግፍ ፅዋ ወይም ህይወት የተጠማ ሰው ምስል ይመጣበታል ። እና ፣ ሹዋ እያለ የሚወርደው ዝናብ እያባበለውና ሆዱን እያባባው ወደ እንቅልፍ አለም ይዞት ጭልጥ ይላል ።

ሀዲስ ጡዋት የነቃው እንቅልፋን ጠግቦ ነበር ። ውብ የሆነች የጡዋት ፀሀይ ወጥታለች ። ሰማዩ የጠራ ሰማያዊ ነበር ። ከሳር ስለት ላይ ኮለል ብለው የሚታዩት ጤዛዎች የተዘሩ አልማዞች ይመስላሉ ። ዝናብ ሲያጥበው ያደረው አየር ቀዝቀዝ ከማለቱም ሌላ አቡዋራ አቡዋራ አይሸትም ። የዱር ፣ የበረሃ ሽቱ ነበር የሚነፍሰው ። እያፏዋጨና እጆቹን እያሻሸ ከመስኮቱ ላይ ዞር ብሎ የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎችን ደብተሮች ማረም ጀመረ ። አርብ ፣ አርብ የሙከራ ፈተና ለተማሪዎች መስጠት ይወዳል ። ታዲያ አርብ በደረሰ ቍጥር ተማሪዎቹ ፡—

ሀዲስ የሚባለው አዲሱ መምህር
አርብ አርብ ያሸብራል የሱጴን አድባር

እያሉ ይ፣.ፍንበታል ።

የማረሙን ስራ ትንሽ እንዳካሄደ የመኪና ድምፅ ይሰማል ። ጎማዎቹ በወፍራም ሰንሰለቶች የታሰሩ በጭቃ የተለወሰ ላንድሮቨር መኪና ነበር ። ላንድሮቨሩ መጥቶ ከደጁ ሲቆም ነበር በውስጡ የነበረው ሰው ታፈስ ብሩ መሆኑን ያወቀው . . . ታፈስም እንደ መኪናው በጭቃ ተለውሶ ነበር . . .

«አንተ መቼም ጭራው የማይያዝ ሰው ሆነሃል ። ደሞ የት ጠፍተህ ከረምክ?» አለው ።

«አዲሳባ ።»
«ምን ልታደርግ?»
«ይህችን መኪና ልገዛ . . .»
«ለምን ብለህ?»
«ለፍጥነት ። የንግድ ስራና ፍጥነት ሊለያዩ አይችሉም ።»
«አዲሳባ እንዴት ናት?»
«አየሩ ደስ አይልም ።»
«እንዴት?»

ታፈስ በቀረበለት ውሀ ጭቃውን ከእጁ ላይ እያጠበ ፣ «አራዳ ላይ የሚነፍሰው የፖለቲካ አየር ፈፅሞ ደስ አይልም ። ሰው ሁሉ የሚያወራው በየቀኑ እየናረ ስለሚሄደው የኑሮ ውድነት ነው ። ወሎም ረሃብ ገብቶ ህዝቡ በመሰደድ ላይ ነው ይባላል ። በተለይም ነገሌ ያለው ጦር በማጉረምረም ላይ ነው እየተባለ ሰው ሁሉ ውስጥ ውስጡን ይንሾካሾካል ። የመንገደኛው አይነ ውሀ ደስ አይልም ። አንድ አይነት የእምቢተኛነት መንፈስ ይታይበታል ። የጎሪጥ ነው የሚያይህ ። በመኪና የሚሄድ ሰው ሲያዩማ ይብስባቸዋል ። የሆነ ነገር ከስር እየፈላ ነው ። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም ያው አመታዊ በሽታቸው እያገረሸባቸው ነው» ብሎት ፣ ግድግዳ ላይ በተሰቀለው የፊት መስተዋት መልኩን ጠጋ ብሎ በማየት ቅልተው የሚታዩትን አይናቹን ካባበሰና እኝ ብሎ ጥርሶቹን ካየ በሁዋላ ፣ «ያዲሳባ የምሽት ህይወት ግን አልተለወጠም ። እንዲያውም ይባስ ብሎ ተጡዋጡፎአል ። አስረሽምችው ነው በየቦታው ። ከተማው በሙሉ 'ጉብልዬ ጉብልዬ' 'ሸጋው በላይዩ' 'አሰምዬ' ሳቢዬ' 'ወገኔ' እያለ ነው ሲዘፍን የሚያድረው አቦ—ሚኒስትሮቹም ጭምር ።

«የሀገር ምግብ ቤቶች እንደ አሸን ፈልተዋል ። ጥሬ ክትፎ ፣ ለብለብ ክትፎ ፣ ጥብስ ክትፎ ፣ በቪቫዝ ሬጋል ውስኪ እያወራረዱ ኧረ ኡዲያ! የሚገርመው ነገር ደሞ የቤቱ ውበት እያበበ መምጣት ነው ። ከተማው ጨርሶ የሴት ገበያ ሆኖአል ። ይህችኛዋን ይዞ ያችኛዋን መተው ሀጢአት መስሎ ይታይሃል ። አስተያየታቸው መርዝ ይተክልብሃል ። በቃ ከወጥመዳቸው ውስጥ ሄዶ መውደቅ ነው ። አስርቱ ቃላት ጤና ይስጥልኝ! አታመንዝር ብሎ ነገር እንዴት ይሆናል? ውበት በምድር ዘርቶ አታመንዝር ብሎ ነገር ሞኝነት ነው ። ኩነኔ ምናባቱ! የተኮነነውስ ያዲሳባን ሴቶች ያላየ ነው ፣ አሀ ! ጠረናቸው ይምጣብኝ ። የሳባ ፣ የክልዮፓትራ ፣ የማርያም መግደላዊት ሽቶ ነው ። «ሞን ሼር አሚ' ሽቱ የተቀባችው በዚያ ፣ 'ሻኔል' የተርከፈከረችው በዚህ ፣ 'ማዳም ሮሸ' ተንከራ የወጣችው በሌላ ፣ በ'ዲዮር' የታጠበችው በተን ፣ 'ኳፉም' የታወደችው በፊት ለፊት ሲመጡብህ ያስብዱሃል ፡ እፍንጫህ ይሰክራል ። ልብህ ጥፍት ይላል ። ሳትወድ በግድ እንዳ

ውሻ ጠረናቸውን ተከትለህ ትሄዳለህ—ሽቱአቸውን ምናቸው ላይ እንደሚቀቡ ለማወቅ ። ያሳዝናል—ላዲሳባ ውብ ሴቶች ሁሉ የሚበቃ ጊዜ ሲጠፉ አያሳዝንም? ስታያቸው ህይወት ምን ያህል አጭር እንደ ሆነች ትረዳለህ» ብሎት ባሳብ ተውጦ ሲተክዝ ቆየና ፡ «ስለ አዲስ አበባ ቆንጆጅት የተፃፈ አንድ ግጥም ላሰማህ» ብሎት ጀመረ ፡

ጉዋ! ያዲሳባ ቆንጆዎች
የውበት ድባብ የንጋት ቅንድቦች
አይናችሁ ከጥልቅ ሸለቆ ላይ
እንደ ተኛ ኩሬ ውሀ ሰናይ
ሲያዩት መልሶ መልክ የሚያሳይ
ሽበቴን አየሁት ካይናችሁ ላይ ።
ጉንጫችሁ እንደ ምሽት ጀንበር ያማረ
ህብረ-ቀለም የተነከረ
ሁለት ላይ የተከፈለ
ሮማን የመሰለ ።

የደም ግባታችሁ—መልኬ መገርጣቱን
ያሳየኛል ፡ በእድሜ ዳዋ መበላቱን ።
ከምላሳችሁ ስር የሚፈሰው ማርና ወተት
ከትንፋሻችሁ የሚወጣው ሙቀትና ግለት
የገላችሁ ውበት የጠረናችሁ ሽቶ
ሌላ ገነት እያስመኝም ነበር ከቶ ።

ህይወት አዳሽ ትንፋሻችሁ
ገነታዊ ሽቱ ጠረናችሁ
አሁን ራቀኝ
ብርድ ብርድ አለኝ
አረጀሁ መሰለኝ?
ወጣትነት—የህይወት አፍላ
ህይወት አዳሽ ትንፋሻችሁ
ኮብላይ እንደ ጥላ ።

ይዞ ጭልጥ ፡ ዘርግቶ ጨለማ ክንፉን
እድሜ እያከሰመ የወጣት ውበቱን ፡
እያከሰለ ፍሙን እያዳፈነ ረመጡን
ከልቡ ላይ እያቀዘቀዘ የህይወት ነበልባሉን ።

የህይወት ህግ ስርአት
የሰው ታሪክ ኡደት
ትውልድ ያልፋል
ትውልድ ይተካል
በህይ ትወጣለች
ህሀይም ትጠልቃለች
ውበት ግን ዘላለማዊ ነች—ትኖራለች ።
ነፍሴ ለውበት እንደ በረሃ አሸዋ
እንደ በረሃ አሸዋ ትጠማለች ።

እንደ መድረክ ተዋናይ ድምፁን ከፍ ገቶ ፡ እጆቹን ወደ ላይ ወደ ታች ፡ ፊቱን ከስተር ለቀቅ እያደረገ ግጥሙን እንብንቦ ከጨረሰ በሁዋላ ፡ «ውብ አይደለም? ድግሞስ አያሳዝንም?» አለው ።

«ልቅሶ ነው» አለ ሀዲስ ።
«የምን ልቅሶ ነው የምትለው ! »
«ወጣትነት እየከዳው በመሄድ ላይ ያለ ሰው ልቅሶ ።»

«አይደለም ። የማጥሀው ደራሲ ጉዋደኛዬ ነው» ብሎት ፣ ስለ ደራሲው ህይወት ያጫውተው ጀመር ። ውበት በጣም የሚጠማው ሰው ነው ።እያነጋገርከው ልቡ ሸፍቶ ይሄዳል ። አንድ ያሰበው ነገር ቢኖር ባካል ካንተ ጋር እያለ በመንፈስ ሌላ ቦታ ሆኖ ነው የሚታየው ። ታዲያ በቅርብ የማያውቁት ሰዎች ኩራተኛ ወይም ምፀተኛ አድርገው ይቆጥሩታል ። ግን እሱ ሁል ጊዜ የሚያስበው ስለ ድርሰቱ ነው ። እንዲያውም አንዳንዴ ድንገት ተነስቶ ደህና ዋሉ—ደህና እደሩ ሳይል ይሄዳል ።

«አንድ ቀን ‘ለምን እንዲህ ትሆናለህ? ለምንስ ጉዋደኞችህ እንዲቀየሙህ ታደርጋለህ? ለድርሰት ስራህ ለምን ጊዜ አታበጅለትም?’ ብዬ ስጠይቀው ምን መልስ ሰጠኝ መሰለህ? የሚገርም ነው ። ‘ምን ላድረግ ብለህ ነው? ድርሰት የነፍሴ ጥሪ ናት ። ጊዜና ቦታ መርጣ አትመጣብኝም ። ቆሌ ናት ። ባሰኛት ቦታና ጊዜ ትቆላኛለች ፣ ታምሰኛለች ። እንደ ዛር የትም ትመጣብኛለች ። ቀናተኛ እመቤት ናት ። ፍቅርዋን ለማንም እንዳጋራባት አትፈልግም ። ስርቃት ታባርረኛለች ፣ ስቀርባት ደግሞ ትርቀኛለች። ድርሰት ክፉ ባላጋራ ናት እባክህ ። ለተወዳጃት ይብላኝ’ ብሎ ሲያስብ ቆየና :—

« ‘ነገሩ ይህ ብቻ አይደለም’ አለኝ ። ‘ሌላስ ምን አለ?’ አልኩት ፣ ‘የድርሰት ፍቅር ጣጣው ብዙ ነው እባክህ ። አንድ ልቦለድ መፅሐፍ ስጀምር ቶሎ ልጨርሰው እፈልጋለሁ ። ለምን መሰለህ? ሳልጨርሰው የሚገድለኝ ይመስለኛል ። እና ፣ ከጀመርኩት ድርሰት ጋር የነፍስ ግቢ ፣ የነፍስ ውጪ ፍልሚያ እንጀምራለን ። እኔ ልጨርሰው ፣ እሱ ሊገድለኝ—ትግል ነው ። ደራሲ መሆን ዘላለም ነፍስ ጡር መሆን ነው’ኮ ። ሴት ከወለደች በሁዋላ ምጡ ትዝ አይላትም ። ሌላ ታረግዛለች ። ምጡን ሁል ጊዜ ብታስታውስ ሌላ እርግዝና ሲያልፍም አይነካት ነበር ። ደራሲም እንደዚሁ ነው ። አንድ ልቦለድ ለመድረስ የደረሰበትን ስቃይ ብቻ ቢያስታውስ ብእር እርም ብሎ ይተው ነበር ። ወልደው ሲስሙ ፣ አለ አይደል ። እንደዚያ ነው ። እና ፣ አንድ ደራሲ ምን ጊዜም ቢሆን ጥሩ ጊዜውን ፣ ጉልበቱንና አእምሮውን ለድርሰት ማዋል አለበት ። ድርሰት ከዚህ ያነሰ መስዋእት አትጠይቅም ። እንዳልኩህ ቆሌዋ ፣ ዛርዋ የሚፈልገውን ሁሉ ይዘው ከፊትዋ ካልቀረቡ በሰው ላይ ትስቃለች ፣ ትሳለቃለች ፣ ታሾፋለች ፣ ታላግጣለች ። እዬ ! የድርሰት ፍቅር የለከፈው ሰው ቀልብ የለውም ። ሰላቢ ናት ። ግን ደራሲ ምን ጊዜም ቢሆን ብቸኛ አይደለም ። ደግነቱ እዚህ ላይ ነው’ ያለኝ ትዝ ይለኛል ። ታዲያ ይገርምሃል ። የድርሰት ካራማ ፊትዋን ያዞረችለት እለት ተደስቶ ይጠጣል ። ያኮረፈችውም ቀን ተናዶ ይጠጣል ። እንደ ጠጣ ነው ። ‘ምን ነው?’ ሲሉት ፣ ‘ተውኝ እባካችሁ ። ሰው ደስታ የሚኖረው በፈጠራ ላይ ሲሆን ብቻ ነው ። ሰው በመሰረቱ ፈጣሪ ነው ። ፈጠራ ላይ ካልሆነ ጊዜና ህይወት ምን ትርጉም አላቸው? እንዲያው ዝም ብሎ በዶ አየር ላይ መንሳፈፍ ነው’ ይላል » ።

ታፈስ ስለ ደራሲ ጉዋደኛው የጀመረውን ጨዋታ በዚሁ አላቆመም ። ቀጠለ ።

«ባለፈው ሰሞን የሆነውን ነገር ላጫውትህ ። ገብሬ መቼም ሴሊት አይተኛም ። ሴት ደስ ይለዋል ። የሴት ውበትና ምስጢር ይማርከዋል ፣ ይኮረኩረዋል ። ይገርምሃል እኮ ፣ 'ሰው ራሱን መሆንና መኖር የሚጀምረው ምሽት ላይ ነው ። መስከር ፣ መደሰት ፣ ማፍቀር ፣ ማሰብና መፍጠር ፣ ይህ ሁሉ የሚጀምረው በሴት ነው ። በመላ አለም ስንቱ ለፍቅር እንደሚቃትት፣ ለፍቅር እንደሚጠማ ፣ በፍቅር እንደሚረካ እስቲ አስብ? ቀን ያለ ስራ ፣ ያለ ሩጫ ምን አለ? ቀን ምን ይታይበታል? ምን ውበት አለው?' ይላል ። እና ፣ የህይወትን ጠረን እያሸተተ ሴት እንደ ጅብ ይዞራል ። የህይወት ጅብ ነው ። ታዲያ ይሄውልህ ባለፈው ሰሞን ከእሱ ጋር ሴቱን ሙሉ ስንዞር ወገግ አለ ። ነግቶአል ፣ አልነጋም እያልን መወራረድ ጀመርን ። ሁለታች ንም ሰክረናል ። ከህይወት አረቄ ብዙ ጠጥተናል ። እሱ አልነጋም ይላል ። እኔ ነግቶአል እላለሁ ። እንዲሁ እየተከራከርን በመኪና ስንሄድ ፣ ገብሬ የመኪናውን መስተዋት ዝቅ አደረገና ፣ አንድ መንገደኛ ጠርቶ 'ስማ ወን ድም ። ሰራተኛ ነህ? . . . እየው እስቲ ። ሁለታችን ተወራርደናል ። እኔ አል ነጋም እላለሁ ። እሱ ደግሞ ነግቶአል ይላል ። ገላግለን ። ማናችን ነን ልክ' አለው ። ሰውዬው በነገራችን ተደንቆ ሲመለከተን ከቆየ በሁዋላ ፣ ምን አለን መሰለህ! ይገርመሃል ። 'ዋ ወንድሞቼ! እኔም እንደናንተው ላገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ ስለሆንኩ ይንጋ አይንጋ? ምና'ውቄ!' ብሎን ፣ 'ወቸ ጉድ! ወይ ተአምር!' እያለ መንገዱን ቀጠለ» ብሎ በሳቅ ፈነዳና ፣ «ይኸውልህ ፣ ገብሬ በሰውዬው ነገር ስለ ተነካ 'ላገሩ ባዳ' በሚል አርእስት ልቦለድ ታሪክ መፃፍ ጀምሮአል ። የደራሲ መነሻ የህ ይወት ገጠመኝ ነው» አለና ታፈሰ ተከዘ ።

ታፈስ ስለ ደራሲው ይህን ሁሉ ለምን እንደሚነግረው ሀዲስ አልገ ባውም ። ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አደረገ ።

«እውነትም 'ላገሩ ባዳ'» አለ ሀዲስ ።
«አዲሱ ጎሳ ቢለው ይሻል ነበር እርእሱን . . .»

«አዎ ፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ስር መሰረት የሌለው ጎሳ ። እሱም ጥሩ ነው — ሳርስት ።»

«እኔ እኮ» አለ ታፈሰ ፣ «አንተ በምታስበው መንገድ አይደለም የም ናገረው ። እኔ የምናገረው ፣ ባስተሳሰቡ ፣ በእምነቱና በምኞቱ ምክንያት የተነሳ፣ በህብረተሰቡ እንደ ባዳ ወይም እንደ አዲሱ ጎሳ ስለሚታየው አዲስ ትውልድ ነው ።»

«ህም . . . በህልም አለም ውስጥ የሚኖር አዲስ ትውልድ . . .»

«ህልም አልከው? አዲሳባን ባየሃት? ጦፋለች» ብሎት አዲስ አበባን በአይነ-ህሊናው እንደሚያይ ሆኖ ሩቅ እየተመለከተ ፣ «ያዲሳባ መንገዶች በዓለም ላይ የተሰሩ የመኪና አይነቶች እንደ ትንግርት የሚታዩ ባቸው የት ርኢት መድረኮች ሆነዋል ። የመኪናውን አይነት ተወው ። አዲስ የሚሰ ሩትን ቪላዎች ብታይ! አቤት! አቤት! አፍ ያስከፍታሉ ። ምናለፋህ ፣ አን ዳንዱ ሰፈር «ቤል ኤር» ተብሎአል ። በቦሎቄና በሰሊጥ ንግድ የከበሩ አዳ ዲስ መሳፍንት ምን የማይሰሩት ነገር አለ ብለህ ነው? አለም ጠባቻዋ ለች ። እዚህ የምታንቀላፋው ፣ የምታዛጋው ፣ የምታዘግመው ህይወት እዚያ ታስካካለች ፣ ትላጋለች ፣ ትጠሩለች ። እሁንግ ተወው ። በመብራት

እየነደደች ነው ። ከጃንሆይ ሰማንያኛ አመት ልደት በአል አንስቶ ከተማይቱ እንደ ጦፈች ፣ እንቅልፍ በአይንዋ የማይዞር የማይመሽባት ከተማ ሆናለች። ይህ ሁሉ ህልም አይደለም ። እውን ነገር ነው ። የዚህ እውን ነገር ተሳታፊ ካልሆን የህይወት እተላ ሆነን እንቀራለን ። እሱን ተወውና አሁን የሚጪንቀኝ ምን መሰለህ? የሴጁን ረጅም ህይወት—አልባ የሆኑ ሌሊቶች እንዴት እንደማሳልፍ ነው ።»

ሲያዳምጠው ቆይቶ ፣ «አሁንስ ቢሆን ምን የሆን ይመስልሃል?» ብሎ ጠየቀው ሀዲስ ፣ 'እተላ' የሚለውን ቃል ይዞ ።

«ምንድን ነን?»
«የህይወት እተላ! የህይወት እተላ ነን» አለው ።

«አይ ሠምሬ ቲሱ!» ብሎ ተለይበትና ፣ ያዲሳባን ውበትና ህይወት ሊታደንቃት የምትችለው ለትንሽ ጊዜም ቢሆን ተለይተሃት ስትመለስባት ነው ። በተለይማ ገንዘብ ሲኖርህ ምስጢርዋ ይገለጥልሃል ። ውበትዋ ይታይሃል ። ብዙ ምስጢር ደብቃ የያዘች ፣ አስደናቂ ውበት ያላት ከተማ ናት— አሸን — ፍሌም — ባላንቻጋ — ሽቱ ። አህ — ተወኝ አቦ ። ይህች ጣፋጭ ህይወት አጭር ናት ። እንደ ጣፈጠች አትቀልቅም» አለውና ተስፋ ቆርጦ እጆቹን ወደ ላይ ወረወራቸው ።

ሀዲስ አቀርቅሮ ሲያስብ ቆየና ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አድርጎ ፣ «ለብዙዎቹ ግን ገሃነም ናት» አለው ።

«እሱን አላውቅም!»
«በህዝቡ አይን ውሀ ላይ ስለሚነበበው ቁጣ የነገርኩኝ መስሎኝ?»
«ምን ይጠበስ ታዲያ! አሳ በቢንዚን?»

«አንቺው ታመጪው አንቺው ታሮጪው ፣ አሉ ። ህዝቡ ፊት ላይ አንድ አይነት የእምቢተኛነት መንፈስ ይነበባል ያልከው አንተው ነህ ። እኔ አይደለሁም ። በህዝቡ አይን ውሀ ላይ የሚነበበውን ብሶት ለማየት አዲስ አበባ መውጣት አያስፈልግም ። ምናልባት በይበልጥ የሚታየው እዚህ በገጠሩ ኢትዮጵያ ነው ።»

«እና?»
«እና ፣ የሆነ ነገር አይሸትህም ወይ? ማለቴ ነው ።»
«እንዴምን ያለ?»
«የሆነ ነገር ፣ እንደ ለውጥ ሽታ ያለ ።»

ታሬስ እንደ መበሳጨት ብሎ ፣ «አትቃዥ እባክህ!» ካለው በሁዋላ ፣ «ምናልባት ሽማግሌው አንድ ነገር ያደርጉ ይሆናል ። ጃጅተዋል ። ሰውም የሚጠብቀው አንድ ነገር ሳያደርጉ አይቀሩም እያለ ነው ።» አለው ።

«እንዴምን ያለ?»

«ለምሳሌ ዘውዳን ለአልጋ ወራሽ እንደ መስጠት ያለ ነገር ። እና ህገ መንግስቱን ማሻሻል ። ከማፈላ የቡና ጀበና ላይ ቆረቆንዳውን ቀሎ ከላንሱ በኋላ ይገነፍላል ። ቆረቆንዳውን እንስተው ትንሽ ቡና ክፍት

ሲጨምሩበት ግን ተመልሶ ይረጋል ። የፖለቲካም ነገር እንደዚሁ ነው» ብሎት እጆቹን በማወናጨፍ የፖለቲካውን ነገር ካሰቡ አውጥቶ ወዲያ ጣለና ፣ «ይልቅ ያንን ነገር ይገኔ መጥቼአለሁ» አለው ።

«የቱን?»
«ፈንጂውን ነዋ ፣ ጅል!»
«አትለኝም!» አለው ሀዲስ እየፈነደቀ ።

«ዛሬ ማታ የሚዘንብ ይመስልሃል?» ብሎ ጠየቀው ፣ ታፈስም የሀዲስ ስሜት ተጋብቶበት እጆቹን እያሻሸ ።

«ኢንጃ ። ግን ለምን?»
«ማታ ሲዘንብ መብረቅ ነበር?»
«አዎን ፣ አልፎ አልፎ መብረቅ ነበር...»
«ነጎድጓዋድስ?»
«ሀይለኛ ነጎድጓዋድም አልፎ አልፎ ይሰማ ነበር...»

«ጥሩ ነው ። ዛሬ ማታም ዝናብ ፣ መብረቅና ነጎድጓዋድ እንደሚኖር ተስፋ አደርጋለሁ ። ዛሬ ካልሆነ ሌላ ቀን ። ሁልጊዜ ሌላ ቀን አለ ። ሌላ ምሽት ፣ ሌላ ንጋት ፣ ሌላ ፀሀይ ።»

«አሁንም አልገባኝም ። የመብረቁና የነጎድጓዋጉዱ ጋጋታ ምን ፋይዳ አለው?»

«ወርካውን መብረቅ ቢመታውስ? ፈንጂው ነጎድጓዋድ ቢሆንስ?»
«አባ ሰይጣን» ብሎት ዝም አለ ።

ታፈሰ እየሳቀ ፣ «ታውቃለህ ፣ አሳቡ የመጣልኝ ትናንት ማታ ነው ። ዝናብ ሲወርድ አሳቡ ድንገት ብልጭ አለልኝ ። አሁን ሳስበው በሌሊት ሄዶ ወርካውን ዝም ብሎ ማፈንዳት የሚያዋጣ አልነበረም ። አደገኛ ይሆን ነበር ። መብረቅ መቼም የሚወድቀው ትልቅ ነገር ላይ ነው ። ለምን ወርካው ላይ ወደቀ?—የቁጣ ምልክት ሊሆን ይችላል ። ፍፁም ሊደረስበት ወይም፣ ጨርሶ ሊያጠራጥር የማይችል ወንጀል ይሉሃል ይኸ ነው።»

ሀዲስ አይናቹን እያቁለጨለጨ ፣ «በወርካው ቦታ አዲሱ ትምህርት ቤት ቆሞ ከድንቁርና የመነጨ አጉል ባህል አመድ ላይ እንደ ብርሃን የጠራ እውቀት ሲያብብ አይታይህም?» አለው ።

«አይታየኝም ። ቅዝቃዜትክን ተወኝ ብያለሁ ።»

«ታዲያ ምንድንነው የሚታይህ? ወይስ ምንም የሚታይህ ነገር የለም?»

«እኔ የሚታየኝ የልባችንን ሰርተን ማንም ሳያውቅብን ስናመልጥ ነው ። በማግስቱ ሰዎች ወርካውን መብረቅ መታው ብለው ሲያወሩ ስንሰቅ ነው የሚታየኝ ። ከሰራነው ጀብዱ የምናገኘው ደስታ ነው የሚታየኝ ። ጀብዱ የህይወት ቅመም ነው ። አንዳንዴ አደጋን ፊት ለፊት ካላዩ የመኖር ትርጉሙ ይረሳል ። ህይወት ራስዋ አንድ አጭር የጀብዱ ምእራፍ ናት ። ሌላ አይታየኝም ።

«ከዚያ በሁዋላ ከትምህርት ቤትህ ጋር ገዶል ወይም ገሃነም ልትገባ ትችላለህ!» ብሎት እያዛጋ ተንጠራራና ፣ «ምስጢሩን ለማንም እንዳልነ ገርክ መቼም ተስፋ አለኝ» አለው ።

የሀዲስ ገረድ ቁርስ ይዛ መጣች ። ትሪው በትኩስ ስጋ እንፍርፍር ተሞልቶአል ። እንቁላሎችና የዶሮ ብልቶች ከተከመረው እንፍርፍር ውስጥ ተሸጠው ይታያሉ ። ጤና አዳም ጣል ያለበት እርጎ በሸክናዎች ቀር ቦአል ።

«አብድ መሰልኩህ?» አለው ሀዲስ ፣ ፊቱን ኮስተር አድርጎ በገፍ የቀ ረበውን ቁርስ እየተመለከተ ።

«አንዳንዴ ሳስበው ጤነኛ አትመስለኝም» ብሎት ፣ እንፍርፍሩን ቶሎ ቶሎ ጎርሶ እርጎውን ከተጎነጨ በሁዋላ ፣ « አቶ ይርጋ ምን ያስባሉ?» አለው ።

«ወደዱም ጠሉም ነገሩን የተቀበሉት መሰለኝ ።»

የታፈሰ አበላል አስጎምጅቶት ሀዲስም መብላት ጀመረ ።

«ምን አሉህ?»

«መቼ ነው? ባለፈው ቀን ቢሮአቸው ድረስ ጠርተውኝ ፣ ‘አይዞህ ፣ በርታ ። ግን የሰው ነገር ስማ ። ዱሮውኑም ቢሆን ሳታማክረኝ ብትቀር ነው እንጂ ችላ ያልኩህ የትምህርት ቤቱን መሰራት ጠልቼ አይደለም ። የጊዜ ችግር ሆኖብኝ ነው እንጂ እኔም ካሰብኩበት ዘመን የለኝም ። ፕላኑን ካዘ ጋጀሁት እንኳዋን ይኸው አስር ነው አስራ ሁለት አመት ሆኖአል ። ግን አድምጠኝ ። ተማክረው የፈሱት ፈስ አይገማም ይባላል’ ብለው ሸኙኝ እልሃለሁ ። በእውነት ልቤን ነው የነኩት ። ስላለፈው ሁሉ ይቅርታ እንዲያ ደርጉልኝ ጠይቄአቸው ወጣሁ» አለው ።

«ሌላ ምንም አላሉህም?»

«ሌላ ችግዝ የሚለኝ ነገር የለም» ብሎት ሁለቴ ከጎረሰ በሁዋላ ፣ «አዎን! አሁን ትዝ አለኝ ። ምን ያህል ገንዘብ እንደ ሰበሰብን ጠይቀውኝ ነበር» አለው ።

«ስንት ነው?»

«ሁለት መቶ አስራ ሁለት ሺህ ብር ከአርባ ሳንቲም ሰብስበናል— እስካሁን ድረስ ።»

«ከዚያስ?»

«ገንዘቡን የት ነው ያስቀመጣችሁት?» ብለው ጠይቀውኝ ነበር። «አቶ ጣሴ ዘንድ ነው አልኩዋቸው . . .»

«እውነትክን ነው?»
«አዎን ። ምን ነው?»

«ይህን ሁሉ ገንዘብ እንዴት ቤት ታስቀምጣላችሁ? ለምን ባንክ አታ ስገቡትም?»

«እዚህ ባንክ የት አለ?»
«መቱ የለም ወይ?»

«መቱ ድረስ እየተመላለሱ በየቀኑ ገንዘብ ማውጣት እንዴት ይቻላል? ለዚያውም ደሞ ቼኩ ላይ ሁለት ሰው ካልፈረመበት እያሉ ጣጣ ፈንጣጣ ያበዛሉ ።»

ታፈሰ ጣቱን ደረቅ እንጀራ ላይ ጠረገና ፣ «በል ወንድሜ ፣ ሰው ሳይሰማችሁ ቶሎ ሂዱና ባንክ ጨምሩት ። ሌባ ሌሊት ቤታቸውን ሰርስሮ ገብቶ ቢሰርቅባቸውስ? የሱጴ ሌባ ባንድ ሌሊት ካምስት ሜትር በላይ ርቀት ያለው ጉድጉዋድ ቆፍሮ ሊገባ ይችላል» ብሎት ፣ ጣቶቹን እንደ ቡሄ ጅራፍ እከታትሎ ካስጮኸ በሁዋላ ፣ «አሁን ገና ገባኝ!» አለ ።

«ምኑ?» አለ ሀዲስ ፣ የጎረሰው እንፍርፍር አልዋጥ ብሎት እየተናነቀው ።

ታፈሰ የፈጠጡትን አይኖቹን ሀዲስ ላይ ተክሎ አሁንም ጣቶቹን ያስጮህ ነበር ። «ነገሩ ግልጥ ብሎ እየተነበበልኝ ነው . . . »

«ምንድን ነው የምትለው!» የሀዲስ የደም ስሮች ተገታትረው ነበር።
«ገባኝ ስልህ።»

«ሀዲስ ሌባ ሰረቀኝ ብሎ ገንዘቡን ሊበላ ነው እዚህ ያስቀመጠው ብለህ አስበህ እንደሆነ ተሳስተሃል!»

ሀዲስ ሲናገር ንዴት እየተናነቀው ነበር ።

«ይኸን ማለቴ አይደለም ።»
«ታዲያ ምንድን ነው የምትለው?»
«ምን ቢያስቡ ነው ገንዘቡን የት እንዳስቀመጥከው የጠየቁህ?»
«ምን አውቃለሁ? ጠንቁዋይ አልቀልብ ።»

«ስማኝ ሀዲስ ። በጣም ሰው ታምናለህ ። አየህ ፣ ህይወት ገና ብዙ አላቀሰለችህም ። ብዙ ጠባሳዎች ልብህ ላይ አላስቀረችም ። ስለዚህ ሰው ታምናለህ . . . »

«እፉ! ሰብከቱን ተወውና ምን ለማለት እንደፈለክ ንገረኝ . . . »

«እስቲ አስበው ፣ እነዚያን መጥፎ ደብዳቤዎች የፃፉብህ ሰው አሁን በድንገት ተነስተው አለሁልህ የሚሉህ ለምን ይመስልሃል? ነብር ቆዳውን አይለውጥም ይባል የለ ። በተለይም አቶ ይርጋ አይስወጡም ። ተኩላ ናቸው ። ገንዘቡን ምን እንዳስቀመጥከው ከታወቀ በሁዋላ ፣ እንበል ሌባ ቢሰርቀውስ? ምን አደረኩት ትላለህ? ሌባ ሰረቀን ብትሉ ማን ያምናችሁዋል? ከዚህ አቅጣጫ በነገሩ አስበህበታል?»

«ምን ነው ጃል ! አቶ ይርጋ ያቶ ጣሴን ቤት ሰርስረው ይሰርቃሉ ልትለኝ ነው?»

«እሳቸው ባይሰርቁም ሊያሰርቁ አይችሉም . . . ?»

«ተው እባክህ ጃል ። ያላሰብኩትን አታሳስበኝ ። እኔ በበኩሌ እንዲህ ያደርጋሉ ብዬ ፈፅሞ አልጠረጥርም ። »

«እንግዲያውስ የኔ ጥርጣሬ ይሆናል ። እርሳው» ብሎት ጣቱን ታጥቦ ወጣ ። ሀዲስም ተከተለው ።

«ይህ ሁሉ እቃ ምንድን ነው?»

ላንድሮቨርዋ መአት እቃ ተጭና ነበር ።

«ቡዋንቡዋዎች ፣ የመታጠቢያ ቤት እቃዎችና ጀኔሬተር ነው ።»

«ለምንህ?»

«ታያለህ» ብሎት መኪናውን እየከፈተ ፣ «በነገራችን ላይ ፣ ከፈታ ውራሬ ቤት ወጥቼ ማዶ አባቴ ቤት ገብቻለሁ ። እያሳደስኩት ነው ። እንዲህ አይምሰልህ ። ግሩም የድሮ ቤት ነው ። ከፈለክ ለምን አብረን ሄደን አታየውም?»

«ልብህ መቼም ካራዳ አይለይም» ብሎት ሳቀበትና ፣ «አሁን ልመጣ አልችልም ። የማርማቸው ደብተሮች አሉኝ ። ሌላ ጊዜ . . .»

«ቻዎ ! የሚዘንብ ከሆነ ማታ እመጣለሁ ። ገንዘቡን ግን ባንክ ብታስገቡት ይሻላል ። ወይም ለኔ ብትሰጡኝ ጥሩ ነበር ። ይህን ያህል ገንዘብ ተንተርሶ መተኛት ሀጢአት ነው ። ብትሰጡኝ ብዙ ትርፍ አገኝበት ነበር ። ገንዘብ ገንዘብን ይወልዳል» አለው ።

«የሀዝብ ገንዘብ እንዴት እናድርገን!»

«ህዝብ ፣ ህዝብ አትበል ! ያመኛል! እኔ የማወራው ስለ ትርፍ ነው ። ሀጢአት ምንድን ነው? ብትለኝ ይህን ያህል ካፒታል ተንተርሶ መተኛት ነው ። ያለ ትርፍ እድገት የለም» ብሎት ላንድሮቨሩን አስነስቶ በሁዋላ ጎማዎቹ ጭቃ ረጭቶበት ሄደ ።

ሀዲስ የተማሪዎቹን ደብተሮች ወደ ማረሙ ስራ ተመለሰ ። ታፈሰ ተከሎበት የሄደው መርዝ ካሰበ አልጠፋም ። በግማሽ ልቡ ፣ ኤጭ ፣ እንጉል ጥርጣሬ ነው ። መሸነፋቸውን አውቀው ይሆናል ። መሸነፍን በፀጋ መቀበል ራሱ ከድል ይቆጠራል።የትልቅነትም ምልክት ነው።ስለዚህ እኔ ነኝ የሰራሁት በማለት የምስጋናው 'ባለቤት' ለመሆን ፈልገው ይሆናል ። ቢሆኑስ ምናለበት? ትምህርት ቤቱ ይሰራ እንጂ ምስጋናው ለማንስ ቢሆን ምን ፋይዳ ይኖረዋል? በማለት አሳቡን ይደመድምና የያዘውን ስራ ማፋጠን ይጀምራል ። ረፋዱ ላይ ስራውን ጨርሶ ንፁህ አየር ለመቀበል ወደ መስኮቱ ሄዶ እንደ ቆመ ቶሎሳ እየተጣደፈ ወደ እሱ ቤት ሲመጣ ከሩቅ ይመለከተውና በሩን ከፍቶ ይጠብቀዋል ።

ሰላምታ ተለዋውጠው ቤት ከገቡ በሁዋላ ፣ «ተልኬ ነው የመጣሁት» ይለዋል ቶሎሳ ጎፈሬውን ጥቁር ጉም አስመስሎ ።

«ከማን? ከፈታውራሪ?»

«አይደለም ። ከአይናለም ነው።»

የሀዲስ ልብ ስንጥቅ ይልበታል ። ያደረበትን ስሜት ከቶሎሳ ለመደበቅ እየፈለገ፣«እሺ . . . ። ምን ነበር መልእክቱ?» ሲለው፣ ቶሎሳ ነጠላውን ወደ ላይ አንስቶ ከደረት ኪሱ ወረቀት አውጥቶ ሰጠው ።

በጥንቃቄ የተጣጠፈውን ወረቀት መዘርጋት እቅቶት እጆቹ ይንቀጠቀጡ ነበር። ቶሎ ብሎ ጀርባውን ወደ ትሎሳ አዞረ ። እግሮቹም እንደ እጆቹ ጤነኛ አልነበሩም ። ትንፋሹንም በሚገባ ለመቆጣጠር አልቻለም ። ትኩሳት በጣም ይዞት የልቡ ትርታ ጨምሮ ነበር ። ወደ ጠረጴዛው ሄዶ ወረቀቷን ከጠረጴዛው ላይ ዘረጋና ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ ደብዳቤውን ያነብ ጀመር፤—

«ይድረስ ለ . . . ሀዲስ» ብሎ ይጀምራል ደብዳቤው። 'ለወንድሜ' የሚለው ቃል ከመሃል ተሰርዞአል . . .

«ያመጣህልኝን መፃህፍት ለማንበብ አልቻልኩም ። አሳቤ እየባከነ ያስቸግረኛል ። የረጋ መንፈስ ከሌለ የሚያነቡት ነገር ሁሉ ተመልሶ እንግዳ ይሆናል ። ከዚህ ቀጥሎ የምነግርህ ነገር አለኝ ። ይህን፤ ደብዳቤ አንብበህ እንደ ጨረስክ መልሱን ፅፈህ ላክልኝ ።፤

«እንደ አንድ ቀን ፊት ለፊት ተገናኝተን ለመነጋገር እድል አላገኘንም ። በቤተ ክርስቲያን ያደረግነው ቀጠሮም አላመቸም ። ስለዚህ ይህን ደብዳቤ ልፅፍልህ ቢቃሁ ።

«አባቴ ሊድረኝ ነው ። ወይም ነገሩን ሰምተኸው ይሆናል ። እኔ ግን በገዛ እጄ በገመድ ታንቄ እሞታታለሁ እንጂ አባቴ የመረጠልኝን ሰው አላገባም ። እንዳልኩህ ፣ ሞቴን እመርጣለሁ ።

«ፍላጎቴ ለመማር ነበር ። ነገር ግን አባቴ ከአይኑ ርቄ እንዳልሄድ ስለሚፈልግ ሳያስተምረኝ ቀረ ። እንዳገባው የታሰበው ሰው ከኔ የባሰ ማይም ነው ። ከመሸታ ሌላ አያውቅም ይባላል ። አባቴ ይህን እያወቀ ለዚህ ሰው ሊድረኝ መነሳቱ የበደል በደል ነው ። ለሞተ ታሪክ አዲስ ምእራፍ የመክፈት ፍላጎቱ አይኑን ጋርዶታል ። እኔ ደግሞ ለዚህ ከንቱ ፍላጎት በመስዋእትነት ለመቅረብ አልፈልግም፤።

«አሁን የምለምንህ ይዘኸኝ ወደ አዲስ አበባ እንድትጠፋ ነው ። አዲስ አበባ ራሱን የቻለ ዱር ነው ሲሉ እሰማለሁ ። ማንም ፈልጎ አያገኘንም ። እንዴት እንኖራለን ብለህ አታስብ ። በቂ ገንዘብ ይዤ እመጣለሁ ። እንደምታስተምረኝ ተስፋ አለኝ ። በእንግሊዝኛ የተፃፉ መፃህፍት እንደ ልቤ እንብቤ ብሞት ግድ የለኝም ። ይህን ሁሉ የምነግርህ ስለማምንህ ነው ። መልሱን ላክልኝ . . . ያንተው . . . አይናለም ተካ ።»

ድምፅዋ እየተሰማውና ባባቡ መጥታ እየታየችው ደብዳቤውን እንደገና አነበበው ። የተጨነቀች ነፍስ ከገሃነም አውጣኝ እያለች ስትጮህ ይሰማው ነበር ። ጭንቅላቱን ይዞ ወረቀቷ ላይ እንዳፈጠጠ ቀረ ። እሺ ይሁን ወይም የለም አይሆንም የሚል ቀላል መልስ አልነበረውም ። እንደ እውነቱ ከሆነ ምንም መልስ አልነበረውም ። የተጨነቀችው ነፍሱ ከውስጡ እየተወራጨች የመረረ እንባ ስታለቅስ ይሰማው ነበር ። ህይወት በየማእዘኑ ለምን እንዲህ አድርጋ እንደምትፈትነው ከቶ ሊገባው አልቻለም ። ወደ ላይ ቀንሰቶ የጠረፉን ግድግዳ በመምታት ተመልሶ የሚወድቅ ማእበል የመሰለ ንዴት ከውስጡ ገንፍሎ እየተነሳ ተመልሶ ሲወድቅ በሚጎሳፈፈው ልቡ ፣ ይህን ያህል ስታምነኝ አዲስ አበባ ይገፍአት መሄድ ቀርቶ ፣ ከሆነ ለምን አብረአት ገደል አልገባም? በማለት እጅ ለእጅ ተያይዘው

በጠፍ ጨረቃ ጭልጥ ብለው ሲጠፉ ይታየውና ወዲያው የህዝቡ ውኸት ከሩቅ ይሰማል—አንተ እምነተ-ቢስ! እያለ እድሜ ልኩን ሲከተለው የሚኖር ውኸት! ባሳብ ሲጨነቅ ያሳለፈው ጊዜ ግፋ ቢል ካንድ ደቂቃ አይበልጥም ። ግን ያቺ ደቂቃ እንደ ዘመን ረዝማ ነበር የታየችው ። በዚያች እንድ አፍታ ውስጥ ከራሱ ከዘለአለም ጋር ፊት ለፊት የተጋጨ መስሎት ነበር የተሰማው ። የውበት ፣ የፍቅር ፣ የተስፋ ፣ የስቃይ ፣ የጭንቀት ፣ የእምነትና የክህደት አፍታ ። በዚያች አፍታ ውስጥ የኢዮብን ስቃይ ሳይቀበል ፣ የዳንቴን ገሃነም ሳያቋርጥ ፣ የአለምን ጉዳድ አሽዋዎች ሳይጉዋዝ አልቀረም። ጴጥሮስ ወደ መንግስተ ሰማያት የሚያስገባውን በር የሚከፍተውን ቁልፍ አልሰጠውም ። ለሁለት የተከፈለው ልቡ መልስ አላገኘም ።

«አሁን መልሱን ልልክልሽ አልቻልኩም ብሎሻል በላት ።»
«እንዴት አድርጌ?»
«ምን ማለትህ ነው?»

«መልሱን ይዘህ እንድትመጣ ብላ ነው የላከችኝ ። ይኸኔ ቁጭ ብላ ትጠብቀኛለች ።»

«ታዲያ ምን ይሻላል?»
«የሚሻለውማ መልሱን ፅፈህ ብትሰጠኝ ነው ።»
«ቀላል አይደለም ።»
«ምኑ?»
«መልሱ ።»

«አሳብክን ወረቀት ላይ ማስፈር ምን ያስቸግርሃል? እድሜ ለአይናለም እኔም እፅፋለሁ ። ጥሩ አድርጋ ፊደል አስቆጥራኛለች ።»

«ለጊዜው ይህ ነው ብዬ የማስፍረው መልስ ስለ ሌለኝ ነው ።»
«ይህንኑ ልንገራታ?»
«የቱን?»

«ለምን ብትለኝ ፣ ለጊዜው ይህ ነው ብዬ የምልከው መልስ የለኝም ብሎሻል ብዬ ።»

«የለም! የለም! እንደ እሱ ብለህ አትንገራት ።»
«ታዲያስ?»
«ከዚህ ሁሉ ለምን እስዋ ዘንድ አትወስደኝም?»
«የት? ቤት?»
«አዎን ።»

«ፊታውራሪ አሉ ። በዚህ ላይ ግቢው ሁሉ ሰው ብቻ ነው ። ግቢው በርበሬ በሚቀነጥሱ ፣ እህል በሚፈጩ ፣ ጌሾ በሚወቅጡ ፣ ድፍድፍ በሚያገሳብጡ ሰዎች ተጣቦአል ። ሰርጉዋ ደርሶ የለ ። ለየካቲት ማርያም ነው ሰርጓዋ።»

«እንደ ምንም ብለህ ዘዴ ፈልግልኝ» አለው ፣ ሰርጉ ምን ያህል ቀን እንደ ቀረው እያሰበ ። አስራ አምስት ቀን ነበር የቀረው ።

ቶሎሳ ጥቁር ጉም የመሰለውን ጎፈሬውን እያከከ አቀርቅሮ ያስብ ነበር ። ፊቱ ብልጠቱን እንደ ጠራ መስተዋት ወለል አርጎ ያሳያል ። እንደ

ንስር አይን የሚፈጥኑት ትናንሽ አይኖቹ ነገር የሚያመልጣቸው አይመስሉም ። የባላገር ቆዳው ገር ቢያስመስለውም ብልጠቱን ሊደብቅ የሚችል አልነበረም ።

«እስዋ እሺ ካለች ደህና» አለ ።
«ለመሆኑ አሁን እንዴት ናት?»

«አዬ የስዋን ነገር ተወው ። በጣም ያሳዝናል ። እህል መቅመስ ከተወች ቆይታለች ። እንደ ዱሮዋም መፅሀፍ አታነብም ። ሰው አታናግርም ። ያ ደስ የሚለው ጨዋታዋና ሳቅዋ ሁሉ ቀርቶ ቤቱን ጭር አድርጋዋለች ። ነጋ ጠባ ዝም ብላ ማልቀስ ነው ። ፊታውራሪም የሚያደርጉት ጠፍቶአቸው ግራ ገብቶአቸዋል ። »

ሀዲስ አውቆ እንዳላወቀ በመሆን ሊያውጣጣው ፈልጎ ፡ «ለምን ይመስልሃል እንዲህ የምትሆነው?» ብሎ ጠየቀው ።

«መዳርዋን ጠልታ ነው ። »
«ታዲያ ለምን አይተውዋትም?»

«እንዴት ተብሎ? ከፊታውራሪ ትንፋሽ አንዴ የወጣች ቃል አትታጠፍም ። ቃላቸውን ማጠፍ ሞት ነው የሚመስላቸው ። አገርስ ምን ይላቸዋል? አሸንፉ ቀረች መባልም እኮ ውርደት ነው ።»

ሀዲስ—የማናቸው ፈቃድ ያሸንፍ ይሆን? እያለ ያስብ ነበር ። በመጨረሻም—ጠንከራ ፈቃድዋ እንባዋ ውስጥ ሙዋምቶ ተሸንፋ መሄድዋ ይቀራል? እና ፡ ለዘለአለሙ ሊለያት ልቤ የገባን ወንዝ አብሮአት ተሻግሮ ይሄዳል ። ስመጨረሻ ጊዜ ደህና ሁኚ አድባርዋ ትከተልሽ ለማለት ። 'ሃይ ፡ ሃይ ፡ ሃይ ፡ ሎጋው ሽቦ' እየተባለ ተሞሽራ ስትሄድ እንባዋ ደርቆ የጨው አምድ እስኪመስል ድረስ ትረግመኝ ይሆናል ። የእስዋም እርግማን እንደ ህዝቡ ውኸት እድሜ ልኬን ሲከተለኝ ይኖራል ። ምናልባት ህይወት ራስዋ ርግማን ሳትሆን አትቀርም ። አላውቅም ። ማን ያውቃል? ታዲያ ይህን ያህል የምሰቃየው ለምንድን ነው? ይህ የተረገመ ትምህርት ቤት !

«እሺ እንግዲህ ዘዴ ከተገኘ ተመልሼ እነግርሃለሁ» ብሎት ወጥቶ ሄደ — ቶሎሳ ።

ሀዲስ ደብዳቤውን ለሶስተኛ ጊዜ እንደገና አነበበው ። አይኖቹ እንባ ቋጥረው ነበር።—ብቻዋን ሳገኛት—ያውም ባገኛት—ምንድን ነው የምላት? አይናለም እወድሻለሁ ። ከልቤ አፈቅርሻለሁ ። ይገፔሽ ብጠፋ ደስታውን አልችለውም። ግን. . . ግን. . . ምን?እንዴት ሊገባት ይችላል? ሰው ቀርቶ ሰማያውያን መላእክትም ቢኖሩ ባለ ጥበባቸው ሁሉ ሊገባቸው አይችልም ።

—ሁለት የወደደን ሰው ስሜት ማን ሊረዳ ይችላል ? መወሰን ምንኛ ስቃይ ነው! ሆኖም በዚህ አለም ስንቶቻችን ነን ህይወታችንን ||ሚመለከት መሰረታዊ ነገር የምንወስነው? ለዚህ ነው ብዙዎቻችን በባርነት ኖረን የምንሞተው ። እንወስንማ ። መወሰን ሲኦል ነው ። እ ፡ በዚህ ጊዜና ቦታ ዝም ብለን እንደ እረፋ መንሳፈፍ አቤት ስንወድ! እንደ የዋሁዋ ሰጎን ራሳችንን አሸዋ ውስጥ ቀብረን ምንም አይነት ፍጭት በሌለበት አለም ውስጥ መኖር አቤት ስንመኝ ። ግን ፡ ማንም ከዚያች የውሳኔ ሰአት ሸሽቶ ሊኖር አይች

ልም ። ህይወት ካለ ውሳኔ ሀይወት አትሆንም ። መወሰን የሰው ልጅ እጣ ፋንታ ነው ። የሞተ ሰው ብቻ ነው ከመወሰን ስቃይ ተገላግሎ ነፃ የሚሆነው እያለ ሲያስብ በሩ ሲመታ ሰማ ።

አንድ ፖሊስ ከበር ላይ ቆሞ ይጠብቀው ነበር ።
መቼም ፖሊስ ባየ ቁጥር ልቡ ስለሚደነግጥ ፥ «ምን ነበር?» አለው።
«የወረዳው ገዢ ይፈልጉሃል»
«ማንን? እኔን? ለምን?»
«ጥራው አሉኝ እንጂ ጉዳዩን አልነገሩኝም ።»

አቶ ጥላሁን ሸዋረጋ የወረዳው ገዢ ፥ ከዚህ በፊት እንጋግረውት አያውቁም ። አብዛኛውን ጊዜ ሱጴ አይኖሩም ። ሲያስኛቸው ወደ ግዛታቸው እንደ መስቀል ወፍ ብቅ ብለው ይጠፋሉ ። አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያጠፉት መቱና አዲሳባ በመመላለስ ነበር ። የሱጴ ወረዳ ገዢ ተብለው ከመሾማቸው በፊት መጀመሪያ በቤተ መንግስት ውስጥ ባሽከርነት ሁዋላም በቤተ ርስት ፀሐፊነት ያገለግሉ ነበር ይባላል ። ታዲያ ከቤተ መንግስት ጋር ቀጥታ ግንኙነት አላቸው ስለሚባል ይፈራሉ ። ለምን ይሆን የፈለጉኝ እያለ ተነስቶ ከፖሊሱ ጋር ሄደ ።

የወረዳው ፅህፈት ቤት ግቢ ስፍር ቁጥር በሌላቸው ባለ ጉዳዮች ተጥለቅልቆአል ። ሽህ አይን አፈጠጠበት ። ፖሊሱ በቀጥታ ወደ ወረዳ ገዢው ቢሮ መራው ። ቢሮው ውስጥ የተረጨው የቁንጫ መግደያ መድሀኒት ቁንጫ ቀርቶ ሰው ይገድላል ።

«ቁጭ በል» አሉት አቶ ጥላሁን ።

ሀዲስ እጅ ነስቶ ቁጭ አለ ። በስንደቅ አላማ ተከቦ ከግድግዳ ላይ ተሰቅሎ ፊት ለፊት የሚታየው የንጉሱ ነገስቱ ፍቶግራፍ ሰው ወደ ታች ይጫናል ።

«ምንድር ነው'ኮ ይህ ሽፍታነት!»
«የቱ ሽፍታነት ፥ ጌታዬ?» አለ ሀዲስ ።

አቶ ጥላሁን ከቅላታቸው የተነሳ የፈረንጅ ክልስ ይመስላሉ ። በራቸው ገለጥ ፥ ገለጥ ያለ ነው ። አፍንጫቸው የታችኛውን ከንፈራቸውን ሊነካ ምንም አይቀረውም ።

«የፊታውራሪ ተካ ዘመድ ነህ?»
«አይደለሁም ።»
«ታዲያ ምንድር ነው ቤታቸው የሚያመላልስህ?»
«ስለማውቃቸው ነው» አለ ሀዲስ ።

«ምናለ ፥ እሳቸው አሁንም አገር የሚገዙ እየመሰላቸው አስቸግረዋል። ባስተዳደር ጉዳይ እንዳይገቡ ቢነገራቸውም እሺ አላሉም ። አንተም እንደ እሳቸው በማያገባህ ነገር እየገባህ ማስቸገር ጀምረሃል አሉ» አሉት ፥ እንደ ነፍጠኛ ጎራዴ የሚያሸሙዋጥጠውን ሪዛቸውን እየጎነተሉ ።

ያቶ ጥላሁን አይን የሀዘን ጥላ የሚያንዣብብበት ይመስላል ። ዘለአለም ተርበው እንደሚኖሩ አይነት ስሜት በሰው ላይ ያሳድራሉ ።

ጥላሁን ሸዋረጋ
የፈረሱ ስም - የጅብ መንጋጋ
አሳዶ ገዳይ በጉቦ
በሚያዝያ ሲምብር ባምሌ ወጀቦ

እየተባለ ስለ አቶ ጥላሁን በጆሮ የሚነገረው ነገር ትዝ አለው ። «ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል» እንዲሉ ፣ ስለ ጉቦ አይናቸውን አያሹም ይባላል ።

«ምን አድርጌ?» አለ ሀዲስ ።

«ምን አድርጌ! ማን አለብኝ ብለህ ተነስተህ የለም ወይ? እንዴት'ኮ ነው ነገሩ? ወይስ ጥላሁን ፣ ማንም እንደ ፈለገው ገብቶ የሚጨፍር በትን የጋለሞታ ቤት ይጠብቃል አሉህ!» አሉት ተቆጥተው ።

ድምፃቸው እንደ ነንድጉዋድ ነው የሚያጉረመርመው ። ሲናደዱ አፍ ንጫቸው በይብልጥ እየረዘመ የሚሄድ ይመስላል ።

«ስለ አዲሱ ትምህርት ቤት ነው?» አለ ሀዲስ ።

«አዎን ። መንግስት አለ ። አስተዳደር አለ ። ማንን አስፈቀድክ?:ማንን ጠየክ? ፕላኑን ማን አፀደቀልህ? ህዝቡን ለመሰብሰብም ሆነ መዋጮ ለመ ጠየቅ ማን ስልጣን ሰጠህ?» በማለት በጥያቄዎች አጣደፉት ።

«እንደ ጥፋት ከተቆጠረብኝ እተወዋለሁ ፣ ጌታዬ ። በቅንነት ያደረ ኩት ነው እንጂ ፣ ማን አለብኝ በማለት የሰራሁት ነገር አይደለም» አላ ቸው ።

«ከህዝብ ገንዘብ ከሰበሰብክ በሁዋላ እተወዋለሁ ማለት ምንድር ነው ትርጉሙ? ወይስ ጥላሁን የእድገት እንቅፋት ነው ለማለት ነው? ስማ! የቡጹ ህዝብ አይኑን ለመክፈት የቻለው እኔ እዚህ ከመጣሁ በሁዋላ ነው ። ከባላ ባቶች መንጋጋ አውጥቼዋለሁ ። ቀን ከሌት እየደከምሁለት ነው ። የእድ ገት አጋር እንጂ እንቅፋት አይደለሁም . . .» ሲሉ ፣ ሀዲስ አቋዋረጣቸውና፣

«እንደሱ አላልኩምኮ ፣ ጌታዬ» አለ ።

«አንዴ ፣ አናግረኝ እንጂ! የዘመኑ ልጆችኮ ሰው ከመጤፍ አትቆጥ ሩም ። መረን ወጥታችሁዋል ። በነገራችን ላይ አዲሳባ ያለህ አይምሰልህ ። እኔ ጥላሁን ቀልድ አላውቅም ። በስልጣኔ ቀናኢ ነኝ ። በስልጣኑ የማይቀና ሰው ባለ ስልጣን አይደለም ። ራሱን ያስደፈረ ባለ ስልጣን የመንግስትን በትረ ስልጣን አክብሮ ያስከብራል ማለት ዘበት ነው ። እና ፣ ወዳጄ ቀልድ ህን ተወኝ!

«ከዛሬ ጀምሮ ያለኔ ፈቃድ በዚህ አገር ምንም ለማድረግ እንደማት ችል እወቅ ። ደግሞ ስራውን አቁም ማለቴ አይደለም» አሉት ።

«እንዴት ላድርግ ታዲያ?» አለ ሀዲስ ግራ ተጋብቶ ።

የሰውዬው ጫወታ ሊገባው አልቻለም ።

«ለመሆኑ እስካሁን ስንት ገንዘብ ሰብስበሃል?»

«ሁለት መቶ አስራ ሁለት ሽህ ብር ።»

ማስታወሻ ደብተር ላይ የሆነ ነገር እየፃፉ ፤—
«ስንት ክፍል ያለው ትምህርት ቤት ለመስራት ነው የታሰበው?»

«ስምንት የመማሪያ ክፍሎች ፣ አንድ አዳራሽ ፣ አንድ ቤተ መፃህፍት ፣ እንዲሁም አራት ፅህፈት ቤቶችና አንድ ያስተማሪዎች መሰብሰቢያ . . .»

አሁንም እየፃፉ ፣ «ስራው መቼ ይጀምራል?» በማለት ጠየቁት ።
«ስራውን ለመጀመር ተዘጋጅተን ነበር ። ግን . . .» ከማለቱ ፣
«ግን ምን?» አሉት ።

ስለ ገጠማቸው የቦታ ችግር አንስቶ ካጫወታቸው በሁዋላ ፣ «ቦታ እንዲሰጠን እዚሁ አመልክተን ነበር ። ያስጠሩኝም ለዚሁ ጉዳይ መስሎኝ ነበር» አለ ።

«የገበያው ቦታ አይሆንም ። እሱ ከህዝብ ጋር የሚያጣላ አሳብ ነው ። ለስንት ዘመን የኖረ ገበያ ወደ ሌላ ቦታ ይዛወር ተብሎ እንዴት ይጠየቃል! አንተስ ብትል እሺ ። ወጣት ነህና ነገሩን አታውቀውም ። አቶ ጣሴ ደጉካንተ ጋር ማበራቸው ነው የገረመኝ ። አዎ ፣ ችግራችሁ ይገባኛል ። አዲሱ ትምህርት ቤት እስኪሰራ ድረስ ትምህርት ማቆም አይቻልም ። ወርካው ደግሞ የህዝብ አድባር ስለሆነ እሱን መንካት በሰው አምልኮት መግባት ይሆናል ። የህዝቡን ሰላምና ፀጥታ የሚያናጋ ነገር በግዛቴ ውስጥ መደረግ ቀርቶ መታሰብ የለበትም ።

«ግን ቦታው ቢገኝ ስራው ምን ያህል ይፈጃል?» አሉት እየፃፉ ።
«ምናልባት አንድ አመት . . .»
«ከህዝብ የተሰበሰበው ገንዘብ አሁን የት ነው ያለው?»
«በኮሚቴው ስም ባንክ ልናገባው አስበናል» በማለት ዋሻቸው ።

ያቶ ጥላሁን ፊት ድንገት ሲለወጥ ታየው ።

«ህጋዊ ሰውነት ያለው ኮሚቴ ነው?» አሉት ።
«የለውም» አለ ።

«እንግዲያውስ የህዝብ ገንዘብ ራሳቸውን ኮሚቴ ብለው በሰየሙ ሰዎች እጅ መኖር የለበትም ። ገንዘቡ ቢጠፋ ወይም ቢባክን ሁዋላ ተጠያቂው ማን ነው? እኔ ጉዳዩን የምመለከተው በዚህ መልኩ ብቻም አይደለም ። ገንዘቡ የትም ባክኖ ቢቀር ህዝቡ በልማት ስራ ላይ እምነት ያጣል ። እኔ እዚህ እያለሁ እንዲህ ያለ ነገር መሆን የለበትም ። ሀላፊነት አለብኝ ። አንድ ነገር ቢደርስ እጠየቅበታለሁ . . .»

«ህዝቡ ከጣለብን እምነት ሌላ ምን ህጋዊ ሰውነት ያስፈልጋል?» አለ ሀዲስ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አድርጎ ።

«እንዴት! እንዴት!»
«ህዝቡ የጣለብን እምነት አይበቃም ወይ? ማለቴ ነው» አለ ።
«አልጠየቅም ልትል ነው!» ብለው ብድግ አሉ ።

ቁመናቸው እንደ ሸምበቆ የረዘመ ነው ። ከመርዘማቸው የተነሳ ከወደ ጀርባቸው ጎበጥ ይላሉ ።

«አላልኩም» አለ ።
«እህሳ?»

«ህዝቡ እምነት ጥሎብኛል ። አደራ ሰጥቶኛል ። ለኔ ከዚህ የበለጠ ህግ የለም ። ሆኖም ተጨማሪ ግዴታ ያስፈልጋል ከተባለ ኮሚቴው ህጋዊ ሰውነት እንዲሰጠው በፅሁፍ እንጠይቃለን» አለ ።

«እስከዚያስ ድረስ?» አሉት ፣ «ገንዘቡ በማን እጅ ይቆያል?»

ሀዲስ ኮስተር ብሎ ፣ «በኮሚቴው እጅ ይቆያል» አለ ።

ጠረጴዛውን በጥፊ መትተው ፣ «ፈፅሞ! በሰነድ ተይዞ ወደ ወረዳው ካዝና መግባት አለበት ። እምቢ ካላችሁም ምናለ ፣ የጥላሁን ግዛት የሽፍቶች አደባባይ ሲሆን እናያለን ።

«ደግሞም ይህን ያህል ገንዘብ ለትምህርት ቤቱ ብቻ መዋል የለበትም ። የሱጴ ህዝብ ልማት ቅደም ተከተል ይዞ በስራት መስራት ይኖርበታል ። ይህን የሚወስንልኝ ደግሞ ያንተ ኮሚቴ አይደለም ። ግዛቱ የኔ ነው። ገንዘቡን ባስቸኳይ ገቢ ባታደርጉ ሁዋላ ውርድ ከራሴ ብያለሁ» ብለው አሰናበቱት ።

ከአቶ ጥላሁን ቢሮ ወጥቶ በቀጥታ ወደ አቶ ጣሴ ደጉ ቤት ሄደ ። አቶ ጣሴ አትክልታቸውን በመኮትኮት ላይ ነበሩ ።

«ምን ነው ደህና?» አሉት ፣ የፊቱን መጥቆር አይተው ።
«ኸረ ጉድ ፈልቶአል» አላቸው ።
ጉሮሮአቸውን ጠረጉና ፣ «ምን ሆነ?» አሉት ።
ካጫወታቸው በሁዋላ ፣ «ምን ማድረግ ይሻላል?» አላቸው ምርር ብሎ።

አቶ ጣሴ ካንጀት ሳቁና ፣ «ጅብ በማያውቁት አገር ሄዶ ቆዳ አንጥፉልኝ ይላል አሉ» በማለት እንደ ገና ሳቁ ።

«ባስቸኳይ ገንዘቡን ካዝና አስገቡ ነው'ኮ የሚሉት» አለ ።
«የቱ ካዝና?»
«የወረዳው ፅህፈት ቤት ካዝና . . .»

«ወደ ኪሴ ቢል ይሻል ነበር? እሱን ተወው ። የቀን ጅብ ነው ። ከዚህ በፊት ፣ የመጠጥ ውሀ አስገባለሁ ፣ መንገድ እሰራለሁ ፣ የገባን ድልድይ አሰፋለሁ ብሎ ከህዝቡ በግድ የገፈፈውን ገንዘብ የበላው እነሰውና ነው ደግሞ አምጡ የሚለው?

«የመቱና ያዲሳባ ባለ ስልጣኖች መተያያ ሊያደርገው ፈልጎ ነው ። አይምሰልህ ። እሱ ብሎ ለህዝብ ገንዘብ አሳቢ! ያው እንደ ልማዱ ለባለ ስልጣኖች ፣ ቅቤ ፣ ማርና ወርቅ ሊጭንበት ነው ። አጅሬ ይህን ያህል ገንዘብ እጁ ገብቶ ይቅርና ፣ አንዲት ብር ንቆ አይምርም ። ላንድ ብር የድሀ መቀነት የሚያስፈታ ሌባ ነው ! መቼ አጣሁት ። አውቀዋለሁ» አሉት ።

«ታዲያ አሁን ምን እናድርግ ነው የሚሉት?» አለ ሀዲስ ተጨንቆ ።

«ምንም ። ዝም ማለት ነው ። ህዝብ እምነት ጥሎብን የሰጠንን ገን ዘብ ለቀን ጅብ አሳልፈን መስጠት የለብንም ። ምናባቱ ያደርጋል ብለህ ነው?»

«ገፍቶ ከመጣም ሌላ ርምጃ እንወስዳለን» በማለት አደፋፈሩት ። «ምን? እንደምን ያለ?» አለ የልብ ልብ ተሰምቶት ።

«ከዚህ ቀደም የተዋጣው ገንዘብ የት እንደ ደረሰ ህዝቡ መጠየቅ እን ዲጀምር እንገፋፋለን ። ፈስ ያለበት ዝላይ ስለማይችል ያኔ ዝም ይላል ።

«ፖለቲከኛን ማሸነፍ የሚቻለው በፖለቲካ ነው ። ህዝቡ ዛሬ እንደ በፊቱ አይደለም ። አይኑን ከፍቶአል ። ለምን? በምን ምክንያት? እንዴት? እያለ መጠየቅ ጀምሮአል ። ደ'ሞ ልንገርህ ። ስለ ገንዘቡ እንዲያነሳ የገፋ ፋው አቶ ይርጋ ይሆናል ።»

«ካሉስ አቶ ይርጋ'ገንዘቡን የት ነው ያስቀመጣችሁት?'ብለው ጠይቀ ውኝ ነበር» አላቸው ።

«ምን አልከው ታዲያ?» አሉት ።
«እርስዎ ዘንድ መሆኑን ነገርኩዋቸው. . . »

«እዪ አንተ ልጅ!!» አሉ ራሳቸውን ነቅንቀው ፣ «ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ ለልብህ ቢሰጠው ምና'ለበት? ለወደፊቱ ግን አስብበት ። ጥራት ያለው መስተዋት ሆኖ መታየት ደግ አይደለም ። ከቅንነትና ከየዋህነት የተነሳ ሞኝ አትሁን ። ግን አይዞህ ። አትስጋ ። የጀመርነውን በጎ አላማ ከግቡ ሳናደርስ ከንዳችንን አንተራስም ። ጥላሁን ፈሪ ያገኘ መሰሎት ይሆናል የደነፋብህ ።»

ሀዲስ በአቶ ጣሴ ቆራጥነት ልቡ እየተበረታታ ፣ «እኔም'ኮ ህዝቡ ከጣ ለብን እምነት ሌላ ምን ህግ ያስፈልጋል ብዬ ነበር» አላቸው ።

«ልክ ነህ» አሉ አቶ ጣሴ ፣ «ምናባቱ ይሆናል ብለህ ነው ። ግፉ ቢል ያው እንደ ለመደው ትምህርት ቤት ላሰራ ነው ብሎ መግለጫ ይሰጥ ይሆ ናል ። የገንዘቡን ልክ እና ስራው መቼ ተጀምሮ እንደሚያልቅ የጠየቀህም ለዚሁ ነው ። ምን እሱ ፣ ይህን አግኝቶ ይቅርና ሰዎች ወፍጮ ሲተክሉ ' የቡና ማበጠሪያ ሲያቆሙ እኔ የሰራሁት ነው ብሎ የሚደነፋ ሰው ነው ። የውሸት ስታትስቲክ አቀናብሮ በማቅረብ የሚወዳደረው ወረዳ አስተዳ ዳሪ የለም ።

«በሉጼ ይህን ያህል ቡና እግር በዚህ አመት ተተከለ ፤ ይህን ያህል ፈረሱላ ቡና ወጣ ፤ ይህን ያህል የእህል ወፍጮና የቡና ማበጠሪያ ተቋ ቁሞመ—ኧረ ስንቱ? የዶሮዎችና የእንቁላል ቍጥር ሳይቀር በራዲዮና በጋ ዜጣ ሲነገር ይኖራል ። የቡና መሬት እመራችሁዋለሁ ያላቸው ጋዜጠኞች በማስታወቂያ ሚኒስቴር ሳይኖሩት አይቀሩም ። በተለይ መቱ ያለው የዜና አገልግሎት ወኪል ግብረ በላው ነው» በማለት ፣ ስለ አቶ ጥላሁን ሸኖረጋ ያሜውቱት ጀመር. . .

ሌላ ንጋት ። ሌላ ፀሀይ ። ሌላ ቀን ። ሌላ ተስፋ ። ከእንቅልፉ ሲነቃ ሰውነቱ ቀሎት ነበር የተነሳው ። ባሳቡ ቆርጦ ነበር ። ባሳቡ የቆረጠ ሰው

በስራ ግዴታና በፍቅር መካከል ምርጫ ማድረግ ቀርቶ የምንንም ፅዋ ቢሆን ያለ አንዳች ማመንታት አንስቶ መጨለጡ አይቀርም ። የምትቀረንን ጊዜ ከዚህም ከዚያም ሳይሆን በከንቱ ማቃጠል ራሱ የከንቱ ከንቱነት ነው በማለት ወደ ጠረጴዛው ሄዶ ፣ «ውድ አይናለም» ብሎ ገና መፃፍ ከመጀመሩ በር ተንኳኳኳ ። ቶሎሳ ነበር ።

ቶሎሳ ከንብንቡን አውልቆ እየተጣደፈ ፣ «እንሂድ ። አይናለም ከቤት ትጠብቅሃለች» አለው ።

ሀዲስ ወረቀቱን ቀዶ ጥሎ ከቶሎሳ ጋር ተነስቶ ለመሄድ እየተዘጋጀ ፣ «ቤት ሰው የለም?» ይለዋል ።

«ማንም የለም ። ፊታውራሪ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደዋል ። አሁድ አይደለም እንዴ? ስራ ቤቶችም የሉም ። እስዋ ብቻ ናት ቤት ውስጥ ያለችው ።»

«አንተስ ከፊታውራሪ ተለይተህ እንዴት ቀረህ?»

«አዎን ፣ ሌት ከዞብ ፣ ቀን ካጀብ አልቀርም ነበር ። ዛሬ ግን ቤት ጠብቅ ተብዬ ነው የቀረሁት» ብሎት ነጠላውን ከፍ አድርጎ የታጠቀውን መሳሪያ አሳየው ።

«ምን ነው ደህና?»
«አንድ ሴራ በመዶለት ላይ መሆኑ ተደርሶበት ነው ።»
«የምን ሴራ?»
«አይናለምን ጠልፎ ለመውሰድ ።»
«ምን!! ...ማን?»
«መቶ አለቃ አሸኔ።»
«አትለኝም!»

«አዎን ፣ ሽማግሌዎች ልኮ ጠይቆ ነበር ። ፊታውራሪ ይህን ሲሰሙ ያደረባቸው ንዴት መቼም ይህ ነው አይባልም ። 'ይሁን መቼስ ፣ የሰውን ምኞት መከልከል አይቻልም ። ግን ከምኞቱ የድፍረቱ! የራሱን ቦታና የሰው ልክ የማያውቅ ባለጌ! ሞኝ ሲስቁለት ያከበሩት ይመስለዋል። ድሀ በድህነቱ ላይ ትሌት ባይጨምር ምናለበት' እያሉ ሲናደዱ ነው የከረሙት ። እሱም በበኩሉ እንዴት ይንቁኛል በማለት ጠልፎ ሊወስዳት መንገድ እየፈለገ ነው አሉ ። ይምጣና ከጎኑ ያገኘዋል!»

ከቤት ተያይዘው ወጥተው መንገድ ከጀመሩ በሁዋላ ሀዲስ በልቡ ተአምር እያልትም እያለ ፣ «ለመሆኑ እንዴት ደረሳችሁበት እባክህ?» አለው ።

«የተደረገ ነገር ቀርቶ የታሰበም አያመልጠን ። አቶ ይርጋ ፣ 'ሀኪም' የሺጥላና እሱ ሆነው ይህንኑ ሲያሴሩ ነው የሚውሉት አሉ ። የወጠኑት ተንኮል ይገርምሃል ።»

«ምንድን ነው የወጠኑት?»

«አቶ ይርጋ ፊታውራሪን ትምህርት ቤቱን ይጎብኙልን ብለው ሊጋብዙ ። ለትምህርት ቤቱ ስራ ብለው ርዳታም ሊጠይቁ ። ግቢው ባዶ

ሲሆን መቶ አለቃ ከታጠቁ ጥቂት ሰዎች ጋር በጎን ሄዶ እይናለምን ጠልፎ ሲጠፉ ። ቆይቶ ሽማግሌዎች ልኮ ሲታረቅና ሲክስ ።»

«ምን አለውና ይክሳል?»

«ሁብትስ ሞልቶአል ። እያሰረ ፣ እየፈታ ሲዘርፍ አይደለም የሚው ለው? ካቶ ይርጋም ጋር ተሻርኮ ቡና ይነግዳል ። አራጣ ያበድራል ። ገንዘ ብስ ሞልቶታል ። ለካሳው ብዙ ወቄት ወርቅ አዘጋጅቶአል አሉ ።»

«እስከዚህ ድረስ?»

«አዎን ። እድሜ ለወይዘሮ ዝናሽ ከምስጢሩ የማናውቀው ነገር አን ድም አልቀረን ።»

ከትምህርት ቤቱ አጠገብ ደርሰው ነበር ። ሀዲስ ትምህርት ቤቱን ለማ የት አልፈለገም ። ፊቱን አዙሮ አለፈ ። ወደ ፊታውራሪ ግቢ የሚያወጣ ውን መንገድ ሲያያዙ ፦

አይናለም   አይናለም
የማይልሽ የለም . . .

የሚለው ግጥም ባሳቡ መጣበት ። አንድ አይነት ቅናት መጥቶ አደረበት ። ወደ እስዋ ነበር የሚሄደው ። ከቤት ውስጥ ብቻዋን ትጠብቀዋለች ። አለም ከውጭ ይጠብቃታል ። ያለ እስዋ ብቻውን ተመልሶ ለመምጣት የሚችል መስሎ አልታየውም ። ቅናት ልቡን ይዞ ያኘከው ነበር ። እንደሚያፈቅ ራት አወቀ ። እና ፣ ሲቃይ ሆነበት ። ላሳርና ለስቃይ ይሆናል የተፈጠርኩት ብሎ አሰበ ። ከግቢው የውጭ ካብ አጠገብ ሲደርሱ ነበር ብዙ የጠብመንሻ አፈሙዞች ከካቡ ላይ ብቅ ብቅ ብለው የታዩት ። ቶሎሳ ፊት ፊት ቀድሞ እየመራው ዋናውን ቤት አልፎ ወደ ጉዋሮ ወሰደው ።

አይናለም ካንድ ትንሽ የሳር ጎጆ ቤት ጥላ ውስጥ ጠጉርዋን ግራና ቀኝ እንዝርግጋ ለቃ ቁጭ ብላ ነበር ። ጎጆይቱ በቤተ ክርስቲያን ቅርፅ የተሰ ራች ክብ ነበረች ። ጎጆይቱን የከበበችው ትንሽ መስክ አረንጉዋዴ የፋርስ ምንጣፍ ትመስላላች ። በእንክብካቤ የተያዙ ፅጌ - ረዳና ጋሩፋ አበባዎች ከጎጆዋ ደጃፍ ላይ ይታያሉ ። ከጎጆዋ በስተቀኝና በስተግራ ትንሽ ራቅ ብሎ የትርንጎ ፣ የሎሚ ፣ የሮማን ፣ የብርቱካን ፣ የዘይቱንና የእንኮይ ዛፎች ነበሩ ።

ቶሎሳ እንደ ጥላ ውልብ ብሎ ከጎኑ ጠፋበት ። ከሰላምታ አስቀድማ አበቦቼ ደስ አይሉምን» አለችው ።

ካንገቱ ጀምሮ እስከ ጫፉ ድረስ በጥልፍ ያጌጠ ረጅም ቀሚስ ለብሳ ነበር ። ትልቅ የወርቅ መስቀል ጡቶችዋን ለሁለት ክፍሎ እመሃላቸው ተጋ ድሞ ይታያል ። ከትከሻዋ ላይ ወርዶ የወደቀው ጠጉርዋን በይበልጥ አያ ጠቆረው ፣ ማን በይበልጥ ማንን ያደምቃል? የሚል ፉክክር የገጠሙ ይመ ስላሉ ።

«አንቺ ይበልጥ ደስ ትያለሽ» አላት ።

ጉንጮችዋ እንደ ፅጌ-ረዳ አበባ ፈኩ ።

«ለዚህ ነበር ሳነብ የምውለው ።»
«አሁንስ?» ለጥያቄው መልስ አልሰጠችውም ።

«ከዚች ትንሽ አለም ሌላ አላውቅም» አለችው ፣ አይኖችዋን መስኩ ላይ ከሚጫወቱ ድንቢጦች ላይ አሳርፋ ።

«ትንሽ ገነት ናት» አላት ፣ ያበቦቹ መአዛ እየሸተተው ።
«ሮሚዮና ዡልየትን አንብበሃል፤ እርግጠኛ ነኝ ።»
«አዎን ። ቆይቻለሁ ካነበብኩት ።»

«ልብወለድ እንዲያው ልብወለድ ይባላል እንጂ በሰው ላይ ይደርሳል ።»
«ልብወለድ ቢሆንም የህይወት መስተዋት አይደል?»
«የሮሚዮና የዡልየት ታሪክ በከፊል የኔ ታሪክ ይመስለኛል ።»
«እንዴት?»

«የሮሚዮና የዡልየት አባቶች ጠላቶች ነበሩ ። የኔና የዚህ ሰውዬ አባቶችም እንደነሱ አባቶች ጠላቶች ነበሩ ። ሮሚዮና ዡልየት በጣም ይዋደዳሉ ። ግን የሚዋደዱ ሰዎች እንከን አያጣቸውም እንደሚባለው ሁለቱም ይሞታሉ፤ በመጨረሻ ቤተሰቦቻቸው ሲታረቁ ። የኛ ታሪክ እዚህ ላይ ለየት ይላል ። እኔና ልጁ በአይን ተያይተን አናውቅም ። አባቶቻችን ናቸው በግድ የሚገፋፉን ። በልጆቻቸው ጋብቻ ቃል ኪዳን ሲገቡ ። ቢታረቁ ደስ ይለኛል ። እኔ ግን የቃል ኪዳን ማሰሪያ መሆን አልፈልግም ።»

«አዎን ፣ እሱን በደብዳቤሽ ገልፀሽልኛል...»
«ታዲያ ምን ነው መልስ ያልፃፍክልኝ?»
«አሳቤን መቁረጥ አቅቶኝ ነው ።»
«አሁንስ?»

ጠጋ አላት ። ከተቀመጠችበት ተነስታ ወደ ሁዋላ አፈገፈገች ። ደመነፍሱን በይበልጥ ተጠጋት ። ከሁዋላዋ ግድግዳ ስለነበረ የምትሸሽበት ቦታ አልነበራትም ። እጆችዋን ይዞ ወደ እሱ ሲስባት በልጃገረድ ስሜትዋ እየተከላከለችው ፣ «ምን ሆንክ? ሰው ይመጣብናል!» ብትለውም ጨክኖ ሊለቃት አልቻለም ። ያደረበት ስሜት ከማሰብ ችሎታው በላይ ሆኖ እንደ ፈረስ ይጋልበው ነበር—እየገረፈው ፣ እየኮረኮረው ፣ እያጋለው... እና ፣ እሱዋም የልጃገረድ እፍረትዋን ገልጣ በግለቱ ሃይል ውስጥ ባህር እንደገባ ጨው እየሙዋሙዋች ትሄድ ነበር—የስሜት ጣእም—የምድር ጨው—የባህር ጨው—የህይወት ሽቱ መአዛ ገነት—የፀሀይ ስባሪዎች ፍንጣሪ—ዘላለም ።

ጥልቀቱ መጨረሻ ከሌለው ህይወት ባህር ውስጥ ሰጥሞ እንደ ወጣ ያህል በረጅሙ ተንፍሶ ለቀቃትና ፣ «ካንቺ ጋር የትም ብሄድ ደስ ይለኛል ። ከዚች ትንሽ ገነት መሰደድ አይሆንብንም ። ፍቅራችን ትልቅ ገነት በሆነልን ነበር ። ካንቺ ጋር ሆኜ ምን ገሃነም ይኖራል? ግን...»

«ግን ምን?» አለችው ።

ግድግዳውን እንደ ተደገፈች ነበር ። እንደ ሀር ነዶ ተዘናፍሎ የተበተነውን ጠጉርዋን ከፊትዋ ላይ ዞር አደረገች ። እንደ ፅጌረዳ ፈክቶ ፊትዋ ላይ አንድ አይነት ጥላ ይጫወት ነበር ።

«አደራ አለብኝ ። »
«የምን አደራ?»

«የህዝብ አደራ ። ምናልባት ስለ ትምህርት ቤቱ ሰምተሽ ይሆናል ። ከህዝቡ ገንዘብ ሰብስቤአለሁ ። አየሽ ፣ ህዝቡ እምነት ጥሎብኛል ። ይህን እምነት አጉድዬ ብጠፋ የት እደርሳለሁ? የትም ብደርስ ከገዛ ህሊናዬ ላመልጥ አልችልም ። እርግጥ ፣ ህዝቡ አንድ ሰሞን ጉድ ብሎ ነገሩን ይረሳው ይሆናል ። አንድ እምነት-ቢስም ሰው ተስፋ ላያስቆርጠው ይችላል ፤ ትዝብቱ ነው እንጂ ህዝቡ ምን ጊዜም ቢሆን ተስፋ አይቆርጥም ። እኔ ግን ከህሊናዬ ገሃነም አልድንም ። ከመጥፎ ህሊና የባሰ ጅራፍ የለም ። የምልሽ ሁሉ ትርጉም ላይሰጥሽ ይችል ይሆናል ። አላውቅም ። እንዴት ብዬ ላስረዳሽ እንደምችል ይቸግረኛል።»

«ታዲያ ለምን መጣህ?»

አይኖችዋ እንባ አላቀረሩም ። ንዴት ነበር የሚፈነጥቁት ። የተስፋ ማጣት ጥላ ፊትዋ ላይ ያንዣብብ ነበር ። -እንደ ገና እቅፍዋ ውስጥ ገብቼ በሙዋሙዋሁ ፣ ትንሽ ተስፋ በሰጠሁዋት ፣ የሚል ስሜት ነበር ያደረበት ። ግን የሚሰጣት ተስፋ አልነበረም ። ውስጡ ባዶ ሆነበት ። እንደ አዳም ከጎድኑ አንድ አጥንት አውጥቶ የሰጣት ይመስል ስሜቱ ውጋት ሆነበት ። ትንሽ ገነት።—ከህይወት ዛፍ ላይ የፍቅር ፍሬ እንብላ ስትለኝ እምቢ ማለቴ ስለ ምን ነው? ከዚች ትንሽ ገነት ከእስዋ ጋር ወጥቼ ብሰደድ፣ ስደት ከሆነ— ራሱ ፅድቅ አይደለምን? ገሃነም አባቱን! ግን በዚህ አለም ስንቱን ተመኝተን እንዘልቃለን? ምኞት ። ምርጫ ። ውሳኔ ። ስቃይ ። ህይወት ስቃይ ነች ። ብትሆንም እንኖራታለን ። ጥያቄው ፣ ከህሊናችን ጋር ሰላም ኖሮን እንዴት እንኑራት ነው ። እ ፣ አንተ የህሊና እሾህ! አንተ የተረገምክ ትምህርት ቤት! . . .

«ምን ነው ዝም አልክ?»
«ምን ልበል?»
«ተስፋ ጥዬብህ ነበር ። »

«አውቃለሁ ። ግን ተስፋ ልሰጥሽ አልቻልኩም ። አዝናለሁ ። ለራሴ ነው የማዝነው ። ምናልባት ሞኝ ሳልሆን አልቀርም ። ነኝ. . .»

«ይህን ልትነግረኝ ነው የመጣኸው?»

ፊትዋ ላይ ያንዣብብ የነበረው ጥላ ጠፍቶ እንደ ማለዳ ሙሉ ፈካ ማለት ጀምራ ነበር ።

«አዎን ። እና ልሰናበትሽ» አላት ።

«ስንብት» ብላ ቃሉን ደገመችና ፣ «በዚህ አለም በቀላሉ መሞት የሚቻልበት መንገድ አለ ይሆን?» ብላ ጠየቀችው ።

ከንፈሮችዋ ሊፈነዱ የደረሱ የፅጌ-ረዳ እምቡጦች መስለው ነበር ፣ አይኖችዋ ላይ የሆነ መራራ ቀልድ ብጤ ይነበባል ።

«ቀላል ሞት የለም» አላት ።
«ለምን?»
«ህይወት ትተናነቀናለች ።»

«ሞት ምን ይመስላል?»
«በምን አውቃለሁ?»
«እንዲያው ሲታሰበው?»

«የህይወት አለመኖር ይመስለኛል ። የሳቅ የልቅሶ—የደስታ የሀዘን፣ የመዋደድ ፣ የመለያየት ፣ የስቃይ የእፎይታ ፣ የተስፋ አለመኖር ። አለ አይደለም ፣ ዘላለማዊ ጨለማና ዝምታ ። አላውቅም . . .»

«ህይወትስ ምንድን ነች?»
«ለራሴም ባወቅሁት ።»

«'አባቴ ይህች አለም፣ ይህች ህይወት ፣ የከንቱ ከንቱ ናት ። ህይወት ማለት ነፋስ እንደ መከተል ነው ። ህይወት እንደ ሽንኩርት ነው—ቢልጡት ውስጡ ገለባ ነው ። ዞሮ ዞሮ የሰው ልጅ የመጨረሻ እድሉ ትቢያ—ትል መሆን ነው' ይላል ። እና ፣ ሁል ጊዜ ከመፅሀፈ መክብብ እየጠቀሰ 'ከንቱ ፣ ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ፣ ሁሉ ከንቱ ነው ። ከፀሀይ በታች ለሚደክምበት ድካም ሁሉ የሰው ትርፉ ምንድር ነው? ትውልድ ይሄዳል ትውልድ ይመጣል—ምድር ግን ለዘላለም ትኖራለች ። ፀሀይ ትወጣለች ፣ ፀሀይ ትገባለች፣ ወደምትወጣበትም ስፍራ ትቸኩላለች ። ነፋስ ወደ ደቡብ ይሄዳል ፣ ወደ ሰሜንም ይዞራል ፣ ዘወትር በዙረቱ ይዞራል ፣ ነፋስም በዙረቱ ደግሞ ይመለሳል ። ፈሳሾች ሁሉ ወደ ባህር ይሄዳሉ፣ ባህሩ ግን አይሞላም . . . ከፀሀይ በታች አዲስ ነገር የለም ። ሁሉ ከንቱ ነፋስንም እንደ መከተል ነው' ይለኛል። እና፣ እኔ ደግሞ ነገሩ ይህ ከሆነ የህይወት ትርጉሙ ምንድን ነው? እላለሁ» አለች ትከዝ ብላ ።

«አባትሽ ለመሆኑ ስንት አመት ይሆናቸዋል?»
«ስድሳ ወይም ስድሳ ሁለት ። ትክክለኛ እድሜውን አላውቅም ።»
«ከዚህ በላይ እድሜ ቢጨምሩ የሚከፋቸው ይመስልሻል?»

«እኔ እንጃ ። እንዳባባሉ ከሆነ ህይወት ለሱ ዋጋ የላትም ። በዚህ አለም ሁላችንም በጉዞ ላይ ያለን እንግዶች ነን ።»

ሀዲስ ሳቀና ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አድርጎ «እንዲህ አይነቱን ስብከት አትስሚ ። እድሜን ጠገብኩ በቃኝ የሚል የለም ። ህይወት ትተናነቀናለች ብዬሽ የለም ። ህይወት ከንቱ የከንቱ ከንቱ አይደለችም ። በህይወት የመጀመሪያ ግዴታ ህይወትን በፀጋ መቀበል ነው ። የህይወት ኮስታራ መልክ በግድ ፈገግ ልትል የምትችለው ያኔ ነው ። በዚህ አለም ተስፋ ከመቁረጥ መታገል ይሻላል። ለመኖር የምናደርገው ትግል እራሱ ክቡር ዋጋ ነው። እርግጥ ሞት አይቀርም ። ሆኖም የማይቀር ሞትን በህይወት ፀንተው መጠበቅ ጀግንነት ነው ። የሰውን ልጅ ከወራዳ ሞትና ከትቢያ በላይ ሚያውለው ምን መሰለሽ? ጀግንነቱ ነው—ለህይወት ያለው ፍቅርና በህይወት ላይ ያለው ፅናት ። የሌላ ግብ መረማመጃ አይደለችም ። አማራጭ የሌላት ራስዋን የቻለች ግብ ፣ ክቡር ነገር ነች ። ይህች ውብ አለም ቤታችን ናት ። ሌላ ቤት ያለን አይመስለኝም ።

«ብዙ ጊዜ ስለ ጭንቀት ፡ ስለ ሰቃይ ስናስብ የህይወት በረከት ፣ ፀጋና ውበት ይዘነጋል ። ጤነኛ ሰው ስለ ጤናው አያስብም ። ግን ትንሽ የጤና እክል ሲያገኘው ስለ እስዋ ይጨነቃል ፣ ይበሳጫል ። ስለ ህይወትም ያለኝ አስተሳሰብ እንደዚሁ ነው ። ውበትዋ ፣ ልግስናዋ ፣ በረከትዋ አይታሰበ

ንም ። ለምን ስለ ሞት እናስባለን? ህይወት ከፊታችን ተደቅና እያለች፣ ሙሉ ግርማ ሞገስዋን ተጎናፅፋ እየተንቦገቦገች ስትጠራን ለምን እንሸሻታለን፣ የሰው ልጅ ጀግንነት መለኪያ ከዚህ ላይ ነው» አላት ።

አሁን የቀልድ ነገር አይኖችዋ ላይ አይነበብም ። ከትንሽ ገንትዋ ባሻገር ሩቅ እየተመለከተች ቁምነገር በተሞላበት ድምፀት ፣ «አዎን ፣ እንዲልከው ህይወት አማራጭ የላትም ። ግን በህይወት ምርጫ ስናጣ ምን እናደርጋለን፣ ዝም ብለን የሚመጣውን ሁሉ እንቀበላለን? ወይስ ምን እናደርጋለን? 'ምን ነው እንደ ርብቃ ፈቃደኛ ብትሆኚ?' ይለኛል አባቴ ። እኔ ርብቃ አይደለሁም ። እንደ ይስሃቅም ያባቴን ፈቃድ ለመፈጸም ለመስዋእትነት እንደ በግ አልጎተትም ። እየሀ ፣ ምርጫ የለኝም ። እና ፣ ምርጫ የሌላት ህይወት ምንድን ናት? ከሞት አትሻልም» አለችው ።

«ታዲያ ምን ልታደርጊ አስበሻል?»
«ገና አልወሰንኩም ። ደህና ሁን ።»

ከመሄዱ በፊት እቅፍ አድርጎ ሊስማት ፈልጎ ነበር ። ተከላከለችው ። «ጉንጭሽን ስሜ ብሄድ ምናለበት?»

«አይሆንም ። ይልቅ ስራው እንዲቃናልህ እመኛለሁ ።»
«የቱ ስራ?»
«የትምህርት ቤቱ ስራ ። ባይሆን አንተ ምርጫ አለህ ።»

የቀሎሳን ጥላ ያየ መሰለው ። ግን ዞር ሲል ቀሎሳ የትም አልነበረም ። የጡዋትዋም ፀሀይ ሞቅ ብላለች ። አበቦቹ ደረታቸውን ገልብጠዋል ። ንቦች ካንዱ አበባ ወደ ሌላው እየበረሩ ማር ይቀስማሉ ። ርግቦች ከዋናው ቤት ጣራ ላይ ተነስተው አንዴ ደረታቸውን አንዴ ጀርባቸውን ለፀሀይዋ እየሰጡ ይበራሉ ። ዞር ብሎ ፣ ምናልባትም ለመጨረሻ ጊዜ ፣ አይኖቹን ጣል ካደረገባት በሁዋላ ፣ «እንችንም ይቅናሽ» ብሎአት ሊሄድ ሲል ፣ «አንዴ ቆይ» አለችው ። ቆም አለ ።

«ተዋውቆ መለያየት መጥፎ ነው ።»

«አዎን መጥፎ ነው ። 'ግን አልፎ አልፎ ያጋጥማል ' እና ፣ አቁስሎ ይተወናል ።»

«ፍቅር እንከን አያጣውም ይባላል ።»
«አዎን ። እንከን የማያጋጥማቸው የታደሉ ናቸው ።»

«አለመታደል ክፋ!» ብላ መስቀልዋን ከንገትዋ ላይ አወለቀችና ልትሰጠው ስትል ፣

«ለምን ብለሽ?» አላት ።

«ለትምህርት ቤቱ» ብላው እጅዋን እንደ ዘረጋች ስታስብ ቆየችና ፣ «መስቀሉን ሽጠህ በምታገኘው ገንዘብ ለትምህርት ቤቱ ጥሩ ደወል ስራበት ። መታሰቢያ ይሆነኛል ። ምኞቴ ነው ። ተቀበለኝ» አለችው ።

«እመኛለሁ ። በተደወለ ቁጥር ድምፁ የሚያስተጋባ ግሩም ደወል፣ ለዘላለም ሲደወል የሚኖር ደወል አሰራልሻለሁ» ብሎ ፣ መስቀሉን ተቀበላት ።

አይኖቹ እንባ አቅረው ነበር። ጉንጭዋን ሰጠችው። እንባዋን ቀመሰ። ጥሎአት ሲሄድ የገዛ ስሜቱን ከመፍራቱ የተነሳ መለስ ብሎ አላያትም። የእንባዋ ጨው ጣእም ብቻ ነበር ምላሱ ላይ የቀረው። መለስ ብሎ ሊያያት ልቡ እየፈለገ መለስ አላለም። ምላሱ ላይ የነበረው የእንባዋ ጨው እንደ ሎጥ ሚስት የጨው አምድ አድርጎ እዚያው እንዳያስቀረው ወደ ሁዋላ የሚጎትተውን የስሜት ገመድ በግድ ወደ ፊት እየሳበ ሄደ፤ የወጣችው ፀሀይ ጨለማ ሆናበት . . .

# ክ ፍ ል ፲፩

ተማሪዎቹ ከጥቁር ሰሌዳው ላይ የተፃፈላቸውን የቤት ስራ በጥድፊያ ይገለብጣሉ ። ከክፍል የሚወጡበት ሰአት ተቃርቦአል ። ልባቸው ወደ ሜዳ ሮጦአል ። ጆሮአቸው የሚጠብቀው የደወሉን ድምፅ ነው ።

ደወል ። ሀዲስ ካንገቱ ላይ ከልቡ አጠገብ ያንጠለጠለውን የአይናለምን ወርቅ መስቀል አስታወሰ ። ልቡን ሞቅ አለው ። መስቀሉ ከልቡ አጠገብ እንዳለ ለማወቅ ደረቱን ዳበሰ ። እዚያው ነበር ። መስቀሉን ባለመሸጥ ወስኖአል ። ገና ባያስገምተውም ፣ ግምቱን ከኪሱ አውጥቶ ለመክፈል ቁርጥ አሳብ አድርጎ ነበር ። መስቀሉ ካ ነገቱ ሳይለይ ፣ ከልቡ አጠገብ ሳይርቅ ፣ አብሮት ከርሰ መቃብር መውረድ ነበረበት ። ከአይናለም መስቀል የሚለየው ነገር ፈፅሞ አልነበረም ።

ሰአቱ ደርሶ እስኪደወል ድረስ በመስኮት ወደ ውጭ ሲመለከት ከርቀት ላይ አመፀኛው ወርካ በኩራት ደረቱን ለፀሀይ ገልብጦ ሰጥቶ ቆሞ ታየው ። የህይወት ጥላ ሆነበት ።-ሌላ አማራጭ መንገድ መፈለግ አለብኝ፣ አለ ፣ ጥርሱን ነክሶ ።

ካለፈው እሁድ ጀምሮ አልዘነበም ። ጥቁር ደመና ከሱዱ ሰማይ ላይ መሰብሰብ ይጀምርና ድንገት እንደ ጥላ እልም ብሎ ይጠፋል ። የሱዱ አየር እየወበቀ ፣ መሬቱም ግለት እየጨመረ ይሄድ ነበር ። ወርካው በቅርንጫፎቹና በቅጠሎቹ መሀከል እንደ ካፍያ በሚወርዱት የፀሀይዋ ጨረሮች እየታጠበ ታላቅ የምፀት ፈገግታ እያሳየው የሚቀልድበት መሰሎት ተናዶ ክመስኮቱ ላይ ዞር ሲል ደወሉ ተደወለ ።

ተማሪዎቹ በስርአት ተሰልፈው እንዲወጡ በማለት ቢጮህም የሚሰማው አልነበረም ። ከበረት እንደ ተለቀቁ እምቦሳዎች እየቦረቁ ሲወጡ ፣ ፋጡማ ብቻ ነበረች እንደ ልማድዋ ወደ ሁዋላ የቀረችው ።

«ክፍል ውስጥ ማስቲካ ማኘክ ክልክል ነው ብዬሽ አልነበረም?» አላት ።

ሲያዩዋትም ፣ ሲያናግሩዋትም ፣ ሲቆጡዋትም ሳቅ ይቀናታል ። ከሳቅ አገር የመጣች ትመስላለች ። ፋጡማ ብሎ በስምዋ የሚጠራት አልነበረም ። 'የሳቅ እናት' እያሉ ነበር የሚጠሩዋት ።

«ተደውሎ የለም እንዴ!» አለችው እየሳቀች ።

ጎበዝ ተማሪ ነበረች ። ሁል ጊዜ ከክፍልዋ አንደኛ ትወጣለች ። ታዲያ በፊት እንዲህ ጎበዝ አልነበረችም፣ «አንተ ከመጣህ ወዲህ ነው መጎበዝ የጀ

መረችው» ይሉታል ሌሎች አስተማሪዎች ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በምታሳየው ጥሩ ጥረት እየተደነቁ ። አንዳንድ ተማሪዎችም ጋሼ ሀዲስ አይኑ ስላረፈ ባት ነው በፈተና አንደኛ የሚያደርጋት የሚሉ መሆናቸውን ሳይሰማ አል ቀረም ። የሚያውቀው ነገር ቢኖር እሱን ለማስደሰት ጥሩ ጥረት የምታደ ርግ መሆንዋን ብቻ ነበር ።

የሚያስተምርባቸውን መፃህፍት እየሰበሰበ ፣ «ለመሆኑ ማስቲካውን የት ደብቀሽ ነው የምትይዥው?» አላት ።

«ከምላሴ ስር» ብላው ሳቀች ።
እሱም ነገርዋ አስቆት ፣ «ሳቅሽን ብታካፍይን ጥሩ ነበር» አላት ።
«ምን ያደርግላችሁዋል?»

«ሁላችንም ካንቺ ጋር እንድንስቅ ነዋ ። ሳቅ የደስታ መስተዋት ነው።»

«ሲያዝንም የሚስቅ አለ ።»
«አዎን ፣ ግን እሱ የልቅሶ ዋዜማ ነው ።»

«አባቴ አዲሳባ እህቶችሽ ዘንድ ተቀምጠሽ ብትማሪ ይሻልሻል ይለ ኛል» አለችው ።

«ጥሩ ነዋ» አላት ።
«እኔ ግን አልፈልግም ።»
«ለምን አትፈልጊም?»

«እዚሁ ብማር ደስ ይለኛል ። ያዲሳባ ትምህርት እንደሚሉት አይደ ለም ። በዚህ ላይ ደግሞ የባላገር ኑሮ ደስ ይለኛል ። ያዲሳባን ግርግር አል ወድም ። »

«የባላገር ኑሮ መውደድሽ ጥሩ ነው ። የኢትዮጵያ ሀልውና መሰረት ባላገር አይደል? ሰቃዩም ባላገር ነው ያለው» ብሎአት ሲሄድ ሲል—

«ይህን ሰሞን ካባቴ ጋር አዲሳባ ሳልወጣ አልቀርም» አለችው ።

«እውነት?»

«ግን እህቶቼን ጠይቄ ቶሎ እመለሳለሁ» ስትለው ፣ ያደራ እናቱ እትቱ በለጡ ትዝ አሉት ። ሽክላ የሚመስለው ሰውነታቸው ታየው ። ቀይ አፈር ባይኑ መጣ ። ቁጭ ብለው ስለ ቀይ አፈር ሲያልሙ ታዩት ። የእናቱን ቤትና ትንሽ ገንዘብ የተወላቸው ቢሆንም ከተለያቸው ጊዜ ጀምሮ ገንዘብ አልላከላቸውም ።—ስድስት ወር ሲሆነኝ አይደለም እንዴ ከተለየሁዋቸው? ሲል አሰበና ፣ «የምትሄጂበትን ቀን ከነገርሽኝ የምልክሽ ነገር አለኝ ። ለመ ሆኑ አዲሳባን በደንብ ታውቂዋለሽ?» አላት ።

«እንክት! አካልለዋለሁ» አለችውና ሳቀች ።

እሱም ስቆ ዝባድ ዝባድ የሚለውን ጠረንዋን እየተነፈሰ ወጣ ። አባ ትዋ አቶ መሀመድ በጥሪኝ እርባታና በዝባድ ንግድ በሱዱ የታወቁ ነጋዴ ናቸው ። ከበሩ ወጣ እንዳለ አቶ ይርጋ ያዙትና ወደ ቢሮአቸው ወሰዱት ።

«ቁጭ በል» አሉት ።

—ከመቼ ወዲህ ሰው ቢሮአቸው ሲገባ ቁጭ በል ማለት ጀመሩ? እያለ በመገረም ሄዶ ቁጭ አለ ። ትህትናም አብዝተው ነበር ። የጋረዳትን ጥቁር ደመና ፈልቅቃ ገና ያልወጣች የሳሳች ብርሃን የምትመስል ደካማ ፈገግታ ከፊታቸው ላይ ትጫወታለች ።

«ርዳታ መሰብሰቡ አፍጥኖአችሁ ነበር ። ስራው ላይ ስትደርሱ ምን ያዛችሁ?» አሉትና አንጌ አገሩበት ።

«ለጊዜው ወደ ሁዋላ የያዘን አንድ ችግር ብቻ ነው . . .»
«ገንዘብ አነሳችሁ እንዴ?»

«ገንዘብ አይደለም ። እድሜ ለህዝቡ በቂ ገንዘብ ተገኝቶአል ። ችግር የሆነው የቦታው ነገር ነው ።»

«የምን ቦታ?»

«የት ቦታ ላይ ቢሰራ እንደሚሻል ። መሬት እንዲሰጠን ለመንግስት ማመልከቻ ፅፈን መልሱን እየተጠባበቅን ነው ።»

አቶ ይርጋ ፈገግ አሉ ።

«እስከዚያስ ድረስ?» አሉት ።
«ቁጭ ብለን መልሱን መጠበቅ ነው ።»
«መልሱ ያልመጣ እንደሆንስ?»

«ምን ማድረግ ይቻላል? ምናልባት ትምህርት ቤቱ ለክረምት እስኪ ዘጋ ጠብቀን ስራውን እንጀምራለን—እርጌው ቤት በቆመበት ቦታ ላይ፣ እሱም ፈቃድዎ ከሆነ» አላቸው ።

«ድልድዩን የምንሻገረው ስንደርስ ነው ይባላል ። እስቲ ለዚያ ያድ ርሰን ። ግን ትመለስ የለም እንዴ?»

«ወዴት?»
«ወደ ትምህርት ቤትህ ።»
«አዎ ።»

«ታዲያ የጀመርከውን ስራ እንዴት አድርገህ ልትሄድ ነው ያሰብ ከው?»

«አቶ ጣሴ አሉ ። እሳቸው ስራውን ይቀጥላሉ ። ሲመኙት የኖሩት ጉዳይ ነው ።»

ሰይጣናዊ ፈገግታ አሳዩት ።

ትንሽ ቆዩና ፣ «አሁን የፈለኩህ ለሌላ ጉዳይ ነበር» አሉት ።
«ለምን ነበር?»

«የፊታችን ቅዳሜ ፊታውራሪ ተካ ትምህርት ቤቱን እንዲጎበኙልን ጋብዤአቸዋለሁ ። ሌሎቹም ያገሩ ባላባቶችና ታላላቅ ነጋዴዎች ተጋብዘ ዋል . . .»

«እሺ» አለ ፣ ተንኮሉን እያውጠነጠነ ።

«እና ፣ ትንሽ ንግግር ታደ'ርጋለህ ። ያዲሱን ትምህርት ቤት ፕላንም ታስረዳለህ» አሉት ።

«መልካም ነው ። እዘጋጅበታለሁ» ብሎ ወጣ ።

ፊታውራሪ ጥሪውን ተቀብለው እንደሆነ ወይም አልተቀበሉት እንደ ሆነ ቆይቶ ለማጣራት አልፈለገም ። ጠላት የባላጋራውን ልብ ቢያውቅ እርፎ ይቀመጥ ነበር እያለ ወጥቶ ሄደ ። ግን ፣ ፊታውራሪ ነገሩን እንዴት አድርገው ለመያዝ እንዳሰቡ ቀኑ ደርሶ ለማየት ልቡ ከፉኛ ተነሳስቶ ነበር ። ሆኖም ልቡ እንደ ተንጠለጠለ አልቆየም ። በማግስቱ ፣ «ለቅዳሜ አይመቸኝም ። እንድ ወንድሜ ድንገት እርፎ ሀዘን ላይ ተቀምጫለሁ ። ጉብኝቱ ከልጁ ሰርግ ውጭ እንዲሆን ቢደረግልኝ ደስ እያለኝ እገኛለሁ » የሚል መልስ ፊታውራሪ መላካቸውን ሰማ ። እነ መቶ አለቃ አሸኔ ከዚህ በሁዋላ ምን ያደርጉ ይሆን? የሚል አሳብ ስላደረበት ልቡ እንደ ገና መንጠልጠል ጀመረ ። ምን ለማድረግ እንዳሰቡ ለማወቅ በጣም ፈልጎ ነበር ። እና ፣ ወደ ዝናሽ ቡና ቤት ሄደ ። ቡና ቤቱ በሰው ጢም ብሎ ተሞልቶአል ። ሀዲስ አካባቢውን ለመምሰል ቢራ ካዘዘ በሁዋላ ሰው የሚለውን ጆሮውን ጣል አድርጎ ያዳምጥ ጀመር ። ዝናው በሱጴ ተናኝቶ ስለ ነበር ፣ እንዳንድ ሰዎች አውቀውት ሳይሆን አይቀርም ፣ ተሰርቀው እያዩት ይንሾካሾካሉ ። አብዛኛዎቹ ግን ድምፃቸውን ከጫጫታቸው በላይ ከፍ አድርገው የሚያወሩት ከጥቂት ቀናት በፊት ዳሪሙ ላይ አንድ ባላባትና ሾፌር በጥይት ገድሎ የእርሻ መኪናዎችንም ስላቃጠለ አንድ ገበሬ ነበር ።

«የትኛው ባላባት ናቸው እባክህ ።»

«ቀኛዝማች በቀለ ቱጂ ስልህ—የዳሪሙው ። እኝህ ሰፊ እርሻ ጀምረው የነበሩት—እገሩን በትራክተር ፈንቃቅለውት ነበር ። አቤት! አቤት ! የእርሻው ስፋት ላይን ይታክታል . . .»

«በጀ? እሺ?»

«ቆመው ሲያሳርሱ ድንገት ከተፍ ብሎ አሳቸውንም ፣ የትራክተሩንም ሾፌር በደረት በደረታቸው ለቆ በጥይት ከዘረራቸው በሁዋላ ትራክተሮቹን በእሳት አጋይቶ ሄደ አሉ እየሸለለ ፣ እየፎከረ ። ዋቆ ይባላል አሉ ። አንድ አይና ሰው ነው ይባላል . . .»

ሀዲስ ትዝ አለው ። የዋቆ መልክ ከፊቱ መጥቶ ቁልጭ ብሎ ታየው ። 'ትራክተሮቹ የሚፈነቃቅሉት መሬቱን ብቻ ሆነ፣ያባቶቻችንንም አፅም ጭምር ነው...'ወይም እንዲህ ያለ ነገር — እያለ ለፊታውራሪ ተካ ያሰማ የነበረው ስሞታ መጥቶ ከጆሮው ላይ ደወለ . . .

«አቤት! አቤት! እሺ ፣ በጀ? በምን የተነሳ ነው አሉ እባክህ?»
«ጭሰኛቸው ነበር . . .»
«በጀ?»
«ዘመናዊ እርሻ አስፋፋለሁ ብለው ነቀሉት . . .»
«በጀ? ጉድ ነው እኮ . . .»
«ሁለታችንንም ይብላ እሳቸዋ ! »

«ምን ጃል?»
«አፈሩ ነዋ ።»

«አቤት! አቤት! ታሪክ ነው ። ጉድ ነው እኮ! እንዳመለጠ ቀረ ወይስ ተያዘ?»

«ተያዘ ። ጥይት አልቆበት ተያዘ ሉሉ . . . »
«እዬ ፣ ያሳዝናል . . . »
«ምኑ?»

«አንድ ጥይት ለራሱ ባለማስቀረቱ ያሳዝናል ። ጀግና ሰው ስንቁን መርሳት የለበትም ።»

«ጀግና አልከው?»
«እህሳ?»

«ወንበዴ ብትለው ይሻል ነበር ። ጭሰኛ ሁላ አልነቀልም ብሎ ማመፅ ከጀመረ እኮ ወዳጄ ፣ ነገ ማንም በመሬቱ ላያዝ ነው ። ሁዋላ መዘዙ ብዙ ነው ። አሁንም ቢሆን ቀኛዝማች ላይ የደረሰው ብዙ ነገር ቀስቁሶአል ። ባለ መሬትና ጭሰኛ የጎሪጥ እየተያዩ ሁዋላ አይሆንም ።»

ሀዲስ ሰዎቹ የሚጨዋወቱትን ነገር ማዳመጥ ትቶ ባሳብ ጎዳና ጭልጥ ብሎ ሄደ ። አንድ ነገር ድንገት ተገለፀለት ። ነገሩ እንደ ብርሃን ወለል ብሎ ታየው ። አረመኔአዊ ጭካኔ በተሞላበት ቂም በቀል ተነሳስተህ በግፍ ሰው ገደልክ ብሎ ያገሪቱ ህግ ዋቆ ላይ ይፈርድ ይሆናል ። ግን ያገሪቱ ህግ የማን ነው? የማንን ጥቅም እንዲጠብቅ ነው የተደነገገው ? ከማን ጥቅም አኳያ ነው አይቶ የሚፈርደው? . . . በስርአቱ ላይ የተከፈተ ያንድ ሰው ጦርነት . . . ሰዉ፣ ጀግና ሞተ አይልም . . . አንድ ጥጋበኛ ወንበዴ ተሰቀለ ነው የሚለው . . . ይህንን ነው የሚለው ህጉም ፣ ሌላ ምን ለማለት ይችላል?

ያንድ ሰው ጦርነት ። ያንድ ሰው ሰራዊት ። የት ሊያደርስ? አንድ እጅ ብቻውን አያጨበጭብም ። አንድ እንጨት አይነድም . . .

«መሬት ላራሹ!»
«ፊውዳላዊ አገዛዝ ይውደም!»
«ተው ስማኝ ሀገሬ ፣ ተው ስማኝ ሀገሬ . . .»

የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጩኸት ፣ ብሶት ፣ ትናንት ትቶት የመጣው ክርክር ጭቅጭቅና በመካከላቸው የነበረው ያሳብ መለያየትና የእርስ በእ ርስ ጥላቻ ፣ ንቀትና ሽኩቻ ትዝ አለው ። በህገ መንግስት የተወሰነ ዘውዳዊ አገዛዝ ይኑር ፣ የንግግርና የመሰብሰብ ነፃነት ይታወጅ ፣ ኢትዮጵያ ከዚህ የበለጠ ለውጥ አያስፈልጋትም ፣ በማለት ሽንጣቸውን ገትረው የሚሞግ ቱ ተማሪዎች ነበሩ ። አወናባጅ ፣ የስርአቱ አፈ ቀላጤዎች ፣ የመሳፍንት ቡችሎች ፡ የሲ. አይ. ኤ. ቅጥረኞች ይባሉ ነበር ። እሳት የላሰው አብዛኛው ወገን ደግሞ ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ጥገናዊ ለውጥ ሳይሆን ስር ነቀል ለውጥ ነው ። መሬት ላራሹ የሚለው መፈክር በተግባር ሊተረጎም የሚች ለው ፣ ያዬ ቡችሎች እንደሚሉት በጥገናዊ ለውጥ አይደለም ።

«ፋና ተሰማራ!
እንደነ ሆ ቺ ሚን እንደ ቼ ጉቬራ!»

በማለት ስብሰባውን የስሜት እሳት ሲለቁበት ፣ ተቃዋሚ የሚባሉት ወገኖች ደግሞ በተራቸው ተነስተው ፣ «እናንት ኢትዮጵያን አታውቁዋትም ፣ ኢትዮጵያ ፣ አታውቃችሁም ፣ ባእዳን ናችሁና የባእዳንን አሳብ ልትጭኑባት ነው የምትፈልጉት! የማርክስና የሌኒን ሰይጣን የተጠናወታችሁ ናችሁ» በማለት ሲምሉ ፣ ባዳራሹ ውስጥ ይፈጠር የነበረው ውጥረት ሁሉ ለህዲስ በአይነ ልቦናው ልክ እንደ ፊልም ይታየው ጀመር . . . የኔስ አቋዋም ምን ነበር? ብሎ ራሱን ጠየቀ ።

አሳቡ ያደላ የነበረው ወደ ስር ነቀል ለውጥ ፈላጊዎች ቢሆንም ፣ ልቡ በሙሉ ከነሱ ጋር አልነበረም ።

‘በጽሁፍ ሰፍሮ የሚገኘው የሰው ልጅ ታሪክ የመደብ ትግል ታሪክ ነው ...’

‘የአለም ወዛደሮች ተባበሩ !’

እንዴት? አእምሮው ውስጥ ዘወትር የሚመላለስ ጥያቄ ነበር ። እንዴት? መልስ አልነበረውም ። «የምንናገረውን ለምን በስራ አንገልፅም? ከብዙ ሙኸት ትንሽ ስራ ትበልጣለች ፣ ብዙም ትናገራለች ። ለውጥ ፣ ለውጥ ስለ ተባለ ውሀው ወደ ወይን ጠጅ ተለውጦ የቃና ዘገሊላው ትእምር ሊደገም አይችልም ። ጥያቄው ምን እንበል? ሳይሆን ምን እናድርግ? እጃችን ምን ይስራ? ነው» እያለ ይወተውት ነበር ። ጉዋደኞቹ ፣ «አሁንስ እጅ እጅ አልክ» እያሉ አፍንጫቸውን እስኪይዙበት ድረስ ።

አሁን መልሱን ከዋቆ በማግኘቱ ደስ አለው ። ድርጅት ። አዎን ፣ ድርጅት ፣ አለ ። በኢትዮጵያ ስንትና ስንት አዋቂዎች አሉ ። ነገር ግን የማያስተባብራቸውና የሚያደራጃቸው የለም ። እና ፣ አንድ በአንድ ይሰበራሉ፣ ይማገዳሉ ፣ ወንበዴዎች ተብለው ። አንድ ሽማግሌ ሊሞት ሲል ልጆቹን ሰብስቦ የሰጣቸው ምክርና የምክሩ ሀቅ ባሳቡ መጣበት . . . እያንዳንዱ ልጅ አንዳንድ ዘንግ አመጣ ። ስበሩት አላቸው—አባትየው ። እያንዳንዳቸው የያዙትን ዘንግ ያለ ምንም ችግር ሰበሩ ። ሌሎች ዘንጎች አምጡ አላቸው ። አመጡ ። አንድ ላይ አስሩዋቸው አላቸው ። አሰሩ ። አሁን ስበሩ አላቸው። ሁሉም አንድ በአንድ ለመስበር ሞከሩ ። አልቻሉም ። ህብረት ፣ አንድነት ጥንካሬ ነውና!

ድርጅት ነው የሚያስፈልገን ፣ አለ ። ግን እንዴት? የትምህርት ቤቱን ስራ እጀምራለሁ ብሎ የተነሳበትን ቀን ረገመ ። ሸታዬ ሌላ ቢራ አመጣችለት ።

«መች ሌላ አዘዝኩ?» አላት ። ከእንቅልፍ እንደ ነቃ ሰው ባንኖ ።
«ታዞልህ ነው ። የበፊቱም ተከፍሎአል» አለችው ።
«ማን ነው የከፈለልኝ?»
«ሰው።»

መቼም ጠብ ካልፈለጉ በቀር የሱዴ ሰዎችን ግብዣ አልቀበልም ብሎ መመለስ እንደማይቻል ስለሚያውቅ የታዘዘለትን ቢራ ተቀበለና ፣ «ቢራውን እያሳየሽ የገረፈሽ ሰው አለ?» አላት ።

«ፍቅር የጋራ ሲሆን ነው» አለችውና ከፈተችለት ።

«ልቤ ሁለት ፍቅረኞች አንድ ላይ ማስተናገድ እያቃተው ተቸገሬ ነው . . . »

«ሌላዋ ደግሞ ማን ናት?»
«ጣውንቷ ሽን መቼ አጣሻት?»

«ትምህርት ቤቱ? ዝጋ ባክህ!» ብላው ፣ «ቢራ! ቢራ!» እያለ የሚጮህ ደንበኛ ለማስተናገድ ሄደች ።

እንደ አራት ኪሎ ጋዜጠኞች ለወሬ የተቅበዘበዘችው ነፍሱ አልረካችም ። እነ መቶ አለቃ ለጥቀው ምን ርምጃ ለመውሰድ እንዳቀዱ የሚያውቅበት መንገድ አልነበረውም ።—እንኳዋን ስላይ አልሆንኩ ፣ ብሆን ኖሮ እንዴት ያለ መጥፎ ስላይ ይወጣኝ ነበር! ብሎ ቢራውን አጋመሰና የተቀረውን ጥሎ ተነስቶ ሄደ ። የመንፈስ እረፍት አጥቶ ነበር ። ለወሬ የማይቸኩል የነበረ ሰው አሁን ድንገት ተነስቶ ወሬ ማሽተት የጀመረበት ምክንያት ግልፅ አልሆነለትም ። ሰላም አልነበረውም ። ወደ ፊት መራመድ አልቻለም ። መውጫ መንገድ ከሌለው ጫካ ውስጥ የገባ መስሎት ነበር የሚታየው ። እና ፣ ወርካው ሁል ጊዜ ከፊቱ አይለይም። ዞር ባለ ቁጥር ይገጨውና መውጫ መንገድ የለም ይለዋል . . .

ተነስቶ ወደ ፊታውራሪ ተካ ግቢ ለምን እንደ ሄደም ምክንያቱ አልገባውም ። ሲደርስ ነበር የታወቀው ። ውስጣዊ ሰላም አልነበረውም ። ሲገባ ለማየት የፈለገውን አላየም ። አይናለም አልነበረችም ። ፊታውራሪ ተካና መምሬ መህረ ብቻ ነበሩ ። እልፍኙ ስፋት የጨመረ መስሎ ታየው ።

«ህዘን ላይ ኖት[ሲሉ]ሰምቼ ነው የመጣሁት» አለ እያጉተመተመ ።

ለምክንያት ያለው ነገር ነበር እንጂ ለዚህ ብሎ አልመጣም ።

«እምን—የቀኖዝማችን ነገር አሁን ቢረሱ ምናለበት! ህዘን ማብዛት ፈጣሪን ማማረር ይሆናል ። ደግ አይደለም ። እሱ ሰጠ ፣ እሱ ነሳ ። ተመስገን ማለት ነው» አሉ መምሩ ።

ፊታውራሪ ትክዝ ብለው፣ሲያስቡ ቆዩና ከንፈራቸውን መጠው ሲያበቁ ፣ «እሱማ ነው ። ግን አብሮ አድጎ አብሮ ያረጀት ጉዋደኛ ድንገት ሲለይ ያሳዝናል ። ጉዋደኞችም ባይሆኑ እኮ አንድ ትውልድ የሆኑ ሰዎች እያለቁ ሲሄዱ ማሳዘኑ አይቀርም ። ዋ! የኛ ነገር! ጊዜውም ጭምር አብሮን እያለፈ ነው ። ልጆቻችንን ተክተን እናልፋለን በማለት ልንፅናና ከማንችልበት ጊዜ ላይ ደርሰናል ። ካብራካችን ተከፍለው የወጡ ልጆች ከባዳ አይሻሉም። አናውቃቸውም ። እነሱም አያውቁንም ። የሚገርም ነው» አሉ ።

መምሩ በረጅም ጣቶቻቸው ሪዛቸውን እየጎነተሉ ፣ «ምን ይደረግ! ጊዜ ያመጣውን አሜን ብሎ መቀበል ነው ። ለሁሉም ጊዜ አለው ብሎ የለ? እንደ ጊዜው ማጎንበስ ያስፈልጋል» አሉ ።

ፊታውራሪ እየተከዙ የነጣላቸውን ቁጭት ማፍተልተሉን አቆሙና ፣ «እይ መምሩ!እንደ ጊዜው አጎንብሱ አሉ? እንደ ንጉሱ አጎንብሱ ቢሉ ይሻል

ነበር ። 'ንጉስ የወደደው ፣ ዘመን የወለደው' ይባል የለ? ንጉሱ እብድ ከሆነ ቡዋልት እንደ ትህትና ይቆጠራል ፣ መንፈሳዊ ከሆነ ቄስ ሁሉ አስተዳዳሪ ፣ አማካሪ ይሆናል ፣ የንጉሱ ጠባይ ንግድ ፣ ብልጠት ፣ ቅናትና ሰው ማታለል ከሆነም ፤ ተንኮል ፣ አልጠግብ ባይነትና ብልጠት ፣ አፈ ጮሌነትና ውሸት እንደ ጥበብ መቆጠር ይጀምራሉ ። በእድሜአችን ያየነው ፣ የደረሰ ነገር ነው ። ልኡል ራስ ካሳ 'ፍኖተ አእምሮ—የእውቀት ጐዳና' በተባለው መፅሀፋቸው ነገሩን ጨርሰውታል ። መፃፉስ ቢሆን ፣ 'መቼ መረጣችሁኝ ፣ እኔ መረጥኩዋችሁ እንጂ' ብሎ የለ?» ብለው ትንሽ ተከዙና ፡—

«ሀብት ማጋበስ የጊዜአችን ፈሊጥና አላማ ሆነና ትተነው በምናልፈው ጥሪት ላይ መተላለቅ ጀምረናል ። ንጉስ የወደደው ፣ ዘመን የወለደው ፈሊጥ! አይ ጉድ! ሰው እንዴት የገንዘብ ተገዥ ይሆናል? ለማናውቀው ዘመን የገንዘብ ቤሰኛ መሆን የሚያሳዝን ነው ።

«በውርደት የተበከለ ሽበት ይዞን ወደ መቃብር መውረድ የሞት ሞት ነው ። ሰው በጭሰኛው እጅ ሲጠፋ! አይ ቀኛዝማች! ምክሬን አልቀበል ብሎ ነው' ኮ» ሲሉ ፡—

መምሬ ነገራቸውን አቋዋረጡዋቸውና ፣ «አዩ—የአሳቸውን ነገር ይጉ ውት ብዬ ምን ነው? እግዜር መቼም መሬት ወርዶ ሰው አይቀጣ ። ሰውን የሚቀጣው በሰው ነው » አሉዋቸው ።

«ሊውነት ነው» አሉ ፊታውራሪ ፣ «እግዜር ሰውን የሚቀጣው በሰው ነው ። ልክ ነው ። ጭሰኛም ምሬት ነው ። በሱ ፈቃድ የተመሩብን ናቸው ። ተርበው እንዳያዝኑ ፣ ጠግበው እንዳይበድሉ አድርጎ መያዝ ሲቻል ከመሬት ተነቀሉ ብሎ ማባረር አሁን ምን ይባላል? እንኩዋን በፈጣሪ ፊት ፀሰውም ዘንድ የሚወደድ ነገር አይደለም ።

«ግን ምን ይደረጋል? መወደድና መጠላት ያለበትን ነገር ሁሉ ረስተናል ። ከፉን ከደግ ለይቶ ማየት አቅቶናል ። ከችኩልነትና ከቸልተኛነት አስተዋይነት ፣ ከእብሪትና ከልክስክስነት ትህትና ፣ ከብልጠትና ከሞኝነት ብልህነት ፣ ከጅብደኛነትና ከፈሪነት ጀግናነት ፣ ከብኩንነትና ከንፉግነት ልግስና፣ ከስግብግብነትና ጨርሶ ራስን ከመጣል በቃኝ ባይነት፣ ይመረጥ ነበር። ኢትዮጵያዊ ባህርያችንን ሲገዛ የኖረው ይኸው መካከለኛውን መንገድ መርጦ የመሄድ ተግባራችን ፣ በዚህ ላይ ፈሪሃ እግዚአብሄር ያለን መሆናችንና ያገር መውደድ ጠባያችን ነበር። ዛሬ ይህ ሁሉ ቀረ . . . »

ፊታውራሪ ተካ ከሙዋቹ ዘመናቸው ጋር የሚያቃስቱ መስለው ታዩት—ለሀዲስ። ፊታውራሪ—ከሞት አፋፍ ላይ ደርሶ በማጣጣር ላይ ላለው ዘመን ተጨንቀው ልባቸው የሚደማውን ያህል ፣ የሱም ልብ አቅጣጫ ሳጥቶ በመባከን የሚደማ መሆኑን ሲገነዘብ ሰቆቃቸው ይበልጥ ይሰማው ጀመር ።

መምሩ ጭራቸውን ባዶ አየር ላይ ነሰነሱና ፣ «ባገራችን ትምህርት ብንፀና ኖሮ ይህ ሁሉ ችግር ባልደረሰብን ነበር ። ሳይቸግር ጤፍ ብድር ነው'ኮ ነገሩ ። ያዳቆን ሰይጣን ሳያቀስ መቼ በዋዛ ይለቃል?

«አሁን እንዲያው ማ ይሙት—ያገራችንን ሰማንያ አሀዱ መፃህፍት በሚገባ ያጠና ሰው ከፈረንጆች በምን ያንሳል? በሰማይ ስለ በረሩ ፣ በምድር

ስለ ተሽከረከሩ ፥ አላቂ ልብሳቸውን ስለ አኸጐጐሩት ፥ ፈራሽ ቤታቸውን ስለ ወለወሉና በፎቅ ላይ ፎቅ ስለ ሰሩ የሚበልጡን ይመስለናል ። ገደል ያገባንም ይኸው ነው ። ለብልጭልጭ እውቀትና ኑሮ በራችንን ከፍተን ከሰጠን በሁዋላ ነው ያገር ልማድና ወግ መጥፋትና መርከስ የጀመረው— አባቶችን መንቀፍ ፤ አገርን መዝለፍ የመጣው ። ልማዱንና ምግባሩን መናቀፍ የጀመረ ትውልድ ምን አገር አለኝ ሊል ይችላል? አፈሩ ብቻ አገር አይሆንም! ኧረ ኡዲያ!» ብለው በያዙት ጭራ አየሩን ይገርፉት ጀመር ።

ፊታውራሪ በመምሩ አሳብ አለመስማማታቸውን ራሳቸውን በመነቅነቅ ገለጡና ፥ «ልማዳቸውን ለነሱ ትተን ጥበባቸውን ብንማር አይከፋም ነበር ። ጣልያን ምሽጎችንን ሰብሮ ድንኳኖቻችንን ቅድስት ምድራችን ላይ ለመትከል የበቃው በምን መሰሉት? በጀግንነቱ አይደለም ። ጎራዴ ያችንን መዘዝ ስናደርግበት ‘ግ ግ ሚያ! ግ ያል!’ እያለ የድመት አይን የሚመስሉትን አይሮፕላን እያቁለጨለጨ ራሱን ትኩስ ሳምባ አስመሰሎ ሲምህ አይተናል ። ልብና ወኔስ ከኛ ዘንድ ነበረች ። እኛን የፈታን አርፕላኑ ፥ መትረየሱና ቦምቡ ነው . . .

«ታዲያ እንዲህ አይነቱን ጥበብ ይማሩ ሲባል፥አብዛኛዎቹ ተምረው የሚመለሱት የፈረንጆችን ያኑዋኑዋር ዘዴ ብቻ ሆነ ። የሰውን አገር አለባበስ ፥ አመጋገብና ያስተሳሰብ ዘይቤ የለመደ ልቡ መሸፈቱ ይቀራል? ሽፍቶች ብቻ ናቸው ባገሩ የሞሉት ። ጥንቱን ነበር እንጂ አልሞ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ?» ብለው ተረቱና ወደ ሀዲስ ዞር ብለው፦

«ተጫወት እንጂ» አሉት—

«እያዳመጥኩ ነው» አላቸው ።

መምሩ የያዙትን ጭራ እንደ ገና አየር ላይ ነሰነሱና ፥ «አዎን ግዳ መጥም ትምህርት ነው ። ምንስ ቢሆን የቄስ ልጅ አይደለህ? የዘመኑ ልጆች ለመናገር ትርጣላችሁ ። እኛ የምናውቀው ዝም አይነትዝም መባሉን ነው። አዋቆች ዝምታን የሚመርጡ ከሆነ ለሞኞች ምን ያህል በበጀ ነበር። እህል አንድ ቦታ ላይ አብዝተው ቢዘሩት ፍሬ ይሰጣል? ገለባ ሆኖ ነው የሚቀረው ። ነገርም ሲበዛ እንዲሁ ነው ። ብዙ ቢተኙ ይሰለቹ ፥ ብዙ ቢያወሩ ይዘነጉ ይባላል እስከ እኒ ተረቱ ። የዘመኑ ልጆች ዝምታን አታውቁም ፥ እንደበታችሁ የሰላ ነገራችሁ የከረረ ነው ። ፈትል ቢያከሩት ይበጠስ የለም ወይ?» ብለው ወደ ጉዋዳ አግተሩና፥ «ግን ትምህርት ቤት አሰራለሁ ብለህ ገንዘብ ትሰበስባለህ አሉ?!» አሉት ።

«አዎን ። አሁን ያለው ትምህርት ቤት በላያችን ላይ ሊፈርስ ነው ፥ ያሉት ክፍሎችም በጣም ተጣበዋል» አላቸው ።

«ያገራችንን ትምህርት ብታስፋፉበት ነበር እንጂ ይህ የፈረንጅ ትምህርት የምትሉትስ ምንም አልረባንም» አሉት መምሩ ።

ፊታውራሪ አይናቸውን ወደ ጉዋዳ ወርወር ከማድረጋቸው ትሎሳ ከተፍ አለ ። አፍ አውጥተው አልተናገሩትም ። ብቻ እጅ ነስቶ በመጣበት ተመልሶ ወጣ ። የመምሩ አይን ሳት ማለት ጀምሮ ነበር ።

«የሀከምናና የኪዶ ጥበብ ትምህርት ቢስፋፋ ጥሩ ነው» አሉ ፊታውራሪ ፥ «ግን ዛሬ የድሀ ልጅ ሁሉ መማር የሚፈልገው ያስተዳደርና የገ

ቲካ ትምህርት ብቻ ሆነ ። ሰውን የማስተዳደር ስልጣን በትምህርት አይደ ለም የሚገኘው ። እሱ የፈጣሪ ፈንታ ነው ። ከሰው መርጦ ለሹመት ፣ ከእ ንጨት መርጦ ለታቦት ይባል የለ?» ሲሉ—

መምሩም ለጠቁና ፣ «በህክምናውስ ቢሆን ፈጣሪ ያላለው ይሆናል? እድሜን የሚቀጥል ሀኪም የለም ። እሱ መድሀኒት ይሁን ያላለው መድሀ ኒት ሊሆን አይችልም ። የፈረንጅ ጥኝነት እስከዚህ ድረስ ነው ። እድሜን ቆርጠው እስካልቀጠሉ ድረስ በምንም አይበልጡን ። የኛው ስር መማስና ቅጠል መበጠስ ይሻላል ። እነሱ የሚያውቁት ይህን አትብሉ ፣ ያንን አት ጠጡ ማለት ብቻ ነው ። እሱ ያለው ላይቀር» አሉ ።

ቶሎሳ ሁለት ብርሌ ጠጅና ሻይ በብርጭቆ ይዞ መጣ ። ሀዲስ ምን ነው አሁን ቶሎሳን ባደረገኝ? የሚል አሳብ መጣበት ። እንደዴ ወደ ጉዋዳ ዘው ብሎ ገብቶ የአይናለምን አይን አይቶ ቢመለስ ደስ ባለው ነበር ። ግን ሳይ ወድ ቁጭ ብሎ በሚያስለቸውና በማይጥመው ጭውውት መካፈል ነበረ በት ።«አብዛኛዎቻችን ወደ አስተዳደርና ወደ ፖለቲካ ትምህርት የምናዘ ነብለው ወደን አይደለም ። ምክንያት አለው» አላቸው ።

«ምንድር ነው ምክንያቱ?» ብለው ጠየቁት ፊታውራሪ ።

መምሩ ሀዲስ የተናገረውን የሰሙ አይመስሉም ። የብርሌአቸውን አንገት ጨብጠው ጠጃቸውን ያንዶቀድቁ ነበር ። ማንቁርታቸው በሰመ መን ተይዛ ከፍ ዝቅ እያለች ከጠጁ ጋር ስትጫወት ትታያለች ።

ሀዲስ ጠጉሩን እንደ ልማዱ ቆፈር ቆፈር አደረገና ፣ «እንደሚታወ ቀው የእደ ጥበብ ሙያ ባገራችን የተጠላ ነው ። አቶ ሀዲስ አለማየሁ 'ፍቅር እስከ መቃብር' በተባለው መፃፋቸው እንደ ገለጡት ፣ ነጋዴው መጫኛ ነካሽ ፣ ገበሬው አፈር ገፊ ፣ ሸማኔው ቁጢት በጣሽ ፣ አንጥረኛው ብረት ቀጥቃጭ ፣ ሸክላ ሰሪው ፣ ቡዳ ፣ ጠይብ ፣ ፋቂው ወናፍ ነፊ ፣ ድንጋይ ጠራቢ እየተባሉ ከህብረተሰቡ ተገልለው እንዲኖሩ ሲደረግ ቆይቶአል ። አሁንም ያለ ፣ የሚታይ ነገር ነው ። ሰው መቼም የሚሰደብበትን ሳይሆን የሚከበር በትን ሙያ ነው የሚመርጠው ። ባሁኑ ጊዜ የሚያስከብረውም ደሞ ይኸው ያስተዳደርና የፖለቲካ ትምህርት ወይም በጠቅላላው የቀለም ትምህርት ስለሆነ ነው ሁሉም ወደ እዚያ የሚያተኩረው ።

«ባገራችን ለጊዜው አክብሮት የሚሰጠው ሌላ ሙያ የለም ። ድምፃ ዊው አዝማሪ ፣ ስእሊው ቀለም ቀቢ ፣ ፀሀፊው ወረቀት አጥቁዋሪ፣ ሌሎችም እንደዚሁ እየተባሉ በሙያቸው ሲሰደቡ ነው የሚኖሩት ። ለሰውነታቸው ክብር ለሙያቸው ዋጋ የሚሰጥ የለም» ሲል፡—

መምሩ ብርሌአቸውን አኖሩና ፣ «ታዲያ ሙያ ስለ ለወጡ የፋቂ ልጅ የፋቂ ልጅ መባሉ ይቀራል ወይ ? ነብር ቆዳውን ሲለውጥ አይችልም» አሉት ።

ሀዲስ በመምሩ ነገር ተደንቆ እየሳቀ፣ «መቼም ሙያ ሊያንጓጉዱ ሰው ከስማይ ተወስኖ የተሰጠ አይደለም ብዬ ነው» አላቸው ፣

መምሩ በያዙት ጭራ እየናን ገረፉና ፥ «ነው እንጂ ! እሱ ያላለውን የሚሆን ማን አለ? ምድርን የዘረጋ ፥ ሰማይን ያለ ምሰሶ ያቆመ ፥ ቀላያትን የቀደደ እሱ ምን የሚሳነው ነገር አለ? ሁኑ ያለውን ነው የምንሆነው ።

«ለጭቅንት ፥ ለዱግንት ፥ ለምስለኔንት ፥ ባለቅንት ፥ ላንበልንት ፥ ለሻለቅንት ለእንደራሴንት ፥ ለወንበርንት ፥ ለንጉስንት የሚመርጠው ማን ነው ልትለኝ ነው ታዲያ? ገበሬ ፥ ነጋዴ ፥ እንጥረኛ ፥ ቀጥቃጭ ፥ ሸክላ ሰሪ እን ጨት ሰባሪ ፥ እንጀራ ጋጋሪ የሚያደርገው እሱ ነው ። ከሱ ትእዛዝ ውጭ ምን የሚሆን ነገር አለ? ከፀሀይ በታች አዲስ ነገር የለም ብሎአል ጠቢቡ ሰሎሞን ። ሁሉም ይህን አውቆ ፥ የተደለደለለትን እንጀራ አሜን ብሎ ተቀ ብሎ ፥ የበታች የበላይን አክብሮ ቢኖር መቼ ችግር ይገጥመን ነበር ። ለዘ መን ፀንቶ የኖረው ስርአታችን ወጋችንና ልማዳችን መቼ ይናጋ ነበር? ሁሉ ከሆነ ቃልቻ ፥ ማን ይሸከም ስልቻ አሉ ። ሁሉም ሊሆን የማይገባውን ልሁን የሚልበት ዘመን መጣ ። ከዚህ የከፋ አመፅ ምናለ ታዲያ ! ይህን ሁሉ ጣጣ ያመጣው ይኸ ዘመናዊ ትምህርት የምትሉት ፈሊጥ ነው ።

«የገበሬው ልጅ ገበሬ ፥ የነጋዴው ልጅ ነጋዴ ፥ የፋቂውም ልጅ ፥ ፋቂ፥ የቀጥቃጩም ልጅ ቀጥቃጭ—ሁሉም ለዘር ማንዘሩ የተሰጠውን ሙያ ተመስገን ብሎ ካልሰራ ያንድ አገር ኑሮ ዘለቄታ አይኖረውም ። ሁሉም እግ ዜር በጥበቡ ባደለው ሙያ ፀንቶ ቢኖር ፥ ምንኛ መልካም በሆን ነበር ። እንዴ ፥ የወፍ ፥ ያንበሳ ፥ የነብር ልጆች ፤ ወፍ፥ አንበሳ፥ ነብር ከመሆን ሌላ ምን ሊሆኑ ይችላሉ? እኛ ግን የታደለንን ባህርይ ስተን ወደ ጥፋት ጎዳና እያ መራን ነው ። ከመአቱ ይሰውረን ከማለት ሌላ ምን ይደረጋል?» ብለው በረ ጅሙ ተነፈሱና ብርሌአቸውን አነሱ ።

ፊታውራሪ ወደ ጉዋዳ ፊታቸውን መለስ አደረጉ ። ቶሎሳ እንደ ልማዱ ፈጥኖ ከተፍ ሲል በጆሮው አንድ የሆነ ነገር ነገሩት ። እጅ ነስቶ ተመልሶ ወጣ ።

ሀዲስ የመምሩ አስተሳሰብ እየገረመው ፥ «እግዜር ለያንዳንዱ ሰው ሙያ መርጦ ይሰጣል ሊሉ ነው?» አላቸው ።

«እንዴታ!»

«አይመስለኝም ። እርስዎ በሚሉት መንገድ ብንሄድ የት እንደርሳ ለን ።»

«ማን ይደርስብናል? ብትል ይሻል ነበር ።»
«እንዴት?» አለ እየሳቀ ።

«ነጮች ሰልጥነናል ቢሉ አይምሰልህ ። የዋሆች ናቸው ። በሰማይ ቢበሩ ፥ በምድር ቢሸከረከሩ ፥ የሆ ረጠ የጣፈጠ ቢበሉ ፥ የለሰለሰ መኝታ ላይ ቢተኙ ዋጋ የለውም ። ደስ ብሎአቸው የሚኖሩም አይምሰልህ ። ይልቅስ ብስጭት ፥ ጭንቀቱ በነሱ ይብሳል ። የነሱ ነገር የከንቱ ከንቱ ነው ። ደስታ እንደ ባለቤቱ ነው ። ምን አጣን? ተመስገን ብለን እግዜር የሰጠንን መብ ላት ነው ያቃተን ። የነሱ ኑሮ የተሻለ እየመሰለን ነው ጥፋት በራሳችን ላይ የምናመጣው» አሉት ።

ቶሎሳ [illegible]ቬሎፕ የታሸገ ወረቀት ይዞ መጥቶ ለፊታውራሪ ሰጣ ቸው ። ፊታውራሪ [illegible]ቀቱን ተቀበሉና አድራሻውን ካነበቡ በሁዋላ ፥

«የእደ ጥበብ ትምህርት ቢስፋፋ መልካም ነው። አፄ ቴዎድሮስም ጥቅሙን
ተገንዝበውት ነበር። ዋ! እንዳሰቡት ቢሆን ኖሮ እንግሊዝ የታባቱ ደፍሮ
መቅደላ ድረስ ይዘልቅ ነበር? አበሻ ጠላቱ ከያዘው መሳሪያ ጋር ተመሳሳይ
የሆነ መሳሪያ ካለው የማይበገር ህዝብ መሆኑን በአድዋ አስመስክሯል።
ሰው ቀርቶ ምድራችንም ጦረኛ ነው—ለጠላት አይመችም። ያንበሶች መኖ
ርያ፣ የነብሮች ተራራ ነበረች። ዛሬ ግን አይደለም። በጦርና በጎራዴ ታን
ክና አሮፕላን መመከት እንደማይቻል ማይጨው ላይ አይተናል።

«ዛሬ ልብ ብቻውን አይበቃም። የራሳችን መሳሪያ ያስፈልገናል፣።
ጠላት ለጠላት መሳሪያ ይሸጣል ወይ? ምን ቀርጦት! ወዳጅ መስሎ ቢሸ
ጥም ልቆጣጠር ማለቱ አይቀርም። እንደዚህ ያለች ውብ አገር፣ ሁሉም የሚ
መኛት አገር ይዞ መተኛት አይቻልም። ቆንጆ ሴት የሚያገባ ምኝ ነው
አሉ። የተባበሩት መንግስታት፣ ኮሌክቲቭ ሴኩሪቲ የሚባለውም ነገር
እንዲያው ነው። የማንን ነፃነት ማን ይጠብቃል? አለም የጉልበተኞች
ናት። ባይናችን ያየነው፣ የምናውቀው ነገር ነው። የሰላም ዳኛ፣ የነፃነት
ዋስትና ከሃይል ሌላ ነገር የለም።

«ታዲያ ምን ያደርጋል? ይህ እያለ ዛሬ ሁሉም ሆድ አምላኩ ሆነ።
ከገንዘብ ሌላ የሚታየው ነገር የለም። ተብለጭልጮ መታየት ብርቅ ሆነ።
ያገር ጉዳይ ተረሳ። መተሳሰብ፣ መተባበር ጠፉ። በገንዘብ ፍቅር ልባችን
ታወረ፣ ወኔአችን ተሰለበ። የሰው ልኩ የሚታወቅበትም ሚዛን የብር ከረ
ጢት ሆነ። እይ ዘመን! ምን ጉድ ጊዜ ያሳየን ጀመር እባካችሁ?» ብለው
ቶሎሳ ያመጣውን ወረቀት ሰጡት — ለሀዲስ።

የሰርግ ጥሪ ወረቀት ነበር።፣የጥሪውን ወረቀት ኪሱ እየከተተ፣ «አመ
ሰግናለሁ» ብሎ እጅ ነሳ።

ፊታውራሪ፣ «ልጃገረዶችም የርብታን ፊቃደኛነት አጡ» ብለው ተከ
ዙና፣ «በልጁ ላይ አርጩሜ የማይቆርጥ ወላጅ፣ ልጁን ይወዳል ማለት አይ
ቻልም ይል ነበር መኩብብ» አሉና አንድ ነገር ትዝ ብሎአቸው፣ «አስተ
ማሪዩን፣ መክብብን እንደምትመስል ነግሬሃለሁ ከዚህ ቀደም?» አሉት።

«አዎን።»

«ቁርጥ፣ እሱን ነው የምትመስለኝ። እሱም እንዳንተ፣ ስለ እደ ጥበብ
በትነሳ ቁጥር፣ 'በሚሰሩት እቃ እየተጠቀምን፣ እያጌጥንና እየተዋጋን፣
ሰሪዎቹን መልሶ መናቅ ያይምሮ እውርነት ነው' ይል ነበር። ስለ ትምህርት
ቤት መስፋፋትም አጥብቆ ያስብ ነበር። የትምህርት ጉዳይ ከቤተስኪያን
ካልተላቀቀ የእደ ጥበብ ትምህርት ሊስፋፋ አይችልም፤ ያገር ነፃነት ክብር
በቅዳሴ በዜማና በሰባት ቤት ቅኔ ሊጠበቅ አይችልም' ይል ነበር» አሉ
ትና፣ «ዘለቄታ ያለውን ነገር ማሰብህ ደግ ነው። ላንተ የሰጠውን ልብ ለታ
ፈሰም ቢሰጠው ምን ነበረበት? የሱም ልብ በፍቅረ ንዋይ ታውሯል።
ሳያጣና ሳይቸግረው ያባቱን ጭሰኞች፣ ያሳደጉትን አሽከሮች ነቅሎ እያ
ባረረ ነው። ግን ምን ይደረጋል? ቢመክሩት አይሰማ፣ አይቆጡት ነገር
ከእንግዲህ ህፃን አይደለ . . . ለማንኛውም ነገር በሚቻለኝ ሁሉ እረዳሃ
ለሁ» በማለት ቃል ከገቡለት በሁዋላ፣ የነገራቸውን አግጣጫ ቀይረው፣
«ግን እነ እቶ ይርጋ አንተ የጀመርከውን በጎ ነገር የተንኮል ወጥመድ
ሊያደርጉት ማሰባቸው እጅግ ያሳዝናል። እዩ! የሰው ልክ አለማወቅ!»

መምሩ ተቆጥተው ፣ «እሱን ይተውት እባክዎን ። ልብ ቢመኝ አይሆን» አሉ ።

«ማስባቸውም ድፍረት ነው ። ጊዜው ተለወጠና ነው እንጂ እንደዱሮ ቢሆን ኖሮ ከዚህ ደጅ ተጥለው አርባ አርባ መገረፍ ነበረባቸው ። ብቻ ምን ይደረግ? ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል አሉ ። ትንፋሼ እያለ አሁን ማይሙት ! እናቱ ሆድ ተመልሶ ይገባ መሰለው ?»

መምሩ አሁንም ፣ «ይተውት ብዬ ምን ነው? ባልሆነ ነገር መናደድ ደግ አይደለም» አሉ ።

«ሆኖአል እንጂ! ባይሆንም ሆኖአል ። ልቡ ከተመኘ ባያደርገውም አድርጎታል ። ተደፍሬአለሁ ። ያስደፈረኝም ጊዜው ነው። ከዚሁ ሁሉ አስቀድሞ ቢገድለኝ ምን ነበረበት! ሰው ለውርደት ተጎልቶ ለምን ይኖራል? እሱ እኮ የገደለኝ ደፍሮ ሽማግሌዎች የላከብኝ ቀን ነው ። የሱ ድፍረት ፣ የሽማግሌዎቹ ቅሌት ። አይ የሰው ልክ አለማወቅ ። ስልጣኔ እጉል መንጠራራት ነው አሉ? ልክን ማወቅ ነበር ። ምንቸት ጋን አይሆን ። ምጣድ የድስት ባልንጀራ ነኝ ብሎ አለላ ተከድና ቀሚስ ለብሶ ከማድ አይቀርብ ። አይ ሞቱ! ሞት ለካ የሚናፈቅበትም ጊዜ አለ!»

«እዬ ፊታውራሪ ምን ነው ። በተከሉዋት ታቦት ይገዞዎታለሁ ፣ እንዴ! ያስቡ እንጂ ። ኢዮብ ያ መከራ ሁሉ ሲደርስበት የስዎን ያህል አላማረረም ። እስዎ ምን ደረሰቦትና ነው? መቼስ ምኞት አይከለከልም» አሉ ።

«ልኩን የሚያውቅ ሰው ለምኞቱ ልክ አለው ። ለምኞቱ ልጉዋም ያደርጋል ። ልኩን የማያውቅ ባለጌ ብቻ ነው ምኞቱን ስድ የሚለቀው ። ይምጣ ብቻ ያቺን ሰአት ነው በናፍቆት የምጠብቀው ። ልኩን እንዲያውቅ ይደረጋል . . .» ሲሉ ፤ ስለ ምን እንደሚከራከሩ ጠረጠረ ።

«ድርሽም አይል . . .»
«የቱ ዘጋጇለትን አያውቅ ይዘጋጅ የለ?»
«እንደ ተነቃበት አውቆአል።»
«ማን ነገሮት?»
«እኔ ። አስጠንቅቄዋለሁ»
«ማን አልዎትና!»

ከፊታውራሪ ግንባር መሀል ያለው ስር እንደ ምሰሶ ተገትሮ ነበር ። አይኖቻቸው እንደ እሳት ቀልተው እሳት የሚተፉ መስለው ነበር ። ሰስ ጠጉራቸው ቆሞ የቆሰለ አውሬ መሰሉ ። ከተቀመጡበት እንደ ወጣት ተወርውረው ተነስተው ፣ «እንዲያው ማን አልዎት! ምን ሊደረግ ሄደው ነገሩት! ጉድ ነው የሰሩኝ ዘንድሮ ። እንደ ዘንድሮ ጉድ ሆኜ አላውቅም ። እዩዩ... ጥፋት ነው የሰሩት» አሉ በጎረና ድምፅ እንደ ቆሰለ አውሬ እያጉዋሩ ፣

መምሩም በበኩላቸው ተነስተው የያዙትን ጭራ ባዶ አየር ላይ እየነሰነሱ ፣ «ጥፋት አይደለም» ሲሉ :—

ፊታውራሪ ፣ «ነው እንጂ! ከዚህ የበለጠ ጥፋት ምናለ! ሳይጠይቁኝ ፣ ሳያማክሩኝ እንዴት ብለው! የውርደት ማቅ ተከናንበህ ፣ ሽበትክን በቅሌት ለውሰህ ፣ ዘር ማንዘርህን አዋርደህ ቅር ነው የሚሉኝ!» ብለው ሲመሁባቸው ሀዲስም በነገሩ እርግጠኛ ሆነ ።

«ኧረ በወላዲትዋ! አይደለም ። ትንሽ ሰው መቼም ትንሽ ነው ። እንቦ ያሳንሳል የተባለው ተረት እንዳይደርስቦት ነው ። ዝቅ ብለሁ ካንድ ትንሽ ሰው ጋር ግብግብ መግጠም ምን ያስፈልጋል? የባሰ ውርደት ነው ። ከት ንሽ ሰው ጋር እልክ ከገቡማ የባሰውኑ የልብ ልብ መስጠት ይሆናል ። እንዴ!! ባለጌን ንቀው ሲተውት ነው'ይ አለዚያማ አብሮ መዋረድ ይመ ጣል ። አልነቁብኝም ብሎ ቢመጣና በደጅዎ ነፍስ ቢያልፍ መጠየቅዎ ይቀራል?»

«ማን ነው የሚጠይቀኝ? ታጥቆ የመጣ ሌባ ደጄ ቢወድቅ ምን የሚያ ስጠይቅ ነገር አለ! ልጅህ ተገዳ ስትወሰድ ዝም ብለህ ማየት አለብህ የሚል ህግ የለም ። አባክዎን ይተውኝ ። ነገር ካበባሹ በሁዋላ ምን ያደርጋል!» አሉዋቸው ሎሽው ።

«የለም ፊታውራሪ» አሉ መምሩ አዘንብሎ የሚታየውን ክብሳታቸ ውን እያስተካከሉ ፣ «ከሉ ጋር ግብግብ መግጠም የርስዎን ክብር ቀንሶ የር ሱን ጀግንነት ከማሳየት ሌላ ትርፍ የለውም ። አይሆንም ። ባለጌን ከሩቅ መሸሽ ነው የሚሻለው ። እንዴ! ስንት ዘዴ እያለ ካንድ ትንሽ ሰው ጋር ግብግብ ለመግጠም እንዴት ይፈልጋሉ? ሁዋላ አይሆንም ። በተከልዋት ታቦት ይዝዎታለሁ ።

«ሰይጣን ሊያስተን አይገባም ። በልጅዎ ፈቃደኛ አለመሆን እንደ ዚያ ሲያዝኑ የታፈሰ ነገር ተጨመረብዎት ። በሙቶ አሊቃው ድፍረት ሲያ ዝኑ የቀኛዝማች በቀለ መርዶ መጣብዎት ። ሀዘን ሲበዛ ደግ አይደለም ። ለሰይጣን መግቢያ ቀዳዳ ይሆናል ። ሰይጣን ሲፈታተንዎት ነው ። በዚህ እድሜ እልክ መግባት የለቦትም ። ለዚሁ ብለው አይደለም እንዴ ልጅዎን ለፊታውራሪ አያና ልጅ ለመስጠት የወሰኑት—ቂም በቀልን ፣ እልክን ከል ብዎ ለማውጣት? ከመቼው ረሱት? አዎን . . . ሰይጣን ሲፈታተንዎት ነው። ሌላ አይደለም ። እንደ ጀመሩት ልብዎን ወደ ዳዊት አምላክ ይመልሱ» ብለው ሲጨርሱ ፊታውራሪ መልስ አልሰጡም ።

«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» ብለው ዝም አሉ ።

መምሩ ፣ «አዎን ። አሜን» ብለው ወደ ሀዲስ ዞር በማለት ፣ «የሰማ ነውን በልቦናችን ያሳድር ። ግን ሲያዩህ ማር ካፍህ ጠብ የሚል አይመስ ልም» አሉት ።

«ልጃችን ነው ። ሰዎቹ ለሱም የሚተኙ አይደሉም ። ተጠንቀቃቸው» እንዳሉት—አቤት! አቤት! የሚሉ ሰዎች ጩኸት ከደጅ ይሰማ ጀመር ።

—አቤት! አቤት! አቤት!

«ምንድን ናቸው?» አሉ ፊታውራሪ ።
«የልጅ ታፈሰ ጭሰኞች ናቸው» አለ ቶሎሳ ።
«ምንድን ነው የሚፈልጉት?»
«አቤት ለማለት ነው የመጣነው ይላሉ ።»
«ስንት ናቸው?»
«ኧረ ብዙ ናቸው ።»
—አቤት! አቤት! አቤት!

ፊታውራሪ ተካ ተነስተው ወደ ሰገነት ወጡ ። መምሬ መሀሪም ተከተ ሉዋቸው . . . ሀዲስ ሳንዳፍታ ወደ ሁዋላ ቀረት ብሎ ፣ ቶሎሳን፣ «እይናለም አሁን እንዴት ናት?» ብሎ ጠየቀው ።

«አሁን ደህና ናት ። እንደ ዱሮዋ መሳቅና መጫወት ጀምራለች» አለው ።

«እውነት?»
«ሁላችንም ደስ ብሎናል ።»
«ቆረጠባት መሰለኝ?»
«አዎ ፣ መቁረጥ ይቀራል? ሲዳሩ ማልቀስ ወግ ነው ።» . . .

—አቤት! አቤት! አቤት!

«ምንድን ነው በደላችሁ? ለማስረዳት የምትችሉ ሰዎች ወደ ፊት ኑ» አሉ ፊታውራሪ ተካ ።

ግቢው ተጣቦ ሲታይ አገር ተገልብጦ የመጣ ይመስላል ። ሁሉም አደ ግድገዋል ።

«አቶ በቀለ! እስቲ አንተ አስረዳ» አሉ ፊታውራሪ ።

ሽበታቸው የተንደፈ ጥጥ የመሰለ አንድ ቀይ ሽማግሌ እንዳደገደጉ ወደፊት ብቅ ብለው መሬት ስመው እጅ ከነሱ በሁዋላ ፣ «እግዚር ያሳይዎ፣ እዚህ እፊትዎ የቆምን ድሆች፣ የዛሬውን አያድርገውና ከወንድምዎ ከቀ ኛዝማች ብሩ ጋር በጥልያን ወረራ ጊዜ በዱር በገደሉ ተዘዋውረን እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ የተዋጋን ሰዎች ነን ። ደስታቸውንም ሆነ መከራቸ ውን ተካፍለናል ። የጌታችን ልጅ መምጣቱን ስንሰማ ፣ ባባቱ እግር ተተ ክቶ ሊሰበስበን ነው በማለት ተደስተን ነበር ። ይኸውና ፣ መሬቱን ለቡና እርሻ እፈልገዋለሁና ልቀቁ በማለት የታጠቁ አሽከሮች ይዞ ቤታችንን በላ ያችን ላይ እያፈረሰብን ነው ። የት እንድረስ አባ ብያ! ካለ እርስዎ ማን አለን» አሉ ሰውዬው እንባ እየተናነቃቸው ።

ሀዲስም እንባው መጣበት ። ከፊታውራሪ ተካ በስተጀርባ ቆሞ ያዳ ምጥ ነበር ።

ፊታውራሪ በለሆሳስ ፣ «አይደረግም!» ሲሉ ሰማ ።

«ተደርጎአል እንጂ ፣ አባ ብያ ። ባይደረግማ መቼ እርስዎን እናስቸ ግር ነበር!» አሉ አቶ በቀለ ።

«ለመሆኑ አሁን እሱ የት ነው ያለው!»

ከሰዎቹ መሀል አንዱ ድምፁን ከፍ አድርጎ ፣ «አባ ብያ ፣ ምድሪቱ ከዳችን ሰማዩ ተደፋብን ፣ ቀኑም ጨለመብን ። ልጆቻችን ሜዳ ላይ ፈሰሱ ። የት እንድረስ እንግዲህ? ከዚህ የት እንሂድ!» ብሎ ጮኸ ።

ሀዲስ እንባውን ለመያዝ አልቻለም ።

«አሁን የት ነው እሱ!» አሉ ፊታውራሪ በቁጣ ።
«እዚያው መሬቱ ላይ ነው» አሉ አቶ በቀለ ።
«ምን እያደረገ?»
«ቤታችንን እያስፈረሰ ነው ።»

ፊታውራሪ ዝም ብለው ሲያስቡ ቆዩና ፣ «አባ መርጋ መካከላችሁ አለ?» አሉ ።

አቶ በቀለ ነበር ፣ «አባ መርጋ ፣'እዚሁ ብትፈልግ ግደለኝ እንጂ ከቤቴ አልወጣም ፣ እይኔ እያየ ቤቴም አይፈርስብኝም' በማለት ከኛ ጋር አልመጣም ። እንደ እሱ በማሰብ ከቤታችን አንወጣም ብለው፤የቀሩ ሌሎች ሰዎችም አሉ» በማለት መልስ የሰጠው ።

«በቅሎዬን ጫንልኝ!» አሉ ፊታውራሪ. . .ይህን ጉድ ባይኔ ሳላይ አልሞትም በማለት ሀዲስ በእግሩ ተከተላቸው ። ሲጋር በቅሎአቸው እንደ ባለሙያ እንዝርት ትሾራለች ። የተከተላቸው ህዝብ ከሁዋላቸው ይተማል ። ከቦታው ላይ እንደ ደረሱ ፊታውራሪ ከበቅሎአቸው ላይ ዱብ አሉ ።

ታፈሰ ሽጉጡን ታጥቆ ሲጃራ እያጤሰ ካንድ ዛፍ ጥላ ስር ቆሞ ነበር። ጥቂት ጎጆዎች እንዳልነበሩ ሆነው ይታያሉ ። የተቀሩትን ለማፈራረስ የታጠቁና ያልታጠቁ ሰዎች ይጣደፋሉ ። ሴቶች ዋይታ ያሰማሉ ። ህፃናት ባዶ ሜዳ ላይ ፈሰው ያለቅሳሉ። የቤት ቁሳቁሶች የትም ተጥለው ይታያሉ ። ውሾች ይጮሃሉ ። ሰንጋ የተጣለ ይመስል ጭልፊቶችና ጆፌ አሞራዎች ከላይ ያንዣብባሉ ። ሜዳ ላይ የፈሰሱትን ጫጩቶች እያነሱ የሚበሩ ጭልፊቶችም ነበሩ ።

«እንዴት! እንዴት! አንተ!» አሉ ፊታውራሪ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ። ግንባራቸው መሀል ያለው ደም ስር እንደ ዘንግ ቆሞአል ። ታፈሰ ሲጃራውን ጥሎ መሬት ላይ ረግጠና ፥—

«ምንድን ነው እሱ?» አላቸው ኮስተር ብሎ ።

«ምን ብዬህ ነበር!»

«ፊታውራሪ» አለ ታፈሰ ፣ «በዚህ ጉዳይ አይግቡብኝ ።»

«እንዴት አንተ! ማን ጠብቆ ባቆየህ መሬት! ሰው የሚልህን ነገር እንዴት አትሰማም? ወይስ ልብህና ጆሮህ ተደፍኖአል!»

«ፊታውራሪ ይተውኝ ብያለሁ!!» አለ ተፈሰ ። በቁጣ ። «እኔ እዚህ የመጣሁት ጭሰኞች የሚሰጡኝን ፍርፋሪ እየለቀምኩ ለመኖር አይደለም ። የመንግስት ስራ ትቼ ገጠር የገባሁት ጭሰኞችን ለመንከባከብ ሳይሆን መሬት ለማልማት ፣ ያለ ስራ የተቀመጠውን መሬት እጥቅም ላይ ለማዋል ነው ። ባባቴ መሬት የፈለኩት ባደርግ የሚያዘኝ ሰው የለም ። መብቴ ነው ። ይህን እንዲረዱልኝ እፈልጋለሁ ።»

ሲናገር ሁሉ የደም ስሮቹ ይገታተሩ ነበር ።

«እነዚህ ደሆች የት ይሂዱ ነው የምትለው? ጎጆ ሰው ላይ ማፈራረስንስ የት ያገኘሽው ትምህርት ነው? እነዚህ ሰዎች ፣ የጌታችን ልጅ ብለው እሽኮኮ እያሉ ያሳደጉህ መሆናቸውን እንዴት ትረሳለህ? ወይስ የገንዘብ ፍቅር እውር አድርጎሃል!» ብለው ሙሁበትና ወደ ህዝቡ ዞር በማለት ፥—

«አባ መርጋ የት አለ? ጥሩት» አሉ ።

አባ መርጋ ጣምራ ምላስ ያለውን ጦር እንደ ያዙ ከህዝቡ መሀል ብቅ አሉ ። ጠይም ፣ ሸበቶ ሽማግሌ ናቸው ። ቁመናቸው ዘለግ ብሎ ከወገባቸው ትንሽ ጎበጥ ይላሉ ። እንጀታቸውን በድግ አስረዋል ።

ፊታውራሪ ወደ ታፈስ መለስ ብለው ፣ «ይህ ሰው ማን እንደ ሆነ ታውቀዋለህ? ወይስ ረስተኸዋል? ረስተኸው ከሆነ እኔ ልንገርህ ። ብጠላት ጊዜ አባትህ በረሃ ለበረሃ ሲንከራተት ጣልያኖች እንዳይገድሉህ እንደ አውሬ በየጫካው እየኖረ ነፍስህን ያተረፈ ሰው ነው ። ባይወልድህም አባትህ ነበር ። ዳሩ ምን ያደርጋል? ወይስ የተማርከው ትምህርት ውለታንና ይሉኝታን ቀቅላችሁ ብሉ ይላል!» አሉት ።

ታፈስ በንዴት ጠጉሩን ነጨና ፣ «እኔ ስለ ውለታና ስለ ይሉኝታ ደንታ የለኝም ። የመጣሁት ላንድ አላማ ነው ። አላማዬን የሚያደናቅፍ ነገር ከፊቴ ቆሞ ማየት አልፈልግም! ከፊቴ መጥፋት አለበት ። በይሉኝታ ታስሬ መሬቴን ጦም አላሳድርም ። በዛሬ ጊዜ ስንት ጭሰኛ አለኝ እያሉ ጭንቅላት መቁጠር ዋጋ የለውም ። ዛሬ ዋጋ ያለው መሬትና እውቀት ነው ። ለኔ ብለው እንደሆነ የፈለጉበት ሊሄዱ ይችላሉ ። አሁንም ፣ በውድ ካልሄዱ በግድ ይለቃሉ ። እንዳልኩት በርስቴ መጠቀም መብቴ ነው!» አለ ጥርሱን ነክሶ ።

አባ መርጋ በሀዘኔታ ራሳቸውን ነቀነቁና ፤ «ታፈስ ፣ በኔ ላይ ጎጆዬን ልታፈርስ? ጡር አይሆንብህም ፣ ልጄ ። የጌታዬ ፣ የቀኛዝማች ብሩ አጥንትስ ምን ይልሃል?» አሉት ፣ እንደ ገደል ማሚቶ በሚያስተጋባ ድምፅ ። ትላልቅ አይኖቻቸው እንባ ቋጥጥረው ነበር ።

ሀዲስ ዝም ለማለት አልቻለም ። ንዴት ጉሮሮውን እየተናነቀው ፣ «ታፈስ ፣ እባክህ እነዚህን ሰዎች ተዋቸው ። ጎጆአቸውን አፍርሰህ የምትጠቀመው ነገር የለም። የድሀ እንባ ምን ያደርግልሃል? እባክህን» በማለት ለመነው ።

«አፍክን ዝጋ አንተ ደሞ! እዚህ ውስጥ የሚያገባህ ነገር የለም ። ሂድና ትምህርት ቤትክን ስራ ። እዚህ ምን ታደርጋለህ!» ብሎ መልስ ሙሽበት ።

«አንድ ቀን ይፀፅትሃል ዋ!» አለው ።
«ዝም በል ነው የምልህ!»

«አባ ብያ!» አሉ አቶ በቀለ፣ «እኛ እኮ እርስዎን ፈርተንና አክብረን እንጂሁም የቀኛዝማች ውለታ ይዞን ነው እንጂ ጎጆአችን የሚፈርሰው በሬሳችን ላይ ይሆን ነበር ።»

«አሁንም ነው!» አሉ አባ መርጋ ጦራቸውን እየነቀነቁ ።

ፊታውራሪ ፣ «እንዴት እንዴት! ምን አልክ!» በማለት ተቆጡ ። «ይህማ አይሆንም ። ምን ሲደረግ! እንዲህ አይነቱ ነገር ምን ሲደረግ ይታሰባል ። በገዛ መሬቱ የፈለገውን ሊያደርግ ይችላል ። መብቱ ነው ። እናንተም ግዴታችሁ ነው ። ተስማምታችሁ ኑሩ አልኩ እንጂ! ለዛቻም በታችሁ እንዴ! ምን ሲደረግ ። ይህ ነው እኮ የሚያስጋኝ ። ፈጣሪ በረቂቅ ስልጣኑ ደልድሎ የዳረገልንን መብትና ግዴታ ካላከበርን ምን ሰላም ይኖራል! መአተ ቁጣውም በላያችን ላይ ይሆናል» አሉ በንዴት ፣ ካባቸውን ትከሻቸው ላይ እያስተካከሉ ።

ታፈስ በፊታውራሪ አነጋገር የልብ ልብ ተሰምቶት ፣ «ይህን አይደለም እኔስ የምለው! ዛሬ እንዲህ ያሉ ነገ ምን የሚያደርጉ መሰልዎት!» አለ ።

«ምን ሊያደርጉ! ምን ሊሆኑ! ዝም በል አንተ» ብለው አንዴ ገላመ ጡትና ወደ ሰዎቹ መለስ በማለት ፣ «የጌታችሁ ልጅ ነው። በበደለ ይከሳል ። እናንተም ለእግዜር ይቅር በሉት ። ግዴታችሁንም ማወቅ ጥበብ ነው ። ፈሪሃ እግዚአብሄርም ይደርባችሁ ። ዛቻ ደግ አይደለም ። ተደርጎም ታስ ቦም አይታወቅም ። ኧረ እንዲያው ምን ቢደረግ!» አሉ ።

«ፊታውራሪ ተሳስተዋል ። በእውነት ተሳስተዋል» አለ ተፈስ ብስ ጭት ብሎ ።

«ሁዋላ ማንን ይዘህ ልትኖር ነው?»

«ገንዘቤን ። ዛሬ ዋጋ ያለው ፣ ዘመድና ወገን የሚሆነው ገንዘብ ነው ። ጭሰኛ አይደለም ። ፊታውራሪ በእውነት ነገሩ አልገባዎትም» አለ ጠጉ ሩን እየነጨ ።

«ኢቡን ተወው» አሉ ፊታውራሪ ፣ «ለጭሰኞች አደላህ ልትለኝ ነው ። አይደለም ። ግን ሰው በዚህ አለም ማንን ይዞ ይኖራል? ባዶ መሬት ድረስ ልኝ ተከተለኝ ቢሉት ተነስቶ አይመጣም ። ዋ! ተው ታፈስ ። ይልቅ ምኑም ያልገባህ አንተ ነህ ።»

«ኢባክዎን ነገሩ እንደሱ አይደለም!»
«እህሳ?»
«መብት አለን ነው'ኮ የሚሉት!»
«የምን መብት?»
«በዚህ መሬት ላይ ። ባዕመ ርስቴ...»

«ምን ቆርጦአቸው! እንዲህ ያለ ነገር አልወጣቸውም ። በማ መሬት ማን መብት አለኝ ይላል? ተበደልን ነው የሚሉት ። እና ፣ ቅድም እንዳል ኩት ፈጣሪ በጥበቡ የዳረገልን መሬት ምን እንደሆነ ማወቅ አለብን ። በዚች ምድር ፍጥረት ሁሉ ቦታ ቦታ አለው ። ጌታ መበደል ፣ ድሀ መለገም የለበትም ። በል አሁን ፣ ከዛሬ ጀምሮ ብትደርስባቸው ጥልህ ከኔ ጋር ይሆ ናል» ብለው ፣ በቅሎአቸው ላይ ወጥተው ሄዱ ።

እልልታው ቀልጦ ያስተጋባ ነበር ።

ሀዲስ ሄዶ ከታፈስ መኪና ላይ ተሳፈረ ።

ታፈስ ፣ «በእውነት ይህ ሽማግሌ ጃጅቶ ጅል ሆኖአል!» እያለ ይሳ ዶብ ነበር ።

«ምን ያድርጉ ነው የምትለው?»

«የጥንቱ ፊውዳሊዝም አክትሞአል ። እየሞተ በሚሄድ ስርአት ላይ ተንጠልጥሎ መኖር ምን ያደርጋል? ጭሰኛ ዋጋ የለውም ። አዲሱ ሃይል ፣ አዲሱ እግዜር ፣ ገንዘብ ነው ።»

«አሁን ምን ልታደርግ ነው ታዲያ?»

«ታዶለህ ። ዛሬ ባይሆን ነገ አባርራቸዋለሁ ። እዚህ የመ[illegible]ት ለቀ ላይ አይዶለም!» ብሎ መኪናውን አስነስቶ በረረ ።

«ተዋቸው እባክህ ። አብዛኛዎቹ ደክመዋል ። አርጅተዋል ። የት ይሄዱ ነው የምትለው?» መኪናዋ በገደል አፋፍ ላይ ስትበር ሀዲስ ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ ያዘ ።

«ዝም በል ብዬሃለሁ ። አንተን አያገባህም ። ሴኔ ብለው እንደሆነ ገሃነም ሲገቡ ይችላሉ ። እኔ የማስበው ስለ መጭው ጊዜ ነው ። አንት ዝም ብለህ ስለዚያ ጭቃ ትምህርት ቤትህ አስብ ። በኔ ጉዳይ አትግባ! እሺ?»

የመኪናው ጎማ የገደሉን ጠርዝ ነክቶ ሲጠመዘዝ የሀዲስ ልብ ባፉ ተፈትልካ ልትወጣ ደርሳ ነበር ። ጥርሱን ፣ ነክሶ የተቀመጠበትን ወንበር በእጁ ጭምድድ አድርጎ ይዞ ዝም አለ ። ሳይታወቀው ያልበው ጀመር ። መኪናዋ ሜዳ ሜዳውን ስትይዝ ነፍሱ መለስ አለች ። እንደ በረረ ሄዶ ሀዲስ ቤት አጠገብ ቆመ ።

ሀዲስ በእፎይታ ተንፍሶ ፣ «ለምን ቤት አትገባም?» ብሎ ጠየቀው ።
«እቸኩላለሁ ።»
«ወዴት?»
«በጉዳዩ አትግባ ብያለሁ!»

«አትቆጣ ። ምናልባት ዛሬ ማታ የዘነበ እንድሆነ የት አገኝሃለሁ?»

«ቤት ታገኘኛለህ ። እንዲያውም አንድ ነገር ዛሬ ባፈነዳ ደስ ይለኛል! ቻዎ።»

ሀዲስ ቤት ሲገባ ፣ ስእት አልፎ ኖሮ ፣ ገረዱ እያጉተመተመች ምሳውን አቀረበችለት ። አንድ ሁለት ጊዜ ጎርሶ ተወው ። እህል አላስኘውም ። አንድ ልቡ ፣ ምን ነው ይህ ዝናብ በመጣ እያለ ይመኛል ። አንድ ልቡ ደግሞ አይናለም ለምን ይሆን መሳቅና መጫወት የጀመረችው? በማለት ያስባል ። አልፎ ፣ አልፎ ፣ እስዋን ያገኛት ይመስል ፣ ለደወሉ ማስሪያ ብላ የሰጠችውን ትልቅ መስቀል ወጣ አድርጎ ይመለከተዋል ። ይቆይና ፣ ታፈስ ብሩ በነዚያ ድሆች ያደረሰው በደልና ግፍ ትዝ ሲለው ይናደዳል ። ምኞት ፣ ትዝታና ንዴት ሲፈራረቁበት ነበር የዋለው ። የመንፈስ እረፍትም ሆነ ሰላም አልነበረውም ። የቤቱ ብርሃን ድንገት ድብዝዝ አለበት ። በመስኮት ወደ ውጭ ሲመለከት ሰማዩ ጠቁሮ ታየው ። ተነስቶ ወደ ታፈስ ቤት ሮጠ ። ደመናው ጆሮ ያለው ይመስል ፣ እባክህ አሁን ዝናብ አታምጣ! እያለ ነበር የሚሮጠው ።

እንደ ሮጠ ሄዶ ከታፈሰ ብሩ ግቢ ሲደርስ የታጠቁ አሽከሮቹ ከውጭ በር ላይ አቆሙት ። አደገኛ ጠላት ይመጣብናል በማለት ነቅተው የሚጠብቁ መስለው ታዩት ። አይኑ ውሀቸው ደስ አላለውም ። ሁላቸውም የመንፈስ ርጋታ አይታይባቸውም ። ይቁነጠነጣሉ ።

«እረ ጉዋደኛው ነኝ» አለ ።
«ቢሆንም ፣ አሁን ማንም አይገባም ።»
«ቀጠሮ ሰላለኝ ነው...»

«አልተነገረኝም» አለው ጠብመንጃውን እንደ ህፃን ልጅ ታቅፎ የያዘው ሰውዬ ። ጎፈሬው ያስደነግጣል ። አይኑ ያስፈራል ።

«ሺ አልገባም ። ግን ፥ ሀዲስ መጥቶአል ብለህ ንገርልኝ ። ለብርቱ ጉዳይ ነው ። በጣም አስቸኳዋይ ነው—ጎሽ እባክህን የኔ ወንድም» በማለት እየተለማመጠ ፥ ወደ ላይ አንጋጦ ሰማይ ሰማዩን ይመለከት ነበር ። ሰማዩ በጣም እየጠቆረ በመሄድ ላይ ይገኛል ።

«ማን አልከኝ?»

«ሀዲስ ። ሀዲስ ሳህሌ በልልኝ ። ጎሽ የኔ ጌታ ።»

እጠገቡ ላለው ሰው አንድ ነገር በጆሮው ሹክ አለ። ሰውዬው ወደ ቤት ሮጠ። የፊታውራሪ ቤት መንትያ የሚመስለው ባለ አንድ ፎቅ ቤት ከፍራፍሬ ዛፎች መካከል ብቅ ብሎ ፊት ለፊት ይታያል ። ሰማዩ አጉረመረመ ። ዝናቡ ትንሽ እንዲቆይ በማለት ለዝናብ አምላክ በልቡ ትንሽ ፀሎት አደረገ ። የተላከው ሰው እየ ሮጠ ተመልሶ መጣና ይግቡ ተብሎአል ብሎ ነገረው ። እየተጠማዘዙ ወደ ሰገነት የሚወጡት ደረጃዎች በእብነ በረድ የተሰሩናቸው ። ትኩስ የቤት ቀለም እውድ ያደርጋል ። አንድ ቀጭን አጭር ወጣት በሩን ከፈተለት ። ወደ እልፍኙ ሲገባ የኤሌክትሪክ ብርሃን አጥለቀለቀው ። ወለሉ ላይ የተነጠፉት ሰፋፊ ቀይ ምንጣፎች ከተመሳሳይ የመስኮት መጋረጃዎች ጋር ተዋህደው አይን ያሞቃሉ ። መደገፊያዎቻቸው ያጌጡ ሰማያዊና ቀይ ሶፋዎች በወግ ተደርድረዋል ። ካንድ ትንሽ ቤተ መንግስት የገባ መስሎት አፉን ከፍቶ የቤቱን ዕቃ አይነት ሲመለከት ፥ ታፈሰ ብሩ ፥ ከሀር የተሰራ ነጭ የሌሊት ልብስ ላይ ሰማያዊ የጡዋት ካፖርትደርቦ ከጉዋዳ ብቅ አለ ። የሰከረ ይመስላል ።

«ይህ ሁሉ የመሳሪያና የዘበኛ ጋጋታ ለምንድን ነው?» አለ ሀዲስ ።
«የት?»
«ውጭ በር ላይ ።»
«ለጥንቃቄ ነው ።»
«በገዛ እጅህ ነው'ኮ ጠላት የምታብዛው።»
«ሀም ።»
«የመጣሁት ለዚያ ጉዳይ ነው . . .»

«የቱ ጉዳይ?» አለውና የሚሰጠውን መልስ ሳይጠብቅ ሄዶ በሁለት ብርጭቆዎች ውስኪ ቀድቶ ሲያበቃ ፥ አንዱን በበረዶ ብቻ ፥ ሁለተኛውን በበረዶና በአምቦ ውሀ አድርጎ ተመልሶ መጣ ። አምቦ ውሀ ያለበትን ውስኪ ለሀዲስ ሰጠው ። እጁ ይንቀጠቀጣል ። ከስካሩም ሌላ ሃይለኛ ድካም ያለበት ይመስላል ።

«እሞሃል ወይስ ምን ሆነሃል?» አለው ሀዲስ ባይኑ እያማተረው ።
«ደህና ነኝ ። ለጤናችን» ብሎት ብርጭቆውን ወደ ላይ አነሳ ።

ሰማዩ በሃይል ማጉረምረም ጀምሮአል ። መብረቁ ብልጭ ድርግም ሲል በመስኮት ይታያል ።

«የመጣሁት ስለ ወርካው ጉዳይ ነው ። ዛሬ ማታ ይዘንባል ። ይዘንባል ብዩ ተስፋ አደርጋለሁ» አለው ስሜቱ በጉጉት እየተነሳሳ ።

«እዝናለሁ ። ዛሬ ማታ አይሆንልኝም» በማለት መለሰለት ።

ሀዲስ ወሽመጡ ቁርጥ ብሎ ፣ «ለምን፤ ለምን አይሆንልህም?» ብሎ ጠየቀው ።

«ምክንያቱን አሁን ልነግርህ አልችልም ። ዛሬ ካንተ ጋር ለመሄድ አልችልም ። ለማንኛውም ሌላ ቀን ይዘንባል ። ምን የሚያስቸኩልህ ነገር አለ?» አለውና ውስኪውን ተጎነጨ ።

ሀዲስ በብስጭት ከውስኪው ደህና አድርጎ ተጎነጨለትና ፣ «እሺ ። አንተ ለመሄድ ካልቻልክ ፈንጂውን ለእኔ ስጠኝ» ብሎት ነጎድጉዋዱ ሲያጉረመርም አዳመጠና ፣ «ዛሬ ማታ መሆን አለበት ። ቁጭ ብዬ ዝናብ ፣ ነጎድጉዋድና መብረቅ ስጠብቅ አልኖርም ። ጊዜ የለኝም ። ለኔ ብለህ ፣ እባክህን» አለው ።

«ፈንጂው እንዴት እንደሚሰራ ታውቃለህ?»

«አሳየኝ ። የከብራት እንጨት ራስ የምታክል ጭንቅላት ያለኝ መሰለህ?»

ነፋስ በሃይል ሲነፍስ ይሰማል ። መብረቅ ብርቅ ፣ ብርቅ ይላል ። ነጎድጉዋዱ ። ሌላ መብረቅ ። ታፈስ ሀዲስን ይዞ ወደ ፅህፈት ቤቱ ሄዱ ። ከጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ አንድ ትንሽ የብረት ሳጥን አውጥቶ ከፈታትና ፈንጂውን አሳየው ። ትንሽ ፈንጂ ናት ።

ሀዲስ ተገርሞ ፣ «አሁን ይህች ፈንጂ ያንን ወርካ እውነት ታፈነዳዋለች?» አለው ።

«ወርካውን ቀርቶ ጋራ ትንዳለች . . . »
«እንዴት ነው የሚሰራው?»

«ቀላል ነው ። ይህን ጥቁር ቁልፍ ልብ አርገህ ተመልከት ። ሜን ስትለው ይህ የምታየው የእጅ ሰአት መስራት ይጀምራል ። ይህኛውን ነጭ ቁልፍ በመጠምዘዝ ሰአቱን ታስተካክላለህ ። በፈለገው ሴኮንድ ፣ ደቂቃ ወይም ሰአት እንዲፈነዳ ልታስተካክለው ትችላለህ ። ጊዜውን እንደ ፈለከው ካስተካከልከው በሁዋላ ፣ ይህን ቀይ ቁልፍ ሜን ታደርጋለህ ። ጊዜው ሲደርስ ቡም፤ በቃ ። ረዘም ያለ ጊዜ ብትሰጠው ይሻላል ። አለዚያ አንተንም ከወርካው ጋር ያፈነዳሃል ። ቢሆን ጥሩ ነበር» አለውና ፈንጂውን ሰጠው ።

«ቀላል ነው ። አመሰግናለሁ ።»

መዝነብ ጀምሮአል ።

«ይሄኛውስ ምንድን ነው?» ብሎ ሀዲስ ታፈስን ጠየቀው ። ሌላ ትንሽ ሰማያዊ ቡዋት ከብረት ሳጥኑ ውስጥ ነበር ።

«እሱ ፣ ለአይናለም የገዛሁት ስጦታ ነው ። ስርጉዋ ደርሶአል» ብሎት ቡዋቱን ከፍቶ ስጦታውን አሳየው ። ከወርቅ የተሰራ የእጅ ሰአት ነበር ።

ሰአቱን ባድናቆት አይን እያገላበጠ ሲመለከተው ቆየና በሁዋላ ፣ «ስጦታ ከምትገዛላት ይልቅ ፣ ጥያቄዋን ተቀብለህ አዲሳባ ብትወስዳት ይበልጥ ደስ ይላት ነበር» አለው ።

«እንዶ ጠየቀችኝ በምን አውቀህ?»
ሀዲስ ነገር እንዳመለጠው አውቆ ድንግጥ አለ ።
«ማን ነገረህ?» አለው ታፈሰ መልሶ ።
«እንዲሁ ሰማሁ ።»

«እኮ እንዴት? የት? ከማን?» በማለት በጥያቄ አጣደፈው ። ጊዜ አልሰጠውም ። አሁንም ቀጠለና ፣ «ከእስዋ ካልሆነ በቀር ይህን ምስጢር ከየት ልታገኘው ትችላለህ? ማወቅ እፈልጋለሁ» ብሎ ቀይ አይኑን አፈጠጠበት ።

«እሺእሱዋው ፣ ናት የነገረችኝ ። አሁን ደስ አለህ? መሄድ አለብኝ ።»

ታፈሰ የሀዲስን ትከሻ ጭምድድ አድርጎ ይዞ አቆመውና ፣ «ለምን? በምን ምክንያት? የት ታውቃታለህ?» በማለት በጥያቄ እንደ ገና አጣደፈው ።

«እንደ መርማሪ ፖሊስ ጥያቄ አበዛህብኝ ጃል! ተወኝ ልሂድበት» አለው ፤ ነገሩ ካፉ በማምለጡ መልሶ ራሱን እየረገመ ።

«አንተንም ጠይቃሃለች ፤ አይደለም? እውነቱን ንገረኝ?»
«አዎ ።»
«እና?»
«እና ፣ ምን?»
«ምን መልስ ሰጠሃት?»

ሀዲስ ተናዶ ፣ «ምን መልስ የምሰጣት ይመስልሃል! ግዴታና ሀላፊነት አለብኝ» አለው ።

«የምን ግዴታ? የምን ሀላፊነት?»
«የትምህርት ቤቱ ስራ ። ለህዝቡ የገባሁት ቃል . . .»

«እሱን ተወው! አሁን ማ ይሙት ለዚህ ብዬ እምቢ አልኩዋት ልትለኝ ነው! ቅጥፈት ነው ። የሆነ ተንኮል ይሸተኛል ። የሆነ ሆኖ ባትደርስባት ይሻልሃል! ቀልዴን አይደለም» በማለት ዛተበት ።

ሀዲስ ጠጉሩን ቆፈረና ፣ «እኔ ላይ ከምትዝት ይልቅ ፣ የምትወዳት ከሆነ ፣ ከምትጠላው ጋብቻ አድናት» አለው ።

መብረቅ ተሰነጠቀ ። ነጎድጉዋድ አስተጋባ ።
«ሰቡ ዘዴ ይፈለጋል ። አንተን አያገባህም ። አርፈህ ተቀመጥ!»

ሀዲስ ፈንጂውን ይዞ መሄድ ከጀመረ በሁዋላ መለስ በማለት ፣ «ፈቃድህ ከሆነ ሽጉጥና የእጅ ባትሪ አውሰኝ» ብሎ ጠየቀው ።

«የእጅ ባትሪውንስ እሺ ፤ ግን ሽጉጡን ምን ታደርግበታለህ?»
«ለጥንቃቄ ያህል ።»

ታፈሰ ወደ መኝታ ቤቱ ሄዶ ብዙም ሳይቆይ ተመልሶ መጣና ሽጉጥና የእጅ ባትሪ ሰጠው ። ሀዲስ ሽጉጡን እጁ ላይ እየመዘነ ሲመለከተው ከቆየ በሁዋላ ፣ «እሺ ። አመሰግናለሁ ። ግን አብረን ለመሄድ ብንችል ጥሩ ነበር» አለው ።

«አልችልም።»
«እኮ ለምን? ፈራህ?»

«ማ! እኔ?» በማለት ደረቱን በትምክህት መታ ፣ መታ አደረገና ፣ «ሜጉላ ቤት ነኝ ። በዚህ ምክንያት ነው የማልሄደው ። ፈርቼ አይደለም ። ሰውን ቀርቶ እግዚርንም አልፈራም» አለ ።

«አገባህ እንዴ!» አለ ሀዲስ ፣ ነገሩ ገርሞት ።

«አይደለም ። ታፈሰ ያገባል ብለህ እንዴት ታስባለህ? ባንድ ቤት ታስሬ መኖር አልችልም ። ቤቶች ቶሎ ይሰለቹኛል ።»

«ታዲያ ሜጉላ ቤት ነኝ ስትል ምን ማለትህ ነው?» አለው ተወናብዶ።
«እንዲት ልጃገረድ ይዤ ነው ።»
«በግድ!»
«የፈለከውን በል ።»
«የማን ልጅ ናት?»

«ያንድ ገበሬ ። ብታያት ቆንጆ ናት . . . እትዉነት ለወላጆችዋ በቂ የደም ካሳ ይከፈላቸዋል» አለ እየቀለደ ።

ሰውነቱን ዝግንን አለው — ሀዲስ ። አንድ ነገር መጥቶ ሰውነቱን ወረረው። በእጁ የያዘውን ሽጉጥ ወደ ላይ ቀና አድርጎ ታፈሰ ልብ ላይ ደገነበት። ታፈሰ መጀመሪያ እንደ መሳቅ ፣ ቀጥሎም እንደ መደንገጥ ካለ በሁዋላ ፈዞ ፣ ዝም ብሎ ቆሞ ቀረ ። ሀዲስ አላበው ። ላቡ በጆሮ ግንዱ ሲወርድ ይታይ ነበር ። ጡዋት የሰማው የቤቶች ዋይታና የህፃናት ለቅሶ መጥቶ ጆሮው ላይ አስተጋባ ። የሽማግሌዎቹ ሀዘን ታየው ። እጁ ተንቀጠቀጠ ።

«ምን ሆነሃል! ምን ነካህ!» በማለት ታፈሰ አይኖቹን አፍጦ ወተወተ።

ሀዲስ መልስ አልሰጠውም ። ዝም ። ዝምታ ። ታፈሰ ደንግጦ ወደ ሁዋላው ቀስ ብሎ እየሄደ ፣ «አንተ ሰው ፣ ጤና አይደለህም እንዴ?» ይል ጀመር ፣ ፍርሃት በተሞላበት ድምፅ ። ከሁዋላው ያለው ግድግዳ አቆመው ።

ሀዲስ አሁንም ታፈሰ ልብ ላይ እንዳነጣጠረ ነበር ። አይኖቹ ፈጠዋል ። ከንፈሮቹ ደርቀዋል ። እጁ በሃይል ተንቀጠቀጠ ። የጡዋቱ ትዝታ ከአይነ-ህሊናው ዞር ሲልለት ፣ አዲሱ ትምህርት ቤት መጥቶ ከፊቱ ድቅን አለበት ።

«ም . . . ምላጩን አትንካው ። ጎርሶአል። ሀዲስ! ትሰማኛለህ? ሽጉጡ አ . . . አልጠበቀም ! ትሰማኛለህ?»

«አዎን ፣ እሰማሃለሁ» አለው አይኑን ጨፍኖ ።
«ምን ነካህ?»
«የጥዋት ጨዋታ ትዝ ይልሃል?»
«የቀልዴን ነበር ። እባክህን ጣትህን ከምላጩ ላይ አንሳው ።»

ሀዲስ የሽጉጡን አፈሙዝ ወደ ታች ዘቅዝቆ ፣ «ጨዋታው አንድ ቀን የምር ይሆናል!» ብሎት ወጥቶ ሄደ ።

ጨለማ ፣ ዝናብ ፣ መብረቅ። ነጎድጉዋድ . . . ሌላ መብረቅ ። ሌላ ነጎድጉዋድ ፣ ደፍ ።

# ክ ፍ ል ፲፱

ሀዲስ ድንገት ከእንቅልፉ ነቃ ። ንቁ ሆኖ ነበር ። እንደ ልማዱ ከመኝታው ላይ ቆይቶ በስመመን እየተገላበጠ ማድፈጥ አልፈለገም ። ከመኝታው ውስጥ ዘሎ ወጥቶ መስኮቱን ከፈተው ። ውብ የሆነች የጡዋት ወርቅማ ፀሀይ እጅ ነሳችው ። ጨረሮችዋ እንደ ሙሽራ አድምተኞች እየጨፈሩ ገብተው ክፍሉን ሞሉት ። ከፀሀይዋ ጋር ሳቀ ።

በጭቃ የተለወሱትን ጫማዎቹንና ልብሶቹን በቆሻሻ ሸሚዝ ጠቅልሎ ከሳጥኑ ውስጥ ቀለፈበትና አዲስ ልብስና ጫማ አወጣ ። ጢሙን ሲላጭ ሁሉ ጠይም መልኩን ከፊት መስተዋቱ ውስጥ እያየ ፈገግታውን መግታት አልቻለም ። ከመስተዋቱ ውስጥ ከመልኩ ባሻገር ፣ ወርካው ፣ እንደ ነጎድጓድ እያጉረመረመ ሲወድቅ ታየው ። የፈንጂውና የነጎድጓዱ ጩኸት ጆሮው ላይ መልሶ አስተጋባ ። ከጨለማው አብራክ ውስጥ ቅፅበታዊ ገሃነመ እሳት በድንገት ብልጭ ብሎ መልሶ ድርግም ሲል ፣ የወርካው ቅርንጫፎች እንደ ግዙፍ የሌሊት ወፎች ጨለማውን ሰንጥቀው እየበረሩ የትም ሲጠፉ ቁልጭ ብሎ ታየው ። ጆር የሚያደነቁር ፣ ልብ የሚያሸብር ፣ በስራ አከላት ፍርሃት የሚለቅ ታላቅ አወዳደቅ ነበር ። ከዚያ በሁዋላ አንድ ታላቅ ፀጥታ በላዩ ላይ ወደቀ ። ከልቡ ትርታና ጆርባው ላይ ከሚወርደው ዝናብ ሌላ ድምፅ አልነበረም ። ወርካው በመውደቁ በዚያ ጨለማ መድረሻ ያጡ አሞራዎች እንደ ጥቁር ቀስቶች በላዩ ላይ ተወርውረው ባለፉ ጊዜ አቤት የደነገጠው መደንገጥ ። ልቡ ዘላ ባፉ ልትወጣ ነበር ። — የድንቁርና ዛፍ ወደቀ ፣ አለ ።

ጠይም ወጣት ከመስተዋቱ ውስጥ ብቅ ብሎ ሳቀበት ።

ገረዱ ለቁርስ ፍርፍር ከምራ ስታቀርብለት እንደ ሌላው ጊዜ ወስፋቱ አልተቆለፈም ። አንድ አይነት ጭንቀት ከጥቁር ፣ ጨምዳዳ ፊትዋ ላይ ይታይ ነበር ። ምግብ ስታቀርብ አስቀድማ እንደምትቆጣ ስለሚያውቅ ፣ ዛሬስ አላስቆጣትም ፣ በልቼ አስደስታታለሁ በማለት ከፍርፍሩ ጋር ግብ ግብ ለመግጠም እጁን ሊሰድ ሲል ፣ «እሪ ከወደ ትምህርት ቤቱ ጩኸት በርክቶአል» አለችው ።

ጭንቀትዋ ወደ ፍርሃት ተለወጠበት ።

«ምን ተፈጠረ?»
«እሪ ጉድ ነው ። እንዲያው ጉድ ነው ።»
የፊት ጥርሶችዋ ረጃጅሞች ስለሆኑ ከንፈሮችዋን መክደን አትችልም ።
«ምንድን ነው እሱ» አላት ፣ በልቡ ፣ ለካ ጥሩ ተዋናይ ነኝና እያለ ።
«ወርካው ወድቆ አደረ አሉ ።»
«የቱ ወርካ?»
«ኢድባሩ!»
«እሪ! ምን ሆኖ?»

«ሺሬ ጉድ ነው! እንዲያው ጉድ ነው!!»
«ምን ሆና ነው!»
«መብረቅ መታው ይላሉ።»

«ወቸ ጉድ ፥ እውነትም ይገርማል» አለ ፥ ውስጥ ውስጡን በደስታ እየፈነደቀ ።

ገረዱ በሁኔታው ተገርማ ትክ ብላ አየችው ።

«እህም . . . ዛሬ እርጎ የለም እንዴ!» አላት ።

እርጎ ልታመጣለት ወደ ጉዋዳ ገባች ። የሚሰማውን ውስጣዊ ደስታ ለመደበቅ ባለመቻሉ በራሱ ተናዶ ራሱን በኩርኩም ገጨ ። ወዲያውኑ በር ሲመታ ሰምቶ ተነስቶ ሄዶ በሩን ከፈተው ። አቶ ጣሴ ደጉ ነበሩ ። ሰው አየኝ ፥ አላየኝ በማለት ወደ ሁዋላ እየተገላመጡ ቶሎ ወደ ውስጥ ዘልቀው በሩን ዘጉትና ፥ «የሆነውን ነገር ሰምተሃል!» አሉት ።

አይናቸውን እየሸሸ ፥ «አዎን ፥ አሁን ሰራተኛዋ ነገረችኝ» አላቸው ።

«የኛን ፀሎት ሰምቶ እግዜር በቸርነቱ ጣለው ልትለኝ ይሆን! ወይስ . . . »

«ታዲያ ምን ጣለው ሊባል ነው» አለ ፥ አንገቱን እንደ ተዋጊ በሬ አቀርቅሮ ።

«ህም . . . ጉድ ነው እኮ ።»
«ምኑ!» አላቸው አንገቱን ቀና አድርጎ ።
«ጉደኛ ነህ» አሉት ።
«እንዴት!»

«አይ ሀዲስ ። አይዞህ ። አትፍራ ። እንደ ራሴ ያህል ነው የማውቅህ ። ካንተ ሌላ ይህን ተአምር ደፍሮ የሚሰራ ሌላ ሰው የለም ። ያንተን ልብ ቢሰጠኝ ጥሩነበር» በማለት አስተማመኑት ።

እሱም ቢሆን ከአቶ ጣሴ የሚደብቀው ነገር ስለሌለ ሀቁን ነገራቸው ።

«ምስጢሩን የሚያውቅ ሌላ ሰው አለ ወይስ ምስጢሩን ብቻህን ይዘህ ነው ያደረከው ።»

«ታፈሰ ብሩ ምስጢሩን ያውቃል» ብሎ መለሰላቸው ።

አቶ ጣሴ ራሳቸውን በቅሬታ ነቅንቀው ፥ «እንዴት ሊያውቅ ቻለ!» በማለት ጠየቁት ።

ታፈሰ ምስጢሩን ሊያውቅ እንዴት እንደቻለ ምክንያቱን ገለፀላቸው።

«እዩሀ ፥ የእሱ ማወቅ ደግ አይደለም» አሉት ፥ በፀፀት ራሳቸውን እየ ነቀነቁ ።

«ምን ነው ምን ይሆናል ብለሁ ነው ? »

«ከቅርብ ቀን ወዲህ ፥ የእሱ ውሎ ከይርጋ እና ከመቶ አለቃ አሸኔ ጋር ሆኖአል» በማለት ነገሩት ።

«ምን አገናኝቶአቸው!»

«ጥቅም» ብለው ከንፈራቸውን በሀዘን መጠጡና ፣ «እንደ ታፈስ ያለ ሰው ሀ ሁ ማስቀጠሉ ይቆጨኛል ። የናት ሆድ ዥንጉርጉር ነው እንደሚባለው የመምህራንም እድል እንደዚሁ ነው» አሉት ።

«የምን ጥቅም?»

«ታፈስ በሙቶ አለቃው እየተረዳ ጭሰኞቹን በዚህም በዚያም ብሎ ነቅሎ ሊያባርራቸው ይፈልጋል . . . »

«እና ፣ እሱስ?» አለ ፣ ሀዲስ ተጣድፎ ።

«እሱ ደግሞ በታፈስ ተጠቅሞ ፣ የፊታውራሪ ተካን ልጅ ጠልፎ ለመውሰድ ይፈልጋል. . »

«ያቶ ይርጋ ጥቅም ደግሞ እዚህ ውስጥ ምንድን ነው?» ብሎ ጠየቀ ፣ አሁንም ነገሩን ለመስማት እየተጣደፈ ።

«አጅሬ ደግሞ በሁለቱ ተጠቅሞ አንተን ከዚህ ለማባረር ነው የሚፈልገው ። ሴራቸውን ሁሉ ደርሼበታለሁ» አሉት ።

«ታላቅ ሴራ ነው ። ግን አይሆንላቸውም» አለ ሀዲስ ።
«ጥላሁን ደግሞ ካቶ ይርጋ ጋር ተጣልቶአል አሉ ።»
«በምን ምክንያት?»

«ምክንያቱ ምን እንደ ሆነ በውል አልደረስኩበትም ። በጥቅም ተጋጭተው ይሆናል ። ይህ ትምህርት ቤት ያላናከሰው ሰው የለም ። የተጣሉበት ምክንያት እኔ እንደሚመስለኝ ፣ በሃይል ተጠቅመህ ገንዘቡን ለምን እጅህ አታስገባም ብሎ ይሆናል አቶ ይርጋ ።»

«ጥላሁን ደግሞ በሃይል ለመጠቀም አልቻለም ። ፈስ ያለበት ዝላይ አይችልም ብየህ የለም?! ለማገኘውም ነገር ያንተም ሆነ የኔ ህይወት አደጋ ላይ ነው ያለው» ካሉ በሁዋላ ፣ በሀዘን ተውጠው ሲያስቡ ቆዩና ፣ «አንተ ንም ፍቅር እንዳያታልልህ እሰጋለሁ» አሉት ።

«የምን ፍቅር?»

«ለአይናለም ያለህ ፍቅር ። ሱዱ ተደረገ የተባለ ነገር ቀርቶ የቱፈሳም ሳይሰማ አያድርም ። የሆነ ሆኖ ልብህ ወደ ትምህርት ቤቱ ስራ በመመለሱ ደስ ብሎኛል» አሉት ፣ ጭንቅ ጭንቅ እያላቸው ።

ያ መከረኛ ባል ሊነሳባቸው ይተናነቃቸዋል ።

«በል አሁን አንድ ነገር ልምከርህ» አሉትና ረጋ ብለው ምክራቸውን ከለገሱት በሁዋላ ፣ እንደ አመጣጣቸው ሁሉ ሰው አየኝ ፣ አላየኝ በማለት እየተገላመጡ ወጥተው ሄዱ ። ሀዲስ ትንሽ ቆይቶ እንደ መከሩት ፊታውራሪ ቤት ለመሄድ ተከትሎአቸው ወጣ ።

ቀኑ መስከረም የጠባ ይመስላል ። ልቡን ሞቅ አለው ። ይነፍስ የነበረው ቀዝቃዛ አየር እንደ እርጎ ይገመጥ ነበር ። ጭቃው ግን አይጣል—አያራምድም ። ሆኖም መንገድ እየመረጠ ለመራመድ ጥረት አያደርግም ነበር ። ደንታ አልነበረውም ።

ሰዎች ከየአቅጣጫው ወደ ትምህርት ቤቱ ይሮጡ ነበር ። ሱቁ ላይ ያን ቀን ጡዋት የቡና ጀበና የተጣደ አይመስልም ። የትምህርት ቤቱ አካባ ቢም እንደ ደራ ገበያ በሰው ብዛት ተጥለቅልቆ በታየው ጊዜ ፥ የወደቀ ውን ወርካ ከበው የሚባባሉትን ነገር ሲያስብ ብቻውን ይስቅ ነበር። አቶ ዶርጋ በዚህ ወቅት ምን ያስቡ ይሆን የሚል ጥያቄ ድንገት ብልጭ አለ በት። ምን ያስባሉ ? ጠርጣሪ ናቸውና ቢጠራጠሩስ ምን ማስረጃ ሊያቀርቡ ይችላሉ? ከታፈሰ ሌላ እኔ የማውቀውን ማን ሊያውቅ ይችላል . . . መብረቅ መትቶ የጣለው ወርካ . . . በማለት እንደ ገና ብቻውን ይስቅ ጀመር . . .

ሀዲስን ብቻውን የሚያስቀው ነገር ምን እንደ ሆነ ቶሎሳ አልገባ ውም ። ተገርሞ ይመለከተው ነበር ።

«አይናስም ዛሬ እንዴት ናት?»

«በጣም ደህና ናት ። ልክ እንደ ዱሮዋ የቤቱ ምሰሶ ሆናለች ። ፊታው ራሪም ደስ ብሎአቸው ፈጣሪን እያመሰገኑ ይህንኑ አሁን ለመምሩ ሲያጫ ውቱዋቸው ነበር» በማለት መለሰለት ።

«ፊታውራሪ የት ሊሄዱ ነው የተነሱት» ብሎ ጠየቀው ፣ ተጭና የም ትጠብቀውን በቅሎአቸውን አይቶ ።

«ወደ ትምህርት ቤታችሁ . . .»

ሀዲስ ቶሎ ነቅቶ ስሜቱን እየተቆጣጠረ፥ «ለምን?» ሲል ጠየቀው ።

እንደ ገና ተዋናይ ሆነ ።

«አልሰማህም እንዴ!»
«ምን?» አለው እንደማያውቅ ሆኖ ።

ቶሎሳ በነገሩ በጣም በመገረም ስለ ወርካው መውደቅ እየነገረው ወስዶ ከአልፍኝ አስገባው ። ፊታውራሪ ለመውጣት ተነስተው ነበር ።

በነጭ የሀገር ልብሳቸው ላይ የደረቡትን ጥቁር ካባ ከትከሻቸው ላይ አስተካከሉና፥«ከትምህርት ቤቱ ግቢ አቅራቢያ ያለው ወርካ ምን ሆኖ ወደቀ ይላሉ?» አሉት ።

«መብረቅ ነው የጣለው ይላሉ!»

«ታሪክ ነው ። ምን ምልክት ሲያሳየን ይሆን» በማለት ራሳቸውን በሚ ጠይቁበት ጊዜ ፦

መምሩ ከጠዋት ድጋማቸው ላይ ቀና ብለው ፥ «ምን ጥሩ ምልክት አለ ብለሁ ነው ። እሱ ያመጣውን እሱው ይያዝልን'ይ» አሉ ።

«ዘመን የለውም እሱ ወርካ» አሉ ፊታውራሪ የወርካው ምስል እየታ ያቸው ፤ አያቴ እንኳዋ ሳይቀሩ በያመቱ ነጭ ከርማ ይሰውለት ነበር ። አባቴም ደም ሳያፈሱበት ሩቅ መንገድ አይሄዱም ነበር ። ታዲያ እኔ ላይ ሲደርስ ከቤታችን የለመደው ምስ ቀረበትና ነው መሰለኝ የወንድሜ ደም ፈሰሰበት ። መክብብ እንደ አረመኔዎች ለግኡዝ ግንድ መስገድ አይገባም ፥ ቀናተኛው የ[illegible]ኤል አምላክ ይቆጣል ይለኝ ነበር ።»

መምሩ ከድጋማቸው ላይ ቀና ብለው የሆነ ድምፅ አሰሙ ። ዋመኩብብ ስም ሲነሳባቸው ደስ አይላቸውም ።

«እርስዎስ ፣ አይሄዱም ወይ?»
«ድጋሜን አልጨረስኩም ።»

መምሩ ጭቃ አይወዱም ። ዝናብ ጠብ ካለ ከቤት አይወጡም ።

«ምን ምልክት ሲያሳየን ይሆን?» አሉ ፊታውራሪ እንደ ገና ።

«በቦታው ላይ ቤተ ክርስቲያን አቁሙ ማለቱ ሳይሆን አይቀምር ። መቼም የሱ መንገድ ረቂቅ ነው» አሉ መምሩ ፣ እንደ ገና ከድጋማቸው ላይ ቀና ብለው ።

«ሃለው መቼ አነሰና! ሰዉ እንደ ሆነ ለክርስትና፣ ለሰርግ ወይም ለቀ ብር ካልሆነ በቅር ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ትቶአል ። ተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን ምን ያደርጋል ብለው ነው? ሃይማኖት ቀርቶ ወግና ሥር አት ሃይማኖት የሆኑበት ቤተ ክርስቲያን ። ጥንት ቲያትር ቤቶች እንደ ቤተ ክርስቲያን ይቆጠሩ ነበር ። ዛሬ ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆኖ ቤተ ክርስቲያናት ቲያትር ቤቶች ሆነዋል' ይል ነበር መክብብ፣ ነፍሱን ይማረውና» አሉ ፊታ ውራሪ ለመሄድ እየተነሱ ።

መምሩ ሌላ የተቃውሞ ድምፅ አሰሙ ።

ሀዲስ ፈገግ ብሎ ፣ «ምልክቱ ምን እንደ ሆነ ገብቶኛል» አለ ።

«ልጅ እኮ አንዳንዴ ይገለጥለታል። ምንድን ነው?» ብለው ፊታውራሪ ጠየቁት ።

«አዲስ ትምህርት ቤት በቦታው ላይ ይሰራበት ማለቱ ሳይሆን አይቀ ርም ። ቦታውን በልቤ ተመኝቼው ነበር» አላቸው ።

ፊታውራሪ በነገሩ ተገርመው ትኩር ብለው ሲመለከቱት ቆዩና ፣ «የሱን ተአምር ማን ያውቃል» ብለው ለመሄድ ተነሱ ።

ሀዲስ ተከትሎአቸው ወጣ ። ያለ ማንም ርዳታ ከበቅሎአቸው ላይ ዘለው ወጥተው ኮርቻው ላይ ጉብ አሉ ። ሀዲስ ከግቢ ከመውጣቱ በፊት በመነመነ ተስፋ ፊቱን ወደ ቤት መለስ አደረገ ። መስኮት ላይ ቆማ ነበር— አይናለም !! የጠዋት ፀሀይ ፊትዋ ላይ ታበራ ነበር ። ፀሀይዋን የምትመለ ከት ትመስላለች ። ፀሀይዋም በቀጥታ እሰዋን የምትመለከት ትመስል ነበር። ቢቃ ይሆን? እርግጠኛ አልነበረም ። ቶሎሳ ባይኑ ይከተለው ስለ ነበረ ቶሎ ብሎ አይኑን መስበር ነበረበት ።

ፊታውራሪ ከግቢ ሲወጡ የተከተሉዋቸው ጠብ መንጃ ያነገተ አንድ ባውና ቶሎሳና ሀዲስ ነበሩ ። ሀዲስ በዚያ ጭቃ ከበቅሎዋ እኩል ለመሮጥ ተቸግሮ ነበር ። አንድ ግጥም ትዝ አለው :—

ምኒልህ
ምን ነው ምናልንህ
በገበሬ ሰደድክበት አውሬ
ካውሬም አውሬ

ዱጉ መቶ ታምሳ
ገባሩ ሰላሳ ።
ማንን ሊያዙ
ዱጎች እንዲህ በዙ
ለስንቱ ዱግ
ችዬ ላደግድግ
ለመቶ ታምሳ ጌታ
ስታጠቅ ስፈታ
ነጠላዬ
አልቆ በላዬ
ማር ስሰፍር
ምን ጊዜ ልቆፍር
ከዳኛ እግር
ሳልለይ ዘወትር
ከበቅሎ እኩል
ሲያሮጠኝ ይውላል ።

ፊታውራሪን የሚያጅቡዋቸው ሰዎች ቁጥር ቀስ በቀስ እየጨመረ ሲሄድ ይታይ ነበር ። ወደ ትምህርት ቤቱ ለወሬ የሚሮጡት ሰዎች ምናል ባትም ሳይወዱ መጥተው ካጀቡ ውስጥ ይገባሉ ። ከትምህርት ቤቱም የሚ መለሱት ሰዎች እንዲሁ ተመልሰው ካጀቡ ጋር ይቀላቀሉ ነበር ። ፊታው ራሪ በዚህ ነገር ቂመኛ መሆናቸውን ያውቃሉ ። «እገሌ እኮ ረግጦን አለፈ፣ ምናለ ፣ ጥፋቱ ከሱ አይደለም ፣ ከጊዜው ነው ካሉ» ሰውዬውን ወግተው ከመያዝ አይመለሱም ። ትልቅ አጀብ ።

ፊታውራሪ ባጀባቸው ከመደሰታቸው የተነሳ አዲስ ህይወት ዘርተው ከኮርቻቸው ላይ ግዙፍ እየሆኑ ከመሄዳቸውም ሌላ ፣ እጅ አነሳሳቸው ሁሉ ተለውጦ እንዲያው ግርማ ሞገስ ጨምሮ ነበር ። «የሰው ክብሩና ግርማ ሞገሱ ሰው አይደለም ወይ» የሚሉት ሀዲስን ትዝ አለው ።

ከትምህርት ቤቱ ሲደርሱ ልክ እንዳሰበው ምድረ ግቢው በሰው ብዛት ተጣቦ አገኘው ። ምድረ ግቢው እንደ ደራ ገበያ ያጉረመርማል ፣ እንደ ወራጅ ወንዝ ይንሹዋሹዋል ፤ አንዳንዱም እንደ ንብ መንጋ ያምባል ፣ ሀዲስ አላስችል ብሎት ፣ ትክሻ ለትክሻ ገጥሞ የቆመውን ህዝብ እየጣሰ ትእ ይንቱ ከሚታይበት ቦታ ላይ ብቅ አለ ። ታላቁ ወርካ እንደ ጎልያድ ተዘርር ታየው ። ሆኖም አይኑን የማረከው ሌላ ነገር ነበር ። መቶ አለቃ አሸኔ ከሌ ሎች ፖሊሶች ጋር ሆኖ ቦታውን እየዞረ በጥንቃቄ ይፈትሽ ነበር ። አቶ ይር ጋም ስር ስሩ ይከተሉታል — የአብድ ነጎራት የሚመስለውን ቦርጫቸውን እያስቀደሙ ። የሆነ ነገር ነበር የሚፈልጉት ። ምን ይሆን የሚፈልጉት! የሆነ ፍንጭ ቢያገኙስ ወዴት ሊያመራቸው ይችላል? ወይስ ከሰው ለዘላለም ተሰውሮ ምስጢር ሆኖ ይኖር ይሆን? በማለት መጠራጠር በጀመረበት ጊዜ የልቡ ትርታ እየጨመረ ሲሄድ ይሰማው ነበር ። ላብ ላብም ይለው ጀመር ። ግን ፣ ቀልቡ ወደ ሌላ ሄደበት ።

ከላይ መስቀል ፣ ከታች አንካሴ የሆነ ረጅም የብረት ዘንግ የጨበጠ ፣ እንደ ዮሀንስ መጥምቁ ቆዳ ያሸረጠ ፣ እየተንናዘለ ከትከሻው ላይ የሚወርደውን ጠጉሩን በቀይ ሻሽ ሸብ ያደረገ አንድ ጠብደል ባህታዊ ድምፁን ከፍ አድርጎ ፣ «መአት መጥቶባችሁአል ። እግዚአ በሉ ። የሀጢአታችሁን ዋጋ የምትከፍሉበት ቀን ደርሶአል ። ሁላችሁ እንደየስራችሁ የእጃችሁን ዋጋ የምታገኙበት ቀን ይኸውና ተቃርቦአል ። የሀጢአታችሁ ዋጋ ፣ የበዳይ እጃችሁ ዋጋ ፣ ሞት ነው ። የምትሰግዱለት አድባር ወድቆአል ። ጣኦታችሁ ተሰብሮአል። እግዚአ በሉ» እያለ ሲጮህ፣ ብዙ ሽማግሌዎችና አሮጊቶች በፍርሃት እየተንቀጠቀጡ ፣ «እግዚአ» በማለት ወድቀው እየተነሱ ይሰግዱ ነበር ።

ፈታውራሪም እንጋቾቻቸውን አስከትለው በህዝቡ መካከል እየተዘዋወሩ እጅ ያስነሱ ነበር ። የህዝቡ አይን እንዲያርፍባቸው የሚፈልጉ ይመስላሉ ። ሆኖም ባህታዊው የህዝቡን ቀልብ እየተሻማቸው ስላስቸገራቸው ሳይሆን አይቀርም አልፎ አልፎ ከፉኛ ይመለከቱታል ። ባህታዊውም ውሌ ይዞልኛል ፣ ሰው ሰምቶልኛል ፣ ውሌ ከሰጠኝ ፣ ቦታ ከተመቸኝ በማለት የባሰውኑ ድምፁን ከፍ አድርጎ ያንኑ በመደጋገም ይጮህ ስለ ነበረ ፈታውራሪን ልብ አላደረጋቸውም ።

—ምናባቱ ይሆን የሚያወራው አለ ሀዲስ ። ታፈሰ ከመቶ አለቃ አሸኔና ከአቶ ይርጋ ጋር አፍ ለአፍ ገጥሞ ሲያወራ ድንገት ከሩቅ አይቶት ። የሰውነቱን መወራጨትና የእጆቹን መወናጨፍ ሲመለከቱ የተጋጋለ ክርክር የገጠመ ይመስላል ። አሁን እርፎ ቢቀመጥ ምናለበት ፣ እያለ ሲያስብ ከበስተ ሁዋላው ፣ «ያሰብነው ሆነልን አይደለም» የሚል ድምፅ ሰማ ። ዞር ሲል በመጀመሪያ የታየው የሰው ደረት ነበር ። ወደ ላይ ቀና አለ ። ጋሼ 'ቀውሌ' ወደ ታች ሳቀበት ።

«አ ! አንተ ነህ እንዴ» ብሎት ራቅ አለው ።

ሀዲስ 'ቀውሌ' አጠገብ መቆም አይወድም ።

ቁልቁል እያየው ፣ «ፀሎትህ የተሰማ ይመስላል» ፣ አለው በምፀታዊ አነጋገር ።

«የመላኩ ገብርኤል ሰይፈ ነበልባል ተአምሩን ሰራ ። ተአምር እያልቅ» አለ ።

«ከሰው የበለጠ ተአምራዊ ነገር አለ ብለህ ።»
«ምን ለማለት ነው?»
«በፀሎት ወርካ ፈንገለህ የምትጥል . . . »
«ትንጣት ታህል እምነት ጋራ ታፈርሳለች ይባል የለ» አለው ።
«እና ብዙዎቻችን ደ'ም የሚጎ'ለን ይኸው ነው ።»
«ለማለት የምትፈልገው ነገር አልገባኝም ።»

«አንተ የምታውቀውን የማላውቅ መሰለህ? እኔ የማውቀውንም አንተ ታውቃለህ . . . »

«እኔ የማውቀውን አታውቅም ! አንተ የምታውቀውንም አላውቅም ። አላውቅም ፣ አታውቅም ፣ አናውቅም !»

«ምን አስቆጣህ ታዲያ?»

«ተቆጣሁ እንዴ?» ሲል የራሱን ድምፅ ሰማ ።

ሰው ሁሉ ፀጥ ብሎ ነበር ። ደንገጥ ዞር ቢል ፊታውራሪ ከባህታዊው ጎን ቆመው አየ ። ሁሉም እንደ እሱ ይመለከታቸው ነበር ። ምን ሊያደርጉ ይሆን? በማለት ሲያስብ ንግግር ማድረግ ጀመሩ ፦

«ስማኝ የሉጼ ሰው ። አሁን አባ መርቆርዮስ ያሉትን ሰምትሃል ። ግን 'እግዚኦ' ማለት ብቻ አይበቃም ። አድባሩ የወደቀው እንዲሁ ያለ ምክንያት አይደለም. . . »

ሀዲስ ጆሮውን አቆመ ። መላ ሰውነቱ ወደ ጆሮ ተለውጦ ነበር ።

ፊታውራሪ ቀጠሉ ፥ «ያለ ምክንያት እሳት ከሰማይ ወርዶ አድባር አይመታም ። ምልክት ነው ። የሰማይ ጌታ ፈቃድ ምልክት ነው . . »

ሀዲስ እንዳሰበው ስለ ሆነለት ውስጥ ውስጡን በደስታ ይፈነድቅ ነበር። —አይ አቶ ጣሴ አለ! በልቡ ፥ ዘዴአቸውን እያደነቀ ።

ቀውሌ ፥ ጎንበስ ብሎ በጆሮው ፥ «እንዲህ አይነቱን ነገር ስሰማ ፀሃያኛው ምእተ አመት ሁለተኛ አጋማሽ ዘመን ላይ ያለን መሆናችን ያጠራጥረኛል» አለው ።

«እሽሽ» አለ ሀዲስ ትእግስት አጥቶ ።

ፊታውራሪ ይቀጥላሉ ፥ «አዎን ፥ የፈቃዱን ምልክት ሲያሳየን ነው ። ግን የሚሰጠንን ምልክት አናይም ፤ አንከትልም ፤ ፈቃዱንም አንፈፅምም ። ልባችን ታውሯልና ነው ። ልባችን ስለ ታወረ ጥንት ለእነ አብርሃም ፥ ለእነ ሙሴ በቀጥታ ይገለጥ የነበረው አምላክ ዛሬ ርቆናል ። ሆኖም ፍቅሩን አልነፈገንም ። በሚያሳየን ምልክት ወደ ፍቅሩ ምንጭ እየጠራን ነው ። አድባሩን በእሳቱ የመታው ስታስቡት ለምን ይመስላችሁአል? ፈቃዱን ፈፅሙ ሲለን ነው ።»

ቀሎሳ አንድ ነገር በጨርቅ ይዞ መጥቶ ሰጣቸው ። በእጃቸው የያዙትን ነገር ከፍ አድርገው ለህዝቡ ያሳዩ ጀመር ። ድንጋይ ነበር የያዙት ። የሀዲስ አይን ተጎልጉሎ ሊወጣ ደርሶ ነበር ። ህዝቡ የባሰውን ፀጥ አለ ።

«ምን ሊያደርጉ ይሆን? » ቀውሌ ነበር ።
«እሽሽ ።»

ፊታውራሪ ይቀጥላሉ ፥ «ምንድር ነው ፈቃዱ? ምስጢሩ ስውር አይደለም ። ብሩህ ልብ ካለን ምስጢሩ ግልፅ ሆኖ ሊታየን ይችላል ። እንግዲህ ልብ በሉ ። ይህ ቦታ ድሮውኑም ቢሆን የተመረጠው ለትምህርት ቤት እንዲሆን ነበር ። ዛሬ ደግሞ እንደምታዩት ትምህርት ቤቱ መስፋፋት አስፈልጎታል ። በትምህርት ቤቱ ላይ የደረሰውን ችግር በመገንዘብ ብዙዎቻችሁ የገንዘብ መዋጮ ስታደርጉ ነበር ። የተነሳችሁበት አላማ ተባርኮአል ማለት ነው ። ምልክቱ ይህ ነው ። ፈቃዱም ከዚህ የተለየ አይደለም ። ይህ ቦታ የወንድሜ አፅመ ርስት መሆኑን መቼም ሳታውቁት አትቀሩም ። ወንድሜ በግፍ የተገደለውም እዚሁ በቆምኩበት ቦታ ላይ ከዚሁ ወርካ ላይ ተሰቅሎ ነበር ።»

ሁሉም ከንፈሩን ይመጥ ጀመር ። ደመናው ሸሽቶ ፀሀይ ብቅ አለች ።

ፊታውራሪ ይቀጥላሉ ፤ «እምን ስም ያለው አይሞትም ። ለማንኛውም ነገር ይህ የተቀደሰ ቦታ ለተቀደሰ ነገር ለመመረጡ እና እናንተም የተነሳ ችሁበት አላማ የተባረከ ለመሆኑ እሱ በተአምሩ ከላከው እሳት የበለጠ ምልክት የለም ። እኔም ላዲሱ ትምህርት ቤት ከዳን የሚያስፈልገውን ቆር ቆር ሁሉ እሰጣለሁ ። ገንዘብ ያለህ በገንዘብህ ፤ጉልበት ያለህ በጉልበትህ ፤ እውቀት ያለህ በእውቀትህ ተረዳዳ ። የእሱ ፈቃድ ነውና» ብለው ፤ ይዘውት የነበረውን ድንጋይ ከፍ አድርገው ለህዝቡ ካሳዩ በሁዋላ ፤ ወርካው ከተን ቀለበት ፤ አፉን እንደ መቃብር ከፍቶ ከሚታየው ጉድጉዋድ ውስጥ ጣሉ ትና ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ፤ «ይህ ቃል ኪዳናችን ይሁን !» በማለት ሙሁ ።

በቦታው የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ወደ ጉድጉዋዱ እየሄደ በእጁ የያዘ ውን ድንጋይ አንድ ባንድ ይጥል ጀመር ። አቶ ይርጋና መቶ አለቃም አል ቀሩ ። ታፈሰ ትልቅ ድንጋይ ይዞ ወደ ጉድጉዋዱ ሲሄዱ ከሩቅ አየው — ሀዲስ ። ተአምር አያልቅም አለ በልቡ እሱም ድንጋይ እየፈለገ ።

የተሸከመውን ድንጋይ ከጉድጉዋዱ ጥሎ ሲመለስ ፊታውራሪ በም ልክት ጠሩትና ፤ «እንግዲህ በርታ ። ፈጣሪ ምኞትህን ባርኮታል ። እግዜር ይርዳህ» ብለው መረቁት ።

ምርቃታቸውን እጅ ነስቶ ተቀበለ ። ታፈሰ ከፊታውራሪ አጠገብ ቆሞ ነበር ። አቶ ይርጋና መቶ አለቃ ራቅ ብለው የጎሪጥ ይመለከቱታል ። ታፈሰ እየተጣደፈ ወደ ሀዲስ መጣና ፤ «ትልቅ ስራ ነው የሰራኸው» አለው ።

«ምን ነበር የሚሉህ?» ብሎ ሀዲስ ታፈሰን ጠየቀው ።
«እነ ማን?»
«እነ አቶ ይርጋ ።»

«እነሱ ! አዎ፤መብረቅ ዛፍ እንዴት አድርጎ ከስር ፈንግሎ ሊጥል ይች ላል? ባይሆን ከላይ ሁለት ላይ ሰንጥቆ እንደሆን ነው እንጂ እያሉ ነበር የሚ ከራከሩኝ» በማለት ጥያቄውን መለሰለት ።

«ምን መልስ ሰጠሃቸው ታዲያ?»

«አሁን እሱን ተወውና ፤ ይልቅ ፊታውራሪ ያደረጉትን ንግግር በደ ንብ አዳምጠሃል ?» ብሎ ጠየቀው ።

«አዎ ።»
«ጥያቄዬ አልገባህም ። በተለይ ስለ አባቴ የተናገሩትን ማለቴ ነው ።»
«አዎ ፤ እሱንም ሰምቻለሁ ።»
«ታዲያ ምን አሰብክ?»
«ምንም ። ምን አስባለሁ ።»

«ስማ ሀዲስ ። አዲሱ ትምህርት ቤት ባባቴ ስም መጠራት አለበት ። ይህንን ነው እንድታስብበት የምፈልገው ። የሞተበት መሬት ነው ። መሬ ቱም ቢሆን ንብረቱ ነው ። የስሙ መጠሪያ ማግኘት ይገባዋል » አለ የምሩን ።

«በዚህ ላይ ውሳኔ ልሰጥ አልችልም» አለው ፍርጥም ብሎ ።
«ለምን?»
«ጊዜው ሲደርስ ህዝቡ ይወስናል ።»
«የቱ ህዝብ?»
«ገንዘቡን ያዋጣው ህዝብ ።»

ታፈስ በሳቅ ፈነዳ ። ከት ብሎ ሳቀ ። ሳቁን የሰሙ ሰዎች ወደ ሀዲስና ታፈስ ይመለከቱ ነበር ። ታፈስ ሳቁን አቆመና ፥ «ለዚሁ ብለህ ህዝቡ ድምፅ እንዲሰጥ ልትጠራ ነዋ» ብሎ አሁንም ሳቀበትና ፥ «ወይስ ያባቱ ስም መነ ሳት የለበትም ለማለት ነው!» አለ ማንባሩን ቁዋጥር ።

ሀዲስ ገልመጥ አለና ፥ «ቀስ በል ። አትጩህ ። እኔ ያባትህ ስም መነ ሳት የለበትም ማለቴ አይደለም ። ለኢትዮጵያ ጀግኖች አክብሮት አለኝ ። ግን የኔ አላማ በህዝብ ገንዘብ ያባትህን ስም ለማስጠራት አይደለም ። ይህ እንዲገባህ እፈልጋለሁ ። 'ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምባዩ ቂጥ አለ' እንዲሉ ፥ ተሰርቶ ሲያልቅ ብንነጋገርበት ይሻላል ። አሁን ምን ያጣላናል ። ያኔ ህዝቡ የፈለገውን ይወስናል» አለ ።

«ታያለህ!» በማለት ዛተበት ።
«ምን ልትሆን!»
«ቆይማ ። ታያለህ ። ታፈስ ምናለ በለኝ . . .»

ሀዲስ ተናዶ ወደ ታፈስ ጠጋ አለና በለሆሳስ ፥ «በወርካው አወዳ ደቅ ልትወነጅለኝ አስብህ ከሆነ ነገሩን ካሁኑ ብትረሳው ይሻላል ። ሁለታ ችንም አገገታችን ድረስ የተዘፈቅንበት ጉዳይ መሆኑን አትርሳ ። አሳቡን ያመነጨኸውና ፈንጂውን ያመጣኸው አንተ ነህ ። ሌላም የማውቀው ብዙ ነገር አለ» አለው በደመ በራድነት ።

«እንደ ምን ያለ ነገር!»

«አባ ቆር እና አባ ዋሴ የሚባሉት ሰዎች ትዝ ይሉሃል ?» አለው በጆ ሮው ።

«ትዝ አይሉኝም ። ማን ናቸው?»

«ሰዎቹ ማን እንደ ነበሩ ብታስታውስ ጥሩ ነው ። በግፍ የፈሰሰው ደማ ቸው ይጮሃል ። ጩኸቱ አሁን አይሰማህም ወይ!»

ታፈስ ጥርሱን ነክሶ አፈጠጠበት ። ሰውነቱ በንዴት እንደ በጋ ቅጠል ይርገፈገፍ ነበር ።

ሀዲስ አሁንም ወደ ታፈስ ጆሮ ጠጋ ብሎ ፥ «ስማ ታፈስ» አለ ፥ «ሌላ ነገር አደርጋለሁ ብለህም አታስብ ። በህይወት እያለሁ የዚህ ትምህርት ቤት ስራ በምንም ሁኔታ አይቆምም ።»

ታፈስ ንዴቱን እንደ ምንም እየተቆጣጠረ ፥ «እናያለን! ግን ወደድ ክም ጠላህም ይህ ትምህርት ቤት ባባቴ ስም ይጠራል ። ታያለህ !» ብሎት መራራ ሳቅ ሳቀበትና ከፊቱ ዞር አለ ።

የተሰበሰበው ህዝብ አሁንም ጉድ ነው እያለ እንደ ጉንዳን ይተራመሳል ። አቶ ይርጋንና ሙቶ አለቃ አሸኔን በአይኑ ሲፈልግ አጣቸው ። ሁሉ ቱም የሉም ። ከዚህ ቀደም አይቶት የማያውቀው አንድ ፖሊስ ነበር ቆሞ ሰዎች የሚያነጋግረው ። ሀዲስ ቀውሌን ፈልጎ አገኘውና ፤ «ይህ ፖሊስ ከየት መጣ? ከዚህ በፊት አይቼው አላውቅም» አለው ፤ በሌባ ጣቱ ወደ ፖሊሱ እያመለከተው ።

«አዲስ የመጣ ፖሊስ ነው ። ወታደር ጎይቶም ይባላል ። አንዳንድ ሰዎች አሁን ገና ደህና ፖሊስ መጣልን እያሉ ስለ እሱ ያወራሉ ። የያዘውን ነገር ቢሞት አይለቅም ይሉታል ። እንደ ሰማሁት ከሆነ ካሁኑ ከሙቶ አለቃ አሸኔ ጋር በስራ መጋጨት ጀምሮአል» አለው ወደ ታች እያየው ።

ሀዲስ ከቀውሌ ራቅ ብሎ ቆመ ። አቶ ጣሴ ደጉ ትከሻውን ነካ አድርገውት ዞር ሲል ፤ «ዘዴእችን ስራ አይደለም ወይ?» አሉት ።

«ጥሩ አድርጎ» አላቸው ።

«አዎ ፤ የሰውን ስነ ልቦና ማወቅ ይጠቅማል» አሉትና ገልመጥ እያሉ ከተመለከቱ በሁዋላ ፤ «ያ መናጢ ምን እያለ ነበር የሚጨቀጭቅህ» ሲሉ ጠየቁት ።

ታፈስ ከፊታውራሪ በስተጀርባ ራቅ ብሎ ቆሞአል ። በቀኝ እጁ ቡጢ ጨብጦ የግራ እጁን መዳፍ እየደጋገመ ይመታል ።

ይጨቃጨቁበት የነበረውን ጉዳይ እና የሰጠውንም መልስ ነገራቸው ።

«ደግ አደረክ» አሉ አቶ ጣሴ ፤ መልካም ቢያስብና ቢሰራ ያባቱን ስም በተሻለ ሁኔታ ያስጠራ ነበር ። ግን አልታደሉም ። ባለጌን ካሳደጉ የጎደለ ፀደቀ ። ያደረገውን ሰምተሃል?»

«ምን አደረገ?»

«የሰው ልጃገረድ አበላሸ ። እሱ ብሎ ሳባቱ ስም አሳቢ! ፊታውራሪ አሁን በማነጋገር ላይ ያሉት የልጅትዋን አባት ነው . . . »

ሀዲስ ወደ ፊታውራሪ ዞር አለ ። አንድ ገበሬ ከፊታቸው ቆሞ ፊታውራሪ ሲያናግሩት አስሬ እጅ ይነሳል ። አፈር እየዘገነ ይበትናል ። ርጥብ ሳር እየነጨ ይበትናል ።

«ምናለ በገንዘብ ይታረቃሉ» አሉት አቶ ጣሴ ።

ሀዲስ ወሬ ለመስማት ወደ ፊታውራሪ ጠጋ አለ ። ወጺያውኑ ቶሎሳ እየተጣደፈ መጥቶ አቶን በነጠላው በመሸፈን ፤ በፊታውራሪ ጆሮ አንድ ነገር ሹክ አለ ። ፊታውራሪ ድንገተ ሲሉ አያቸው ። ካባቸው ከትክሻቸው ላይ ወደቀ ። ራሳቸውን ያዙ ። ታፈስ ሮጠ ደገፎ ያዛቸው ። ሀዲስ ባይበልጥ ጠጋ አለ ።

«መቼ ነው!» አሉ ፊታውራሪ ።

ሀዲስ ጆሮውን አቆመ ።

«አሁን ነው» አላቸው ቶሎሳ ።

ሰው ሁሉ በፊታውራሪ ሁኔታ በመደናገጥ ፥ «ምን መጣ ምን ሆነ» እያለ ዙሪያቸውን መሰብሰብ ጀምሮአል ።

«ወላዲትዋ ምን ነው ምን አልኩሽ!!» አሉ ፊታውራሪ እንደ ገና ራሳቸውን ይዘው ።

ልቡ ተሸበረ—ሀዲስ ። ብዙም አልተጠራጠረም ። ነገሩ ምን እንደ ሆነ ገባው ። «ጠለፉዋት አይደል!» አለ ።

ፊታውራሪ ባንዳፍታ ተለውጠው ኳጅተው ሲወድቅ የደረሰ ሽማግሌ መሰሉ ። ታፈሰና ቶሎሳ ደገፈዋቸው ወደ ታፈሰ መኪና ወሰዱዋቸው ።

«ጉድ ሆንኩ ። ወይኔ ! በገዛ እጄ እጄን ቆረጥኩት !» ይሉ ነበር— ፊታውራሪ ።

መኪናዋ አንዴ አጉዋርታ ፥ ጭቃ እየረጨች በረረች ።

«ምን ሰምተው ይሆን?» አለ ቀውሴ በዚያ ቁመቱ ሀዲስ ላይ እንደ ጭላ እያንዣበበበት ።

ሀዲስ ራቅ እያለው ፥ «ምን አውቄ» አለው ።
«መርዶ ያሰሙ ይመስላሉ ...»

«ከመርዶም መርዶ ሊሆን ይችላል» ብሎት ፥ ጥሎት ሮጠ ። ወዴት እንደሚሮጥ አያውቅም ነበር ። ግን ትንፋሹ እስኪቆረጥ ድረስ ነበር የሚሮጠው ።

ህይወት ... አጭር ... ሩጫ ... ናት ... ሩጥ .. ሩጥ .. ሩጥ .. ሩጥ—ግን ወዴት? የዘናሽ ቡና ቤት በር ከውጭ በሰረገላ ቁልፍ ተቆልፎአል ። የተዘጋ በር ። የተቆለፈ በር ። የተዘጋ ፥ የተቆለፈ ህይወት ። በሩን በሃይል ደበደበው ። አቤት የሚለው አልነበረም ። ቁና ቁና እየተነፈሰ የተቆለፈውን በር ተደግፎ ቆሞ ሳለ ቅልጥ ያለ ኡኡታ ሰማ ። ጆሮውን አቁሞ ያዳምጥ ጀመር ። እሱ ከሚኖርበት ቤት አቅጣጫ ነበር ኡኡታው የሚመጣው ። ያው የተለመደው ዱላ ሳይሆን አይቀርም ብሎ ዝም አለ ። ከጠጅ ቤት ወጣ ብሎ በጠገበ ዱላ አናት ሳናት መቱለጥ በሱዷ እንግዳ ነገር አልነበረም ። ኡኡታውም ቢሆን የተለመደ 'ሙዚቃ' ነበር ።

በሩን በቡጢ ገጩና ፥ 'እርግጠኛ ነኝ ፥ ጠልፎ ወስዶአታል !' አለ ። 'ሆ ! እሱ እኮ ሲፈጥን ከአይን ይቀድማል ፥ እሳት የላሰ ሰው ነው' እያሉ አንዳንድ ሰዎች ስለ ሙቶ አለቃ አሸኔ የሚጫወቱት ነገር ትዝ አለው ።

ዋቆ የትያዘ ሰሞን ስለ ሙቶ አለቃ ጀግንነት በየመሸታ ቤቱ የሚወራው ነገር ሁሉ ጆሮው ላይ ያስተጋባ ጀመር — «አይ ጀግና! እናቱ እሳት ወለድኩ ትበል ። እንዲያው እንደ አሞራ በር ሄዶ እኮ ነው ባንድ ጊዜ መድረሻ አሳጥቶ የያዘው ። ሲተኩስማ ለጉድ ነው አሉ ፥ ጥይቱ መሬት ጠብ አትልም ። አገር ያንቀጠቀጠውን ወንበዴ እንዳውሬ ጫካ ለጫካ አሳዶ የፈጀ

አስሮ እንዶ በግ እየነዳ የሚመጣ ጀግና፤ እናቱ ወለድኩ ትበል ። እንዴ፣ እሱ እዚህ ባይኖር እኮ የሱዲ ሴባ አያኖረንም ነበር ። ፀጥ አ'ርጎ እኮ ነው አገሩን የያዘው ። ቆራጥነቱስ! አይ ቆራጥ! በሰው ካለ ፍንክች የለም ። ደግ ነትም ማንም ዘንድ የለም ። ሰው በልቶ ጠጥቶ የሚጠግብ አይመስለውም ። መመንዘር ነው ። እባ መስጠት ሰው ተቸግሮ ካየ ገንዘብ ኪሱ ባይኖር ተበ ድሮም ቢሆን የሚሰጥ ጀግና!»

ፊታውራሪም ቢሆኑ ስለ ሙቶ አለቃ አሽኔ ወንድነት ተጠራጥረው አያውቁም ። «አጉል ድፍረቱን ቢተው እኮ ማስፈያ ጀግና ነበር ። እሱ ባይ ኖር የዋቆን እጅ የቱ ወንድ ደፍሮ ይይዝ ነበር?» በማለት ስለ ወንድነቱ ያላቸውን አድናቆት ሳይሸሽጉ ይናገራሉ ።

ሀዲስ ቡጢ ጨብጦ በሩን እንደገና በሃይል መታው ። የውሻ ልጅ!' አለ ። ራሱን ነበር የሚሰድበው ።— 'በዚህ አለም ቀንቶአቸው ሲኖሩ የሚች ሉት በገጠማቸው እድል ያለ ምንም ማመንታትና ማወላወል ለመጠቀም ወደ ሁዋላ የማይሉት ብርቱዎች ብቻ ናቸው ፣ የተቀረነው የህይወት አሜ ፋሪዎች ነን! አለ በንዴት ።

'ሜጉላ ቤት. . .አይናለም. . .በጀርባዋ ተንጋልላ. . .ጠጉርዋ ተበትኖ. . . የረገፈ አበባ — ጥርሱን ነከሰ ።

ኡኡታው እየበረከተ ሄደ ። ኡኡታው አሁንም የሚመጣው እሱ ከሚኖርበት ቤት አቅጣጫ ነበር ።

—እንደ እሱ ድፍረት ቢኖረኝ ኖሮ ይኸኔ ከአይናለም ጋር ካንድ ሜጉላ ቤት ውስጥ የህይወት ማር ወለላ እጠጣ ፣ ለእግዜር እፍንሜ ደስታ ብቻ ከገነት የተተከለች ብርቅ አበባ እሸት ፣ ለመላእክት ጆሮ ብቻ ተብሎ የተቀነባበረ ጣእመ ሙዚቃ አዳምጥ ነበር ፣ እያለ ወደ ቤቱ ማምራት ጀመረ ። ከመንደሩ ሲደርስ ኡኡታውና ግርግሩ ከአቶ ጣሴ መኖሪያ ቤት ደጃፍ ላይ ሆኖ በማየቱ ደነገጠና እየፈጠነ ወደ ቤታቸው አመራ ።

ሁሉም ባንድነት ይጮሃል ፣ ሁሉም ባንድነት ይናገራል ። የሚደማ መጥ አልነበረም ። ትያይዞ መጯዋጯዋህ ብቻ ነበር ። ሰዎቹን እየገፋ እንደ ምንም በማለት ሰው—ሰራሽ ቀለበቱን ጥሶ ወደ ፊት ብቅ ሲል ፣ አንድ ጠብ ደል ፣ ቀይ ፣ ራሰ በራ ሰው ፣ ካናቱ ላይ እንደ ምንጭ ቡልቅ ፣ ቡልቅ እያለ ከሚወርድ ደም ከተፈጠረች ትንሽ የደም ኩሬ ውስጥ ሽብልል ብሎ ወድቆ አየ ። ሰውዬው አልሞተም ። ትንሽ ትንሽ ይተነፍሳል ። ያደፈጠም ይመ ስላል ። ቀና ባለ ቁጥር ሁሉም በያዘው ዱላ ስለሚወርድበት የሞት መስሎ አድፍጦአል ። የት እንደማያውቀው ጠፋው እንጂ የሰውዬው መልክ ትዝ ብሎታል ።

የቤት ሰራተኛው ከተሰበሰበው ህዝብ መሃል ቆማ አያት ። እህል ውሀ የማያሰኝ ዱላ ይዛለች ። እየተጋፋ ሄዶ ተጠጋትና ፣ «ምንድን ነው ነገሩ ፣ የረጋሳ እናት?» አላት ።

«ሌባ ተይዞ ነው» አለችው ፀሀይ የሚሞቀውን ጥርስዋን እያሳየችው ።
«የምን ሌባ?»
«ያቶ ጣሴን ቤት ሰብሮ ገብቶ ሊሰርቅ ሲል የተያዘ ሌባ ነው ።»
«ቀን በቀን ?» አለ ሀዲስ ፣ ተገርሞ ።

«በመንደሩ የቀሩት አንዳንድ ሴቶች ቤቱን ሰብሮ ሲገባ አይተውት በመጩዋጩዋህ ባይዙት ኖሮ የልቡን ሰርቶ ያመልጥ ነበር» አለችው በያዘችው ዱላ መሬቱን እየቆረቆረች ።

ወዲያውኑ አቶ ጣሴ ደጉ ሲሮጡ መጡ። ገና ከመድረሳቸው ፥«ምንድን ነው እሱ! ምንድን ነው እሱ !» እያሉ ጮሁ ።

ከተሰበሰቡት ሰዎች መሃል አንዱ ፥ «ቤትዎን ሌባ ሰብሮት ነው» አላቸው ።

ሌላ ነገር አልጠየቁም ። እንደ እብድ ዘለው ወደ ቤት ገቡ ። የበሩ ቁልፍ ተሰብሮአል ። ሀዲስ ተከትሎአቸው ወደ ቤት ገባ ። ተያዩ ። ቤቱ ውስጥ ሌላ ሰው አልነበረም ።

ቤት እንደ ገቡ በቀጥታ ያመሩት ወደ አንድ አሮጌ የሳጠራ ወንበር ነበር ። ካሳጠራ የተሰራውን ወንበር ወደ ታች ገልብጠው ውስጡን ተመለከቱ ። ሰውነታቸውም ፥ እጃቸውም ይንቀጠቀጥ ነበር ። ከሳጠራው ወንበር ውስጥ ምን እንደሚፈልጉ ሀዲስ አልገባውም ። ብቻ የሳጠራውን ወንበር እንደ ነበረ መልሰው ካስቀመጡ በሁዋላ ፥ በረጂሙ ተንፍሰው ፥ «ተመስገን እምላኬ» አሉ ።

ከዚያ በሁዋላ ራሳቸውን ይዘው ፥ ቤታቸው ላይ የደረሰውን ሁኔታ በሀዘን እየተመለከቱ ፥ «አየህልኝ ይህን ጉድ !» አሉ ።

እብድ ሲጫወትበት የዋለ ቤት ይመስላል ። አቶ ጣሴ መቼም ስርአት ያልያዘ ነገር ማየት አይወዱም ። መኝታቸው ምስቅልቅሉ ወጥቶአል ። ሳጥናቸው ተሰብሮ እውስጡ የነበረው ልብስ ሁሉ ተንልጉሎአል ። የፅህፈት ጠረጴዛቸው መሳቢያዎች ተሰብረው የትም ተጥለዋል ። የተማሪዎች ደብተርና ወረቀት ወለሉ ላይ ተበትነዋል ።

ወደ ሀዲስ መለስ ብለው ፥ «ለመሆኑ ሌባው ተያዘ ወይስ አመለጠ?» ብለው ጠየቁት ።

ቢያልባቸውም አሁን ነፍሳቸው ተመልሳ የገባች ይመስላሉ ።

«ተይዞአል» አላቸው ።

አንድ ፖሊስ ከወደቀው ሌባ ላይ እያንዣበበ ፥ «ዋእ ወዲ አይተ ። ተነስ እንጂ ምን የሞተ ሰው መስለህ ትተኛለህ» ይለው ነበር ። ሌባው አምልቆ ሲመለከት ፖሊስ በማየቱ ነፍስ ዘርቶ ከተኛበት ብድግ አለ ። የዱላ መአት ወርዶበታል ፥ 'ሌባ ተይዞ ዱላ ይጠየቃል?' እንዲሉ ።

አቶ ጣሴ መናፍስት ያዩ ይመስል ድንግጥ ሲሉ አያቸው — ሀዲስ ። ፊታቸው ሁሉ ባንዳፍታ ተለዋወጠ ። አይናቸውን ማመን ያቃታቸው ይመስላሉ ።

«ምን ሆኑ?» አላቸው ሀዲስ ።

«ይህ ሰው ያቶ ይርጋ አሽከር አይደለም እንዴ!!» አሉ ፥ በመገረም አፋቸውን ይዘው ። «አንተ» አሉ ቀጥለውም ፥ «ወዳጆ አይደለህም ወይ? አታውቀኝም?» አሉት ።

ሴባው ፣ ወዳጆም ይሁን ማን መልስ አልሰጣቸውም ። ሀዲስም በመ ፀናበዱ ነገሩን ለማገናዘብ አልቻለም ። አሳቡ ሁሉ ተበታትኖአል ።

«ያውቁታል?» በማለት አዲሱ ፖሊስ አቶ ጣሴን ጠየቃቸው ።
«አሳምሬ» አሉ አቶ ጣሴ ፣ «አቶ ይርጋ ቤት የኖረ አሽከር ነው ።»

«ማን ነው አቶ ይርጋ?—የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር?» በማለት ፖሊሱ ጠየቃቸው ።

«አዎን» አሉት አሁንም በመገረም አፋቸውን ይዘው ። ሴባው እን ዴም ቀና አላለም ። እንዳቀረቀረ ቀርቶአል ። ደሙ በጆሮ ግንዱ ይወርዳል ።

«የርስዎ ቤት ነው የተሰበረው ፣ አይደለም?»
«ነው» አሉት ፖሊሱን ።
«የጠፉዎት እቃ ወይም ገንዘብ አለ?»
«ለጊዜው አላውቅም» አሉት ።
«ፖሊስ ጣቢያ መጥተው ቃልዎን ሊሰጡን ይችላሉ?»
«ደስ እያለኝ።»
«እንዴ ወደ ቤት ለመግባት ይፈቀድልኝ» በማለት ጠየቃቸው ።
«ይቻላል።»

ፖሊሱ ወደ ቤት ገብቶ ጥቂት ደቂቃዎች ከቆየ በሁዋላ ተመልሶ መጥቶ ፣ «እሺ እንግዲህ» አለ ፣ «የምስክርነት ቃላችሁን ለመስጠት የም ትፈልጉ ከኔ ጋር ወደ ጣቢያ ኑ ።»

እህል ውሀ የማያሰኝ ዱላ የያዙ የመንደር ሴቶች ቃላቸውን ለመስጠት ወደ ጣቢያ መንጋጋት ጀመሩ ።

ሀዲስን ፣ «አንተ እዚሁ ቆይ» አሉት አቶ ጣሴ ።

የሀዲስ ሰራተኛ ከሰዎቹ ተነጥላ እየሮጠች ተመልሳ መጣችና ፣ «ጡዋት አንድ ደብዳቤ ሰው ልኮ ነበር» አለችው ።

«ከየት?»

«ከእመቤት አይናለም ጋ ነው ብላ ነው አንድ ሴት አምጥታ የሰጠ ችኝ ።»

«የት አለ ደብዳቤው?»
«ቤት ነው ። ጠረጴዛው ላይ ።»

ሀዲስ የአቶ ጣሴን ቤት በር ዘግቶ ጠባቂ ካቆመ በሁዋላ ወደ ቤቱ እየ ሮጠ ሄደ ። ሲደርስ በሩ ተቆልፎ አገኘው ።— ጅል! አለና ወደ ፖሊስ ጣቢ ያው ሮጠ ። እጣቢያው ሳይገቡ ደረሰባቸው ። ሰራተኛውን ከሁዋላዋ ጎብ አደረጋትና ፣ «ቁልፉን! የቤቱን ቁልፍ!» አላት ።

«ውይ አፈር በሆንኩት! ረስቼው» ብላ ቁልፉን ከመቀነትዋ ላይ ፈታ ሰጠችው ። መቼም ቀኑ ለሩጫ ጻርጎታልና ቁልፉን ይዞ እንደገና ወደ ቤቱ

ይሮጥ ጀመር —'ሩጥ ያለ ቀን ያስሮጣል' እያለ ። የበሩ ቁልፍ ሁልጊዜ እሺ
ብሎ አይከፈትለትም ። ያስቸግረዋል ። እንደ ምንም ተናንቆ ከፈተ ። ሰራ
ተኛው እንዳለችው ፥ ደብዳቤው ጠረጴዛው ላይ ነበር ።

ያ የሚያውቀው የአይናለም የእጅ ፅሁፍ ነው ። የልብ ትርታው ሲዘል
ተሰማው ። እሱም የሰላምታውን ነገር ዘሎ ያነብ ጀመር — «...ስለዚያ
ጉዳይ በዛሬው ቀን ቆርጫለሁ ። ከዚህ በሁዋላ የሚሆነውን ነገር አላው
ቅም ። ቢሆንም ዛሬ ይለይልኛል ። ከዛሬ በሁዋላ ምናልባት የማንገናኝ
ከሆነ የትምህርት ቤቱን ደወል ነገር አደራ ። ድምፁ ደስ የሚል ቆንጆ
ደወል እንደሚሆን ተስፋ አለኝ ። በል ደህና ሁን» የሚል ነበር ደብዳቤው ።

መልእክቱ አልገባውም ። እንቆቅልሽ ሆነበት ። እንደገና መልሶ ቀስ
ብሎ አነበበው ። ቃላቱም ፥ አረፍተ-ነገሮቹም ያው እንደ በፊቱ እንቆቅልሽ
ሆኑበት ። ወረቀቱ ላይ የውሀ ጠብታ የሚመስል ነገር ይታያል—እን
ባዋ ይሆን? ሳይታወቀው ደብዳቤውን ወደ አፍንጫው ወስዶ አሸተተው ።
ደስ የሚል ገነታዊ ሽቱ ያዘለ የገነት አየር የተነፈሰ መሰለውና እንደገና አሸ
ተተው ። እና ፥ ግራ ተጋብቶ—ምን ማለትዋ ነው? አለ ። «ስለዚያ ጉዳይ በዛ
ሬው ቀን ቆርጫለሁ?»—የቱ ጉዳይ አለ ። ነገሩ የባሰውኑ ፍች የሌለው እንቆ
ቅልሽ ሆነበት። —ብቻዬን ተነስቼ ኮብልዬ ጠፍቻለሁ ማለትዋ ይሆን? ግን
ብቻዋን ተነስታ የት ልትደርስ? የት ልትሄድ ትችላለች? ከተወለደች የገ
ባን ወንዝ ተሻግራ አታውቅም ። አለምዋ ከምታየው አድማስ አልፎ አያ
ውቅም ። ወይስ...ወይስ ከመቶ አለቃው ጋር ኮብልላ ይሆን...ወደ አዲ
አዲሳባ...ይህን አልነበረም የምትመኘው?...አዎን ፥ ሊሆን ይችላል...
አስተምርሻለሁ ካላት...አጅሬ ወስጄ አስተምርሻለሁ ብሎአት ይሆናል...
እሱ የልቡን ካገኘ ምን ግድ ይኖረዋል?...እሱ እንደሆን ይሉኝታ የለ
ውም...ግን እንደ አይናለም ያለች ልጅ ካገኘ ለምንና ለማን ብሎ ነው
ይሉኝታ የሚኖረው?...እኔ ነኝ እንጂ ሞኙ...እሱ ደፋር ነው ። ደፋር!
ደፋር! ደፋር! እያለ ወደ ፊታውራሪ ግቢ ይሮጥ ጀመር...—አንተ ሞኝ ሩጥ...
ሩጥ...ሩጫ እጣ ፈንታህ ነውና ሩጥ...ህይወት ራስዋ ሩጫ ናት...ሮጠው
የማይደርሱበትን ነገር እየሮጡ ማሳደድ...የሌለ ነገር ማሳደድ...ሰዶ
ማሳደድ...የተረገመ ህይወት...የተረገመ ትምህርት ቤት...

ከፊታውራሪ ግቢ እንደ ሮጠ ደረሰ ። ቆም ብሎ ትንፋሹን ያዘ ። ነገሩ
ትንፋሽ የሚያስይዝ ነበር ። ምንድን ነው ጉዱ አለ ። የሆነውን ነገር የሚነ
ግረው ሰው አልነበረም ። ትርምስ ግርግርና ለቅሶ—ጩኸትና ዋይታ ። ወን
ዶች ራሳቸውን ይነጫሉ ፤ ሴቶች ደረታቸውን ይደልቃሉ ። ምንድን ነው
ነገሩ እያለ ሲጨነቅ ቶሎሳ ራሱን ይዞ እየተንጎራደደ ሲጮህ ከሩቅ አየው ።
ሮጠ ወደ እሱ በመሄድ ነገሩ ምን እንደ ሆነ ጠየቀው ።

«የውሸት ሳቅ ኖሮአል ለካ...ስታሞኘኝ ነበር ለካ...» በማለት ይህ
ንኑ እየደጋገመ ነበር የሚጮኸው—ቶሎሳ ።

«ምንድን ነው ነገሩ? ንገረኝ እባክህ!»

አልሰማውም ። የሚሰማውም አይመስልም ። በሀዘኑ ተውጦ ጠፍቶ
አል ። እነዚያን ቃላት እየደጋገመ ይጮሃል ። ሀዲስ ሊታገስ አልቻለም ።
ሁለቱንም እጆቹን በሃይል ጭምድድ አድርጎ ይዞ ወደ ግድግዳ አስጠጋ
ውና ፥ «የሆነውን ነገር ንገረኝ ነው የምልህ!» በማለት ጮኸበት ።

«ኢጇን ቆረጠችው . . . እህህህ!»
«ምን አድርጋ!»
«ምን ይወራል ! ምን ይወራል! እህህህ!»
«ለቅሶውን አቁምና ንገረኝ!»

«ለሰው የሚራራው አንጀትዋ እንዴት በራስዋ ላይ ጨከነ! ጨከነ ጨከነ! እህህህ!»

«አሁን የት ናት? የት ናት?!»
«እልፍኝዋ ውስጥ ናት ። አትተርፍም ! አትተርፍም! እህህህ!»

ቶሎሳን ለቀ ወደ አይናለም እልፍኝ ሮጠ ። በሩ ተዘግቶ ነበር ። በሩን ለመስበር ምንም አልቀረውም ። ታፈሰ ነበር የከፈተለት ። ፊታውራሪ ፣ መምሩና ታፈሰ ሶስቱም አፋቸውን ከፍተው ቀሩ ። ተንደርድሮ እንደ ገባ ተንደርድሮ ሄዶ አይናለም ላይ ወደቀ ። ከድንክ አልጋዋ ላይ ተጋድማ ነበር ።

«አለሁ በዪኝ እባክሽ ! አለሁ በዪኝ ! ጥፋተኛው እኔ ነኝ ! እኔ ነኝ ጥፋተኛው ፣ ለዚህ ያበቃሁሽ ! እባክሽ አለሁ በዪኝ !»

አይኖችዋን ቀስ ብላ ከፈተች ። በእንባዎቹ ውስጥ ንህ ሲቀድ ታየው ። ህይወት ሰጪ የሆነችው ፀሀይ እየወጣች ትሄድ ነበር ። ሶስቱም አፋቸውን እንደ ከፈቱ ቆመው ይመለከቱዋቸው ነበር ። በተለይ ፊታውራሪ የማይታመን ራእይ የሚመለከቱ ይመስል ያረጁ አይኖቻቸውን ማመን አቅቶአቸው ነበር ። ጆሮአቸውም የሚሰማውን ነገር ማመን የተሳነው ይመስላል. . .

# ክ ፍ ል ፲፫

«አፍርሱልኝ ነው'ኮ እምለው !»

ሰውዬው አበዱ እንዴ? የሚል ይመስል ነበር ፣ ሰዉ ሁሉ ። እውነትም ፊታውራሪ ያበዱ ይመስሉ ነበር ። የሳሳው ጠጉራቸው ቆሞአል ። ከግንባራቸው መሃል ያለው የደም ስር ቱቆጥቶ ተገትሮአል። እርጋታ አጥተዋል። ቁጭታቸውን የሚወጡበት ነገር አጥተው ሲቅበዘበዙ ሳያቸው ሰው ፣ ታድኖ የሚበላ አውሬ አጥቶ የተናደደ ያረጀ አንበሳ ይመስሉ ነበር ። ለእይናለም ሰርግ ሲሰራ የከረመው ታላቅ ዳስ ባንዳፍታ ድምጥማጡ ሲጠፋ እያዩ ፣ «አዎን ፣ ከፊቴ አጥፉልኝ! ጥንቱን የተረገመ ምኞት ምንም ቢያደርጉት አይባረክም ። ገባ ለያይቶን የሚናረው ያለ ምክንያት አይደለም ። ግን በዚህ እድሜ ባያሳዝነኝ ምን ነበረበት? ደስ ብሎኝ ለመሞት አልታደልኩም ። ርግማን ነው ! ሌላ አይደለም ። ርግማን ነው !» ይሉ ነበር ፣ ደጋግመው ።

ታፈሰ አጠገባቸው ቆሞ ዳሱ ሲፈርስ ይመለከት ነበር ። ፊታውራሪ በንዴት ዞሩበት ።

«ይህን ርግማን ፣ መአተ ቁጣ በቤቴ ላይ ያመጣኸው አንተ ነህ!» ብለው ጮሁበት ።

ዳተኛ አንገቱን ደፍቶ ፣ «ምን አድርጌ?» አላቸው ።

«ደሞ ምን አድርጌ? ይለኛል! የሌባ አይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ አሉ ። የድሀ እንባ አታምጣብኝ ብዬህ አልነበረም?»

«ብለውኝ ነበር።»

«ታዲያ ምን አደረክ? ሄደህ ጭሰኞችን አባረርክ ። የሰው ቤት አፈረስክ ። ይባስ ብለህ የሰው ልጃገረድ አበላሸህ ። መቼም ሰው የሚነግራችሁን ነገር አትሰሙም ። ትቃራኒውን ነው የምታደርጉት ። ልባችሁ አይታወቅ ፤ አመላችሁ ቅጥ የለው ። መአት ዘርቶ ፍዳ ማጨድ!!»

ታፈሰ ካጠገባቸው ዞር አለ ።

ዳሱን ወደሚያፈርሱት ሰዎች እየተመለከቱ ፣ «አዎን ፣ ቶሎ ፣ ቶሎ በሉ ። የሰው ምኞት እንደ ሆነ ከንቱ ነው ። የከንቱ ከን ቱ ነው» ይሉ ነበር ።

ሀዲስ ፣ ዳሱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ሲሄድ ባየ ቁጥር ፣ ውስጥ ውስጡን ይኮፈስ ነበር ። አሁን ግን ልቡ ላይ ያለው ደስታ ይ ሁን ሀዘን ለይቶ ለማወቅ አልቻለም ። ማንኛውም ነገር ጨልሞበት ነበር ።

«እምን ፥ ከፊቴ አጥፉልኝ!» አሉ ፊታውራሪ ሙከ ብለው ።

ዳሱ ድምጥማጡ እየጠፋ ሲሄድ ይታይ ነበር ። ፊታውራሪ ጠጉራቸውን እየነጩና እያጨበጨቡ ይንጎራደዱ ነበር ። ሁኔታቸው አስፈሪው— እሱንም ። እንደ ታፈሰ ከፊታቸው ዞር ሲል አሰቦ ነበር ። ድንገት ፊጠራት የነቁበት መስሎት ደነገጠ ።

አይኖቻቸው እውስጡ ድረስ ዘልቀው ልቡን የሚመለከቱት ስለ መሰለው የመጨነቅ ስሜት አደረበት ። መጀመሪያ ሲተዋወቃቸው ያደረበት ስሜት ትዝ አለው። ከአይኖቻቸው ለመሰወር እየፈለገ ዝም ብሎ ቆመ—አይናቸውን በአይኑ እየሸሸ ። አንድ የረሱትን ነገር ለማስታወስ ጥረት ሲያደርጉ ቆዩና ፥ «እምን ፥ የምን ወረቀት ነበር የላከችልህ?» አሉት ።

ስለ ደብዳቤው የነገሯቸቸውን ገረድ በልቡ እየረገመ ሳይወድ ወረቀቷን ከኪሱ አውጥቶ ሰጣቸው ። ደብዳቤውን ተቀብለው በሚያነቡበት ጊዜ እጃቸውም ከንፈራቸውም ይንቀጠቀጥ ነበር ። አይናቸው ከላዩ ላይ በመነሳቱ በእፎይታ ተነፈሰ ። ልዩ ልዩ ጥላዎች ከፊታቸው ላይ ያንዣብቡ ነበር ። ደብዳቤውን እንደ አንብበው ወጡት ። ግን ያልገባቸው ነገር እንዳለ ከፊታቸው ያስታውቅ ነበር ። ግንባራቸውን ቁጥጥረው ለሁለተኛ ጊዜ አነበቡት ። አሁንም ነገሩ ግር ስላላቸው ግንባራቸውን ሳይፈቱ ፤

«የምን ደወል ነው እሱ?» አሉት ።
«የትምህርት ቤቱ...»
«የቱ ትምህርት ቤት?»
«አዲሱ ትምህርት ቤት።»

ነገሩ ይበልጥ አስገርሞአቸው ትኩር ብለው ይመለከቱት ጀመር ። ሆኖም እሱን የሚመለከቱም አይመስሉም — ሲያዩአቸው ። እንዴት ሆኖ? የት ሄጀ? በማለት ራሳቸውን የሚጠይቁ መስለው ነበር የሚታዩት ። ይህን ብቻ አልነበረም በላያቸው ላይ ያየው ። ድንገት በራሱ ላይ እምነት ደጣ ፥ ከስልጣኑ የወደቀና ያረጀ አምባ ገነን ምስል ነበር በአይነ-ህሊናው የመጣው—ሲመለከታቸው። ብዙ ነገር እንደ ፈለጉት በፈለጉበት ጊዜ ሲያደርጉ የኖሩ ሰው ፥ አሁን ልጃቸውን በፈቃዳቸው አንበተው የመዳር ቀላል ነገር ከቁጥጥራቸው ባሻገር ሆኖባቸው ፥ በራሳቸው ላይ እምነት ፥ በህይወት ላይ ተስፋ አጥተው አይናቸው ውስጥ ይነድ የነበረው እሳት በርዶ ሲመለከታቸው ፥ በመፍረስ ላይ እንዳለው ዳስ ውልቅልቅ ፥ እንክትክት እንኩትኩት ብለው ታዩት ። አዘነላቸው ።

አንድ የረሱት ሌላ ነገር ድንገት ትዝ ያላቸው ይመስል ቍቁጥጥር የነበረውን ግንባራቸውን ፈታ አደረጉና ፥ «ቅድም ስትናገረው ከነበረው ነገር ውስጥ የምታስረዳኝ ነገር አለ» አሉ ።

«ምን ነበር?» አላቸው ።

«'እኔ ነኝ ጥፋተኛው' ስትል ምን ማለትህ እንደ ሆነ ብታስረዳኝ?» አሉት ።

«እኔ?»
«አዎን።»
«መቼ ነው እንዲህ ያልኩት?»

«ቅድም ከቤት ስትወጣ . . . እ . . . እያለቀሰክ፥ 'እኔ ነኝ ጥፋተኛው' ትል ነበር . . . እ . . . »

ሀዲስ ትዝ አለው ። ሌላስ ምን ቀባጥሬ ይሆን እምሳኪ? ብሎ አሰበ ። ግን አላሙነታም ። የሆነውን ነገር ሁሉ ከስር እንስቶ ነገራቸው ። አንዳንዱ የሚያዳምጡት አይመስሉትም ነበር። የሚነግራቸውን ነገር ማዳመጥ ትተው ባሳብ ጭልጥ ብለው ይሄዱና ፥ «ወይ ጉድ! ጉድ ነው'ኮ ። ከቤቱ ጣራ ስር የሚሆነውን ነገር ሁሉ አውቃለሁ የሚል ማን ነው? ከንቱ ነው ። የቤቱን ጉድ ሁሉ የሚያውቅ የለም ። ወይ ጊዜ! አባትና ልጅ ልብ ለልብ የማይተዋወቁበት እንዲህ ያለው ክፉ ጊዜ ይምጣ! ትንግርት ነው!» በማለት ከፉኛ ራሳቸውን እየነቀነቁ ያጨበጭቡ ጀመር ።

አንዳንዴም ታውሮ ከርሞ ድንገት በነቃ ጊዜ በገጠመው አዲስ እውነታ ምን ማድረግ ይቻለው ዘንድ አጥቶ እንደሚቸገር ሰው ይሆኑበት ነበር ። ምናልባትም የገጠማቸው ነገር የልብ ኩራታቸውን ጭምር ሳይነካው አልቀረም ። «ወይ እኔ ሰውዬው! እሺ?» አሉት በመጨረሻ ።

«ይሄው ነው» አላቸው ።
«ለትምህርት ቤቱ ስራ ስትል ነዋ አይሆንም ያልካት!»
«አዎን ፥ የህዝብ አደራ አይደል?»
«ስራው ባይዝህስ ኖሮ?»

ሀዲስ አቀርቅሮ ዝም ብሎ ቀረ ። ግን ፊታውራሪ ጥያቄአቸውን በዚያው አላቆሙም ። «'እኔ ነኝ ጥፋተኛው' ስትል ምን ለማለት አስበህ እንደ ሆነ አሁንም አልገለፅክልኝም» አሉት ።

ሀዲስ ጠጉሩን ቆፈረና ፥ «ፊታድዋን ብፈፅም ኖሮ ይህ አደጋ አይደርስባትም ነበር ለማለት ነው» አላቸው ፥ ፍርጥም ብሎ ።

«ግን እኔን ገድለህ ሄድክ ማለት ነው ። ወይ ፈጣሪ! የጥፋት መልክተኛ ነህ ወይስ ምንድር ነው? ወይ ተአምር! የዚህ ነገር ትርጉሙ ምንድር ነው'ኮ? እያሉ ራሳቸውን በመነቅነቅ ሲያጨበጭቡ ቆዩና ፥—

«ቶሎሳ፤የት አለ?» አሉ ።

ከየት መጣ ሳይባል ከተፍ አለ ።

«መምሩ የት ናቸው?»
«ከእመቤቴ እልፍኝ ናቸው? ።»
«ምን ይሰራሉ?»
«ዳዊት እየደገሙ ጠበል በመርጨት ላይ ናቸው ።»

«ጥራቸው» አሉትና ፥ ወደ ሀዲስ መለስ ብለው ፥ «የደወሉን ነገር አደራ ብላህ የለ? አዎን ። ጥሩ ነው ። ምናለ» በማለት ተክዘው ፋቅ ሲመለከቱ ቆዩና ፥ ትዝ ያላቸው ነገር ስለ ዘገኑናቸው ሳይሆን አይቀርም ፥ «በስመ አብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» ብለው ካማተቡ በሁዋላ ፥ «'የሞት ሙሽራ ሆኜ ሄጃለሁ ። ለተዝካሬ የሚወጣውን ገንዘብ ሳዲሱ ትምህርት ቤት ደወል አውልልኝ ። ከዚህ ሌላ ኑዛዜ የለኝም' ብላለች ትታልኝ ልትሄድ ባሰበችው ደብዳቤ ላይ» አሉና በነገሩ በጣም አዝነው ለእሱ ሳይሆን ለራሳቸው ፥ —ይህን መአት የሚያመጣብኝ ፈጣሪ ምን ብበድለው ይሆን? ለሰው ክፉ አይ

ደለሁ ። የተራበ ሰው ጠመሁን ፥ የተቸገረ ባዶ እጁን ከደጄ ተመልሶ አያውቅ ። የድሀ እንባ የለብኝም ። ምን በደልኩ? በምን ሀጢአቴ ያልዘራሁትን መከራ ያሳጭደኛል?

እሰዋስ ብትሆን? ለወግ ለማእረግ ሳብቃሽ አልኩዋት እንጂ ሌላ ምን በረልኝ አልኩዋት? ካይኔ እትራቂ ማለት ነውር ነው? ሀጢአት ነው? ኩብልላ ለመጥፋት ወይም ራስን ለማጥፋት መነሳት አሁን ምን ይባላል? ወይ ጊዜ! የዘመኑን ልጆች ልብ እንዲህ ያጠጠረው ፥ እንደ አሸዋ ሆዳቸውን ያቪከረው ነገር ምንድር ነው? ወይስ በእነሱ ሊቀጣን አስቦ ይሆን? በማለት ብቻቸውን ሲያወሩ ቆዩና እንደገና ወደ ሀዲስ መለስ ብለው ፥ «መቼም እሱ ያመጣውን ሰው አልችል አይልም ። ማለፊያ ነው። ‘ሰው ያስባል እሱ ይፈፅማል ፤ የሰው ምኞት ብቻውን ከንቱ ነው’ ይል ነበር መክብብ» ብለው ንግግራቸውን በማቋዋረጥ እተኩረው ሲመለከቱት ከቆዩ በሁዋላ ፥ «መክብብን እንደምትመስል ከዚህ ቀደም ነግሬሃለሁ?» በማለት ጠየቁት ።

«አዎን» ብሎ መለሰላቸው ።

«አዎን ። እሱም እንዳንተ ከስንት ትውልድ ጀምሮ ዘር ማንዘሩ ሁሉ ቄሶች ነበሩ ። ከአስራ አራት ትውልድ ጀምሮ ። ግን ምን ያደርጋል? ቄስ ለራሱ አያውቅ ። እሱም በገዛ እጁ ነው ራሱን ያጠፋው» ብለው አሁንም ለሀዲስ ሳይሆን ለራሳቸው ፥ —ሰው ራሱን በገዛ እጁ ለማጥፋት እንዴት ይነሳል? ለሰው ምንም ፍቅር የለውም ማለት ነው'ኮ ። ለቀረው ማሰብ እንዴት ለሰው ልጅ ይሳናል? ሰው ሙዋች ነው ፥ ቢሆንም ከፍጡራን ሁሉ የርህራሄ ፥ የመስዋእትነትና የመቻል ተሰጥኦ ያለው ያለ ሰው ማን አለ? አይ ሰው! በማለት ሁለቱንም እጆቻቸውን ወደ ሁዋላ አጣምረው ይዘው በማቅርቀር ወደ መሬት እየተመለከቱ ሲያስቡ ከቆዩ በሁዋላ ፥ «ደግ ነው እሱ ያለው ሳይቀር ። ደግነቱ ለተዝካርዋ ሳይሆን ለሰርግዋ የታሰበውን ወጭ ለትምህርት ቤቱ ስራ እንዲውል አደርጋለሁ ። ፈቃዱ ይህ ከሆነ ። ግን ከተሰራ ሳይቀር ሰፋ ይበል ። ለስምዋ መጠሪያ ቁና ሰፋች መባል ደግ አይደለም ። ስም አይሞትም» አሉት ።

ሀዲስ ባንድ ፊት ደስ ሲለው በሌላ በኩል ልቡ እየተከፋ ፥ «አስቀድሞ የተዘጋጀ ፕላን አለ ። አሁን እሱን መስወጡ ጊዜ ይፈጃል» አላቸው እየተነጫነጨ ።

«መቼ የተሰራ ፕላን ነው?»
«ቆይቶአል።»

«ታዲያ የቆየ ፕላን ለዛሬ አይሆንም ። ዛሬ የሚታቀደውም ለወደፊቱ እንደሚያገለግል ሆኖ መቅረብ አለበት ። ሉዱ ደግሞ እያደገች በመሄድ ላይ ነው ያለችው ። ግን ፥ ምን የሚያስቸኩል ነገር አለ?» አሉት ።

ሲያስበው ሉዱ ሃመጣው ላንድ አመት ጊዜ ብቻ ከመሆኑ በስተቀር የሚያስቸኩል ሌላ ነገር አላገኘም ።

«መልስ አልሰጠኸኝም ። ምን የሚያስቸኩል ነገር አለ? አዲሱ ፕላን እስከሚዘጋጅበት ጊዜ ድረስ አንድ ወይም ሁለት ወር ቢዘገይ ምን ልዩነት ያመጣል? ከተሰራ ሳይቀር ቋዋሚና ዘላቂነት ያለው ነገር ቢሰራ ይሻላል ብዬ ነው» አሉት ።

«የጀመርኩትን ስራ በጅምር ትቼ መሄድ ስለማልወድ ነው» ብሎ ሃቁን ነገራቸው ።

«የት ትሄዳለህ?»

«የመጣሁት ላንድ አመት ነው ። ከመጪው መስከረም በፊት ወደ ትምህርት ቤቴ እመለሳለሁ ። እና ፣ ከመመለሴ በፊት ስራው አልቆ ልማየት ፈልጌ ነው እንጂ ሌላ የሚያስቸኩልስ ነገር የለም» አላቸው ።

ፊታውራሪ በነገሩ በመገረም ራሳቸውን ነቀነቁና ፣ «'ሰው ያስባል ፣ እሱ ይፈጽማል' ይል ነበር መክብብ ። እዎን ፣ ልክ እሱን ነው የምትመስለው ። የነገውን ማን ያውቃል? የነገው ቀርቶ ዛሬ ጠዋት ከቤቴ ስወጣ ይህ አደጋ ይደርስብኛል ብዬ አላሰብኩም ነበር ። ሞትም ሆነ እንጀራ ባሰቡት ቦታ ላይሆን ይችላል ። የህይወት ምስጢርዋ ረቂቅ ነው ። እስቲ አስብበት ። ለትልቅ ትምህርት ቤትም ትልቅ ደወል ማስፈለጉ አይቀርም ። ችግር ከገጠመህ እረዳሃለሁ ። ቅድም እንዳልኩት ለልጁ ሰርግ ታስቦ የነበረው ወጪ ሁሉ ለዚሁ ስራ ይውላል...» እንዳሉት መምሩ እንደ ወፍራም ቁምቡርስ እየተሳቡ መጡ ።

ሀዲስ ፊታውራሪን ተሰናብቶ በመሄድ ላይ ነበር ።

«መምሩ አሁኑኑስርጉ መስረዙን ለፊታውራሪ ይጻፉልኝ» ሲሉ ቆምአሉ ።

«በምን ምክንያት ብዬ?»
«የሆነውን ነገር ይግለፁለት ። ሰው ከሆነ እሱም ማዘኑ አይቀርም ።»

«እንዴት ተብሎ? ባይሆን የሰርጉ ቀን ተላልፎአል ቢባል ይሻላል ። የልጅ ነገር ነው የተሰራው ። ውሎ አድሮ ሳይፀፀታት አይቀርም ።»

ፊታውራሪ በመጨረሻ ያሉትን ሳይሰማ በመሄዱ ተቆጨ ። መምሩ ጥምጥማቸው እስኪነቃነቅ ድረስ ነበር የሚከራከሩት ። —ምን ብለው ይሆን? እንደ እንቁ የሚያበሩት ከዋክብት ለጥያቄው የሚሰጡት መልስ አልነበራቸውም ። ምፀታዊ ፈገግታ የምታሳየው ግማሽ ፣ብርማ ጨረቃም በበኩልዋ የምታካፍለው ምስጢር አልነበራትም ። ከወትሮ ዝቅ ያለ መስሎ የሚታየው ጥቁር ሰማይም ፀጥ ብሎአል ። አንድም ጉም ለምልክት አይታይበትም ። ከዋክብቱና ጨረቃዋ አንድ ላይ አድመው ጉሞችን ከሰማዩ ላይ ለምሽቱ ያባረሩዋቸው ይመስል ። የሀዲስ ልብ በሀዘን ተወረረ ። በአይናለም ላይ ስለ ደረሰው አደጋ ራሱን ይቅር ለማለት አልቻለም ። የወንጀለኛነት ስሜት አድሮበት ነበር ። እና ፣ በእንቁ መሳይ ከዋክብት ጉራማይሌ ተንቆጥቆጦ በዝምታ ተንጣሎ የሚታየው ጥቁር ሰማይ ሊያፅናናው ከቶ አልቻለም ።

የዛሬው ምሽት እንደ ሌሎች ምሽቶች የሀዘኔታ ድምፀት አይሰማበትም ። የዋሽንት ድምፅ ኮለል እያለ ፣ ከፍ እያለ ወደ ሰማየ ሰማያት ሲዘልይሰማ ነበር ለከዋክብቱና ምፀታዊ ፈገግታ ለምታሳየው ግማሽ ጨረቃመገሳ የሚያቀርብ ይመስል ። የዋሽንቱን ፣ ሀዘኔታ የተሞላበት ጠለቅ ያለድምፀቱን ነበር የሚወደው ። ሲያዝን ፣ የሰውን ልጅ አሳዛኝ የህይወትታሪክ የሚነግረው እየመሰለው ለወትሮው በሀዘን ተውጦ ያዳምጠውነበር ። በዛሬው ምሽት ግን ሳቅ ሳቅ ነበር የሚለው ። እንደ ማስካካት

ይታጣዋል ። ወደ ቤት ሊገባ ሲል የሌሎች ዋሽንቶች ድምፅ ሰማ ። ሁለት ነበሩ ። ነገሩ እንግዳ ስለ ሆነበት —እነዚህ ደግሞ ከየት መጡ? በማለት ቆሞ ያዳምጥ ጀመር ። ያባ ጨፌ ድቤ ከሰሞኑ ፀጥ ብሎአል ። — ድቤው ተበሳ! ወይስ የት ሄዶ ነው? በማለት ራሱን ጠየቀ ።

ሁለቱን ዋሽንቶች ከዚህ ቀደም ሰምቶአቸው አያውቅም ። ነባሩ ባለ ዋሽንት —እንደ ሀዲስ— ነገሩ እንግዳ ሆኖበት ሳይሆን አይቀርም ፣ ጨዋታውን አቋርጦ አደፈጠ። አዲሶቹም ዝም አሉ። ዋሽንቶቹ አድፍጠው ሲጠባበቁ ብቸኛ ጅብ ከሩቅ ሲጮህ ተሰማ ። የቅርብና የሩቅ መንደሮች ውሾች እየተቀባበሉ ይጮሁ ጀመር ። 'አታሳልፈው! አታሳልፈው! ያዘው!' የሚባባሉ ይመስላሉ ። የጉረቤቱ አውራ ዶሮ እንደ ልማዱ ድንገት ጮኸ ። እኩለ ሌሊት ሳይሆን ድንገት ተነስቶ ይጮሃል — ሁል ጊዜ ። ሀዲስም በሚሰማው ጊዜ ሁሉ ፣ 'ይህ አውራ ዶሮ እብድ ሳይሆን አይቀርም' ይላል ።? ጮሆ ከጨረሰ በሁዋላ የመንደሩ ዶሮዎች ጩኸቱን ተቀብለው ማስተጋባት ይጀምራሉ ።

—የመንደሩ ዶሮዎች እብዱን አውራ ዶሮ ተከትለው ያለ ጊዜ ከጮሁ እብድ መሆን አለባቸው ፣ ይላል—አንዱ ሌላውን እየተከተለ ሲጮህ እያዳመጠ ። ጊዜን በመለካት ረገድ የዶሮዎች ትንሽ ጭንቅላት ያለው ምስጢራዊ ተሰጥኦ ሁልጊዜ ይደንቀዋል ። — ምፅአትን አስቀድመው የሚያበስሩ እነሱ ሳይሆኑ አይቀሩም ፣ ይላል ። እና ፣ በምፅአት ቀን ፣ ከንቱን ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ የዘረጋ አውራ ዶሮ ዳመና ላይ ቆሞ ሲጮህ ባሳቡ ይመጣበታል ። የቤትጩኸት ጨለማውን ሰንጥቆ ይሰማ ጀመር ። 'የሀኪም' የቪጥላ የፍቅር ዱላ ።

ነባሩ ባለ ዋሽንት ጨዋታውን ጀመረ ። ሀዲስ ጆሮውን አነቃ ። አዲሶቹም አብረውት ጀመሩ ። ከነባሩ ባለ ዋሽንት ድምፀት ላይ የንዴት ስሜት እይሎ ይሰማ ነበር ። ድምፁን በመሰባበር ወደ ላይ ከፍ እያለ ፣ እየራቀ ፣ እየመጠቀ ፣ ጭልጥ እያለ ሲሄድባቸው አዲሶቹም የእሱን ፈለግ ይዘው ሊከተሉት ይሞክራሉ ። ፍልሚያ ይዘው ነበር ።

—እወዳታለሁ ፣ ግን እውነትም ፣ እውነተኛ ፍቅር እንከን አያጣውም! አለ።

ግን ፣ — ስለዚያ ጉዳይ በዛሬው ቀን ቆርጫለሁ... ስትል ምን ማለትዋ ነው? በማለት ያስብ ጀመር ። የቱ ጉዳይ? በደብዳቤዋ የተባለውን ጉዳይ እንደሚያውቅ አድርጋ ነበር የፃፈችው ። ነገሩ እየቆየ ይከነክነው ጀመር ። ምን ማለትዋ ይሆን? ከዚህ ቀደም ያላትን ነገር ሁሉ ወደ ሁዋላ ተመልሶ አንድ በአንድ እያስታወሰ ያሰላስል ጀመር ። ፍንጭ የሚሰጠው ነገር አላገኘም ። —ወይስ አሳቤን በተሳሳተ መንገድ ተርጉማው ይሆን? ሊሆንይችላል ። ግን ፣ ምንም ትርጉም አላገኘለትም ። ምናልባት ሞትን እያሰበች አእምሮዋን በሳተችበት ወቅት ይሆናል የፃፈችው... የሞት ጥላ እየታያት ። ሀዘን የተጫነው ልቡ ከበደው ።

—ፍቅር ፣ ከሀዘን ሌላ ምን ሙዚቃ ፣ ምን ቋንቋዋ ፣ ምን ቃላት ይኖሩዋል ? በማለት የትካዜ ከርቤ ይታጠን ጀመር ። ከዋክብቱ ሁሉ የእንባ ጠብታዎች መስለው ታዩት ። ባለ ዋሽንቶቹም የልቡን ሀዘን የደረሱበት

ይመስል ፤ ጣፋጭ እሪት የሆነ ጣእመ ዜማ ጭልጥ ካለው ጨለማ ላይ ያን ቀረቁሩ ነበር ...

ዱዋ!

የጨለማው ፀጥታ ተናጋ ። ሸለቆዎች የተኩሱን ጩኸት ተቀብለው አስተጋቡ ። ዋሽንት ተጨዋቾቹ ፀጥ አሉ ።

ዱዋ!

ሌላ ተኩስ...እና ፤ እረጭ ያለ ፀጥታ...

ምእራፍ ፫

# ክፍል ፲፩

አቶ ጣሴ ደጉ ሀዲስን ጡዋት በማለዳ ከጣፈጠ እንቅልፉ ቀ ሰቀሱት ። እንደ ልማዱ ትንሽ ተንጫነጨ ። ሆኖም እንደ ሌላው ጊዜ ሳይሆን ቶሎ ብሎ ነቃ ።

አቶ ጣሴ ባንድ አዳር በጣም ተጨማደውና ጎብጠው ታዩት ። ተስፋ የሚባል ነገር ከውስጡ ተጨምቆ የወጣ ሰው ይመስላሉ ። ትንፋሻቸው ሲጥ ሲጥ እያለ ያስጨንቃል ። እሳቸው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ከሄዱበት ጊዜ ጀምሮ አላያቸውም ። አልተገናኙም ። አደራ ብለው የሄዱትን ቤት ጥሎ በመሄዱ ሲፀፀት ነበር ያደረው ። ግን እድሜ ለሠራተኛው ቤቱ ባዶውን አልዋለም ።

«ማታ የሆነውን ነገር ሰምተሃል?» አሉት ።

«ምንም አልሰማሁም ። ምን ሆነ?» አላቸው ፥ በእጃቸው የያዙትን እቃ ባይኑ እየቃኘ ። አረንጉዋዴ የብረት ሳጥን ይዘዋል ።

«የተያዘው የይርጋ አሽከር ሞቶ አደረ...»
«እውነት! የት? እንዴት?» አለ ሀዲስ ።
«ማታ ተኩስ አልሰማህም?»
«አንድ ሁለት ጊዜ ሲተኮስ ሰምቼ ነበር...»

«አዎን ፥ ከእስር ቤት ሰብሮ ለማምለጥ ሲሞክር ተገደለ ነው የሚሉት ። ግን እውነት አይደለም ። ነገሩን ደርሼበታለሁ» አሉትና ፥ ከአስማቸው ጋር እየተናነቁ ፥ «ለጥያቄ ትፈለጋለህ ተብሎ ነው ከእስር ቤት እንደ በግ ተጎትቶ የተወሰደው። አሁን ማ'ይሙት ፥ በውድቅት ጭለማ ለጥያቄ የሚፈለግ ተራ ሌባ አለ? ለዚያውም ጎይቶም የሚባለው ፖሊስ በመስቀለኛ ጥያቄ እያጣደፈ ቃሉን ሲቀበለው ነበር የዋለው ... አይ ፖሊስ! ካንጀቱ ፖሊስ ነው!...የለም ወዳጄ ። ከእስር ቤት ሲያመልጥ አይደለም የተገደለው ። ምስጢር እንዳያወጣ በግፍ የተሰዋ ሰው ነው ። ይህ ነው ሃቁ» ብለው ነገሩት ።

ሀዲስ ራሱን ይዞ አቀረቀረ ። አሁን ነገሩ ሁሉ ግልፅ ሆኖ ታየው ። 'የት ነበርኩ?' አለ ። ልቡ የት እንደ ነበረ አላጣውም ። በአካል እንጂ በመንፈስ ቤታው ላይ አልነበረም ።

«ገንዘቡ አልተነካም አይደለም?» አለ ሀዲስ ።
«አልተነካም ።»
«ሳጥንዎን ሁሉ ሰብሮ እንዴት ሳያገኘው ቀረ?»

«ገንዘቡ እፊት ለፊት ካንድ አርጌ የሳጠራ ወንበር ውስጥ ነዘር» አሉት ።

«ኧረ !!» አለ ሀዲስ ተገርሞ ።

«አዎ ፥ ሌባ እፊት ለፊት የተቀመጠ ነገር አያይም» አሉ አቶ ጣሴ ። «አብዛኛውም ሰው እንደዚሁ ነው ። ግልፅ ቦታ ላይ ያለ ነገር አይታየንም ። የተደበቀ ነገር አለ በማለት የማይታይ ወይም የሌለ ነገር ስንፈልግ ነው የም ንውለው ። ሀይወትን እፊት ለፊት ብንመለከታት በረከትዋ ብዙ ነው ። ግን የምናየውን ትተን የማናየውን ስንፈልግና ስንመኝ ጊዜ እናጠፋለን» በማ ለት ትክዝ ብለው ሲያስቡ ቆዩና ፥ «ግን» አሉ ፥ «እስካሁን የሚገርመኝና ያልገባኝ ነገር ገንዘቡ እኔ ጋ መሆኑን ለማወቅ እንዴት እንደ ቻለ ነው ።»

ሀዲስ ራሱን በጣም ነቀነቀና ፥ «እኔ ነኝ የነገርኩዋቸው ብዬዎት አል ነበረም?» አለና ጠጉሩን በንዴት ቆፈር ቆፈር አደረገ ።

«አዎ ፥ ረሳሁት ። አረጀሁ መሰለኝ ። ነገር ይረሳኛል» አሉት ።

«አዎን !» አለ ሀዲስ ፥ «አንድ ቀን ገንዘቡን የት እንዳኖርነው ፥ በነ ገ ር መሃል ፥ እግረ መንገዳቸውን ጣል አድርገው ስለ ጠየቁኝ እርስዎ ዘንድ መሆኑን ነገርኩዋቸው ።»

'ምንኛ ሞኝ ነኝ! መቼ ነው ልቤ ሰው መጠርጠር የሚጀምረው' አለ በልቡ ።

«እግዜር ይባርክህ» አሉ አቶ ጣሴ ድንገት ነፍስ ዘርተው ። እሁን የሚያጠራጥር ምንም ነገር የለም ። ተራ ሌብነት እንዳልሆነ እሁን በጣም ግልፅ ነው ።»

«ግን እንዴት ቀን በቀን?» አለ ሀዲስ ።

«አዩህ ፥ ተንኮለኛ ሰው በማይጠረጥሩበት ጊዜ ነው ዱብ እዳ የሚተ ለው ። ከትናንት የተሻለ አመች ቀን የለም ። ሰው ሁሉ እንዳለ ከቤቱ ገል ብ ተ ብሎ ወጥቶ ወርካውን ለማየት ሄዶ ነበር ። ደርጋ ምን ሞኝ! ምናልባት የገፋፋውም የወርካው መውደቅ ይሆናል ። የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል አሉ። ግን እድሜ ለመንደር ሴቶች፥ በተለይ ያንተ ሠራተኛ። እስዋ ናት እሱ ጭንቅላቱን መታ የጣለችው ። ወንድነት ማለት እኮ ልብ ነው ። ይህ ያንጠ ለጠልነው ነገር አይደለም» በማለት ትክዝ ብለው ሲያስቡ ከቆዩ በሁዋላ ፥ ከሚተናነቃቸው ሳል ጋር እየተናነቁ ፥ «እንዳሰበው ቢሆንለት ኖሮ ምን ይውጠን ነበር? ህዝቡስ ምን ይለን ነበር! ተሰረቀብን ብንል ማን ያምነናል? በልተውት ነው ብሎ ነው የሚፈርድብን» አሉ ።

«ግን» አለ ሀዲስ ብስጭት ብሎ ፥ «ግን ፥ አቶ ደርጋ ለምን እንዲህ ይሆ ናሉ! በእውነቱ አይገባኝም ። በእውነት ሰው እንዲህ ይሆናል ብዬ ማመን ያስቸግረኛል ። ለምን? ለምን?»

« ተንኮል ። ተንኮል!» አሉ አቶ ጣሴ ። «ያለ ተንኮል የሚያስበው ነገር የለም ። ተንኮለኛ እያለ በሰላም ለመኖር አይቻልም ። ወደ ሁዋላ ያስቀረ ንም ተንኮልና ምቀኝነት ነው ።»

ሀዲስ በንዴት ጠጉሩን ቆፈረና ፣ «አሁንስ ይተውናል ብለሁ ነው? እንዲያው ምን ብናደርግ ይሻላል!» አለ ።

«የምናደርገውን እኔ አውቃለሁ ። የመጣሁትም ለዚሁ ነው» አሉትና ይዘው ያመጡትን ትንሽ አረንጉዋዴ የብረት ሳጥን ከነቁልፉ ሰጡት ።

«ምንድን ነው እሱ?» አላቸው ።
«ገንዘቡ ነው ።»

«እንዴ! ምን ነው? ለምን እርስዎ ጋ አይቀመጥም?» አላቸው ተደናግጦ ።

«ፊታውራሪ ዘንድ አትሪው ። እዚያ ይሻላል» በማለት መከሩትና ፣ «ደግሞም እሳቸው ዘንድ መቀመጡ ጥሩ ነው ። እምነት ከጣልክባቸው እሳቸው ይበልጥ ሊያምኑህና በማናቸውም ነገር ሊረዱህ ይችላሉ ። አሁንም ቢሆን ባንተ ላይ ጥሩ እምነት እንዳላቸው ሰምቻለሁ ። በቤታቸው ላይ የደረሰውን መቼም ታውቃለህ ፣ አይደለም?» አሉ አቶ ጣሴ ።

«አዎ ። ያሳዝናል» አለ ፣ የወርካው መውደቅ ፣ ገንዘቡን ለማስረቅ የተደረገው ሰይጣናዊ ሙከራ እና ፣ የአይናለም አሰቃቂ ድርጊት አንድ ላይ ተደራርቦ ባንድ ቀን መድረሱ እየገረመው ።

«ፊታውራሪም በነገሩ አዝነው ጋብቻውን ሰርዘዋል አሉ» ሲሉት— የምስራች እንደ ሰማ ሰው ደስ ብሎት ፣ «እውነት!» አለ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

«ልጅትዋም ደግ አድርጋለች» ካሉ በሁዋላ ፣ እጮኛ ስለ ነበረው ስለ ዳኛቸው እያና አንዳንድ ነገር አንስተው ሲያጫውቱት ቆዩና ፣ «አዎ ። ግን» አሉ አቶ ጣሴ ፣ «ግን ፣ አንድ አጥብቄ የምለምንህ ነገር አለ» አሉት ።

«ምን?»

«ፍቅር አያታልህ ። የትምህርት ቤቱን ነገር አደራ ። ከዚህ የበለጠ የምጥልብህ አደራ የለኝም. . .ቆይ! ቆይ ። አድምጠኝ ። ልብ ብለህ ስማኝ. . . አዎን ። ይህን ትምህርት ቤት ለመስራት ካሰብኩ ዘመን የለኝም ። ፕላኑንም ያሠራሁት እኔ ነኝ ። ደርጋ አይደለም ። በዚህም ፣ በዚያም ብሎ አሳቤን አጨናገፈው ። እያዘንኩ ቀረሁ . . .

«አሁን አንተ መጣህና ልቤን አነሳሳኸው ። ተዳፍና የቆየውን ምኞቴን ቀሰቀስከው ። ባንተ ፣ የቀድሞ ማንነቴን መልሼ አየሁ ። ተስፋዬ እንደ ገና እንሰራራ ። ደስ አለኝ ። ይህ ምኞት ፣ ይህ ተስፋ ከእንግዲህ በተለመደው ትንኮልና ምቀኝነት ተመልሶ አይዳፈንም ፣ አይሞትም ። ባንተ እንደ ገና ያገኘሁትን ተስፋ በልቤ እንደ ጨበጥኩ ወደ መቃብሬ እወርዳለሁ» በማለት የጀመሩትን አሳብ ሳይደመድሙ የሀዲስ ሰራተኛ ቁርስ ይዛ መጣች ። ቁርሱን ልብ ያደረገ የለም ። ሀዲስን ገላመጠችው ። እያልጎመጎመች ወደ ጉዋዳዋ ገባች ።

አቶ ጣሴ ንግግራቸውን ቀጠሉ ፥ «አዎን ፥ አላማዬን ከግቡ አድርስ ልኝ። ይህ ነው አደራዬ ... ቆይ ፥ ቆይ ... አድምጠኝ ሀዲስ ። ምክሬንም ስማ ። አንድ ምሳሌ ላጫውትህ ። አንድ ሊቅ ነበር ይባላል ። ማን ነው ብልህ? ቢሉት፥ 'ከያንዳንዱ ሰው ሊማር የሚችል'፤ ማን ነው ጠንካራ ሰው፤ ቢሉት ፥ 'ስሜቱን የሚቆጣጠር' ፤ ማን ነው ሀብታም? ቢሉት፥ 'በቃኝን የሚያውቅ '፤ ማን ነው የተከበረ ሰው? ቢሉት፥ 'ሰውን የሚያከብር'፤ ብሎ መለሰ ይባላል ። በተፈጥሮ ብልህ ነህና ይህን ምሳሌ ተጠቀምበት ... ቆይ እንጂ! ... ቶሎ ነገር የሚገባው ማን ነው? ቢሉ ፥ እኔ ደግሞ ፥ ብትእግስት ነገር የሚያዳምጥ ሰው ነው እላለሁ ...» እንዳሉ የሀዲስ ሰራተኛ ተመልሳ መጣች ።

ያቀረበችው ቁርስ አልተነካም ። እንዳለ ነበር ። ሳይበርድ ሊልቀረም ። አሁንም ሀዲስን ገላመጠችውና እንደ ልማድዋ እያልጎመጎመች ተመልሳ ወጣች ።

አቶ ጣሴ ምክራቸውን ካቆሙበት ቀጠሉ ። «አንድ ነገር ልንገርህ፥ ሀዲስ ። ቅንና ግልፅ መሆን ጥሩ ነው ። ግን ሰው እያዩና እየገመቱ መሆን አለበት ። ሰው ሁሉ እንዳንተ ቅን አይደለም ። አጉል ግልፅ መሆን አንድም የዋህነት ፥ አልያም ብልግና ነው ። ግን የየዋህ አምላክ አለ ። ማንንም አይነ ካህም ። በርታ ። እግዜር ካንተ ጋር ይሁን ። የዚያን ሊቅ ምሳሌ ተጠቀም በት ። እኔም እድሜዬን ሙሉ የሱን ምሳሌ ለማስተማር ስሞክር ነው የኖር ኩት ። ገንዘቡንም ወስደህ ለፊታውራሪ በአደራ አስረክባቸው ... የለም ... የለም ሀዲስ ። ጥያቄ አልፈልግም ... ልጄ በሞቴ ተወኝ ። አደራዬን አት ርሳ ። በል ደህና ሁን» ብለው ፥ በጥያቄ እንዳያስቸግራቸው ተጣድፈው ወጥተው ሄዱ ።

አይናቸው ላይ እንባ ይታይ ነበር ። ሲመጡ ጎብጠው ነበር ። ሲሄዱ ግን አንድ ፥ የሆነ አዲስ ሃይል ፥ ያገኙ ነበር የሚመስሉት ። ሀዲስ የተጠራ ጠረው ነገር ቢኖርም ፥ አላማቸው ግልፅ አልሆነለትም ። እና ፥ ተጨንቀ ። ለጭንቅ የጣፈው ሰው!

ቀኑ እሁድ ነበር ። የሰንበቴ ጉዳ ገበያ ቆምአል ። ከገበያው መካከል ለሰው መስቀያ ተብሎ የተሰራው እንጨት ከገበያተኞቹ በላይ ከፍ ብሎ ይታያል ። ገበያው እንደ ክረምት ጅረት እየሞላና እየሰፋ ይሄድ ነበር ። ግን ገበያተኞቹ ከንግዱ ይልቅ በሰው መስቀያ እንጨቱ ላይ ያተኩሩ ስለ ነበር ለኪስ አውላቂዎች ሁኔታው በማመቸቱ አልፎ አልፎ ግርግርና ሽብር ይፈ ጠር ነበር ... የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል እንዲሉ ።

— ያዘው! ያዘው! ያዘው!

የተያዘው ተይዞ ፥ ያመለጠውም ካመለጠ በሁዋላ ገበያተኞቹ የሰው መስቀያውን እንጨት ወደ ማየቱ ይመለሳሉ ። ከፊታቸው ላይ ትእግስት የሚሉት ነገር ፈፅሞ አይታይም ነበር ። ሁሉም የስእቱን መድረስ በናፍ ቆት የሚጠብቁ ይመስላሉ ። ሀዲስ ፥ ሰው ሲሰቀል አይቶ ስለማያውቅ ፥ ከመስቀያው ላይ ነፍስ የሚያወዛውዛትን ሸምቀቆ ቀና ብሎ ባየ ቁጥር ሰው ነቱን በጣም ይዘገንነው ነበር ። ግን አይኖቹ አያርፉም ፤ እምቢ እያሉት ወደ ሸምቀቆው ይሮጡበታል ።

—ሞት ለምን አይን ይስባል? አስቀያሚ ነው ። መልክ ጥፉ ነው ። ያስጠላል ። የሰው መጨረሻው አቤት ማስጠላቱ! አቤት ማስቀየሙ! ደግሞ ሲያሳዝን ። አቤት እንዴት ያሳዝናል! የሞተን ሰው ሲመለከቱት በህይወት ኖር የሚያውቅ አይመስልም ። ህይወት የለሽ ነገር ሁሉ ጅል መስሎ ነው የሚታየው ።"አቤት ፣ ሞት ጅል ሲያስመስል ፣ እያለ ሲያስብ ፣ የፊታውራሪ ተካ ገረድ 'የፊታውራሪን ምሳ' በተለጎመ ትልቅ አገልግል አዝላ ገበያውን ሰንጥቃ እያለፈች ስትሄድ ከሩቅ ተመለከታት ። እንዴ እንኩዋን ቆም ብላ ከመስቀያው ላይ የተንጠለጠለውን ሽምቀቆ አልተመለከተችም ። መንገድ መንገድዋን ብቻ ነበር የምታየው ። ሰው ሁሉ የፊታውራሪን ምሳ በአይኑ ይከተል ነበር ።

እኩለ ቀን ሲሆን ተቃርቦአል ። ፀሀይዋ ከጠራው ሰማይ እምብርት ላይ ተንጠልጥላ እንደ ወስፌ እናት በቀጥታ የሚወጉትን ጨረሮችዋን ታዘንባለች ። ወርካው ከወደቀበት ሌሊት ጀምሮ የበልግ ዝናብ ጠብ ብሎ አያውቅም ። ጉሙ ፊቱን አጥቁሮ ይመጣና ሱጴ ላይ ሲደርስ ስቆ ያልፋል ! የወበቅ ፣ የአቡዋራና የላብ ርግማን ወደ ሁዋላው ትቶ ። ሳሩ ሁሉ ደርቆ ወደ አቡዋራ መለወጥ ከጀመረ ቆይቶአል ። የትም ቢሄዱ አቡዋራ— አቡዋራ ብቻ! ሱጴ ላይ አንድ ቀን ሳይዘንብ ከዋለ ፣ መሬቱ ወዲያውኑ ክው ብሎ አቡዋራ ይሆናል ።

የፊታውራሪ ገረድ አገልግሉን እንዳዘለች ገበያውን አልፋ ዳገቱን መያያዝ ስትጀምር ተመለከታትና ፣ ፊታውራሪ እንዳሰቡት ቢሆን ኖሮ እኮ ዛሬ የአይናለም ሰርግ ይሆን ነበር አለ — ሀዲስ በልቡ ።

የተንጠለጠለች ፀሀይ!

«ብቻህን ቆመህ ምንድን ነው የምትፈላሰፈው?»— ታፈሰ ነበር ።
«ምንም» ብሎት ሰላምታ ሰጠው ።
«መስቀያውን እያየህ የምትፈላሰፍ መሰሎኝ ነበር» አለው ።

«ስለ ሞት መፈላሰፍ ምን ያስፈልጋል? አስቀያሚ ነው» በማለት ትኩር ብሎ እያየው በፈገግታ መልስ ሰጠው ።

ሀዲስ ታፈሰን እንደ ገና በማየቱ ተገረመ ። ሁለተኛ የሚያናግረው አልመሰለውም ነበር ።

ታፈሰ ተኩሉ ያማረ ቅጠልያ ካኪ ሱሪና አንገቱ ክፍት የሆነ እጀጉርድ ሸሚዝ ለብሶ ነበር ። ጣቶቹ በትላልቅ ጥምዝ የወርቅ ቀለበቶች ነደዋል ። ትንሽ የወርቅ መስቀል ከደረቱ ጠጉር መሃል ተጋድሞ ይታያል ።

«ሞት አስቀያሚ ነው ካልክ' እዚህ ቆመህ' ምን' ትጠብቃለህ ታዲያ?»

«ወሬ ።»

«አዎን፣ ወሬ። ታውቃለህ ፣ አንዱ ሲሞት ስናይ እኛም አንድ ቀን የምንሞት አይመስለንም ። ሁልጊዜ የሚሞተው ሌላው ሰው ነው ፣ እኛ አይደለንም ። ሰው ፣ በእውነት ፣ ራሱን እያታለለ የሚኖር ሞኝ ፍጡር ነው ። ጅሎች ነን» አለ ፣ ታፈሰ ሽምቀቆውን በርቀት እየተመለከተ ።

«ይህን አባባል ከዚህ ቀደም ሰምቻለሁ ፤ ወይም አንድ ቦታ አንብቤ ዋለሁ» አለ ሀዲስ ።

«ግን ፥ እውነት ነው ። ሰው ጅል ነው! ደግሞ ልንገርህ ። ሌላው ሰው ነው እንጂ እኔ አልሞትም የሚለው አስተሳሰብ ነው የሰው የከፋት ትልቁ ምንጭ ። የሰው ክፋት ክርፋት ሰማይ ድረስ ይቀረናል ። በዚህ አለም ማንም ለማንም ደንታ የለውም ፤ ምክንያቱም ሙዋች ሁልጊዜ ሌላው ሰው ነውና ።»

«ምናልባት ይሆን ይሆናል ። አላውቅም ። ግን የሰው መጨረሻው ሞት ነው ብዬ ማመን ያዳግተኛል ።»

«ታዲያ ምን ይሆናል?»
«ከሞት በላይ የሚያውለን አንድ ነገር መኖር አለበት ...»
«እንደ ምን ያለ?»
«በዚህ አለም ትተነው የምናልፈው ስራ ። አንድ ነገር ።»
«ጅል አትሁን ።»
«እሆን ይሆናል ።»
«ለመሆን ዛሬ የሚሰቀለው ሰው ማን እንደ ሆነ ታውቃለህ?»
«አላውቅም ።»

«ዋቆ ነው ። ቀኛዝማችን የገደለው ወንበዴ» ብሎት ሲጃራ አውጥቶ አቀጣጠለ ።

«ወንበዴ ነበር? እህ» አለ ሀዲስ በለሆሳስ ።
«ታዲያ ምን ነበር?» አለው ታፈስ ቆጣ ብሎ ።

ሀዲስ የነገሩን አቅጣጫ ለወጠና ፥ «እንዲያው ለመሆን ከመቼው ለዚህ አበቁት?» በማለት ጠየቀው ።

«ህዝቡ ከቅጣት ቶሎ ብሎ መማር አለበት ። የስራው ስራ ቀልድ አይደለም ...»

«ግን ህዝቡ ከእሱ ህይወት ይበልጥ የተማረ እንደ ሆነስ? ሁዋላ ምን ይከናል? የስማእታት ምሳሌ እየቆየ ነው የሰደድ እሳት የሚሆነው» ብሎት ፥ ተከዞ ለዋቆ የተዘጋጀውን ሽምቀቆ በርቀት እየተመለከተ ሲያስብ ቆየና ፥ «'ጨቋኞች ገዢዎች ሲሞቱ አገዛዛቸውም አብሮአቸው ያከትማል፤ የሰማእታት አገዛዝ ግን የሚጀምረው ካለፉ በሁዋላ ነው' ሲባል ሰምተህ አታውቅም?» አለው ።

«ጅል አትሁን ። የእሳት ራት ሁሉ ሰማእት አይሆንም!»
«ምናስቆጣህ?»
«ትዘላብዳለህ!» ብሎት ሲጃራውን ወረወረ ።

የሲጃራዋ ቁራጭ መሬት ከመንካቷዋ ሁለት ሰዎች ተረባረቡባት ። የቀደመው ይዞአት ሄደ ። የተቀደመው ፈጦ ቀረ ። ታፈስ ሲጃራ አውጥቶ ሰጠው ። ሀዲስ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አደረገና ፥ «አሁን እንዴት ናት?» ብሎ ጠየቀው ።

«ማን?»
«አደናለም ።»

«ከእስዋ ርቀህ ብትኖር ይሻልሃል ብዬሃለሁ!»
«ስለ ጨዋነትዋ መጠየቅ ነውር ነው?»
«አያገባህም!»

ወበቁ በጣም አይሎአል ። ገበያው ደርቶአል ። የሰው አይነት እንደ ጉንዳን ይተራመሳል ። አቤት! የሻሹ አይነት ። አቤት! የሸንጥላው ብዛትና አይነት ። አቡዋራውም እንደ ፋብሪካ ጢስ ቀጥ ብሎ ወደ ሰማይ ይትናል ። የመስቀያው እንጨት ከገበያተኛው በላይ ነግሶ ይታያል ። ፊታውራሪ በበቅሎ ሆነው ከነአጀባቸው ገበያውን ለሁለት ሰንጥቀው እጅ እያስነሱ አለፉ ። ገበያ በቆመ ቀን እንደ ፀሀይ ብቅ ይላሉ — እጅ ለማስነሳት !

«ሸታዬ እንዴት ነች?» ብሎ ታፈሰ ሀዲስን ጠየቀው ።ምፀታዊ ጥያቄ መሆኑን ሀዲስ አላጣውም ። ቢሆንም ፣ «አይቻት አላውቅም» በማለት መለሰለት ።

«ተቀይመሃት ነው?»
«በምን ምክንያት እቀየማታለሁ?»
«ከኔ ጋር ስላደረች ። ግን ትወድሃለች» አለው ።
«ሀም!»
«ደግሞ ፣ ባል ትፈልጋለች ።»
«ታዲያ አንተ ለምን አታገባትም?»
«እስዋ አንተን ነው የምትፈልገው ።»
«እኔን ለምን? ይልቅ አንተ አትሻላትም?»
«እኔ በቀላሉ ልጠመድ አልችልማ ።»
«እኔስ?»
«አንተ ገራገር አውሌ ነህ ። ሴቶች የሚያዋጣቸውን ነገር ያውቃሉ» አለው ።

ሀዲስ በታፈሰ ነገር አልተናደደም ። ሳቀና ፣ «ገራገር እመስላለሁ? አታውቀኝም ። ለማንኛውም ነገር አመሰግናለሁ» አለው ።

«ለምኑ?»
«ለምክርህ!»
«ሸጉጤ የት አለ?» አለው ።
«ለምን አሁን ፈለከው? ልትገድለኝ ነው?»
«እፈልገዋለሁ ።»
«ጠፍቶብኛል ። እዚያው ሜካ ውስጥ ነው የጣሉብኝ ።»
«አትቀልድ!» አለው ።
«እውነቴን ነው ። ቀልዴን አይደለም» አለው ሀዲስ ፣
ዋሸቶ — «ሌላ ገዝቼ እሰጥሃለሁ ። አዝናለሁ ።»

ገበያው እንዴ ተተራመሰ ። አቡዋራው ተነሳ ።

—ያዘው! ያዘው!

ግርግሩ ትንሽ ቆይቶ ፀጥ አለ ። ፊታውራሪ እንደ ገና ገበያውን ሁለት ላይ ሰንጥቀው አለፉ ። ያያቸው ሁሉ እጅ ይነሳል ። እሳቸው በቅሎአቸው ላይ ሆነው አፀፋውን ግራና ቀኝ ይመልሳሉ . . .

«ስማ ሀዲስ» አለ ታፈሰ ፣ «አንድ ምክር ልስጥህ ።»
«ካንተ መቼም ደግ ምክር አይጠፋም ። ምንድን ነው?» አለው ።
«ለምን አትሄድም?»
«ወዴት?»
«ወደ ትምህርት ቤትህ ። ወደ ዩኒቨርሲቲህ ተመለስ ።»
«ለምን ቢባል? እስቲ ንገረኝ?»
«ለራስህ ስትል ...»
«እንዴት ማለት?»

«ስማ ሀዲስ» አለ ታፈሰ ፊት ለፊት እያየው ፣ «ህይወትህ አደጋ ላይ ነው ። እመነኝ ። ጠላቶችህ አደገኛ ሰዎች ናቸው ...»

«ሌላስ?»

«ገንዘብ ፍለጋ አይደለም የመጣኸው? አንድ ነገር ልንገርህ ። የሚበቃህን ገንዘብ እኛ እንስጥህና ሂድ ...»

«እናንተ እነማን ናችሁ?»
ታፈሰ ደንገጥ ብሎ ፣ «ለምሳሌ ፈታውራሪ ... እኔ» አለው ።

«ስላሰባችሁልኝ አመሰግናለሁ ። በእውነት ከልቤ ነው የማመሰግነው ። ግን ገንዘባችሁን ለራሳችሁ አድርጉት ።

«እኔ ሌላ አላማ አለኝ ። ይህን የጀመርኩትን ስራ ከፍፃሜ አድርሼ ሳላይ የትም አልሄድም ። እዚሁ እሞታለሁ ። ጠላቶችህ ናቸው የምትላቸውን ሰዎች ይህን ቁርጥ አሳቤን ንገራቸው» አለው ፍርጥም ብሎ ። ጠጉሩን ቆፈር ፣ ቆፈር አደረገ ።

«ሞኝ አትሁን ። ይልቅ ምክሬን ብትሰማ ይሻልሃል» [አለ ታፈሰ በመበሳጨት ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

«ምክሩን ለራስህ አርገው! እና ፣ አሁን ተወኝ» አለ ሀዲስ ።

«ሞኝ አትሁን ነው የምልህ!» አለ ታፈሰ፣ «ቀልድ መስሎህ ይሆናል ። አይንህን ከፍተህ የቀን ህልም አታልም ። ትምህርት ቤት ፣ ምናምንቴ እሰ ራለሁ ብለህ ያስነሳኸው አቧዋራ በሁዋላ ተመልሶ አንተኑ ያስለቅስሃል— ያውም ለማልቀስ ጊዜ ብታገኝ ። ህይወትህን በደህና ይዘህ ጀንበር ሳለች ብትሮጥ ይሻላል ። ገንዘቡም ቢሆን ይጠቅምሃል ። ባዶ እጁን ለመጣ ሰው፣ ያለ ምንም ድካም ገንዘብ ማግኘት ቀላል አይደለም ። ጥሩ እድል ነው ። እያ ምልጥህ ።»

ሀዲስ ታፈሰን በጥላቻ አይን እየተመለከተው ፣ «ይህን ልትነግረኝ ነው የመጣኸው! ምን ቢመጣ ምን ፣ የትም አልሄድም ብያለሁ ። ወይ ጉድ ጉድ ፣ ወይ ፍንክች! የምለው ነገር ይገባሃል?» ካለው በሁዋላ ፣ «ጠላቶቼ እነማን እንደሆኑ አውቃለሁ ። ከዚህ እንድሄድላቸው የሚፈልጉበትም ምክ ንያት ይገባኛል ። አይዞህ ። እነሱ የተዘጋጁልኝን ያህል እኔም ተዘጋጅቼ ላቸዋለሁ» አለው ።

«ሒውነት!»

«ይሞክሩኝ ። አንድ ህይወት ናት ያለችኝ ። እስዋንም ለዚህ ትምህርት ቤት በደስታ እሰጣለሁ ።»

«ታስቃለህ» አለ ታፈሰ ፣ «በእውነት ታስቃለህ ።»

ቀፎው እንደ ተነካበት የንብ መንጋ ገበያው ድንገት መተራመስ ጀመረ ። ፖሊሶች ዋቆን ወደ መሰቀያው ቦታ በማምጣት ላይ ነበሩ ። ሀዲስ ዋቆን ለማየት አንገቱን እስኪያመው ድረስ ወደ ላይ ቢንጠራራም አልሆነለትም ። ታፈሰም ወደ ላይ ይንጠራራ ነበር ።

ሰማይ ድረስ የተነሳው አቡዋራ ጋረዳቸው ። ታፈስ የአቡዋራውን መጋረጃ ተራገመ ። ሃይለኛ ነፋስ ከምስራቅ ወደ ምእራብ ድንገት ይነፍስ ጀመር ። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ የአቡዋራው መጋረጃ ተገለጠ ። ዋቆ ከገበያተኞቹ በላይ ከፍ ብሎ ቆሞ ይታይ ነበር ። ከህይወት በላይ ግዙፍ የሆነ መስሎ ነበር የሚታየው ። ሞትን ድንክ ሊያደርገው ቆርጦ የቆመ ነበር የሚመስለው ። ሸምቀቆው ከራሱ ላይ ያንዣብባል—እፉኝ ከፍቶ ። ከሩቅ ከሚታየው አድማስ ላይ አይኑን አሳርፎ የቆመ ይመስላል—አንድ አይኑን ። አለምን ለመጨረሻ ጊዜ የሚሰናበት ይመስል ነበር—ይህችን ውብ አለም ። ገበያው ፀጥ ያለ የሰው ባህር ሆኖአል ።

ዋቆ በገዛ ራሱ አንገቱን ሸምቀቆው ውስጥ አስገባ ። አንድ ፖሊስ ዋቆ ከቆመበት የሆነ ነገር ላይ ወጥቶ ሸምቀቆውን አንገቱ ላይ አስተ ካከለለትና ተመልሶ ወረደ ። አንድ ቃል አልተናገረም ። አልተራገመም ። አልተርበደበደም ። ፖሊሱ ከመውረዱ ዋቆ በገዛ ራሱ ከቆመበተ የሆነ ነገር ላይ ራሱን ወረወረ ። አልተፈራገጠም ፣ ፀጥ አለ ።

እልልታው ባንድ ፊት ፣ ዋይታው በሌላ በኩል ይቀልጥ ነበር ። ብዙ ሰዎች አፈር እየበተኑ ይምሁ ነበር ። አቡዋራ እንደ ገና ተነሳ ። የአቡዋራ መጋረጃ ዋቆን ጋረደው ። እንባው ጠብ አለ — ሀዲስ ።

— ያዘው! ያዘው! ያዘው!

«ምንም የሚያስለቅስ ነገር የለም» አለ ታፈሰ ።

ሀዲስ እንባውን ጠረገና ፣ «ሁልጊዜ እንደምለው ፣ የሰማእታት አገዛዝ የሚጀመረው ከሞቱ በሁዋላ ነው ። ዋቆ አልሞተም ። እሳቡ በጭሰኞችህ ልብ ዘላለም ይኖራል» አለው ።

«ላህልም ዳገት የለውም ። አይንህን ከፍተህ ቀን በቀን ህልም ብታይ ፣ ነገሩ ዞር ዞር ያው ህልም ሆኖ ነው የሚቀረው» ብሎ ፣ ምፀታዊ ፈገግታ አሳየውና ፣ «በነገራችን ላይ ፣ አቶ ጣሴም ነገሩን ስራዬ ብለው መከታተል እንዲተዉ ንገራቸው።እሳቸውም እንዳንተው የዋህ እየሆኑ ሄደዋል» አለው።

«የቱን ነገር?» በማለት እያወቀ ጠየቀው ።

«የሴጎውን ጉዳይ ።»

«ለምን ብለው ይተዋሉ? ሲያመልጥ ሲሞክር ተገደለ ተብሎ የተነዛ ው ወሬ በጣም አጠራጣሪ ነው ። ከነገሩ በስተጀርባ አንድ የሆነ ተንኮል መኖር አለበት» ሲል ፡—

ታፈሰ ጥፍ በማለት ነገሩን ለማቅለል ሞከረና ፣ «ይህን ነው የምልህ ። ምንም ማስረጃ ሳይኖር ሰው መጠርጠር አደገኛ ነው ። በገዛ እጃችሁ ጣላት እየገዛችሁ ነው ። አቶ ጣሴን ተዋቸው ። አንተ ግን እር ፊህ መቀመጥ ወይም መሄድ—ያለህ ምርጫ ይህ ነው ። ይህን ሁሉ የምነግርህ በጉዋደኝነት ነው» አለው ።

«አንተን የመሰለ ጉዋደኛ የያዘ ምን ጠላት ያስፈልገዋል» በማለት በነገር ወጋው ።

«ምን ማለትህ ነው!»
«ምንም ።»

ታፈሰ በንዴት አይኑ በርበሬ መሰለ ። ትንፋሽ ያጠረው ይመስላል ። አፍንጫውን ነፋ ። አቡዋራው ሰክኖ ነበር ። የዋቆ ሬሳ በነፋስ ሃይል ይሸከረከራል ። ሀዲስ ፣ ሰውነቱን ከፋኛ ዘገነነው ። አይኑን ጨፈነ ።

«ሴላም ምክር ልስጥህ» አለ ታፈሰ ።
«ቀጥል ።»
«ሁለተኛ ፊታውራሪ ቤት ባትደርስ ጥሩ ነው ።»
«ካልክስ አሁን ልሄድ ነው ።»
«ከዚህ መሄድ ለምን እንደማትፈልግ ልንገርህ?» አለ ታፈሰ ቅንድቡን ከፍና ዝቅ እያደረገ ።
«ለምን እንደ ሆነ ነግሬሃለሁ።»

«ለሱ አይደለም ። ይህ ትምህርት ቤት ምናምን የምትለው ነገር ሽፋን ነው. . .»

«ታዲያ ለምን ይመስል ሃል?»

«ምክንያቱን ታውቀዋለህ ። እኔም አውቀዋለሁ ። ለአይናለም ስትል ነው ። አላማ ፣ አደራ ፣ ሕዝብ ፣ ጂኒ ፣ ቁልቁዋል እያልክ ድርቅ ብለህ ስታወናብድ ይገርመኛል! አሁን ጠባይህ ገብቶኛል ። ውስጥ ውስጡን የሚሄድ አባብ ነህ ። ዝግ ችሎት ፣ አለ አይደል? ባቋዋራጭ በሀብት ልትነከር ፣ ኡ? አይንህን ከፍተህ ቀን በቀን ህልም አታልም ብያለሁ ። »

ሀዲስ መልስ ሳይሰጠው ጥሎት ሄደ ።

ገንዘቡን ይዞ በቀጥታ የሄደው ወደ ፊታውራሪ ቤት ነበር ። ቶሎ ሳ ወደ እልፍኝ አላስገባውም ። እየመራ ወደ ጉዋሮ ወሰደው ። ፊታውራሪ እትክልት ውስጥ ቆመው ነበር ። ባሳብ ተመስጠው ተፈጥሮን የሚያደንቁ ይመስላሉ ።

—ሰው በእድሜ እየገፋ ሲሄድ ፣ ሁሉም ነገር ፣ ድንቅና ውብ ስለሚሆንበት ፣ ሩጫ ትቶ ቆም በማለት የተፈጥሮን ተአምር ማድነቅ ይጀምራል ፣

የሚል ነገር የት ይሆን ያነበበው? ሀዲስ ይህን ነገር የት እንዳነበበ ሊያስታውስ አልቻለም ። ሊያስቸግራቸው አልፈለገም ። ዝም ብሎ ቆመ ። ቶሎሳ እንደ መሳል አለ ። የውሸት ሳል ነበር ። ፊታውራሪ ዞር አሉ ። ሀዲስ እጅ ነሳ ።

«እንደ ምን ዋልክ?» አሉት ፣ የጉሞቸን መለዋወጥ እየተመለከቱ ። ልዩ ልዩ ጥላ ይመጣል ፣ ይሄዳል ። ይዳምናል ። ደግሞ ፀሀይ ከደመናው ውስጥ ብቅ ትላለች ። ከዛፎች ላይ ወፎች ያዜማሉ ።

ሀዲስ እንደ ገና እጅ ነስቶ ፣ «ጉዳይ ነበረኝ» አላቸው ።

«ጉዳይህን ተናገር» አሉት ፣ አንድ ንብ አበባ ላይ አርፋ ማር ስትቆስም ባድናቆት እየተመለከቱ ።

«ይህን ገንዘብ እርስዎ ዘንድ ለማኖር ፈልጌ ነበር ። ፈቃድዎ ቢሆን» አላቸው ።

«የምን ገንዘብ?»
«ለትምህርት ቤቱ ህዝብ ያዋጣው ገንዘብ ነው ።»
«ስንት ይሆናል?»
«ሁለት መቶ አስራ ሁለት ሽህ ብር ከሃምሳ ሳንቲም ነው ።»

«ብዙ ገንዘብ ነው» ብለው ፣ ንብዋ የቀሰመችውን አበባ ቀጥፈው እያሸተቱ ፣ «እስካሁን የት አኑረኸው ነበር?» በማለት ጠየቁት ።

ገንዘቡ እስካሁን ማን ዘንድ እንደ ነበረና በአቶ ጣሴ ቤት ላይ በደረሰው አደጋ ምክንያት ምን ስጋት እንዳደረበት አንድ ባንድ ከገለፃላቸው በሁዋላ ፣ «ለማንኛውም ነገር ፣ ከዚህ ሁሉ ስጋት ገንዘቡ እርስዎ ዘንድ ቢሆን ልኝ ይሻላል ብዬ ነው ። ፈቃድዎ ከሆነ» አላቸው ።

«አዎ ፣ የአቶ ጣሴ ቤት በሌባ መሰበሩንና ሌባውም ወህኒ ቤቱን ሰብሮ ሊያመልጥ ሲል የተገደለ መሆኑን ሰምቻለሁ ። ደሞ ሌባው ያቶ ይርጋ አሽከር ነበር ይባላል...»

«አዎ ። ብዙ ዘመን ቤታቸው የኖረ አሽከር ነው ።»
«ነገሩ ተንኮል ያለበት ይመስላል?»
«እኔም ይህንኑ ጠርጥሬ ነው።»

«ማለፊያ» አሉ ፊታውራሪ ፣ «ገንዘቡ እኔ ዘንድ ባደራ ይቀመጣል ። ከደራ የበለጠ ክቡርና ከባድ ነገር የለም ። 'መተማመን ከሌለ አደራ ሰጭም ሆነ አደራ ተቀባይ አይኖርም' ይል ነበር መኩብብ።»

የመኩብብን ስም ሲያነሱ ፣ ቀጥሎ የሚጠየቁትን ጥያቄ ስለሚያውቅ ፣ — መኩብብን እንደምትመስል ነግሬሃለሁ ፣ ይል ነበር ፣ በልቡ ።

«ማለፊያ ነው ። በርታ ። ያንተን ልብ ለታፈሰ ቢሰጥ ጥሩ ነበር» አሉት ። የቀጠፉትን አበባ እያሸተቱ ።

«ገንዘቡ እርስዎ ዘንድ እንዲሆን የፈለኩበት ሌላም ምክንያት አለ» አላቸው ።

«ሌላው ምክንያት ምንድን ነው?» አሉት ።

«የወረዳው ገዢ ገንዘቡን ካዝና ካላስገባህ በማለት ወጥረው ይዘውኛል» አለ ።

«እንደሱ አለ?»
«በየቀኑ እያስቸገሩኝ ነው...»

«እንዲህ የተስገበገበው ለምን መሰለህ? ያው እንደ ልማዱ ሊበላው ነው ። ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል የሚለውን አባባል በሚገባ በስራ የሚተረጉም ሰው ቢኖር ጥላሁን ብቻ ነው ። ግን ሲቀደም ነበር!» አሉ ።

«እንዴት?» አለ ሀዲስ ።

«ሳይሆንለት ቀረ እንጂ ፥ ይርጋ ሊቀድመው ነበር ። ጉድ'ኮ ነው!» አሉ ተገርመው ።

ነገሩ ተከሰተለት ። ምናልባት አቶ ይርጋ ገንዘቡን ቀድመው እጃቸው ውስጥ ለማስገባት የቸኮሉት የአቶ ጥላሁን ፍላጎት ገብቶአቸው ይሆናል ።

ፊታውራሪ ተካ የቀጠሩትን አበባ አሁንም እያሹ ተቱ ፥ «ግድ የለም ፥ አይዞህ ። ገንዘቡን ማንም አይነካውም ። የወረዳው ገዢ አምጣ ብሎ ካስቸገረህ እኔ ጋ መሆኑን ንገረው ። ያኔ እንተያያለን ። አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል አሉ ። ለመሆኑ ምን ምክንያት ሰጠህ?» አሉት ።

«የህዝብ ገንዘብ እንዳይባክን ሃላፊነት አለብኝ ነው የሚሉት...»

«እንዲህም አ'ርጎ የለ! ሕዝቡን ግጦ የበላው ማን ሆነና ነው? ግን ምን ይደረግ? እሱስ ምን ያድርግ? ህዝቡ ላይ ጅቦች የሚለቁት ሌሎች ናቸው ። እሱ ምን አጠፋ? እንደ መሩት እየተመራ ነው ። አሽከር የሚኖረው እንደ ጌታው አይደል?» ካሉ በሁዋላ ትክዝ ብለው ቆሩ ።

እጅ በመንሳት ተሰናብቶ ሊሄድ ሲል ፥ እንዲቆይ አዘዙት ።

የደመናው ጥላ እየገፈፈ ሄደ ። የደመናው ጥላ እየገፈፈ ሲሄድ ተፈጥሮም በልዩ ልዩ ቀለማት እያሸበረቀች ስትፈነጥዝ ትታይ ነበር. ። ፀሀይ ወጣች ። የተነደፈ ጥጥ የሚመስለው ጉም ሰማይ ላይ ልዩ ልዩ ቅርፅ እያበጀ ይጫወታል ። ከፊታውራሪ ቤት ባሻገር ፥ ከአልቁ ወንዝ ማዶ ፥ ከአድማሱ ጋር የተሰፋ መስሎ ከሩቅ ከሚታየው ጥቁር ሰማያዊ ተራራ ላይ ፀሀይዋ ወርቅማ ጨረሮች ታዘንባለች ። ሀዲስ ዝም ብሎ ቆሞ የፊታውራሪን አይን ባይኑ ይከተል ነበር ። አሳዘኑት ። ይህችን የማትጠገብ ውብ አለም ተሰናብተው ከመሄዳቸው በፊት ላንዳአፍታ ቆም ብለው ለመጨረሻ ጊዜ የሚያደንቁዋት መስለው ነበር የሚታዩት ። ቀዝቀዝ ያለ አየር ፥ ጫካውን ፥ ሳር ቅጠሉንና ሳሩን እያጫወተና ለዘብ ባለ ሙዚቃ ስልት እያስደነሰ ይነፍሳል ። ወፎች ሰልፍ ገብተው ወደ ገባ በረሃ ይበራሉ ።

ጠለቅ ባለ ድምፅ ፥ «የደወሉንም ነገር አስብበት» አሉት ።

«ሊሺ» አለ ።
«የተቀላውስት ዘር ነህ ፣ አይደለምን»
«ነኝ።»

ትኩር ብለው በዚያ በሚያስፈራው አይናቸው እያዩት ፣ «ጠባይህ ሸጋ ፣ አሳብህ ጥሩ ፣ አጥንትህም የጨዋ ነው» አሉ ።

ሀዲስ የሚሰጠው መልስ አልነበረውም ። ዝም አለ ።

«ትምርትም አለህ ።»
«ገና አልጨረስኩም» አለ ።
«'ትምርት ማለቂያ የለውም' ይል ነበር መኩብብ . . . »

«አዎ ፣ ቁርጥ እሱን ነው የምትመስለው ። እና ፣ እያወቁ በሄዱ ቁጥር አለማወቅ ይከተላል። 'ሰው በመጨረሻ የሚያውቀው አለማወቁን ነው' ይል ነበር» እያሉ ወደ ቤት ሲያመሩ ፣ ሀዲስም ተከትሎአቸው ሲሄድ፣ «ለመማሩ እንደ ሆነ ትደርስበታለህ ። ምን የሚያስቸኩል ነገር አለ? ብልህ ሰው ትምህርት ቤት ባይገባም ከህይወት ሊማር ይችላል ። ከህይወት የበለጠ ትምህርት ቤት የለም» በማለት ፣ ቤት ገብተው ከድንክ አልጋቸው ላይ አረፍ ካሉ በሁዋላ ፣ «ግን አንድ የማታውቀው ወይም ያልገባህ ነገር አለ ። ያገራችንን ባህል ፣ ወግና ስርአቱን ማወቅ አለብህ ። እስቲ መካሪ ሽማግሌዎች ፈልግ . . . » እንዳሉት ቶሎሳ እየተጣደፈ መጥቶ በጆሮአቸው አንድ ነገር ነገራቸው ።

ፊታውራሪ ደንግጠው ፣ «መቼ!» አሉ ።

መምሬ መሀሪ አራቱንም ማእዘን በመስቀላቸው እየባረኩ ገቡ ።

«ዛሬ ነው አሉ ። ቀን ላይ» አላቸው ቶሎሳ ።
«እንዴት ነው የሞተው?» አሉ ከተቀመጡበት ተነስተው ።

ሀዲስ ማን ይሆን የሞተው በማለት ደነገጠ ።

መምሬ መሀሪም ነገሩን ቀደም ብለው ሰምተውት ስለ ነበረ፣ «ድንገት ልባቸው ቆሞ ነው አሉ የሞቱት» አሉና ምክንያቱን ነገሩዋቸው ።

ሀዲስ ነገሩ ግልፅ ስላልሆነለት የባሰውኑ ተጨነቀ ።

ፊታውራሪ ፣ «አያና ሞተ! ወይ ጉዋዴ!» በማለት ፣ ካባቸውን ከላያቸው ላይ ጥለው ራሳቸውን በመያዝ ፣ «የታሪክ ጉዋዴ ! ወንድሜ ! እኔ እኮ ጠላትንነትክን አልጠላም ነበር ። ወይ የታሪክ ጉዋዴ! እንግዲህ ማን ቀረ? ብቻዬን ቀረሁ!» እያሉ ይጮሁ ጀመር ።

ዋይታው ባንዳፍታ ቀለጠ ። ስራ ቤቱ ሁሉ ተሰብስቦ ይላቀስ ጀመር ። ምን እንደ ተፈጠረ፣ ማን እንደ ሞተ አያውቁም ። ግን እንባ እየተራጩ ያለቅሳሉ ። እቶ ጣቤ ደጉ ጡዋት ፣ ስለ ፊታውራሪ አያና ልጅ ስለ ዳኛቸው በአእምሮው ላይ የቀረፀበት ምስል ቁልጭ ብሎ ታየው — ሀዲስ ።

ዳኛቸው አያና ቀኑን ሙሉ በየመሸታ ቤቱ እየዞረ ሲሰክር ይውላል ። ማታ የብርሴ ጉዋደኞቹ የወሳንሳ ተሸክመውት ወስደው ካባቱ በር ላይ ይጥሉታል ። ያፈረደባቸው ምስኪን ያባቱ አሽከሮች አንስተው ያስተኙታል ።

ሎሊት ተነስቶ አባቱን ከተኙበት እየጎተተ ወስዶ ሳጥናቸውን በግድ ያስ ከፍታቸውና ብር አስቆጥሮ ይወስዳል—«ብር እምላኩ!» ብሎ እየሰደባ ቸው ። ዘወትር እንዲሁ ነበር ።

ለሰው አይነግሩት የከብር ፣ ከሰሰው አያሳስሩት ወይም ተኩሰው አይ ገድሉት የስጋ ነገር—የገዛ ስጋቸው ፣ አፈር ያነሳ ስጋ—ሆኖባቸው እንዲሁ ጡኖት ማታ . . . እህህ የልጅ ጠላት አይስጣችሁ . . . ከልጅ ጠላት ሰውረን ማለት ነው . . . እህህ . . . በማለት አንጀታቸው እያረረ ይኖሩ ነበር ።

እንደ ልማዳቸው ድስት ጠራርጋ የምታጎርሳቸው ገረዳቸው—ድስቱን ወስዳ ከመቃብራቸው ላይ ስትጥለውና ፣ ድስቱ ፍርክስክሱ ወጥቶ ገሎቹ ከመቃብራቸው ላይ ሲበተኑ በአይን ህሊናው ታየው ።

ገል ።
የገል ስብርባሪ ።
ህይወት ።

ሀዲስ በግርግሩ መሃል ሹልክ ብሎ ወጣ ። ሲሄድ ሁሉ ፣ ‘መካሪ ሽማ ግሌ ፈልግ’ ሲሉ ምን ለማለት ፈልገው ነው? እያለ ባሳቡ ነገሩን ያወጣና ያወርድ ነበር . . . እሳቸው የሚናገሩት ነገር እንቆቅልሽ ። እስዋ የምትፅፈው ነገር እንቆቅልሽ ። ያቶ ይርጋ ነገር እንቆቅልሽ ። ያቶ ጣሴም አሳብ እንቆ ቅልሽ ። ሁሉም ነገር እንቆቅልሽ ። ህይወት ራስዋ እንቆቅልሽ ።

ከትናንት ጀምሮ በመከታተል የደረሰበት ነገር ሁሉ ከልቦለድ ታሪክ እየላቀበት እየሳቀና እያዘነ እንደ እርኩም አጎንብሶ ሲሄድ ፣ አንዲት ሴት ካንድ ዛፍ ጥላ ስር ብቅ አለችበት ። ከዚህ ቀደም አይቶአት ያውቃል ። የት እንዳያት ግን ጠፋው ። ቀና ብላ በሙሉ አይንዋ ሰው አታይም ። የደስ ደስ ያላት ፣ ጎራዳ ናት ። በእጅዋ ይዛ የነበረውን ቁራጭ ወረቀት ሰጠችው ።

«ከማን ነው?» አላት ።
«አፉን ሲዳማ እምቤኩ» አለች በኦሮምኛ ።

በችኮላ ወረቀቱን አነበበ ።

የመልእክቱ ፍሬ ነገር እንዲህ የሚል ነበር—«የስጠኝ ምክር አን ዱም ከመሬት አልወደቀም ። የላክህልኝን ደብዳቤ አሁንም ደጋግሜ እያነ በብኩት ነው ። ለድግሱ የታሰበው ዳስ ፈርሶአል ። ሰርጉም ተሰርዞአል ። ለድግሱ ታስቦ የነበረውም ወጭ ለትምህርት ቤቱ ማሰሪያ እንዲውል ተደ ርጎአል ። ብሎኛል ። ተአምር ነው የሆነው ።

«አሁንም የጨነቀኝ ነገር አለ ። አባቴ ከፊቱ እንድለይበት ወይም ርቄው እንድሄድ አይፈልግም ። ጭንቄን ለማን ላዋይ? የሚሰማኝ የለም ። አሁንም ካንተ ብልሃትና ዘዴ አይጠፋምና ይህ መልክት እንደ ደረሰህ—ያለ ህን ምክር በደብዳቤህ ግለፅልኝ ።»

እጅና እግር የሌለው ሌላ እንቆቅልሽ! የቱ ደብዳቤ? አለ ። አንድ አሳብ መጣለት ።

«ስሚ የኔ እህት !»
«ለኪ ፣ አፉን ሲዳማ እምቤኩ ።»

ኦርምኛ እየቆጠረ ፣ «ኢሳ . . . ላማ . . . ጌፍቲኬ ቢራ ዱቢኢቲ ። ኦፋ! ተይው!! ገድ የለም» ብሎ ፣ ኦርምኛ መናገር አለብኝ እያለ ፣ የፈለገውን መልእክት ወረቀት ላይ ፃፍ ፃፍ አድርጎ ሰጣትና ፣ «መልሲሳ አማ ናፈዲ ። ምን ነበር? . . . አሱማት ቢኢጋ ። ዱፌ» አላት ።

ሴትዮዋ ወረቀቱን ይዛ ሮጠች ። ተአምር እያልትም እያለ ዛፍ ጥላ ስር ቆሞ ይጠብቃት ጀመር ። ልቡ ክፉኛ ተሰቅሎበት ። ደቂቃዎች እንደ ሰአት ረዘሙበት ። መንገድ መንገዱን ሲያይ ሴትዮዋ ብቅ አለች ። እዚያው ቆሞ አልጠበቃትም ። ወደ እሱዋ ሮጦ ሄደ ። ከአይናለም ዘንድ ይዛ የመጣችውን ደብዳቤ ሰጠችው ።

«ኢሺ» ብሎ ካሰናበታት በሁዋላ ፣ አንድ ዛፍ ተጠግቶ ደብዳቤውን በናፍቆት ገለጥ አደረገ . . . .

«ውዴ አይናለም . . . »

«አንዴ ተለያየን እንቀርም ። ያላንቺ አለሚ ባዶ ትሆንብኛለች ። አንቺ የሌለሽበት ህይወት ሊጥመኝ አይችልም ።ስሚኝ ውዴ—ስርግሽ ሲቀር የሚ ችልበትን መንገድ ሳስብበት ነበር ። ያንቺም ምኞት ከዚህ የተለየ አይመ ስለኝም ።

«እንዲህ አድርጊ ። ሰርግሽ ሊደርስ ሁለት ወይም ሶስቱ ቀን ሲቀረው ታንቄ እሞታለሁ ብለሽ ተነሺ ። ነገሩ እንደሚመስል ሆኖ በጥንቃቄ መደ ረግ አለበት ። ዘዴውን ላንቺ እተዋለሁ ። እስከዚያ የንቁብሽ እንደ ሆነ ሁዋላ ነገሩ እጉል ይሆናል ። እንደሚመስል አድርገሽ በጥንቃቄ ነገሩን የፈፀምሽ እንደ ሆነ ግን ፣ ፊታውራሪ ጨክነው አይድሩሽም ። ምናልባ በዩኝ ። ሰርጉ ከቀረ ስለ ወደ ፊት ኑሮአችን ሌላ ብልሃት እፈልጋለሁ ። ይህን ደብዳቤ ካነበብሽው በሁዋላ አቃጥዩው ።

አፍቃሪሽ
ሀዲስ ሳህሌ»

ደብዳቤውን እንደ ገና አነበበ ። ተአምር እያልትም አለ ። እንደ ታመ ከረች! ደብዳቤውን አቃጥላ ባለ መጣልዋ ደስ አለው ። የእጅ ፅሁፉ በጣም ደስ ይላል ። ግን የእሱ የእጅ ፅሁፍ አይደለም ። ማን ይሆን እንዲህ ያለ ደብዳቤ በኔ ስም የፃፈላት! አለ ። እሱ መሆን አለበት ብሎ ወደ ታፈሰ ቤት ሮጠ ።

ታፈሰ ብሩ ቤት አልነበረም ። ባቡን እየጠረገ አንዱን አሽከር ፣ «የት ነው የሄደው?» ሲል ጠየቀው ።

«ከሰዎች ጋር ነው የወጡት ።»
«ወዴት ይሆን የሄደው?»
«ወደ ደናቸው ሳይሆን አይቀርም ።»
«ቆይቶአል ከወጣ?»
«አዎን ፣ ቆይተዋል ።»

ሀዲስ ሰአቱን ተመለከተ ። ጀንበርዋ ልትጠልቅ አሽቆልቁላለች ። ዝም ብሎ ወደ ቤት ገባ ። አሽከርየው ደስ አላለውም ። «እዚሁ እጠብቀዋለሁ» ብሎት ቁጭ አለ ።

እንግዳ ቤቱ ትንሽ የቤተ መንግስት አዳራሽ ይመስላል ። ክፍሉ ውስጥ የሚታዩት ውድ የቤት እቃዎችና ትላልቅ 'የክሪስታል' ብርጭቆ ዎች አይን ይስባሉ ። አሽከርየው ቅር እያለው ትቶት ወጣ ። ሀዲስ የሚ ጠብቀው እድል ነበር ። ጊዜ አላጠፋም ። ተነስቶ መሳቢያዎችን እየከፈተ የሆነ ነገር ይፈልግ ጀመር ። ካንዱ መሳቢያ ወደ ሌላ እንደ እብድ እየሮጠ ቢከፍታቸውም የተፈለገውን ነገር አላገኘም ። እያላበው ቆሞ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር ሲያደርግ የታፈሰ ፅህፈት ቤት ትዝ አለው ። ሮጦ ሄዶ በሩን ሞከረው ። አልተቆለፈም ነበር ። በሩን ከፍቶ ወደ ውስጥ ገባ ። በግራ በኩል ያሉትን የጠረጴዛውን መሳቢያዎች አንድ በአንድ ሞከረ ። ሶስቱም ተቆልፈው ነበር ። ዞር በቀኝ በኩል ያሉትን መሳቢያዎች ይሞክር ጀመር ። የመጀመርያ መሳቢያ ክፍት ቢሆንም ምንም አልነበረበትም ። ሁለተኛው መሳቢያ ለአይነት ተቁጥጥረው በተቀመጡ የቡና ዘሮች ተሞልቶ ነበር ። ሶስተኛውን መሳቢያ ሳብ ሲያደርግ ወፍራም ፋይል አገኘ ። ቶሎ ቶሎ ፋይሉን እያገላበጠ የሚፈልገውን ነገር ሲፈልግ — ያውና! ብሎ አንድ ወረቀት ከፋይሉ ውስጥ ገንጥሎ አወጣና ፣ ትንፋሹን ይዞ ፣ የታፈሰን እጅ ፅሁፍ ፣ አይናለም ከላከችለት ደብዳቤ ላይ ካለው የእጅ ፅሁፍ ጋር ያስተ ያይ ጀመር ። ወዲያውኑ ድምፅ ሰማ ። ፋይሉን በችኮላ ከቦታው መልሶ ፣ ሮጦ ሄዶ ገና ቁጭ ከማለቱ ከታፈሰ ጋር አይን ለአይን ተጋጩ ።

«ቤቱ ውስጥ ትርጥ ነበር እንዴ?» አለው ታፈሰ ባርኔጣውን እያስ ቀመጠ ። ከላይ እስከ ታች 'ብሉ ጂንስ' ለብሶ ተረከዙ ረጂም የሆነ ጥቁር ቦት ጫማ አድርጎአል ።

«ከዚህ አልተንቀሳቀስኩም ። ከመጣሁ ጀምሮ እዚሁ ነበርኩ ። ምን ነው?» አለው ።

«ሰው ሲሮጥ የሰማሁ መስሎኝ ነበር» ብሎት ክፍሉን በአይኑ ይቃኝ ጀመር ። ሀዲስ አይኑን ባይኑ ሲከተል ፣ ወደ ፅህፈት ቤቱ ከሚያስገባው በር ላይ ያለው መጋረጃ ተገልጦ ታየው ። በሩም ገርበብ ብሎ ነበር ።

ሀዲስ ቶሎ ብሎ ፣ «የት ነበርክ?» አለው ።

«ከነጋዴዎች ጋር ወደ ደኔ ሄጄ ነበር» ብሎ መለሰለት ፣ አገጩን እከክ እከክ እያደረገ ።

አንድ የከነከነው ነገር እንዳለ ፊቱ ላይ ያስታውቅ ነበር ።

«ሸጥከው?»
«የለም ።»
«ለመሆኑ ስንት እንስጥህ አሉህ?»
«ሰባት መቶ ሽህ ብር ።»
ሀዲስ አፉዋጨና ፣ «ታዲያ ለምን አልሸጥከውም?» አለው ።

«ሚሊዮን ብርም ቢሰጡኝ አሁን አልሸጠው ። ከዚያ ደን ጋር ፍቅር ይዞኛል ። ታላቅ ደን ነው» አለ ።

«ገንዘቡስ?»

«ገንዘብ ከሌላ ቦታ ላገኝ እችላለሁ ። ዶኑ ግን ለጊዜው መቆየት አለበት ። ብሸጠውም ከሁለት ሚሊዮን ብር በታች አልነካውም ። ቆይቶ ያወጣል ። ታያለህ ። ለጊዜው ግን ከዶኔ ጋር የያዘኝን ፍቅር መጨረስ አለብኝ » ብሎት ሄዶና 'አፔሪቲቭ' ለመስራት ቀይ ቬርሙጥና ጂን እየቀዳ ይቀላቅል ጀመር ።

ታፈስ ዶኑን በጣም ይወደው ነበር ። ሳይጎበኘው ውሎ አያውቅም ። እንደ አይኑ ብሌን ነበር የሚመለከተው ። ከታላላቅ ዛፎች መሃል እየተሽሎከለከ መሮጥ ይወዳል ። ሲደክመው ደግሞ በጣም ከሚወደው አንድ ታላቅ ዛፍ ስር ቁጭ ብሎ ፣ ጉሬዛዎች ፣ እንደ ጀርባቸውን ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ደረታቸውን ለፀሀይ እየሰጡ ካንዱ ዛፍ ወደ ሌላው በመዝለል ፣ የሚያሳዩትን የሰማይ ላይ ትርኢት ማየት በጣም ያስደስተው ነበር ። እሺ ብሎ ዶኑን ያልጎበኘለትን ሰው እንደ ጠላቱ ነበር የሚመለከተው ።

«አንድ ልስጥህ ?»
«የለም እቸኩላለሁ» አለ ሀዲስ ።
«ከቸኮልክ ለምን መጣህ?» የሚል ነበር የታፈስ መልስ ።
«በዚህ ሳልፍ እንዲሁ ልይህ ብዬ ነው ።»

«እዚህ አካባቢ ምን ታደርጋለህ?» ብሎት ፣ የሰራውን 'አፔሪቲቭ' ቀመሰና «እም» አለ ።

«የምኖርበትን አካባቢ እየዞርኩ ማየትና ማጥናት ደስ ይለኛል» አለውና ለመሄድ ተነሳ ።

«ጥናቱን ትተህ ከሱጴ ብትሄድ ይሻላል...»
«ስለ እሱ ጡዋት ተነጋግረናል ።»

«የመጣሽው አሳብህን የለወጥክ መሆንክን ልትነግረኝ መስሎኝ ነበር ።»

«የለም ። ምንም የተለወጠ ነገር የለም ። እንዲሁ በቀላሉ አሳቤን የምለውጥ ሰው አይደለሁም ።»

«ምን ሆንሃል ?»
«ምን ሆንኩ ?»
«ጤነኛ አትመስልም ።»
«አይደለሁም» ብሎት ወጣ ።

ለማንኛውም ነገር የእጅ ፅሁፉ የታፈስ ብሩ አልነበረም ።

ያን ሌሊት ሀዲስ የሰላም እንቅልፍ ተኝቶ አላደረም ። የዋቆ ምስል እየመጣ ያባንነው ነበር ። ባና በኑቃ ቁጥር በጀርባው ተንጋሎ በደረት አይኑ ጨለማው ላይ ማፍጠጥ ይጀምራል ። እና ፣ ማን ይሆን በኔ ስም የገፈላትን ይላል ። ነገሩ እንቆቅልሽ ሆናበት ፍች ሲያጣ አሳቡ ወደ ሌላ ይሄዳል ። ምን ማለታቸው ይሆን፤ በማለት ፊታውራሪ ስላሉት ነገር ያስባል ። ባሳብ ጎዳና ተጉዞ ተጉዞ በሚደክምበት ጊዜ እንቅልፍ ሸለብ ሲያደርገው የዋቆ ምስል መጥቶ እንደ ገና ያባንነዋል ። እንዲሁ ሲባንንና ባሳብ ሲኳዋትን ነጋለት ። እንደ ምን አደርሽ ፀሀይ፤ እንደ ምን አደርሽ ህይወት? ህይወት አይብለው!

ስለ ገንዘቡ እንደ ነገሩት ማድረጉን ሲነግራቸው ወደ አቶ ጣሴ ቤት ሄደ ። አቶ ጣሴ ቤት አልነበሩም ። በሴሊት ነው ወደ ትምህርት ቤት የሚ ሄዱት ። እረፍት ቢኖራቸውም ከትምህርት ቤት አይቀሩም ። የትምህርት ቤቱን አየር ካልተነፈሱ መቼም አይሆንላቸውም ። ሆኖም ትምህርት ቤት ሲደርስ አላገኛቸውም ። እንግዳ ነገር ሆኖበት ሲያስብ አቶ ይርጋ አስ ጠሩት ።

ቢሮአቸው ውስጥ ሌላ ወንበር የለም ።

«አሁን ግ ይሙት እንዲሁ አምልጠህ የምትቀር ይመስልሃል !» በማለት ሙሁበት ።

ሰላላዋ ድምፃቸው እንደ መርፌ ጆሮውን ጠቀጠቀችው ።

«የሚሉት ነገር አልገባኝም» አለ ሀዲስ ፣ እንደ ጡዋቱ አየር ቀዝቀዝ ብሎ ።

«አዎ ፣ ምን ይገባሃል ። አውቆ የተኛ ሰው ቢቀሰቅሱት አይሰማም አሉ» በማለት ከተረቱበት በሁዋላ አንዴ አገሱበትና ፣ «የስራ ሽው አት ልና ጭፍን ህጉ-ወጥነት በትምህርት ቤቱ ላይ ሲያስከትል የሚችለው ጉዳትና አደጋ አልታየህም ። እንዴት ብሎ ይታይሃል ! አይንህ እንደ ሆነ በእብሪት ተጋርዶአል ። ይህ ትምህርት ቤት በህዝቡ ዘንድ ጥሩ ስም ነበ ረው ። ባንተ ምክንያት ስሙ መጥፋት የለበትም ። ስለዚህ ሁሉ ተጠያ ቂው አንተ ነህ » አሉት እየደነፉ ።

ሀዲስ አሁንም ቀዝቀዝ በማለት ፣ «የትምህርት ቤቱን ስም የሚያ ጠፋ ምን ነገር ሰራሁ?» አላቸው ።

«አሁን ግ ይሙት ፣ ወርካውን እኔ አልጣልኩትም ልትለኝ ነው!» በማለት ከወንበራቸው ላይ ተነሱና ፣ «ምን ነው ሽዋ! እኔ ይርጋ ፣ ይሆን ተውና የዝንብ ጠንጋራም አውቃለሁ ። በዚሁ የሚቀር አይምሰልህ ። እኔን የሚያሳስበኝ የትምህርት ቤቱ ስም ነው ። በሰዎች አምልኮ ቀልዶ መኖር አይቻልም ። ደሞ ያልሰማሁ አይምሰልህ ። በቦታው ላይ አዲሱን ትምህርት ቤት ለመስራት ተመኝታችሁ እንደ ነበረ ደርሼበታለሁ ። የስ ራሽው ተንኮል የትምህርት ቤቱን ስም ማጥፋትና ከህዝቡ ጋር ማጋጨት ብቻ ሳይሆን ፣ በህዝቡ አምልኮት ላይ እንዲህ አይነቱን ነገር መፈፀም ራሱን የቻለ የፖለቲካ ወንጀል ነው ። ያውም የወንጀል ወንጀል! ...» እያሉ የዛቻ ማእት አወረዱበት ።

«አሁን ልሄድ እችላለሁ ?» አለ ሀዲስ ።

አቶ ይርጋ ጠረጴዛቸውን እየደበደቡ ፣ «ይህን ነው እኮ የምለው! እብሪት!» በማለት ፣ ሰላላዋ ድምፃቸው ጣራውን ጥሳ እስክትወጣ ድረስ ሙሁበት ።

በልቡ ሰኔና ሰኞ እያለ ወጣ ። አቶ ጣሴ ደጉን አሁንም ቢፈልጋቸው ሊያገኛቸው አልቻለም ። ሌሎች አስተማሪዎችን ስለሳቸው ቢጠይቅም ፣ የት እንዳሉ የሚነግረው ሰው አላገኘም ። አቶ ጣሴን ምን ዋጣቸው?

ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ቀማስ ተጠራጠረ። የወርካው ነገር ከብዶአቸው ይሆን? ስለ ተጠራጠራቸው መልስ ራሱን ጠላ ።

ደወል ተደወለ ። ደወል? ያዲሱ ደወል ድምፅ ተሰማው ። ውበቱ ታየው ። ክፍል ገብቶ በሚያስተምርበት ጊዜ ፣ ባዛጋ ቁጥር ፋጡማ መሀመድ ትስቅበታለች ። አየር ለመቀበል ወደ መስኮት ጠጋ አለ ። ወርካው በነበረበት ቦታ ላይ ያዲሱ ትምህርት ቤት ህንፃ ቆሞ በአይን ህሊናው ሳንዳፍታ ታየው ። ለእረፍት ተደወለ ።

ተማሪዎች አንድ ላይ ተንጋግተው ሲወጡ ፋጡማ መሀመድ ወደ ሁዋላ ቀረች ።

«ክፍል ውስጥ ማስቲካ ማኘክ ተይ ብዬሽ አልነበረም» አላት መፃህፍቱን እየሰበሰበ ።

የሳቅ እናት ። ሳቅዋን ጀመረች ። ጠረንዋ ተለወጠበት ። ለስለስ ያለ ሽቶ ነበር የሚሸተው ። ፍልቅልቅ ብላለች ። የለበሰችው ቆንጆ ብጫ ቀሚስ ቅላትዋን በይበልጥ ያጎላል ። ሰውነትዋ የጣዝማ ማር ወለላ ይመስላል ። አይንዋ እንደ ኮከብ ያበራል ። ለፃድቃን ወይን እንድታቀብል አላህ ለጀነት የመረጣት ትመስላለች ።

«አዲሳባ እንዴት ነበር?» አላት ። መልስዋ ሳቅ ነበር ።
«መልክቱን አደረስሽልኝ?»

ከዶብተርዋ ውስጥ ደብዳቤ አውጥታ ሰጠችው ።

«ከአትዬ በለጡ ጋ ነው?»
«አዎ» ብላ ሳቀች ።
«ጎሽ» ብሎአት ደብዳቤውን ሊያነብ ሲል ፣

አንድ ነገር ልትሰጠው እጅዋን ስትዘረጋ አያት ። ሰማያዊ ቡዋት ነበር ።

«ምንድን ነው እሱ?»
«የኔ ስጦታ ነው» ብላ ሳቀች ።

ቡዋቱን ከፍቶ አየ ። ፓርከር ብእር ነበር ።

«ለኔ ነው?»

ሳቀች ።

«ምን አሳሰበሽ?»

እየሳቀች ሮጣ ወጣች ።

ከአትዬ በለጡ ያመጣችለትን ደብዳቤ ከፍቶ ማንበብ ጀመረ ። ደብዳቤው፥ «...የላክልኝ ገንዘብ ደርሶኛል ። የላከሃትም ልጅ አንድ ቀሚስና ጫማ በተጨማሪ ገዝታ ሰጥታኛለች ። ስለኔ አታስብ ። ደህና ነኝ ። ነገር ግን ፣ ከናትህ ቤት ጎን ያሉት ባለስልጣን ፣ ትልቅ መኖሪያ ቤት ለመስራት እፈልጋለሁ ። ግቢው ስለሚጠበኝ ግምት ልስጥሽና ቦታውን ልቀቂልኝ በማለት ጠዋት ማታ ያስቸግሩኛል ። ሊሰጡኝ ያሰቡት ግምት በጣም ትንሽ ነው ። አሁንማ ፣ እምቢ ካልሽ ሌላ ቦታ ንጣፍ ሰጥቼሽ አባርርሻለሁ ። ደንቡም ይፈቅድልኛል ። ከሁለት መቶ ሽህ ብር በላይ የሚያወጣ ቤት በዚች ጎጆ ምክንያት ተጉዋጉሎ መቅረት አይችልም ፣ እያሉ ማስፈራራት ጀምረዋል ። አንዴ መጥተህ ነገሩን መልክ ብታስይዘው ጥሩ ነው ። እኔ እንደ ሆንኩ አቅም የለኝም ...» የሚል ነበር ።

በጣም ተናዶና አዝኖ ፣ 'እኔስ ምን አቅም አለኝ፣ ድሀ ቦታ ያጣበት አገር!' ሲል ተኩስ ሰማ ። አንዴ ብቻ አልነበረም የተተኮሰው ። ሁለቴ በተከታታይ ፣ ሶስተኛው ደግሞ ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ነበር የተተኮሰው ። እየተጣደፈ ሲወጣ ፣ ሌሎች መምህራን ወደ ትምህርት ቤቱ ፅህፈት ቤት ሲሮጡ አይቶ እሱም በሩጫ ተከተላቸው ።

አንድ አይናው ዘበኛ ካቶ ይርጋ አለሙ ቢሮ በር ላይ ቆሞ 'እሪ' ይላል ።

«ምንድን ነው! » አለ ሁዲስ ።
«ተጋደሉ ! ተጋደሉ !»
«እነማን ናቸው የተጋደሉት?»
«ኡ ! ኡ ! ኡ ! ያገር ያለህ !»

ሁዲስ ዘበኛውን ገፍቶ ፣ ሌሎችን መምህራን በመከተል ወደ አቶ ይርጋ ቢሮ ገባ ። ቀውሌ በቁመቱ ጋረደው ። ከፊቱ ገፋውና ወደ ፊት ብቅ አለ ። አይኑን ጠባ ። ቁዋቅ ሲለውም ፈሰገ ። አይኑን ጨፍኖ ወጣ ። አቶ ይርጋ ፣ እንትላቸው ፈሶ ፣ አይናቸውን በድንጋጤ እንዳፈጠጡ አፋቸውን ከፍተው ፣ ወንበራቸው ላይ እንዳሉ ወደ ሁዋላ ተንጋለዋል ። አቶ ጣሴ ደጉም በጀርባቸው ከወለሉ ላይ ተዘርረዋል ። በአፋቸው ደም ይፈስሳል ። ግን የሰላም እንቅልፍ የተኙ ይመስሉ ነበር ። ሽጉጣቸው እጃቸው ላይ ነበር ።

ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ የመቶ አለቃ አሸኔ አራት የታጠቁ ፖሊሶች አስከትሎ ሲገሰግስ መጣ ።

«ምንድን ነው?» አለ ሁዲስን ሲያይ ።

ሁዲስ ፈዞ ቆሞ ነበር ። ምላሱ የከዳው ይመስል በሌባ ጣቱ ወደ አቶ ይርጋ ቢሮ አመለከተው ። መቶ አለቃው ገባምጦት አለፈ ። አብዛኞዎቹ ተማሪዎች ተደናግጠው በየቦታው ቆመዋል ። ጥቂቶቹ አገሬ አውቆኝ በማለት እየወጡ ወደ ቤታቸው ይሮጣሉ ። ጭምጭምታ የሰሙ ሰዎች ከየአቅጣጫው ወደ ትምህርት ቤቱ መጉረፍ ጀምረዋል ። ሁዲስ ፈዞ እንደ ቆመ ፣ አንድ ተማሪ በኤንቬሎፕ የታሸገ ወረቀት አምጥቶ ሰጠው ። በድኑ ነበር ኤንቬሎፑን የከፈተው ። ደብዳቤው ከአቶ ጣሴ ደጉ መሆኑን ሲረዳ ፣ ከመጥፎ ቅዥት የባነነ ይመስል ራሱን ነቅንቆ ነቃ ።

«. . . ልጄ ሁዲስ ። ልጄ ልበልህ ። በስጋ ባልወልድህም በመንፈስና በአላማ አባትና ልጅ ነን ። አባቤ ምን እንደ ነበረ ይህን ደብዳቤ ከማንበብህ በፊት ደርሰህበት ይሆናል ።

«እንቅፋትህን ከፊትህ አስወግጃለሁ ። እኔም አብሬው ሄጃለሁ ። አዲሱ ትምህርት ቤት እየታየኝ ነው የምሄደው ። የደስታ ጉዞ ። ሰባት ሺህ ብር ሰራተኛህ ዘንድ ትቻለሁ ። ሶስቱን ሺህ ለትምህርት ቤቱ አራቱን ሺህ ለራስህ አድርገው ። የኑዛዜዬ ቃል መለወጥ የለበትም ። ያ 'የፍቅር' አለን ጋዳንም ትቼልሃለሁ ።

«መቶ አለቃውን ተጠንቀቀው ። ታፈሪንም አትመነው ። ከእሱ ጋር ነው ። ወርቁውን በፈንጂ የጣለው ሁዲስ ነው በማለት ህዝቡን ሊያስነሱ

ብሀ ሲያቤሩ ነበር ። ግን ፣ ነገሩ ታፈሰን በቀጥታ ፣ ፊታውራሪን ደግሞ በተዘዋዋሪ መንገድ ስለሚነካ ፣ አሁን የመረጡት ዘዴ ፣ አንተን በገንዘብ በመደለል ወይም በማስፈራራት ካገር ለማስወጣት ነው ። ለማይቀር ሞት አትፍራ ። አደራ አላበዛም ። ልጄ ደህና አሁን . . .»

ሀዲስ በዝምታ እንባውን አፈሰሰ ።

የቡጤ ሰው ወሬ ይጠግማዋል ። ግን እንደ ተጠማ አይቀርም ። ባለፈው ቀን ከወርካው መውደቅና ፊታውራሪ ቤት ውስጥ በደረሰው ትንግርት የቡና ጀበና ሳይጥድ ፣ ጉድ ነው ሲልም አደረ ። በሁለቱ ሰዎች ቀብር ላይ ፊታውራሪ ተካና ታፈሰ ብሩ አልተገኙም ። ለፊታውራሪ እያና ቀብር ወደ ኖጳ ሄደው ነበር ። ነገሩ የወሬ ሰርግና መልስ ሆና ሰነበተ ። ሀዲስ የሚጠነሰስበትን ሴራ የሚሰማበት መንገድ አጥቶአል ። በአቶ ጣሴ ደጉ ሞት አይንንና ጆሮውን ያጣ ያህል ነበር የሚሰማው ። በመሆኑም ሀዘኑ በጣም ከባድ ነበር ። ትምህርት ቤቱም መሪ በማጣቱ መዝረክረክ ጀምሮአል ። ዲሬክተሩም ፣ ምክትሉም ፣ አስተዳዳሪውም አቶ ይርጋ አለሙ ነበሩ—ነፍሳቸውን ይማረውና !

ለማንኛውም ነገር ሀዲስ ጊዜ አላጠፋም ። የወደቀውን ወርካ አስፈልጦ ከቦታው በማስነሳት ፣ መሬቱን የማስመንጠርና የማስደልደል ስራ ጀምሮአል ። ወርካውን ደፍሮ የሚፈልጥለት ሰው አጥቶ በጣም ተቸግሮ ነበር ። ከሌላ ቦታ የመጡ የቀን ሰራተኞች ባያገኝ ኖሮ ጉዱ ፈልቶ ነበር ። እነሱም ቢሆን ወሬ ሰምተው ፣ በተለይም ከመካከላቸው አንድ ሰው ወርካውን ሲፈልጥ ፣ መጥረቢያው እግሩ ላይ ከባድ የመቁሰል አደጋ ካደረሰበት በሁዋላ ፣ በመፍራት አንፈልጥም ብለው ነበር ። ሀዲስ ተጨማሪ ወጭ ማድረግ ነበረበት ። ወርካውን ሲያስፈልጥ ፣ መሬቱን ሲያስቆፍርና ሲያስደለድል ውሎ ወደ ቤቱ ሲሄድ አንድ ነገር ትዝ ብሎት ወደ ፖሊስ ጣቢያው ጎራ አለ ።

እንደ አሮጊት ጥርሶች የወላለቁ መዝጊያዎች ፣ እንደ ቆላ ቁስል የሚቀሉ ምርጊታቸው የፈራረሰ ግድግዳዎች ፣ የበሰበሱ ነገሮች ሽታ ታፍኖና ታፍን የቆየ የሰው መንፈስ እየቀፈፈው ነበር ወደ ፖሊስ ጣቢያው የገባው ። በር አንኳኩቶ ወደ መቶ አለቃ አሸኔ ቢሮ ገባ ። ሰውዬው ፣ በሲጃራ ጢስ ታፍና ነበር ። ካፈነው የሲጃራ ጢስ ውስጥ ፊቱን ብቅ አድርጎ ፣ «ምን ኖሮአል? . . . አው! አንተ ነህ እንዴ? ይህን ቦታ ታውቀዋለህ?» አለው በመገረም እየተመለከተው ።

የአይኖቹ ቅላት ያው ነበር ። እሳት የሚተፉ ይመስላሉ ፤ ለማየትም ያስፈራሉ ። የአይኖቹ ቅላት ፣ ሁልጊዜ እንደ ተናደደ የሚኖር ሰው ያስመስለዋል ።

«አምን ፣ የመጣሁ ሰሞን አንድ ቀን የክብር እንግዳህ በመሆን እዚሁ ቦታ ተገኝቼ ነበር ። ወንበርዋም ይችው ሳትሆን አትቀርም» አለና ፣ ወንበርዋን ስበ ተቀመጠ ። ሰባራ ወንበር ነበረች ።

አሸኔ ሌላ ሲጃራ መዘዝና በያዘው ቁራጭ ሲጃራ አዲሱን እቀጣጥሎ ሲያቢታ ፣ ባፉም ባፍንጫውም መሀት የሲጃራ ጢስ እየለቀቀ ፣ «ዛሬ ምን

እግር ጣለህ ታዲያ?» ሲል ጠየቀው ፣ በሲጃራው ጢስ ውስጥ አጨንቁሮ እያየውና ሰውን በሚጠራጠሩ ትላልቅ ቀይ አይኖቹ እየመረመረው ።

ሀዲስ ጠጉሩን ቆፈረና ፣ «የመጣሁት ያቶ ጣሴ ደጉን ቤት የሰበረው ሌባ ጉዳይ እንዴት እንደ ተዘጋ ወይም የት እንደ ደረሰ ለማወቅ ነበር» አለው ።

የመቶ አለቃ አሸኔ ድንጋጤውን ለመደበቅ አልቻለም ። ሲጃራ በሲጃራ አቀጣጠለ ። በሲጃራ ጢስ ውስጥ አጨንቁሮ እያየው ፣ «አንተ እዚህ ውስጥ ምን የሚያገባህ ነገር አለ? የተሰበረው ቤት ያቶ ጣሴ ። ወኪል ነህ ወይስ ጠበቃ» አለው ።

«ነገሩ ያገባኛል ብዬ ነው . . . »
«እንዴት?» በማለት የሀዲስን ቃል ወረቀት ላይ ፃፍ ፃፍ አደረገ ።

«ሌባው ሊሰርቅ የሄደው ለትምህርት ቤቱ ስራ በመዋጮ ከህዝብ የተሰበሰበውን ገንዘብ ሳይሆን አይቀርም ብዬ ነው» አለው—ሀዲስ ።

መቶ አለቃው የሲጃራ ጢስ ባፉም ፣ ባፍንጫውም ለቀቀ ። እንደ ጢስ ማውጫ ነበር የሚጨሰው ። ሀዲስን ለማስፈራራት አሁንም አንድ ነገር ወረቀት ላይ ፃፍ ፃፍ አደረገና በሲጃራ ጢስ ውስጥ አጨልጎ እያየው ፣ «ይህን ለማለት የሚያስችል ምን ማስረጃ አለህ?» በማለት መስቀልኛ ጥያቄ ያቀርብለት ጀመር ።

ሀዲስ ትክሻውን ነቅንቆ አደረገና ፣ «ያካባቢ ሁኔታ የምትሉት ነገር አለ አይደል? አጠራጣሪ ሁኔታ አለ» አለው ።

መቶ አለቃው በንዴት የሲጃራውን ቁራጭ ባመድ ተሞልቶ ከሚታየው መኮስተሪያ ውስጥ አወደመና ፣ «ሌባው ያቶ ይርጋ አሽከር ነበረ የሚባለውን አሉባልታ ሰምተህ ነው? መሰረት የሌለው አሉባልታ ነው ። ሰውዬው ካቶ ይርጋ ቤት ከወጣ ቆይቶአል ። ከእሳቸው ቤት የወጣውም ሰርቆ ነው ። የታወቀ ልማደኛ ሌባ ነበር ። ወህኒ ቤት ሰብሮ ሊያመልጥ ሲሞክር በዘብ ጠባቂዎች ተገድሎአል ።

«ይሄው ነው ። ሌላ ታሪክ ወይም ምስጢር የለውም፤ግን አንተ ታላዝናለህ ። ከዚህ በፊት የፈተና ውጤት አጭበርብረዋል በማለት ጥሩ ስማቸውን ለማጥፋት ሞክረህ ነበር ። አሁን ደግሞ ሙት ወቃሽ በመሆን ያለ ምንም ማስረጃ የሌባ ተባባሪ ናቸው በማለት ስማቸውን ለማጥፋት ተነስተሃል ። አጥንታቸው በሰላም ቢያርፍ ምናለበት!» ከተቀመጠበት ተስፈንጥሮ በመነሳት ሀዲስ ላይ እንደ ሞት ጥላ በረጅም ቁመቱ እያንዣበበ ፦

«ይህ ሁሉ ወዴት እንደሚያመራ ታውቃለህ?»

ሀዲስ ወደ ላይ ቀና ብሎ እያየው ፣ «ወዴት ነው የሚያመራው?» አለው ።

«ባቶ ይርጋ መገደል ያንተም እጅ እንዳለበት ራስህን በራስህ አሁን አሁን አጋልጠሃል ። ባንተና ባቶ ጣሴ መሃል ባቶ ይርጋ ላይ የተጠነሰሰ

ሲራ ነበር ማለት ነው ። ነገሩ የሚያመራው ወደዚህ ነው» ብሎ ፥ ወደ ወንበሩ ተመለሰና የሆነ ነገር ፃፍ ፃፍ ካደረገ በሁዋላ ፥ «የንፁህ ሰው ደም በከንቱ ፈስሶ የሚቀር አይምሰልህ ። የሴባ ተባባሪ ናቸው የምትሉት በምን ምክንያትና ለምን አላማ እንደ ሆነ አሁን ገብቶኛል ። ወርካውን የጣሉት እነ ማን እንደ ሆኑ ተከታትለው ስለ ደረሱበት ነው በግፍ የተገደሉት ። ግን አይምሰልህ ። እውነት ተሸፍና አትቀርም ። ምናለ በለኝ ። ይህን ነገር ከዳር ሳላደርስ ብቀር እኔ አሽኔ ወንድ አይደለሁም! ቁጭ ብዬ እሸናለሁ!» አለና ጠረጴዛውን በጨበጠው ቡጢ አንዴ ደለቀው ።

ሀዲስ ፍንክች አላለም ። ወደ ላይ ቀና ብሎ እያየው ፥ «መቶ አለቃዬ ፥ እኔ እንዲህ አይነቱ ውንጀላ አያስደነግጠኝም ። ደግሞ ፥ የምፈራው ነገር የለም» አለው ፥ ቃላቱን ርግጥ እያደረገ ።

«ማንን ተማምነህ ወይም ምን ይዘህ ነው እንዲህ የምትንጠባረር ብኝ!»

«ሀቅ ።»

«እሺ ። ሀቁን ማወቅ ትፈልጋለህ» ብሎ የጠረጴዛውን መሳቢያ ከፈተ ። የፈለገውን ነገር አላገኘም ። ደንግጦ ሁለተኛውን መሳቢያ ሳበ ። አይኑ ፈጠጠ ። እያሳበው ሶስተኛውን መሳቢያ ሳበ ። ሀዲስም ያልበው ጀመር ። መሳቢያው ውስጥ ያለውን ፋይልና ወረቀት ጎልጉሎ የፈለገውን ነገር ሲያጣ ጠረጴዛው ላይ ያለውን ደወል ደወለ ።

እንደ ገና መሳቢያዎቹን እያወጣ አንድ ባንድ ይፈትሽ ጀመር ። የፈ ለገውን ነገር አላገኘም ። አይኖቹ ፈጠጡ ። በጣም ያልበው ጀመር ። ሀዲስም እሱን አይቶ አላበው ። ደወሉን እንደ ገና በሃይል ደወለ ። እያከ ታተለ በሃይል ደወለ ። ትእግስት አጥቶ ነበር ። —የምን ሀቅ ሊያሳየኝ ፈልጎ ይሆን? አለ በልቡ ። ጭንቅ ያዘው ።

አንድ ወታደር ፖሊስ መጥቶ ሰላምታ ገጭ አድርጎ በትጠንቀቅ ቆመ ። ሀዲስ ጆርባውን ላብ ላብ አለው ።

«የወዳጆ ጉርሙ ፋይል የት አለ! እዚህ ፥ አንደኛው መሳቢያ ውስጥ ነበር ። »

«ወታደር ጎይቶም ወስዶታል ፥ ጌታዬ . . .»
«ለምን? በማን ትእዛዝ!»

«እኔ እንጃ ፥ ጌታዬ ። ግን ፋይሉ ከመዘጋቱ በፊት ማየት አለብኝ ሲል ነበር ፥ ጌታዬ ።»

«ምናባቱ አገባውና! ማን ስልጣን ሰጠው!»
«እኔ እንጃ ፥ ጌታዬ ።»

መቶ አለቃ ደመ ነፍሱን ዘሎ ከቢሮው ወጣ ። ራሱን ስቶ እብድ ሆኖ ነበር ። ሀዲስ ጊዜ አላጠፋም ። መቶ አለቃው ሲጭረው የነበረውን ወረቀት አንስቶ፥ ከኪሱ ያንን ደብዳቤ በማውጣት ሁለቱን የእጅ ፅሁፎች

ያመሳክር ጀመር ። የሜግ ድምፅ ሰምቶ የመቶ አለቃውን ወረቀት ጠረጴዛው ላይ ቶሎ ብሎ ወረወረ ። ወረቀቱ ቦታውን አልያዘም ።

የመቶ አለቃ አሸኔ የቆሰለ አውሬ መስሎ ነበር ። ንዴት እየተናነቀው ጫን ፤ ጫን ይተነፍሳል ። የሆነ ሰይጣናዊ ተንኮል ሀዲስ ላይ ድንገት ያየ ይመስል እያፈጠጠበት ፣ «ከወታደር ጎይቶም ጋር ምን ግንኙነት አለህ?» በማለት ጠየቀው ።

«ምንም ።»
«ታውቀዋለህ?
«አላውቀውም ። ለምንድነው የምትጠይቀኝ?»

መቶ አለቃ አሸኔ መልስ አልሰጠውም ። ባሳብ ተውጦአል ። ግን የሚያስብ አይመስልም ። ተወናብዶ ሚዛኑን ያጣ ሰው ነበር የሚመስለው ። ሀዲስ ፣ ሰውዬው ሚዛኑን እስኪያገኝ ድረስ እድል አልሰጠውም ። ሹልክ በማለት እግሬ አውጭኝ አለ ። የሆነ አደጋ ታይቶት [illegible] ። አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል እንዲሉ ፤ ትንሽ አሳ ለማጥመድ ወደ ፖሊስ ጣቢያው ጎራ ያለው ሰው ትልቅ ዘንዶ ይዞ ወጣ ። የመቶ አለቃ አሸኔ የእጅ ፅሁፍ ደብዳቤው ላይ ካለው እጅ ፅሁፍ ጋር ፈፅሞ አይመሳሰልም ።

ወደ ቤቱ ሮጦ የታፈሰን ሽጉጥ ያዘ ። ሰራተኛው የወታደር ጎይቶምን መኖሪያ ቤት አመለከተችው ። በቀጥታ ወደዚያ አመራ ። ጀንበርዋ አቆልቁላለች ። ብርሃንዋ አድማሱ ላይ ቀይ ሆኖ ይታያል ። ወፎች ረድፍ ገብተው ወደ ገባ በረሃ ይበራሉ ። ከብቶች እምቡዋ እያሉ ወደ ቤት ያመራሉ ። እምቦሳዎች ከቤት ሲሞሁ ይሰማል ። ጢስ ከየቤቱ ይጨሳል ። ጎጆዎች ህይወት ዘርተዋል ።

ከወታደር ጎይቶም ቤት ደጃፍ ላይ አንድ ሰው ቁጭ ብሎ መፅሀፍ ሲያነብ ከሩቅ ተመለከተ ። ጠጋ እያለ ሲመጣ ነው የሰውዬው ጎፈሬና ጢም ጎልቶ የታየው ። ልቡ ድንግጥ አለ ። እሱ ነው? ወይስ እሱ አይደለም? እያለ ሲያመነታ ፣ ሰውዬው ከሚያነበው መፅሀፍ ላይ ቀና ሲል ፊት ለፊት ተያዩ

«ማእ !» ብሎ ጮኸ ሀዲስ ።
«ፕሮፌሰር!»

ተቃቅፈው ተሳሳሙ ። እና ፣ ሁለቱም በመገረም ቆመው እየተሳሳቁ ይተያዩ ጀመር ።

ዮሀንስ ጴጥሮስ አልተለወጠም ። በጣም አጭር ነበር ። በተአምር ድንክ ከመሆን ያመለጠ ነበር የሚመስለው ። ከቁመቱ ይልቅ ጎፈሬው ነበር ጎልቶ የሚታየው ። ፊቱ እንደ ዝንጀሮ ፊት ጠጉር ብቻ ነበር ። ከቅጥንቱ የተነሳ ሃይለኛ ነፋስ ይዞት የሚሄድ ይመስላል ። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ነፋስ በተነሳ ቁጥር 'ማእ ድንጋይ ኪስሽ ጨምሪ!' እያሉ ይቀልዱበት ነበር ። ጠጉር ፣ አጥንት — ሌላ ሰውነት አልነበረውም ።

ሁለተኛ ዓመት ላይ ነበር ፈተናውን ወድቆ ከዩኒቨርሲቲ የወጣው ። ፈተናውን የወደቀው ጥንቅሳት እንቢት ባይሆን ፈፅሞ አያጠናም ነበር ።

የሱሪት ሱስ እንዳለበት ሰው በረጅም ፉል አፍንጫው አየር አስሬ ወደ ላይ እየሳበና በቂጡ ወልቆ ዱብ ሲል የሚደርሰውን ሱሪውን ወደ ላይ እየጎተተ ፣ «ምን መሰለህ ፤ ፈተና ማለፍ እኮ የቢሮክራሲ ክርስትና ልጅ መሆን ማለት ነው ። የእውቀት መለኪያ አይደለም ። የቢሮክራሲ ድቁና ፣ ቅስናና ጵጵስና ተቀበልክና አዋቂ የሆንክ መሰለህ!

«እውነቱን ነው . . . ምን መሰለህ ፤ ትምህርት ቤቶች የጭቆና መሳሪያ ዎች ናቸው ። መጋረጃው ተከፍቶ የሀቅ ፀዳል ግልጥልጥ ብሎ የሚታይባ ቸው ስፍራዎች ሳይሆኑ ውሸትና ቅጥፈት የሚሰበክባቸው የጨለማ ቤተ መቅደሶች ናቸው ። ስብእናህ ተሙዋልቶ ለተሙዋላ ህይወትና ኑሮ የምት ዘጋጅባቸው ስፍራዎች አይደሉም ። ይልቅ . . . ምን መሰለህ . . . ነገሩን ጠለቅ ብለህ ብታየው . . . ትምህርት ቤቶች የገዢው መደብ መሳሪያ እን ድትሆን . . . እ . . . ለገዢው መደብ ድቁና—ቅስና . . . እ . . . ጵጵስና ነው ። የገ ዢው መደብ አላማ መለኪያ የሆነውን ፈተና ካለፍክ ምናለ—በቃ ጥም ቀት ፣ ክርስትና — እርገት — ዲያቆን ። ያዳቆነ ሰይጣን ደግሞ ሳያቀስ አይለቅም ።

«ምን መሰለህ—ፈተና አለፍክ—ድግሪ—በአራት መቶ ሃምሳ ብር ተቀ ጠርክ ። በቃ ። ከዚያ ወዲያ ምን አለም አለ! ባዶ ቅል ። እንደ ባዶ ናስ የሚጮህ ። የተማረ ደንቆሮ ። ብር ሀቁ ፤ ምቾት ጭንቁ ፤ ሆድ አምላኩ ። እኔ ፈተና ለማለፍ ግድም ደንታም የለኝም ። የገዢው መደብ ዲያቆን መሆን አልፈልግም» በማለት የጦፈ ክርክር ይገጥም ነበር— ጥሩ ጭንቅላት እያለህ ለምን አታጠናም? ብለው በጠየቁት ቁጥር ። ታዲያ የክርክሩ ማሳ ረጊያ ሁልጊዜ የስድብ ውርጅብኝና ናዳ ነበር—የኢምፔሪያሊዝም አፈ - ቀላ ጤዎች ፣ ቡችላዎች ፣ የፊዩዳሊዝም ጋሻ ጃግሬዎች ፣ አደግዳጊዎች ፣ የቡርዣ የዎች ዲያቆናት — ጠምጣሚ ቄሶች — እነ ድግሪ አምላኩ — ደንቆሮዎች ወዘተ . . . ወዘተ ። ይሁን እንጂ ፣ ‘ማእዱ’ በማለት ከማሞካሸት አልፎ ቂም የሚይዝበት ወይም አምርሮ የሚጠላው ተማሪ አልነበረም ።

ትንሽ የሚጠሉት ክርክሩን በመሰልቸት ‘ዮሀንስ መጥምቁ’ ሲሉት በቅርብ የሚያውቁት አንዳንድ ጉዋደኞቹ ደግሞ—‘ትንሹ ጴጥሮስ’ እያሉ ይጠሩት ነበር—ወዲያው ካድ ያደርገናል ስለሚሉ ።

«ምንም አልተለወጥክም ጃል» አለ ሀዲስ ሳህሌ አፍንጫውን ነፋና ።
«አንተም የሱሪ አየር የተስማማህ ትመስላለህ?» አለው ማእ ።
«የሚገርም ነው» አለ ሀዲስ ፣ «እዚህ ምን አመጣህ?»
«ወንድሜን ልጠይቅ መጥቼ ነው . . .»
«ወታደር ነይቶምን?»
«አዎ ፤ ትተዋወቃላችሁ?»
«የለም ። ግን ላንድ ጉዳይ ፈልጌአቸው ነው ።»

«ግን እሱ ያውቅሃል ። ስላንተ አንስቶ ሲያጫውተኝ ነበር ። ትምህ
ርት ቤት ማሰራት ጀምረሃል አሉ ። »

«አዎ ፣ ግን መቼ ነው የመጣኸው?»
«ትናንት ወደ ማታ ። ወዳንተ ለመምጣት ሳስብ ነበር ።»
«ወ፡ድምህ አሁን የት ርቻው?»

«ቅድም እንደ ወጣ አልተመለሰም ። ስላንድ ነገር ይናደድ ነበር ። ወንድሜ ሁል ጊዜ ባለቆቹ እንደ ተናደደ ነው የሚኖረው። ምን መሰለህ» በማለት አፍንጫውን አስሬ ወደ ላይ እየሳበ ። ስለ ወንድሙ በመጠኑ አጫወተው ።

ጎይቶም በየጠቅላይ ግዛቱ ያልሰራበት ፖሊስ ጣቢያ የለም ። ካለቆቹ ጋር እየተጣላ ካንድ ጠቅላይ ግዛት ወደ ሌላ፣ ካንድ ፖሊስ ጣቢያ ወደ ሌላ ጣቢያ እያዘዋወሩት ሲንከራተት ይኖራል ።

እንደ ማእ አባባል ታዲያ ካለቆቹ ጋር የሚጣላው በግል ጥቅም አይደለም ። በኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ምፅዋ በሚሰራበት ጊዜ በኮንትሮባንድ የሚያዙ በብዙ ሺህ ብር የሚገመቱ እቃዎች ባለቆቹ ሲበዘበዙ አይቶ ፣ ‘ለምን እንዲህ ይሆናል?’ በማለቱ የበላይ ትእዛዝ አይቀበልም ተብሎ ወደ ሸዋ ተባረረ ።

አራተኛ ፖሊስ ጣቢያ ተመድቦ ሲሰራ የሌባ ጠር በመሆን ለጥቂት ወራት ታዋቂነትን አትርፎ ነበር ። ሆኖም ፣ አለቆቹ ጉቦ ሲበሉ ደርሶባቸው ለበላይ በማመልከቱ፣ እንደ ጥፋተኛ ተቆጥሮ ወደ ኢሉባቡር ጠቅላይ ግዛት መቱ እንዲዛወር ተደረገ ። እዚያም አንድ አሳዛኝ ነገር ገጠመው ። ባልዋ የሞተባት አንድ ማይም ሴት በፃፈችው ማመልከቻ ላይ የንጉሰ ነገስቱን ክብር ነክታለች በመባል ተወንጅላ ለብዙ ጊዜ ታስራ ነበር ። ነገሩ ገርሞት፣ጉዳዩን ሲከታተል፣በተንኮል ወረቀቱን ራሳቸው ፅፈው፣ደግ ደጉን ክፍል ካነበቡላት በሁዋላ፣እስዋ ምንም ሳታውቅ ያስፈረምዋት፣የባልዋን የቡና መሬት ለመቀረማመት የሚፈልጉ ካንዳንድ ባለ ስልጣናት ጋር የተመሳጠሩ የፍርድ ቤት ሰራተኞች ሆነው አገኛቸው ። ከዚያ በሁዋላ መቱ ውሎም አላደረ ። ባስቸኳይ ወደ ሱዳ እንዲዛወር ተበየነበት ። በዚሁ የተነሳ የማእርግ እድገት አግኝቶ አያውቅም ።

ሀዲስ የጎይቶምን ታሪክ ሲያዳምጥ ቆየና ፣ «ከህሊና ንፅህና የበለጠ ሹመት የለም ። ክልቡ ፖሊስ ነው ! አሁን ሁሉም እንደሱ ቢሆን ምን አለበት» አለ ።

«ምን መሰለህ? አንድ ቀን ህዝባዊ ፖሊስ ሲፈጠር ሁሉም እንደሱ ይሆናል» አለው ፣ ማእ ።

ሀዲስ የእጅ ሰአቱን ተመለከተ ።

«ቸኩለሃል መሰለኝ?»
«አዎ ፣ በጣም የሚያስቸኩል ጉዳይ አለኝ ። የሚመጡ ይመስልሃል?»

ማእ አፍንጫውን ነፋና ፣ «እኔ እንጃ ። ከሁለት ፖሊሶች ጋር ነው የወጣው ። አንድ ፣ የሆነ ነገር ለመከታተል የሄዱ መሰለኝ ። በነገሩ ላይ ሲወያዩ ነበር ። ግና ፣ ምን ይባባሉ እንደ ነበረ አልተከታተልኩም» አለውና ፣ «ምን መሰለህ? እሱ ተመልሶ እስኪ መጣ ድረስ ለምን ዝናሽ ቡና ቤት አንሄድም? እርግጠኛ ነኝ እስከዚያ ድረስ ይመጣል ። ጎይቶም ማምሸት አይወድም ። ቢጠጣም ከጠላ ሌላ ነገር አይቀምስም ። እሱንም ቢሆን ቤቱ የተጠመቀ ካልሆነ አይነካውም» አለው ።

«ዝናሽም ቤት ደርሰሃል?» አለ ሀዲስ ።

«አዎ ፤ እንዲያውም አንድ ያፃፈችኝን ግጥም ላንብብልህ» ብሎት ከኪሱ ቁራጭ ወረቀት አወጣና ያነብ ጀመር ።

ሆይ ፣ ሆይ ! የልደታ ፋኖ የውቤው በረሃ ዳኛ ፤
የሴሊት አሞራ የፍቅር መጋኛ
የልደታ ሱሰኛ
የሴት ቀበኛ
ደርሶ መልስ ፍቅር ሲደራ
ብር ሲመዘዝ ሲዘራ
ሲጠፍ ዳንኪራ
ሆይ ! ሆይ ! ሴቱ እስኪነጋ
ቻቻና ማሪንጊ ከሊፕሶና ኮንጋ
ታንጎ ቡጊውጊ እንደ ገና ሩምባ
ሩምባ ማምቦ ስምባ...

«ጥሩ አይደለም ወይ?» አለው ።
«ያለፈ ትዝታ ነው» አለ ሀዲስ ስእቱን እያየ ።

«ምን መሰለህ? ትዝታ እኮ ምጥፎ አይደለም ። ሰው ያለ ትዝታ አይ ኖርም ። የህልውናችን አንድ አካል ነው» አለውና አፍንጫውን የሱሪት ሱስ እንዳለበት ሰው ነፍቶ ፤ «ምን አይነት ቅኔ ነው የምትወደው አንተ?» በማለት ጠየቀው ።

ሀዲስ ጠጉሩን ቆፈረና ፣ «እኔ የምወደው? ... በሰው ልብ ተስፋ ፤ ፍቅርና ቆራጥነትን የሚያጠነክር ውበት ያለው ቅኔ ነው የምወደው ። በቃ ላት ጨዋታ ደስ አይለኝም ። እና ፣ ደግሞ ስላለፈው ትዝታ ለምን ሁልጊዜ እንደምንዘፍንና እንደምንቀኝ አይገባኝም ። ምናልባት ያለፈው ዘመንና ጊዜ ህይወትና ኑሮ የተሻለ መስሎ እየታየን ይሆናል ። ቆይ ... እውነቴን ነው ።

«ባለ ቅኔዎች ብቻ ናቸውስላለፈው ትዝታ የሚቀኙትና የሚፅፉት ማለቴ አይደለም ። ተራውም ሰው ቢሆን ፤ ስምተሀ እንደ ሆን ፤ የሚያወ ራው ስላለፈው ዘመን ጥሩነትና ትሩፋት ስለ ሰው ደግነት ፣ ጨዋነት ፣ ጤን ነትና እድሜ ነው ። ግን ሀቁ ፣ ያሁኑ ዘመን ካለፈው ፣ ዛሬ ከትናንት ፣ ነገ ደግሞ ከዛሬ ይሻላል ። ሰው ዛሬ ከትናንት የተሻለ ይበላል ፣ ይጠጣል ይሰራል—ባጠቃላይ እነጋገር ማለቴ ነው ። የሰው እድሜም ቢሆን እድሜ ለሳይንስ ፣ ካለፈው ዘመን አሁን ረዝሞአል ። እውነቴን ነው የምልህ ፤ ሰው ስላለፈው ዘመን ትዝታ ለምን ሁልጊዜ እንደሚዘፍንና እንደሚያወራ አይገባኝም ። ለኔ ፣ ምን ጊዜም ቢሆን ፣ ደስ የሚለኝ የወደፊቱ ተስፋ ነው ። እና ፣ ቅኔ ይህን ተስፋ በሰው ልብ ማጠናከር አለበት እላለሁ ። በኔ ግምት ወርቃማው ዘመን መጭው ዘመን ነው» አለው ።

ማኦ አፍንጫውን ነፋና ፣ «ምን መሰለህ? ጥሩ ውይይት ነው የጀመ ርነው ። አሁን ባለፈው ሁኔታ ተስፋ ማድረግ ከንቱ ነው ። ግን ውይይቱን ዘናሽ ቤት ሄደን እንቀጥል ። ቢራም ጠምቶኛል» አለ ።

«አሁን አልሄድም ። ወንድምህን ማግኘት አለብኝ ። እንዳልኩህ ነገሩ በጣም አስቸኳይ ነው» አለውና አሁንም ሰአቱን ተመለከተ ።

«ምን መሰለህ? ሳያትም የምፈልጋት ልጅ አለች ።»
«የት?»
«ዝናሽ ቤት?»
«እውነት ።»
«ሽታዬን ታውቃታለህ? እስዋም እንደ ዝናሽ ጨዋታ ደስ ትለኛለች ።»
«ኢ ...ቆንጆ ናት ።»
«እንዲያ ?»
«እውነት ! የለም ። ባይሆን ሁዋላ ... »

«እሺ» በማለት ተስፋ ቆርጦ ፣ «እስቲ ስለ ትምህርት ቤቱ ንገረኝ? ሙቱ ስለ ትምህርት ቤቱና ስላንተ ብዙ ይወራል ። ዝነኛ ሆነሃል» አለው ።

«ስራው በቅርብ ቀን ውስጥ እንደሚጀመር ተስፋ አለኝ ።»
«ባዶ ተስፋ ነው ።»
«ለምን እንዲህ ትላለህ? !» አለ ሀዲስ በማእ አባባል ተገርሞ ።
«መጀመሪያውኑ ትምህርት ቤት ለመስራት ምን አሳሰበህ?»

«ለምን አላስብም?» አለ ፣ ማእ ስለ ትምህርት ቤትና ስለ ትምህርት ያለውን አስተሳሰብ ስለሚያውቅ ባዶ ለሆነ ክርክር በር መክፈት እየጠላ ፣ «መቼም ቁጭ ብዬ ከንፈሬን ከመምጠጥ ትንሽ ስራ ብሰራ ይሻላል ብዬ ነው ። በጎ ምኞት ብቻውን ቁዋት አይሞላም ። የትምህርት ክፍሎች እጥ ረት አለብን ። ችግሩ መፈታት አለበት ። አለ አይደል ፣ ትንሽም ሻማ ብት ሆን በጨለማ ውስጥ ማብራት ደስ ይላል ።»

ማእ በዚያው ነገሩን አላቆመም ፣ «ጊዜህንና ጉልበትክን በከንቱ ነው የምታባክነው» አፍንጫውን አስሬ መንፋት እየጀመረ ፣ «ምን መሰ ለህ ፤ ለህዝቡ የእርሻው ቦታ፣መንገዱ፣ፋብሪካው፣አስተዳደሩና ፍርድ ቤቱ ሁሉ ትምህርት ቤቱ ነው ። ከሚደርስበት ግፍና ስቃይ ፤ ምዝበራና ጭቆና በቂ ትምህርት አግኝቶአል ። አሁን የሚፈልገው መሰረታዊ ለውጥ ነው እንጂ ተጨማሪ የትምህርት ክፍሎች አይደለም ። ይህን ማወቅ አለብህ ። እንደ ዱር አውሬ አፍንጫ፣ነገር ከሩቅ ለማሽተት የሚችል አፍንጫ እንዲ ኖርህ ያስፈልጋል ። የለውጥ ፍላጎት አየር በየቦታው እየነፈሰ ነው ። አል ሸተተህ እንደ ሆነ ያሳዝናል ። አፍንጫ ከሌለህ ምንም ሳደርግልህ አልች ልም ። ግን፣ ጊዜህን በከንቱ እያጠፋህ ነው» አለው ።

ሀዲስ ጠጉሩን ቆፈረና ፣ «እና ፣ ምን አድርግ ነው የምትለኝ? ቁጭ ብለህ የሚነፍሰውን የለውጥ አየር አሽትት ነው የምትለኝ?» ካለው በሁ ዋላ፣እየተነጫነጨ ፣ «የለም አንተ እንደምታስበው ጊዜዬን በከንቱ በማ ጥፋት ላይ አይደለሁም ። የነገውን የተሻለ ህይወት መመኘት ወይም ቁጭ ብሎ ማሽተት አይበቃም—መፍጠር አለብን።የወደፊት ህይወት ተዘጋጅቶ የሚጠብቀን ነገር አይመስልህ ፤ ከዛሬ ጀምሮ የምንፈጥረው ነገር ነው ። መማር ያለብን ነገር ምን እንደ ሆነ ታውቃለህ? ራሳችንን ማስታየትን ሳይሆን ማስራትን—ድርጊት። ብዙዎቻችን በልባችን ቅን እንመኝ ይሆናል፣ ድርጊት ላይ ግን ዜሮ ነን» አለ ሀዲስ፣ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

«እንደ ቄስ ነው የምትናገረው !»
«ይሆናል ። የህይወት ቄስ አይደለሁ ።»

«ሃይማኖተኛ ነህ?»
«አልገባኝም ጥያቄህ?»
«ማለቴ በእግዜር ታምናለህ?»

ሀዲስ ጥያቄው እያሳቀው ፣ «ባገኘሁትና ደስ ባለኝ ። የማቀርብለት ብዙ ጥያቄዎች ነበሩኝ» ብሎት ቀጠለና ፣ «እኔ የማምነው በህይወት ነው ። ከህይወት ውጭ የሆነ እምነት የለኝም ። ታሪኬ ከላይ ተፅፎ የተሰጠኝ ነው የሚል እምነት የለኝም ። ታሪኬ ከላይ ተፅፎ የተሰጠኝ ነው የሚል እምነት ኖሮኝ አያውቅም ። ሊኖረኝም አይችልም ። ለታሪኬ ሃላፊው እኔው ነኝ—ብድል ይሁን ለሽንፈት» አለው ።

«እና ፣ የራስክን ታሪክ እየሰራህ ነዋ!» በማለት አሾፈበትና ፣ ቀጥሎ ፣ «ምን መሰለህ፣ የምትሰራው ትምህርት ቤት ባንተ ቤት ለውጥ የሚያስገኝ ወይም እድገትን የሚያስከትል ይመስልሃል ። የቡርዧዋ ህሊናዊ እድፍ ገና አልለቀቀህም» አለው ።

ሀዲስ አልተቆጣም ። በጥሞና ፣ «ስማ ማእ ፣ እድገት ስንል ምን ማለት እንደ ሆነ በትድሚያ መታወቅ አለበት» ብሎት ጠጉሩን እንደ ልማዱ ቆፈር ቆፈር አደረገና ፣ «እኔ እድገት የምለው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምጥቀት ብቻ አይደለም ። የሰው ልጅ እውነተኛ እድገት የማግኘት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የመሆን ጉዳይም ነው ። የሰው ልጅ ክብር ። አሃዛዊ እድገት ብቻውን ፋይዳ የለውም ። ለውጥም ስንል ለማን? መነሻውና መድረሻው ሰው መሆን አለበት» አለውና ስእሉን ተመለከተ ። ጭለማው አይን ያዝ ማድረግ ጀምሮአል ።

«ለምን ማርክሳዊ መፃፍቶችን አታነብም?» ብሎ ጠየቀው ።
«አያነብም ያለህ ማን ነው?»
«መፅሃፍ ትራሱ መሆንክን አውቃለሁ ። ግን . . .»
«ግን ምን?»
«ሳይንሳዊ አመለካከት የለህም ።»

«ማርክሲዝም የድርጊት መመሪያ መሆኑን አትርሳ ። ቀኖናዊነት አይደለም ። የነገውን የወደፊቱን ህይወት የምንፈጥርበት ሳይንስ እስከ ሆነ ድረስ ይዘቱና አቅጣጫው እየሰፋ መሄድ አለበት ።

«ትናንት እንደ ዛሬ አይደለም ። ነገ እንደ ዛሬ አይሆንም ። ህይወት ሁልጊዜ አዲስ ነች ። ማንም ሰው የውሀ ዋና ከመፃፍ ብቻ አይማርም ። ዋና ለመማር ውሀ ውስጥ ገብቶ መዋኘት ያስፈልጋል ። ህይወትም እንደ ዚሁ ነው ። ከህይወት የበለጠ አስተማሪ የለም ።

«እና ፣ ደግሞ አንድ ሰው አብዮታዊ ወይም ማርክሳዊ የሚሆነው በድህነት ተወልዶ ስላደገ ወይም ሶሻሊስታዊ ስርአት የማይቀር ታሪካዊ ሀቅ ነው ተብሎ ስለ ተነገረው ወይም ስላነበበ አይምስልህ . . .» እንዳለ ፣ ወታደር ጎይቶም እየሮጠ ሲመጣ በማየቱ ደስ ብሎት ንግግሩን አቋረጠ ።

ወታደር ጎይቶም ዮሀንስ የመንፈስ ርጋታ አይታይበትም ። «ዋይ፤ ወዲ አይተ» ይል ነበር ደጋግሞ ። ሀዲስ ራሱን አስተዋወቀና ፣ «ጉዳይ ኧበ ረኝ» አለው ።

ጎይቶም በጣም ቸኩሎአል ።

«ጊዜ የለኝም ። የምን ጉዳይ ነበር?» አለው ፣ በንዴት ጣቶቹን እያ ፍጮኸ ።

«ስለ ወዳጆ ጉርሙ ፋይል ነበር» አለ ሀዲስ ።

ጎይቶም ድንገት በነገሩ ተማርኮ ፣ «ስለሱ ፋይል ምን የምታውቀው ነገር አለ?» በማለት ጠየቀው ።

ሀዲስ እንደ አጋጣሚ ከመቶ አለቃ አሸኔ ስለ ፋይሉ የሰማውንና እንዲሁ አቶ ጣሴ ስለ ወዳጆ እሙዋሙዋት ያጫወቱትን ባጭሩ ከነገረው በሁዋላ ፣ «እንግዲህ የኔ እድል የሚወሰነው በዚህ ፋይል ነው ። እንደ ሰማ ሁት ፋይሉ በእጅህ ይገኛል ። ራሴን መከላከል አለብኝ ። ከፍ ያለ የትን ኮል ወንጀል እየተቀነባበረብኝ ነው» አለው ።

«ዋእ ፣ ወዲ አይተ ፣ ሐቂ ዝደሊ ስብአብዛ አለም ሰላም አይህልዎን» ብሎ እንደ ገና ጣቶቹን አፍጮኸና ፣ «አንተ አርፈህ ተቀመጥ ። ነገሩን እንደ ጀመርኩ እኔው ከፍፃሜ አደርሰዋለሁ» አለ ።

«ፋይሉ አሁን የት ነው?»

«ዋእ ፣ በጂ ነው ። ግልፅ የሆነ ወንጀል ነው የተፈፀመው ። የትም አያመልጥም ።»

ማአ ጣልቃ ገባና ፣ «ጀመረህ እንግዲህ ! ለምን አርፈህ አትቀመጥም? ከዚህ በሁዋላ የት እንደሚያደርስህ ታውቃለህ? እንጦሮጦስ !» አለው ።

«ዋእ ! ሱጥ በል !»
«ዋእ ! እንታይ ይመስለካ ?» አለ ማአ ።
«አንተ ነገሩዎ ዘይሰምእ ንርእሱ ይገዶ» አለው ።
«አይንከን ጨፍነህ ኑር ነው የምትለኝ?»

ከዚያ በሁዋላ ሁለቱ ወንድማማቾች ፣ «ዋእ ! ዋእ !»

እየተባባሉ ይጨዋጨዋሁ ጀመር ። በዚያ ‘ቴስታቸው’ ካሁን አሁን ይፋ ለጣሉ ብሎ ሀዲስ ስግቶ ነበር ።

ጎይቶም ጣቱን እንደ ጅራፍ አጩሆ ቤት ገባና መሳሪያውን ይዞ ሄደ . . . ጨረቃና ከዋክብት የማይታዩበት ድፍን ጨለማ ነበር . . .

# ክ ፍ ል ፲፪

ድፍን ሉጴ ትኩስ ወሬ አግኝቶ ፣ በቀዘቀዘ ጀበና ላይ ጉድ ! ጉድ ! ይላል ። ሀዲስ ተጠርቶ ወደ ፊታውራሪ ግቢ በማምራት ላይ ነበር ፣ ባለ ፈው ምሽት የደረሰውን ታሪክ እያስታወሰ ...

ወታደር ጎይቶም ዮሀንስ ትእዛዝ አልቀበልም ብሎ ከማመፁም በላይ ፣ በረሃ ከሽፍቶች ጋር ለመደባለቅ የተዘጋጀ መሆኑ ስለ ተደረሰበት ከማም ለጡ በፊት እጁ እንዲያዝ በማለት መቶ አለቃ አሸኔ ጥብቅ ትእዛዝ ሰጥቶ ነበር። የሚተባበረው ፖሊስ ግን አላገኘም። ተንኮሉን ለመሸፈፉን ፣ «በሄደ በት ቦታ ሁሉ የአለቆቹን ስም በውሸት እያጠፋ መኖር የለመደ ወንበዴ ነው» በማለት ፣ ጎይቶም ባለፉት አመታት ከስንት ቦታ በዝውውር እንደ ተባረረ ምሳሌ በመጥቀስ ፖሊሶቹን ሊያግባባ ቢሞክርም አልሆነለትም ።

ነገሩ በጣም ግልፅ ነበር ። ያን ምሽት ከጣቢያው ፖሊሶች መካከል ወዳጆ ጉርሙን ለጥያቄ የፈለገ ሰው አልነበረም ። ለጥያቄ ትፈለጋለህ በማለት የህግ እስረኛውን በውድቅት ከተኛበት ቀስቅሶ የወሰደው የጣቢ ያው ፖሊስ አዛዥ ራሱ እንደ ነበረ ሌሎች የህግ እስረኞችና ተረኛው ዘብ መስክረዋል ። ሆኖም ዋናው ቁም ነገር ይህ አይደለም ። ጎይቶም ፣ የወ ዳጆን ቃል እንዳለ ተቀብሎ ካዘጋጀ በሁዋላ ፣ ወዳጆን በማስፈረም ፋይሉ ውስጥ ያኖረው ዘገባ ወጥቶ ፣ በምትኩ ፣ «እኔ ወዳጆ ጉርሙ ፣ እድሜዬ 38 የሆነ፣ ያለ ምንም ስራ የምኖር ...... ቀን አካባቢው ጭር ብሎ ስላየሁ ፣ አቶ ጣሴ ደጉ የተባሉትን ሰው ቤት ሰብሬ ገብቻለሁ ። ሆኖም የወሰድኩት ነገር የለም ። ሰዎች ድንገት ስለ ደረሱብኝ ለመያዝ በቅቻለሁ ። ርግጥ ከሁለት አመት በፊት አቶ ይርጋ አለሙ ቤት ባሽከርነት ስርቻለሁ ። መተ ዳደሪያ ስለ ሌለኝ ከዚህ በፊት ሁለት ሶስት ጊዜ ያህል በስርቆት ተይዤ ታስሬአለሁ ። ከአቶ ይርጋ አለሙም ቤት ለመውጣት የበቃሁት በእም ነት ማጉደል መሆኑን አረጋግጣለሁ ...» የሚል ፣ ወዳጆ ቃሌ ነው ብሎ የፈረመበት ዘገባ ከፋይሉ ጋር ተያይዞአል ። ነገር ግን ለጎይቶም በሰጠው ቃል፣ «...ከብዙ ዘመን ጀምሮ እስከ መጨረሻው እለት ድረስ አቶ ይርጋ አለሙ ቤት በታማኝነት ሲሰራ መቆየቱንና አቶ ጣሴ ደጉን ቤት ሰብሮ ሊገባ የቻለው ፣ አቶ ጣሴ ወንጀል ሰርተው ከህዝብ ለትምህርት ቤቱ ስራ የተሰበሰበውን ገንዘብ ይዘው ሊጠፉ ነውና እንደ ምንም ብለህ ቤቱን ሰብ ረህ ገንዘቡን አምጣልኝ ፣ ይህን ያደረግህ እንደሆነ ከኔም ሽልማት ፣ ከህዝ ቡም ከፍተኛ ምስጋናና ምርቃት ፣ በእግዜርም ፊት ዋጋህን ታገኛለህ ስለ ተባልኩ ነው ...» የሚል ቃል ነበር የሰጠው ። ወዳጆ በፊርማው አረጋ ገጠ የሰጠውን ቃል አንድ ኮፒ ለራሱ አስቀርቶ ነበር — ጎይቶም ።

ወዳጆ ጉርሙ በውድቅት ለጥያቄ ትፈለጋለህ ተብሎ ከተወሰደ በሁዋላ ፣ ወደ ወህኒ ቤቱ አልተመለሰም ። በዚያን ምሽት ከእስር ቤት ላማ ምለጥ ሲሞክር የተያዘ ወይም የተገደለ ወንጀለኛ እንዳልነበረ ተረኛ ዘብ

በሰጠው ቃል ከማረጋገጡም ሌላ ፥ የጣቢያው አዛዥና አቶ ይርጋ አለሙ ሰውዬውን ይዘው ከጣቢያው ሲወጡ ያየ መሆኑን መስክሮአል ።

ጎይቶም ይህንኑ ለስራ ባልደረባው ሲያስረዳ ነበር የዋለው ። እና ፥ መቶ አለቃው ተናዶና ተደናግጦ ፥ «ይህ ሰው በሄደበት ቦታ ሁሉ ያለቆቹን ስም በተንኮል ከማጥፋት ሌላ ስራ የለውም ብያቸዋለሁ ። አሁንም ቢሆን ፥ የሰውዬው ቃል ነው ብሎ ያስፈረው ነገር ሁሉ ውሸት ነው ። እንዲህ አይነቱ ጭፍን ቅጥፈት ከፖሊስ አይጠበቅም ። ይህን ያደረገው ደግሞ ባንዳንድ ተንኮለኞች በገንዘብ ተገዝቶ ነው ። እና ፥ የሰውዬን ትክክለኛ ቃል ከራሱ እንደ ገና መቀበል ነበረብኝ ። እንደምታውቁት ፥ የንፁሃን ስም በከንቱ እንዳይጠፋ ፥ እኔም ሆንኩ እናንተ መሃላና ሃላፊነት አለብን ።

«ሰውዬውንም ይገኙ የሄድኩት ፥ ቤቱን ሰብሮ እንዴት እንደ ገባ በበታው ተገኝቶ እንዲያሳየኝ ነበር ። ነገር ግን መንገድ ሲደርስ ፥ ጭለማን ተገን አድርጎ ለማምለጥ ሞከረ ። 'ቁም!' ብለውም እምቢ አለ ። የእጅ ባትሪ ይዤ እየተከታተልኩት አንድ ጊዜ ወደ ሰማይ ተኮስኩ ። አሁንም አልቆመም ። ለሁለተኛ ጊዜ ተኮስኩ ። አሳቤ እግሩን ለመምታት ነበር ። ግን ጀርባው ላይ ተመትቶ ወደቀ . . . ግን ተንኮለኞች እንደሚሉት ይህ የተደረገው ለተንኮል አልነበረም ። ለሀቅ ስል ነው ። አሁንም ጎይቶም መያዝ አለበት !» እያለ ቢወተወትም የሚሰማው ፖሊስ አላገኘም ።

የሚሰማው በማጣቱ እንደ እብድ ያደርገው ጀመር ። የመሳሪያ ግምጃ ቤቱን ቆልፎ ፥ እንደ አበ ደች ውሻ እየተቅበዘበዘ መሳሪያ ይዞ ይወጣል ። ጎይቶም ወደ ፖሊስ ጣቢያው ፥ እሱ ደግሞ ወደ ጎይቶም ቤት ሲሄድ መንገድ ይገናኛሉ ። ምን ሊያደርግ ይሆን? በማለት ራቅ ብሎ ከሁዋላ ይከተል የነበረ ፖሊስ ፥ መቶ አለቃው መሳሪያ ሲያቀባብል ሰምቶ «ጎይቶም ተበላሸህ !» ሲል ጮሆ ያስጠነቅቀዋል ። መቶ አለቃው ወደ ሁዋላ ዞር ብሎ አንድ ጥይት ይለቅበታል ። ፖሊሱ ታፋውን ተመትቶ ይወድቃል ። ጎይቶም በደረቱ ከተኛበት ስፍራ ሁለት አከታትሎ ይተኩሳል ። ከዚያ በሁዋላ ፀጥታ ይሰፍናል ። ተኩስ የሰሙ መንደረተኞች ግርግርና ሩጫ ይጀምራሉ ። ገሚሱ ወደ ሌላ አቅጣጫ ነበር የሚሮጠው ።

በዚህ ጊዜ ነበር ሀዲስና ማእ ሲሮጡ መጥተው ከስፍራው የደረሱት ። ጎይቶም በአሸኔ ጥይት ተመትቶ የወደቀውን ፖሊስ ይረዳ ነበር ። አሽኔ ጭጭ ብሎ ከቀረ ቆይቶአል ።

«እንታይ እዚ!» እያለ ማእ ይጮሃል ።
«ሱጥ በል!»
«ይህን አልነበረም የፈራሁት!»
«ዝም በል ነው የምልህ!»
«ዋእ!»
«ዋእ!»

ሀዲስ በሁለቱ ወንድማማች ጥል ብቻውን ሳቀ ። ወደ ፊታውራሪ ቤት የሚያወጣውን ዳገት ጨርሶ ወጥቶ ነበር ። ቶሎሳ ወደ እልፍኝ አስገባው ። ፊታውራሪ ከድንክ አልጋቸው ላይ ነበሩ ። መምሩ መስቀል አሳለሙት ።

«ቁጭ በል» አሉት ፊታውራሪ ።

«ቁጭ አለ ፡፡ አይኑን ወደ ጉዋዳ ጣል አደረገ ፡፡ ምንም አላየም ፡፡ ብቅ ያለም የለም ፡፡

«ሒሀሳ!» አሉ ፊታውራሪ ፡፡
«ደህና» አለ ፡፡

«በትምህርት ቤቱ የተነሳ ሰው ሁሉ ተሳለቀ አይደለም ወይ?» አሉት ፡፡

መቼም ነገር አያመልጣቸውም ፡፡ ሁሉም አይንና ጆሮአቸው ነው ፡፡ ሆኖም ፡ ፊታውራሪ ይህን ሊጠይቁት እንዳሳስጠሩት ሰውነቱ ነገረው ፡፡

«ተንኮለኞች በተንኮላቸው ይጠፋሉ» አለ ሀዲስ ፡፡
«አዎ ፡ ነገር ለሰራው ፡ እሾህ ላጣሪው! ቃየል ሞት ያመጣብን ወን ድሙ ላይ ባደረበት ቅናትና ምቀኛነት ነው» መምሩ ነበሩ ፡፡

«አዎ ፡ ሰው የእጁን ዋጋ አያጣም »አሉ ፊታውራሪ ሪዛቸውን አለ ንጋ በሚመስሉት ጣቶቻቸው ሳብ ለቀቅ እያደረጉ ፡፡ ቀጠሉና ፡ «ፋጡማ መሀመድ የምትባለውን ልጅ ታውቃታለህ?» በማለት ጠየቁት ፡፡

«አዎ ፡ ተማሪዬ ነች፡፡»
«ልከሻት ታውቃለህ?»

«አዎ ፡ አዲሳባ ስትሄድ አደራ እናቴ ዘንድ ልኬአታለሁ» አለ ፡ እያሳ በው ፡፡

«የለም ፡ እዚህ ቤት ማለቴ ነው» አሉት ፡፡
«እንዲያውም» አላቸው ፡ የባሰውን እያሳበው ፡፡

«አንድ ደብዳቤ ከአይናለም ዘንድ መልሰህ ወስደህ ነበር ፡፡ ያ ደብዳቤ አሁን በእጅህ ይገኛል?»

ሀዲስ መሀረብ አውጥቶ ግንባሩንና ማጅር ግንዱን ጠረገ ፡፡ በላብ ሰውነቱ ርሶአል ፡፡ የተኮነነች ነፍሱ ገሃነም እሳት እንደ ገባች ያሀል ነበር የሚያልበው ፡፡ በእሱ ስም ለአይናለም የተፃፈውን ደብዳቤ በሚንቀጠቀጥ እጁ ከደረት ኪሱ አውጥቶ ሰጣቸው ፡፡ ፊታውራሪ ተካ ደብዳቤውን ቀስ ብለው ያነቡ ጀመር ፡፡ ከነፍሱ ጋር ተሙዋገተ ፡፡ የተኮነነች ነፍሱ እቶን እሳት ውስጥ ገባች ፡፡ ከዚያ ወጥታ ፡ ቅዝቃዜው እንደ ስለት የሚወጋ በረዶ ውስጥ ተጣለች ፡፡ ካደረበት ሰቃይ የተነሳ ዘመን ያለፈ መሰለው ፡፡ ፊታውራሪ ደብዳቤውን አንብበው ከጨረሱ በሁዋላ ፡ ለመምሬ መሀሪ አሳልፈው ሰጡ ፡፡

መምሩ ደብዳቤውን እንደ ድጋም ሲያነበንቡ ፡ ፊታውራሪ ሪዛቸውን እየጎነተሉ ዝም ብለው ያስቡ ነበር ፡፡

«ጉድ ነው ! ሳጥናኤል . . . ዲያብሎስ ራሱ እንዲህ አይነቱን ተንኮል አይሰራም!» አሉ መምሩ ፡ ደብዳቤውን አንብበው እንደ ጨረሱ ፡፡

ሀዲስ ላቡን ጠረገና ፣ «በስሜ የተፃፈ ነው እንጂ እኔ አልፃፍኩትም ። በኔ ስም ይህን ተንኮል ማን እንደ ሰራ ስፈልግ ነበር» እያለ ንፁህ መሆኑን ለማሳመን ወተወተ ፣

«አንተ እንዳልሆንክ ደርሰንበታል ። የምትናዘዘው ነገር የለም ። አይዞህ ። ደብዳቤውን ፋጡማን አስይዘው የላኩት አቶ ይርጋና መቶ አለቃው ነበሩ ። እግዜር መሬት ወርዶ ሰው ባይቀጣም ፣ እሱ በላካቸው ሰዎች የእጃቸውን ዋጋ አግኝተዋል ። እግዜር ለጥፋተኞች የሚቆርጠው አር ጩሜ ያው ሰውን ነው ።

«ይህን ተንኮል በምን ምክንያትና ለምን አላማ እንደ ፈፀሙ እናውቃለን ። ወይኔ ተካ ! የወንድ ልጅ ልክ ሚዛን እንዳልነበርኩ ሁሉ !» አሉ ፣ ጣቶቻቸውን በንዴት ፣ በቁጭትና በእልክ እንደ ጅራፍ እያጮሁ ።

«አዬ ! እባክዎን አይናደዱ ። የልጅ ስራ ነውኮ የሰሩት ። ይተውት ። ተከናንበው ቢተኙ ገልጠ የሚያይ አምላክ የእጃቸውን ዋጋ ሰጥቶአቸዋል ። እሱን ማመስገን ነው ፣ ማማረር ደግ አይደለም» አሉ መምሩ ፣ የመጣውን ሰይጣን የሚያባርሩ ይመስል አየሩን በያዙት ጭራ እየገረፉ ።

በነገሩ ፣ እስካሁን ድረስ ሲጠራጠር የቆየው ታፈሰ ብሩን ነበር— ሀዲስ ። ልቡ ላይ ተጭኖ የነበረው ድንጋይ የወረደለት ይመስል ቀለል አለው ። ላቡ ሰውነቱ ላይ ደረቀ ። ግን ያደረበት ስሜት ምን እንደሆን ለይቶ ለማወቅ አልቻለም ። ደስታ? ሀዘን? ንዴት? ውስብስብ ያለ ስሜት !

«ስራውን ጀምረሃል አሉ?» ፊታውራሪ ነበሩ ።
«የቱን ስራ?»
«የትምህርት ቤቱን።»
«አዎ።»
«ወርካውንም አስፈለጥክ አሉ።»
«እዎ።»

ሀዲስ እንደ ገና ያልበው ጀመር ።

«ህም» የሚል ድምፅ አሰሙ ፣ ትኩር ብለው እያዩት ።

ሀዲስ አቀረቀረ ።

«ምን ነው ዋሸሁኝ ?» አሉ ፊታውራሪ ።
ቶሎ ማሰብ ነበረበት — «አልዋሸሁም» አላቸው ።
«እህሳ?»

«ከዚህ በፊት እንደ ነገርኩዎት ወርካው የነበረበትን ቦታ ለአዲሱ ትምህርት ቤት አምኘው ነበር ። የሰጠ ቦታ ነው ። አንድ ቀን ፣ በህልሜ አንድ አዛውንት ያ ሃን ቦታ ትምህርት ቤት ስራበት እያሉ ድንጋይ ሲያቀብሉኝ አየሁ ። እና ፣ የታየኝን ራእይ እውን ለማድረግ ወርካውን በፈንጂ ጣልኩት» አለ ፣ የአቶ ጣሴን ምክር እያስታወሰ ።

«መብረቁ አንተው ራስህ ኖረሃል ለካ!» አሉት ።

ሀዲስ ፈገግ ብሎ ዝም አለ ።

«አዎ» አሉ ፊታውራሪ ፣ «'አምላክ ፊታዱን በመረጠው ሰው ያስፈፅማል' ይል ነበር መክብብ . . . »

ሀዲስ በልቡ ቃላቸውን እየደገመ ፤—እሱን እንደምትመስል ከዚህ
በፊት ነግሬሃለሁ፤ አለ ።

«ቁርጥ እሱን» ።

መምሩ የውሸት ሳል ሳሉ ። የመከብብ ስም ሲነሳ ያስሳቸዋል ወይም
ያስነጥሳቸዋል ።

«አዎ» አሉ ፊታውራሪ እንደ ገና ፤ «ያላንድ ታሪክ ወደዚህ አላመ
ለከተህም ። የእሱን መንገድና ጥበብ ማን ያውቃል ። ሰው ያስባል እሱ
ይፈፅማል ። በፈለገው ጊዜ በመረጠው ሰው ።»

ፊታውራሪ በትካዜ ሩቅ ይመለከቱ ጀመር ። ግን ፊታቸው ላይ ሀዘን
አይታይም ። ፊታቸው ብሩህ ሆኖአል ። ራእይ የሚያዩ ይመስላሉ ። «በማ
ንኛውም ነገር ላይ ያምላክን ስምና ምልክት ማንበብ የሚቀናቸው ሰው
ናቸው» በማለት አቶ ጣሴ ደጉ ስለ ፊታውራሪ ያጫወቱት ነገር ትዝ አለው።
ግን ፤ አሳቡ የሮጠው ወደ አይናለም ነበር ። ደብዳቤው በኔ ያልተፃፈ መሆ
ኑን ስትረዳ ምን ብላ ይሆን፤ አለ ። በእሱ ላይ ጥላ የነበረው እምነት አሁን
ሲታየው ፤ የገዛ ልቡን መልሶ እንደ ጦር ወጋው ። ሳይታወቀው አቃሰተ ።

«ትምህርት ቤቱ ዲሬክተር አልተሾመለትም ፤ አይደለም?» አሉት
ፊታውራሪ ።

«ገና ነው ።»
«የነገርኩህን ጽምን አደረስከው?»
«የቷን?»
«መካሪ ሽማግሌ ፈልግ ብዬህ አልነበረም?»

ነገሩ ባይገባውም ፤ «እሺ እፈልጋለሁ» ብሎ ፤ ተሰናብቶ ሲወጣ ፤
«እኔም አስቸኩዋይ ስራ አለኝ በማለት» መምሩ ተከትለውት መጡ ።

መንገድ ላይ ሲደርሱ ፤ በጭራቸው አየሩን እየገረፉ ፤ «ፊታውራሪ
ያሉህ ነገር ገብቶሃል ወይ?» ብለው ጠየቁት ።

«ሁለተኛ ጊዜአቸው ነው እንደዚህ ሲሉኝ ። እንቆቅልሽ ሆኖብኛል ።
ምን አስቀይሚአቸው ይሆን? እያልኩም አስባለሁ» አላቸው ።

«ኧረ በእልቂይቱ ማርያም !! የቄስ ዘር ሆነህ! ኧረ ተወኝ! ይህ የፈ
ረንጅ ትምህርት ያደድባል ልበል! የኛን ትምህርት ዘልቆ የተማረ ሰው
ቀርቶ ትንሽም ቅኔ ቤት የቆጠረ፣ ሰው የተናገረው ነገር ይቅርና የሚያስበ
ውም ይገባዋል» አሉና ቆም ብለው ፤ «እንዴ? 'እሺ ሽማግሌ እፈልጋለሁ'
ብለህ ስትወጣ ያሉህ ነገር የገባህ መስሎኝ ነበር ። ኧረ በእልቂይቱ ማርያም!
የተናገሩት ነገር ምንም ሰምና ወርቅ የለውም» አሉት ።

«ሽማግሌ ላክብኝ ማለታቸው ነው!»
«እህሳ ! የቄስ ልጅ ሆነህ? ምን ነው ጨዋ ሆንክብኝ?»

ሀዲስ እቆመበት ፈዞ ቀረ ። ደስታ ነበር ያፈዘዘው ። ከልቡ ጥልቀት
ውስጥ ልዩ ጣእም ያለው ውብ ዜማ ይፈልቅ ነበር ፤ እና ፤ አለም ከእሱ

ጋር የምታዘያ መስለው ። አለም በሙሉ ወደ ሚእመ ሙዚቃ ተለወጠ በት . . .

«የንፍስ አባት አለህ ?»
«ኢ?»
«የንፍስ አባት አለህ ወይ?»
«የለኝም ።»
«ታዲያ ምናለ? እኔ ብሆንህሳ?»
«ጥሩ።»

«ኢንግዲያው ፣ እሁድ እሁድ ከቤተስኪያንም አትቅር ። እንዴ? ሃይ ማኖትኮ በተግባር ነው . . .»

«ደህና ።»

«ምን ነካህ? በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ . . .» ብለው መስ ቀላቸውን ሲያወጡ ፡—

«ምንም አልሆንኩ ። ደህና ነኝ ። ደህና አይደለሁም እንዴ?» በማለት ጥሎአቸው ሮጠ

መምሩ ሲያሳልሙት ያወጡትን መስቀል እንደ ያዙ ፣ ሀዲስ ቁልቁ ለቱን ሲሮጥ ፣ ቆመው እንደ ትንገርት ይመለከቱት ነበር . . .

# ክ ፍ ል ፲፯

የበልግ ዝናብ ከጠፉ ሰንብቶአል ። ምን እንዳባረረው አይታወቅም ። ስራ የፈታው ገበሬ ሁሉ ጡዋት ፣ ቀንና ማታ ፣ «እሪ ምን መአት መጣ!» እያለ ወደ ሰማይ ያንጋጥጣል ። ዝናብ ሲያመጡ ይችላሉ የሚባሉት የመ ንደር አዋቂዎች ሁሉ ምናምን እየተጎመጠመጡ ወደ ሰማይ ቢተፉም ፣የዝ ናብ ጠብታ ከየት መጥቶ ! ሰማዩም እንደ ምድሪቱ ክው ብሉ ደርቆ ነበር ።

አካባቢውን የሚያናግር የገበሬ ጅራፍ አይሰማም ። እረኞች ዘፈን እየተቀባበሉ መዝፈን ትተዋል ። ወንዞች ስለ ደረቁ ሽለቆዎች እንደ በፊቱ በደስታ አያስካኩም ። ውሀ የጠማቸው አለቶች ዝም ብለው አፍጠ ዋል—ዝም—የመቃብር ዝምታ።

የእርሻ ማሳዎች ህይወት አይታይባቸውም ። በውሀ ጥማት አረው ቀርተዋል ። ከተዘራው እህል ፍሬ ውስጥ ሞቶ ዘር የሰጠ አንድም አይታ ይም ። ከብቶች የሚግጡት ርጥብ ሳር አልነበረም—ቆመው የሚያሽቱት አፈር እንጂ ። አፈር ። ያፈር ሽታ ።

አንድም የወፍ ዘር አይታይም ። ቃል ወደ ተገባላቸው ምድር በጊዜ የተሰደዱ ይመስላሉ ። ጥምብ አንሳ ብቻ ነበር ፣ ሱጴ ሰማይ ላይ የሞት ጥላውን እያጠላ የሚያንዣብበው ።

ተፈጥሮ አኩርፋ ሰው ላይ ፊትዋን ያዞረች ትመስላለች ። ግንቦት መጨረሻ ላይ በየቀዬው ፣ በየአድባሩ የተነፈረላት ንፍሮ ፣ የፈላላት ቡና ፣ የተጨሰላት እጣንና የፈሰሰላትም ደም ቁጣዋን መልሳ እርቅ እንድታወ ርድ አላደረጋትም ። ይልቅ ፣ የንዴትዋ ነበልባል ይባስ ብሉ እንደ እሳት ምላስ እየላሰ ልብ ያቀልጥ ነበር ። የታላቁ አድባር መውደቅ የተፈጥሮ ቁጣ ምልክት ይሆን? . . . እና ፣ ሰው ሁሉ ተሰብስቦ ፣ እግዚኦ! ሰውረን ከመአቱ . . . እያለ በመሙህ ምህላ ቢገባም ፣ መስዋእት ቢያቀርብም እርቅ አልወረደም ። ሱጴ እንደ ገሃነም ደረቀች ። እግዚኦ! እግዚኦ! በየቦታው— በየቀኑ ። ይሁን እንጂ ፣ የሱጴ ህዝብ ለሰራው ሀጢአት የሚከፍለው ዋጋ አላገኘም ። ለሰው ሀጢአት ቤዛ ሆኖ በመስቀል ላይ የሞተው የሰው ልጅ በቅርቡ ተመልሼ እመጣለሁ ካለ ሁለት ሽህ ዘመን ሲሆን ምን ቀረው! የሱጴ ትእግስት እያለቀ በመሄድ ላይ ነበር ። ሰውን ከጥፋት የሚያድን ከሰው ሌላ ማን አለ! ምናልባት ሌላ ስግእት ያስፈልግ ይሆን?

ከትምህርት ቤቱ ፕላን ላይ ቀና ብሉ ሀዲስ ጫን ተነፈሰ። በስራው ረገድ ትንሽ ርምጃ በማድረጉ ደስ ብሎት ነበር ። ያዲሱ ትምህርት ቤት መሰረት የሚጣልበትን ስፍራ የመደልደል ስራ አሁንም አላለቀም ። የበልግ ዝናብ መጥፋት ባንድ ፊት ለትምህርት ቤቱ ስራ ሳይታሰብ የደረሰ ምርቃት ሆኖ ነበር ። በእርሻ ወራት የቀን ሰራተኛ ማግኘት ያስቸግራል ። እዚህ

ግባ በማይባል ርካሽ የጉልበት ዋጋ ስራ ፈላጊ ሞልቶ ተርፎ ነበር ። ሆኖም አድባሩ ከወደቀበት ቦታ ላይ እንስራም በማለት የሚመለሱ ብዙዎች ነበሩ ።

የመሬት ምንጠራውንና ድልደላውን ስራ ለማየት ወጣ ሲል አንድ የስድስተኛ ክፍል ተማሪ መጥቶ አስተማሪ እንደ ሌላቸው ነገረው ።

«ማን ነው ገብቶ ማስተማር የነበረበት?»
«ጋሼ ቀውሴ።»

«አስተማሪ ፣ መምህር እገሌ ተብሎ በስሙ ነው የሚጠራው ! አስተ ማሪዎቻችሁን ማክበር አለባችሁ።»

ተማሪው እንደ ማፈር ብሎ አቀርቅሮ ራሱን ሲያክ ከቆየ በሁዋላ ፣ «በዚህ ሳምንት ምንም አልተማርንም ። ክፍል ገብቶ የሚያስተምር አስ ተማሪ የለም ። ቢገቡም ምንም ሳያስረዱን ይሀን ፣ ይህን አንብቡ ብለውን ነው ጥለውን የሚወጡት» አለው ።

ሀዲስ ያለ መርሀ ግብሩ ስድስተኛ ክፍሎችን ለማስተማር ገባ ። ክፍሉ ጨርሶ የእብዶች መንጋ ሆኖ ነበር ። አንዱ ተማሪ አስተማሪ መስሎ ባለ ተማሪዎች እየቀለደ ተማሪዎቹን ያስቅ ነበር ። ሀዲስ ሲገባ ሁሉም እንደ አይጥ እየተሽሎከለኩ ሄደው ቁጭ አሉ ። ዝም ፣ ፀጥ አሉ ። ውስጥ ውስ ጡን በሽቆ ደሙ ቢፈላም ፣ ፈገግ ብሎ ፣ «ልጆች አንድ ነገር ልጠይቃ ችሁ ። መልሱን ማን ይሰጠኛል?» አላቸው ።

ሁሉም እጃቸውን አወጡ ።

«ጥያቄው ምን እንደሆነ ሳታውቁ?» ብሎ ሳቀና ፣ «እሺ ። ነፃነቱን የሚያከብርና የሚወድ ማን ነው?» በማለት ጥያቄውን አቀረበላቸው ።

«እሺ አንተ።»

«ላገሩ የሚሞት።»
«እሺ አንቺ።»
«ኢትንኩኝ የሚል።»
«እስቲ አንተ ደ'ሞ ... የለም ... አዎ ፣ አንተ»
«እንደ ፈለገው የሚኖር ... ሳይፈራ የፈለገውን የሚናገር።»
«ሌላ መልስ ያለው አለ? እሺ አንተ ... አዎ»
«እንደ ኢትዮጵያ ህዝብ ለብዙ ዘመን በነፃነት የኖረ ።»

«እሺ ልጆች ። ጥሩ ነው ። ግን እኔ ያሰብኩትን መልስ አላገኛችሁ ትም ። ነፃነቱን የሚወድና የሚያከብር ሰው ማን ነው? ብትሉኝ ፣ እኔ የምሰ ጠው መልስ ፣ ግዴታውን አውቆ የሚያከብር ሰው ነው የሚል ይሆናል ። ለምን? ብትሉኝ ፣ ግዴታውን የማያውቅ ሰው ነፃነቱን ያውቃል ወይም ይወዳል ወይም ያከብራል—ለነፃነቱ ይታገላል ወይም ይሞታል ብዬ ስለ ማላምን ነው ። ህይወት ራስዋ የግዴታዎች ሰንሰለት ናት ። እና ፣ ግዴታ ውን አውቆ የሚያከብር ሰው ምን ጊዜም ፣ ለማንም ባርያ ሆኖ አይኖርም ።»

ዝም አሉት ። አልገባቸውም ። እሱም አሳቡን በይበልጥ ሊያብራራ ላቸው አልፈለገም ። ወደ መደበኛ ትምህርት ገብቶ ፣ ውስጥ ውስጡን እየበሸቀ ፣ ማስተማር ጀመረ ።

ከክፍል እንደ ወጣ በቀጥታ ሄዶ ፣ «ለመምህራን ሁሉ ! በተማሪዎች ስም ዛሬ ከቀትር በሁዋላ በዘጠኝ ሰአት ስብሰባ እንድናደርግ እጠይቃለሁ» የሚል ወረቀት በሰሙ ፅፎ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለጠፈ ። አቶ ይርጋ ከሞቱ ወዲህ በትምህርት ቤቱ ፣ በተለይም ባስተማሪዎች ዘንድ ዲሲፕሊን የሚባለው ነገር ፈፅሞ ተበላሽቶ ነበር ። ሰአትን አክብሮ ክፍል ገብቶ ማስተማር ቀርቶአል ። በተከታታይ ለሁለት ፣ ሶስት ቀን ምንም ምክንያት ሳይሰጡ ዝም ብለው የሚጠፉም አንዳንድ አስተማሪዎች ነበሩ ። ግን ግንን ያዛል የሚል መንፈስ ባስተማሪዎቹ መካከል የተፈጠረ ይመስላል ። ታዲያ እንዲህ አይነቱ መንፈስ የተፈጠረው ያለ ምክንያት አልነበረም ። ከአቶ ይርጋ አስከሬን ላይ አፈር በተጫነ ማግስት ፣ መምህራኑ ሁለት ወይም ሶስት ላይ ተከፍለው ፣ እገሌ ዲሬክተር ይሁን ፣ የለም እገሌ ነው የሚሆነው በማለት ፣ ትምህርት ቤቱን የማስተማሪያ ቦታ ሳይሆን የስውር ሴራና የግልፅ ጦርነት መድረክ አድርገውት ነበር ። የእጅ መንሻ ጉቦ እየያዙ ወደ ጠቅላይ ግዛቱ የትምህርት ሚኒስቴር ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት የሚሮጡ መምህራንም አልታጡም ። አንዳንዶቹ ደግሞ ደጋፊዎቻቸውን ያጠጡና ያበሉ ነበር ። ተማሪዎቹን ግን ዞር ብሎ አይቶ! ሀዲስ በነገሩ ሳይገባ ገለልተኛ ሆኖ ለመቆየት ቢፈልግም ፣ የተማሪዎቹን ችግር እያየ ዝም ብሎ ለመቀመጥ አልቻለም ።

ማስታወቂያውን ወስዶ ከለጠፈ በሁዋላ ለምሳው አልሄደም ። ካንዳንድ ተማሪዎች ጋር ሆኖ በድልዳሎው ስራ ሲረዳና ሰራተኞቹን እየተቆጣጠረ ሲያሰራ ነበር የዋለው ። እንደ ቀንድ አውጣ የሚጎተተው ስራ ካሁኑ ተስፋውን ሳያመነምንበት አልቀረም ።

የቀጠራቸው የቀን ሰራተኞች ፣ ጥላው የት እንደ ደረሰ ቆመው ከማየት ሌላ ለስራው ትጋት አልነበራቸውም ። ሁኔታቸውን ሲመለከቱት ስራውን ለመስራት ሳይሆን ለመቆጣጠብ የመጡ ይመስሉ ነበር ። አብዛኛዎቹ የያዙዋቸውን አካፋና ዶማዎች ተደግፈው ስላለፈው ደግ ዘመን የሰው እድሜ ረጅም የሆነበት—ሰው ብርቱና ጠንካራ የነበረበት—ጤናና ጥጋብ የሞላበት—መተሳሰብና ፍቅር የሰፈነበት—ደግ ዘመን ነበር የሚያወሩት ።

እንደ በሬ ቱ ወደ ጉዋሮ ዞር ብሎ ከሁለት እግር ቡና ላይ አንድ እንቅብ ሙሉ ቡና በመሸምጠጥ አለም ዘጠኝ እያሉ በባዶ ኩራትና ባጉል ስንፍና ተኮፍሶ መኖር እየቀረ ሄዶአል ። እንስተኛ ገበሬ ከመሬቱ ላይ እየተነቀለ ወደ ገጠር ቦዘኔነት እየተለወጠ በመሄድ ላይ ይገኛል ። ባለፈው ደግ ዘመን ትዝታ አይኖቻቸውን ማንከራተታቸው ሀዲስን አላስደነቀውም፤ የነገውን ተስፋ የሚያሳያቸው ማንም ፣ ምንም የለም ። ለእነሱ መጪው ጊዜ እፉን ከፍቶ የሚጠብቅ ጨለማ ፣ ቀዝቃዛ ፣ አስፈሪ መቃብር ነበር ። እና ፣ ወደ ሁዋላ መሸሽ ነበረባቸው ። የሰው ልጅ ከዛሬ ነገ የተሻለ ይሆናል በሚል መንፈስ ተነሳስቶ በህይወት ላይ ፅኑ ተስፋና እምነት እንዲኖረው ምን ማድረግ ይሻል ይሆን? በማለት ሀዲስ መሬቱን በአልከ ፤ በንዴት በሃይል ይቆፍር ጀመር... ሰአቱ እንዴት እንዳለፈ አልታወቀውም ። ዘጠኝ ሰአት ሆኖ ነበር ። ወደ ስብሰባው አዳራሽ ሄደ ።

የቀረ አንድም መምህር አልነበረም ። ምን አዲስ ነገር መጣ! በማለት ወሬ ለመስማት የተሰባሰቡ ይመስላሉ ። የአቶ ይርጋ ቦታ ለማን ተሰጥቶ ይሆን? ሁሉም በጉጉት የሚጠባበቁው ወሬ ነበር ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ

መመሪያና ትእዛዝ ፥ ወይም የማስተማሪያ መሳሪያዎች ካሉ የሚሳክበት እለት ነበር ።

ሀዲስ ተነስቶ ለመናገር ሲያስብ ፤ ጋሼ 'ማይዘር' ቀደመና ፥ «የተሰበሰብንበት ምክንያት ምንድን ነው?» ብሎ ጠየቀ ።

አቶ ይርጋ ለምክትል ዲሬክተርነት እጭተውት ነበር ይባላል ።

«ቢፈቀድልኝ ምክንያቱን ላስረዳ» ብሎ ተነሳ ሀዲስ ።

«በተማሪዎች ስም ብለህ የሰበሰብከን ለመሆኑ ማን ስልጣን ሰጥቶህ ነው? ወይስ ተማሪዎች ወክሉህ?» አለው አሁንም ጋሼ ማይዘር ።

«የኔ ውክልና ለህሊናዬ ብቻ ነው።»

«ታዲያ ስለ ህሊናህ አንተው ተጨነቅበት እንጂ እኛን ምን አገባን!» ብሎ መለሰለት ።

«ይናገር !» አለ ዱቤ ።

ቤቱ ፀጥ አለ ።

ሀዲስ ንግግር አሳበዛም ፥ «መቼም እንደምታውቁት እያንዳንዳችን ለተማሪዎቻችን ሃላፊነት አለብን ። ማስተማር ከባድ ሃላፊነት ነው ። ተማሪዎች ጡቦች አይደሉም ። የነገው ህይወት ናቸው ። ያገሪቱ የወደ ፊት እድልም የሚወሰነው በነሱ ነው ።

«ስለዚህ ጊዜአቸውን በከንቱ ልናጠፋባቸው አይገባም። መስዋእት በመሆን ነጻን እያለቅን እነሱ ነገ እንዲያበሩ ማድረግ አለብን ። ለዚህም ነው አስተማሪዎች የምንደኛነት መንፈስ ሊኖራቸው አይገባም የሚባለው። የነገው ህይወት ገንቢዎች ናቸውና...»

«በሁዋላ የመጣ አይን አወጣ!» አለ ጋሼ 'ታዲያስ '።

እሱም ላስተዳዳሪነት ታጭቶ ነበር ይባላል ።

«ልጅ ለናትዋ ምጥ አስተማረች ብትል አይሻልም ወይ!» አለው 'ማይዘር' ።

ሀዲስ አልተናደደም ። ንግግሩን ቀጠለ ፥ «ይቅርታ ። ያስተማሪዎች ሃላፊነት ምን እንደ ሆነ ላስተምራችሁ አይደለም ይህን ስብሰባ የጠራሁት ። ግን ፥ አቶ ይርጋ ከሞቱ ወዲህ የነበረን የስራ ዲስፕሊን የተበላሸ መሆኑ ለማናችንም ስውር አይደለም ።

«ያለ ተመልካች ያለ ገራፊ ፥ ያለ ተቆጪና ያለ ጎትጓቾች ሃላፊነት አለብን ብለን ራሳችንን በራሳችን በመምራት ለመስራት አለመቻላችን እጅግ ያሳዝነኛል ። ምን ጊዜም ቢሆን የቅርብ ታዛቢያችን የገዛ ህሊናችን መሆን አለበት። ለህብረት ሰቡ፥ ለስራችን፥ ለወገናችን ትንጣት ታህል ሃላፊነት የማይሰማን ሰዎች አፋችንን ሞልተን ስለ ነፃነት ስንናገር በጣም ይገርመኛል !» ብሎ ቁጭ አለ ።

«አቤት ! አቤት ! እንዲህም አድርጎ የለ ቻል !» አለ 'ማይዘር' ።

«ዳግማዊ ይርጋ ! እሳቸውም 'ዲሲፕሊን !' እያሉ ነበር ጡዋት ማታ ጭንቅል ጭንቅላታችንን የሚቀጠቅጡት ።» ጋሼ 'ታዲያስ' ነበር ።

ሀዲስ በንዴት ሙክ ብሎ ፣ «እኔና እሳቸው ስለ ዲስፕሊን ያለን አስ ተያየትና አስተሳሰብ አንድ አይደለም ። እኔ የምናገረው የንጉዱቱን ኢትዮ ጵያ ለመገንባት ስለሚያስችለን ዲስፕሊን ነው ! ስለ ባሪያዎች ዲስፕሊን አይደለም !» አለ ።

«የንጉዱቱ ኢትዮጵያ!» አለ 'ማይዘር' ፣ «ስራ ላይ እንዲውል የታቀ ደውን ስርአተ ትምህርት ቢሰማ ኖር እኮ እንዲህ አይልም ነበር ። እህ... እንጨት ፈላጭ ፣ ውሀ ቀጂና የጉዋሮ አትክልት ኮትኳዋች አስተምራ ችሁ አውጡ መባሉን አልሰማህም መሰለኝ!»

ሀዲስ ከተቀመጠበት ተነስቶ ፣ «ትምህርት ቤቶች የሸቀጣሸቀጥ ፋብሪካዎች አለመሆናቸውን ... እ... የነገው ትውልድ ሰብእና በጥንቃቄ የሚታነፅባቸው ቅዱስ ስፍራዎች መሆናቸውን ካመንክበት ለምን ሀሞት ክን ኮስተር ፣ ወኔህን ጠበቅ አድርገህ አትታገልም ታዲያ ! ሀላፊነቱ የማን መሰለህ?» ብሎት ቀጠል አደረገና ፣ ስለ 'ሴክተርሪቪው' ምንነት በደንብ ሳልረዳ ልከራከርበት አልፈልግም ። እኔ እስከማውቀው እስከዚህም ከፉ አይመስለኝም» አለውና ወጥቶ ለመሄድ በር ላይ ሲደርስ አንድ አይናው እን ካሳ ዘበኛ ብቅ ጥልቅ እያለ መጥቶ ፣ ያለ ወትሮው ለጥ ብሎ እጅ ከነሳው በሁ ዋላ የታሸገ ደብዳቤ ሰጠው ። ከዘበኛነቱም ሌላ የትምህርት ቤቱ ገምጃ ቤት ቁልፍ ያዥም በመሆኑ አቶ ይርጋ ከሞቱ በሁዋላ ራሱን የቻለ ፈላጭ ቆራጭ ሆና ነበር ። ማን ተናግሮት፤ እጅ ያስነሳ እንደ ሆነ ነው እንጂ እሱ እጅ አይነሳም ነበር ።

ሀዲስ በስሙ የተላከውን ደብዳቤ ከፍቶ አነበበው...«ይህ ደብዳቤ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ የእልቁ ማርያም ትምህርት ቤት ተጠባባቂ ዲሬክ ተር ሆነው ስራዎን በትጋትና በታማኝነት እንዲሰሩ አስታውቃለሁ...» የሚል ነበር ደብዳቤው ። ከመደንገጡ የተነሳ ፊቱ አመድ ለበሰ...

የጠረጠረው አልቀረም ደረሰ ። ይህንኑ አውቆ ነው ለካ ስብሰባ የጠ ራን... እሱ ምን አለበት ። ባለ ወገን ነው... የመምህራን ማሰልጠኛ ትም ህርት ቤት በር ገጭቶት የማያውቅ ፣ ትምህርቱን ያልጨረሰ ተማሪ ይሾ ምብን?... ጉድ ነው... ምን መንግስት ፣ ምንስ አገር አለን ተብሎ ይወ ራል... እየተባለ ሲወራ ነበር የተከረመው ። ሆኖም ከስራ ገበታ ላይ ያለ ፈቃድ የሚጠፋ ወይም ስሕት አሳልፎ የሚመጣ አስተማሪ አልነበረም ። እንዲያውም ፣ አዲሱ ተጠባባቂ ዲሬክተር ማንኛውንም ችግር በግልፅ ውይይት ለመፍታት የሚያደርገው ሀቀኛ ጥረት ፣ የሚያሳየው ሀቀኛ አርአ ያነትና ትህትና አስፈላጊም ሆና ሲገኝ የሚወስደው ቆራጥ ርምጃ ፣ በመ ጠኑም ቢሆን አሉባልታን አጥፍቶ የትብብር ፣ የመግባባትና የመተማመን መንፈስ እየፈጠረ እንዲሄድ አድርጎ ነበር ። ቢሆንም ፣ «እየህ አቶ ሀዲስ ፣ አበሻ ፊት ሲያሳዩት አይወድም ። ጭፍራን መያዝ ከባድ ነው ። እለዚያ የምትለግመጣቸው መስሎአቸው ይንቁሃል ። በተለይ ደግሞ እገሌን ባይኑ ቁራኛ ያዘው ። ተንኮለኛ ነው ። ቢቻለው ሊያጠፋህ ወይም ስራህን አደና ቅፎ ሊያሳጣህ ነው የሚፈልገው ። ላንተ ብዬ ነው ። አንተ ገር የዋህ ሰው ነህ በማለት ተጠግተውት ባለ መዋሎቹ ሊሆኑ የሚፈልጉ አንዳንድ አስ

ተማሪዎች አልታጡም ። ይሁን እንጂ ፣ ሁዲስ የሚለግሳቸው ጆሮ አልነበረውም ። ስራ እጅግ ይበዛበት ነበር ።

ያስተዳደር ስራ አይወድም ። በጣም ያሰለቸዋል ። ልቡ ሁልጊዜ አዲሱ ትምህርት ቤት ስራ ላይ እንደ ተንጠለጠለ ነበር ። እና ፣ ስራው ደግሞ እንደ ምኞቱ አይሄድም — ፈቅ አይልም — ያዝግማል — ያንቀላፋል ። ዛሬ የመጣው ሰራተኛ ነገ አይገኝም ። ትናንት የነበረው ሰራተኛ ዛሬ አይታይም ። አቤት የበአላቱ ብዛት ! በአንድ ልደታ ፣ በአምስት አቡየ ማዲቁ ገዶል እንደ አከርማ የሚሰነጥቁ—በሰባት ሰላሴዎች—በአስራ ሁለት ሚካኤል—በአስራ ስድስት ኪዳነ ምህረት—በአስራ ዘጠኝ ገብርኤል—በሃያ አንድ ማርያም—በሃያ ሶስት ጊዮርጊስ—በሃያ አራት ተክለ ሃይማኖት—በሃያ ሰባት መድህኔ አለም—በሃያ ዘጠኝ በአለ እግዚአብሔር ። በዚህ ላይ ደግሞ ፣ በአለ ንግሶች አሉ ! ጥቅምት ሚካኤል— ህዳር ጊዮርጊስ — ታህሳስ ገብርኤል—ጥር ማርያም—የካቲት ኪዳነ ምህረት—መጋቢት መድህኔ አለም ግንቦት ልደታ—ግንቦት ማርያም ደብረ ምጥማቅ ፣ በአንድ ወይም በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በአላት ያላጌጠ የኢትዮጵያ ቀን የለም ። ውግዘት ። ስራ የለም ። ታቦት ይገባል ታቦት ፣ ይወጣል ። ፅዋ ካንዱ ቤት ወደ ሌላ ቤት ይገባል ። ቄስ ዳቦ ይቆርሳል ። ጠበሉን ይቀምሳል ! ይባርካል ። ጠበል ፣ ሰንበቴ ፣ ማህበር ፣ ድግስ ። መላእክቱን ፣ ቅዱሳኑን ፣ ሰማእታቱን እንደ ጠባያቸው ማባበል ፣ ማስደሰት ይኖራል ። ዋ ! እስዚያ ወደ መንግስተ ሰማያት የሚወስደውና ላንድ ጉዞ ብቻ የሚያገለግለው ‘ቲኬት’ እንዴት ይገኛል? የተኮነነች ነፍስ ! ስራ የለም !

ልደት—ግዝረት—ክርስትና—ጋብቻ—ሰርግ—መልስ ። ስራ የለም !

ሞት—ለቅሶ—ቀብር—ሀዘን ላይ መቀመጥ—ሰልስት—አስራ ሁለት አርባ—ተዝካር—ሙት አመት ። ስራ የለም !

ሽምግልና—ሙግት—አውጫጭኝ—አፈርሳታ ። ስራ የለም !

የዘመን መለወጫ ቀን—የዘውድ በአል—ገና—ጥምቀት—የሰማእታት ቀን— የድል ቀን— ፋሲካ— ንጉሱ የተወለዱበት ቀን— ቡሄ— መስቀል መጣ ። ስራ የለም !

ኮሶም የጠጡ እለትም ስራ የለም ።

ጊዜ ? ስለ ጊዜ ማን ደንታ አለው ! ጥላዎች በፈቃዳቸው ይመጣሉ ፣ ይሄዳሉ ፣ ያጥራሉ ፣ ይረዝማሉ ። ሰው ሊያሳጥራቸውም ሆነ ሊያስረዝማቸው ሀይል የለውም ። ፀሐይ ትወጣለች ፣ ትገባለች ፣ ቀን ይነጋል ፣ ይመሻል ። ወራት ይመጣሉ ፣ ይሄዳሉ ። ነፋስ ይነፍሳል ። ጊዜ ይሄዳል ። ሰው ምን ሊያደርገው ይችላል ! ለሁሉም ጊዜ አለው—የመወለድ ጊዜ ፣ የወጣት ጊዜ ፣ የማፍቀር ጊዜ ፣ የሰርግና የጋብቻ ጊዜ ፣ የእርጅና ጊዜ ፣ የሞት ጊዜ ፣ የሳቅና የሀዘን ጊዜ ። ሰው ስለ ፈለገ እህል አይዘራም ፣ በፈለገው ጊዜ የዘራውን አያጭድም ። ለመዝራት ጊዜ አለው ። ለመከር ጊዜ አለው ። ስለዚህ ምን የሚያስቸኩል ነገር አለ—የት ለመድረስ ነው? እሱ ያለው ላይቀር! ጥላዎች እየረዘሙ ይሄዱና ጀንበርዋ ስትጠልቅ ይጠፋሉ ። ስራ? ነገም ሌላ ቀን ነው ። እና ፣ ነገ ይዞ የሚመጣውን ማን ያውቃል? ሰው ያስ

ባል ፣ እሱ ይፈጽማል ። ሰራተኞቹ ሀዲስን እንደዚያ የሚያጣድፈው ነገር ምን እንደሆነ ሲገባቸው አልቻለም ።-ትምህርት ቤቱ እንደ ሆነ ሲያልቅ ያልቃል—ምኝ ! ፈረንጅ እይሉት አበሻ ፣ ምን አዲስ ፍጡር መጣብን ? ነበር የሚሉት—ከበስተጀርባው ።

ጊዜ ! ጊዜ ! ጊዜው ይሄዳል ። ግን የትምህርት ቤቱ ስራ ባለበት ቆሞ ይረግጥ ነበር ። መሰረቱ ወጥቶ ግድግዳዎቹ ብቅ ብቅ ብለው መታየት ጀምረዋል ። ግድግዳዎቹን እያየ ከአናጢዎችና ከግንበኞች ጋር ሁለተኛ ላለመዋዋል ቆሞ ይገዘት ነበር ። ሲላቸው ይመጣሉ ። ሲያሰኛቸው ደግሞ ዝም ብለው ይጠፋሉ ።

በየጠጅ ቤቱ እየዞረ እነሱን መፈለጉ ነበር ያሰለቸው ። ሰካራሞች ! ጠጅና ጠላ በማንቆርቆሪያዎች ስራ ቦታ ድረስ ቢያመጣላቸውም አልሆነለትም ። እነሱ መጠጣት የሚወዱት እዚያው እለመዱት ጠጅ ወይም ጠላ ቤት ነበር ።

ግድግዳዎቹን እየተመለከተ ቆሞ ሲተክዝ እንዳሰበው በመስከረም ወደ ዩኒቨርስቲው እንደማይመለስ ታየው ። የሰራተኛ ያለህ እያሉ የሚጮሁት ግድግዳዎች ነበሩት ። ሰኔ ሚካኤል ። ሰኔ ማርያም ። ነገሩ ሰኔና ሰኞ ሆነበት ። ሰራውን የጀመረበትን ቀን ረገመ ። ኤሎሄ! ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ! ብሎ ለመጮህ ምንም አልቀረውም ። እንባው መጣበት ።

የመኪና ድምፅ ሰምቶ ዞር አለ ። ታፈሰ ብሩ ነበር ።

ለብዙ ጊዜ ተገናኝተው አያውቁም ። እንዲያውም አቶ ይርጋ አለሙና የመቶ አለቃ እሸቴ ከሞቱ ወዲህ አልተገናኙም ። ታፈሰ ሆነ ብሎ ሀዲስን ይሸሸው ነበር ። ትንሽ ከሱቶአል ። ጠቆርም ብሎአል ። ከመሬቱ ላይ ከነ ዱላቸው ጭሰኞች እንዱ ተከቡበት ለጥቂት እንደ ሳተው ሀዲስ ሰምቶ ነበር ። ታፈሰ አውቆ የሚሸሸው መሆኑን በመገንዘብ ሄዶ እንኩዋን አተረፈህ አላለውም ። ሀዲስ ስራ እንደሚበዛበት ሁሉ ፣ እሱም እረፍት እንደ ሌለው ይሰማል ።

ታፈሰ በቡና ችግኝ ተከላ ስራ ብቻ አልነበረም ተጠምዶ የሰነበተው ። የበልግ ዝናብ ጠፍቶ አነስተኛ የቡና ገበሬዎች ከባድ ችግር ላይ መውደቃቸውን በማየት ፣ ከአዲስ አበባ እህል ፣ በርበሬ ፣ ጨው ሳሙናና የምግብ ዘይት በብዛት እያስመጣ ያለ ምንም ትርፍ ቅድሚያ ክፍያ አስፈርሞ በመስጠት የመጪውን አመት የቡና ሰብላቸውን ካሁኑ እጁ ማስገባት ጀምሮአል ።

«የእጅ ስራህን ቆመህ ታደንቃለህ?» አለው ፣ ከመሬት ብቅ ማለት የጀመረውን ህንፃ እያየ ።

«ማድነቅ አልከው! እያደማኝ ነው ። »
«ደህና ሂዶልሃል ።»
«ምን ሄደ ! የቀንድ አውጣ ጉዞ ነው ። »
«በነገራችን ላይ እንኩዋን ደስ አለህ» አለ ታፈሰ ።
«ስለ ምን?»
«ተጠባባቂ ዲሬክተር ሆነሃል አሉ ። »
«አንተም እንኩዋን ከሞት ተረፍክ» አለው ሀዲስ ተራውን ።

በፊት የሚያውቀው ታፈስ አይደለም ። ተለውጦአል ። እንደ በፊቱ እንደ መጣለት አይናገርም ። ለማለት የሚፈልገውን ነገር እያሰበ ነበር የሚናገረው ። የአዲስ ዘመን ጋዜጣ በእጁ ይዞአል ።

«ይህን ጋዜጣ አንብበሃል ?» ብሎት ጋዜጣውን ሰጠውና ፣ «በመጀ መሪያው ገፅ ላይ በስተግርጌ ስለ ትምህርት ቤትህ የተፃፈውን አንብብ» አለው ።

ሀዲስ ቸኩሎ ጋዜጣውን ዘረጋ ።

ሁለት አምድ ላይ በሰለሳ ስድስት ኮር ፊደል የተፃፈ:—
«212 ሽህ ብር የሚፈጀው የሱዱ ትምህርት ቤት ስራ ተጀመረ»
የሚል አርእስት ከጋዜጣው ላይ ብቅ ብሎ አፈጠጠበት ። ትንፋሹን ውጦ ዜናውን ያነብ ጀመር...ከአንደኛ ገፅ ጀምሮ ስምንተኛው ገፅ ላይ የሚያ ልቀውን በሰፊው የተፃፈውን ዜና አንብቦ ሲጨርስ የኮረኮሩትን ያህል እየተንከተከተ ሲስቅ ቆየና ፣ «የወረዳው ገዢ የነገሩ ባለቤት ሆኑ አይደ ለም እንዴ!» ብሎ ጋዜጣውን ሊመልስለት ሲል—«ርእሰ አንቀፁን አን ብበው» አለው ።

ሁለተኛውን ገፅ ቀሎ ብሎ ከፈተ።«ህዝቡን ለልማት ስራ የማስተባ በር ሃላፊነት» የሚል ርእስ በጉልህ ተፅፎ ይታያል ። ሀተታውን ያነብ ጀመር...

ርእሰ አንቀፁ ፣ በህዝብ መዋጮ ሱዱ ላይ የተጀመረውን ትምህርት ቤት ስራ ዜና ማስረጃ በማድረግ ይነሳና ፣ የወረዳው ገዢ ፣ ህዝቡን ለዚህ የተቀደሰ ክቡር አላማ በማግባባት ፣ በማስተባበርና በመምራት ረገድ ያሳ ዩትን ችሎታ ካደነቀ በሁዋላ ፣ ሌሎችም የህዝብ አደራ የተጣለባቸው ገዥ ዎችና ሹማምንት ፣ ቀንና ሌት ለሚወዱትና ለሚወዳቸው ህዝብ ከሚደ ክሙለትና ደከመኝ ከማይሉት ንጉሰ ነገስቱ ጎን ቆመው ፣ ለሀገሩ አንድ ነትና ነፃነት ቀናኢ ፣ የሆነውና ለንጉሰ ነገስቱ ፍቅር ታማኝነት ያለውን ጀግናውን የኢትዮጵያን ህዝብ ለልማት ስራ እንዲያስተባብሩ በማሳሰብ ሀተታውን ይደመድማል ።

«ምስጋናው ለማንም ይሁን ለማን ብቻ ትምህርት ቤቱ ይሰራ ። ግን ባልሰሩት ስራ ምስጋና መሻት ያሳዝናል ። ህዝቡ ምን ይለኛል? ብሎ ማሰ ብም እኮ ጥሩ ነበር ። ሁዋላ ትዝብት ላይ የሚጥል ነገር ነው» ብሎት ሀዲስ ጋዜጣውን ለታፈስ መለሰ ።

«የቱ ህዝብ!» አለ ታፈስ ።
«የሱዱ ህዝብ ነዋ !»

«እሱን ተወው እባክህ! በማለት አመናጨቀውና ፣ «ከፈለክ ዜናውን ልታስተባብል ትችላለህ» አለው ።

«ምን ቆርጦኝ!» አለ ሀዲስ ፣ «እኔ የምሰራው ዝና ለማትረፍ ወይም ምስጋና ለማግኘት አይደለም ። የፈለገ ሰው ሊመስገንበት ፣ ሊሾም ፣ ሊሸ ለምበት ይችላል ። የኔ ደስታ ስራው አልቆ ማየት ነው ።»

«የፈለከውማ እየ ሆነልህ ነው» አለ ታፈሰ ።
«የፈለኩት የትኛው?»

«ዛሬ ተጠባባቂ ሆነሃል . . . ነገ ደግሞ ትጠቀልለዋለህ ። ከዚያ በሁዋላ ደግሞ ምን እንደምታደርግ ማን ያውቃል?» አለና ሲጃራ ለኮሰ ።

ሀዲስ «ህም» የሚል ድምፅ ከማሰማት ሌላ ምንም አላለውም ።

«እና ፣ አካሄድህ ሁሉ አስቀድሞ የታሰበበትና የታቀደ ነው ። በፊት ሳይህ ፣ በቀን አይኑን ከፍቶ ህልም የሚያልም ሰው ትመስለኝ ነበር ።»

«አሁንስ?» አለ ሀዲስ ።
«አደገኛ ሰው መሆንክን ተረድቻለሁ።»
«እንዴት?»

«በእውነት አደገኛ ሰው ነህ» በማለት የሲጃራ ጢስ ባፉም ባፍንጫውም እያተነነ ፣ «እቶ ጣሴን ካቶ ይርጋ ጋር ፣ ወታደር ጎይቶምን ከመቶ አለቃ አሸኔ ጋር እርስ በእርስ አጋጭቶ ከባድ ጠላቶችን ከፊቱ የሚያስወግድ ሰው ክሩቅ ሊሸሹት የሚገባ አደገኛ ሰው ነው ።

«ወርካው የወደቀእለት ፊታውራሪ በነገሩ እንዲገቡበት ለማድረግ እንዴት እንደ ቻልክ እስካሁን ይገርመኛል ። ታውቃለህ? እንዲህ አይነቱ ጥበብና ዘዴ በቢሮክራሲ ቋንቋዋ «የሰይጣን አግራጭ» ይባላል ። ባጭሩ ፣ አንተ ራስህ ልታጠፋቸው ያልቻልካቸውን ጠላቶች ምቹ ጊዜና ሁኔታን ጠብቀህ በመጠቀም እርስ በርሳቸው እንዲጠፋፉ ማድረግ ነው ። የማ ጥቅም ከማን ጋር ሊጋጭ እንደሚችል በማወቅና በመጠቀም ረገድ በእውነት ተክነሃል ። እውነተኛ ገፅታህ ምን እንደ ሆነ እስካሁን ሳላውቅ በመቅረቴ ሞኝ ነኝ ። በእውነት ሞኝ ነበርኩ» አለው ።

ሀዲስ ጠጉሩን ቋፈረና ፣ «ታፈሰ አመነኝ ። አሁንም ሞኝ ነህ!» አለው ።

«አሄሄ ። ምን ነው ጃል? ስንተዋወቅ ባንተናነቅ !» አለ ታፈሰ ።
«ምናለ ብትተወኝ ! አታውቀኝም !»

«አውቅሃለሁ ። አሁን በጣም አውቄሃለሁ ። አላማችን አንድ ነው ። የምንለያይበት ነገር ቢኖር አላማችንን ለመቀዳጀት በምንመርጠው መንገድ ነው ። እኔ ፊት ለፊት መሄድን እመርጣለሁ ። የምጠላውን እጠላለሁ ፣ የምወደውን እወዳለሁ ፣ የምወስደውም ርምጃ እንደዚያው ግልፅ ነው» አለው ።

«እኔስ ?»
«አንተ ፣ ውስጥ ውስጡን የሚሽሎከለክ አባብ ፣ ያውም መርዘኛ አባብ ነህ ።»

ሀዲስ የኮረኮሩትን ያህል ክት እያለ ይስቅ ጀመረ ። እንባ እስኪወርደው ድረስ ሆዱን ይዞ ካንጀቱ ሲስቅ ፣ ታፈሰ ተናዶ ፣ «ሰው እውነቱን ሲነግሩት የኮረኮሩትን ያህል ይስቃል ይባላል» አለው ።

ሀዲስ ሳቁን አቁሞ እንባውን ጠረገና ፣ «ስማ ታፈሰ ። ስለኔ የፈለክ ውን ልታስብ ትችላለህ ። ግን ልክ አይደለህም ። ፍፁም ተሳስተሃል ። እመነኝ ። ስሞት የብር ምልክት መቃብሬ ላይ እንዲሆንልኝ የምፈልግ ሰው አይደለሁም ። ስልጣን ፈላጊም አይደለሁም ። ከዚህ የበለጠ እንዴት ብዬ እንደማስረዳህ አላውቅም ። ብታምነኝ እመነኝ ፣ ባታምነኝ ገደል ግባ!» ብሎት ሊሄድ ሲል ፣ «አሁን ወዴት ማምራት እንደ ጀመርክ አጣ ሁትና ነው !» አለው ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

ሀዲስ ቆም አለና ፣ «እንዲያውም ብታውቀው ጥሩ ነው ። ፊታውራሪ ዘንድ ሽማግሌዎች ልኬአለሁ ። ከፈለክ አንደኛ ሚዜዬ ልትሆን ትችላ ለህ ። ወደዚያ ነው የማመራው ። ግን ፣ አንተ በምታስበው ምክንያት ወይም በምትለው ነገር አይደለም ።

«ሌላም ነገር ልንገርህ ። ካቶ ይርጋና ከመቶ አለቃ አሸኔ ጋር አብረህ ተባብረህ ካገር ልታስወጣኝ ተነስተህ ነበር ፣ አይደለም ? አዎ ፣ አንተ የመቶ አለቃውን ክንድ በመጠቀም ቄሰኞችን ነቅለህ ለማባረር ስትፈ ልግ ፣ እሱ ደግሞ ባንተ ተጠቅሞ ያንትህን ልጅ ፣ ቢቻለው በህጋዊ ጋብቻ ፣ ባይቻለው ጠልፎ ለማግባት ያስብ ነበር ። በኔም ሆነ በፊታውራሪ ቤት ላይ መሳሪያ ሊያደርጉህ ነበር ። ደግነቱ ተንኮላቸው አልሰመረላቸውም ። አንተ እንደምታስበው በኔ ምክንያት አይደለም ። ለሀቅ የቆሙ ሰዎች በመኖራቸው ነው »ብሎት ጥሎት መንገድ ከጀመረ በሁዋላ ፣ ሌላ ነገር ትዝ ስላለው እንደ ገና ተመልሶ መጣና ፣ «የማጫወትህ አንድ ሌላ ነገር ቀርቶኛል ። ምናልባት ዛሬ የመጨረሻ ጊዜአችን ሳይሆን አይቀርም ብዬ ነው» በማለት ፣ በእሱ ስም ለአይናለም ስለ ተፃፈው ደብዳቤ አንስቶ ፣ ካጫወተውና ፣ ደብዳቤው ለምን አላማና በእነ ማን እንደ ተፃፈ ባጭር ባጭሩ ከነገረው በሁዋላ ፣ «ታስታውስ እንደ ሆነ ፣ አንድ ቀን ፣ ስለ አይ ናለም ምኞት አንስተን ስንነጋገር ፣ 'አንተ አያገባህም ፣ ዘዴ ይፈለግል ታል' ብለህ ስለ ነበረ ፣ ደብዳቤውን ለመቶ አለቃው ብለህ በኔ ስም የፃፍ ከው አንተ ነህ ብዬ ጠርጥሬ ነበር ። እንደ ጠረጠርኩት ሆኖ ቢገኝ ኖሮ የማደርገውን አላውቅም ነበር ። ምናልባት ዛሬ በህይወት እዚህ ቆመን አንነጋገርም ነበር ። አዎ ፣ እንዳልከው ፣ በዚህ አደገኛ መሆኔን እኔም ራሴን እየተረዳሁ ሄጃለሁ» ብሎት እየቸኮለ ጥሎት ወደ ቤቱ ሄደ ።

ፊታውራሪ ተካ ዘንድ የላካቸው የነገር አባቶች መልስ ይዘው የሚ መለሱበት ሰአት ተቃርቦ ነበር ። ሰራተኛው ፣ የረጋሳ እናት ፣ ሽር ጉድ ትላለች ።

«ቡናው ፣ ቁርሱ ፣ ጠላው እንዴት ነው?» አላት ።
«ሁሉም ደርሷል» አለችው ።

ቤቱን የአውደ አመት ቤት አስመስላዋለች ። የእጅ ሰአቱን ተመል ከተ ። ወደ መስኮት ሄዶ መንገድ መንገዱን እያየ ፣ በታፈሰ ብሩ ነገር በመ ናደድ ፣ አንዱ የሌላውን ልብ እንዴት አድርጎ ለማወቅ ይቻል ይሆን ! ሰው ጨው አይደለም ፣ ተቀምሶ እንዳይታወቅ ! ምን ብናደርግ ይሻል ይሆን? እያንዳንዱ ሰው የከፋትን መንገድ ትቶ ደግ ደጉን ማሰብ ቢጀምር ይህ ህይወት ፣ ይህ አለም ምንኛ ጣፋጭና ውብ ፣ የሰው ሞቱ ምንኛ ክቡር በሆነ ነበር ! አለ ። ሰው ባልገባውና በማያውቀው ነገር ፣ በዚች ውብ ምድር በዚች የጋራ አለም ፣ ያውም ለዚች አጭር ህይወት ፣ አንዱ ለሌላው እቶን እሳት ፣ ገሃነም ሆና ገሃነም የሚፈጠርበት አሳዛኝ ሁኔታ አሳዘነው ።

እንደ ገና የእጅ ሰአቱን ተመለከተ ። እነዚህ ሰዎች ምን ነካቸው? አለ
መንገድ መንገዱን እየተመለከተ ። ከላካቸው ሽማግሌዎች መካከል ፣ በተ
ለይም ሁለቱ ፣ ነገሩ ይህን ያህልም ደስ ሳይላቸው ነበር ሃላፊነቱን በቅሬታ
የተቀበሉት ። አፍ አውጥተው ባይነግሩትም ፣ በዝምታ ፣ ሆ! የፊውታራሪ
ተካ ቦርኬጀርሶን ልጅ? እንዴት ይሆናል? የሚሉ ይመስሉ ነበር። ሃምሳ አለቃ
ጎይቶም ፣ 'ዋእ ! ከሆነ ፣ ሆነ ፣ ካልሆነም ችግሩ ምንድን ነው? በጎ መመ
ኘት ድፍረት አይደለም' በማለት ደፍሮ ባያደፋፍራቸው ኖሮ በጣም ፈር
ተው ነበር ።

ጎይቶም ከእነሱ ጋር በመኖሩ ደስ አለው ሀዲስ ። ጎይቶም እጁን ሰጥቶ
ጉዳዩ ሲመረመር ከቆየ በሁዋላ በነፃ ከመለቀቁም በላይ የሃምሳ አለቅና
ማእረግ ከተሰጠውና ወደ ቡኢ እንዲመለስ ከተደረገ ሰንብቶአል ። እና ፣
ሀዲስ ፖሊስ ጣቢያ ድረስ እየተመላለሰ ስለ ጠየቀውም ይሁን ወይም
በሌላ ፣ በሁለቱ መካከል የተፈጠረው ዝምድና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠነከረ
ይሄድ ነበር። — እነዚህ ሰዎች ምን ነው የቀሩ መላክተኛ ሆኑብኝ? በማለት
እነሱን መጠበቁ ሰልችቶት ከመስኮት ላይ ዞር ሊል ሲል የነገር አባቶቹ
ሲመጡ በሩቅ አያቸው ።

አይን ውሆቸው ደስ አላለውም ። ውስኪ ከፈተ ። ሰራተኛውም ትኩስ
ምግብ ካቀረበች በሁዋላ እየ ፎከረ የሚደነፋ የቡና ጀበና ይዛ ቀረብ አለች ።
ውስኪው ፣ ጠጁ ፣ ጠላው ተቀዳ ። የእጣን ጢስ ቡልቅ አለ ።

ሀዲስ ልቡ ተሰቅሎበት እህል አልዋጥለት እያለው ይተናነቀው
ነበር ። የምስራች ሳይሆን መርዶ ይዘው የመጡ ይመስላሉ ።

ሃምሳ አለቃ ጎይቶም ነበር መጀመሪያ የተናገረው ። የአስመራ ቡና
ጀበና ትንሽ መሆንዋንና ቡናውም የሚቀዳው ባፍዋ እንደ ሆነ ሲያስረዳ
ከቆየ በሁዋላ ፣ አዲስ አበባ ደርሶ የቡና ጀበና ባየ ጊዜ በመረገም ፣ «ዋእ !
ተባዕታይ ጀበናውን ዶ እሉ እዩ !...ወንዴ ጀበናም አለ እንዴ ! ብዬ
ለመናገሬ ዘመዶቼ 'ወንዴ ጀበና ! ' እያሉ ሲስቁብኝ ይኖራሉ» ብሉ አሳ
ቃቸው ።

ሶስቱም ቁርሱን እምብዛም አልተዳፈሩትም ። የበረቱት ውስኪው
ላይ ነበር ። ማእዱ ተነስቶ ጣታቸውን ከታጠቡ በሁዋላ ግን ቀድሞ ይና
ገር በማለት ሳይሆን አይቀርም እርስ በርሳቸው ይተያዩ ጀመር ። የሀዲስ
ልብ ቀጥ ልትል ምንም አልቀራትም ። መልሱ ያም ይሁን ይህ ደንታ
አይኖረኝም በማለት ራሱን ሲያደፋፍር የቆየው ሰው አሁን ሰአቷ ስት
ደርስ ድፍረት አነሰው ።

ከሶስቱ በእድሜ የሚበልጡት አረጋዊ ጉሮሮአቸውን በትንፋሻቸው
ጠረጉና ፣ «ልጃችን እንኳዋን ደስ ያለህ ። እኛም ደስ ብሉን ነው የተመ
ለስነው ። እሳቸውም እንዳከበሩን ያክብራቸው ። አላሳፈሩንም» ካሉ
በሁዋላ ፣ እንደ ገና ጉሮሮአቸውን ጠረጉና ፣ «ቢሆንም አንድ ገደብ አድር
ገውብታል ። ይኸውም ልጅትዋን በምንም ሁኔታ ካጠገቢ ይዞአት እንደ
ማይሄድ ቃል ይግባ የሚል ነው ። ይህን ካደረክ ፍጥምጥሙም ሆነ ሰርጉ
ጥንድ ቀን በሚቀጥለው ወር ሲሆን እንደሚችል ቃል ሰጥተውናል ። መል
ሱን ልክ የዛሬ ሳምንት ይዘን እንድንመለስ ጠይቀውናል» አሉት ።

አረጋዊው ባሉት ሶስቱም መስማማታቸውን በመግለጥ በአዎንታ ራሳቸውን ነቀነቁ ።

«እሺ ። አስቤበት መልሴን እነግራችሁዋለሁ» አለ ሀዲስ ፥ በደስታ ተውጦ ።

«ዋአ ! ምን የሚታሰብበት ነገር አለ? ያሉህን እሺ ብለህ መቀበል ነው እንጂ ።» የማምሳ አለቃ ጎይቶም ነበር ።

አረጋዊው በጎይቶም አሳብ አልተስማሙም ። «እሱ ያለው ይሻላል ። ያስብበት ። ቃል ቃል ነው» አሉ ።

የሀዲስ ጎረቤት የሆኑት ሶስተኛው ሽማግሌም ፥ «አስቦበት መልሱን ይስጠን» በማለት ከአረጋዊው ጋር ባሳብ ተስማሙ ። ብዙ መናገር አይወዱም ። ፊታውራሪ ተካ እሺ ይላሉ የሚል እምነት ባይኖራቸውም አረጋዊው ሰው በሽምግልናው እንዲገቡ ያደረጉት እሳቸው ነበሩ ። እንደ ተለመደው ማመልከቻ ሲፅፍላቸው ነበር ነገሩን እንደ ቀልድ ያነሳባቸው ። ስለሚወዱት ነገሩ አይሆንም ሊሉት አልፈለጉም ። «የሰው መውደድ ያለው ሰው ምን አጣሁ ሊል ይችላል?» በማለት በመጨረሻ የተናገሩትም እሳቸው ነበሩ ።

ቀን መጣ ። ቀን ሄደ ። ሽማግሌዎቹም መልሱን ለመስማት ተመልሰው የሚመጡበት ቀን ደረሰ ። ቁርጥ ያለ መልስ አልነበረውም ። ግማሽ ልቡ — ከምወዳት ልጅ ጋር እዚህ ቀርቶ የትስ ሄጄ ብኖርም ናለበት? ከሚወዱዋት ልጅ ጋር ውለው የሚገቡበት ጎጆ ሁሉ ትንሽ ገነት ነው ። ሌላ ምን እፈልጋለሁ? ብርቅ የኢትዮጵያ ቶጳዝ! የግላችን የሆነች ትንሽ ቀዬ — ትንሽ ገነት ። ፍቅር ። በዚህም አለም ከፍቅር የበለጠ ውድ ነገር ምን አለ? በማለት ራሱን አግባብቶ ማሳመን ላይ ሲደርስ ሲል፥ሌላው ግማሽ ልቡ ደግሞ— ምን ብርቅና ውድ የኢትዮጵያ ቶጳዝ መስላ ብትታይህ ፥ ምን ብትወዳት ፥ ለእስዋ ብለህ በነፃነትህ ላይ መደራደር የለብህም ! ፍቅር ምንድር ነው ያለ ነፃነት ? ሀብት ምን ዋጋ አለው ያለ ነፃነት? ገነት ያለ ነፃነት ያው ገሃነም ነው ። ምን ጊዜም ቢሆን ሰው ከሰውነቱ ያንሳል ፥ ያለ ነፃነት ። ማን ነው በነፃነቱ ላይ ተደራድሮ በደስታ እኖራለሁ ለማለት የሚችለው ? ሰው ከሆነ ማንም ! ፍቅር እግረ-ሙቅ አይደለም ። እስረኛ ሊያደርገኝ አይገባም ። በፍቅር ስም ፥ ለፍቅር ስል የባርነት ቀንበር በወደ ፊት ህይወቴ ላይ አልጥልም ፥ እያለ በተከፋፈለ ልቡ ከራሱ ጋር ተጨንቆ ሲሙዋገት ሽማግሌዎቹ መልሱን ከእሱ ለማወቅ ተመልሰው የሚመጡበት ቀንና ሰአት ደረሰ ።

በሁለተኛው አሳቡ ፀና ። ፊታውራሪ ተካ ያደረጉለትን ገደብ ለመቀበል እንደማይችል ነገራቸው ። ሶስቱም በመገረም አፋቸውን ከፍተው ይሰሙት ነበር ። በመጨረሻ ፥ «ይሄው ነው ። አዝናለሁ ። የማምንበት ነገር ሆኖብኝ ነው ። ነፃነቴን ሊጋብቻ ብዬ አልለውጥም ። እንዲያው በውሸት እሺ ብል ህሊናዬ ይወቅሰኛል ። እሳቸውንም ልዋሻቸው አልችልም ። እንዲያው በከንቱ አለፋሁዋችሁ» አላቸው ።

ይህ ሰው እብድ ነው ወይስ ጤና? የሚሉ ይመስሉ ነበር ። አሳቡ ሊገባቸው አልቻለም ። «ምን ቸገረህ ፥ እሺ በል ። ፊታውራሪ ይሆን አሉ ወይም አላሉ ሰው የሚኖረው እህልና ውሀው ባለበት ቦታ ነው» በማለት ሊያግ

ባቡት ቢሞክሩም አልሆንላቸውም ። ማምረሩን በማየት ተነስተው ሄዱ ። ከልቡ ላይ ትልቅ ሸክም የወረደለት ይመስል በደስታ ተነፈሰ ። በመሆኑም ሽማግሌዎቹ ከፊታውራሪ ዘንድ ያመጡት መልስ ምንም አይነት ቁጭትና ፀፀት አላሳደረበትም ። ፊታውራሪ ባጭሩ የሰጡት መልስ ፣ «ምን ሲደረግ ! ፈፅሞ አይታሰብም !» የሚል ነበር ።

መልሱ ይህ ብቻ እንዳልሆነ ሳይሰማው አልቀረም ። ነገሩን ክብረ ነክ አድርገው ስለሚመለከቱት ፣ ተናደው ፣ «ይህ መናጢ የድሀ ልጅ ፣ ፊት ባሳየው ለዚህም በቃ ! ወይ መዋረድ ! እንዴት ቢንቀኝ ነው እንዲህ ያለ መልስ ደፍሮ የሚልክብኝ ! ባለጌ የባለጌ ልጅ !» ብለውት ይሆናል በልባቸው ። ያሉትን ቢሉ ደንታ አልነበረውም ። ተልእኮአቸው ጫፍ ከደረሰ በሁዋላ ሳይሳካ በመቅረቱና ሽማግሌዎቹ ስላዘኑ ብቻ ነበር ቅር ያለው ። በተለይ ሁለቱ ሽማግሌዎች የፊታውራሪን ዝምድና በጣም ፈልገው ነበር ። ሳይሆን ቀረ !

የጋብቻውን ነገር እርግፍ አድርጎ ወደ ሁዋላ ስለ ተወ ፣ የትምህርት ቤቱን ስራ ከፍፃሜ ለማድረስ የበለጠ ነፃነት አግኝቶ ነበር ። ትምህርት ቤት ለክረምት ወራት ከተዘጋ ቆይቶአል ። የማስተማርና የቢሮ ስራ ቀርቶለታል ። መላ ጉልበቱንና አእምሮውን በትምህርት ቤቱ ስራ ላይ ለማዋል አመች ጊዜና ሁኔታ ቢኖረውም ስራው እንደ ልቡ ምኞት አልሄድ እያለ እንደ ቀንድ አውጣ ስለሚጎተትበት ፣ አናጢዎች ሲጠፉ አናጢ ፣ ግንበኞች ሲቀሩ ግንበኛ ፣ አንዳንድ ቆፋሪዎችና ተሸካሚዎች ሳይገኙ ሲቀሩ ቆፋሪና ተሸካሚ እየሆነ በዝናብና በፀሀይ ነግቶ እስኪመሽ ድረስ ይሰራ ነበር ። በማንኛውም የቤት ስራ ሙያተኛ ሊሆን ምንም አልቀረውም ። እጆቹ መጅ አውጥተው ገብረዋል ። እንጨት እየ ነከሱ አንንታን ቅልህም በማለት ያላግጡበት የነበሩት ማጋዝና መላጊያ እንደ ልቡ እየታዘዙት በእጁ ላይ ልክ እንደ ሸማኔ መወርወሪያ 'ሸው ሸው' ማለት ጀምረዋል ። ባንድ ማእዘን ላይ ከሶስት እስከ አራት ምስማሮች እያጣመመ ያበላሽ ነበር ። አሁን እያንዳንዱዋን ምስማር ይዞ በመዶሻ እያስተካከለ ጭንቅል ጭንቅላትዋን ሲወቅራት ወለም ዘለም ሳትል ቀጥ ብላ ትገባለች ። ግን ምን ያደርጋል ! ስራው ፈቅ አይልም ። ከሁሉም ነገር በይበልጥ አናዶ አንጀቱን የሚያቆስለውና የልብ ቃር የሚያስይዘው አናጢዎችና ግንበኞች አጣመው የሚሰሩትን ስራ እየተከታተለ ማቃናቱ ነበር ። ውሀ ቅዳ ውሀ መልስ ። ገንብቶ ማፍረስ ። አፍርሶ መገንባት ። ሀሙስን ያሳለፈው በዚህ ሁኔታ ነበር—አፍርሶ በመገንባት ።

ግንበኞቹም ሆኑ አናጢዎቹ አንዱን ግድግዳ አጣመው ስለ ሰሩት ተናዶ ነበር የዋለው ። —እንከን የማይወጣለት ክብ ወይም ቀጥ ያለ መስመር ለመስራት በማይቻልበት ሁኔታ ምን አይነት ስልጣኔ ለመገንባት ይቻላል! ይል ነበር እየደጋገመ ። ግድግዳው ፈርሶ እንደ ገና መሰራት ነበረበት ። የግንበኞቹና ያናጢዎቹ አይኖች ጦር ቢሆኑ ኖሮ በስንት ጦር ተወግቶ በሞተ ነበር !

ሰውነቱ ቢደክምም አእምሮው አላርፍ ብሎ ስላስቸገረው እንቅልፍ ሊወስደው አልቻለም ። ተነስቶ ውጭ ሲወጣ ደስ የሚል ውበት የተጎናፀፈች ሙሉ ጨረቃ ሳቅ ብላ እንደ ምን አመሸህ? አለችው ። ጨረቃዋ ዙሪያ ሰማያዊ እንቁዎች መስለው የተርከፈከፉት ከዋክብትም እየጣቀሱት ታዲያስ ጃል? ይሉት ነበር ። የልቡን ሀዘን እንቆረቆረላቸው . . .

ባለ ዋሽንቱም ቀጠሮውን ጠብቆ እሩት ከግር ጨወታውን ማንቁርቁር ጀምሮአል ። ጨለማውን ይዳስሳል ። ወደ ሀዋው ይመጥቃል ። ጨረታዎቹንና ከዋክብቱን እየ ኮረኮረ ያሳስቃቸዋል ። ሴሎቹ የት ሄዱ? ተስማምተው ለሶስት ህብረ ዜማ መፍጠር ጀምረው ነበር ። ሀዲስ ጆሮዎቹን አንቅቶ ሲጠባበቃቸው ቆየ ። ብቅ አላሉም ። ይልቅ ያባ ጨሬ ተናዳጅ ድቢ ድው ! ድው ! እያለ የጨለማውን ልብ ትርታ ሲያስተጋባ ይሰማ ነበር ። ንፋሱ በጣም ብሶበት ነበር ። የገባ በረሃ አጋንንት አንድም ሳይቀር ስምቶ ጭራውን እየቆላ አገር እንዲያተራምስ የሚፈልግ ይመስላል—ድሲታወጣ ያ እብድ አውራ ዶሮ ሙሽ ። የመንደሩ ዶሮዎች ውሽቱን እየተቀበሉ አስተጋቡ . . . እና ፣ አንድ ሰው ወደ ቤቱ አቅጣጫ ሲመጣ አየ ።

«ማን ነው !»

መልስ አላገኘም ።

ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ፣ «ማን ነው !» አለ እንደ ገና ።
«ማን ቢሆን ደስ ይልሃል?»

የሴት ድምፅ ነበር ። ሽታዬ ነበረች ።

ተያይዘው ወደ ቤት ገቡ ። ከንፀንብዋን ስታነሳ በማሾው ብርሃን ፊትዋ ፈካ ። አይኖችዋ ቦግ ፣ ጥቁር ረጅም ጠጉሩዋ ዝንፍል ብለው ታዩት።

«ዛሬ ከየት ተገኘሽ ?»
«ከሰማይ ።»
«እንደ ሁብስተ መና !»
«አዎ ።»
«ፍቅር መራቤን እግዜር ሰምቶአል በይኛ !»
«ፍቅር የት ታውቅና !»

ትላልቅ አይኖችዋ ውስጥ የሆነ ትንኮል ብልጭ እያለ ከመቅዕበት ተመልሶ ድርገም ብሎ ሲጠፋ ይታያል ። ምን ሰምታ ይሆን ? አለ በልቡ ። አይኖቹ ጥፍሮችዋ ላይ አረፈ ። ደም ተነክረው የወጡ ያውሬ ጥፍሮች ይመስላሉ ።

«እውነት ፣ ምን ነው ፣ ደህና ?» አላት ።
«ካንተ ጋር ለማደር ነው የመጣሁት ።»
«በምን እድሌ ።»
«ምን ነው ጠፋህ ልጄ ?»
«ስራ እየበዛብኝ ነው ።»
«የምን ስራ ?»
«የትምህርት ቤቱ ።»

«ስለ እሱ መስማት አልፈልግም» አለችው ፣ እንደ መነፋነፍ አድርጋአት ።

«ታዲያስ ? ቁጭ በያ ። ራት ይቅረብልሽ ?»
«ማታ ፣ ማታ አልበላም ። ስንቴ ልንገርህ!?»

«አዎ ፣ ራትሽ ፍቅር ነው ። ይቅርታ» ብሎአት ፣ ከብርድ ለማላቀቅ እጆቹን እያፋጨ ፣ «ወይዘሮ ዝናሽ እንዴት ናቸው?» ብሎ ጠየቃት ።

—እንኳልህ ! ሂድና እስዋን ጠይቃት የምትል ይመስል ትክሻዋን ነቅንቃበት ዝም አለች ።

«የምትጠጭውስ ነገር? ውስኪ አለኝ።»
«ይሁን በልጣኔ ነው ።»

ከላካቸው ሽማግሌዎች ጉብዝ የተረፈውን ውስኪ አውጥቶ ለስዋም ለራሱም ቀድቶ ሲያበቃ ብርጭቆዋን ሰጣትና ፣ «ለጤናችን» ብሎአት የራሱን ብርጭቆ ከፍ አደረገ ።

ዝም ብላ የብርጭቆዋን ከንፈር በከንፈርችዋ እንደ መሳም እያለች ውስኪውን ተጎነጨች ። ያ አይኖችዋ ውስጥ የሚጫወተው የሆነ ተንኮል አልጠፋም ። ብልጭ እያለ ተመልሶ ድርግም በማለት ይጠፋል ። ሆኖም የመከፋት ምልክት ክብ ፊትዋ ላይ አይታይም ። እንዲያውም ደስ ያላት ትመስላለች ።

«አንድ ነገር ልንገርህ ?»
«ምንድ' ነው?» አላት ፣ የምትለውን ነገር ቶሎ ለመስማት ጉጉቶ ።

የብርጭቆዋን ከንፈር ቀስ ብላ በከንፈርችዋ እየዳበሰች ስታስብ ቆየችና ፣ «ይቅር ። አሁን አይደለም ። ሁዋላ» አለችው ።

ወሽመጡ ቁርጥ ብሎ ፣ «እሺ ፣ እንደ ፈለግሽ» አላት ።

ብዙ መናገርም የምትፈልግ አትመስልም ። ካጥብዋ ጋር እንደምትጫወት ፊትዋ ላይ አንዳፍታ ፈካ ብሎ ወዲያው ተመልሶ የሚጨልመው ደከም ያለ ፈገግታ ያመለክታል ። እንዲያ እያሰበች ብርጭቆዋን በከንፈርችዋ ቀስ ብላ ስትዳስስ ማየት ደስ ይላል ። ብርጭቆ እያያዝዋ ጭምር ልብ ይማርካል ።

«ስቲ ስለ ራስሽ አጫውቺኝ» አላት ።
«ምን ታሪክ አለኝ ብለህ ነው ?!»

«ሰው ብርጭቆ አይደል—ተገዛ ፣ ተሰበረ ተብሎ ታሪኩ የሚያልቅ ። እንዴት ታሪክ የለሽም ?» በማለት ስላስቸገራት ስለ ራስዋ አንዳንድ ታሪክ አንስታ ታጫውተው ጀመር ።

የተወለደችው በጎጃም ጠቅላይ ግዛት ብቸና አውራጃ . . . . . . በምትባል መንደር ነበር ። ስለ እድሜዋ አላነሳችም ። አባት እናትዋ በህይወት ይኑሩ አይኑሩ የምታውቀው ነገር የለም ። ከተለየቻቸው ብዙ ዘመን ሆኖአል ። ቤተሰብዋ በጣም ጎስቋዋላ ስለ ነበረ ፣ ኑሮ መሮአት እንጀራ ለመፈለግ ነበር አንድ ቀን ከቤት ኰብልላ የጠፋችው ። ከሁዋላዋ የተወደችው አንድም ቅር የሚያሰኛት ነገር አልነበረም ። የወደፊት ህይወትዋን ዱካ እየተከተለች ነበር የምትሄደው—ከጎስቋዋላ ህይወት ፣ ከተወለደችበት መንደር ፣ ካደገችበት ወንዝ እየራቀች . . . እየራቀች ።

በልብዋ አንድ ተስፋ ይዛ ነበር ከቤት የወጣችው ። ቆንጆ ቤት የትም ብትሄድ እንጀራ አታጣም እየተባለ ሲነገር ትሰማ ነበር ። እና ፣ ቆንጆ ፣ የወጣላት ቆንጆ ነበረች ።

ግን ፥ ቆርጣ ከቤት እንድትወጣ ያደረጋት ፥ በመልክ ከሆነ እዚህ ግቡ የማይባሉ የውሻ ቂጣ የመሰሉ የመንደርዋ ሴቶች አዲስ አበባ ከርመው ሲመለሱ ፥ በጥልፍ ቀሚስና በጥበብ ነጠላ ተንቆጥቁጠው ፥ በወርቅ እምባር ድሪና ጌጣ ጌጥ ነደው ፥ እንቁጣጣሽ መስለው ለህዳር ጊዮርጊስ ወይም ለጥር ማርያም ብቅ ሲሉ ስታይና ስለ እነሱ በመንደሩ የሚነዛው ወሬ ጆሮዋ ሲገባ በልብዋ ያድር የነበረው ቅናትና ተስፋ ነበር ። እንደ እነሱ እንቁጣጣሽ ፥ የመስቀል አበባ መስላ ወደ መንደርዋ ስትመለስ ሁል ጊዜ በአይነ ህሊናዋ ይታያት ነበር ። ነገር ግን ያ ጌጥ ሁሉ እንዴት እንደሚገኝ የነገራት ሰው አልነበረም ። ወደ አዲስ አበባ ወጣ ካሉ ፥ ሀር ስጋጃ ላይ የሚያስተኛና በወርቅ የሚያስጌጥ ባል መንገድ ላይ የሚገኝ ይመስላት ነበር ።

ሁሉም ነገር እንዳሰበችውና እንደ ተመኘችው አልሆነም ። ከመንደርዋ ውጭ የገጠማት አለም የባሰ መራራና ጭካኔ የተሞላበት ነበር ። ጠጅ ቀጂነት—እምቡላ እምቡላ ያለ ህይወት ። ግርድና—ከዘመናዊ ባርነት ያላነሰ ኑሮ፤ለብልግና እንጂ ለሚስትነት የሚፈልጋት ወንድ የትም አሳጋጠማትም ። ሁሉም ርካሽ ስሜቱን በርካሽ ዋጋ አርክቶ ዞር ለማለት ነው የሚፈልገው ። ጨወታው እያደረ ቢገባትም እንደ እድል ሆኖ የታወቀች ሸርሙጣ ለመሆን እንኳዋን አልቻለችም ። ወንዶችን ማታለልና ማጭበርበር ፈፅሞ አይሆንላትም ። ሙያው የሚጠይቀውን መሰረታዊ ዘዴና ስልት ለመጠቀም ባለመቻልዋም ብርና ጌጥ ማካበት አልሆንላትም ። እፍንጮ በር በኩራዝ ቤት ኑሮ መራራ ህይወትዋን ስትገፋ ከዝናሽ ጋር ትተዋወቃለች ። ጎረቤቶች ነበሩ ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ የእንጀራ ገመዳቸው ይተሳሰራል ። ዝናሽ ነበረች ሱጴ እንድትመጣ ያደረገቻት ። በመጨረሻ በረጅሙ ተነፈሰችና ፥ «እና ፥ ይሄውልህ እዚህ ነኝ ። ፍለጋ የወጣሁት ቆንጆ ባል አልተገኘም ። የልጅነት ወዜ ተሙዋጠ ፥ ውበቴ በልዞ ጠፍቶ ባዶ እጄን ዘመዶቼን ተመልሼ ሄጄ እንዴት አያቸዋለሁ? መንደሩስ ምን ይለኛል? በማለት እንደ ወጣሁ ቀረሁ» አለችው ።

«አሁንም ቆንጆ ነሽ ። የፈለግሽው ባል አንድ ቀን ይገኝ ይሆናል» አላት ።

ከት ብላ ሳቀች ። ካንጀትዋ አልነበረም የሳቀችው — የቀልድ ሳቅ ነበር ። ቀጥሎ ምን እንደሚላት ሲያስብ አንድ የሆነ ነገር በሃይል ሲፈነዳ ሰማ ። የመንደር ውሾች እየተቀባበሉ ጮኹ ። ያ መከረኛ ዶሮም ጮኸ ። ሌሎችም ተቀበሉት ። ያባ ጨፌ ድቤ ንዴት አይሉ ነበር ።

አልጋ ላይ ወጡ ። እንባዋም ወደ ጆሮግንድዋ ይፈስ ነበር ። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ሳቁዋን አቆመች ። አይኖችዋም ደረቁ ። «ነገ ጡዋት መሄዴ ነው» አለችው ድርቅ ባለ ድምፅ ።

«የት?»
«ወደ መቂ።»
«ለምን?»
«ባል ላገባ።»
«ትቀልጃለሽ?»
«የለም ፥ እውነቴን ነው ። ጥሩ መ ሳሕ የምሆን አይመስልህም?»
«በጣም እንጂ!»

«እውነቴን ነው ። ጥሩ ሚስት ይወጣኛል ።»
«ለመሆኑ ማን ነው እሱ ? እድለኛ ሰው መሆን አለበት ።»

«ታውቀዋለህ ። ዮሀንስ ጴጥሮስ ነው ። ይጠብቀኛል ። ነገ በሌሊት ተነስቼ ነው የምሄደው ። ልሰናበትህ ነው የመጣሁት ። ልሰናበትህ ለምን እንደ መጣሁ ግን አላውቅም» አለችው ።

የለቅሶ—የሳቅ—የንዴት—የሀዘን—የትኛው ስሜት እንዳደረባት ለይቶ ለማወቅ አልቻለም ። አይኖቹን ጣራው ላይ ተክሎ ዝም ብሎ ቀረ ።

«ምን ነው ዝም አልክ ?»
«ምን አልሽ ?»
«ለምን ዝም አልክ ?»

«ምን ማለት እችላለሁ ? አንዳንድ ጊዜ ለሚሰማን ነገር ቃላት ማግ ኘት ያስቸግራል ። ለማንኛውም ነገር መልካም እድል እመኝልሻለሁ ። አሁንማ እህትና ወንድም ሆነናል» አላት ።

«የማዝነው ለወይዘር ዝናሽ ነው . . .»
«ያውቃሉ መሄድሽን ?»

«የለም ። አታውቅም ። እንድታውቅም አልፈልግም ። ካወቀች አትለቀኝም ። ተደብቄ ነው የምሄደው ። እየመጣሁ እጠይቃታለሁ» አለችው ።

ለረጅም ጊዜ ሲጨዋወቱ ቆዩ ።

ማልቀስ ጀመረች ። ለረጅም ጊዜ አንገቱ ስር ተሸጉጣ አለቀሰች ። በዚያው እንቅልፍ ወሰዳት ። እሱም እንቅልፍ ወሰደው ።

ስትቀሰቅሰው ለጥቂት ደቂቃዎች እንኳዋን እንቅልፍ የወሰደው አልመሰለውም ። ሆኖም ጎህ ሊቀድ ደርሶ ነበር ።

የሚተናነቃትን እንባ በግድ እየዋጠች ፥ «ደህና ሁን ። ባይነ ስጋ ያገናኘን» አለችው ።

«ቆይኝ ብሎአት ሳጥኑን ከፈተና ሁለት መቶ ብር አውጥቶ ሰጣት ።»

መልሳ ወረወረችለት ።

«ላባክሽ ፥ ለስንቅ እንዲሆንሽ ነው ።»
«የት የምሄድ መሰለህ!»

«ቢሆንም ። እባክሽ ለኔ ስትይ» ብሎ አስጨንቆ ያዛት ። ሳትወድ በግድ ተቀበለችው ። አንቆ እያገላበጠ ሳማት ። እንባውን ለመቆጣጠር አልቻለም ። ወጥታ ሄደች ። ከአይኖቹ እስከትሰወር ድረስ በር ላይ ቆሞ እንባ በቋዋጠሩ አይኖቹ ተከተላት ። ከሚሰጻ ጭጋግ ውስጥ ገብታ ጠፋች ። «ሽታዬ!» ስምዋ አፉ ውስጥ ቀረ . . .

ጊዜ አሳጠሩም ። ቶሎ ተጣጥቦ ተነሳ ። ገረዱ ቁርስ አቀረበችለት ። እንደ ጅብ ነበር የሚበላው ። ታዲያ ገረዱ ደስ ይላታል ። ቁርሱም ከቀን ወደ ቀን እየበዛ ይሄድ ነበር ። ቁርሱን በልቶ ወደ ስራው ሮጠ ።

ብዙ የመንደሩ ሰዎች ካዲሱ ትምህርት ቤት ዙሪያ ተሰብስበው ጠበቁት ። «ምን መጣ» በማለት እንደ ሮጠ መጥቶ ከመካከላቸው ዘሎ ገባ ።

አይኖቹን አላመነም ። አይኖቹን ብልጥጥ አደረገ ። አፉም እየተከፈተ ይሄድ ነበር ። መጥፎ ህልም የሚያይ ነበር የሚመስለው ። ነገር ግን ነገሩ ህልም አይደለም ። ያደረበት ድንጋጤ ብርክ አስያዘው ። ተንገዳገደ ። ጉልበቱ ከስር ሊከዳው ምንም አልቀረውም ። ራሱን በሁለት እጆቹ ጭምድድ አድርጎ ይዞ በዝምታ እንባውን አፈሰሰ ።

የትምህርት ቤቱ አንድ ግድግዳ ግማሽ ጎን ፍርስርሱ ወጥቶ እንዲል ነበረ ሆኖአል ። ባለፈው ሌሊት የሰማውን ፈንጂ አስታወሰ ። እና ፥ ከውስጥ ሰውነቱ ፈነዳ ። ግማሽ አካሉ በፈንጂ ፈርሶ ታላቅ ሰታይ ላይ ያለ ይመስል ሰትሰቅ ፥ ሀቅ እያለ ያለቅስ ጀመር ። እናቱ የሞቱ እለት እንኳ ያንን ያህል አላለቀሰም ። ፍርስራሹን ለማየት የፈራ ይመስል አይኖቹን ጨፍኖ ነበር የሚያለቅሰው ።

የሆነ ሰው ትከሻውን ሲነካው ተሰምቶት በእንባ የራሱትን አይኖቹን በግድ ከፈተ ። ፊታውራሪ ተካ ነበሩ ። አካባቢው በሰው ተሞልቶ ማሰዳ የቆመ የደራ ገበያ መስሎአል ።

«አይዞህ ። እንዴ ! ግንብ ሰው አይደል ፥ ቢፈርስም ይሰራል» አሉት ።

መሀረቡን አውጥቶ እንባውን ጠረገና ፥ «እንዴት እንዲህ ያለ ወንጀል ይሰራል ! እኔን ቢገድሉኝ ምን ነበረበት ? ወይስ በገዛ ልጆቻቸው ላይ የፈፀሙት ወንጀል መሆኑን አጥተውት ነው !» አለ ምርር ብሎ ፥ ወባ እንደ ያዘው ሰው መላ ሰውነቱ ክፉኛ እየተንቀጠቀጠ ።

«ዋእ ! ወይ አይተ ! ይህን ወንጀል የሰሩ ሰዎች የትም ሊያመልጡ አይችሉም ።» አለ የማምላ አለቃ ጎይቶም ከሁዋላው ። ከንዴቱ ብዛት አይኖቹ እንደ እሳት ቀልተው ነበር ።

«ትምህርት ቤቱ ምን አደረጋቸው !» አለ ሀዲስ እንደ ገና ።

«የተሰራው ባምልኮ ቦታ ላይ መሆኑን አትርሳ» ካሉት በሁዋላ የፈረሰውን ግድግዳ አተኩረው እየተመለከቱ ፥ «የወርካው መውደቅ የብዙ ሰዎችን የእንጀራ ገመድ ሳይበጥስ አልቀረም ። በዚህ ብቻ የሚያቆሙም አይደሉም ፥ ወዳጄ ። ቢሆንም አትስጋ ። ነገሩ ከእንግዲህ የኔ ጉዳይ ፥ የኔ ጦርነት ነው» አሉት ፊታውራሪ ።

«በሬሳዬ ላይ ካልሆነ ህይወቴ እያለች ማንም አይነካውም !» አላቸው በእልክ ። ሌትም ዘብ መቆም እንዳለበት ነበር የሚታየው ።

እሱም ፥ ይህን፣ሰይጣናዊ ወንጀል የፈፀሙት ያባ ጨፌ ሰዎች ይሆናሉ የሚል ግምት ነበረው ። ግን' 'ከእንግዲህ የኔ ጦርነት ነው፥ ሲሉ ምን ማለታቸው እንደ ሆነ አልገባውም ። ለማሰብም ጊዜ አልነበረውም ። ብዙ

ሰዎች እየመጡ ፥ «አይዞህ ፥ አሁን መልሰን እንሰራዋለን ተጨማሪ ገንዘ
ብም ካስፈለገ እኛ እሰጥልሀ ፥ ተስፋ አትቁረጥ ፥ በርታ» በማለት ያፅናኗት
ነበር ። ጉዳቱ አልበረደለትም ። ቢሆንም ሀዘኑ እየቀለለለት ይሄድ ነበር ።
የፈረሰውን ግድግዳ ባጭር ጊዜ ውስጥ መልሶ እንዴት እንደሚሰራው
ነበር የሚያስበው ።

ፊታውራሪ ና ሰላሴት ተከትለውአቸው ሄደ ። ቤት ሲደርሱ ሳይታወ
ቀው አይኖቹ ይቃኙ ጀመር ። አይኖቹ የቃኙት እንዲያው በከንቱ ነበር ።
የሚያርፉበት ዕጊረዳ አላገኙም ።

መምሬ መሐሪ ከድጋማቸው ላይ ቀና ብለው ፥ «ቦታው ላይ ቤት ከ
ሲያን ቢሰራበት ኖር እኮ ማንም አይነካውም ነበር ። ይህ ዘመናዊ ትምህ
ርት ቤት የሚባለው ነገር ቤተ ሰቦችን ከመሊያየት ፥ ወግና ስርአትን ከመ
ናድ ሌላ ያስገኘው ፋይዳ ምንድን ነው ?» አሉ ።

ጥምጥማቸው የዘቁዋላን ጋራ መስሎአል ። ፊታውራሪ በክፉ አይን
ሲያዩዋቸው ጊዜ ቀንድዋን እንደ ተመታች ላም ምልስ አሉ ። ፊታውራሪ
አልተቀመጡም ። ዝም ብለው ይንጎራደዱ ነበር ። አንዳንዴ ወደ መስኮት
ሄደው ሩቅ እየተመለከቱ ሲያስቡ ይቆዩና መንጎራደዳቸውን ይቀጥላሉ ።
ሀዲስ ቆሞ በአይኑ ይከተላቸዋል ። አንዳንዴ በቀጥታ ወደ እሱ ይመጡና
አንድ ነገር ሲሉት ከቃጡ በሁዋላ በመተው መንጎራደዳቸውን እንደ ገና
ይጀምራሉ ። መምሩም ድጋማቸውን አቁመው ፊታውራሪን በአይን
ይከተሉ ነበር ። በመጨረሻ ሲገሰግሱ ወደ ሀዲስ መጡና ፥ «ቁጭ በል»
ብለው አዘዙት ።

ትእዛዛቸውን አክብሮ ቁጭ አለ ። እሳቸው ግን አልተቀመጡም ።
ላዩ ላይ ቆመው ቁልቁል እየተመለከቱት ፥ «ቃል እንድትገባልን የፈለግ
ነውን ነገር ለምን እምቢ አልክ ፥ ንቀኸን ነው ወይስ ሌላ ግምት ኖሮህ
ነው?» አሉት ፥ በጎርናና ድምፅ ።

«ኧረ ! እንዳሉት ይሁን ማለት አቅቶኝ አይደለም» አላቸው ፥ ወደ
ላዩ አሻቅቦ እያያቸው ።

«ታዲያስ?»
«ውሸት ምን ያደርጋል ? ብዬ ነው ። ልዋሾት አልቻልም ።»
«የላኩቸው ሰዎች አሁን ያልከውን አልነበረም የነገሩን ።»

«በመሰረቱ ይሄው ነው ። ንቀት አድሮብኝ ወይም ሌላ ግምት ኖሮኝ
አይደለም ። አባት እንዲሆኑኝ የምፈልገውን ያህል የውሸት ቃል ልሰጥ
ዎት አልፈልግም ። ነፃነቴን እወዳለሁ» ካለ በሁዋላ ፥ አይኖቹን ወለሉ ላይ
ተክሎ ፥ «ገና ለገና አባት ይሆኑኛል ብዬ ልዋሾት አልፈልግም ። እኔ
ሀብት ፈላጊ አይደለሁም ። ካቅሜ በላይ ለመንጠራራትም ምኞት የለኝም ።
የምፈልገው ነገር ቢኖር ፍቅርና ነፃነት ነው» አላቸው ፥ በተሰባበረ ድምፅ ።

መንጎራደዳቸውን ቀጠሉ ። ወደ መስኮቱ ሄዱ ። ሩቅ ሲመለከቱ
ቆዩ ። መጡ ። ሄዱ ። በመጨረሻ መጥተው ላዩ ላይ ቆሙና ፥ «መልካም
ብለሃል ። ለሰው ልጅ ዋና ሀብቱ ቃሉ ነው ። ቃል ሰውየው ነው ። ደግ
ነው ። እንዳሰብከው ይሁንልህ ። ከዛሬ ጀምሮ ፍቅርና ነፃነት ያንተ ናቸው ።
ላጂ ነህ» አሉት ።

ተንስቶ ጫማቸውን ሳመ ። እንስተው ጉንጭና ጉንጩን አገላብጠው ሳሙት ። መምሩም ፈጥነው ደርሰው መስቀላቸውን አሳለሙት ። ቶሎሳ ከየት መጣ ሳይባል ሮጦ መጥቶ ጉልበቱን ሳመው ። ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳሙ ። ከደስታው ብዛት ጣፋጭ እንባ ይወርደው ነበር ። ከዚያ በሁዋላ ስርጉን በሚመለከት አንዳንድ ዝርዝር ነገሮች እንስተው ሲነግሩት ሁሉ በግማሽ ልቡ ነበር የሚያዳምጣቸው ። ለምሳ እንዲቆይ ቢነግሩትም እሺ አላለም ። በዚያን ሰአት የፈገለው ነገር ቢኖር ፣ ውጭ ወጥቶ እየሳቀ መርጥ ክንፍ አውጥቶ በደስታ አየር ላይ መንሳፈፍ ፣ ከወፎች ጋር መብረርና ማዜም ነበር ። እውነትም ሳይታወቀው ብቻውን ይሮጥና ይስቅ ነበር ። አለም በሙሉ አብሮት የሚስቅ ነበር የሚመስለው ። ያየው ነገር ሁሉ ቆንጆ ሆኖ ፣ ልዩ ውበት ተጎናፅፎ ነበር የሚታየው ። ማንኛውም ነገር የእሱን የልብ ደስታ የሚያስተጋባ የእሱን የልብ ትርታ ስልት ይዞ የሚጨፍርና የሚያዜም ነበር የሚመስለው ። እና ፣ ከሁሉም ነገር ጋር የጋለ ፍቅር ይዞት ነበር ...

የፈረሰውን ግድግዳ መልሶ መስራት የጀመረው በዚህ መንፈስና ስሜት ነበር ። በልቡ ጥላቻ ወይም ቁጭት አልነበረም ። ይልቅ እያንዳንድ ድዋን ጡብ አንስቶ ከቦታዋ የሚያኖራት በጋለ ፍቅርና በታደሰ ተስፋ ነበር ። እና ፣ ግድግዳው ከፍ እያለ በሄደ ቁጥር በልቡ ያደረው ፍቅርና ተስፋ ከቀን ወደ ቀን አብሮት እያደገ ይሄድ ነበር ።

የሱጴ ልጃገረዶችና ጎረምሶች ከፊታውራሪ ተካ ግቢ በየቀኑ እየተሰበሰቡ የሰርግ ዋዜማ መዝፈን ከጀመሩ ቆይተዋል ። ሰውም በየቤቱ ቡና የሚያከትመው በአይናለም ተካና በሀዲስ ሳህሌ ስርግ ወሬ ነበር ። እንደ ውጉ ከሆነ በእሱም ቤት መዘፈን ነበረበት ። ግን ምንም አይነት ዝግጅት አላደረገም ። ፊታውራሪ ዝግጅት እንዲያደርግ አልፈለጉም ። ከእሱ ይጠበቅ የነበረው የሰርጉ እለት እድምተኞቹንና ሚዜዎቹን ይዞ መምጣት ብቻ ነበር ። ቤትም ሳይቀር እዚያው ፊታውራሪ ግቢ ውስጥ እንደሚዘጋጅለት ተነግሮታል ። ነገሩን ባይወደውም ምርጫ አልነበረውም ። ችግር የፈጠረበት ነገር ቢኖር እድምተኞቹንና ሚዜዎቹን በመምረጥ ላይ ነበር ። ብዙ ሰው አያውቅም ። ጉዋደኞችም አላፈራም ። ሱጴ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ጊዜውን ያሳለፈው በቁም ነገር ብቻ እንደ መሆኑ መጠን ሀዘኑንም ሆነ ደስታውን የሚካፈሉት የቅርብ ወዳጆች ባለ ማፍራቱ ቆጨው ።

ምን ጊዜም ቢሆን የሰው መድሀኒቱ ሰው መሆኑ በሚገባ የተከሰተለት እነማን እድምተኞችና ሚዜዎች ላድርግ ? እያለ ማሰብ በጀመረበት ጊዜ ነበር ። ይህም ብቻ አልነበረም ያሳሰበው ። ለክፉም ሆነ ለደግ ፣ በሚኖርበት ህብረተሰብ ውስጥ ስር ያልሰደደ ሰው ፣ ስር እንደ ሌለው ዛፍ መሆኑ እየታየው፣ ሰው ብቻውን አይደለም፣ ሊሆንም አይችልም ይል ነበር— ብቻውን ።

ከነገር አባቶቹ ሌላ እድምተኞች አላገኘም ። ከቀውሌ በቀር መምህራኑ ሁሉ ለክረምት ኮርስ ሄደው ነበር ። ቀውሌንና ጎረቤቱ የሚኖሩትን ሽማግሌ ልጅ ሁለተኛና ሶስተኛ ሚዜ አድርጎ ከመረጠ በሁዋላ ታፈሰ ብሩን ፍለጋ ሄደ ። ደጉ ውስጥ ሲዞር እንደ ምንም ፈልጎ አገኘው ።

ታፈሰ ሁሉንም ነገር ያውቅ ስለ ነበረ እየቀለደ ፣ ለየፈሩት ይደርሳል ፣ የጠሉት ይወርሳል ይባላል ፣ መንድም እግዜሩ አለው ።

ሀዲስ አርእስተ ጉዳዩን ለውጦ ፡ «እውነትም ይህ ደን ያንቀጥቅጣል» አለው ።

«የወርቅ ማእድን ነው» የሚል ነበር የታፈሰ መልስ ።
«የቡና ችግኝ ተከላው ስራ እንዴት ነው?»

«አምስት ሽህ እግር ቡና ተክያለሁ ። ነሐሴ ሳያልቅ ወደ አስራ ሁለት ሽህ እግር ቡና ለመትከል ነው ያቀድኩት ። ከሶስት አመት በሁዋላ ምን አለፋህ ጥቁር ወርቅ መሸምጠጥ ነው ። ደህና ሁኝ አራዳ ብዬ የመጣሁት ለቀልድ አይደለም ።»

«እንዳስብከው ባጭር ጊዜ ውስጥ የሚሊዮን ብር ጌታ ልትሆን ነው ።»

ጉሬዛዎች ፡ ካንዱ ዛፍ ቅርንጫፍ ወደ ሌላው እየዘለሉ ውብ የሆነ ፡ አይንና ልብ የሚማርክ የሰማይ ላይ ትርኢት ያሳያሉ ። የወፎቹ ዝማሬ ልብ ይመስጣል ። ድኩላዎችና ሚዳቆዎች ገላጣ አረንጉዋዴ ሜዳ ላይ ከምትገኝ አንድ ትንሽ ምንጭ ውሀ እየጠጡ ይሄዳሉ ። የፀሀይዋ ጨረሮች ወርቅማ ዝናብ በዛፎቹ ቅርንጫፎች መካከል ያዘንቡ ነበር ።

«ግን አንተ ባቋዋራጭ መንገድ ቀደምከኝ» አለ ታፈሰ ፡ አንድ ረጅም ሰንበሌጥ በጥርሶቹ መካከል ይዞ ።

«እንዴት ?»
«አንዳንድ ሰው እድለኛ ነው—ከሚሊዮን ብር ጋር ይጋባል» አለው ።
«ሀዲስ ለብር ሲል ነው የሚያገባው ብለህ በእውነት ታምናለህ ?»
«ለፍቅር ፡ ስለ ፍቅር ብቻ ብለህ ነዋ !»
«ብታምንም ፡ ባታምንም ፡ አዎን !»

ታፈሰ በሳቅ ፈነዳ ። ሜካው ሳቁን ያስተጋባ ነበር ። ሳቁን አቁሞ እንባውን ጠረገና ፡ «ጅል አትሁን ። ከቆንጆ ሴት ጋር ሚሊዮን ብር ሲገኝ የሚጠላ ሰው የለም» አለውና ፡ አይኖቹን ጣል አድርጎበት ለጥቂት ጊዜ ከተመለከተው በሁዋላ ፡ «ወንድም እግቾ ፡ አይዞህ ። አትዘን ። ለመሆኑ ለምን ኖርአል የፈለከኝ ? ሁለተኛ የምንገናኝ አልመሰለኝም ነበር» በሚለት ለስለስ ብሎ ጠየቀው ።

ሀዲስ አመነታ ። ሆኖም በልቡ አልጠላውም ። እሱን የሚጠላበትም ምክንያት አልነበረውም ።— ሀብት ፈላጊ አለ መሆኔን ምን ብዬ ባስረዳው ይሆን ሊረዳልኝ የሚችለው ? በማለት በራሱ ጉድለት ነበር ያዘነው ።

«ታዲያስ ምን ነበር?» አለው እንደ ገና ።
«የመጣሁበት ጉዳይ ያስቃል ።»
«ንገረኝና እንሳቅ ።»

«ደግሬምህና ሚዜ እንድትሆነኝ ልጠይቅህ ነበር የመጣሁ» ብሎ ሊስቅበት ለማየት ራሱን አዘጋጅቶ ይጠብቀው ጀመር ።

ታፈሰ አልሳቀም ። ረዘም ላለ ጊዜ ዝም ብሎ ሲመለከተው ቆየ ። ያላቢ ጥላ ፊቱ ላይ ውልብ እያለ ሲጠፋ ይታይ ነበር ። ፈገግታው ም ብልጭ ብሎ ተመልሶ ይጠፋል ።

«ታዲያስ?» አለ ሀዲስ ።
«ሀም...አማችም ሚዜም ልታደርገኝ?»

«ያውም አንደኛ ሚዜዬ ። ሌላ የማውቀው ሰው የለኝም ። ምን ታስ ባለህ ታዲያ?»

«ሌሎቹስ እነ ማን ናቸው?»

የሌሎቹን ስም ነገረው ።

«አንደኛ አሽከርህ ልታደርገኝ ነዋ?»
«እንዴት?»
«ሞኝ አይደለህ...»
«እና?»

«ሞኝ ሙሽራ ፣ ሰርገኛ አሽከሩ ይመስለዋል ሲሉ አልሰማህም ?»
«ሞኝ ነህ ካልከኝ ሳይቀር ያን ቀን አንተን እያ...ኝ ፣ ልክ እንደ አሽከሬ ነው የማዝህ ። »

«አይታወቅህም እንጂ ትምህርት ሚኒስቴር ስራ ፍለጋ ቢሮዬ መጥተህ ከተገናኘንበት ቀን ጀምሮ ስታዝኝ ቆይተሃል ። ምክንያቱ አይገባኝም ። ሳስበው ይገርመኛል» አለው ።

ከዚያን ሰአት ጀምሮ እንዳሽከር ማገልገል ብቻ ሳይሆን እንደሚደረው ታላቅ ወንድምም ሆኖ አስፈላጊውን ነገር ሲያሙዋላለት ይጥር ነበር። የሰርጉ ቀን ሊደርስ ሶስት ቀን ሲቀረው ታፈስ ትምህርት ቤት ድረስ በመኪናው መጥቶ ጠራው ። ሀዲስ ተናዶ ሳቡ ጠብ እስኪል ድረስ ይስራ ነበር ። ላቡን ከግንባሩ ላይ እየጠረገ መጣ ።

«ለሰርጉ ሶስት ቀን የቀረው ሙሽራ ሳይሆን መናጢ ኩሊ መስለሃል» አለው ታፈስ ፣ አዳፋ ልብሱን ባይኑ እየተፀየፈ ።

«ምን ላ'ርግ እባክህ!»
«ምን ነካህ?»

«ይሄው እንደምታየው ነው» ብሎት በንዴት በረጅሙ ተነፈሰና ፣ «ሰራተኞች የሉም ። በየቀኑ ማርያም ፣ ገብርኤል ፣ ጊዮርጊስ ፣ ሚካኤል እያሉ ይጠፋሉ ። ጊዜን በከንቱ ነው የምናባክነው ። እና ፣ በጣም ያናድደኛል ። ይብልጥ የሚያናድደኝ ደ'ሞ ምን መሰለህ ? ጠበል ጠዲቅ ፣ ሰንበቴ ፣ ማህበርና ፣ ክርስትና ፣ ድግስ እየተባለ የሚወድመው ያለ የሌለ ጥሪት ነው ።

«ይህች ድሀ ፣ ጎስቋላ ፣ ግን ውብና አሳዛኝ አገር እንዴት አድርጋ ልትበለፅግ እንደምትችል እኔ እንጃ ! ይህ ትውልድ ጎጂ ልማዱንና ባህሉን እንዳርጊ ኑና አውጥቶ በመጣል ራሱን ለመለወጥ ካልቻለ በቀር በዚህ ሁኔታ የት እንደምንደርስ አላውቅም ። ስልጣኔ ማለት እኮ ምርቱንና ግርዱን ባንድነት የያዘ አርጌ ጋሪ መጎተት ማለት አይደለም ። አላማችንን ለመለወጥ ፊታችንን ወደ ፊት ማዞር አለብን ። እና ፣ ሰው ከተለወጠ የማይለወጥ የህብረተሰብ መዋቅር የለም !» በማለት ስሞታውን ባንድ ትንፋሽ ደረደረለት ።

«ኧኸኸኸኸ ! እውነትም ተናደሃል!»
«ለምን አልናደድም?»

«ቀስ በል» ብሎት ባይኑ ቲፕ እየተመለከተው ፣ «እንዲህ ስትሆን ነው የምታናድደኝ። እሰምን ለመለወጥ ነው የተነሳሽው — ኤ ? አይ እናቴ ። እንዲህም አ'ርጎም የለ ። ወንድም አግቼ ፣ ይህን ቀልድህን አቁም ። ስማ ልንገርህ፣ ሙሴ፣ አይሁዶችን ከምድረ ግብፅ ለማውጣት ይዞአቸው ሲሄድ ምድረ በዳ ሲደርሱ ምን ብለው እንደ ሙሁበት ታውቃለህ ? 'ሽንኩርት ! ስጋ !' እያሉ ነው የሙሁበት ! አንድም ያመሰገነው ሰው አልነበረም ። ነፃነት ወይም የወደ ፊት ህይወት የሚባለውን ነገር ብዙ ሰው ሲገባውም፣ ሊሸከመውም አይችልም ። ባንተ ህልም ማንም ደንታ የለውም ። እንዲያው ነው የምትምሸው !» አለው ።

«አርጌ ጋቢ ብቻ ነው የሚሞቀው ያለህ ማን ነው ? ተወኝ እባክህ ። ሀፃን ልጅ ሲያጥቡት ማልቀሱ አይቀርም ። ሰው ለተሻለ ህይወት አሰምን ለመለወጥ ከፈለገ ራሱ መለወጥ አለበት ። ቁም ነገሩ ይህ ለውጥ የሚያስከትለው ቁጣ ወይም የህጋዊነት ጥያቄ ሳይሆን ፣ የለውጡ ይዘትና አቅጣጫ ነው ። ወደ ፊት ካልተመለከትን ያሁኑን ፣ የዛሬውን ሁኔታችንን እንዴት ብለን ልንለውጠው እንችላለን ?» አለ ምርር ብሎ ።

«ወንድም አግቼ ፣ አሁን አታልቅስብኝ ። ትዳር ይለውጥሃል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ። ይለውጥሃል ደ'ሞ ። ምናለ በለኝ ። አሁን ውስጥህ የሚነደው እሳት የትዳር ሀላፊነት ሲጫንበት ይበርድ ይሆናል» ብሎት ይዞት ወደ ቤት ወሰደውና በስጦታ ወረቀት የተጠቀለለ ትልቅ ቡጥት ከመኪናው ላይ አውርዶ ሰጠው ።

«ምንድን ነው እሱ ?»
«ስጦታ ነው ።»
«የምን ስጦታ ?»
«ክፈተውና እየው ።»

ሀዲስ ቸኩሎ ቡጥቱን ከፈተው ። ሙሉ ጥቁር ልብስ ፣ ነጭ ሸሚዝና ጥቁር ጫማዎች ነበሩ ።

«ለምን ብለህ ነው ?»
«ለሰርግህ ። የገበሬ ሙሽራ ሳጅብ ኖሮአል ?»

«ልብሴን ሊታጅብ ነዋ !» ብሎት ጉንጩን ሳመውና ፣ «ውድ መሆን አለበት» አለ አይኖቹን ስጦታዎቹ ላይ ጥሎ ።

«ገንዘብ ለመቼ ነው ?»

«ሚሊየነር አልሆንክም ገና ። ካሁኑ እንዲህ ብኩን ከሆንክ እንዴት ባለህ ሚሊየነር ለመሆን እንደምትችል አይገባኝም ። 'ከጥቃቅን ወጭዎች ተጠንቀቅ ፤ ትንሽ ፍሳሽ ትልቅ መርከብ ታስጥማለች' ብሎ አሏ ቤንጃሚን ፍራንክሊን ።»

«ስለ እሱ አታስብ ።»

ለሰርጉ እለት የቀሩትን ሁለት ቀናት ሀልም አልሞ እንደሚኖር ሰው ሆኖ ባሳብ ባህር ላይ እየተንሳፈፈ ነበር ያሳለፋቸው ። ወደ ስራው ለመሄድ አልቻለም ። ቀናቱ ረጅም ይሁኑ አጭር ግምት አልነበረውም ። ሰአቶቹ ፈጥነው ወይም ዝግ ብለውበት እንደ ሆነ አላውቅም ። ሀዲስ ሳህሌ አይናለም ተካን ሊያገባ ! አንዳንዴ ነገሩን ለማመን ያቅተው ነበር ። ታፈሰና ሌሎቹ ሚዜዎች መጥተው ሲያለብሱት ሁሉ ፣ 'እውነት ላገባ ነው?' እያለ ይጠራጠር ነበር ።

«ይህ ሁሉ እድምተኛ ከየት መጣ ?» ብሎ ታፈሰን ጠየቀው ።

የበቅሎ ፣ የፈረስና የሰው ብዛት ከቤቱ ፊት ለፊት ያለውን ሜዳ አጣቦ ይታይ ነበር ።

«ጥላ ቢስ መናጢ ሙሽራ የፊታውራሪን ደጅ እንዴት አድርጎ ይረግጣል!»

«ሰራዊት ስትመለምል ነዋ የከረምከው !»

«ዝም በልና ልበስ ። ጊዜው ሊደርስ ነው ። ፊታውራሪ በቀጠሮ ሰአት ቀልድ አያውቁም ። የዘገየህ እንደ ሆነ ከደጅ እንደሚመልሱህ እወቅ ። እውነቱን ነው ። 'ዘግይቶ የመጣ ሰው የሚጠብቀው የተዘጋ በር ነው' ስለሚሉ ፣ የሰው ማንነቱን የሚገምቱት በቀጠሮ አክባሪነቱና በቃሉ ነው» አለው እያለባበሰው ፣ «አዎን ፣ አሁን ሰው መሰልክ !»

«ልኬን በምን አወክ እባክህ ?»
«ጠንቋዋይ ቀልቤ ።»
«ግን ይሆን ካባና ባርኔጣ አላደርግም ።»

«እዚህ ሙሽራ ለመምሰል ከፈለክ ካባና ባርኔጣ የግድ ያስፈልጋል ። አለዚያ ሰው ይስቅብሃል ። እኔ ደ'ሞ ሰው የሚስቅበት ሙሽራ አጅቤ መሄድ አልፈልግም ።»

አጅበውት ወጡ ። የጠራች ደማቅ ፀሀይ ከጠራ ሰማይ ላይ ኩልል ብላለች ። ያጃቢው ብዛት መጠን አልነበረውም ። በሀር ጨርቅና በወርቅ ጌጣጌጥ የተንቆጠቆጠች በቅሎ ተዘጋጅታ ትጠብቀው ነበር ። በጥቁር ልብሱ ላይ ካባውን ደርቦና ባርኔጣውን አድርጎ በቅሎ ላይ ሲወጣ በራሱ ሳቀ...

ሃይ ፣ ሃይ ፣ ሃይ ፣ ሎጋው ሽቦ !
ሽቦ ያውና ሽቦ
እህም ፣ እህም ፣ ሎጋው ሽቦ !
ሃይ ፣ ሃይ ፣ ሃይ ፣ ሎጋው ሽቦ...

እንደ ወጉ ደጅ አላስጠኑትም ። የሚያስቀጥረው ወርቅና ስጦታ አልነበረውም ። የፊታውራሪን ጉልበት ስሞ ወደ ተዘጋጀው ዳስ ገባ ። ተንጣሎ የተሰራው ዳስ ድፍን የሱኳ ህዝብ ቢመጣ ውጦ የሚያስቀር ይመስላል ። እልልታው ቀለጠ ። የተኩስ እሩምታ ሰኢን አናጋ ። የልጃገረዶችና የጎረምሶች ዘፈን ደመቀ—ደራ ። በተጋባዦና በተጨዋቾቹ ላይ ሽቶው እንደ

ውሀ ተርከፈከፈ ። ሌላ እልልታ ። ሌላ የተኩስ እሩምታ ። ሙሽራይቱ በደንገጡሮችዋ ታጅባ ከጉዋዳ ብቅ አለች ። ፊትዋን ለማየት አልቻለም ። ባይን ርግብ ተሸፍና ነበር ። አሁንም አላመነም ። ህልም የሚያይ ነበር የሚመስለው ። ከበሮው ይደለቃል ። ይከላላል እምቢልታው ። መሲንቆው ይመታል—ያቅራራሉ ፣ ያቀንቅናሉ አዝማሪዎች ። ይቀርባል በገፍ ጠጅ በማብረጃ ፣ አረቄ በጠርሙስ ፣ ጥጥ የመሰለ ሙጣ ስጋ የሳንሳ እየተ ያዘ...

አይናለም
አንቻለም
ዝንታለም
ውባለም
ከቶ አንቺን አይቶ የጠገበሽ የለም...

ዝናሽ ትክዝ ብላለች—ሆይ ሆይ—በጠፍ ጨረቃ ጭቤ ብልጭ ሲል—የሽጉጥ ተኩስ እንደ ቡሄ ጅራፍ ሲንጣጣ—እልልታ—የውቤ በረሃ ጀግና ወድቆ ውሀ ፣ ውሀ ሲል—የፖሊሶች ፊሽካ ። ፀጥታ ። ሙዚቃው እንደ ገና ሲደራ ! ዳንኪራው ሲቀልጥ ፣ ደርሶ መልስ ፍቅር በየጉዋዳው ሲጦፍ ። ደግሞ ልቡ ያበጠው ጎረምሳ አንድዋን ሲጎነትል፣ ሲያታጥባት በጥፊ—ሌላ እልልታ፣ግርግር ፣ ጥርስ ረገፍ እንደ ቆሎ መሬት ላይ ሆጭ ሲል ። ሙዚቃ..

ፊታውራሪ ተካ ቀጭን ነጠላቸውን ትከሻቸው ላይ ጣል አድርገው በተጋባዡ ህዝብ መካከል እየተዘዋወሩ «ብሉ ፣ ጠጡ» በማለት ከመጋበዝ ሌላ ፣ ስጋ አቆራረጥ ፣ አያያዝና አበላል የማያውቅ ሰው ሲያጋጥማቸው በንዴት ቶሎሳን እየጠሩ ፣ «ምንድን ነው ይኸ ስጋ እንደ ሽንኩርት የሚ ከትፈው ። ቢላዎውን ቀማውና አቆራረጥና አበላል አሳይልኝ ! ... እንዲህ ነው !» ይሉ ነበር ! ቶሎሳ ከሰውየው ቢላዎ ቀምቶ ፣ ሽንጡን ወይም ታናሹን በያዘው ቢላዎ ነካ ፣ ነካ ፣ ገልበጥ ፣ ዋጥ ፣ ቆረጥ ፣ ዋጥ ሲያደርገውና እጅ ነስቶ ቢላውን ለምስኪኑ ሰውዬ መልሶ ሲሰጥ ባድናቆት እየተመለከቱ...

ዝናሽ አሁንም ባሳብ ጎዳና ርቃ ሄዳለች ። ቀይ ፣ ብጫ ፣ ሰማያዊ ፣ አረንጉዋዴ መብራቶች ይታዩዋታል ። ከርቤ ፣ እጣን ፣ ብርጉድ ፣ ሽቶ ፣ የበረሃ ሽታ ይሸታታል ። የታንጎ ፣ የዋልትዝ ፣ የቡጊ ውጊ ፣ የማምቦ ፣ የቻቻ ፣ የማሪንጌ ፣ የሳምባ ፣ የኮንጋ ሙዚቃ ከዲን ማርቲን ፣ ከፍራንክ ሲናትራ ፣ ከቢል ሄሊ ፣ ከሊትል ሪቻርድስ ! ከፋትስ ዶሚኖ ፣ ከናት ኪንኮል ፣ ከዶሪስ ዴይ ዘፈኖች ጋር ውሉ እንደ ጠፋ ልቃቂት እየተወሳሰበ ከገነት ፅጌ መናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በላይ ነግሶ የሰፈሩን ፀጥታ ሲያናጋ ይሰማታል ። እንደ ሰራ አይገድል !...

ዘፈኑ ፣ እልልታው ፣ እስክስታው ፣ ከበሮው ፣ መሲንቆው ፣ እምቢልታው ይቀልጣል ። ጠጁ ፣ አረቄው ፣ ጠላው ፣ ቢራው እንደ ውሀ ይቀዳል ። ብርንዶና ሙጣ ይቆረጣል ። አልፎ አልፎ የተኩስ እሩምታ ይሰማል ። እለም ዘጠኝ ሆና ነበር ።

አይናለም ፣ አይናለም
የማይልሽ የለም ።
አበጀሽ ! አበጀሽ ...

«ታዲያስ ?» አለው ታፈሰ ።
«ደከምኞል ።»

«አ አ! መበርታት አለብህ ። ጫጉላ ቤት ሳትደርስ መድከም የለም ። ጫጉላሽ አብቦአል ዛሬ ፥ ብር አምባር ሰበረልዎ ፥ ሀዲስ ልጅዎ ሳንል እንዴት ይሆናል ። ክብሩም ሆነ ኩራቱ'ኮ እዚህ ላይ ነው ...»

«በፈጠረህ ዝም በል!»

የፍካሬ ድጋም ምን ያደርግላታል ?
ውዳሴ ማርያም ምን ያደርግላታል ?
ብሉይ ኪዳን ማንበብ ምን ያደርግላታል ?
የፍቅር መሰረት ሀዲስ ይበቃታል ...

«ሰከርክ መሰለኝ ?»

«ትንሽ'ጠጣ ። ይረዳሃል ። ሁዋላ ውርደት ነው ። ግን አትፍራ ። ትንሽ ብትጠጣ ድፍረትና ጥንካሬ ይኖርሃል ። ደግነቱ ልጅቱ ደካማ ናት ። በዚህ ላይ ደ'ሞ ጥፍሮችዋን ሲጋዋ ድረስ በመቁረጥና ከትናንት ጀምሮ እንኮላ ሙሉ ኮሶ በማጠጣት የባሰውን ሳያደክሙዋት አልቀሩም ።»

የሱዲ ባላባት ማለፊያ ደግሶ
መምህር ባረከለት ማእዱን ቀድሶ ።
የገባ ወንዝ ውሀ ፥ ውሀው ጠጅ ሆኖ ሲያሰክር ሁሉን
መገን አንቺ ሆዬ ፥ መገን ሱዲ ቦር ፥ ባይናለም አየን ...

«በፈጠረህ ተወኝ ። ሰራዬ ደከሞኛል ። ይህን ካባ ከላዬ ላይ የምጥልበት ጊዜ ነው የናፈቀኝ ። ጅል ያስመሰለኛል ።»

«ልእልል ሀዲስ ሳህሌ ነው የመሰልከው !...እውነቴን ነው ። ግን ስለ ድካም አትናገር ። ስለ ድካም መስማት አልፈልግም ። ሙሽራህ ፍቅር ይዞአት ጫጉላ ቤት የምትገባልህ አይምሰልህ ። ይዛ የምትመጣው ነገር ቢኖር ንፅህናዋንና ድንግልዋን ነው ። በግድም ሆነ በውድ መውሰድ ያለብህ ያንን ነው ። ወንድነትህ የሚታወቀው ያኔ ይሆናል ። አለዚያ እንተን አያድርገኝ ። እስዋም ክብርናዋን ይዛ ባትገኝ ወዮላት ! እርባ ገርፈህ ፥ የተቆረሰ ድፎ ዳቦ አሸክመህ ወደ አባትዋ ጡዋት በማለዳ እየገረፍክ መሸኘት ነው ። ትሰማለህ ?»

«ለፍልፍ !»
«እስዋ አሁን ምን የምታስብ ይመስልሃል ?»
«ሂድና ጠይቃት !»

«ምን እንደምታስብ አውቃለሁ ። ስለ ክብርናዋ ይሆናል የምታስበው። ስንት ዘመን ጠብቃ ስላቆየችው ክብርናዋ ። እና ፥ እያሳዘናትም ታለቅስ ይሆናል ። የባላገር ልጆች ጭንቀት እየተጨነቀች ይሆናል ። እንዳዲሳባ ጋብቻ እንገዶቹ፣ሽኝተህ ወደ መኝታ ቤትህ በመግባት ፥ እንደሚሆነው አይምሰልህ ። እዚህ ሁሉም ጆሮውን አቁሞ የሚጠብቀው ጫጉላ ቤት ውስጥ የሚሆነውን ነገር ዜና ነው ። ያንተ ፥ የእስዋ ፥ የቤተሰቡ ክብርና ኩራት በዜናው ይወሰናል ፡፡ እድሜ ለድንግል ማርያም !» አለው ።

ሀዲስ ነገሩ ሰልችቶት በመበሳጨት ፊቱ የነበረውን መለኪያ እንስቶ ውስኪውን ባንድ ትንፋሽ ጨለጠው ...

«ለንጊያ ነው ?» ብሎት ሌላ ቀዳለት ፣ «ከብርና መገበስ ቀላል ስራ አይደለም ። እንዳልኩት ፣ ድፍረትና ጥንካሬ ያስፈልጋል ።»

ሀዲስ የተቀዳለትን መጠጥ አይቶ አልተወውም ። አንስቶ አጋመሰው ።

«ኢ... እንደሱ ማለቴ አይደለም ። ከስካሩም ሙሽራ ይሰውረን አቦ!»

«የሚዜ ቀርተሩ ከሚሉህ ሄደህ እንደ ቀውሴና እንደ ጎይቶም ለምን አትዘፍንም ?»

ወደ አይተ ! ጎይቶም ከበሮውን እየደለቀ የትግሬ ዘፈን ያቀልጣል ። ዘፈኑን በደንብ የሚቀበለው ሰው አላገኘም ። ቢሆንም ግድ አልነበረውም ። ዘፈኑን ብቻውን ይለው ነበር ። ስእሉ ደረሰ ። መምሬ መሀሪ ምርቃትና ቡራኬ አወረዱ ። ዘፈኑ እንደ ገና ደራ ። እምቢልታው ተንኳለለ ። እልልታው ቀለጠ ። የጥይት ተኩስ ሳያቋርጥ ይንጣጣ ነበር ። ሙሽራና ሙሽሪት የፈታውራሪን ጉልበት ስመው ወጡ...

ከሙሽሮቹ ፊትና ሁዋላ የተያዙት ችቦዎች ጨለማውን ወደ ቀን ብርሃን ሊለውጡት ምንም ያህል አይቀራቸውም ነበር ። ጥቁሩ ሰማይ በሚስቁ ከዋክብት ተሰግጦ ይታያል ። እንደ ታጀቡ ሄደው ሜጉላ ቤታቸው ደረሱ ። በሩ ተዘጋባቸው ። ብቻቸውን ቀሩ ። ካባውን ወርውሮ ክራቫቱን አላላ ። አይናለም ዝም ብላ ቆማ ነበር ። ሄዶ አይኑ ርግብዋን ገለጠ ። ሰውነትዋ እንደ ቅጠል ይርገበገብ ነበር ። አይኖችዋ ትኩስ እንባዎች ያፈሳሉ ። አይኑ ርግብዋን ቀስ ብሎ ከራስዋ ላይ ሲያነሳ ረጅም ጠጉርዋ ተንዶ ሄዶ ትከሻዋ ላይ ዝርግፍ አለ ።

አገጭዋን ይዞ ወደ ላይ ቀና አደረጋትና ፣ «አለምዬ ፣ እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅሽ ። ያ ደብዳቤ ከኔ ዘንድ አለ መሆኑን ስታውቂ ምን ተሰማሽ ?» አላት ።

መልስ አልሰጠችውም ። ጉንጭዋ ላይ ሳማትና ፣ «ምን ትለኝ ይሆን ብዬ አዝኜ ነበር» አለ ፣ አይን አይንዋን እያየ ።

አይኖችዋ እንደ ሰማይ ከዋክብት አበሩበት ።

«እኔም ተስፋ ቆርጬ አዝኜ ነበር» አለች በሚንቀጠቀጥ ድምፅ።
«ለምን አለምዬ ?»

«እምነት የጣልኩበት ነገር ሌላ ሆኖ ሲገኝ ለምን አላዝንም ። እና ፣ በርግጥ ላደርገው አስብ ነበር» አለች ።

«ምን ?»
«ራሴን ለመግደል ።»

«አለማድረግሽ ደስ ይለኛል» ብሎ ወደ ደረቱ አስጠጋትና ፣ «እኔ ህይወትሽን ነው የምፈልገው ። እንደ ተመኘሽው ትግሬያለሽ» አላትና ፣ አንገትዋ ስር ሽጉጥ አለ ።

ከበር ሲደለቅ ይሰማል ። ዘፈኑ ፡ እልልታው ይቀልጣል ። መላ ሰውነትዋ ሲንቀጠቀጥ ተሰማው ።

«አይዞሽ» አላት ፡ «አትፍሪኝ ። ያው ዱሩ የምታውቂው ሀዲስ ነኝ ። አዲስ አውሬ አይደለሁም ። ካንቺ ጋር ብቻዬን እንደዚህ ፡ እንዳሁኑ ፡ ለመሆን እመኝ ፡ እልም ነበር ... ካልሆነም ከዚህ መስቀል ጋር ሞቼ እቀበር ነበር ። ይህ መስቀል ትዝ ይልሻል ?»

መስቀሉን በአንባዋ ውስጥ ተመለከተችው ። ነጭ መሀረብ አውጥቶ ላንባዋን ጠረገላት ። እና ፡ አቅፎ ሳማት ። በመጀመሪያ አፀፋውን አል መለሰችለትም ። እንደ ገና ሳማት ። ለከንፈሮችዋ ሲጠማና ሲራብ የቆየውን ያሀል ነበር የሚስማት ። እንደ እሳት የሚፋጀው የስራ አካላቱ ያቀልጣት ይመስል እጆቹ ውስጥ እየደከመች፣ እየመጥመጠች ትሄድ ነበር.. ገሃነመ እሳት ነበር — ገሃነመ ፍቅር ። የሰማይ ከዋክብት በሙሉ ወደ አበቦች ተለወጡ—ላዩ ላይም ረገፉ...

ቀጥሉ የሰማው እልልታና የተኩስ እሩምታ ነበር ።

# ክ ፍ ል ፲፭

ልባቸው ውስጥ የሚነደውን የፍቅር ፍም እየሞቁ ምሽት ላይ ጀንበርዋ የፍም አሎሎ መስላ ስትጠልቅ ባድናቆት ይመለከታሉ ። ጡዋት በማለዳ ተነስተው በወጣት እግሮቻቸው ጤዛዎችን እያረገፉ ወደ ፀሀይ መውጫ ይሮጣሉ ። እንደ ምን አደርሽ ፀሀይ ? እንደ ምን አደርሽ ህይወት ?

ሌቱ በትላልቅ ሳቂታ ከዋክብት የተሞላ ፣ ጣፋጭ እንደ ማር ወለላ ፣ አጭር እንደ ቅንጆ ህልም ነበር ። ቀኑም ሆነ ሌቱ ፣ ምሽትም ሆነ ንጋቱ ፣ ሁሉም አጭር ፣ ፈጣን ፣ እንደ ፍቅር ውብ ፣ እንደ ጫጉላ ቤት ፍቅር ጣፋጭ ፣ እንደ አዲስ ፍቅር ፈጣን ነበር ።

የሱዲ ሰማይ አብርአቸው ይሰቃል ። መልካዎች ከነሱ ጋር ያስካካሉ ። የሱዲ ምድር ከወጣት እግሮቻቸው ስር አብራቸው ትደንሳለች ። የምድር አበባዎች ሁሉ ከነሱ ውብ ፍቅር ጋር አብረው ይፈነዳሉ ! ያብባሉ ! ይፈካሉ ። ወፎች ፣ የንፋስ ሽውታዎች ፣ የጫካ ሹክሹክታዎችና ወራጅ ምንጮች የሚያዜሙት የእነሱን ፍቅር ዜማ ነበር ። ቢራቢሮዎችና ንቦች ካንዱ አበባ ወደ ሌላ እየበረሩ የሚተርኩት የእነሱን የፍቅር ታሪክ ነበር ። ከዛፍ ጥላ ስር አረፍ ብለው የሚመለከቱት የጠራ ቀዝቃዛ ምንጭ መልሶ የሚያንፀባርቀው የሁለቱን ፍቅር ነበር ።

የሱዲ ሜዳዎችና ሸንተረሮች ፣ ፊታቸው ይነጠፉሉ ። ሸለቆዎች ርምጃዎቻቸውን ማህሌት ቆመው ይቀድሳሉ ። ተራሮች ፣ ሳር ቅጠሎች ፣ የምድር ዛፎች ባለፉባቸው ቦታዎች ሁሉ ያረግዳሉ ። በውብ ፍቅር አለም ውስጥ ያለ ሁለቱ ሌላ ፍጡር ያለ አይመስላቸውም ነበር ። እጅ ለእጅ ተያይዘው ሲሮጡ ፣ ሲገቡና ሲወጡ ያያቸው ሁሉ ፣ ከክፉ አይን ይሰውራችሁ የማይላቸው ሰው አልነበረም ።

የምን ያደባባይ ፍቅር ነው ! ስዶች ! አሳዳጊ የበደላቸው ! አበስኩ ገበርኩ ! የሚሉዋቸውም አንዳንድ ሰዎች ነበሩ ። ፊታውራሪም ይህንኑ ሰምተው ፣ «ሰው አይንና አፍ መግባት ጥሩ አይደለም» ይሉዋቸው ነበር ብዙ ጊዜ ደጋግመው ! ሁድ ሁድዋን እየተመለከቱ ። አይናለምን ያው እንደ ወትሮዋ ሽንቅጥ ብላ ሲያዩዋት ደስ አይላቸውም ።

በምሳ ሰአት ከፊታውራሪ ማእድ መለየት አይፈቀድላቸውም ። የፊታውራሪ ገረድ እንጀራውን አዝላ ስትመለስ ጠብቀው ለምሳ ይቀርባሉ ። አንዲት ደቂቃ አሳልፈው የት ሊገቡ ! ፊታውራሪ በጣም ይቆጣሉ ። እንዳጋጣሚ ሆኖ ዛሬ ትንሽ ዘግይተው ነበር የደረሱት ። እሳት ለብሰው ፣ እሳት

ጎርሰው ጠበቁዋቸው ። ጥፋቱን እንዳወቀ ህፃን ሁሉቱም አቀርቅረው ቁጭ አሉ ። አገልግሉ አፉን ከፍቶ ይጠብቃል ።

«የት ነበራችሁ !» አሉ ሙከ ብለው ፤ ሆድ ሆድዋን እየተመለከቱ ። የተለወጠ ነገር አላዩባትም ። በይበልጥ ሽንቅጥ እያለች ነበር የምትሄደው ።

«ውጭ ወጥተን ነበር» አለ ሀዲስ ፥ እንደ ህፃን መቆጠሩ ውስጥ ውስጡን እያናደደው ።

«እኮ የት ?»
«ትምህርት ቤት ነበርን ።»

ሕሉቱ ቅዳሜ ነበር ። ማለዳ በጡዋት ተነስተው ነበር ወደ ትምህርት ቤት ተያይዘው የሄዱት ። ባንድ ፊት ሰራተኞቹን እየተቆጣጠረና እየረዳ ፥ በሌላ በኩል ደግሞ አይናለምን እንግሊዝኛ ሲያስተምራት ነበር የዋለው ። ቤት ውስጥ ፥ ሽርሽርም ላይ—በየትም ቦታ—እንግሊዝኛ ያስተምራታል ። እና ፥ የሚሰጣትን ትምህርት የመቀበል ችሎታዋ በጣም ያስደስተውና ያደ ፋፍረው ነበር ። እንዲያውም የመማር ፍላጎትዋ ሱዴን ጥሎ እንዲሄድ ልቡን ያነሳሳው ነበር ። ግን የትምህርት ቤቱን ስራ ለማን ጥሎ ! ስራው ከፍፃሜ አይደርስም ፤ በየጊዜው ያልታሰበ አዲስ ችግር እየተፈጠረ ይጎ ትታል ። ሲሆን ለመስከረም ፥ ካልሆነም ለጥቅምት ያልቃል ብሎ የገመ ተው ስራ ይሄውና ህዳር ላይ ፈቅ አላለም ። ሰራተኛ እንደ ልብ አይገኝም ። የሱዴ ህዝብ ቡና እሸት ላይ አይኑን መጣል ጀምሮአል ።

«እሱስ ይሁን ፥ እሺ!» አንቺ ደ'ሞ አደባባይ ምን ታደርጊያለሽ ? አር ፈሽ ቤትሽ አትቀመጭም ? የሴት ልጅ ክብርዋ ቤትዋ ፥ ማጀትዋ ነው ። እጅ ለእጅ ተያይዞ በያደባባዩ መታየት ደግ አይደለም ብያለሁ ። ማንኛ ውም ነገር ከልኩ ማለፍ የለበትም !» አሉ ፊታውራሪ ተቆጥተው ።

«ምን'ጠፋሁ አባዬ ?» አለች አይናለም ቀና ብላ ።

«በጨዋ ቤት ሙያም ሆነ'ፍቅር በልብ ነው» ብለው መምሩም ማእዱን ከመባረካቸው በፊት ፥ «ደግ አይደለም ብያለሁ» አሉ ።

«ምኑ ?» አለች ።

ጉንጮችዋ ሊፈነዱ የደረሱ የፅጌረዳ እምቡጦች መስለዋል ። አይ ኖችዋ እንደ ባህር እንቁዎች ያበራሉ ። የደም ግባትዋ ከሩቅ ይጣራል ። ጠጉርዋ ለስለት የቀረበ ጥቁር የሆር ነዶ ይመስላል ።

«ደሀ ተያይዞ ባደባባይ መታየት !» አሉ ፊታውራሪ ። «ጨዋ ካሳደ ገው ጨዋ ልጅ የሚጠበቅ ነገር አይደለም ። ስሜትን ባደባባይ መግለጥ የእንስሳ ጠባይ ነው ። ስሜታችንን ካልተቆጣጠርንና በልኩ ካላደረግነው ሁዋላ ከእንስሳ በምን እንሻላለን ? ያበሻ ፈረንጅ መሆን ጥሩ አይደለም ። አጉል ነው ።

«ጣሊያኖችን የምጠላው በዚህ ምክንያት ነበር ። ፍቅራቸውም ሆነ ጥላቻቸው ፊት ለፊት ነው ። ፈረንጆች በጥበብ የመራቀታቸውን ያህል

በጠባይ ወደ እንስሳ ደረጃ ተመልሰው እየወረዱ ነው ። ስሜትን በወግ ፥ በልክ ካልያዙት ያስጠላል ፥ ያስድባል ። ከእንግዲህ በናንተ ምክንያት መሰደብ የለብኝም !» አሉ ። በዚያው ንግግራቸውን አላቆሙም ። ቀጥለውም ፥ «የማእድ ሰአትም መከበር አለበት ። የለት እንጀራችን አፉን ከፍቶ እንዲጠብቅ ማድረግ ከነውርም ሀጢአት ነው ። ማንኛውም ሰአት መከበር አለበት ። ለሁሉም ጊዜ አለው ። ከእህል ጋር የምንገናኝበት ጊዜ ፥ የእረፍት ጊዜ ፥ የስራ ጊዜ—ሁሉም ጊዜ ፥ ጊዜ አለው ። በተለይ ባገራችን የማእድ ጊዜ ከሁሉም ይበልጥ ይከበራል ። እኛ እንደ ፈረንጆች እንደ ኩብት በደረሰንበት ስንግጥ እንውልም!» በማለት ሲናገሩ ሁለቱ እየሰረቁ ይጠቃቀሱ ነበር ።

ያን ቀን ማታ ሀዲስ አይናለምን እንግሊዝኛ ሲያስተምራት ከቆየ በሁዋላ ፥ ባወጣላት ስም «አለምዬ» ብሎ ጠርቶአት ፥ «የዚህ መከረኛ ትምህርት ቤት ስራ ቢያልቅልኝ እዚህ አንድም ቀን አላድርም ነበር ። መማር ይኖርብሻል ። እዚህ ጊዜ ማጥፋት የለብንም» አላት ።

«ባባዬ ነገር ተቆጥተህ ነው ?»

«ቁጣ እንኳዋን አይደለም ። ግን ከትምርትሽም ሌላ ነፃነት እንዲኖረን ያስፈልጋል ። የራሳችንን ህይወት መኖር አለብን ።»

«ግን እንዴት ? አባቴ እንደ ሆነ ሌላ ቦታ የመሄዳችን ጉዳይ ቀርቶ ከዚህ ግቢ እንድንወጣ አይፈልግም።»

«ስለሚወዱሽ ነው ። ይህን አትርሺ ። ካንቺ መለየት አይፈልጉም» ብሎ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አደረገና ፥ «እኔና እሳቸው ላንቺ ያለን ፍቅር አንድ ቀን መጋጨቱ አይቀርም ። ችግር ይታየኛል» አላት ።

«የምን ችግር ?»

«ይገሮሽ ለመሄድ የተነሳሁ እለት የፈጠጠ ችግር ብቅ ማለቱ አይቀርም. . .»

«ለምን ተብሎ ! እንዳልከው የራሳችንን ህይወት መኖር አለብን ።

«በዚያ ላይ መማር እፈልጋለሁ ። እዚህ ደንቆሮ መቅረት አልፈልግም ። አንተም ትምህርትህን መጨረስ አለብህ» ።

«እምን አለምዬ ፥ ግን የማይታይሽ ነገር አለ ።»
«ምን?»

«ፊታውራሪ የንብረታቸውን አስተዳደር ሁሉ ወደኔ መግፋት ከጀመሩ ቆይተዋል ። ከጭሰኞች ገንዘብ ቆጥሮ መቀበል ፥ እርቦ ማስፈር ፥ ቡና ማስመዘን ፥ የቤት ኪራይ መቀበል ፥ ወፍጮ ቤቶችን መቆጣጠርና የጭሰኞችንና የቤት ተከራዮችን አቤቱታ መስማት ካሁኑ አስጠልቶኛል» ብሎ ከተቀመጠበት ተነስቶ እየተንጐራደደ ፥ «መቼ በዚህ ብቻ ። የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር የሆንኩት በምን ምክንያት መሰለሽ ? ያባትሽና የታፈሰ ስራ ነው ። በዚህም በዚያም ብለው እዚሁ እንድቀር ነው የሚፈልጉት ። በዚህ የተነሳ ያለ ስሜ ስም ወጥቶልኛል» ብሎአት አስተማሪዎች ከበስተ ጀርባው የሚሉትን ይነግራት ጀመር ።

ጠጉርዋን ሹሩባ እየሰራች ታዳምጠዋለች ። የማሾው ብርሃን ክፍሉን አጥለቅልቆታል ። እናትዋ በህይወት ሳሉ የሱጹን ወይዛዝርት ተቀብለው የሚያስተናግዱበት አልፍኝ ነበር ። አልፍኙ መሃል ብረት የመሰለ ትልቅ ምሰሶ ቆሞ ይታያል ። የቤቱ ማገሮች ሁሉ የታሰሩት በምርጥ መጫኛዎች ነበር ። አባትና እናትዋ የጫጉላ ቤት ጊዜአቸውን ያሳለፉት ከዚሁ ቤት ውስጥ ነበር ይባላል ።

«እነሱ እንደሚሉኝ ብሆን ኖሮ አይቆጨኝም ነበር ። ግን ፣ የሌለኝን መልክ ሲሰጡኝ ያሳዝናል» አላት ።

«ምን እናደደህ ? ሰዉ ከሰው ራስ ላይ አይወርድም ። የፈለጉትን ይበሉ እንተነትክን እንደሁ የሚለውጠው የለም» አለችው ።

«እንዲያው ስታስቢው ለሀብት ብዬ ያገባሁሽ ይመስልሻል ?»
«ከዚህ በፊት ይህንኑ ጥያቄ ደጋግመህ ጠይቀኸኛል . . .»
«አዎን ፣ ግን መልስ አልሰጠሺኝም ።»

ሹሩባዋን ሰርታ ስለ ጨረሰች ነጭ ሻሽ ሸብ አደረገችና ፣«‘ሰው ስለ ራሱ የሚወራውን ነገር ሁሉ ሰራዩ ብሎ ከሰማ ያብዳል’ ይላል አባቴ» አለችው ።

«ለምን እንዲህ ይሉኛል!»
«ምን ነካህ?»
«ለንፁህ ስሜቴ ለምን የተጣመመ ትርጉም ይሰጡታል!»
«ቅናት ነው ።»

«በሌላው አይን ውስጥ ያለውን ትንሽ ጉድፍ ትተን በራሳችን አይን ውስጥ ያለውን ትልቅ ግንድ የምናይበት ጊዜ መቼ ይመጣ ይሆን !» አለ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

እየተነሳች ፣ «በጣም መሽቶአል ፣ እንተኛ ። ነገ እሁድ ነው ። ከቤተ ስኪያን የቀረን እንደ ሆነ መምሩና አባቴ ይገ’ሉናል» ብላ ሳቀችና ፣ «ደግሞ ‘ከህይወት ውጭ ሃይማኖት አላውቅም’ እንዳትለኝ ። መስማት አልፈልግም» ብላው ወደ መኝታ ቤት ልትሄድ ስትል ፣

«ነገ’ኮ የወላጆች ቀን ነው» አላት ።

«ታዲያ የወላጆች ቀን የሚከበረው በሌሊት ነው?» ብላ ወደ መኝታ ቤት ሄደች ።

—ይህ የተረገመ ትምህርት ቤት አለ ፤ ከዚያ መከረኛ ትምህርት ቤት ስራ እስከ ወዲያኛው ተገላገሉ በራሳቸው ትንሽ አለም ውስጥ በሰላምና በፍቅር መኖር የሚጀምሩበት ቀን ነበር የናፈቀው ...ያ ቀን መቼ ይመጣ ይሆን ? ያ ውብ አለም የት ይሆን የሚገኘው?... ማሾውን አጥፍቶ ተከተላት......

ደስ የሚል እሁድ ነበር ። ሰማዩ እንደ ምንጭ ውሀ የጠራ ፤ ፀሀይዋ እንደ ሙሽራ ያማረች...ደስ የሚል ቀዝቃዛ አየር ይነፍሳል ። ባንድ ፊት

የሕሁድ ገበያ ቆሞአል ። በሌላ በኩል የወላጆችን ቀን ምክንያት በማድረግ በእልቱ ማርያም ትምህርት ቤት በአል ተዘጋጅቶ ግቢው በሰንደቅ አላማዎች ፣ በዘንባባዎችና በአበቦች አጊጦ አሸብርቆአል ።

ግቢው በእንግዶች ተጣቦአል ። ፊታውራሪ ተካ ባር ኢጆርሶ ፣ ታፈሰ ብሩ ፣ እያናለም ፣ የሃምሳ አለቃ ጎይቶምና ሌሎች ታላላቅ እንግዶች የክብር ስፍራቸውን ይዘዋል ። የወረዳው ገዥ ፣ አቶ ጥላሁን ሸዋረጋ የሉም ። ስለ ትምህርት ቤቱ ስራ ርምጃ በየጊዜው በሚሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫና ምናልባትም ከህዝብ ዘርፈው ለባለስልጣናች በሚያቀርቡት መተያያ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ፣ በንጉስ ነገስቱ መልካም ፈቃድ ፣ ከካባ ሽልማት ጋር የቀኛዝማችነት ማእረግ ተሰጥቶአቸው የሶርና ገባን አውራጃ በመሾም ከሱጴ ከሄዱ አስራ አምስት ቀን አልፎአቸዋል ...

ሹመቱ ፣ አልሸኹም ዞር አሉ አይነት ቢሆንም ፣ አቶ ጥላሁን ተሹመው ርቀው መሄዳቸውን ሲሰማ የሱጴ ህዝብ በታላቅ እፎይታ ነበር የተነፈሰው ። ተጋና እንደሚነገረው ሄዶ ሹመት ያዳብር ያላቸው ሰው አልነበረም ። የደገሱት ድግስ በከንቱ ቀረ ። ለማኝ እንኳዋን በደጃቸው አልዞረም ይባላል ። ሆናም ከህዝቡ ጥላቻ ያገኙት ትምህርት የለም ። «የሱጴን ህዝብ ምን በደልኩት? በደከምሁለት ፤ አይትን በከፈትሁለት እንዲህ ጉድ ያ'ርገኝ ! ብሻርማ ምን ሊያ'ረገኝ ኖርአል ? ደግነቱ አሁንም ሱጴ በጇ ናት ። ቆይ ብቻ ! እያሉ በመዛት እዳ እንዳለበት ሰው በሌሊት ተነስተው ነበር የሄዱት ....

ትኩስ ቡናና ሻይ ፣ ለስላሳ መጠጥ በያይነቱ በገፍ ይቀርባል ፤ ይሸጣል ፤ ይጠጣል ፤ ሁለት ሶስት ቦታ ላይ በብረት ምጣድ የሚታመሰው የበግና የፍየል ጥብስ ይንቻቻል ፤ ምራቅ ያስውጣል ። ዳቦው ፣ ድፎ ዳቦው ቆሎውና ዳቦ ቆሎው—በያይነቱ ነበር ። ጋሼ ዱቤ ይገምጥጣል ፤ ይቆረጥማል ፤ ይጎነጫል ። እና ፣ ያዘጋጀውን የስፖርት ውድድርና ጅምናስቲክ ለማሳየት ይጣደፋል ፤ ተማሪዎቹን ያጣድፋል ።

በደንብ ልብሳቸው አጊጠው የተሰለፉት ምርጥ ተማሪዎች ሁለት መዝሙሮች ካሰሙ በሁዋላ ፣ ሀዲስ ሳህሌ ንግግር ለማድረግ ለዚሁ ከተዘጋጀ አንድ ሳጥን ላይ ወጥቶ ቆመ ። ፀጥታ ሰፈነ ።

እንግዶቹን እንኳዋን ደህና መጣችሁ በማለት በመምህራኑ ፣ በተማሪዎቹና በራሱ ስም ምስጋና በማቅረብ ፣ በወላጆችና በመምህራን ፣ እንዲሁም በትምህርት ቤቱና በወላጆች ፣ ባጠቃላይ በትምህርት ቤቱና በሱጴ ህብረተሰብ መካከል ሊኖር ስለሚገባው ጠንካራ ግንኙነት አንስቶ ንግግር ሲያደርግ ከቆየ በሁዋላ ፣ «አዎ ፣ በወላጆችና በመምህራን መካከል ጥሩ ግንኙነት መኖር አለበት ። ልጆችን ወደ ትምህርት ቤት መላክ ብቻ አይበቃም ። የመምህራኑም ስራ ልጆችን ፊደል ማስቆጠር ብቻ አይደለም ። በሚቻል ሁሉ መምህራን ስለ ተማሪዎቻቸው ቤተሰብ ሁኔታ ለማወቅ መጣር አለባቸው ። የነገውን ትውልድ በጥሩ ሁኔታ ኮትኩተን ማሳደግ የምንችለው በወላጆችና በመምህራን መካከል የጋራ ትብብርና ጥረት ሊኖር ሲችል ነው ። ትምህርት ቤት ዶሴት አይደለም ።

«ትምህርት ቤት የህብረተሰቡ አካል ፣ የህብረተሰቡ ችግር ተካፋይና ለህብረተሰቡ ችግር መፍትሄ ሰጭ መሆን አለበት ። እና ፣ ለዚህ የጋራ ጥረትና ትብብር አሁን በያዝነው የትምህርት አመት ሰፊ እድል ይጠብቀናል ። እንደምታዩት አዲስ ትምህርት ቤት እየተሰራ ነው ። አዲስ ህንፃ ብቻውን አዲስ ትምህርት ቤት አይሆንም ።

«በወደቀው ወርካ ምክንያት አዲሱን ትምህርት ቤት በጥላቻ አይን የሚመለከቱ አንዳንድ ሰዎች አይጠፉም ። አንዳንድ ትንኮለኞች እንደሚሉት ወርካውን የጣለው ሰው አይደለም ። ስለዚህ ፣ ትምህርት ቤቱን በጥላቻ አይን እንዳይመለከቱት ፣ የትምህርት እድል በሚናፍቁት ስፍር ቁጥር በሌላቸው ምስኪን ልጆች ስም አደራ እላለሁ» በማለት በቃል ያደርግ የነበረውን ንግግር ሲጨርስ ፣ እንግዶቹ ሁሉ የተሰማቸውን ደስታ በጭብጨባ ገለጡለት ።

ተማሪዎቹ ሌሎች ሁለት መዝሙሮች አሰሙ ። የአካል ማጠንከሪያ ትርኢት ቀጠለ ። በሚገባ የተቀነባበረ ቆንጆ ትርኢት ነበር ። የተማሪዎች ስፖርት ውድድር ሲጀመር ፣ ታፈስ ብሩ መጥቶ ፣ «እንኳዋን ደስ ያለህ ። ጥሩ ንግግር ነበር» አለው ሀዲስን ።

«ከልብ የሚናገሩት ነገር ሁሉ ጥሩ ነው» በማለት መለሰለት ።
«በትምህርት ላይ እምነት ያደረብህ ትመስል ነበር ስትናገር» አለው ።
«ነውና » አለ ሀዲስ ።

«ላንድ አመት ብቻ የመጣህ መስሎኝ ነበር» አለው ፣ አሁንም በምፀታዊ አነጋገር ።

«ነበር ። ግን አሁንም እዚህ ነኝ።‘ሴላቪ’ይላል ፈረንሳይ» አለ ሀዲስ።
«አስተማሪ ለመሆን ቆረጥክ ማለት ነው?»

«ቆረብኩበት ። እውነቴን ነው ። ህግ ለመማር ነበር ፍላጎቴ ። አሁን አሳቤን ለውጫለሁ» አለ ሀዲስ ፣ አዲሱን የትምህርት ቤት ህንፃ በፍቅር አይን ከሩቅ እየተመለከተ ።

«ለምን?»

«መምህርነት ክቡር ሙያ ነው ። ክቡር ሙያ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን የሰውን ችሎታ ፣ ትእግስትና ነፍስ የሚፈትን አስቸጋሪ ሙያ ነው ። ሳስበው ፣ የወደፊቱን ህይወት ገንቢዎች ከማፍራት የበለጠ ደስ የሚል ሙያ ያለ አይመስለኝም» አለው በስሜት ።

የወላጆች የጆንያ ሩጫ ውድድር ተጀምሮ ስለ ነበረ ሰው ሁሉ ይስቃል ።

«የወደፊት ህይወት ገንቢዎች ስትል መጠንቀቅ አለብህ» አለ ታፈስ።
«ምን አይነት ጥንቃቄ?»

ታፈስ የጠበቀው ጥያቄ ነበረና ፣ «ባሁኑ ጊዜና ወቅት መሪዎች ሲሆኑ በሚችሉት ላይ ማተኮር ያስፈልጋል ። ትምህርትን ለማዳረስ ሲባል የቀ

ለም ትምህርት እንዲሳተፉ ማድረግ የማያስፈልግ ችግር መፈልፈል ይሆናል ። አደገኛ ነው» ብሎት ፣ አርእስተ ነገሩን ለወጠና ፣ «የፖለቲካም ሰው ሆነሃል» አለው ።

«እንዴት ?» አለ ሀዲስ ።

ታፈሰ ቶሎ ብሎ አርእስተ ነገሩን የለወጠው ፣ «አደገኛነቱ ለማን ነው?» የሚለውን ጥያቄ ለመሸሽ አስቦ እንደ ሆን ሀዲስ ነገሩን አላጣውም ። ክርክርም ለማንሳት ጊዜና ፍላጎት አልነበረውም ።

«ወርካውን የጣለው ሰው አይደለም ስትል አሳከኝ ። የተደጋገመ ውሸት እያደር እውነት ይሆናል የሚሉትን ጥበብ ይዘሃል» አለው ።

«አሁንስ ቢሆን ማን ጣለው ልትለኝ ነው !» ብሎት የእጅ ሰአቱን ተመለከተ ። አዲሱን ህንፃ ለወላጆች የሚያስጎበኝበት ሰአት ደርሶ ነበር ።

«ግን አንድ ነገር እንዳትረሳ» አለ ታፈሰ ።
«ምን ?»
«ያዲሱን ትምህርት ቤት ስም» ብሎት ዞር አለ ።

ሀዲስ የክብር እንግዶችንና ወላጆችን ይዞ ስለ አዲሱ ህንፃ ፕላንና ስራ አጭር ገለፃ ካደረገ በሁዋላ እየዞረ ያስጎበኛቸው ጀመር ። አይናለም ከእነሱ ጋር አልነበረችም ። የትምህርት ቤቱን የውስጥ ጉብኝት ጨርሰው ሲወጡ አይናለም ፣ እንቁላል በማንኪያ ይዛ ሩጫ ውድድር ላይ ስትካፈል በሩቅ ተመለከታት ። ቀድማ ነበር ። ውድድሩን ባሸናፊነት ለመጨረስ ትንሽ ሲቀራት እንቁላሉ ወደቀባት ። ሀዲስ ሳቀ ። ፊታውራሪ ይመለከቱዋት ኖሮ ራሳቸውን ነቀነቁ ።

«ይህ ደግሞ ምንድን ነው ?» አሉት ።
«የትምህርት ቤቱ ደወል ነው» አላቸው ።

ስራው ገና ያላለቀ በአክሱም ሀውልት ቅርፅ የተሰራ ማማ ይታያል ።

ፊታውራሪ የትምህርት ቤቱን ስራ በማድነቅ ፣ «ተአምር ነው» ካሉ በሁዋላ ወደ ታፈሰ ዞር በማለት ፣ «ወደ እንደዚህ አይነቱ በጎ ስራ ልብህ ቢመለስ ጥሩ ነበር ። ሀብት ጤዛ ነው» አሉት ።

ታፈሰ ከሁዋላቸው ቆሞ ነበር ። መልስ አልሰጣቸውም ። ግን ነገራቸው ሆዱን እንዳደበነው ፊቱ ላይ ይታወቅ ነበር ። ፊታውራሪ ከሀዲስ ጋር ሲያወዳድሩት ሁልጊዜ ይናደዳል ። እና ፣ ለሀዲስ ያለው ጥላቻ ስር እየሰደደ ይሄድ ነበር ። ግን ጥላቻው ፊቱ ላይ አይነበብም ። ሀዲስን ሲያየው ይስቃል ፣ ይጫወታል ። ሲያመቸው በነገር ነካ አድርጎት ይሄዳል ።

«ግን ምን ያደርጋል ?» አሉ ፊታውራሪ ፣ «አንዱ በለፋ ሌላው ክብርና ሹመት ይነግድበታል ። መቼም የተቀማጭ አፉ ምላጭ ነውና።»

አቶ ጥላሁን ቀኛዝማች ተብለው ሶርና ገባን መሾማቸው ፣ እንደ እግር ውስጥ እሳት ያቃጥላቸው ነበር—ፊታውራሪን ።

በእሉ እየደመቀ ሄዶ ነበር ። በልዩ ልዩ ክፍሎች መካከል የሚደረገው የስፖርት ውድድር ተጋግሎአል ። ሀዲስ ፥ አይናለም ከፋጡማ መሀመድ ጋር ቆማ ስታወራ አይቶ ወደ እነሱ ሄደ ። ፋጡማ ገና ስታየው ጥላቸው ሄደች ። እንደ ዱሮዋ አትስቅም ።

አይናለም በሁኔታዋ ተገርማ ፥ «ምን ነካት ?» አለች ።
«እኔን አፍራ ይሆናል» አላት ።

«የለም ፥ እኔንም አላናግር ብላኝ አኩርፋ ነበር ። በጣም ጉዋደኛዬ ነበረች ።»

«እውነት? እዚህ ሳለሽ ?»
«አዎ ፥ እንለያይም ነበር ።»
«ታዲያ አሁን ምን ነካትና ታኮርፋለች ?» አለ ሀዲስ ።
«እኔ እንጃ !»

«ግድ የለም ። አንድ ቀን ቤት እንጋብዛታለን ። ከዚያ በሁዋላ እንደ ገና ጉዋደኞች ትሆናላችሁ» አላት ።

«ያኔ እንደ መጣህ ቤት እየመጣች ስላንተ ብዙ ታወራልኝ ነበር» አለች ።

«እውነት? ምን እያለች?»

«ጥሩ አስተማሪ መጣልን ። አቤት ቀልዱ ደስ ሲል ፤ ትምህርቱ ሲጥም ትለኝ ነበር ። ዝናህን ስታወራልኝ ነበር የምትውለው» አለች ።

«በዝና ነዋ ልብሽ የገባሁት» አላት እየሳቀ ።

ጉንጮችዋ ባንዴ ፍም መሰሉ ። ወዲያውኑ አንዱ ተማሪ መጥቶ ቁራጭ ወረቀት ሰጠው ። ሀዲስ ወረቀቱን አነበበ ። ሆኖም አሳቡ መልእክቱ ላይ አልነበረም ያረፈው ። የእጅ ፅሁፉ ነበር የማረከው ።

«ምን ሆንክ ?» አለችው አይናለም ።

«ይህ የእጅ ፅሁፍ ትዝ ይልሻል ?» አላትና ወረቀቱን ሰጣት ። ቀውሴ የላከው መልእክት ነበር ።

አይናለም ፥ የእጅ ፅሁፋን በጥንቃቄ ስትመለከት ቆየችና ፥ «አዎ ፥ ትዝ አለኝ ። ያንን ደብዳቤና ይህን የፃፈው ሰው አንድ ነው» አለች ።

«ልክ ነሽ»አላት ደንግጦ ። ግን ለማረጋገጥ ያህል ፥ «ይህን ወረቀት ፅፎ የሰጠህ በርግጥ ቀ...እ—እቶ ታከለ ነው ?» በማለት ወረቀቱን ይዞ የመጣውን ተማሪ ጠየቀው ።

ተማሪው መልስ አልሰጠም ።

«አትናገርም እንዴ ?»

ተማሪው ዲዳ ነበር ። ግን ፥ ጆሮው ትንሽ ትንሽ ይሰማል ።

«ይህ የማን እጅ ፅሁፍ ነው ?» አለው ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

ተማሪው ወደ ራሱ አመለከተ ። ሀዲስ ራሱን ይዞ ቀረ . . .

ህዳር አለፈ ። ታህሳስ መጣ ። የሰው አይን እየነመራ በሚሄደው ቡና ፍሬ ላይ አርፎ ነበር ። የቡጂ አየር ለለውጥ ያህል ቀዝቀዝ ብሎአል ። ከዲሳባ የሚነፍሰው ወሬ ግን ሞቅ ያለ ነበር ። ሆኖም ፣ ጋዜጣውም ሆነ ራዲዮኑ ምንም የሚሉት ነገር አልነበረም ። የተለመደው ዜና ፣ ሀተታና ዘፈን—ሌላ ነገር የለም ።

ለማንኛውም ነገር ሀዲስ ለወሬ ጊዜ አልነበረውም ። ስራ ። ስራ ። ስራ ። ለነፃነቱ ነበር የሚሰራው ። በእሱና በነፃነቱ መካከል የቆመ ነገር ቢኖር የትምህርት ቤቱ ስራ አለ ማለቅ ነበር ። የስራው አካሄድ ነፃነቱን ሊሰጠው የሚፈልግ አይመስልም ። ግን ያለ እረፍት ይሰራ ነበር ። ከፊታውራሪ ተካ ጋር የምሳ ሰአት ቀጠሮውን ለመጠበቅ ከሚሮጠው በቀር ቀኑን ሙሉ አያርፍም ። ይሰራል ። እንደ እብድ ይሰራል ።

አይናለም ደስ ያላት አትመስልም ። ያለ አመልዋ አመል አውጥታ መነጫነጭ ጀምራለች ። ተነስቶ ሊሮጥ ሲል ፣ «ከትምህርት ቤቱ ስራ ሌላ የሚታይህ ነገር የለም ። አንደኛውን ጠቅለህ እዚያው ለምን አትገባም!» ትለዋለች ።

«አለምዬ ፣ ለነፃነታችን ነው'ኮ የምሰራው ። ስራውን የጨረስኩ ለት ነፃ እንሆናለን ፤ ትምህርት ቤት ትገቢያለሽ» ቢላትም አይገባትም ፣ ወይም እንዲገባት ስለማትፈልግ ዝም ብላ ታኮርፋለች ።

ፊታውራሪም ሁኔታውን በማየት ፣ «የት ለመድረስ ነው እንዲህ የምትሮጠውና የምትጣደፈው ? ለሁሉም ጊዜ አለው ብሎአል ሰ‥ሞን ። ሰው ያስባል ፣ እግዜር ይፈፅማል» እያሉት ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሀሳ‥ነት እየ ጫኑበት ይሄዳሉ ። ሳያማክሩት 'ልጅ ሀዲስ ሳህሌ ያለኝን ንብረት ሁሉ እንዲያስተዳድር ሙሉ ስልጣን የሰጠሁት መሆኔን በተለመደው ፊርማዬ አረጋግጣለሁ' . . . » በማለት ማዘዣ ፅፈው ለሚመለከተው ሁሉ ከበትኑ ቆይተዋል ። «ይሄዋ ! አላልንም ነበር ? አጅሬ የሽማግሌውን ሀብት ጠቅ ለለ» የማይል ሰው አልነበረም—በተለይም መምህራኑ ።

ከስራው መጉዋተትና ከሀሜቱ ሌላ ያስተዳደሩም ስራ ያናድደው ነበር ። ደመወዝ በወቅቱ አይደርስም ። 'ምን እየበላን እናስተምር?' በማለት አስተማሪዎች ይነጫነጩበታል ። እውነትም አብዛኛዎቹ የሚኖሩት በዱቤና ባራጣ ብድር ነበር ። አራጣ አበዳሪዎች ወር ጠብቀው ሲመጡ አስተማሪዎቹ ተነስተው ከስራ ገበታቸው ላይ ይጠፋሉ ። አስተማሪዎቹ ቢገኙም የትምህርት መሳሪያዎች አብዛኛውን ጊዜ አይገኙም ። 'በምን እናስተምር ?' የሚል ጥያቄ በየእለቱ ይቀርብለታል ። 'ጠመኔ እንሁንልህ ወይስ ወረቀት ? ሽሚዞቻችን ጫፍ ላይ እየፃፍን እናስተምርልህ?' በማለት የሚያንጉዋጥጡትም አንዳንድ አስተማሪዎች ነበሩ ። ይህ ሁሉ ተዳምሮ ያበሳጨዋል ። ሁልጊዜ ያበሳጨዋል ። ርግጥ ብሶታቸው ብሶት ነበር ። ግን በብሶት የተነሳ ዲስፕሊን የሚላላበትና ተማሪዎች የሚበደሉበት ምክንያት ሊታየው አልቻለም ። የመምህራን ስብሰባ የሚደረግበትን ቀን ጠብቆ ስለ ዲስፕሊን ጉዳይ አነሳ ። ምንም አዲስ ነገር አልተናገረም ። እነሱም ለበኩላቸው በግማሽ ልብ ነበር የሚያዳምጡት ።

በመጨረሻ ፣ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አድርጎ ፣ «አዎን ፣ ችግራችሁ ይገባኛል ። የናንተ ችግር የኔም ችግር ነው ። ጠመኔዎች የሉም ። ወረቀቶች የሉም ። መፃህፍት የሉም ። አዎን ፣ እነዚህ ሁሉ የሉም ። የሰራች ሁበት ደሞዝ እንኳዋን በጊዜ መጥቶ አይከፈላችሁም ። ግን ፣ ችግር አለ ብለን መዘረክረክና መላላት የለብንም ። ከዚህም የባሰ ችግር ቢመጣ በብርታት ወደ ፊት መግፋት አለብን ። ብርቱ ችግር በሚገጥምበብት ጊዜ በብርታት ወደ ፊት መግፋት የሚችሉት ብርቱዎች ብቻ ናቸው ይባላል ። የመምህራን ተልእኮ ይኸው ነው ። አለዚያ አርአያነታችን ከምን ላይ ነው ?» አለ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

ክፍሉ ፀጥ ብሎአል ። እንደ ዮሀንስ መጥምቁ በከንቱ ብቻውን በምድረ በዳ እንደ ጮኸ ቆጠሩት—እሱም ዝም አለ ።

«የደላው ሙቅ ያኝካል ይባላል!» አለ 'ማይዘር' ።

ሽሙጡ ቢገባውም ሀዲስ የመናደድ መልክ አሳሳየም ፣ «እንደኔ ይድላህ!» አለው ።

ቀጥሎ የተናገረው 'ታዲያስ' ነበር ። «ያለውን አብቃቅታችሁ ለመስራት ሞክሩ ፣ ቆጥቡ ፣ አታባክኑ ስትል ምን ለማለት ፈልገህ እንደ ሆነ አልገባኝም ? ጠመኔና ወረቀት ትሰርቃላችሁ ማለትህ እንደ ሆነ በቀጥታ ንገረን . . .»

«አልወጣኝም !»
«ታዲያ ምንድን ነው የምትለው ?»

«ለተማሪዎቻችን ያለብንን ሀላፊነት በጋራ እንወጣው ነው የምለው ! ችግርና ብሶት ያለብንን ሀላፊነት ሊያስተን አይገባም !»

«የሌለ ነገር መቆጠብ የምንችልበትን መንገድ ካሳየኸን ምናለ ታዲያ !» አለ 'ማይዘር' እያሾፈ ።

ዱቤ ለጠቀና ፣ «ስለ ቁጠባ ማስተማር እኛን አልነበረም ። ምን የምንቆጥበው ነገር አለና ? አህያውን ፈርቶ ዳውላውን አሉ ። ላይ ላሉት ሰዎች ብታሰማ ይሻላል ። የሚባክኑ ነገሮች ያሉት እዚያ ነው . . .»

ሀዲስ ነገሩን አቋዋረጠው ፣ «ለነማን ?» ብሎ ጠየቀው ።

ዱቤም ፊቱን አዙሮበታል ። መልስ አላገኘም ። እሱው ቀጠለና ፣ «ለንጉሱ ነገስቱና ለሚኒስትሮቻቸው ማለትህ ነው? »አለው ።

«አልወጣኝም ! ጎመን በጤና !»
«ምን አስፈራህ ? እውነቱን ተናግሮ እመሸበት ማደር ነው . . .»
«ተናግሮ ከሚያናግር ሰውረን !» አለ ዱቤ ።
«አሜን!» ጋሼ 'ታዲያስ' ነበር ።

«ጌቶቼ ስሙኝ !» አለ ሀዲስ ድምፁን ከፍ አድርጎ ፣ «የኛ እርስ በርስ በነገር መጎሻሸም ዋጋ የለውም ። የትም አያደርስንም ። ከባድ ሀላፊነቶች ተሸክመናል ። እነሱም ውጭ ሲንጫጩ የምትሰሙዋቸው ልጆች ናቸው ።

«እነሱ ከኛ የሚጠብቁት ብሶታችንን እሮሮአችንን ሳይሆን ፣ ፍቅ
ራችንን መስዋእትነታችንን ፣ ሙሉ አእምሮአችንና ጉልበታችንን ነው ።
እምን ፣ ይህን ስል አንዳንዶቻችሁ በሆዳችሁ ትስቁብኝ ይሆናል ። አሉባ
ልታ ልማዳችን ነውና አይገርመኝም ። የማይሰራ አእምሮ የሰይጣን መደ
ብር ነው ይባላል ። ቅን ልቦና የሌለው ሰው ምን ጊዜም ቢሆን ሌላው ቅን
ያስባል ብሎ ሊያምን አይችልም ።» በንዴት እየገነፈለ ፣ «ይህን ትምህርት
ቤት ስሰራ ቆማችሁ የምትስቁብኝ ሰዎች አላችሁ ። የራሴን ታሪክ የምገ
ነባ ወይም መረማመጃ ድልድይ የምሰራ የሚመስላችሁ ሰዎችም አትጠ
ፉም ። ለማንኛውም ነገር ስለኔ የፈለጋችሁትን ልትሉ ትችላላችሁ ። ከባ
ለቤት ያወቀ ቡዳ ነው እንደሚባለው የልቤን የማውቀው እኔ ነኝ ። ይሁ
ንና እዚህ እስካለሁ ድረስ ከዛሬ ጀምሮ በዚህ ትምህርት ቤት ስርአት ይኖ
ራል ! ይከበራልም!»

ያን ቀን ለምሳ ቤት አልሄደም ። ባንድ ጀንበር ፣ ፊቱ ላይ የቆመውን
መሰናክል—የትምህርት ቤቱን ስራ—ለማስወገድ የተነሳ ይመስል ነበር—
እንደ እብድ ሲሰራ ላየው ሰው ። ስራ ፈተው የሚቆሙት ሰራተኞች ላይ
ይጮህ ነበር ። ይሰድባቸው ነበር ። መሳሪያዎቻቸውን ቀምቶ ሁለተኛ
እዚህ እንዳላያችሁ ! በማለት ያባርራቸው ሰራተኞችም ነበሩ ። ልትጠልቅ
እያቆለቆለች በምትሄደውም ጀንበር ላይ ጮኸ !

ቤት ሲደርስ እንደ ልማዱ ሮጦ ሄዶ አይናለምን አቅፎ አልሳማትም ።
ወደሱ ልትሮጥ ከቃጣች በሁዋላ በሁኔታው ተደናግጣ ቆም አለችና ፣
«የት ነበርክ?» አለችው ።

«የት የነበርኩ ይመስልሻል ! ስራ ላይ ነው የዋልኩት !»
«ለምን ትጮሃለህ ታዲያ ?»
«አልጮህኩም!»
«ለምሳ ተጠብቀህ ነበር ። »

«የፈለጋችሁትን ያህል ጠብቁኝ ! ካልራበኝ አልበላም ። ግዴታ የለ
ብኝም ። ነፃ ሰው ነኝ ። እኔ እንቺን ያገባሁት አባትሽን ማእድ ለማቋቋረስ
ወይም ወኪል ለመሆን አይደለም!»

«ምን ሆነሃል ?» አለች የታችኛውን ከንፈርዋን ጣል አድርጋ ። አይ
ኖችዋ እንባ አቅረው ነበር ።

ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አደረገ ። ሳንዳፍታ ዝም ብሎ ተመለከታት ።
ሄደና አቅፎ ግንባርዋ ላይ ሳማት ። እንባዎችዋ ኮለል ብለው ወረዱ ።

«አለምዬ ፣ ይቅርታ አድርጊልኝ» አላት ፣ ጠጉርዋን እየደባበሰ ።

የረጠበውን አፍንጫዋን እንደ ህፃን ልጅ ወደ ላይ እየሳበች ፣ «በጣም
ነው የተለወጥክብኝ ። ልታስፈራኝ ጀምረሃል ። እንዲህ አልነበርክም»
አለችው ።

«ልክ ነሽ» ብሎአት እንባዎችዋን ጠረገላት ።
«ምን እየሆንክ ነው?»

«ምን እንደ ሆንኩ አላውቅም» ብሎ እንደ ገና ግንባርዋ መሃል ላይ
ሳማትና ፣ «ምናልባት ነፃነታችን እየናፈቀኝ ይሆናል ። እና ፣ የዚህ ትም

ሀርት ቤት ስራ መጉዋተት ያንን የምናፍቀውን ቀን እያራቀው ያናድደኛል ። በዚህ ላይ ደ'ሞ የሰዉ ነገር ያበሳጨኛል ። ግን አታስቢ ። ሰላም ይኖረናል ። እና ፣ ጎተራ ሙሉ ፍቅር ። እሺ አለምዬ? . . . አዎን ፣ እንደሉ ። ፈገግታሽ እንደ ጠዋት ፀሀይ ነው ። አይኖችሽ እንባዎች ሲያፈሱ ዳግመኛ ለማየት አልፈልግም» አላት ።

ተቃቅፈው እንደ ቆሙ ታፈስ ከየት መጣ ሳይባል እንደ ጥላ ውልብ ብሎ ይገባል ።

«ፍቅራችሁ አሁንም አላለቀም እንዴ!» ብሎ የእይናለምን ሆድ በሌባ ጣቱ ወጋ ወጋ ካደረገ በሁዋላ ፣ «እኮ መቼ ነው ይህ ሆድሽ ወደ ፊት ገፋ ብሎ የሚታየው ?» አላት ።

«ፈታውራሪም እሱን ነው የሚጠብቁት» አለ ሀዲስ ፈገግ ብሎ ።

«የልጅ ልጅ ማየት ይፈልጋሉ ። ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ ። ጠዋት ማታ ዳዊት የሚደግሙት ለምን መሰለህ ? የልጅ ልጅ ሳታሳየኝ አትግደለኝ እያሉ ነው ። በልጅ ልጆቻቸው ዘላለም መኖር ይፈልጋሉ ። ማንም ሞቶ ለመቅረት የሚፈልግ የለም» ካለ በሁዋላ ፣ ጃኬቱን አውልቆ ጥሎ ካንድ ትልቅ በርጩማ ላይ ሄዶ ተቀመጠና ፣ «እህት አለም ፣ ምን ዝም ብለሽ ታይኛለሽ ? ጉሮሮዬ ደርቆአል . . . አ! በነገራችን ላይ» አለና ያመጣላትን ሁለት ቢልቃጥ ሽቶ ከጃኬቱ ኪስ ውስጥ አውጥቶ ሰጣት— 'ማዳም ሮሽ' ነው ። በሴቶች ላይ የምወደው ሽቶ ነው ። አንተም ትወደዋለህ ። የሰለጠነ አፍንጫ ካለህ!»

ጉንጭና ጉንጩን አገላብጣ ስማው የሚጠጣ ነገር ልታመጣለት ስትሄድ ፣ «የእግዜር ውሀ አላልኩም ዋ ! መሬትን ያህል ነገር የሚሸረሽር የድሀ ጉሮሮ እንዴት አድርጎ እንደሚችለው አላውቅም» ሲል ሙሽባት ። አዲስ ውስኪ አምጥታ ከፈተችለት ።

«ስልጣኔ ይሉሻል ይኸ ነው !» አላት ።

«ብቻ ያለቀ እንደ ሆነ መምሩ ያኮርፉኛል ። እስቲ ያችን መድሀኒት ሳይሉኝ አይውሉም ። እምቢ ስላቸው ግዝት ነው የሚቀራቸው» አለችና ወደ ጉዋዳ ስትሄድ በአይኖቹ እየተከተላት ፣ «ቆንጆ አይደለችም ወይ? የኔ እህት ባትሆን ኖሮ ይቆጨኝ ነበር ። እድለኛ ነህ» አለው ።

«ነኝ።»

ታፈስ አርእስተ ነገሩን ለወጠና ፣ «እንደ እብድ መስራት ጀምረሃል አሉ? ጥድፊያው ምንድን ነው ?» በማለት ጠየቀው ።

«ስራውን ቶሎ ለመጨረስ ነዋ።»
«እና ?»
«እና ፣ ለመሄድ ።»

«ካሳብህ አውጣው ። ዲሬክተር እንድትሆን አድርገናል ። ትንሽ ቆይተህ ደ'ሞ ማን ያውቃል ? ፊታውራሪ ተስሚነት አላቸው ። ብር ሰሚ ጆሮ አያጣም ። ስለ ወደ ፊት እድላችሁ ማሰብ አለብን ። ያገባሃት ልጃችን መሆንዋን አትርሳ» አለው ።

ቁስሉ እንደ ተነካ ሰው ሀዲስ ድንገት ተቆጥቶ ፡ «ብትተውን ምናለ በት ! የማንንም ርዳታ አንፈልግም ። ህይወታችንን ፕላን አታድርጉልን ። የራሳችንን ህይወት እኛው እንደ ፈለግን እንመራዋለን ። ተውን !» አለ ።

ታፈስ ካንጀቱ ስቆ ሲያበቃ ውስኪውን ከተጎነጨ በሁዋላ ፡ «የሌሎ ችን ህይወት ፕላን ለማድረግ ከሆነ ግን ወደ ሁዋላ አትልም ፡ አይደለም ?» አለው ።

«የሰው ልጅ ህይወት ጣም እንዲኖረው እመኛለሁ ።»
«ታዲያ እኛ ከዚህ የተለየ ሌላ ምን ነገር ተመኘንልህ ?»
«ነገር አታጣም!»

«ማጣመሜ አይደለም ። ማስተካከሌ ነው ። አንድ ያላስተዋልከው ነገር አለ ። ሽማግሌው በዚህ እድሜአቸው ብቻቸውን መቅረት አይፈል ጉም ። ያይናቸው ማረፊያ ይፈልጋሉ ። ከናንተ ሌላ ምን ይምጣ? እስቲ ንገረኝ ። ልጃቸውን በጣም ይወዱዋታል ። ጥሎባቸው ደ'ሞ ባንተ ላይ እምነት አላቸው ። እስብበት እስቲ ።»

«አንተ በኔ ቦታ ብትሆን ምን ታደርግ ነበር ?»

«እኔ ባንተ ቦታ ብሆን ኖሮ መጀመሪያ አላገባም ነበር ። ለማንኛውም ነገር ጨዋታችንን እንለውጥ ። የሞራል አስተማሪ መሆን ያስጠላኛል ። ሞራል የሚያበዙ ሰዎች ሀይል ካገኙ ጨቋኞች ይሆናሉ» ብሎት ውስ ኪውን ጨለጠና ሌላ ውስኪ ለራሱ ጢም አድርጎ ከቀዳ በሁዋላ ፡ «እንዳ የሁት የትምህርት ቤቱ ስራ ሲያልቅ ምንም አልቀረውም ። ግሩም ስራ ነው» አለው ።

ሀዲስ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አደረገና ፡ «እስካሁን ያልቅ ነበር ። ግን ይህ የቡና ንግድ እያለ በየት በኩል ! ሰው ሁሉ አብዶአል» አለ ።

«እኔም አብጃለሁ ። ሱዲ ጥርና የካቲት ላይ የማያብድ ማን አለ ? የቡና ንግድ ያሳብዳል ። ዋጋው ሰማይ እየወጣ ሄዶአል ።»

«ሀልምህ እውን ሊሆን ነዋ ?»
«ልክ እንደ ትምህርት ቤትህ !»
«ለዚህ ነዋ ሰሞኑን የጠፋኸው ።»
«ወደ አዲሳባ ወጥቼ ነበር ። »
«የውሀ መንገድ አድርጎሽዋል! አዲሳባ እንዴት ነው?»

«ጠፋለች ! ፍፁም ጠፋለች ። ሰው መሬት ለቆ ሲሄድ ምንም አልቀ ረውም ። አስረሽ ምችው ነው ነጋ ጠባ ። በቦሎቄ ፡ በቡና ፡ በስሊጥ ንግድ የጠገበው ያራዳ ገበሬ ብሩን የሚጥልበት አጥቶአል ። ምሽትና ንጋት የለም። እና ፡ ሴቶቹ ደ'ሞ - ዋው !»

«ሌላስ ምን አዲስ ነገር አለ ?»
«ወሬ ፡ ወሬ ፡ ወሬ ፡ እንደ ሰደድ እሳት ይቀጣጠላል ።»
«የምን ወሬ ?»

«ነገሌ ያለው ጦር አምፆአል ፤ ሌሎችም ክፍለ ጦሮች ውስጥ ውስ ጡን እየተገናኙ ነው እየተባለ ይወራል ። ከዲሳባ የተላኩትን አንዳንድ ጀኔራሎችንም ይዘው አስረዋቸዋል ይባላል ።»

«እውነት ነው ?» አለ ሀዲስ ነገሩ ቀስቅሶት ።

«ቅዠት ነው ። ምኞታቸውን ነው የሚያወሩት ። ተማሮችና ስራ አጦች እየፈጠሩ የሚነዙት ወሬ ነው ። ዋጋ ናረ ። ኑሮ ተወደደ ። የቤንዚን ዋጋ ጨመረ ። ስራ ጠፋ ። ወሎ ተራበ ። ታዲያ ምን ይሁን ! የኢትዮጵያ ገበያ ከአለም ገበያ ዋጋ ውጣ ውረድ ውጭ አይደለም ፤ ሊሆንም አይችልም። ደ'ሞ መንግስት ለሁሉም ስራ ሊፈጥር ኖሮአል ? ዝም ብለው ነው የሚ ቃዡት !»

ውጭ ሃይለኛ ንፋስ ይነፍስ ነበር ። ያፏጭጫል ። ያጉዋራል ። የቤቱ መዝጊያዎችና መስኮቶች በሲቃይ ይንሳጠጣሉ ። አይናለም ራት አስይዛ መጣች ። ቀይ ጨርቅ ትልቅ መሶብ አስቀድሞ ገባ ። ቢታቴ ድስቶች — አለላ የተከደኑ ቀሚስ የለበሱ — ተከታትለው መጡ ።

«የለውጥ ንፋስ እየነፈሰ ነዋ ?» አለ ሀዲስ ።
«የምን ለውጥ ነው የምታወራው ?» አለ ታፈሰ በነገሩ በሽቆ ።

«ኢዚህም እኮ ሰዉ ጤና አይደለም ። ኑሮ መሮታል» አለው እጁን እየታጠበ ።

«ምናለ ታዲያ ይጠብቁዋ ። መና ከሰማይ ይወርድላቸዋል !» ንፋሱ አሁንም በሃይል ይነፍሳል ። የቤቱ ጣራ ሁሉ ይንጫጫል ። መዝጊያዎ ቹና መስኮቶቹ ማቃሰታቸውን አልተውም ።

«ኢሳት ካለበት ጭስ አይጠፋም ብዬ ነው ።»

«አትቃዥ እባክህ !» አለ ታፈሰ ተቆጥቶ ። «ወታደር ውስጥ ውስ ጡን ይነጋገራል ብሎ ነገር የለም ። የመንግስቱ ንቁይ ግርግር አስተም ሮናል ። ሀይለ ስላሴ እስካለ ድረስ አንድ ነገር ይደርሳል ብለህ አታስብ ።»

«ወሎ ተራበ የሚባለውስ ?»

«እሱ ፣ ስራ የፈቱ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና የሰይጣን መደብር የሆኑ አንዳንድ ወስላቶች የሚያናፍሱት ወሬ ነው ። አገርን አለማወቅ ነው'ኮ ይህን የሚያመጣው ። ተወኝ ጃል ። ልብላበት ፣ የሀት አለም ምግብ ሳይ በርድ» ብሎ እንጀራውን ቆረሰ...

ከባድ ራት ነበር ።

ንፋሱም አላቆመም ። በሃይል ይነፍስ ነበር ። ታፈሰ ከመሄዱ በፊት ፣ «የትምህርት ቤቱ ደወል ካዲሳባ ተጭኖአል ። ምናልባት በሶስት አራት ቀን ውስጥ እዚህ ሳይደርስ አይቀርም» አለው ።

«ቆንጆ ደወል ነው ?» አለች አይናለም በወሬው ተደስታ ።
«ልክ እንደ አንቺ ። ድምፁም የያሬድ ።»

# ክ ፍ ል ፲፱

የካቲት ባተ ። አቡዋራውና ወበቁ አሸንፎአል ። የመሬቱ ግለት እያራምድም ። ሰማዩም ጭምር የተቃጠለ ይመስላል ። ፀሀይዋ ምህረት አልነበራትም ።

የትምህርት ቤቱ ስራ አልቆ ቀለም የመቀባቱ ስራ ተጀምሮአል ። ውጭው ወደ ቀይ በሚያደላ ቡናማና ቀዝቀዝ ባለ ብጫ ቀለማት እያሸበረቀ ይሄዳል ። አይናለም ነበረች ቀለማቱን የመረጠችው ። ምርጫዋ ግሩም ነበር ። እሱ የቀለማት ውህደት ነገር እምብዛም ስለማይገባው በደወሉ ቤት ስራ ላይ ማተኮር ከጀመረ ቆይቶአል ። በአክሱም ሀውልት ቅርፅ የወጣው የደወሉ ቤት ስራም በሚያስደስት ሁኔታ እየተፋጠነ በመሄድ ላይ ነበር ።

አዲሱን ትምህርት ቤት አስመርቆ አርጌውን የሚያፈርስበት ቀን ሁልጊዜ ባይኑ ላይ ይሄዳል ። እያንዳንዱ ቀን ወደ ነፃነቱ እያቀረበው ሲሄድ ይታየዋል ። ስለ አዲሱ ትምህርት ቤት ስም ገና አልቆረጠም ። እስካሁን አዲሱ ትምህርት ቤት—መከረኛ ትምህርት ቤት—የተረገመ ትምህርት ቤት እያለ ነበር የሚጠራው ። አሁን ግን ለዚህ ውብ ነገር ምን የተዋበ ስም ላውጣለት ይሆን ? እያለ ማሰብ ጀምሮአል ። በታፈሰ አባት ስም የመሰየም ነገር ፈፅሞ አይታየውም ። ውስጡ አይሆንም የሚለው ነገር አለ ። ነገሩ ከታፈሰም ሆነ ከፈታውራሪ ጋር ሊያቀያይመው እንደሚችል አላጣም ።

«ጎበዝ ! በሉ እንጂ ። መቆም የለም !» ብሎ ጮኸ ፣ ሰራተኞች ቆመው ሲያወሩ አይቶ ።

ምን እንደሚባባሉ ያውቃል ። ሁሉም ሁልጊዜ ቆመው የሚያወሩት ስለ ወሎ ድርቅ ወይም ወታደሮች ጥያቄ አቀረቡ ስለሚባለው ነገር ፣ ወይም ቤንዚን ላይ የተጨመረው ዋጋ ስላስከተለው ችግርና የህዝቡ ጉምጉምታ ነበር ። በሳምንት ወይም በሁለት ሳምንት በጭነት መኪና ተንገላቶ በሚመጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ መረባረብ ተጀምሮአል — ጥርሱ አልቆ ድዱ ብቻ የሚታይ ጋዜጣ ቢሆንም ቅሉ ! ሰአት ሲደርስ ሁሉም ራዲዮ ለማዳመጥ ይሮጣል ። አልፎ አልፎ በወሎ ጠቅላይ ግዛት አንዳንድ ቦታ ላይ የደረሰው የድርቅ ችግር በንጉስ ነገስቱ መንግስት ጥረት በመወገድ ላይ ነው እየተባለ ከሚነገረው ሌላ አብዛኛውን ጊዜ ያው የተለመደው—ግርማዊነታቸው በደብረ ነጎድጓዋድ ቅዱስ ዮሀንስ ቤተ ክርስቲያን ፣ ወይም በደብረ ሀይል ቅዱስ ራጉኤል ተገኝተው አስቀደሱ ፣ የውጭ እንግዶችን ተቀብለው እጅ አስነሱ ፣ መልእክት ላኩ ፣ የሚኒስትሮች ካቢኔ በትናንቱ እለት በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ተነጋገረ ፣ ህዝቡ ቀበቶውን ጠበቅ እንዲያደርግ የንግድና ቱሪዝም ሚኒስትር ዛሬ አስገነዘበ

—እሰታዊ ዜና ነበር። የጋዜጦች ርእስ አንቀፆችም ያው የተለመደውን ዘፈናቸውን ነበር የሚዘፍኑት—ለምለሚቱ ኢትዮጵያ በፀሀዩ ንጉስ ቆኃድሉ የሶስት ሽህ ዘመን ታሪክዋ ታድሶ ማርና ወተት የሚፈስባት ሆናለች እያሉ...

ሙሽው በማያባሩ—አጎብጉበው—አጎብድደውና አሽቃብጠው በማይደክሙ ከንቱ ብእሮች ይናደዳል። በሽሙጥ፣ ባሉባልታና በነቀዝ ፀተበሉ በሽተኛ ብእሮች ይበሳጫል። በንጉሰ ነገስቱ መንግስት ሳንሱር መጋረጃ ተጋርደው ተለጉመውና ታፍነው በታላቅ ስቃይ ሲሚያቃስቱ ብእሮች ያዝናል። ሀዘኑ እጥንቱ ድረስ ዘልቆ ይሰማዋል። እና፣ ለህሊና ነፃነት አክብሮት የሌለውና ሀላፊነት የማይሰማው ሳንሱር፣ የሰው ልጅ ክቡር ሰብእናን አፍ አውጥቶ ከመርገምና ከመስደብ ከመናቅና ከማዋረድ ይቆጠራል ይላል ሀዲስ—በንዴት። እውነት ስትታፈን አሉባልታ ቀለብ ቢሆን ምን ያስገርማል!

«ጎበዝ እንበርታ!» አለ።

ስራ አይፈታም። ሰው ስራ አያስፈታም። ለራሱ አንድ ቦታ ረግቶ አይቆምም። ሌሎችንም አያስቆምም። ስራ። ስራ። ስራ። ተስፋው እውን እየሆነና እየተቃረበ መሄዱን በሚመለከትበት ጊዜ ይበልጥ እየተማደፈ ሰዎቹንም ያጣድፍ ነበር።

ሆኖም፣ የሰራተኞቹ ልብ በየእለቱ እየሸፈተበት ይሄድ ነበር። የሚነፍሰው አየር ጥሩ አልነበረም። በተለይም በመምህራኑ አካባቢ የሚነፍሰው አየር ያስፈራ ነበር። ተማሪዎቹም ሳይቀሩ ጉም ጉም ማለት ጀምረዋል። ከዲሳባ የሚነፍሰው አየር የሱጴንም አየር እየበከለው በመሄድ ላይ ነበር።

የካቲት 12 ቀን 1966 እ.ም. በመላ ኢትዮጵያ የሚገኙ መምህራን የስራ ማቆም አድማ መቱ የሚል ወሬ ሱጴ ደረሰ።

«ጉድ ፈላ፣ አሽከር በቅቤ በላ!» አለ። በማግስቱ አንድም አስተማሪ ወደ ትምህርት ቤቱ ብቅ አላለም። እሱም እንደ ሌላው ሰው ሁሉ ሰአት እየጠበቀ ወደ ራዲዮ ይሮጥ ጀመር። ከሚነፍሰው የጋለ ፖለቲካዊ አየር ጋር የሰውም የልብ ትርታና ትኩሳት እየጨመረ ይሄድ ነበር፤ ያዲሳባ ሴይቼንቶ ነጂዎች ስራ አቆሙ—የመምህራን ስራ ማቆም አድማ እንደቀጠለ ነው—በፈተና ወድቀው ከትምህርት ገበታ የተገለሉ አንዳንድ ተማሪዎች በተፈጠረው ሁኔታ በመጠቀም በህዝብና በግል ንብረቶች ላይ ጉዳት አደረሱ... በየእለቱ የፖለቲካው ትኩሳት እየጨመረ ይሄድ ነበር።

ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ እየሆኑ መሄዳቸውን በውል ሊገነዘብ የቻለው፣ የካቲት 16 ምሽት ላይ ንጉሱ ለኢትዮጵያ ህዝብ በራዲዮ ንግግር ባሰሙ ማግስት ነበር። ለጦር ሀይሎች የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግ ትእዛዝ ሰጥተናል። የትምህርት አጠቃላይ ጥናት እውነተኛ አላማውና ጥቅሙ ለህዝባችን በሚገባ ተገልጦለት እስኪገነዘበውና የሚያስፈልገው ድርጅት እስኪሟላ ድረስ እንዲቆይ አዘናል። የመምህራን ጥያቄ በጥናት ላይ ስለሆነ ባንድ ወር ውስጥ የሚሰጠውን ውሳኔ እየተጠባበቁ የማስተማር ተግ

ባራቸውን በፍጥነት እንዲቀጥሉ እናስታውቃለን . . . ንጉሳዊው ንግግር በተደረገ ማግስት ብቅ ያለ አንድም አስተማሪ አልነበረም ።

ሀዲስ ፥ እንደ በፊቱ መማሃትም ሆነ መግዛት መቅረቱ ይሆን ? እያለ ሲያስብ ሁለተኛ ክፍለ ጦር—የተደረገው ጭማሪ በቂ አይደለም በማለት አቤቱታ አቅርቦአል የሚለውን ወሬ ሲሰማ—ነገሩ አማላረኝም ማከተሙ ላይሆን አይቀርም ፥ በማለት የትምህርት ቤቱን ስራ ከስር ከስሩ ያጣድፍ ጀመር ። ደግነቱ ሰራተኞቹ የስራ ማቆም አድማ አልመቱም ። በመምህራት ስራ ማቆም ምክንያት ትምህርት ቤቱ ላልተወሰነ ጊዜ በመዘጋቱ ሙሉ ጊዜውን በስራው ላይ አሳርፎ ነበር ።

ሲናፍቀው የነበረው ቀን ደረሰ ። ህልም እውን ሆነ ። ደረሰ ስአቱ ። ነፃነቱን የሚቀዳጅበት ቀን ተቃረበ ። ስራው በሙሉ ተጠናቆ ያለቀበትን ቀን ቢሞት አይረሳውም። ረቡእ የካቲት 20 ቀን 1966 ዓ.ም. ነበር ። የተባረከ ቀን ! እንዴት ሊረሳው ይችላል ? በህይወቱ ውስጥ አንድ የታሪክ ምእራፍ ተፈፅሞ ሌላው የታሪክ ምእራፍ የተከፈተበት ታሪካዊ ቀን ነበር ።

ያን ምሽት የምስራቹን ለውድ ባለቤቱ ሊያበስር ወደ ቤቱ ሲሮጥ ወጣት እግሮቹ አየር ላይ የሚንሳፈፉ እንጂ መሬት የሚረግጡ አይመስሉትም ነበር ። ከልቡ ጋር ነበር የሚንሳፈፉት ። እየቀለቀለች የምትሄደውም የምሽት ጀንበር ፡ ባንድ ቀይ ፥ ካሉስ ፥ ሀምራዊና ወርቃማ ብርቱካን ቀለማት ከነደደው አድማስ ላይ፡፡እንደ እሱው ትንሳፈፍ ነበር ። ብርማ ጠርዝ ያለው ጥቁር ስስ ደመና የእሳት አሎሎ መስላ የምትንሳፈፈውን ጀንበር ፊት ሁለት ላይ ከፍሎት ይታያል ። አንድ ሰአሊ በፈጠራ ብሩሹ ኩዋል ያደርጋት ትመስላለች—ጀንበርዋ ። ከድማሱ ላይ የተሰሩት ተራሮች እናት በእሳት የተያያዘ ይመስል ነበር ።

እንደ ሮጠ ቤት ገብቶ ባለቤቱን በደስታ አገላብጦ ከሳማት በሁዋላ ፥ «ቢቃ አለቀ ። ስንጠብቀው የነበረው ቀን ደረሰ !» አላት ።

«የደወል ቤቱ ?» አለች ደስታውን መልሳ በማስተጋባት ።

«አዎን እሱም» አለ፥ «ደወሉ ነገ ይሰቀላል—በተጋበዘው ህዝብ ፊት። ራሴ ነኝ አውጥቼ የምሰቅለው ። አብረን እንደውለዋለን ። እና ፥ ሱዶ ላይ የፍትር ፥ የተስፋና የድፍረት ድምፅ እናሰማለን ።»

«የትምህርት ቤት ደወል አንድ ትዝታ ይቀሰቅስብኛል» አለች ።
«የምን ትዝታ ?»
«በትምህርት ቤት ያሳለፍኩትን ጊዜ ።»

አይናለም በእልቁ ማርያም ትምህርት ቤት እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ ተምራለች ። ትምህርት ቤት ከመግባቷ በፊት በመምሬ መሀረርዳታ ዳዊት ደግማ ተመርቃለች ። ሲላት ዳዊቱን በቃል ታንበለብለዋለች ። ሲጠቀችና ፥ «ያሰቡት ነገር ከፍፃሜ ደርሶ ሲመለከቱት ደስ ይላል ፥ አይደለም ?» አለች ።

«በጣም እንጂ» አለ ።«ያሳለፉት ገሃነም ሁሉ ይረሳል ። እና ፥ ሰው ከንፁህ ስራው ፊት ሲቆም ራሱ እግዜር ይሆናል ።»

«ሀጢአት አትናገር!»
«ሰው እግዜር አለ የሚለው ምን አይቶ መሰለሽ ? ስራውን ነው ።»
«አበድክ እንዴ !»
«የለም ተደስቼ ነው ።»
«'የሀዘን ጥላ የሌለው ደስታ የለም' ይላል አባዬ ።»

«የምደሰተው ለራሴ ሳይሆን የከብት ጭራ እየተከተሉ ለሚውሉት ልጆች ነው ። ያነሳሱኝም እነሱ ናቸው ።»

«ጥሩ ነው» አለችው ። «የሞቀ ውሀ ገንቦው ውስጥ ተጨምሮልሃል ። ይልቅ ሳይበርድብህ ሂድና ታጠብ ።»

ገላውን ለመታጠብ ሄደ ።«ወንድ ልጅ እንዴት በየቀኑ ገላውን ይታጠባል ?»ይላሉ ፊታውራሪ ። ቤት ቤት የመሆን ነገር እየመሰላቸው ደስ አይላቸውም ።«ወንድ ልጅ ከቤት ወጥቶ የሚመለስበትን ሰአት ስለማያውቅ ምን ጊዜም ቢሆን ለመከራ መዘጋጀት አለበት እንጂ ፣ ይሄ በየቀኑ የመተጣጠብ ነገር ደግ አይደለም»ይላሉ ፣ አምርረው ።

ገንቦው ቂጥ ላይ የነበረውን ውታፍ ዞር አድርጎ ገላውን ይታጠብ ጀመር ። ያሳለፋቸውን ችግሮች ከላዩ ላይ የሚያጥብ ያህል ነበር የሚሰማው ።

የገንቦ ቂጡን ስድስት ቦታ ላይ ሸንቁር ጥሩ የገላ መታጠቢያ ሰርቶአል።

ከገንቦው ጆሮዎች ጋር በላስቲክ የተያያዘውን ስድስት ጉጦች ያለውን የብረት ውታፍ ዞር ሲያደርጉት ውሀው ሹዋ እያለ ይወርዳል ። በእጅ በሚሰራው መዘውር ገንቦውን ለማውረድና መልሶ ለመስቀል ይቻላል ። የፊት መታጠቢያም እንዲሁ በማሰር ሰርቶ ነበር ። ማሰሮውን ዘግቶ ቀና በማድረግ በቀላሉ መጠቀም ይቻላል ። ውሀው አይደፈርስም ፣ አይቆዋረጥም ። ያዲሳባን ቡዋንቡዋ ያስንቃል ።

ገላውን ታጥቦ እንደ ወጣ ሮጦ ሄዶ ራዲዮውን ከፈተ ። አርእስተ ዜና . . . በጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራው የሚኒስትሮች ጉባኤ ባንድ ድምፅ ተስማምቶ አባሎቹ ስራቸውን ለመልቀቅ ለግርማዊነታቸው ልመናቸውን አቅርበዋል . . .

«አሁን የተነገረውን ወሬ ሰምተሻል ?» አላት ።
«አዎን ፤ ምን ማለታቸው ነው ?»
«ኢኛ አልቻልንም ልቀቁን ማለታቸው ነው ።»
«ኢና ፤ አሁን ምን ይሆናል ?»

«ምን አውቃለሁ ። ምናልባት ለውጥ ሊመጣ ይሆናል ። አሻፈረኝ ብሎ የወጣው ህዝብ ነጁን ሰጥቶ ወደ ቤቱ እንደማይመለስ ተስፋ አደርጋለሁ ። ኢትዮጵያ ለውጥ ያስፈልጋታል ። አዲስ ትውልድ የራሱን አዲስ ተስፋ መጨበጥ አለበት ።»

«ሁዋላ አገር የተበጠበጠ እንደ ሆነስ ?»

«ካልደፈረሰ አይጠራም !» ከማለቱ ፊታውራሪ ፣ ከተፍ አሉ ቶሎሳን አስከትለው ።

ገና ሳይቀመጡ «በራዲዮ የተነገረውን ወሬ ሰምታችሁዋል ?» ብለው ጠየቁ ።

«አዎን ፣ ስለሱ ነበር የምናወራው» አለ ሀዲስ ።
«ታዲያ ይህ በመቀጣጠል ላይ ያለው እሳት የጤና ይመስልሃል ?»

«አዎን» አሏቸው ፍርጥም ብሎ ። «ጤናማ ምልክት ነው ። እኔ እንደሚታየኝ የ'ሳቱ ግብ ሰላም ነው ። ባገሩ ሰው ሆኖ ሰውነቱ ታውቆና ተከብሮ መኖር የማይፈልግ የለም ። አገር የጋራ ናት የሚባለው ነገር በስራ መተርጎም አለበት ። ለይስሙላ ብቻ የምንወደውና የሚወደን ህዝ ባችን ቢሉት ምን ፋይዳ አለው ?» ብሎ ነገሩን ሳይቆርጥ ድንገት በሩ ተንኳኳኩዋ ።

ቶሎሳ ጠብመንጃውን እንደ ያዘ ወደ በሩ ሄደ ። ምናልባት ታፈሰ ሳይሆን አይቀርም ብሎ አስቦ ነበር ። ያምሳ አለቃ ጎይቶም ከሁለት ፖሊ ሶች ጋር ከጨለማ ውስጥ ብቅ ሲል አይቶ በመደንገጥ ፣ «ግቡ ፣ ግቡ ። ምን ነው ደህና ?» አለ የሶስቱንም ሰዎች ፊት በማሾው ብርሃን እየመረ መረ ።

«ደህና ነው...የለም አንቀይም ። እንቸኩላለን» ብሎት እጅ ነስቶ ከፊታውራሪ ጋር አጭር ሰላምታ ከተለዋወጠ በሁዋላ ፣ «የመጣነው አዲሱ ትምህርት ቤት ላ...» ከማለቱ ።

«ምን ሆነ ?» አለ ሀዲስ ራሱን ይዞ ።
«ወደ አይተ ! አትደንግጥ ። ምንም አልሆነም ። »
«ታዲያ ምንድን ነው ?»
«ዋእ ፣ አላናግር አልከኝ ።»
«እሺ ።»

ሁለት ሰዎች ወደ ትምህርት ቤቱ በጉዋሮ በኩል ሲገቡ በጥርጣሬ መያዛቸውንና ሁለቱም የእጅ ቦምብ ይዘው እንደ ነበረ ከገለፀለት በሁዋላ ፣ «አሁን በምርመራ ላይ ነው የሚገኙት ። አላማቸው ምን እንደ ሆነ እንደ ርስበታለን» አለው ።

«መቼ ነው ይህ የሆነው ?» ፊታውራሪ ነበሩ ።
«አሁን ማምሻውን ነው» አሏቸው ጎይቶም ።
«ፀጥታውስ እንዴት ነው ?»

«ምን ፀጥታ አለ ብለው ነው ? ተናግቶአል ። ስራ ያቆሙት አስተ ማሪዎች ህዝቡ እንዲያምፅ ውስጥ ውስጡን እየጎተጎቱት ነው ። ተማሪዎ ችም ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ እየተዘጋጁ ናቸው ይባላል ። ካዲሳባ የሚ መጣውማ ወሬ አይጣል ነው ። ጆሮ ይበጥሳል» አላቸው ።

«ደጉን ቀን ያምጣው እስቲ» አሉ ፊታውራሪ ።

ሀዲስ ከጎይቶም ጋር ወደ ትምህርት ቤቱ ለመሄድ ፈልጎ ነበር ። ምን ያስፈልጋል ? ዘብ ተደርጎበታል በማለት ሁሉም አከላከሉት ።

ያን ሌሊት ጥሩ እንቅልፍ አልተኛም ። ሲቃዥ ነበር ያደረው—ትምህርት ቤቱ በቦምብ ሲመታ እየታየው ። በፍርስራሹ ላይ ቆሞ እያለቀሰ ። ህዝብ ይፋረዳችሁዋል ! በማለት ይጮህ ነበር—በህልሙ ። በጮኸ ቁጥር አይናለም እየደነገጠች ትቀሰቅሰው ነበር ።

ነጋ አልነጋ በማለት ተነስቶ ወደ ትምህርት ቤቱ ሮጠ ። የጡዋት ጨረር ያረፈችበት አዲሱ ትምህርት ቤት ተውቦ ይታያል ። ሁሉም ነገር ደህና ነበር ። የጡዋቱን ቀዝቃዛ ንፁህ አየር በደስታ ተነፈሰ ።

ግቢው ባዳዲስ ስንደቅ አላማዎች እንዲያ አሸብርቆ ሲታይ ብቅ ብሎ ታየው ። ፎር ሲል እርጌው ትምህርት ቤት አፈጠጠበት ። የመኪና ድምፅ ሰማ...

«የማታውን ወሬ ሰማህ ?» ታፈሰ ነበር ።
«አዎን።»
«የሚገርም ነው ።»

«አሉባልተኞች የሚነዙት የፈጠራ ወሬ ነው ስትል የነበረው የሸውና ደረሰ አይደለም ወይ ?»

«ምንድን ነው የደረሰው ? ካቢኔ ቢሰናበት ካቢኔ ይተካል ። ምን የሆነ መሰለህ ?» በማለት ደነፋበት ።

«ማን» አለ ሀዲስ ፣ «ህዝቡ ተመልሶ እንደ በፊቱ እንዳማይገዛ ይሰማኛል ። ታጥቦ ጭቃ እንዳማይሆን ተስፋ አደርጋለሁ ።»

«ምኝ አትሁን ። እመነኝ ምንም ነገር አይመጣም» ብሎት ፣ ሲጃራ አውጥቶ አቀጣጠለና ትምህርት ቤቱን ሲመለከት ከቆየ በሁዋላ ፣ «ቆንጆ ትምህርት ቤት ነው» አለው ።

«ትንሽ አስተዋፅኦ ናት ።»
«ስለ ስሙስ ፣ ምን ወሰንክ ?»
«ገና አልቆረጥኩበትም ።»
«ለምን ?» አለው ፊቱ ልውጥ ብሎ ።
«አዝናለሁ ። እያሰብኩበት ነው ።»
«አታስብ ። የፈለከውን በለው» ብሎት ሊሄድ ሲል፡—
«ምረቃው ላይ አትገኝም ማለት ነው?» አለው ።

«ወደ አዲሳባ መሄዴ ነው ። አሁን ካልተነሳሁ ጎሬ ላይ አይሮፕላን ያመልጠኛል ።

«እንደማትቀየመኝ ተስፋ አደርጋለሁ» አለው ።
«ስለ ምኑ ?» ፊቱ ጠቁሮ ነበር ።
«ስለ ስሙ ።»

«የፈለከውን በለው ብዬሃለሁ ።»
«አሁን ሳስበው ‘የካቲት 66 ትምህርት ቤት’ ቢባል ጥሩ መስለኝ ።»

«አቤቴም እዚህ ቦታ ላይ የተሰቀለው በየካቲት ወር ነበር» ብሎት ሄደ ።

በአይኖቹ ተከተለው ። ያደረግሁት ነገር ልክ ነው ? ወይስ አይደለም ? በማለት ራሱን ሲጠይቅ ቆየ ። በመጨረሻ ፀፀት አላደረበትም ። አንድ ቀን ምክንያቱን ይረዳው ይሆናል አለ ።

ሰአቱ ደረሰ ። ምድረ ግቢው በተማሪዎችና በተጋበዙት እንግዶች ተጣበ ነበር ። ከመምህራኑ መካከል አንድም ብቅ ያለ አልነበረም ። ነገሩ ሳያናድደው አልቀረም ። ሆኖም በሌላ በኩል ያስደሰተው ነገር ነበር ። የቡና ለቀማ ስራቸውን ጨርሰው ወደ የአገራቸው ለመመለስ በመዘጋጀት ላይ የነበሩት የቀን ሰራተኞች በምረቃው በአል ላይ ተካፋይ ለመሆን መምጣታቸውን በማየቱ ነበር የተደሰተው ። እምና ለትምህርት ቤቱ ስራ ገንዘብ ያዋጡ ምናልባት በመካከላቸው ይገኙ ይሆናል ። ስማቸውንም ሆነ መልካቸውን አያስታውስም ። ግን በቅርብ የሚያውቃቸው ያህል ነበር የሚሰማው ።

ምስጋና ከማቅረብ ሌላ የሚናገረው ነገር አልነበረውም ። ትምህርት ቤቱ ራሱ ይናገር ነበር—በራሱ ውበ ቋንቋዋ—በራሱ ውብ ድምፅ።ባለቤቷን ጠራት ። አደይ አበባ መስላ ብቅ አለች ። ከደወል ቤቱ ላይ ቢጫስ ጎል ወጥቶ ደወሉን ሰቀለው ።

«ደውዪው !» አላት ከደወሉ ቤት አናት ላይ ቆሞ ።

የደወሉ ውብ ድምፅ ከአካባቢው አየር ጋር ተዋህዶ ዙሪያ ገባውን ይቃኝ ጀመር …

# ድህረ-ታሪክ ።

## ክ ፍ ል ፳

መምህራን ስራ በማቆማቸው ፣ ልክ ላንድ ወር ፣ ማለትም ከየካቲት 11 ቀን እስከ መጋቢት 11 ቀን 1966 እ.ም. ተዘግቶ የቆየው ትምህርት ቤት ተከፈተ ። አሮጌው ትምህርት ቤት ፈርሶ በቦታው ላይ ጥሩ የመጫወቻ ሜዳ ተሰርቶአል ። ከትምህርት ቤቱ ህንፃ ስራ በተረፈ ገንዘብ የተሰሩት አዳዲስ ጠረጴዛዎች በየክፍሉ ተደርድረው ይታያሉ ። ሁሉም ነገር አዲስ ነበር ።

መምህራኑም በድል የታደሰ አዲስ መንፈስ ይዘው ነበር ወደ ትምህርት ቤቱ የተመለሱት ። የኢትዮጵያ መምህራን ያቀረቡዋቸው አስራ አምስት ጥያቄዎች አብዛኞዎቹ ተቀባይነት አግኝተዋል ። የትምህርት አጠቃላይ ጥናት ለጊዜው እንዲቆይ ተደርጎአል ። መምህራን ባዲሱ ህገ መንግስት ሰልፍ የማድረግ ፣ ከመንግስት ጋር የመደራደርና ትምህርት ሚኒስቴር በሚያወጣቸው እቅዶች ፣ መርሀ ግብሮችና ውሳኔዎች የመሳተፍ መብታቸው ተከብሮአል ። ድል ነበር !

ህዝቡ ባንድ ፊት ፣ «ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም ! እንደ በፊቱ አንገዛም ! መሬት ላራሹ ! በወረቀት ላይ ብቻ የሰፈረ ነፃነት አንፈልግም !» እያለ በየአደባባዩ ትእይንተ ህዝቡን ሲቀጥል—አዲሱ ካቢኔ ደግሞ በበኩሉ—የገሊላው ተአምር ከማንም አይጠበቅም ! ዉሀ ወደ ወይን ጠጅ የሚለውጥ የለም! ጥያቄው አገራችን ምን ታድርግልን? ሳይሆን ፣ ምን እናድርግላት ? የሚል መሆን አለበት ። ፋታ ፣ ፋታ ፣ ፋታ ፣ ይል ነበር ። ጋዜጦች ባንድ ፊት ፋታ ይለምናሉ፤በሌላ በኩል ተንፍሱ ፣ ይላሉ ። መጋረጃው ተገልጦ መቅደሱ መታየት ጀምሮአል ። ጥሩ የነፃነት አየር ፣ የተበፋ አየር ይነፍሳል ። የልቡ ትርታ ያልጨመረ ማን ነበር? ሀዲስ ፣ የራዲዮ ጣቢያ ታማኝ ደንበኛ ሆኖ ነበር ።

አንድ ቀን—መጋቢት ወር መጨረሻ ላይ—ሀዲስ እንደ እብድ ብቻውን እየሳቀ ወደ ቤት መጣ ። ሰቆ አያባራም ። ዝም ብሎ ይስቃል ። አንጀቱን እስኪያመውና እንባ እስኪወርደው ይስቃል ።

«የሚያስቅ በሽታ ያዘህ እንዴ ? ምንድን ነው እሱ ?» ትለው ነበር አይናለም ተጨንቃ ።

በካርቦን ኮፒ የተፃፈ አንድ ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ ሰጣት ።

«የምን ወረቀት ነው ?»

«የተበተነብኝ ወረቀት ነው ። አንብቢው ። ከዛሬ ጀምሮ ትምህርት ቤቱ፡ እንዳልደርስም ቢሮዬን አሽገው አባረውኛል» አላትና ሳቁን ቀጠለ ።

እህህ ! ! . እሆሆሆ ! . . ኢሂሂ ! . .

«ማን ነው ያባረረህ ?»
«የኔው ጉዋዶች ! የትምህርት ቤቱ መምህራን ።»
«ምን ይሁን ብለው?»

ፊታውራሪ ከየት መጡ ሳይባል ከተፍ አሉ ። ሳቁን አቁሞ የሚስቅ በትን ምክንያት ነገራቸው ። ለነገሩ እንግዳ አልሆኑም ። የተበተነው ወረቀት እሳቸውም እጅ ገብቶ ነበር ።

«ከባላባት ቤተሰቦች ጋር ተመሳጥሮ ህዝቡን ሲገፍና ሲያስለቅስ የኖረ የቀን ጅብ !! ትምህርት ቤት አሰራለሁ በማለት ከድሀው ላይ ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን መዋጮ ሰብስቦ ሃምሳ ሽህ ብር የማታወጣ ዚጋባ በመቀለስ የቀረውን ገንዘብ የበላ አይናውጣ ሌባ!!! የስልጣን ጥሙን ለማርካት ሲል ሀቀኛ ሰዎችን እርስ በርስ አጣልቶ ያጋደለና እጆቹን በንፁሃን ደም የታጠበ ነፍሰ ገዳይ... ህዝብ የሚያመልከበትን ወርካ የጣለ የለየለት ቀንደኛ የህዝብ ጠላት !!! ፋጡማ የምትባለውን ጎበዝ ተማሪ አባልጎ ካስረገዛት በሁዋላ ከትምህርት ቤቱ እንድትወጣ ያደረገ ፣ በመምህርነት ቀርቶ ባንድ ቀን እንግድነትም የትምህርት ቤት ደጃፍ መርገጥ የሌለበት ባለጌ...» ያልተባለው ነገር የለም ።

አይናለም ወረቀቱን አንብባ እንደ ጨረሰች ፣ «ፋጡማ!» አለች ።

ለተቀረው ውንጀላ ሁሉ ዋጋ የሰጠችው አትመስልም ። ጥያቄዋ ደንቆት ፣ «አዎን ፋጡማ» አላት ።

«እና ?»
«እና ምን ? ትምህርት ቤቱን ለቃ ሄዳለች ። ይሄው ነው ።»
«ለምን ሄደች ?»
«እኔ ምና 'ውቃለሁ ። ሄደች ፣ በቃ ! ከፈለግሽ ሂጂና ጠይቂአት !»

ፋጡማ ትምህርት ቤቱን ለቃ ወደ አዲሳባ ከሄደች ቆይታለች ። ሀዲስ ካገባ ጀምሮ ፈገግታዋ ሁሉ ጠፍቶ ነበር ። ልቡዋም ትምህርት ላይ አልነበረም ።

«ምንድን ነው ጭቅጭቁ ?» አሉ ፊታውራሪ ከቆሙበት መስኮት ላይ ዞር ብለው ።

«ምንም አይደለም» ብሎ ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አደረገና ፣ «በቁርጥ የማነጋግርዎት ጉዳይ አለኝ» አላቸው ።

«ምንም አይደለም ንገረኝ» አሉት ።
«መሄድ አለብኝ ።»
«ወዴት ?»
«ወደ'ዲስ አበባ ።»
«ለምን ?»

«ከእንግዲህ እዚህ የምሰራው ነገር የለም ። እዚያ ትምህርት ቤት ተመልሼ ማስተማርም አልፈልግም ። ወረቀት ስለ ተበተነብኝ ወይም ቢሮዬ ስለ ታሸገብኝ አይደለም ። የምፈልገው አስተማሪ ለመሆን ነው ።

ግን፡ለማስተማር መማር ያስፈልገኛል ። ፊትም ቢሆን ስራውን እንደ ጨረ ስኩ ለመሄድ አስቤ ነበር ። ከነገ ዛሬ ስል እስካሁን ቆየሁ ። አሁን መሄድ አሰብኹ» አላቸው በምር—ኮስተር ብሎ ።

ፊታውራሪ ረጋ ብለው፣ «ጊዜው ደግ አይደለም ። እንደሚሰማው ከሆነ አዲሳባ የተቀጣጠለው እሳት ገና አልበረደም ። እንዴት ይሆናል ? ሄደ ህስ ምን ታደርጋለህ ?» አሉት ።

«እንደ ምንም ብዬ ስራ ፈልጌ አገባለሁ ። ከዚያ እስዋንም ወስጄ ትምህርት ቤት አስገባታለሁ ። እኔም ማታ ማታ እማራለሁ ።»

«ማለፊያ ነው ። ለራሳችሁ ጥሩ አስባችሁዋል ። አይ የዘመኑ ልጆች!» አሉ ተከዘው ።

«እንዴት ?» አላቸው ቅር ተሰኝቶ ።

«እንዴት ? ማለት ያባት ነው» ብለው ሪዛቸውን በረጃጅም ጣቶቻቸው እየነነተሉ ፣ «በዚህ ክፉ ጊዜ አንድ ላይ ለመሆን ማሰብ በተገባ ነበር ። እኔ እንደ ሆንኩ አርጅቻለሁ ፤ ከእንግዲህ ምን ይቀረኛል ? ስንትስ እድሜ ይኖረኛል ? አንድ የቤተሰብ አላፊና ሰብሳቢ መኖር አለበት ። የስ ጠሁሁን አደራና ሀላፊነት እንዴት አድርገህ ነው እሄዳለሁ የምትለው ? እዩ ብልህ አስተዋይ ትመስለኝ ነበር» አሉት ።

ሀዲስ ክፉኛ ተናዶ፣ «የሱዋስ ትምህርት እንዴት ይሁን ነው የሚሉት ? »አላቸው ። 'ሀብትዎ ገደል ሊገባ ይችላል ! ራስዎን ብቻ መውደድ የለብዎትም ! ነፃነታችንን ይስጡን' ቢላቸው በወደደ ነበር ።

«እስዋ የምትፈልገውን ትምረጥ» አሉ ፊታውራሪ ።
«ጥሩ ነው ። ትምረጥ !»
«እኔ ለመሄድ አልችልም» አለች ።

«እሺ ። ምናለ ታዲያ እኔ ግን እሄዳለሁ ። እዚህ ልቆይ አልችልም !» አለ ።

«ለመሄድ የማልችልበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ አውቀሃል ?»
«ግልፅ ነው !»
«ግልፅ አልሆነልህም ። ቅሪት ነኝ» አለች ።

ፊዞ ቀረ ። የፊታውራሪ ፊት እየፈካ ይሄድ ነበር ። ፍንጭታቸው ብልጭ ሲል ታየው ። ሳቁን ለመግታት አልቻሉም ።

የባላባቶች ልጆች በመብራት እየተፈለጉ በሚሾሙበት ጊዜ ታፈሰ ብሩም የስርናና የገባ አውራጃ ገዥ ሆኖ መሾሙ በሱዴ ተሰማ ። እሱ አዲስ አበባ ነበር ። የሹመቱ ወሬ እንደተሰማ ፊታውራሪ ትካ ቤት ፈንጠዚያ ሆኖ ዋለ ። ፊታውራሪን በጣም ያስደሰታቸው የታፈስ መሾም ሳይሆን የቀኛዝማች ጥላሁን ሽዋረጋ መሻርና ከስልጣን መባረር ነበር ።

«እየሀ ፣ እሱ አይረባም እንጂ ሹመቱስ ማለፊያ ነበር ። ስርና ገባን ለመግዛት ቤታችን ሲመኘው የኖረ ነገር ነው ። ማለፊያ ነው ። ቢከፋም

ቢለማም ለማዛት ያው ያገሩ ባላባት ይሻላል ሲሉ ነበር የዋሉት ። ሀዲስ ግም ከንዴም ሁለት ሶስት ጊዜ ፣ «አንተም አይዞህ ። ማንም እንዳባረረህ አትቀርም ። ከልኩ የሚያልፍ ነገር የለም» ብለውታል ።

ከሳምንት በሁዋላ ታፈሰ ብሩ ሶርና ገባ አውራጃ ፅህፈት ቤት ተግ ባቶ ስራ መጀመሩ ተሰማ ። አንድ ቀን ሀዲስ ደጅ ቁጭ ብሎ ፀሀይ እየሞቀ አይናለምን ሲያስተምርና ሲያነብ ቶሎሳ ሲሮጥ መጥቶ ፣ «ትምህርት ቤቱ ምን እንደ ተባለ ሰምተሃል ?» አለው ።

ሀዲስ ደንግጦ ፣ «ምን ተባለ !» አለና ጠየቀው ።
«ራስ ቢትወደድ መኩንን እንዳልካቸው ትምህርት ቤት ።»

አይናለም ፣ ዛሬ ትንሽ እመም አርጎኛል ብላ ቤት ገባች ። ሆድዋ ንፉ ብሎ ነበር ። ተአምር እያልቅም አለ ሀዲስ በልቡ ታፈሰን እየታዘበ ። «ታያለህ!»በማለት የፎከረበት ቶክራ ትዝ አለው ። ይህ በሆን በሁለተኛው ቀን ታፈሰ ብሩ በአውራጃው ባለ ስልጣናችና ፖሊሶች እንደታቦት ታጅቦ ወደ ሱቁ መጣ። የማይሰግድለት ሰው አልነበረም። ፊታውራሪ ቤት ስንጋ ተጥሉ ፣ አረቄ በጠርሙስ ፣ ጠጅ በማብረጃ ፣ ስጋ የሳንሳ ተይዞ ቀርቦ ወዲ ያውኑ ሰርግና ምላሽ ሆነ ። እምቢልታ ተንካለለ ። አዝማሪ አቀነቀነ ።

ሀዲስ ፣ ክቡር ታፈሰ ብሩን ብቻውን እንዳገኘው ፣ «ሹመት ያዳ ብር» አለው ።

«ይልቅ ባንተ ላይ የደረሰውን ሰምቼ አዝኛለሁ»
የሚል መልስ ነበር የሰጠው ።

«እሱ ምንም አይደለም ። በለውጥ ጊዜ በማንም ላይ ሊደርስ የሚ ችል ነገር ነው ። ሆኖም ለውጡ እዚሁ ላይ እንደማያቆም ተስፋ አደርጋ ለሁ» ብሎት ጠጉሩን ቆፈር ቆፈር አደረገና፣ «የመጀመሪያ ስራህን ውጤት አየሁት» አለው ።

«የቱን ?»
«ለትምህርት ቤቱ ያወጣህለትን ስም ።»

ታፈሰ እንደ ማፈርም ፣ እንደ መቆጣትም ብሎ ፣ በምፀታዊ አነጋ ገር ፣ «ወንድም አማች ፣ እሱ የፖለቲካ ጉዳይ ነው» አለ ።

«ባይሆን» አለ ሀዲስ ፣ «ባባትህ ስም ብታስጠራው ይሻል ነበር ።»
«ቂል አትሁን !»
«ሊሆን ይሆናል ።»
«ስማ ሀዲስ» አለ ታፈሰ፣ «የዚህ አውራጃ ገዥ ስለ ሆንኩ ያቀረብ ኩት ገፀ በረከት አይምሰልህ።»
«ሊሆን?»

•

ቢሻራ በንዴት እያጨሰ ፣ «አንድ ነገር ልንገርህ» አለ ታፈሰ ፣ «በት ንሽ ነገር የምትረካ ትንሽ ነፍስ ታናድደኛለች ። ከፍ ወዳለ ነገር መመል ከት አልቻልክም ። እስከዚያ የሰማይ መናር ጥቅሙ ምንድን ነው ?

«የኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ወይም ጠቅላይ ገዥ የማል ሆንበት ምንም ምክንያት የለም ። አዎ ፣ አሁን አንተ በልብህ የምታስበው ነገር ይገባኛል ። ለመሾም ፣ ለመሸለም ብሎ ነው የትምህርት ቤቱን ስም ገዐ በረከት አድርጎ ያቀረበው እንደምትል ይገባኛል ። አዎ ፣ ልክ ነህ ። አሳማዬን ለማሳካት የማላደርገው ነገር አይኖርም ። ካስፈለገም ከሰይጣን ጋር እተባበራለሁ ። ወንድም እግች ፣ አለም እንዲህ ናት ። ዳር ቆሞ እንባ ማፍሰስ ዋጋ የለውም ። ጠንካራ ልቦና ሰጥቶህ በራስህ ላይ የደረሰውን ነገር ብታስተውል የምለው ነገር ይገባህ ነበር ። የምትበላ በት አለም ነው ።»

«ለስጠኸኝ ምክር አመሰግናለሁ» አለ ሀዲስ ።

ታፈሰ ሲጃራውን በንዴት ወረወረና በንቀት አይን ተመለከተው ።

«የንግዱንና የርሻውን ስራ ተውከው ማለት ነው ?»

«ስልጣን ሲታከልበት እሱም ይሰምራል ። ከፈለክ ወኪል ላድርግህ ። በተለይ ያን ደኔን እንደኔ ሆኖ የሚጠብቅልኝ ሰው እፈልጋለሁ» አለው ።

«ለኔ አታስብ ። የራሴ እቅድ አለኝ ።»

«ወይም ወደ ትምህርት ቤቱ ልመልስህ ። መምህራኑ እርስ በርሳቸው ተበጣብጠዋል ይባላል ። የሚበጣበጡበትም አንዱ ምክንያት አንተ ነህ» አለው ።

በመምህራኑ አብዛኞቹ ሀዲስ ሳህሌ ይመለስ ሲሉ ፣ ጥቂቶቹ ደግሞ አይመለስም ፤ ፊሳ ከወጣበት ቤት ተመልሶ አይገባም በማለት እርስ በእርስ እንደሚፋጁ ሀዲስ ሁልጊዜ ይሰማል ።

«እሱንም አልፈልግም» አለ ሀዲስ ።
«የሱዳ ወረዳ ገዥ ባደርግህስ ?»
«እግዜር ይስጥልኝ ።»
«ታዲያ ምንድን ነው የምትፈልገው !» በማለት ጮኸበት ።
«ምንም ።»
«ምንም ? ለኔ ብለህ እንደ ሆነ ገደል ልትገባ ትችላለህ !»

በዚሁ ተለያዩ ። ታፈሰ እንዳለውም በአስተዳደር ስራ ብቻ አልተወሰነም ። የቡና ንግዱን በወኪሎች ያሰራል ። አንድም ጭሰኛ ሳይቀረው ከመሬቱ ላይ አባሮ ሰፊ የቡና እርሻ አስጀምሮአል ። የኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት ጠቅላይ ገዥ ሲሆን ነው እየተባለ በሰፊው መወራትም ጀምሮ ነበር ። ፊታውራሪም ፣ ህልማቸው በሱ እየደረሰ መሄዱን እየተመለከቱ ይኩራሩበት ጀምረዋል ። ያልኮራ የባላባት ቤት ሰብ ማን ነበር ! የእይናለም ሆድ ወደ ፊት እየገፋ ሲሄድ ባዩ ቁጥር ደግሞ ይበልጥ ደስ ይላቸው ነበር ። ደስተኛ ሽማግሌ እየሆኑ ሄደዋል ። ሀዲስ ደስታቸውን ሊያበላሽባቸው አልፈለገም ። ከትእግስት ጋር ጥሩ ፈገግታ ያሳያቸው ነበር . . .

ያለ ምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም
ለኔ ለኔ ሳንል ላንድነትዋ ቆመን
ኢትዮጵያን እናንሳ ከሁሉ አስቀድመን . . .

—ጉድ ፈላ ! እኮ ምን እየሆነ ነው ? . . .

ተነሳ ተራመድ ከንድህን አበርታ
ላገር ብልፅግና ሰወገን መከታ ።...

—ጉድ መጣ ! ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም ይባላል ።

«አላልኩም ነበር ?» አሉ ፊታውራሪ አንድ ቀን በክረምት ውስጥ ፤ «በስፈሩበት ቁና መሰፈር መጣ ። የንጉስ የቅርብ ረዳቶች ቤት እንዲውሉ ከተደረገ ምን ንጉስ አለ ይባላል ? ቀኝ እጆቹ የተቆረጠበት ንጉስ እስረኛ ነው ። ከእንግዲህ ንጉስ አለ ማለት ከንቱ ፥ የከንቱ ከንቱ ነው ፥ ወዳጄ ። ዘውድ ከእንግዲህ ባለቤት የላትም ። መንገድ ላይ ስትንከባለል ያገኛት ይወስዳታል ። ዱሮም ቢሆን ዘውድ የጉልበተኛ ናት ። እስቲ ይሁን ። እንደ ሚሉት ኢትዮጵያ ትቅደም ። ደጉን ቀን ያምጣ» ብለው ነበር ።

መስከረም 1967 ላይ የፊታውራሪ ትንቢት ደረሰ ። ንጉሱ ከስልጣን ወረዱ።ሀዲስ ጆሮዎቹን ራዲዮው ላይ ተክሎ ቀርቶ ነበር ። ህልም የሚያይ ነበር የሚመስለው ።

«ይሄው ያልኩት ደረሰ አይደለም ? ቀስ በቀስ ገዝግዘው ገረሰሱት ። የታሰረ ንጉስ አላውቅም ብዬህ አልነበረም ? ተአምር ነው እኮ ! እንዲህ ያለ ብልሃት በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶም አይታወቅም ። ጉድ ነው ። በእውነት ትንግርት ነው ፥ ጥበበኞች ናቸው» አሉ ። ደንግጠው ነበር ።

«አሁን ገና አዲስ የታሪክ ምእራፍ ተከፈተ ። ከዛሬ ጀምሮ ሶስት ሽህ አንድ ሆኖአል» አለ ሀዲስ ራዲዮውን ዘግቶ ።

«ግን» አሉ ፊታውራሪ ፥ «የት አለ ሌላ ንጉስ ያነገሱት ?»

«ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ተቋዋቁዋመ አላለም እንዴ ራዲዮው ?» አላቸው ።

«እሱስ ብሎአል ። ግን ያለ ንጉስ እንዴት ይሆናል ማለቴ ነው እንጂ ። ኢትዮጵያ ያለ ንጉስ ኖራ አታውቅም ። ንጉስ ይነግሳል ፤ ይወርዳል እንጂ አገር ያለ ንጉስ እንዴት ይሆናል ?» አሉት ።

«ለምን አይሆንም ?» አላቸው ፥ በነገራቸው በሆዱ እየሳቀ -

«ሆኖ አያውቅማ ! ግራ የገባ ነገር ነው ። ወጣት ስትባሉ አገራች ሁን አታውቁም ብያለሁ ። ሁዋላ ጉድ እንዳይፈላ ነው የምሰጋው ። ያቆየነውን ባህል ለማውረስ አልቻልንም ። በስንት መከራ ያቆየናትን አገር በሰላም አስረክበን እፎይ እንዳንል ደግሞ ይህን መላ ቅጡ የማይታወቅ ነገር አመጣችሁ ። ሆ!ሆ! አገር ያለ ንጉስ? የኛ ትውልድ በእውነት የተረገመ መሆን አለበት» በማለት በነገሩ ሲገረሙና ሲተክዙ ከቆዩ በሁዋላ፥ «ዛሬስ በጎ ናት ?» አሉት ።

«ደህና ነች ። አሁንም አልተሻላትም» አላቸው ።

አይናለም ፥ ወገቤን ይቆርጠኛል—ውሀ መሳይ ነገር ይፈስኛል ማለት ከጀመረች ቆይታለች ። ከህመምዋ የተነሳ ሀዲስ ከስውነት ወጥቶ ነበር ። ስለ እስዋ ጡዋት ማታ ያስባል—ይጨነቃል—አንድ ነገር የሆነች እንደሆን በማለት ይፈራል ። ወደ ጎሬ ወስጄሽ ላስመርምርሽ ባላት ቁጥር እምቢ ስትለው ይናደዳል—ያኮርፋል ። ማቃሰት ስትጀምር ደግሞ ሄዶ እቅፎ

ያፅናናታል ። አንዳንዴ ቫል ሲላት ስለ ቱጡማ አንስታ ፣ «እውነት ምንህ ነበረች ? እስቲ እውነቱን ንገረኝ !» ትለዋለች ። «ምኗም አልነበረችም ። ምናልባት እንዲሁ ጥሎባት ትወደኝ ነበር ። የሰጠችኝንም ማስታወሻ አሳይቼሻለሁ ። ይሄው ነው» ቢላትም አታምነውም ። በሌላ ጊዜ ደግሞ ስለሚወለደው ወይም ስለምትወለደው ህፃን የተሻለ ስም አግኝቶ እንደ ሆነ ትጠይቀዋለች ። ወንድ ከሆነ ፣ ተስፋዬ ቤት ከሆነች ፣ ኢትዮጵያ ከሚል ስም ሌላ እስካሁን አላገኘም ። የወንዱም ሆነ የቤትዋ ስም ደስ ስለማይላት ሌላ ፈልግ ትለዋለች ። ስለ ስም ሳይሆን ስለ እስዋ ጤንነት ነበር ሲያስብ የሚውለው ። ህመምዋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠናባት ይሄድ ነበር ። ሆኖም እንደዚያ እየተሰቃየች አንድም ቀን ከውብ ፊትዋ ላይ ፈገግታ ተለይቶ አያውቅም ። ልዩ ፍቅር እያሳደረችበት ትሄድ ነበር ።

ብትወድም ባትወድም ወደ ጎሬ ሲወስዳት ቀርጦ መኪና ተከራይቶ ቤት ሲመለስ አስወርዶአት ጠበቃችው ። ቤተሰቡ በሙሉ ተሰብስቦ ይላቀስ ነበር ። ደም ከፉኛ መትቶአታል ። አለም ዞረበት ። እድሉን እየረገመ አጠገብዋ ድፍት ብሎ ትንፋሽዋን ከመጠበቅ ሌላ የሚያደርገው ነገር አልነበረውም ። ለምግብ ለእንቅልፍና ለእግዜርም ቄምር ደንታ አልነበረውም ። የመንፈስ ብርታት ብቻ የሚፈውሳት ይመስል —ደህና ትሆኛለሽ—እያለ ዝም ብሎ ያፈጥባት ነበር ። በመጨረሻ አይኖችዋን ለመግለጥ በቃች ። ቀስ በቀስም ማገገም ጀመረች ። ግን ለሚቀጥሉት ሁለት ወራት ከቤት ለመውጣት አልቻለችም ። የካቲት ዞር መምጣቱ ትዝ ያለው ካሊጋ ወርዳ ቤት ውስጥ መንሸርሸር ከጀመረች በሁዋላ ነበር ።

የቡና ንግድ ወራት ጫፍ ላይ ደርሶአል ። ግን የቡና ማከተሚያ ወሬ ስለ ቡና ዋጋ ውጣ ውረድ— ወይም መርከስና መወደድ ሳይሆን —ስለ እድገት በህብረት ፣ የስራና የእውቀት ዘመቻ ተማሪዎች መምጣት—ሸፍተው ጫካ ስለ ገቡ ሰዎች ነበር ። አለም ተገለባብጦ ጠበቀው ።

የፍየል ወጠጤ ትከሻው ያበጠ
ልቡ ያበጠበት
እንዋጋ ብሎ ለነብር ላከበት
የማትረባ ፍየል ዘጠኝ ትወልዳለች
ልጆችዋም ያልቃሉ እስዋም ትሞታለች !

ፊታውራሪ ተካ ነገሩ አላማራቸውም ። ደኅሞም ፣ ሊገባቸው አልቻለም ። «ምን ቁጣ ነው ? ምንስ መአት መጣብን ? ምን ሰው ባገር ቀረ ? ብዬ ነበርኮ ። አገር አለ ንጉስ ፣ አገዛዝ አለ አሊጋ አይሆንም ብዬ ነበር ።»

ሀዲስ ራዲዮኑን ዘግቶ ፣ «በመካሄድ ላይ ያለው እኮ የመደብ ትግል ነው ። ታሪክ ሁሉ የመደብ ትግል ታሪክ ነው አለ ።

«ይህን ‘መደብ መደብ’ የምትለውን ነገር ተውኝ ! ታሉም ሆነ ቁዋን ቁዋው አይገባኝም !» አሉ ። «ይህ በፈጣሪ ስራ መግባት ነው ። እሱ በጥበቡ ደልድሎ በሰጠ ሰው ለምን ይጣላል ? ሁሉም መኖር ያለበት እንደ አርባ ቀን እድሉ መሆን አለበት ። እንዴ ? ከአንጨት መርጦ ለታቦት ፣ ከሰው መርጦ ለሹመት ሲባል አልሰማህም ? ዳሩ ምን ያደርጋል ! አሄሄ !» ሲሉ ታፈሰ ብሩ ከየት መጣ ሳይባል ጨለማ ለብሶ ፣ ጨለማ ሆኖ ከተፍ አለ ።

ባሩድ የሸተተው አውሬ መስሎአል ። የስከረ መሆኑም ያስታውቃል ።
«ምን ነው ደህና !» አሉት ፊታውራሪ ደንግጠው ።
«ምን ጤና አለ ብለው ነው ! »አለ ሀዲስን በክፉ አይን እየተመለከተ ።
«ምን ሆንክ?» አሉት ።

«በስራዬ ላይ ሌላ ሰው ተሹሞአል ። እኔም ከስራ ተባርሬአለሁ ። ትናንት ሲሰግድልኝ የነበረው ሰው ሁሉ ዛሬ እር የነካው እንጨት አድርጎኛል ። ወይኔ ታፈስ !» ብሎ ፤ በንዴት ጫን ተነፈሰና ወደ ሀዲስ መለስ በማለት ፡ «ደስ አለህ ?» አለው ።

«ስለ ምኑ ?» አለ ሀዲስ ።

«እኩል ስለሆን» አለና ቡጢ ጨብጦ ፡ «ግን እኔ ወድቄ አልቀርም ። ታያለህ ፤ ይህን ነገር መዋጋት አለብን !» በማለት ደነፋ ።

«ማንን ይዘህ ? መሬት ድረስልኝ ቢሉት ተነስቶ አይከተልም ብዬህ ነበር ። አልሰማኸኝም ። ሰውን ሁሉ ነቅለህ አባረርከ ። ምን ተይዞ ? ማንን ይዞ?... የለም ፡ የለም ታፈሰ ። የእነሱም እንባ ነው ይህን ሁሉ መአት ያመጣብኝ» አሉት በምሬት ።

ታፈሰ ጥርሱ እያፏጨ ፡ «ፊታውራሪ አሁንም ነገሩ ፈፅሞ አልገባዎትም ። ይህን ነገር ካሁኑ ካልተዋጋነው ጨርሶ ያጠፉናል ። ታፈሰ ምናለ ይበሉኝ ! ስልጣኑን የያዙት ኮሚኒስቶች ናቸው ...»

ሀዲስ ስለ ሳቀ ፡ «ምን ያስቅሃል ?» ብሎት ወደ ነገሩ በመመለስ ፡ «ዛሬ በጣፋጭ ቃላት የሚሸነግሉን ቆይተው መሬት ፡ ንብረታችንን ስመ ውረስ ነው ። ሩቅ ሳንሄድ እዚሁ ቅርብ በግብፅና በደቡብ የመን እንዲህ ሆናአል ። እዚህም ነገ ያው ነው» አለ ።

«እንዴት ? እንዴት ? የማንን መሬት ማን ይወርሳል ! ያለ ባለቤቱ ፈቃድ !?» አሉ ፊታውራሪ ።

«ሀይለ ስላሴ ከዙፋናቸው የወረዱት በፈቃዳቸው ነው ?» አለ ታፈሰ ።
«እሱ የተለመደ ነው ።»

«ይህም ይመጣል!» ብሎ በጨለማ ሲቅበዘበዝ እንደ መጣ ሲቅበዘበዝ ወጥቶ ሄደ ።

የታፈሰ ሁኔታ ደስ አላለውም—ሀዲስ ። ነጋ አልነጋ ብሎ ሲፈልገው ሄደ ። ቤት አላገኘውም ። ወደ ደኑ ሄደ ። ታፈሰ ከሰዎች ጋር ነበር ። ሲሰነባበቱ ነበር የደረሰው ። ሰዎቹ ከሄዱ በሁዋላ ፡ «ቀልደኞች !» አለ ታፈሰ ።

«ምንድን ነው ?» አለው ሀዲስ ።

«ባምስት መቶ ሺህ ብር እንግዛህ ነው የሚሉኝ ። ሞኞችውን ይፈልጉ ። ይህን ደን ቢያንስ ቢያንስ ባንድ ሚሊዮን ብር ተኩል ልሸጠው እችላለሁ ። ከዚያ በታች ንክች አላደርገውም» አለ ፡ ከፍ ካለ ቦታ ላይ ቆሞ አይኑ ሊያይ እስከሚችልበት ድረስ ደኑን እያየ ።

«ጥሩ ነው» በማለት ሀዲስ ጠጉሩን ቆፈረና ፣ «ስማ ታፈሰ ፣ አሁን የመጣሁት ላነጋግርህ ነበር» አለው ።

«ስለ ምን ?» አለ ታፈሰ ።
«ማታ ያየሁብህ ሆኔታና የምትናገረው ነገር ደስ አላለኝም...»
«ምን?» አለው ።

«ይሄ እዋጋለሁ ምናምን የምትለውን ነገር ብትተው ይሻላል ። በገዛ እጅህ በራስህ ላይ ጥፋት መጋበዝ ይሆናል ። የምክሩትም አልሆኑላቸውም ።»

«ባይተባበሩ ነው ። ዱሮውንም ፈሪዎች አይተባበሩም » አለው ።

ሀዲስ ቶሎ ብሎ ፣ «ቢተባበሩም አይሆንላቸውም» የሚል መልስ ሰጠው ።

«ለምን ?» አለ ታፈሰ ፣ ቅንድቡን ከፍ አድርጎ ።
«ህዝብ ላይ መተባበር ከንቱ ነው ። ይህን ነው ማየት ያለብህ...»

ታፈሰ አንዴ ሳቁን ለቀቀና ፣ «የትኛውን ህዝብ ነው የምትለው ! ስራ ፈቶችና የመንደር አውደልዳዮች ሆያ ሆዬ ቢሉ እውነት መሰለህ ? የህብረተሰቡ ዝቃጮች ተነስተው ሆያ ሆዬ ቢሉ እውነት አይምሰልህ ፣ ታያለህ ። አገሪቱ ኢትዮጵያ ናት ። ህዝቡም የኢትዮጵያ ህዝብ ነው ። አሁን ለጊዜው ዝም ያለው ሁሉ አሜን ብሎ የገበረ መስሎህ ከሆነ ተሳስተሃል ። መሪ ነው የሚጠብቀው» አለው ።

ሀዲስ ጠጉሩን ቆፈረና ፣ «ህዝቡ ከእንግዲህ ጭቆናን መልሶ ይቀበላል ብለህ አትመን ። ደግሞም ፣ የለውጥን መምጣት በታላቅ ስሜት የሚቀሰቅሰው አንተ ዝቃጭ የምትለው የማህበረሰቡ ክፍል ነው ። ሳዲሱ አለም በቀራጥነት ታጥቀው የሚነሱት እነሱ ናቸው» አለው ።

ታፈሰ አሁንም በሳቅ ፈነዳና ፣ «እና ፣ አሁን ምን ታጣለህ ? የትም ቦታ ሰርተህ ልትኖር ትችላለህ...እ...ለለውጥ ያህል ለራስህ ብቻ ሳይሆን ለህዝቡ ጥቅም ብታስብ ምናለበት» ሲል ሀዲስ ፣ ታፈሰ እንደ ገና በሳቅ ፈነዳ ።

«ምንድን ነው ያሳቀህ !» አለ ሀዲስ ቆጣ ብሎ ።
«ታስቀኛለህ ። ሞኝ ነህ ። በእውነት ሞኝ ነህ...»
«እንዴት ?»

«ይህን ሁሉ ጥፋት ፣ ሞትና ህገ ወጥነት እያየህ እንዲህ ስትል ይገርመኛል ፣ ያስቀኛል...»

«አንድን ለውጥ የምትለካው በዚህ መስፈሪያ አይደለም ።»
«ታዲያ በምንድን ነው!» በማለትት ሳለቀበት ።
«በይዘቱና በሚከተለው ትክክለኛ አቅጣጫ...»
«እና ፣ ይዘቱና አቅጣጫው ምን ይሆናል ልትለኝ ነው!»
«ታውቀዋለህ» አለ ሀዲስ ።

«ፍትህ ! እኩልነት ! ዴሞክራሲ !» እያለ በማራከስ ሲቀልድ ቆየና ፣ «አይ እናቴ ! እንዲህም አርጎ የለ ! ስለ ሞኞች ህልምና አለም አትንገረኝ ። ያስቀኛል ። በኢትዮጵያ ቀርቶ በሌሎችም አገሮች እውነተኛ ፍትህ ፣ እኩልነትና ዴሞክራሲ ይሰፍናል ብሎ የሚያምን ሰው ሞኝ ወይም እብድ መሆን አለበት ። ጥላ ማባረር ነው» አለው ።

ሀዲስ በበኩሉ ጠንከር ባለ አነጋገር ፣ «ጭቆናን አሜን ብሎ ተቀብሎ ከመኖር አሁን አንተ ያልከውን ጥላ ማባረር ይሻላል ።»

«እውነት በዚህ ታምናለህ ?» አለው ፣ ታፈሰ ።

«አዎ ፣ ግን ባፌ ብቻ በመሆኑ ያሳዝነኛል ። ያፍ ቂልምጫ ዋጋ የለውም ።»

«ማለት በዚህ ጥፋት ሁሉ ? በዚህ ርካሽ ሆያ ሆዬ ?»

«እኔ ጥፋት ነው አልለውም ። ለኔ ልማት ነው ። የጭቁን ህዝቦች የበላይነት ነው ። አንተ እንደምትለው ሆያ ሆዬም አይደለም ። ለኔ ፣ በብዙ ዘመን ንባብ ካገኘሁት ፣ አንተ አሁን ሆያ ሆዬ ነው ከምትለው ነገር ያገኘሁት ትምህርት በእጥፍ ድርብ ይበልጣል ። አብዮት ከሚፈጥራቸው ሰዎች የበለጠ ተአምራዊ ነገር የለም» ሲል ፣ ታፈሰ አይኖቹን ወደ ውጭ ጎልጉሎ አፈጠጠበት ።

«ምን ሆንክ?» አለው ሀዲስ ።
«ሩቅ ሄዶ መዋጋት ምን ያስፈልጋል ?» አለ ፣ አይኖቹን እንዳፈጠጠ ።
«ምን ማለትህ ነው ?»

«ይህን ማለቴ ነው !» ብሎ ፣ ሽጉጡን መዘዘና አከታትሎ ሁለት ጊዜ ተኮሰበት ።

ሀዲስ በቆመበት ድንጋይ ሆኖ ቀረ ። ታፈሰ እንደ ገና በሳቅ ፈነዳ ።

«አስኮናኝ ነህ» አለው ታፈሰ ።
«አንድ ነገር ይቆጨኛል» አለ ሀዲስ ንዴት እየተናነቀው ።

«ምን ?»

«ሳልጥልህ መቅረቴ» አለው ፣ ያን ምሽት ታፈሰ ቤት ሆኖ ያደረበት ስሜት ትዝ እያለው ።

«ወንድም አማች ፣ ለሱ አትቸኩል ። እንደርስበታለን ። አሁን ከሌሎች የእንጨት ነጋዴዎች ጋር ቀጠሮ አለኝ ።»

ትንሽ ከሄደ በሁዋላ መለስ በማለት ፣ «በነገራችን ላይ ፣ የትምህርት ቤቱ ስም የካቲት 66 እንዲባል ከስልጣን ከመነሳቴ በፊት ወስኜ ነበር ። አሀሀሀ! » እያለ ሲስቅ ፣

ሀዲስ ጮክ ብሎ ፣ «እንደ ገና ስንገናኝ ከሁለታችን አንዳችን የምንስቀው ሳቅ የመጨረሻ ይሆናል !» አለ ።

ከዚያ በሁዋላ ከታፈሰ ጋር ተገናኝተው አያውቁም ። ድኑን ለመሸጥ ሲያስማማ ይውላል ፤ ገኘ አጥቶ ይበሳጫል ፤ ይናደዳል ፤ ይጠጣል ፤ ይብ ክራል ሲባል ሀዲስ ከሩቅ ይሰማል ። በመጨረሻ በሰባት መቶ ሽህ ብር ገዢ አገኝቶ ቀብድ ሲቀበል ነው የሚል ወሬ ተሰማ ። እንዲጋጣሚ ሆኖ በዚያኑ ቀን የገጠርን መሬት ለህዝብ ያደረገው አዋጅ ድንገት ታወጀ ። ታፈሰ ሲሮጥ መጣ ። ታፈሰ ሽጉጥ ታጥቆአል ። ሀዲስ ላይ ድንገት አፈጠ ጠበት ። ሰውነቱ ተለወጠ ። አይኑ ደም መሰለ ።

«አንተ የውሻ ልጅ !» ብሎ ሽጉጡን መዘዘ ።

ሀዲስ ከተቀመጠበት ተወርውሮ ተነሳ ። ቶሎሳ ዘሎ ታፈሰን ያዘው ። መምሩ በመስቀላቸው ታፈሰን ተማጠኑት ።

«ምንድን ነው እሱ !» አሉ ፊታውራሪ በነገሩ ግራ ተጋብተው ።
«ጠላታችን እዚሁ ነው!» አለ ታፈሰ ከቶሎሳ ጋር እየተናነቀ ።
«የምን ጠላት !» አሉ ፊታውራሪ ።
«አንተው ነህ የራስህ ጠላት ። እኔ የማንም ጠላት አይደለሁም . . .»

«ምንድን ነው ነገሩ ! ምን ጉድ መጣ ? ማን ነው'ኮ የሚያስረዳኝ!» አሉ ፊታውራሪ ተናደው ።

ታፈሰ ሽጉጡን መልሶ አጎኑ ሻጠና ፣ «ገን አመለሳለሁ ። ያኔ ከሁለ ታችን አንዳችን ይለይልናል ። ታያለህ!» ብሎ እንደ እብድ እየሮጠ ወጣ ።

«ይህ ሰው አብዶአል ? ወይስ ምን ነካው ? ደግሞ ወዴት ነው የሚ ሮጠው ?» አሉ ፊታውራሪ ነገሩ ሁሉ እያስደነቃቸው ።

«መአት ቁጣ ነው ሌላ አይደለም ። ስምንተኛው ሽህ ማለት'ኮ ይኸው ነው ። ወንድም በወንድሙ ላይ ሲነሳ ከማየት ሌላ ምን ምልክት አለ ?» አሉ መምሩ ።

«ምንድን ነው ነገሩ ? በምን ተጣላችሁ ?» አሉ ፊታውራሪ ወደ ሀዲስ መለስ ብለው ።

«ምንም አይደለም ። ጥሉ በኔና በታፈሰ መካከል ብቻ አይደለም ። ባገር የመጣ ነው ። ገሃነመ እሳት ገና ሲንቀለቀል ይታየኛል» አለ ።

«ሰው ቻሎ አበደ ልበል ? ወይስ እኔው ነኝ ጤና ያጣሁት ?» በማለት ይተክዙ ጀመር ።

ቶሎሳ እየሮጠ መጥቶ ፣ «አንድም ክብት አልቀረንም!» አለ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

«እንዴት?» አሉ ፊታውራሪ ።
«ተነዱ . . . ተወሰዱ . . .»
«ማን ነው የነዳቸው?»
«ጭሰኞች ፣ የኛው ጭሰኞች . . .»
«ለምን'ኮ ?»

«ወረሱዋቸው ። ከመሬቱ ጋር ። መቼ ይህ ብቻ ! የእህል ጎተራዎች ፣ የቡና መጋዘኖች ፣ ወፍጮ ቤቶች ሁሉም አልቀሩቸውም ። ወርሰናል ፣ የኛ ነው እያሉ ይጨፍራሉ ። አልሊታውና ዘሬን እየቀለጠ ነው—በየቦታው ። ስርግና ምላሽ ሆኖአል» በማለት ነገሩቸው ።

«የኔ ጭሰኞች ?» አሉ ፊታውራሪ ።
«አዎ ።»
«የኔን ጉብረት ወረሱ ?»
«አዎን ፣ ወርሰናል ይላሉ ።»
«ብዙ የለም» አሉ መምሩ ።
«የኔን ከብቶች ነዱ ?»

«ብያለሁኮ ። ሎሌ በጌታው ላይ ያምፃል በስምንተኛው ሽህ» ሲሉ መምሩ ፣ አንድ የቤት አሽከር ጫን ጫን እየተነፈሰ ገባ ።

«ምንድን ነው ? እንስማው ጉዱን ። መቼም የጉድ አገር ሆኖአል ። የኢዮብን ጆሮና ልብ ይስጠን ማለት ብቻ ነው ። እግዜር ስጠ ። እግዜር ነሳ እንበል እንጂ !» አሉ ፊታውራሪ ።

«ልጅ ታፈሰ በገበሬዎች ተከበዋል አሉ ?» በማለት አሽከሩ ባንድ ትንፋሽ ነገሩቸው ።

«ለምን?» አለ ሀዲስ ።

«መሬታቸው ላይ ያለውን ደን ሊያቃጥሉ ሲሉ ደርሰውባቸው ነው አሉ . . .»

ሀዲስ ተነስቶ ወደ ቤቱ ሮጠ ። አይናለም ትኩዋኩዋል ነበር ። ከታፈሰ የወሰደውን ሽጉጥ ወስዶ ሊሄድ ሲል ፣ «የት ነው የምትሄደው?» አለችው ።

አይኖችዋ እንደ ንጋት ኮከብ ያበራሉ ።

«መጣሁ» አላት ።
«ሽጉጡ ምን ያደርግልሃል ?» አለችው ።
«ለጉዳያው ነው . . .»
«ወዴት ልትሄድ ነው ?» አለች አፍዋ ፈራ ተባ እያለ ።
«አይዞሽ መጣሁ» ብሎ ከንፈርዋ ላይ ሳማት ።
«ምንነው ልቤ ፈራ ?» አለች ።
«አይዞሽ ምንም የለም ። አሁን እመጣለሁ» ብሎአት ሊሄድ ሲል ፣—
«ምንድን ነው ይሄ የመሬት አዋጅ ?» አለች ።

«ስመለስ ስለ እሱም አጫውትሻለሁ» ብሎ አሁንም ሊሄድ ሲል ጠበቅ አድርጋ ያዘችው ።

እንደ ገና ከንፈሮችዋ ላይ ሳማት ።

«ሀዲስ አትሂድ ፣ ደስ አላለኝም ። ምንም ሊገባኝ አልቻለም ። ምንድን ነው እሱ?»

«መጣሁ አለምዬ» ብሎ ጥሎአት ወጣ ።

በር ድረስ ተከተለችው ። ያፈጠነውን ያህል ይሮጥ ነበር ። ቶሎሳ እንዳለው ፥ ገበሬዎች በየቦታው ይጨፍራሉ ። እልልታውና ዘፈኑ ይቀል ጣል ። ሰዉ እንዳለ ከቤቱ ተገልብጦ የወጣ ይመስላል ። የጥምቀት በአል ምስጋና ይንሳው !

እንዶ ሮጠ ታፈስ ብሩ መሬት ላይ ደረሰ ። ዶኑ መጋየት ጀምሮአል ። ገሃነመ እሳት ራሱ የሚንቀለቀል ነበር የሚመስለው ። ጦርና ጠብመንጃ የያዙ ገበሬዎች አድፍጠዋል ። አንዳንዶቹ ኡኡታ ያሰማሉ ። ኡኡታውን የሰሙ ያካባቢው ገበሬዎች ወደ ስፍራው እየሮጡ ሲመጡ ይታያሉ ። አድፍጠው የነበሩት ገበሬዎች ሁሉ አፈጠጡበት ። አንዳንዶቹም የያዙ ትን መሳሪያ ደገኑበት ።

«ቁም ! ማን ነህ አንተ !» አለ አንዱ ከመካከላቸው ።
«ሀዲስ እባላለሁ» አለ ።
«መምህር ፥ እዚህ ምን አመጣዎት ?» አለ ሌላው ።
«ምንድን ነው ነገሩ ?» አለ ሀዲስ ።

መጀመሪያ የተናገረው ሰው ነበር ፥ «ታፈስ ዶኑን እያጋየ ነው ። እሳ ቱን እንዳናጠፋው ይተኩስብናል ። እጅህን በሰላም ስጥ ብንለውም እሺ አላለም ። ግን ህይወታችን እያለ ይህ ደን ተቃጥሎ አያልቅም ። ሆ ብለን ልንገባ ስንል ነው የደረስከው» በማለት መልስ የሰጠው ።

«ቆዩ ፥ ቆዩ ። እኔ አግባባዋለሁ ። እና ፥ እሳቱን እናጠፋለን ። አትተ ኩሱ» አለና ወደ ዶኑ ሮጠ ገባ ።

የጢስ ጉም ዋጠው ። ጢሱ አፈነው ። ከመታፈኑ የተነሳ ያስለው ጀመር ። በመቀጣጠል ላይ ያሉት ርጥብ ዛፎች ሲንጣጡ ፥ የመሸጉ ወታ ደሮች ተኩስ ከፍተው አለም የተደበላለቀች ያህል ያስፈራል ። ተቃጥሎ ያለቀ ዛፍ ሲገነደስ እንደ መድፍ ያጉዋራል ። እሳት በየቦታው ይንቀለ ቀላል ። ሀዲስ እየተጨናበሰ ፥ እየተደናበረ ፥ እየሳለና እየተሽሎከለከ ሄዶ ታፈስ ወደሚያዘወትረው ስፍራ ሲጠጋ ፥ «ታፈስ ! ታፈስ ! ሀዲስ ነኝ ። ስማኝ ታፈስ !» እያለ ይጮህ ጀመር ።

የገደል ማሚቶ የገዛ ድምፁን መልሳ ታስማው ነበር ። ጉሬዛዎች በእሳት ወደ አልተያያዘ ዛፍ ይዘላሉ ። ሚዳቋዎችና ዱኩላዎች ደንብረው ይሮጣሉ ።

«ታፈስ ! ሀዲስ ነኝ ። እባክህ ስማኝ» እያለ ሲጮህ ፥—

ከበስተጀርባው ፥ «የያዝከውን ሽጉጥ ጣል ! ጣለው ነው የምልህ !» የሚል ድምፅ ሰማ ።

ሀዲስ የያዘውን ሽጉጥ ጥሎ ዞር ሲል ፣ የጠብመንጃ አፈ ሙዝ አፈጠ ጠበት ። ከታፈስ ጋር አይን ለአይን ተጋጩ ።

አውቶማቲክ ጠብመንጃውን ሀዲስ ደረት ላይ አነጣጥሮ እንደ ደገነ ፥ «በመምጣትህ ደስ ብሎኛል ። በደህና ትቼህ በመምጣቴ ሲቆጨኝ ነበር» አለ ጥርሱን እየ ነከሰበት ። «እንኩዋን ደህና መጣህ ። ፀሎትክን አድርስ ።

ግን፣ ለካ ፀሎት አያስፈልግህም? እግዜርን የት ታውቀውና! ማርከሲስት አይደለህ? ሆኖም በጥቂት ደቂቃዎች እግዜርን ታገኘዋለህ ። እና፣ ገሃነም እንድትወርድ ይፈርድብሃል!» አለው ።

ሀዲስ ጀርባውን አሳበው ።

«ስማ ታፈስ» አለ ፣ «የምታደርገው ነገር እብደት ነው ። ምን ለመ ሆን ነው ? ደትን አቃጥለህ ምን ታገኛለህ?»

«ይቃጠል ! ይንደድ ! የኔም አንጀት ተቃጥሎአል» አለ ።
«በህይወት ከደን የተሻለ ብዙ ነገር ሞልቶአል ።»
«እንደ ምን ያለ ?»
«እንደ መኖር ያለ . . . »

«ዝም በል ነው የምልህ!» ብሎ ጠብመንጃውን አቀባበለና ፣ «የተ ጫወትነውን የሞት ጨዋታ ታስታውሳለህ ? ያሁኑ እውነተኛው ነው!» አለው ።

የደም ስሮቹ ሁሉ ተገታተሩ—ታፈስ ። አይኖቹ ደም ለበሱ ። ጥርሱን ነከሰ ። ሀዲስ ላብ አሰመጠው ።

«ታፈስ እባክህን አስብበት» አለ ሀዲስ ፣ «እጅህን ብትሰጥ ምናለ በት ? ምንም አትሆንም ።»

«ግንባርህ ላይ ወይስ ደረትህ ላይ ብለቅብህ ትመርጣለህ ?» አለው ጥርሱን ነክሶበት ።

«እሱን እንደፈለክ ። ስቃይ የሌለበት ሞት የለም ። ግን እኔን በመ ግደል የምታተርፈው ነገር የለም ። አንተም ትሞታለህ ። ተከበሃል ። ያለ ሁህ እድል እኔ ብቻ ነኝ» በማለት ሀዲስ ተጨንቆ ወተወተ ።

«ለምን እኖራለሁ ? ያለኝ ሀብት ሁሉ ሄዶአል» አለና ድንገት እንደ እብድ ብቻውን ስቆ ሲያበቃ ፣ «አንተም የቁዋመጥከው ሀብት ሄዶአል ። መኖር ምን ያደርግልሃል ? እጦት የቁም ሞት ነው» ብሎ የጠብመንጃውን አፈ ሙዝ ሀዲስ ግንባር ላይ አነጣጥሮ ያዘ ።

«እዝናለሁ ። ፈፅሞ አታውቀኝም ። ለኔ ሀብት ምኔም አይደለም » አለና ድንገት ፣ «ከሁዋላህ ! ተጠንቀቅ !» ብሎ ጮኸ ።

ታፈስ ዞር ከማለቱ ሀዲስ እንደ ነብር ዘሎ ያዘው ። የታፈስ ጠብመንጃ ባረቀ ። ታፈስ ሚዛኑን አጥቶ ነበር ። ሀዲስ ፊቱ ላይ ሁለት ቡጢ አከታ ትሎ ካሳረፈበት በሁዋላ ይዞ ጣለው ። ተናንቀው መሬት ለመሬት ይን ከባለሉ ጀመር ።

እጠገባቸው ያለው ቁጥቋጦና ሳር ቅጠሉ ሁሉ በእሳት ተያይዞ አል ። የተቃጠለ ግንድ እየተገነደሰ ይወድቃል ። ሀዲስ እንደ ጅግት የከ ረረ ቢሆንም ፣ ታፈስ ጠንካራና ፈጣን ስለ ሆነ ፣ የሀዲስ ግንባር ፣ አፍንጫና አፍ ክፉኛ መድማት ጀምሮአል ። አይኑ ሁሉ በደም ተሸፍኖአል ። ግን

አልለቀቀውም ። ጉሮሮውን አንቆ ይዞ ይታገለው ነበር ። እየተንከባለሉ በእሳት ተያይዘ ወደሚነድ አንድ ቁጥቋጦ ተጠጉ—ላብ—ደም—እሳት ! ሀዲስ ለህይወቱ ታገለ ። አንቆ ትንፋሹን ሊያወጣው ሲል ፥ ታፈሰ ፥ ደመ ነፍሱን መሬት ሲቡዋጥጥ የወደቀ እንጨት አገኘቶ ፥ ሀዲስን አናቱን ብሎት ከላዩ ላይ ጣለው ። ሀዲስ አእምሮውን አልሳተም ። ለመነሳት ሲንደፋደፍ ፥ ታፈሰ ሜዳ ላይ ወድቆ የነበረውን የሀዲስን ሽጉጥ አንስቶ ዞር አለበት ። ሀዲስ አይኖቹን ጨፈነ ።.ወዲያው ሁለት ጥይት በተከታታይ ተተኮሰ ። ሀዲስ እንደ ገና አይኑን ሲከፍት ታፈሰ ዘጭ ብሎ ሲወድቅ አየው ። ደም ባፉ ቡልቅ ቡልቅ እያለ ይወርድ ነበር ። ሀዲስ እንደ ምንም በደረቱ ተስቦ ሄዶ አንገቱን ቀና አድርጎ ያዘው ።

«አ ! . . .አሁንም አለህ ? አቃተኝ አ—አይደለም አንተን መግደል!» አለ ታፈሰ ወደ ሰማይ እያየ ።

«ለምን ታፈሰ ? ይህ ሁሉ ለምን ኖርአል ?» አለ ሀዲስ ።

«ያለፈ አለፈ ። አ—አሁን ተወው» አለና ፥ አይኖቹን ሰማይ ላይ ተክሉ ፈገግ አለ ። «እንዳልከው የብር ምልክት መቃብሬ ላይ አድርግልኝ ። እና ፥ እዚሁ ደኔ ውስጥ ከዚያ ከምወደው ዛፍ ስር ቅበረኝ ። ተበቶ እንደ ጨበጡ መሞት ጥሩ ነው ። አይ—አይመስልህም ?» ብሎ አይኖቹን ሰማይ ላይ እንደ ተከለ ለመጨረሻ ጊዜ ፀጥ አለ ።

በፊት ያነጋገረው ባላገር ሲሮጥ መጥቶ ፥ «መምህር ፥ ደህና ኖት ? ባልደርስልዎት ኖር ሊገድልዎት ነበር ይህ ሽፍታ» አለ ።

ጠብመንጃ ይዞአል ።

የታፈሰን አይኖች ከድኖ ፥ «ደህና ነኝ» ብሎ ተነሳ ።

በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ሰዎች እሳቱን ለማጥፋት' ይራወጣሉ ። እሳቱን በቅጠልና ባፈር ይደበድባሉ ። ሀዲስ የታፈሰን ሬሳ አስይዞ ወደ ቤት ሄደ ።

ቤት ሲደርስ ሌላ ውዝግብ ጦር ጠበቀው ። ፈታውራሪ ተካ ታጥቀው ተነስተዋል ። አይናለም ታለቅሳለች ። መምሬ መሀሪ ፈታውራሪን በመስቀል ይማጠናሉ ። የሀዲስ ሁኔታና የታፈሰ ሞት ሲጨመርበት ነገሩ ይበልጥ ተወናብዶ ቤቱ.ልቅሶ በልቅሶ ሆነ ። አይናለም ወደ ሀዲስ ትሮጥ ጣለች ። እንዴ እንቷ ልጅ ሬሳ ላይ ወድቃ ትጮሃለች ። ወደ አባትዋ ትሮጥና ነጠላቸውን ይዛ ታለቅሳለች ።

«ማን ነው የገደለው ?» አሉ ፈታውራሪ ።

«እሱ ሞቶአል ። እርስዎ ደግሞ አሁን ምን ሊሆኑ ነው የተነሱት ?» አለ ሀዲስ ንዴት እየተናነቀው ።

«ልጄን ማን አባቱ ነው የሚይዘው!»
«ማን ነው እጅዎ ሊያዝ ነው ያለው ?»

«ሰምቻለሁ ። ደርጎች የሚባሉ ሰዎች መጥተዋል አሉ ። መሬቴን ፣ ሀብቴን ፣ ንብረቴን ፣ ማዘረፋቸው አንሶቻቸውና ደግሞ እጄን ሲይዙ ፈለጉ ! ባ ላገር ሲዘርፈኝ እንደ ቤት ቁጭ ብዬ ማየቴ አንሰና እጄ ይያዝ!

«ይህን ጉድ ሲያሳየኝ ኖርአል የጎለተኝ ! የቱ ወንድ ነው የኔን እጅ የሚይዘው ? ከንዴ ምን ቢደክም አንድ ጠብመንጃ መያዝ አያቅተውም» ብለው ለመሄድ ተነሱ ።

«ኧረ ባማላጅትዋ!» አሉ መምሬ መሀሪ ። «ሬሳ ቤት አስቀምጠው እንዴት ይሄዳሉ ?»

«ሙታናችንን ለመቅበር ከእንግዲህ ጊዜ የለንም ። መሬትም ሰውም ከድቶናል ። መቀበሪያም የለን ። ዱሮውንም ቢሆን የጀግና ቀባሪ አሞራ ነው ። ዱሩ እንደሆን ያው የምናውቀው ዱር ነው ። ሌላ ምን ይመጣል?»

«ኧረ እባክዎን አይሆንም... »

«ሊገራችሁ እሾህ ፣ ገላችሁ ቆንጥር ያልለመደው እናንተው እዚሁ እንደ ፍጥርጥራችሁ ሁኑ ። እኔ እጄን ለማንም አልሰጥም ። እንዴ ! ከብት ከበረቴ ፣ እህል ከመሬቴ ወረሱ ። ይህ አልበቃ ብሎአቸው ደግሞ እጄን ለመያዝ ፈለጉ ? ያው እንዳባቶቼ እሞታለሁ እንጂ እጄንስ ለማንም አልሰ ጥም ! የሰው ነገርም በቃኝ ። ያበላሁዋቸው ያጠጣሁዋቸው...እ...ሲቸ ገሩ ከችግር ያወጣሁዋቸው ! ሲታረዙ ያለበስኩዋቸው ! ሲታመሙ የጠ የቅሁዋቸው ዛሬ ጊዜ አይተው ይከዱኝ!? ከብቶቼን ይንዱ!? እህሌን ከመ ሬቴ ይውረሱ!? ዋ ሰው ! የሰው ነገር በቃኝ !» በማለት ቶሎሳንና ሌሎች አምስት ታማኝ አሽከሮቻቸውን አስከትለው ! ድጋቸውንና ዝናራቸውን አሳምረው ተነሱ ።

የአይናለም እምባና ልመና የመምሬ መሀሪ ተማኅፅና ግዝት ትጥቃ ቸውን ሲያስፈታቸው አልቻለም ።

«በሚወዱዋት ፣ በተከልዋት እልቂ ማርያም...»

«ይልቅ በፀሎትዎ አይርሱኝ መምሩ...አንተም የልጄን ነገር አደራ ።

የልጅ ልጅ ለመሳም አላደለኝም» ብለው ወጡ ። ገረዳቸውም አገ ልግልዋን ይዛ ተከተለቻቸው...

ሀዲስ አይናለምን ከማፅናናት ሌላ የሚያደርገው ነገር አልነበረም ። የታፈሰን ኑዛዜ አለመፈፀሙ እየቆጨው እልቂ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጉዋሮ አስቀበረው ። ቀብሩ አላማረም ። እልቃሽ ቆማ አገር ተላቅሶ አልተቀበረም ። ጭር ያለ ቀብር ነበር ።

ፊታውራሪ ተካ ሸፈቱ ተብሎ አገር ተረብሾ ነበር ። ሌሎች የሱዳ ባላባቶችና የቀድሞ ባለርስቶች ሁሉ ከነአሽከሮቻቸው ገቡላቸው...እሁ ንማ ከጎናቸው የተሰለፈው ሰራዊት አገር ይፈታል...ርዳታ ከሌላ ቦታ እየመጣላቸው ነው አሉ...የሸፈቱት የወንድማቸውን ልጅ ደም ለመበቀል ነው ይባላል...የሚል ወሬ በድፍን ሱዳ ይነዛ ጀመር...

አንድ ቀን ጠዋት ሀዲስ ተጨንቆ ሲያስብ ፣ የሃምሳ አለቃ ጎይቶም ወደ እነሱ ቤት ሲመጣ ከሩቅ አየው ። የመጣበትን ምክንያት በልቡ ጠረ ጠረ...

«ግድ የለም ንገረኝ» አለ ሀዲስ ።
«አርፈዋል» አለው ።
«እንዴት መቼ ?»

ፊታውራሪ ወደ ባላገር ሄደው ካንድ ርስታቸው ላይ ትንሽ ጎጆ ውስጥ ተቀምጠው ነበር ። እንደ ተወራው ሳይሆን ከቶሎሳና ከሌሎች ጥቂት ታማኝ አሽከሮቻቸው ሌላ ማንም አጠገባቸው አልነበረም ። የሃምሳ አለቃ ጎይቶምና እሱን የተከተሉት ፖሊሶች በጠቋሚ ከስፍራው ደር ሰው ፤ ፊታውራሪ ተካ በሰላም እጃቸውን እንዲሰጡ ይጠይቃሉ ። ከቤት ውስጥ አንድ ጥይት ይተኮሳል ። የሽጉጥ ጥይት ነበር ። ለጊዜው ፀጥ ይላል ። ቤቱን የከበቡት ፖሊሶች ግራ ይጋባሉ ። ከዚያ በሁዋላ ከቤቱ ውስጥ የቶ ክስ እሩምታ ይከፈታል ። ፖሊሶቹም በበኩላቸው ተኩስ ይከፍታሉ ። ቶሎሳ እየተኮሰ ሲወጣ ተመትቶ ይወድቃል ። ሌሎቹም እንዲሁ እየ ተኮሱ ለማምለጥ ሲሞክሩ እየተመቱ ይወድቃሉ ። በመጨረሻ ፣ አገልግል የያዘች አንድ ሴት ብቻዋን እየጮኸች ስትወጣ ተኩሱ ይቆማል ። ፊታ ውራሪ ቀደም ሲሉ የገዛ ሽጉጣቸውን ጠጥተው ነበር የሞቱት ።

«ኢና ፣ ይህ ከፊታውራሪ ኪስ ውስጥ የተገኘ ወረቀት ነው» ብሎ ለሀ ዲስ ሰጠው ፣ «ልጄን ጊዜ ከዳት ብለህ እንዳትከዳት አደራ ። ስላሴ ቅበ ሩኝ» የሚል መልእክት ነበር ...

«አስከሬናቸውስ?» አለ ሀዲስ ።

«ስላሴ ተቀብርአል ። ከአያታቸውና ካባታቸው ጎን ። በጣም አዝና ለሁ» አለው ጎይቶም ።

እውነትም ከልቡ አዝኖ ነበር ። አይኖቹ እንባ አቅረዋል ።

«ምንም አይደለም» አለ ሀዲስ ።
«ኦሮማይ !»
«ኢ?»

«ምን ይደረጋል ማለቴ ነው ። ከጥልያን የወረስነው ቋንቋ ነው» አለ ጎይቶም ።

ጎይቶም ተሰናብቶት ሊሄድ ሲል ሀዲስ ፣ «ለመሆኑ ዮሀንስ እንዴት ነው?» ብሎ ጠየቀው ።

«ወዲ ከልቢ !» የሚል መልስ ሰጠው ።
«ምነው ?» አለ ሀዲስ ።
«ኬይዶ የሉንዲው...»
«እ?»
«ሄድዋል ።»
«ወዴት?»
«የናት አገር ጥሪ ብሎ...ናብ በረኻ ። ቤሽቲያ !»

«እውነት?» አለ ሀዲስ ተገርሞ ። ግማሽ ልቡ ሩስ ሸታዬ ነበር የማ ያስበው ።

«ሄደ ። አባ ደርሶአል አሉ ። ከሻእቢያ ጋር ተቀላቅሎአል ። እኔ ሳላ ውቅ በፊትም የማህበር ሾኡቴ እባል ነበር ። ቢሸቲያ ! ወኡሳህል ይሁን ወይም ከርከ ላይ አንድ ቀን ግምባር ለግምባር ገጥመን ስንታኮስ ይታዩ ኛል» አለ ሩቅ እያየ ።

ጎይቶም ከልብ ያዘነ ይመስላል ፤ ሲናገር ሁሉ ቁር ሀማሴን እንደ ያዘው ሰው ሰውነቱ ይንቀጠቀጥ ነበር ።

«የናት ሆድ ዥንጉርጉር ነው ይባላል» አለ ሀዲስ ፡ የጎይቶም ሀዘን እየተጋባበት ።

«ዋ እንዶ ! ወላዲት ሀገርና ሆንቲ ኢትዮጵያ እያ ። እን ካልእ አይፈልጥን ። ግን እርግይ ። እንዳልከው የናት ሆድ ዥንጉርጉር ነው» ብሎ ራሱን ነቀነቀ ።

«አሁን እስዋ እንዴት ናት ?» ብሎ ሀዲስ ጎይቶምን ጠየቀው ።
«ማን ?» አለ ጎይቶም ።
«ሸታዬ—ባለ ቤቱ ?»
«ዋእ ! እስዋማ የአምስት ወር ቅሪት ናት ። ቢሸቲያ !» አለው ።

ሀዲስ ከጎይቶ ምከተለየ በኋላ ቤት ገብቶ ፡ «አለምዬ ፣ ከዚህ እንሂድ» አላት ።

«የት» አለችው አይኑን አይኑን እየተመለከተች ።
«ወደ አዲሳባ» አላት ።
«አባቴ ሞተ ፣ ሞተ አይደለም ? ንገረኝ ፣ ግድ የለም» አለች ።
«አዎ» አላት አገዞ ።
«እንደ ወጣ የትም ወድቆ ቀረ ?»
«ስላሴ ተቀብረዋል ። እንደ ፍላጎታቸው» አላት ።

አላለቀሰችም ። ይዘው የሚሄዱትን እቃ ሲያዘጋጁ ውስው አመሹ ። መምሬ መሀሪን ሊሰናበቱ ፈልገው ነበር ። አላገኙዋቸውም ። ፊታውራሪ ከሄዱ ወዲህ ብቅ ብለው አያውቁም ። መምሩ ባዶ ቤት ምናልባት አይወዱም ይሆናል ። የትኛውን ማእድ ሊባርኩ ... ጡዋት እቃቸውን አስጭነው ተያ ይዘው ሲወጡ ፤ አንድ ጊዜ ብቻ ወደ ሁዋላ መለስ ብላ ያባትዋን ግቢ ተመ ለከተች ። ጭር ብሎአል ። እና ፣ መንገዳቸውን ቀጠሉ ። ቀኑ ማክሰኞ ነበር ።

በትምህርት ቤቱ በኩል ሲያልፉ ፣ 'የካቲት 66 ትምህርት ቤት' የሚል ፅሁፍ በትልቁ ተፅፎ በማየቱ ቆም አለ ። ያወል ቤቱም ከሩቅ ይታያል ። ሲያወል ሁሌቱም ሰሙ ። ተያዩ ። ደስ የሚል ድምፅ ነበር ። የሰላም ፤ የፍቅር ፤ የወደፊት ህይወት ጥሪ ...

«አንድ ቀን እንመለስ ይሆናል» አላት ፣ ሌላ ትልቅ ትምህርት ቤት እየታየው ።

አይናለም መልስ አልሰጠችውም ። አይንዋ ወደ ሌላ ነገር ነበር የሚ መለከተው ። አይንዋን ባይኑ ተከተለ ። የፌታውራሪ ገረድ ፥ ከዳን የሌ ሰው ባዶ አገልግል አዝላ ፥ ዳገቱን ቀስ እያለች ስትወጣ ከሩቅ ትታይ ነበር ። አይናለም እንባዋን ለመያዝ አልቻለችም. . .

ከመርዳሳ በተኩራዩዋቸው በቅሎዎች የገባን ወንዝ ቁልቁለት ተያ ያዙት ። ፀሀይዋ ግላለች ። ዝምታ የሰፈነበት ጉዞ ነበር ።

«መንገዱ እንዴት ነው ? ሰላም ነው ?» ብሎ መርዳሳን ጠየቀው ።
«መንገዱስ ሰላም ነው...»
«ሌላውስ ?»
«ሌላው አይወራ ። አገሩ ተናግቶአል ።»
«አይዞህ ቢናጋም ለሰላም ነው ።»
«እስቲ ያድርገዋ ። እዚህ ኖጿ ላይ ሰሞኑን ሰላም የለም...»
«ምን ሆነ ?»

«ዘማቾች ዳስ ውስጥ እንደ ተኙ በእሳት አቃጥለው ፈጁዋቸው ። ከሳት ውስጥ ያመለጡትንም በጥይት ጨረስዋቸው ። እዬ ያረመኔ ስራ ነው የተሰራው ።»

«እነማን ናቸው እነሱ ?»
«ዳኛቸው የሚባለው የፌታውራሪ አያና ልጅና ግብረ አበሮቹ...

«እነሱም ታድነው ተገደሉ ይባላል ። የለም ፥ ውሸት ነው ፥ አልተ ገደሉም የሚሉም አሉ ። የሆነ ሆኖ እንዲህ አይነቱን ጭካኔ መፈፀም አልነበረበትም ።»

«መሬት ከሄደ ጡዋትና ማታ በምን ይጠጣ ብለህ ነው !» አለውና ኮርቻው ላይ ከተመቻቸ በሁዋላ ፥ «መሬት እንግዲህ የባለቤቱ ሆናለች ። ለምን እርሻ አትጀምርም ?» ብሎ ጠየቀው ።

አይናለም ከኮርቻው ጋር የተጠፈረች ነበር የምትመስለው ። ባቅሟ መጥዋ ቀናባት ። አንዴም ወደ ሁዋላ ገልመጥ አትልም ። ዝም ብላ ፊት ለፊት ነበር የምትመለከተው ።

«እዬ ጌታዬ ምኑ ተይዞ» አለ መርዳሳ ፥ «ባለ መሬቶች ከዛሬ ነገ ይመለሳሉ እያሉ ያስወራሉ ። እኛ ጋ ያሉት ዘማቾች አዋጁ አለ ጊዜው ነው የታወጀው ፥ የመሬት ከበርቴዎች ትጥቃቸውን ሳይፈቱ ድሀው ገበሬ ተደራጅቶ ሳይታጠቅ አዋጁን ማውጣት ድሀውን ለማስፈጀት ካልሆነ ዋጋ የለም ይሉናል ። ገና ነገሩ አልገባንም» አለው ።

ሀዲስ አሁንም ኮርቻው ላይ እየ ተመቻቸ ፥ «አይምሰልህ ። መብትህ ያውልህ...እወቅበት ካልተባለ ድሀው ገበሬ ምን ይዞ ይደራጃል ? አላ ማውና ስልቱ ያልገባቸው ሰዎች ናቸው ያለ ጊዜው የታወጀ አዋጅ ነው የሚሉት ። አዋጁን አውጆ መሞትም ራሱ ታላቅ ስራ ነው» እያለው ሲጉ ዋዙ ፥ ከገባ ወንዝ ድልድይ ላይ ደረሱ ። ሀዲስ የበቅሎውን ሉጉዋም ገታ አደረገ ። አይናለምም በቅሎዋን ቆም አደረገች ።

ፏፏዋቴው ከላይ ወደ ታች በቁጣ ይናዳል ። ቀስተ ዳመና ከታች ወደ ላይ ይወረወራል ፡ የገባ ወንዝ እየ ጋለበ ይወርዳል ። ወደ ሌላው ትልቅ ወንዝ—ወደ እማይሞላው ባህር—ዝንተ አለም ወደማይሞላው ውቅያኖስ ።

ላንዳፍታ የሰው ልጅ ህይወት ታሪክ በሚወርደው ወንዝ ላይ ተፅፎ ተነበበው ። ፀሀይ ትወጣለች ትጠልቃለች ፡ ትውልድ ያልፋል ትውልድም ይተካል ። የሰው ልጅ ህይወት ታሪክ ግን ይቀጥላል ። የሰው ልጅ በነፃነት ፣ በእኩልነትና በሰላም ለመኖር የሚያደርገው ተጋድሎ በከንቱ ሊሆን አይችልም ። አለበለዚያ የትግሉ አላማና ትርጉም ምንድን ነው? የለም ፡ ህይወት ምን ጊዜም ቢሆን ከንቱ አይደለችም—አለ ባሳቡ ፣ እፊቱ እየተዘረጋ የሚሄደውን የገባን ወንዝ እየ ተመለከተ ።

«አለምዬ አይዞሽ ። ህይወትን ያለ ድፍረትና ያለ ተስፋ አያኖሩትም ። ‘እንሂድ ፣ ወደፊት እንሂድ’ ይላል ወንዙ» አላት ።

እና ፤ ድልድዩን ተሻገሩ...

ልክ በቀጠሮ ሰዓት በመደረሱ ደስ ብሎት ረድም ቅልጥሙን አመሰገነ ። በስንት ደጅ ጥናት ያገኘው ቀጠሮ ነበር።

‹‹ቀጠሮ አለህ?›› ብላ ጠየቀችው የቢሮ ጸሐፊ።

ሽቶዋ ያውዳል። ጡቶችዋ ጠላት ላይ የተደገኑ ሮኬቶች ይመስላሉ። ‹‹ኮደልቴ›› ጥቁር ሹራብ ለብሳለች። የልብ ቅርጽ ያለው ያንገት ጌጥዋ ከጡቶችዋ መሃል ተሸጉጦ ይታያል። ቶሎ ብሎ አይኑን ከጡቶችዋ ላይ ነቀለ። ፈገግ አለች። ትኩስ የተሸለቀቀ በቆሎ እሸት የሚመስሉትን ጥርሶቹን አሳያትና ‹‹አዎን፤ ቀጠሮ አለኝ›› አላት።

‹‹ ጠብቅ ይመጣሉ›› አለችው የእጅ ቦርሳዋን እየከፈተች። ረጃጅም እግሮችዋ በጠረጴዛው ስር ይታያሉ። ቀይ ቀለም የተቀቡት አውራ ጣቶችዋ የሚያሾፉበት መሰለው። እንደገና ዓይን ለዓይን ተጋጩ።

በማንኩሳ ማተሚያ ቤት ታተመ
0113 691933

ዋጋ 200 ብር
ሁለት መቶ ብር ብቻ